www.abyssinialaw.com

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች



ቅጽ-20

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች ቅጽ-20

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ድረ-ገጽ፡- www.fsc.gov.et
ስልክ፡- +251 111 55 34 00
ፋክስ፡- +251 111 56 55 83
የመ.ሣ.ቁ.፡- 6166
ነጻ የስልክ ጥሪ፡- 992

www.abyssinialaw.com

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

# ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

## ቅጽ-20

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ግንቦት 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

www.abyssinialaw.com



## *የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት*

*በተሻሻለው የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ሥር የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሠበር ችሎት የሚሰጠው የህግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኙ የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል ተብሎ መደንገጉ ፍርድ ቤቶች የሠበር ችሎቱ የሰጠውን የህግ ትርጉም ተከትለው በመስራት ለተመሳሳይ ጉዳዮች ተመሳሳይ ውሳኔዎች እንዲሰጡ ለማስቻል ነው፡፡ በሀገሪቱ ያሉ ፍርድ ቤቶች ለተመሳሳይ ጉዳዮች ተመሳሳይ ውሳኔዎችን መስጠት መቻላቸው የዳኝነት አገልግሎቱ ተገማች እንዲሆን ከማስቻሉም በላይ ባለጉዳዮችን ካልተገባ ወጭና ከእንግልት ሊያድናቸው እንደሚችልም ይታመናል፡፡ ይህን እውን ለማድረግ በተቻለ መጠን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች በአግባቡ ታትመው በመላው ሀገሪቱ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶችና ለተለያዩ አካላት እንዲሁም ለህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሰራጩ ይደረጋል፡፡*

*በሌላ በኩል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች በጥራዝ መልኩ መዘጋጀታቸው ጥናትና ምርምር ለሚያካሄዱ የህግ ተመራማሪዎች፤ ለህግ ባለሙያዎች ለጠበቆች፣ ለምሁራንና በጠቅላላው ለህብረተሰቡ ውሳኔዎችን ተደራሽ ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑም ስለ ታመነበት ጭምር ነው፡፡*

***ዳኜ መላኩ***

***የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት***

www.abyssinialaw.com

## *የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ /ቅፅ 20/*

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **አሠሪና ሠራተኛ** | | | | | 1 |
| 1. | የአሰሪውን ትእዛዝ አልፈፀመም ተብሎ የስራ ስንብት ያደረገ አሰሪ ትእዛዙ ያለመፈጸሙን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>*አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13* | 119639 | የደብረዘይት ሄልሜክስ ቁራዎች ድርጅት<br>እና<br>እነ አየለ ዲባባ<br>/ሦስት ሰዎች/ | 30/5/2008 ዓ.ም | 2 |
| 2. | በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ በግልጽ በተቀመጡ ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር አንዲት ሰፍሰጡር ሴት ከወሊድ በኂላ አራት ወራት ውስጥ ከስራ ያለመባረር መብት ያላት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 25፣27፣29/3/ እና 87/5//6/ | 121063 | መ/ርት ሙሉነሽ መለሰ<br>እና<br>ዋሊያ አጠቃላይ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት | 24/06/2008 ዓ/ም | 5 |
| 3. | የግል አሰሪና ሠራተኛ (ስራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ) እና በሰራተኛ የሚነሳ ማንኛውም የስራ ክርክር የሚፈታው በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ስለመሆኑ፣<br>*አዋጅ ቁጥር 632/2001 አንቀጽ 4* | 98771 | እነ አቶ ታረቀኝ መኮንን<br>እና<br>አሲ. ሚፍታህ ኤጀንሲ | 24/8/2008 ዓ.ም | 9 |
| 4. | አንድን ሰራተኛ በስራ ላይ አልተገኘም ማለት የሚቻለው የስራ | 117862 | ጎል ኢትዩጵያ | 20/10/2008 ዓ.ም | 13 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ውሉ ፀንቶ እስከቆየበት ጊዜ ድረስ ብቻ ስለመሆኑ፡- *አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 27 (1) (ለ)* | | እና አቶ ዲዲሞ አጋቶ | | |
| 5. | የዝውውር ውሳኔን ተከትሎ ሰራተኛው ለአምስት የሰራ ቀናት የሰራ ቦታ ላይ አልተገኘም በማለት የማሰናበት እርምጃ ተገቢነት ለማጣራት ፤ ከነባራዊ ሁኔታ እንዲሁም ሰራተኛው የሰራ ቦታ ላይ መገኘት ከሚችልበት ሁኔታ አንፃር እንዲሁም ከቀረበው ማስረጃ አንፃር በመመዘን የሚወሰን ስለመሆኑ ፤ | 125004 | አዲስ ፋና ጠቅላላ ሽቀጣ ሽቀጥ እና ሆቴሎች ንግድ አ.ማ እና አቶ ሊቁ ብርሃነ | 22/10/2008 ዓ.ም | 17 |
| 6. | አሰሪ የተጠየቀን የስራ ስንብት ክፍያን በተመለከተ አጠቃላይ ተቃውሞ አቀርቦበት እያለ ፤ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ስሌቱን በተመለከተ አልተቃወመም በሚል በመተርጎም በሰራተኛው የተጠየቀን የስንብት ክፍያ ዳኝነት ሙሉ በሙሉ በመወሰን የሚሰጥ ዳኝነት ተገቢ ስላለመሆኑ ፤ፍ/ቤቱ በሕጉ አግባብ አስልቶ መጠኑን ሊወሰን የሚገባ ሰለመሆኑ ፤ *አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 40 (1 እና 2)* | 119694 | ንብ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ እና አቶ አለማየሁ ሁሉቃ | 27/11/ 2008ዓ.ም | 22 |
| 7. | ለጡረታ አፈፃፀም ተብሎ የመንግስት ሰራተኛን የግል ማህደር በኤጀንሲው እንዲላክ ተጠይቆ፤ሰራተኛው የመንግስት | 127154 | ኢትዩጵያ እህል ንግድ ድርጅት | 23/1/ 2009 ዓ.ም | 28 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ንብረት አልመለሰም በማለት ማህደር አልክም ማለት ህጋዊ ስላለመሆኑ ፤<br>የጡረታ አበል የማግኘት መብት የዕዳ መያዣ ሊደረግ ወይም በውርስ ወይም በማናቸውም መንገድ ሊተላለፍ የማይችል ስለመሆኑ<br>*አዋጅ ቁጥር 345 /97 አንቀፅ 47 (2) ፣ 44 እና 55 (2)* | | እና<br>አቶ ካሳሁን በዛብህ | | |
| 8. | አሰሪ ሰራተኞችን ከማሰናበቱ በፊት በትክክል አጣርቶ እርምጃ መውሰድ ሲገባው ፤ክርክር ከተጀመረ በኃላ ከስንብት ደብዳቤ ሌላ ደብዳቤ መፃፉ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁን ዓላማ እና መንፈስ የማያሟላ ስለመሆኑ ፤<br>*የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 91 (1) (3)*<br>*አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 (1) (ሸ) ( ቀ)* | 125778 | ሲው ኢንፍራስትራክቸር<br>እና<br>እነ አቶ መሳይ ወ/ገብርኤል<br>( አራት ሰዎች) | 23/1/ 2009 ዓ.ም | 32 |
| 9. | አንድን ሰራተኛ የሥራ መሪ ነው ሊባልበት ስለሚቻልበት አግባብ፡-<br>የሥራ መሪን በተመለከተ ክርክር ሲነሳ ተግባራዊ ሊሆኑ ስለሚገባቸው ህጎች፡-<br>የስራ መሪ የሚያቀርባቸው የመብት ጥያቄዎች ቀሪ ስለሚደረጉበት የይርጋ ጊዜ | 116038 | ፍራውን ኮ/ህንፃ ተቋራጭ<br>እና<br>እነ አቶ ካህሳይ ገ/እግዚአብሄር<br>(ሁለት ሰዎች) | 21/2 /2009 ዓ.ም | 37 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | *አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀፅ 2(!)፣ 3(2(ሐ)*<br>*የፍ/ሕ/ቁ.1677(1)፣1845፣2512፣2593* | | | | |
| 10. | ተዋዋይ ወገኖች በስራ ውል ስምምነታቸው በግልፅ ኮሚሽንን የደሞዝ አካል አድርገው እስከተዋዋሉ ድረስ ቅራኔ በተነሳ ሰዓት ኮሚሽንን እንደ ደመወዝ አይደለም በማለት መውሰድ ተገቢ ስላለመሆኑ<br>*አዋጅ ቁ.377/1996 አንቀፅ 53(2(መ)* | 117070 | ወ/ሮ ወይንሸት በቀለ<br>እና<br>ኦሎምፒያኮስ ሄኔኒክ አትሌቲክስ ማህበር (ግሪክ ክለብ) | 22/2/ 2009 ዓ.ም | 46 |
| ***የፍትሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት*** | | | | | 49 |
| 11. | ቼክን በተመለከተ በአጭር ስነ ስርዓት /Summary proceding/ ዳኝነት ታይቶ እንዲወሰን ክስ በቀረበበት ወቅት ተከሳሽ መከላከያውን እንዲያቀርብ ጥያቄ አቅርቦ ተፈቅዶለት መልስ እንዲያቀርብ ተደርጎ መልስና በሕግ አግባብ ምስክር ቆጥሮ እያለ ምስክሮች ሳይሰሙ ይኼው ታልፎ የቼክ ባሕርይን ብቻ መሰረት ተደርጎ ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ ትክክል ስላለመሆኑ<br>*የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 285/1/ 286 እና 291*<br>*የን/ሕ/ቁ. አንቀጽ 717* | 103478 | አቶ ኤልያስ ተፈራ<br>እና<br>አንዋር ሁሴን | 18/4/ 2008 ዓ.ም | 50 |
| 12. | አንድ ከሳሽ ክሱን የመሰረተው በብዙ ጉዳዮች ወይም በተለያዩ | 109054 | አቶ ነገሠ ግዛው | 27/7/2008 ዓ.ም | 55 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ነገሮች ላይ የሆነ እንደሆነ በተለይ በእያንዳንዱ ጉዳይ እንዲታይ የሚጠይቀውን ዳኝነት መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 224(2) | | እና አቶ ሐረጸ ቤኛ | | |
| 13. | አንድ በፍርድ ቤት የተወከለን ሰው በችሎት ተገቢ ያልሆነ ስነ ምግባር አሳይቷል በማለት ፍ/ቤት የውክልና ስልጣንን መሻር የማይቻል ስለመሆኑ፣ *ፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 58* | 102141 | አቶ አደን የሱፍታረ እና አቶአህመድ አብዱላሂ ተረቢ | 29/7/2008 ዓ.ም | 59 |
| 14. | ተከሳሽ ከሳሽ ያቀረበውን ክስ አምኖ ነገር ግን ሕግ ወይም ሌላ ፍሬ ነገር በመጥቀስ የቀረበብኝ ክስ ዋጋ የለዉም ብሎ የሚከራከር ከሆነ ሙግቱን የሚጀምረው ተከሳሽ ስለመሆኑ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 258/1/* | 114816 | ዳዊት በለጠ የጠጠር አምራች ድርጅት እና አብዱልራዛቅ | 26/10/2008 ዓ.ም | 63 |
| 15. | የይግባኝ መዝገብ በድሀ ደንብ እንዲከፈት የሚቀርብ ጥያቄን ለመወሰን አመልካች ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ( ንብረት በመታገዱ ፣ገንዘብ ማንቀሳቀስ የማይችል እና የሚከፍለው ገንዘብ የሌለ እንደሆነ) ለዳኝነት የሚከፈለው ገንዘብ ያለው ወይም የሌለው መሆኑ መጣራት እና መረጋገጥ ያለበት ሰለመሆኑ፤ *የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 567 ፣ፍ/ሕ/ቁ 1793/ለ/ እና ሕገመንግስት* | 117754 | አክሰስ ሪል እስቴት እና ጋቢኢንቨስትመንትኃ/የተ/የ ግ/ማ | 8/10/ 2008 ዓ.ም | 66 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | *37(1)* | | | | |
| 16. | መብቴን የሚነካ ፍርድ ተሰጥቷል በሚል የሚቀርብ የፍርድ መቃወሚያን ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይቅርብ በማለት የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢ ስላለመሆኑ፤<br>መቃወሚያ መቅረብ ያለበት ክርክሩን ሰምቶ ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት ስለመሆኑ<br>*ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418* | 115892 | ወ/ሮ መሰረት አንዳርጌ<br>እና<br>እነ አቶ ይበልጣል ስመኝ<br>( ሦስት ሰዎች) | 11/11/2008 ዓ.ም | 70 |
| 17. | በክርክር ሂደት ላይ ፤ የቀረቡት የባለሙያ አስተያየቶች ተቃራኒ ይዘት ካላቸው ፤ ግልፅ መሰፈረት እና ምክንያት በሌለበት አንደኛውን ተቀብሎ ሌላውን ውድቅ ማደረግ ተገቢ ስላለመሆኑ፤<br>*ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 250 እና 136(1)* | 115963 | አቶ ኤልያስታምራት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አስቴር መከተ<br>(ሁለት ሰዎች) | 8/11/ 2008 ዓ.ም | 75 |
| 18. | የሰበር አቤቱታ በህጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሳይቀርብ ጊዜው ካለፈ የሰበር አቤቱታ ከመቅረቡ በፊት የይግባኝ ማስፈቅጃ ማመልከቻ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ፤<br>አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 22(4) ፣ ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 324 | 101277 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>ሚ/ር አቤንቻንድ<br>ፓፓትላል | 23/1/ 2009 ዓ.ም | 81 |
| 19. | በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ በግልፅ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ | 121387 | አፍሮ ፅዩን | 26/1 /2009 ዓ.ም | 84 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ይቆጠራል የሚለው ድንጋጌ በልዩ ስርዓት( በአጭር ሁኔታ) ለሚመሩ ክርክሮች ላይ ጭምር ለቀረበ መልስ ላይም ተፈፃሚ የሚሆን ስለመሆኑ፤<br>*ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 284 (ሀ)* | | ኮ/ጋ/የተ/የግ/ማህ<br>እና<br>እነ አቶ ያሬድ ተሾመ<br>( ሦስት ሰዎች ) | | |
| 20. | ከሳሽ ያቀረበው ክስ እና የክሱ ዝርዝር ይዘት የተለያየ ሆኖ የተገኘ ከሆነ ፤ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ በማዘዝ ፤የክርክሩን ሂደት መምራት ያለበት ስለመሆኑ፤<br>*ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 90(1)* | 122249 | አቶ በላይ አየለ<br>እና<br>በአ/አ/ከ/አ/ከ/ፅ/ቤት አዲስ ዙ ፓርክ ማዕከል | 26/1 /2009 ዓ.ም | 87 |
| 21. | አንድ የዳኝነት አካል የሥረ - ነገር ስልጣን ባይኖረውም እንኳን የሰጠው ውሳኔ ሥርዓቱን ተከትሎ እስካልተሻረ ድረስ የፀናና የመጨረሻ በመሆኑ አዲስ ክስ በተመሳሳይ ጉዳይ ማቅረብ ተገቢ ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5/1/ እና 212 | 105677 | እነ ወ/ሮ ጥሩነሽ ገ/ወልድ /ስድስት ሰዎች/<br>እና<br>እነ አቶ መኮንን ገ/ወልድ/ ሶስት ሰዎች/ | 30/1/2009 ዓ.ም | 90 |
| 22. | በክርክር ወቅት ጣልቃ እንዲገባ የተፈቀደለት ተከራካሪ በመጀመሪያ ሊያቀርብ የሚፈልገውን መቃወሚያ እንዳያቀርብ የሚከለክለው ህግ የሌለ ስለመሆኑ፣<br>( የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41 ፣234/1/ | 108647 | ወ/ሮ ወርቂቱ ገመዳ<br>እና<br>ወ/ሮ ደመቀች ብርሃኑ | 15/3/2009 ዓ.ም | 96 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 23. | ሒሳብ አስተሣሣቢ የመመደብ ሥልጣን ያለው ዋናው ጉዳይ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለውና የግራ ቀኙን ክርክር የሰጠው ፍ/ቤት ስለመሆኑ፣<br>አንድን ጉዳይ ለመወሰን የቀረቡት /የተሰጡት/ የሙያ አስተያየቶች ተቃራኒ ይዘት ባለበት ሁኔታ የአንድን ባለሙያ አስተያየት ብቻ በመቀበል መወሰን ተገቢ ስላለመሆኑ፣<br>( የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 136፣145/1/፣246፣248 እና 264 | 105956 | አምሣሉ ወርቁ ኮንስትራክሽን<br>እና<br>ትድሃር ኤክስካቬሽን ACዝ ሙቪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | 19/3/2009 ዓ.ም | 101 |
| 24. | ፍ/ቤቶች እውነትን ለማውጣት ማስረጃ አስቀርበው መስማት አለባቸው ሲባል በቀረበው ማስረጃ እውነት እስከተረጋገጠ ድረስ የግድ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የሚገደድበት ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ፣<br>የፍትሐብሔር ክርክር ማስረጃ የሚሰማውና ፍሬ ነገር እንዲጣራ የሚደረገው በማስረጃ የሚገኘው ፍሬ ለዳኝነት አሰጣጡ እጅጉን አስፈላጊና የግድ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ፣ | 109563 | እነ አሰፋ መንግስቱ ኮንስትራክሽን ኪራይ /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማህበር | 26/3/2009 ዓ.ም | 112 |
| 25. | ማናቸውም ተከራካሪ ወገን በመከላከያ መልሱ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል የሚያምን መሆኑን የገለጸ እንደሆነ ወይም በሚደረግ ምርመራ የእምነት ቃሉን የሰጠ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በታመነው | 107217 | የዳንግላ ወረዳ ውሃ ሀብት ልማት ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ሙሉጌታ ገበየሁ | 29/3/2009 ዓ.ም | 119 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ነገር ላይ ብቻ ፍርድ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 83 ፣234/1/ /ሠ/ ፣ 241 እና 242 | | | | |
| 26. | ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ቤት የሚከራከሩበትን ጉዳይ በእርቅ መጨረስ የሚችሉና የእርቅ ውሉን ጉዳዩን ለሚያየው ፍርድ ቤት አቅርበው ማፀደቅ እንደሚችሉ ፍርድ ቤት ቀርቦ የፀደቀ የእርቅ ውል ሥምምነት በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ያህል አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ያለው ከመሆኑ ባሻገር በዚህ እርቅ ውል ተካፋይ ያልሆነ መብቴ ተነክቷል የሚል ወገን የፍርድ መቃወሚያ ሊያቀርብ የሚችል ሥለመሆኑ<br>*የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.276፣277(1) እና 358* | 114623 | እነ ሃጂ አባመጫ<br>(ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የኦሮሚያ ክልል ደንና ዱር አራዊት ድርጅት<br>(ሁለት ሰዎች) | 22/06/2009 ዓ.ም | 124 |
| ንብረት | | | | | 128 |
| 27. | በመንግስት የተወረሰን ቤት የባለቤትነት መብት ከሌለው ሰው/አካል/ መግዛት የማይንቀሳቀስ ንብረትን በቅን ልቦና ባለሀብትነትን የሚያጎናጽፍ ስላለመሆኑ፣<br>*አዋጅ ቁጥር 47/67* | 112190 | አይከል ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት<br>እና<br>ሼክ ሸምሱ መሀመድ | 28/7/ 2008 ዓ.ም | 129 |
| 28. | ማንኛውም የቀበሌ መኖሪያ ቤት የተከራየ ሰው የራሱ ቤት | 123056 | ወ/ሮ ትሁኔ አዳኔ | 24/10/2008 ዓ.ም | 133 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ከገነባ ወይም የጋራ ሕንጻ ቤት ከገዛ ወይም የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲን ቤት ካገኘ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ቤቱን የለቀቀ ከሆነ ቤቱን ባለበት ሁኔታ ለአስተዳደሩ ማስረከብ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>*የአ.አ.ከ.አስተዳደር ባወጣው የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁ. 3/2007 አንቀጽ 42/ሀ* | | እና<br>በጉ/ክ/ከ/ወ/7/ኮ/ቤ/አ/ል/ፅ/ቤት | | |
| 29. | ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው አካል ፈቃድ ሳያገኝ በህጋዊነት ከያዘው ይዞታ ጎን ያለን የከተማ ቦታ አስፋፍቶ መከለልና መጠቀም የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>*አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 5(2)* | 111311 | ን/ስ/ስ/ላ/ክ/ከ/ወ ወረዳ 03<br>እና<br>አቶ ሲሳይ ተስፋዬ | 23/7/2008 ዓ.ም | 136 |
| 30. | የከተማ ቦታ የሊዝ ይዞታ በሚቋረጥበት ወቅት /ሲቋረጥ / ባለይዞታው እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ በቦታው ላይ ያሰረፈውን ንብረት በማንሳት ቦታውን አግባብ ላለው አካል መልሶ ማስረከብ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>*አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 26(5) እና (6)* | 107777 | የሱሉልታ ከ/አስተዳደር<br>እና<br>አቶ ደባልቄ ደምሴ | 28/7/2008 ዓ.ም | 140 |
| 31. | በትግራይ ክልል በገጠር መሬት ላይ የሚደረግ ልውውጥ | 106436 | አቶ ተክሌ ይይ ተስፋይ | 25/8/2008 ዓ.ም | 145 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሕጋዊ ነው የሚባለው በውልና ማስረጃ ፀድቆ የወረዳው የመሬት ዴስክ አውቆ በቅጽ ተሞልቶ የተለዋወጡ ከሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣ *የትግራይ የመሬት አዋጅ ቁጥር 239/06 እና ደንብ ቁጥር 48/2000* | | እና ወ/ሮ ንግስቲ ገ/መድህን | | |
| 32. | የመሬት የይዞታ መብት ያለው ሰው ፤በይዞታው ላይ የአላባ የመጠቀም መብት መስጠቱ በሌላ ጊዜ ይዞታውን በስጦታ የማስተላለፍ መብቱን የማይገድብ ስለመሆኑ ፤ *የአ/ብ/ክ/መ/መሬት አጠቃቀም አዋጁ 133/98 አንቀፅ 1፣7* | 119557 | አቶ ማናለው ተካ እና ወ/ሮ እቴነሽ ተካ | 19/11/2008 ዓ.ም | 148 |
| 33. | የገጠር መሬት የይዞታ ባለመብት የሆነ በሙሉ ፍቃድ የሰጦታ ውል አድርጎ እንዲሁም ውሉ በሚመለከተው አካል ከተመዘገበ በኃላ ፤በውሉ ላይ ያልተመዘገበ ቅድመ ሁኔታ በመዘርዘር ውሉ ፈራሽ እንዲሆን በማለት የሚቀርብ ጥያቄ ውልንም ህግንም የሚቃረን መሆኑ *የአ/ብ/ክ/መ አዋጅ 133/98 አንቀፅ 15 እና 17 ፤ የአ/ብ/ክ/መ ደንብ ቁጥር 51/99 እና የፍ/ሕ/ቁ 2436 ፣2437 ፣2438 ፣2439* | 118191 | አቶ ድጋፌ ክፍሌ እና አቶ ጎሣ ገድል | 24/1/ 2009 ዓ.ም | 152 |
| 34. | የማይንቀሳቀስ ንብረት የሸጠ ሰው ንብረቱን ከሌሎች ሰዎች | 100395 | ወ/ሮ አማረች ማሬ | 29/3/2009 ዓ.ም | 157 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቁጥጥር ይዞታ ሥር ነፃ አድርጎ ፣የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ባለሀብትነት ለማስተላለፍ የሚያስችሉ አስፈላጊ ሰነዶች ለገዢ የማስረከብና የማይንቀሳቀሰዉን ንብረት የማይነካ የባለሀብትነት መብት ለገዥ ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆነ ተግባራትን የመፈጸም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875፣ 2879(1)፣2281 | | እና<br>እነ ወ/ሮ ሜሪ ታደሰ<br>( ሦስት ሰዎች) | | |
| *የዳኝነት ስልጣን* | | | | | 164 |
| 35. | የከተማ ቦታን በሊዝ በመጫረት ጨረታውን በማሸነፍ የሊዝ ውል የተፈጸመ እንደሆነ ይህን የውል ግንኙነት ለመዳኘት የሚችለው ፍርድ ቤት ስለመሆኑ፣<br>*የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004*<br>*የፍ/ሔር/ሕ/ቁ. 1731፣1808/2/* | 117819 | የወላይታ ዞን የቦሌ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ዐ/ሕግ<br>እና<br>ወ/ሮ ታደለች ዲባራ | 15/7/2008 ዓ.ም | 165 |
| 36. | በኦሮሚያ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚነሱ የከተማ ቦታን ከማስለቀቅና ምትክ ቦታ እና ካሣን ከመክፈል አንጻር የሚነሱ የመብት ጥያቄዎችን በመጀመሪያ ደረጃ የማየት ስልጣኑ በከተማው አስተዳደር የተዋቀረው አካል ስለመሆኑ፣<br>*የኦሮሚያ ክልል የመሬት ሊዝ አዋጅ ቁ. 721/2004 አንቀጽ* | 114622 | አቶ አወል አማን<br>(ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ አሳለፈች እንዳግቤ<br>/ሦስት ሰዎች/ | 9/9/2008 ዓ.ም | 169 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | *ቁ. 26፣27፣28፣29 እና 30*<br>*አዋጁን ለማስፈጸም የወጣው ደንብ ቁጥር 155/2005 አንቀጽ 26፣55 እና 56* | | | | |
| 37. | የአዲስ አበባ ከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የቤት ባለቤትነት ክርክርን አጣርቶ የመወሰን ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ፣ | 110901 | አቶ ተክለስላሴ ገላን<br>እና<br>ልደታ/ክ/ከ/የመ/ል/ከተማ ልማት ጽ/ቤት | 25/9/2008 ዓ.ም | 174 |
| 38. | ከፊል የዳኝነት ሰልጣን ላለው አካል በፍሬ ነገር ደረጃ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑ በግልፅ ተቀምጦ እያለ፤ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በሕግ አተረጎጎም ረገድ ብቻ የተሰጠውን ስልጣን በማለፍ ማስረጃን በመመዘን በፍሬ ነገር ላይ የሚሰጠው ድምዳሜ ሰርዓቱን የተከተለ ስላለመሆኑ ፤<br>*የአ/ብ/ክ/መ/ መገናኛ ብዙሀን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ 200/2005 አንቀፅ 13(2)* | 119704 | አማራ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት<br>እና<br>አቶ ዳንኤል ከፈለ | 22/11/ 2008ዓ.ም | 178 |
| 39. | የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተደራጀባቸውና ባልተደራጀባቸው | 116154 | እነ አቶ ሚሪንዳ ዋሲሁን | 13/03/2009 ዓ/ም | 181 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ክልሎች ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሚነሱ ይግባኞች መቅረብ ያለባቸው ከፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጋር አቻ ስልጣን ላላቸው በየክልሉ ላሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 154 የዒ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/2/ አዋጅ ቁ. 322/95 | | ( አሥር ሰዎች)<br>እና<br>ኢትዩ ቴሌኮም | | |
| ጉሙሩክ | | | | | 185 |
| 40. | ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣ ህግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣው ህግ ስለመሆኑ፣<br>በአዲሱ የጉሙሩክ አዋጅ ቁ. 859/2006 አንቀጽ 182 ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው ክርክር ካላስነሳው ጉዳይ በሌሎች ህጎች የተመለከቱት ድንጋጌዎች በማይነካ ሁኔታ ስለመሆኑ፣<br>*የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 22/2/ የኢፌድሪ የወንጀል ህግ ጠቅላላ ክፍል በአንቀጽ 6* | 101462 | አቶ ነጂብ አዳም አቡባክር<br>እና<br>የኢትዮ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | 20/11/2009 ዓ.ም | 186 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 41. | የተሻረው ህግ ይሰራ በነበረበት ጊዜ የተፈጸመ ወንጀል ሲኖርና በዚህ ህግ ግን እንደወንጀል ያልተቆጠረ ሲሆን ሊያስከስስም ሆነ ሊያስቀጣ አይችልም ፤ ክሱም ተጀምሮ እንደሆነ የሚቋረጥ ስለመሆኑ፣<br>*የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 5/3/*<br>*አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 99፣ አዋጅ ቁ. 859/2006* | 111960 | ወ/ሮ አባይነሽ ፈቀደ /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>የሺ ኃይሌ | 06/3/2009 ዓ.ም | 192 |
| ውል | | | | | 196 |
| 42. | የዋስትና ውል ግዴታ ሰራተኛው ተቀጥሮ በሚያገለግልበት ወቅት ለሚደርሰው የገንዘብና የንብረት መጥፋትና መጉደል ተጠያቂ የሚያደረግ ስለመሆኑ፣<br>*የፍ/ሔር/ሕ/ቁ. 1933/1/ 1897* | 109392 | አቶ ሶፎኒያስ ኃ/ማርያም<br>እና<br>ካልዲስ ኮፊ ኃ/የተ/የግ/ማ | 28/7/2008 ዓ.ም | 197 |
| 43. | በተሸጠ ነገር ላይ የተገኘው ጉድለት ለውል ማፍረሻ ምክንያት ሊሆን ስለማይችልበት ምክንያት<br>*የፍ/ሕ/ቁ.2344(2) ፣2289(1)* | 107542 | ኦሻምትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>ኖንግፋን ሞተርስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | 14/8/2008 ዓ.ም | 201 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 44. | የስጦታ ዉል ውስጥ ተቃራኒ የሚሆን ቃል ከሌለ በቀር ስጦታ ከተደረገ በኋላ ልጅ መወለዱ ስጦታውን ለመሻር ምክንያት የማይሆን ስለመሆኑ፣ *ፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2450* | 115981 | እነ ሕጻን መይሙና ሀሰን /አምስት ሰዎች/ እና የሕጻን ሃሊሃ ሀሰን ሞግዚት | 26/09/2008 ዓ.ም | 207 |
| 45. | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ በይዞታው ስር የሚገኙትን የመንግስት ቤቶች ለማከራየት የሚያደርጋቸው ውሎች ያልተጠበቁ ምክንያቶች ካልተከሰቱ እና በተለይም ደግሞ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል በተከራይ ወገን በኩል ጥፋት ተፈጽሟል ካልተባለ በቀር በድርጅቱና በተከራዮች መካከል የሚደረጉ ውሎች በየዓመቱ እየታደሱ የሚቆዩ ስለመሆኑ፣ *የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6/1/* | 108638 | አቶ መህቡክ ከድር እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | 22/09/2008 ዓ.ም | 212 |
| 46. | በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2472 ላይ ገንዘብ ስለመከፈሉ ማስረጃን በተመለከተ የተደነገገው ፤ ከብድር ውጭ ለሆነ ግንኙነት ከተከፈለ ገንዘብ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ ፤ | 116961 | ወ/ሮ አስቴር አርአያ እና ወ/ሮ አወጣሽ መሐሪ | 19/11/ 2008ዓ.ም | 216 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 47. | በአንድ ሰነድ ላይ ያለን ፊርማ በቴክኒክ ምርመራ የማን እንደሆነ ለማረጋገጥ ባልተቻለ ጊዜ ፊርማው ሲፈረም የነበሩ ምስክሮችን ቃል በመስማትና በሌሎች ማስረጃዎች ፊርማው የማን እንደሆነ በመመዘን ማረጋገጥ የሚቻል ስለመሆኑ *የፍ/ሕ/ቁ. 2472(1)* | 114553 | አቶ ኤልያስ ስሜ ተሰማ እና ወ/ሮ ዘነበች ተመስገን ጫካ | 29/11/2008 ዓ.ም | 221 |
| 48. | አንድ ዕቃ ለመሸጥ /በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለማስረከብ/ የተዋዋለ ወገን ከዕርሱ አቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ውሉን መፈጸም ባልቻለ ጊዜ በቅድሚያ ለዚሁ ስራ የተቀበለውን ገንዘብ ከወሰደበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ከመመለስ ውጭ ውሉን ባለመፈጸሙ ምክንያት ለደረሰው ኪሳራ እንዲከፍል የማይገደድ ስለመሆኑ፣ ፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2356/1/ | 117036 | ፀጉ ብርሃን ትሬዲንግ ሀ/የተ/የግ/ማህበር እና ኮሎኔል ይትባረክ አማረ | 12/3/2009 ዓ.ም | 225 |
| 49. | የደረሰው ጉዳት አጓዥ በፈጸመው ተግባር ወይም ባደረገው ጉድለት እንዲሁም ይህ ተግባር አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጥር የሚችል መሆኑ እየታወቀ ሲሆን የኃላፊነት መጠኑ በህጉ ከተቀመጠው ውጪ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ፣ በልጅ ቀለብ አወሳሰን ረገድ ልንከተላቸው ስለሚገቡ መሰረታዊ መርሆች | 109061 | ወ/ሮ ነጋሪነት ሰለሞን የህጻን የአብስራ ቴዎድሮስ እና ስካይ ባስ ትራንስፖርት ሲስተም | 19/3/2009 ዓ.ም | 235 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | *( የን/ሕ/ቁ. 597፣ 599)*<br>*(የፍ/ሕ/ቁ. 2091፣ 2092*<br>*የኢ.ፌ.ድ.ሪ የቤተሰብ ህግ ቁ.. 213/92 አንቀጽ 197* | | | | |
| 50. | በአንድ ውል ውስጥ ውልን የሚያፈርሱ የስምምነት ቃሎች ተገልጸ ከተጻፈና የዚህም ስምምነት አፈጻጸም ጉዳይ ተሟልቶ ከተገኘ አንደኛው ተዋዋይ ውል ፈርሷል ሲል መግለጽ የሚችል ስለመሆኑ፣<br>*የፍ/ሕ/ቁ. 1786* | 105752 | አቶ አዲሱ ግርማሁን<br>የኮንስትራክሽን<br>ኢንተርፐራይዝ<br>እና<br>ጉዞ ኮንስትራክሽን<br>ኢንተርፐራይዝ | 26/3/2009 ዓ.ም | 246 |
| ***ከውል ውጭ ኃላፊነት*** | | | | | 251 |
| 51. | በአንድ ሰው ላይ ለደረሰ ጉዳት ኃላፊነትን በሚጥሉ የተለያዩ የህግ ድንጋጌዎች ምክንያት ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ለጉዳቱ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ በሚሆኑበት ጊዜ ኃላፊ ከሆኑት ሰዎች አንዱ ብቻ ጥፋት የሰራ እንደሆነ በመጨረሻ የተወሰነውን ዕዳ እርሱ እራሱ ብቻ የመቻል ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ፣<br>*ፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2157* | 117506 | የመ/ፈ/አቅርቦት ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ አዲሱ ገዛኸኝ | 8/9/2008 ዓ.ም | 252 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 52. | በመሬት ይዞታዬ ላይ ጉዳት ደርሶብኛል በማለት የሚቀርብ ክስ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ<br>*ፍ/ሕ/ቁ 2143* | 119563 | ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት<br>እና<br>አቶ ሐጂ ነገዋ | 26/1/ 2009 ዓ.ም | 255 |
| ***ቤተሰብ*** | | | | | 258 |
| 53. | እድሜው ያልደረሰ ልጅ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ የሚያስችል የሞግዚት ስልጣን ይሰጠኝ ጥያቄ ፍ/ቤቶች የህፃንን መብትና ድህንነት ቅድሚያ እንዲሰጠው በማደረግ ሲወሰኑ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የቀረበውን መሰረታዊ ጥያቄ እና አማራጭ መፍትሔ መኖሩን አለመኖሩን በማጣራት መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>*የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሰት 36 (2) ፣ ፍ/ብ/ሕ/ቁ 280 እና 289(1)*<br>*የቤተሰብ ህግ አዋጅ 213/1992 አንቀፅ 43* | 116950 | ወ/ሮ አስቴር በቀለ ጭጭ አይበሉ<br>እና<br>ተጠሪ የለም<br>( ተጠሪ የሌለበት ) | 23/7/ 2008 ዓ.ም | 259 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 54. | የጋብቻ የምስክር ወረቀት ተገቢውን ስርዓት ተከትሎ የተሰጠ አይደለም ተብሎ መሰረዝ ጋብቻ አልነበረም ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ፣ | 105694 | አቶ ተሾመ ዘርፌ<br>እና<br>ወ/ሮ ፈሰሰች ወንድማገኝ | 27/7/2008 ዓ.ም | 264 |
| 55. | የገጠር መሬት እንደሌላው ንብረት በመቁጠር ከቤተሰብ ህጉ አንጻር የሚታይ ስላለመሆኑ ፣<br>በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በአንድ ተጋቢ ስም ተዘጋጅቶ ከተሰጠ በኋላ ጋብቻ ቢፈፀምና ተጋቢዎቹ መሬቱን የጋራ ለማድረግ ሊስማሙ የሚችሉ ስለመሆኑ፣<br>*የአማራ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 133/1999 አንቀጽ 24/3/ ደንብ ቁ. 151/1999 አንቀጽ 20/6/* | 114279 | ወ/ሮ ደስታ ታከለ<br>እና<br>አቶ ፀጋ ታዲያስ | 30/7/2008 ዓ.ም | 268 |
| 56. | ባል ወይም ሚስት የጡረታ አበል ተጠቃሚ ሆነው ባሉበት ፍቺ ቢከሰት የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነው ባል ወይም ሚስት የጡረታ አበል ለባል ወይም ለሚስት ሊያካፍል የሚገባ ስላለመሆኑ ፣<br>*የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95 አንቀጽ 35* | 113002 | አቶ ባልቻ አበባ<br>እና<br>ወ/ዎ አልማዝ አሲ | 28/8/2008 ዓ.ም | 272 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 57. | በአባት በኩል ያለን መወለድ መቃወም የሚቻለው የልጁ አባት ነው ተብሎ በህግ ግምት የሚሰጠው ሰው እሱ የሞተ ወይም ችሎታ ያጣ እንደሆነ ከተወላጆቹ አንዱ የመካድ ክስ በማቅረብ መቃወም የሚችል ስለመሆኑ፣ *የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/1992/አንቀጽ 167፣174 እና 179* | 116119 | ወ/ሮ ሙሉ በዳዳ እና እነ ወ/ሮ ኩሪ በዳዳ | 22/9/2008 ዓ.ም | 276 |
| 58. | የመጀመሪያ ሚስት በንብረትዋ ላይ ስምምነት ባላደረገችበት ፤ባል ሁለተኛ ሚስት ሲያገባ መቃወሚያ አላቀረበችም በማለት በንብረትዋ ላይም ስምምነት አድርጋለች በማለት በመደምደም ፤ሁለተኛ ሚስት እኩል እንድትካፈል በማለት የሚሰጥ ውሳኔ ህጋዊ ስላለመሆኑ | 120844 | አቶ ሃንደግባ ሸኩር እና ወ/ሮ አለምቴ ኢብራሒም | 27/8/ 2008 ዓ.ም | 279 |
| 59. | አንድ ሰው ህጋዊ ባለይዞታው ሳይቃወም በሌላ ሰው ይዞታ ላይ ቤት ወይም ንብረት ያፈራ እንደሆነ የዚሁ ቤት/ ንብረት/ ባለመብት የሚሆን ስለመሆኑ፣ የፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 1179(1)(2) ከኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40 አኳያ ሲታይ ስለሚችልበት አግባብ | 105125 | አቶ አህመድ ዑመር እና እነ አቶ ተስፋዬ አብርሃ /ሁለት ሰዎች/ | 05/3/2009 ዓ.ም | 284 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| ውርስ | | | | | 291 |
| 60. | በፍ/ብ/ህ/ቁ. 842/3/ መሰረት የተተኪ ወራሽነት ጥያቄ ተቀባይነት እንዲያገኝ ሊሟሉ ስለሚገባቸው ጉዳዮች፣ | 110040 | እነወ/ሮእሴተማርያምአክሎግ (ሶስት ሰዎች) እና የለም | 3/06/2008ዓ/ም | 292 |
| 61. | ለአንድ ውርስ ወራሽ የሆነ አንድ ሰው ውርስ ከተከፈተ በኋላ የሞተ እንደሆነ የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባያወጣም ለውርሱ አይገባም እስካልተባለ ድረስ የወራሽነት መብቶች ለእርሱ ወራሾች የሚተላለፍ ስለመሆኑ | 113529 | ወ/ሮ እቴቱ ከንባው (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ ቀለሚ ዓለማየሁ | 28/6/ 2008 ዓ.ም | 295 |
| 62. | አንድ ፍ/ቤት የውርስ ክርክርን አስመልክቶ የሚቀርብለትን የውርስ አጣሪዎች ቃለ- ጉባኤ ከማስጽደቁ በፊት በእርግጥ የውርስ ሀብት የማጣራት ሕጋዊ ሂደት ተከትሎ የተካሄደ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ፣ *የፍ/ሕ/ቁ. 946፣950፣1062፣1079፣1080* | 108328 | ወ/ሮ ጫልቱ ዋቀዩ እና አቶ ፍቃዱ ዋቀዩ | 13/7/2008 ዓ.ም | 299 |
| 63. | ሚች በተወው ኑዛዜ መሰረት ውርሱ ሲጣራ እንዲሁም ኑዛዜው በፍ/ቤት ሲፀድቅ ተቃውሞ ሳያቀርብ ፤ ኑዛዜው ከፀደቀ በኃላ ኑዛዜው ይሻርልኝ በማለት የሚቀርብ ቅሬታ | 118105 | አቶ ተስፋዬ በቀለ እና እነ ወ/ሮ እሸቷ ጎሸዬ | 23/1/ 2009 ዓ.ም | 304 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ ፤<br>በሥር ፍ/ቤት ያልቀረበን ክርክር በይግባኝ ደረጃ ላይ ማቅረብ ተቀባይት የሌለው ሰለመሆኑ፤<br>*ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 329 (1)* | | ( 3 ሰዎች ) | | |
| 64. | አንድ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ወራሽነት መብቱን ለአካላ መጠን ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 15 ዓመት ባለው ጊዜ ውሰጥ የውርሱን ንብረት ለመጠየቅ በይርጋ የማይታገድበት ስለመሆኑ ፤<br>*ፍ/ብ/ሕ/ቁ 198 ፣ 1000(2)* | 120841 | ወ/ሮ ካባ ተካ<br>እና<br>አቶ ድሪባ ዳዲ | 23/1/ 2009 ዓ.ም | 308 |
| 65. | የተሰጠ ወራሽነት ማረጋገጫ የተሰረዘ ከሆነ ፤በይግባኝ ካልተሻረ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተሰጠ የውርስ ባለቤትነት ውሳኔ የሰረዝልኝ ጥያቄን ክርክር ስምቶ መወሰን ያለበት እንጂ በቀድሞ ያልተነሳ የይርጋ ተቃውሞ በመቀበል ጥያቄው ውድቅ ሊደረግ የማይገባ ሰለመሆኑ ፤ | 117435 | አቶ ተስፋዬ መኮንን<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሰብለ ለማ<br>( ሁለት ሰዎች) | 24/1/2009 ዓ.ም | 311 |
| 66. | የአንድ ሰው መብትና ግዴታ ለተወላጆቹ በውርስ ሊተላለፍ የሚችለው በሟቹ ምክንያት የሚቋረጡ ካልሆነ በቀር ሟቹ በሞተበት ቀን የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች ስለመሆናቸው፣ | 110680 | ወ/ሮ ፅጌሬዳ በቀለ<br>እና<br>ወ/ሮ ፍቅርተ በቀለ | 30/2/2009 ዓ.ም | 314 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | *የፍ/ሕ/ቁ. 826/2/*<br>ሟች የድርሻ መልቀቅ ውል ፈጽሞ ከዚያም ኑዛዜ ቢያደርግና ይኸው ኑዛዜ የድርሻ መልቀቁን ውል እስካልነካ ድረስ የውሉን ተፈጻሚነት ሊያስቀር የማይችል ወይም በአዲሱ ኑዛዜ ተተክቷል ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣<br>*የፍ/ሕ/ቁ. 900 እና 901* | | | | |
| ***ባንክና ኢንሹራንስ*** | | | | | 319 |
| 67. | የመድን ሥራ የሚሰሩ የመድን ኩባንያዎች በመድን ፖሊሲ ውስጥ ፖሊሲውን ተጠያቂነትን አያስከትልም ወይም በፖሊሲው መሰረት የካሳ ክፍያ ጥያቄ መነሻ የሆነው ክስተት ከደረሰ በኃላ የተወሰነ ድርጊት ከተፈፀመ ወይም ሳይፈፅም ከቀረ ኃላፊነቱ ቀሪ ይሆናል የሚል የውል ሁኔታ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>*አዋጅ ቁጥር 559/2000 በአንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1* | 88135 | ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ (አ.ማ)<br>እና<br>ወ/ሮ ነፃነት ሀቤቤ | 16/11/ 2005ዓ.ም | 320 |
| 68. | የመድን ውል ሽፋን ተጠቃሚ ለተገለገለበት ጊዜ በውሉ መሰረት የአርቦን ክፍያ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ ፤<br>የአርቦን ክፍያ በአንድ ወር ጊዜ ባለመጠየቁ ውሉ እንደተቋረጠ ስለሚቆጠር ክፍያውን የመጠየቅ መብት፤ | 117608 | ኢትዩጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>የኖሌ ካባ ወረዳ ጤና ጥበቃ ፅ/ቤት | 23/1/2008 ዓ.ም | 323 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ጉዳት ከደረሰም ኃላፊነት ለመውሰድ አይገደድም ከሚል መደምደሚያ ለብድር (ዱቤ) ላይ ለተመሰረተ ግንኙነት ተፈፃሚ ሰላለመሆኑ ፤<br>*የን/ሕ/ቁ 666 (4)* | | | | |
| 69. | ከአንድ በላይ የሆኑ ከሳሾች በጋራ በመሆን የህብረት ክስ ሊያቀርቡ ስለሚችልበት ሁኔታ<br>የመድን ሰጪውና የመድን ተቀባዩ ባደረጉት የመድን ሽፋን ውል ላይ የማግለያ ድንጋጌ በስምምነታቸው እስካሰፈሩ ድረስ ይኸው ሊጠበቅ የሚገባ ስለመሆኑ<br>*የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.35* | 104544 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>እነ አቶ ፀጋብ ገብሩ | 25/9/2008 ዓ.ም | 328 |
| 70. | ለአንድ ንብረት የሚከፈለው የኢንሹራንስ ገንዘብ ***የመያዣ መብት ላላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ይሰጣል*** የሚለው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንሹራንስ ሰጪው ላልተከፈለ የአርቦን ክፍያ ኢንሹራንስ ገቢውን ከመጠየቅ ውጪ የመያዣ መብት ያለውን አካል መጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ<br>የን/ሕ/ቁ.684(1) | 115763 | ብሔራዊ የኢትዮጲያ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ<br>እና<br>የኢትዮጲያ ንግድ ባንክ | 9/02/2009 ዓ.ም | 334 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **ወንጀል** | | | | | 337 |
| 71. | ፍ/ቤቶች የገንዘብ መቀጫን ሲወስኑ ከግምት እና ግንዛቤ ውስጥ ሊያስገቡዋቸው የሚገቡ የተከሳሽ ግላዊና የወንጀሉን ሁኔታዎችን በማገናዘብና ፤ በወንጀል ህጉ እና በቅጣት መመሪያው ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ መወሰን ያለባቸው እንጂ በደፈናው የገንዘብ መቀጮ መወሰን ተገቢ ስላለመሆኑ ፤<br>*የወ/ሕ/ቁ 88 /2/ እ 90 90 (2)፣ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2000* | 88542 | አቶ ቢሆነኝ ደምሴ<br>እና<br>የት/ብ/ክ/መ/ዓቃቤ ሕግ | 17/11/ 2005ዓ.ም | 338 |
| 72. | በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ሥርዓት ህግ መሰረት ክስ እንዲሻሻል መፍቀድ የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብትን የሚያጣብብ ነው የሚባል ስላለመሆኑ<br>*የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 188፣119 ኢፌድሪ ሕግ መንግስት አንቀጽ 20(1)* | 116405 | የአ/ሥ/ፀ/ኮሚሽን ዐቃቢ ሕግ<br>እና<br>አቶ ቴዎድሮስ አብርሃ ቀለቲ | 2/7/2008 ዓ.ም | 342 |
| 73. | የወንጀል ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ ይሁን በይግባኝ ደረጃ የሚመለከት ፍ/ቤት ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ የማስረጃውን አጭር መግለጫ፣ ማስረጃውን የተቀበለበትን እና | 113143 | የአ/ብ/ክ/መ/ፍትህ ቢሮ<br>እና<br>እነ አቶ ሕሊና ሀይሌ | 30/7/2008 ዓ.ም | 346 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ያልተቀበለበትን ምክንያቶች በፍርድ ላይ ማስፈር የሚገባው ስለመሆኑ፣<br>*የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 149/1/* | | (ሦስት ሰዎች) | | |
| 74. | ከአንድ የወንጀል ድርጊት በኃላ ተከታትሎ የተፈፀመ ድርጊት ፤አንድን ወንጀል ከግብ ለማድረስ ሲል ተከታትሎ የተደረገ ድርጊት ከቀድሞ አሳቡና ሊደርስበት ከቀደው ግብ ጋር የተያያዘ በዋናው ወንጀል የሚጠቃለል ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ የሚጣራበት አግባብ፤<br>ዓ/ሕግ ባስከፈተው የይግባኝ መዝገብ ላይ መ/ሰጭ ሕግን መሰረት አድርጎ የሚቀርበው ክርክር ተቀባይት ሊያጣ የማይገባው ስለመሆኑ፤<br>ወ/ሕ/ቁ 88(3) | 119159 | አቶ ደጀኔ መኮንን<br>እና<br>ፌ/ዓ/ሕግ | 20/11/2008 ዓ.ም | 353 |
| 75. | በእምነት ማጉደል ወንጀል ላይ የተቀመጠው ያልተገባ ጥቅም የማዋል ሓሳብ መርሕ ፤ ለከባድ እምነት ማጉደል ወንጀልም ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ ፤<br>*ወ/ሕ/ቁ 675(3) እና 676 (2) (ሀ)* | 118084 | አቶ ንጉሴ አሊ<br>እና<br>ፌ/ዓ/ሕግ | 21/11/2008 ዓ.ም | 359 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 76. | የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የቅጣት ውሳኔ መመሪያ መሰረት በማድረግ በማረም የሚጠው ውሳኔ ከተጠየቀ ዳኝነት ውጭ ተሰጥቷል የሚያስብል ስላለመሆኑ<br><br>*የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.2/2002 አንቀፅ 21(1) (ሀ) ፣ ወ/ሕ/ቁ 184(!0 (ለ) እና 194 (1) (ለ)* | 117877 | አቶ ማሰረሻ ገሰሱ<br>እና<br>የፌ/ዓ/ሕግ | 22/11/ 2008ዓ.ም | 363 |
| 77. | በሙከራ ደረጃ ለተፈፀመ ወንጀል ቅጣት እንደሚቀንስ በግልፅ በመመሪያ ቁ.2/2006 ላይ ባይደነገገም ነገር ግን በወንጀል ህጉ ቅጣትን በመሰለው እንዲያቀል ለፍ/ቤቱ በተፈቀደበት ሁኔታ መሰረት ቅጣትን አቅሎ ሊወሰን የሚችል ሰለመሆኑ ፤<br>*የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.2/2006 አንቀፅ 24 ፣*<br>*የወ/ሕ/ቁ 31 እና 180* | 119500 | ወ/ሮ ፀሀይ ውብዬ<br>እና<br>ፌ/ዓ/ሕግ | 22/11/ 2008ዓ.ም | 367 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 78. | ለሽብር ተግባር የሚያገለግል ንብረት ይዞ መገኘት ወንጀል ተፈፅሟል የሚባልበት አግባብ፤ በልዩ ሁኔታ በህግ የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሽ ከዞረባቸው ወንጀሎች ውጭ ፤ ዓ/ህግ የሚያቀርበውን ክስ የወንጀል ደንጋጌውን የሚያቋቁሙት የህጋዊ ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን የማስረዳት ሸክም የመወጣት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፤ *የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 ፣ የወ/ሕ/ቁ 23(2) ፤ የፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥ 652* | 102982 | ት/ብ/ክ/መ/ዓ/ሕግ እና አቶ ቡሽራ ያህያ | 26/11/ 2009ዓ.ም | 371 |
| 79. | የጉምሩክ ወንጀል ጋር በተያያዘ ፤ተከሳሽ በወንጀሉ ጥፋተኛ ባይባልም ንብረቱ የሚወረሰው ስለድርጊቱ አፈፃፀም ሁኔታ የሚያስረዳ አጥጋቢ ማስረጃ መቅረቡን ፍ/ቤቱ አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው ስለመሆኑ ፤ *አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 104 እና አዋጅ ቁጥር 859/2006* | 108550 | ኢ.ገ.ጉም.ባለስልጣን እና አቶ ልዑል ገዳሙ | 26/11/ 2009ዓ.ም | 375 |
| 80. | በአንድ የወንጀል ድርጊት በዋና ወንጀል አድራጊነት ወይም ግብረ አበርነት የተሳተፉ ተከሳሾች በግል ሁኔታዎች ሊኖር ከሚችለው ልዩነት በስተቀር ለተመሳሳይ የወንጀል አፈፃፀምና | 101003 | መክብብ ሞገስ እና የፌደራል ሥነ ምግባርና | 2/3/2009 ዓ.ም | 380 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የወንጀል ተሳትፎ ተመጣጣኝና ተመሳሳይ ቅጣት ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ<br>የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርዓት ቁጥር 196(1) ለሰበር ስርዓትም ተፈፃሚነት ያለውና ከተከሳሾች አንደኛው ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ የሆነበትና አያስቀርብም የተባለን ተከሳሽ ጭምር ሊያካትት የሚገባ ስለመሆኑ፡-<br>*የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 25፣22*<br>*የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፣4፣6*<br>*የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ 2/2006 አንቀፅ.3(2)* | | ፀረ ሙስና ኮምሽን | | |
| 81. | በወንጀል ተጠርጥሮ በህግ ከለላ ስር የሚገኝን ተጠርጣሪ በዋስትና የመለቀቅ ጥያቄ ባነሳ ጊዜ ተጠርጣሪው በከተማው ውስጥ ቋሚ የመኖሪያ /የመታወቂያ/ አድራሻ የለውም በማለት የዋስትና መብቱን መከልከል ህገ መንግስታዊ ስላለመሆኑ፣<br>*አንቀጽ 19/6/፣ 25 እና የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 69/ሀ/* | 131863 | መሐመድ እንድሪስ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ህዳር 8 ቀን 2009 ዓ.ም | 386 |
| 82. | ወንጀል ፈጽሞ የተከሰሰን ህፃን ደህንነት ሊጠበቅበት ሥለሚችልበት አግባብ<br>ለአዋቂ ጥፋተኞች የተደነገጉት መደበኛ ቅጣቶች ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ስለመሆኑ፡- | 118130 | ህጻን አይማሲ አገዘ<br>እና<br>የአማራ ክልል ዐ/ህግ | 30/3/2009 ዓ.ም | 391 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | *የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህግ መንግሥት አንቀጽ 36 (2)፣ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 3(1)፣ የአፍሪካ የህፃናት መብቶች ደኅንነት ቻርተር በአንቀጽ 4 (1)*<br>*የወንጀል ህግ አንቀጽ 53 (1)፣ 157፣ 168*<br>*የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ 171፣180* | | | | |
| 83. | የዋስትና መብት የሚነፈግባቸው ምክንያቶች ፍርድ ቤቶች ከተለያዩ ሁኔታዎች አንፃር እየተመለከቱ ሊመዝኗቸው የሚገባቸው ስለመሆኑ<br>አንድ ተከሣሽ የዋስትና መብት ቢከበርለት ግዴታውን የሚፈጽም የማይመስል ነው ተብሎ ግምት የሚወሰደው በቂና ህጋዊ ሊባሉ በሚችሉ ምክንያቶች ሊሆን እንደሚገባ፤ እንዲሁም ምክንያቶቹ በቂና ህጋዊ ናቸው የሚለው ጉዳይ ከተለያዩ ከባባዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባህርይ አንፃር ፍርድ ቤቱ ሊገነዘበው የሚችለው ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ ስለመሆኑ<br>*የወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 67(ሀ)* | 134228 | አቶ ስማቸው ከበደ<br>እና<br>የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ | 08/6/2009 ዓ.ም. | 398 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **አፈፃፀም** | | | | | 417 |
| 84. | የጋራ ወራሾች ሀብት በሆነ ንብረት ላይ ከእንዳንዱ የጋራ ባለሀብቶች ላይ ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያላቸው ሰዎች የባለድርሻውን ድርሻ ለመያዝ የሚችሉ ስለመሆኑ፣ በውርስ ሀብት እና የጋራ ወራሾች ያልተከፋፈሉ የውርስ ንብረት መካከል ስላለው ልዩነት *የፍ/ሕ/ቁ. 943፣1052፣1053፣1060 እና 1260* | 117735 | ህጻን ሣራ ማርቆስ እና እነ አቶ ስዩም አሰፋ(አምስት ሰዎች) | 28/07/2008 ዓ.ም. | 418 |
| 85. | አንድ ለፍርድ ማስፈጸሚያ በሐራጅ ይሸጥ የተባለን ንብረት በባለሙያው የተቀመጠውን የሐራጁ መነሻ ዋጋ አነሰ በማለት የሐራጅ ሽያጩ ተከናውኖ ውጤቱ ባልታወቀበት ሁኔታ የተጀመረው አፈጻጸም ቀሪ ይሁን ማለት ተገቢ ስላለመሆኑ፣ | 104943 | አቶ ይልማ ፈለቀ እና አቶ ጥበቡ ፈለቀ | 30/7/2008 ዓ.ም | 424 |
| ልዩ ልዩ | | | | | 428 |
| 86. | አንድ ጠበቃ በገባው ውል መሰረት እስከ መጨረሻው ድረስ ጉዳዩን ከተከታተለና ከሙያው አንጻር እውቀትና ጥረቱን ተጠቅሞ አገልግሎት ከሰጠ የተፈለገው ውጤት ባለመምጣቱ ብቻ የተሟላ አገልግሎት አልሰጠም ሊሰኝ የማይችል ስለመሆኑ እና በውሉ መሰረት የተስማሙበትን የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ቀሪ ሊያደርገው የማይችል ስለመሆኑ | 117907 | እነ ወ/ሮ ዘውዱ ፍቅሬ እና አቶ አበራ ጌታነህ | 22/9/2008 ዓ.ም | 429 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 87. | አንድ ጠበቃ ሕግን የማስከበር ፣ፍትህን የማስገኘትና ለፍትህ አስተዳደሩ የማገዝ ኃላፊነቱን በመተው ተቃራኒ ተግባራትን ሲያከናውን የቆየ መሆኑ ከተረጋገጠ የጥብቅና ፍቃዱ ሊሰረዝ የሚችል ስለመሆኑ<br>*የአማራ ክልል የጥብቅና ፍቃድ አሰጣጥ ምዝገባና የጠበቆች ሥነምግባር ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁ. 75/1994* | 114888 | አቶ አትሁነኝ አልማው<br>እና<br>የአ/ብ/ክ/ ፍትህ ቢሮ አቃቤ ህግ | 20/3/2008 ዓ.ም | 431 |
| 88. | በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ተይዞ የሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሁለት /ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በህብረት የያዙት እና ያልተከፋፈሉት በሆነ ጊዜ ከተከፋዮቹ አንዱ ንብረቱን ለመግዛት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኖ የቀረበ እንደሆነ የፍርድ ባለእዳው እንደቀረበ ተቆጥሮ የተቀዳሚነት መብት የሚሰጠው ስለመሆኑ፣<br>*የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 443፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 126/1/፣ 1386-1409* | 124618 | እነ ወ/ሮ ደብካ መሰለ<br>እና<br>ሣጅን ሀይሉ ሞገስ | 22/3/2009 ዓ.ም | 440 |

www.abyssinialaw.com

# አሠሪና ሠራተኛ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 119639

ጥር 30 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች:- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

**አመልካች** -የደብረዘይት ሄልሜክስ ቄራ ድርጅት- ተወካይ ፀጋ መርጋ ቀረቡ

**ተጠሪዎች** - 1.አየለ ዲባባ
2. ግርማ ፍቃዱ
3. መኮንን ሳህለ

} ጠበቃ አቦነሽ በላቸው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው የአሁን ተጠሪዎች በአድአ ወረዳ ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካች ላይ በመሠረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገርም ባጭሩ በድርጅቱ ውስጥ በቆዳ መግፈፍ እርድ ሥራ መደብ ተቀጥረው ሲሰሩ ቆይተው ተከሳሽ ድርጅት በቀን 14/06/2007 እና በ16/06/2007 በተጻፈ ደብዳቤ የስራ ዉሉን አቋርጦ ያላግባብ ከስራ ያሰናበታቸው በመሆኑ እና በደብዳቤ የተገለፁት ምክንያቶች የስራ አስኪያጅ ትዕዛዝን አለመቀበል፣ ስራን በመሰልቸት ማጓተት፣ በቀን 8 ሰዓት አለመስራት፣ እንዲሁም ከስጋ መጫን ጋር የተያያዘ ሲሆን አንቀበልም ያልንዉ የስራ አስኪያጅ ትዕዛዝ ባለመኖሩ፣ ስራን ያላጓተትን በመሆኑ፣ እንደ ህጉ ሙሉ የስራ ሰዓት አንሰራም ያላልን በመሆኑ እና የተቀጠርንበት የስጋ መግፈፍ ቢሆንም በተጨማሪ ስንታዘዝ ለስጋ መጫን የተቀጠሩትን አግዘን ስንጭን የነበረ በመሆኑ የተጠቀሱት ምክንያቶች በሙሉ ሆነ ተብለው ከስራ ለማሰናበት በተከሳሽ ድርጅት የተፈጠሩ በመሆኑ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ተብሎ ልዩ ልዩ ክፍያ ይከፈለን በማለት ጠይቀዋል፡፡ ተከሳሹ ለክሱ በሰጠው መልስ በቆዳ መግፈፍ ሥራ ላይ የተሰማሩ ቢሆንም እነሱ ስራ በሌላቸው ጊዜ ተከሳሽ ሌላ ስራ ማሰራት እንደሚችል በህጉ የተፈቀደ በመሆኑ፣ ሰራተኛው ምን አይነት ስራ ቢሰራ ትርፍ ያስገኛል የሚለውን ከግምት በማስገባት ሰራተኛውን ከተቀጠረበት ስራ ዉጪ ማሰራቱ ከስራ ስምሪት ስልጣን የመነጨ መብት በመሆኑ፣ ከሳሾች ታዘው ስራ አንሰራም ስላሉ ስጋ በጊዜ ሳይጫን ቀርቶ በምን አገባኝነት የተከሳሽ ንብረት እንዲጠፋ ስላደረጉ ተከሳሽ በአዋጅ

www.abyssinialaw.com

ቁጥር 377/1996 መሰረት ያለማስጠንቀቂያ አሰናብቷል፡፡ ነገር ግን ከሳሾች በ17/06/2007 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ወደ ስራ ለመመለስ ጠይቀዉ ተከሳሽ ወደ ስራ የመለሳቸው ቢሆንም በገዛ ፈቃዳቸው ስራውን ትተው ክሱን ያቀረቡ በመሆኑ መሰናበታቸው ህጋዊ ነው ይባል፤ ከዓመት ዕረፍት በቀር ሌሎች ክፍያዎችም ሊከፈሏቸው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተው የወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተከሳሽ ያቀረበው መከራከሪያ በራሱ ምስክሮች ጭምር አለመረጋገጡን በመጥቀስ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ብሎ ተከሳሽ በአዋጁ መሰረት ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ለከሳሾች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ውሳኔዉን በማሻሻል በአንቀፅ 38 መሰረት ክፍያ ለዘገየበት የተወሰነውን ቅጣት በመሻር ሌላው የውሳኔ ክፍል እንዲፀና ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጓል፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ህዳር 2/2008 ዓ.ም ያቀረቡት ማመልከቻ ተመርምሮ ለተጠሪዎች የተሰጠው ስራ ቀድሞ ሲሰሩት ከነበረው ስራ ጋር ተያያዥነት (ተመሳሳይነት) ያለው መሆን አለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች ተጣርቶ የመወሰን አለመወሰኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪዎችም ቀርበው ታህሳስ 14/2007 ዓ.ም በተጻፈ መልስ የተቀጠሩበት የቀዳ ገፋፊነት ስራ ከጭነት የስራ መደብ የተለየ መሆኑን እና ለሸክም ስራውም አልታዘዙም የተባለው ከእውነት የራቀ መሆኑን በመጥቀስ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡ አመልካቹ ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከላይ ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የሰበር አቤቱታ በቀረበበት ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪዎችን ከስራ ለማሰናበት ምክንያት ያደረገው የስራ ሰዓትን ተከትሎ በትጋት አለመስራትንና ከስራ መደባቸው ዉጭ የጭነት ስራ እንዲሰሩ ሲታዘዙ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ አክብረው አለመስራታቸውን ሲሆን ተጠሪዎች የተጠቀሱት ምክንያቶች ሆነ ተብሎ ለስንብት የተዘጋጁ ናቸው በማለት በመካድ ተከራክረዋል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀጽ (2) እና (7) እንደተመለከተው ማንኛውም ሠራተኛ በስራ ዉሉ እና በስራ ደንቡ መሰረት በአሰሪው የሚሰጠውን ትዕዛዝ የመፈፀም እንዲሁም የአዋጁን ድንጋጌዎች፤ የህብረት ስምምነትን፤ የስራ ደንብንና በህግ መሰረት የሚተላለፉ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡ አመልካች በዚህ የህጉ አግባብ ስራውን በመምራት ለስራው

www.abyssinialaw.com

ውጤታማነትና ቅልጥፍና የሚረዱ የተለያዩ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ሰራተኞችን ለስራ የማሰማራት ተግባር እንዲያከናውን የተፈቀደለት ቢሆንም ለስንብቱ የተጠቀሱት ምክንያቶች መኖራቸውን፤የሰጠው ትዕዛዝም አለመከበሩን የማስረዳት ግዴታ ይኖርበታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የተካደውን ፍሬ ነገር በማስረጃ ለማጣራትና ማስረጃንም ለመመዘን ስልጣኑ የተሰጠው የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃዎች ሰምቶ ተጠሪዎች ለስንብቱ የተጠቀሱትን ምክንያቶች አለመፈፀማቸውን አረጋግጫለሁ በማለት የስንብቱን ህገ ወጥነት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች የስራ ግዴታቸውን አለመወጣታቸዉን በማንሳት አመልካች ያቀረበውን ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ ስላላስረዳ የስራ ውሉን ማቋረጡ ህገወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ የአሰሪና ሰራተኛ የአዋጁን ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ ያገናዘበ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም በውሳኔው የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስላላገኘን ተከታዩን ውስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 41726 በ23/10/2007ዓ.ም. ተሻሽሎ የተሰጠው ፍርድ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 229654 በ04/02/2008 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ ፍርድ ቤት ህዳር 6/2008 ዓ.ም በዋለ ችሎት የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ብ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ/ 121063

የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች:- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች :- መ/ርት ሙሉነሽ መለሰ ወኪል ገ/አምላክ አበጋዝ ቀረቡ

ተጠሪ:- ዋሊያ አጠቃላይ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በአ/ብ/ክ/መንግስት ጎንደር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገርም ባጭሩ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በመምህርነት የስራ መደብ ላይ ከ2004 ዓ/ም እስከ 2007 ተቀጥረው ስራቸውን ሲሰሩ እንደነበር፣ በስራቸው ላይ እያሉ ነፍሰጡር የነበሩ ቢሆንም የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ሳይወስዱ በመውለዳቸው በህጉ የተጠበቀላቸውን የድህረ ወሊድ ፈቃድ በመጠቀም ላይ እያሉ ያልተጠቀሙበትን የቅድመ ወሊድ ጊዜ በድህረ ወሊድ በመጠቀም ወደ ስራቸው ሲመለሱ ተጠሪ አመልካች ከስራ ተሰናብተሻል ያላቸው መሆኑንና ይህም ከህጉ ይዘትና መንፈስ ውጭ መሆኑን ጠቅሰው የተጠሪ እርምጃ ህገ ወጥ ነው ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ቀርቦ በሰጠው መልስ አመልካች በራሳቸው ጊዜ ያልተጠቀሙበትን የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ለድህረ ወሊድ መጠቀማቸው ህጋዊ ያለመሆኑና ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖር ከስራ ገበታቸው በመቅረታቸው መሰናበታቸው ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካች የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ሳይጠቀሙ በድህረ ወሊድ ጊዜ መጠቀማቸውና ከስራ መቅረታቸው ህጋዊ አይደለም በማለት ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት በዚህ ረገድ የተጠየቁትን የአመልካች ክፍያዎችን ውድቅ አድርጎ ከህዳር 01 ቀን እስከ ህዳር 12 ቀን 2007 ዓ/ም ድረስ ያለውን ውዝፍ ደመወዝ ብቻ ይከፈላት ሲል ወስኗል፡፡ አመልካችም በውሳኔው ቅር በመሰኘት ቅሬታውን ለሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ፍ/ቤትና ቀጥሎም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም በሁለቱም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ከፍ ሲል በተገለጸው መልኩ የተሰጡትን ውሳኔዎች በመቃወም ለማስቀየር ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በቅድመ ወሊድ

www.abyssinialaw.com

ጊዜ ያልተጠቀመችበት የአንድ ወር የእረፍት ጊዜ በድህረ ወሊድ ጊዜ ከሚሰጠው ሁለት ወር የእረፍት ጊዜ ጋር መጠቀም አትችልም በማለት የሰጡት ውሳኔ የህጉን መንፈስና ይዘት ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ አንድ ሴት ከወለደች በኋላ ከአራት ወራት በፊት ከስራ መሰናበት የለባትም ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 87/4/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ያላገናዘበ እንዲሁም በሌሎች የመንግስት ሰራተኞች ህግጋት የተመለከተውን የመብት ጥበቃና የህግ አተረጓጎም ያልተከተለ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አቤቱታውም ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት የህግ ትርጉም ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪም ቀርበው መልስ ሊሰጡ ስላልቻሉ መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

በመሰረቱ የአሰሪና ሰራተኛ ህጉ በአንድ በኩል ሰራኛው ያለአግባብ ከስራ እንዳይፈናቀል ጥበቃ የሚያደርግ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የኢንዱስትሪ ሰላምን በመፍጠር የምርትና ምርታማነት እድገቱ እንዲጨምር ዋስትና ሲጪም እንደሆነ የሚታወቅ ነው፡፡ ይሄንኑ መሰረታዊ ሐሳብ መነሻ ባደረገ መልኩ ብሎም የኢንዱስትሪ ሰላሙን ከመጠበቅ አኳያ አንድ ሰራተኛ በአዋጅ ቁ/ 377/96 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል "ሀ" እስከ "በ" ባሉት ስር የተዘረዘሩትን ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ አሰሪው ያለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል መደንገጉን ከህጉ አጠቃላይ ድንጋጌዎች ከአንቀጽ 87/6/ ድንጋጌ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

እንዲሁም ህጉ ለተለዩ የሰራተኛ ክፍሎች የተለዩ ጥበቃ የሚያደርግባቸው ምክንያቶች መኖራቸውን ህጉ ያሳያል፡፡ ህጉ በአዋጅ አንቀጽ 14፣ ከአንቀጽ 87 እስከ 88 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች በተለየ መልኩ ድንጋጌዎችን ከአስቀመጠላቸው ሰራተኞች መካከል ሴት ሰራተኞች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ድንጋጌዎች በአንድ በኩል ሁሉንም ሴት ሰራተኞችን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በተለየ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሴት ሰራኞችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ እርግዝናና ወሊድ ደግሞ ሴቶችን በተለያየ ሁኔታ ውስጥ እንዲገኙ የሚያደርጉ ሁኔታዎች በመሆናቸው በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ ሴቶች ህጉ ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል፡፡ ወሊድን በተመለከተ ህጉ ለሴቶች የሚያደርገው ልዩ ጥበቃ የቅድመ ወሊድና የድህረ ወሊድ ፈቃድ ከክፍያ ጋር የማግኘት መብትና እንዲሁም በሌላ ጊዜም ሀኪም እንድታርፍ ካዘዘ ከክፍያ ጋር እረፍት የማግኘት መብት ስለመሆናቸው የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 88 ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ እንዲሁም አሰሪው

www.abyssinialaw.com

ሰራተኛዋ ነፍሰ ጡር ከሆነችበትና ከወለደችበት ቀን ጀምሮ በአራት ወራት ውስጥ ከስራ እንዲያሰናብታት ህጉ ጥበቃ የሚያደርግ መሆኑን ከአዋጅ አንቀጽ 87/5/ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ባልወሰዱበት ሁኔታ የወለዱ ሲሆን በአዋጅ አንቀጽ 88/3/ የተጠበቀላቸውን የስልሳ ቀን የድህረ ወሊድ ፈቃድ ከክፍያ ጋር አግኝተው በቅድመ ወሊድ ጊዜ ሊጠቀሙ ይችሉ የነበረውን የሰላሳ ቀን የወሊድ ፈቃድ በህጉ የተጠበቀላቸው የድህረ ወሊድ ጊዜ ሲያልቅ አንድ ላይ በመጠቀም ላይ እያሉ ተጠሪ በህጉ የተጠበቀላቸው የድህረ ወሊድ ጊዜ በማለቁ አመልካች ስራ ላይ አልተገኘም በሚል የስራ ውልን ያቋረጠባቸው መሆኑን ክርክሩ ያሳያል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው አንዲት ሴት በእርግዝና ምክንያት በህጉ የተጠበቀላት የቅድመ ወሊድና የድህረ ወሊድ ፈቃድ ጊዜ የሚታወቅ መሆኑን ህጉ ቢያስቀምጥም በቅድመ ወሊድ ጊዜ በህጉ የተጠበቀላትን የፈቃድ ጊዜ ሳትጠቀም ብትወልድ በቅድመ ወሊድ ጊዜ ይሰጥ የነበረው ፈቃድ ያልተጠቀመች ሴት ሰራተኛ ይህንኑ ጊዜ በድህረ ወሊድ ጊዜ መጠቀም የምትችል መሆኑን ያለመሆኑን ግን ህጉ በግልጽ አያስቀምጥም፡፡ ይሁን እንጂ ህጉ ከወሊድ በኂላ አንድ ሴት ሰራተኛ አራት ወር ሳይሞላት ከስራ ልትሰናበት እንደማትችል በአዋጅ አንቀጽ 87/5/ ስር የተመለከተው ድንጋጌ በህጉ ያለውን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል መሆኑን ተቀባይነት ያላቸው የህግ አተረጓጎም ደንቦች ያስገነዝባሉ፡፡ አንድ ልዩ ህግ አግባብነት ባለው ድንጋጌ ውስጥ ግልጽ የሆነ መፍትሔ ካላስቀመጠ ይኸው ድንጋጌ ባለበት ክፍልና ምእራፍ ስር ያሉትን ድንጋጌዎች አስተሳስሮ በማየት ተገቢውን ትርጉም መስጠት የህግ ትርጉም ደንቦች የሚፈቅዱት ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች በአዋጅ አንቀጽ 25፣ 27 እና 29/3/ ድንጋጌዎች አግባብ ካልሆነ በስተቀር ከወሊድ በኂላ አራት ወራት ውስጥ ከስራ ያለመባረር መብት ያላቸው መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 87 /5/ እና /6/ የሚያስቀምጥ በመሆኑና ተጠሪ ደግሞ ለስንብቱ ህጋዊ ምክንያት ነው በማለት የሚያቀርበው ክርክር በአዋጅ አንቀጽ 27 /1/ለ// ድንጋጌ ስር የተመለከተውንና ህግ አውጪው ከወሊድ ጋር ባልተያያዘ ሁኔታ ተቀባይነት ያለውን ድንጋጌ በመጥቀስ በመሆኑና የአመልካች ከስራ መባረር ከዲሲፕሊን ወይም ከቅነሳ ስርዓት ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ ባላስረዳበት ክርክሩ የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች በህጉ ያለውን ክፍተት በማየት ተገቢውን የህግ አተረጓጎም በመከተል ለጉዳዩ በአዋጅ አንቀጽ 87/5/ የተመለከተውን ጥበቃ ተግባራዊ ማድረግ ሲገባቸው ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት የሌለውን የአዋጅን አንቀጽ 88 /4/ ድንጋጌን መሰረት በማድረግ መወሰናቸው ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው የህግ ትርጉም አተገባበር ሆኖ አልተገኘም፡፡ ቀጥሎ መታየት ያለበት ውጤቱ ነው፡፡ የስራ ውል የተቋረጠበት አግባብ ከሕግ ውጭ ነው ከተባለ ውጤቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 42 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት የጠየቁት የተለያዩ

www.abyssinialaw.com

ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ነው፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 35/1/ለ/ መሠረት የሁለት ወር ደመወዝ፣ ክፍያ ለዘገየበት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 38 መሠረት የሁለት ወር ደመወዝ፣ በአዋጅ አንቀጽ 43/4/ሀ/ ደግሞ ካሳ በህጉ በተቀመጡት ስሌቶች መሠረት አመልካች ሊከፍሏቸው ይገባል ብለናል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የዓመት እረፍት የጠየቁ በመሆኑና ተጠሪ ደግሞ አመልካች የወሰዱ ስለመሆኑ ገልጾ የሚከራከር በመሆኑ አመልካች የአመት እረፍት ያልተጠቀሙ መሆን ያለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተጣርቶ እንዲወሰን ማድረጉ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሌላው አመልካች የጠየቁት የዳኝነት ጥያቄ ያልተከፈላቸው ደመወዝ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ክፍያ ከድህረ ወሊድ ፍቃድ መጠናቀቅ በኃላ ለነበረው ጊዜ ስራ ስላልሰሩ በአዋጅ አንቀጽ 377/96 አንቀጽ 54 መሠረት እንዲከፈላቸው ማድረግ ሕጋዊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የተጠየቀው ክፍያ ህጋዊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0122481 በ16/06/2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0123818 በ30/06/2007 ዓ.ም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 46890 በ18/02/2008 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው ከሕግ ውጪ ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለአመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 35/1/ለ/ መሠረት የሁለት ወር ደመወዝ፣ ክፍያ ለዘገየበት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 38 መሠረት የሁለት ወር ደመወዝ፣ በአዋጁ አንቀጽ 43/4/ሀ/ ደግሞ ካሳ እና በአንቀጽ 39 እና 40 መሠረት ደግሞ የአገልግሎት ክፍያ በህጉ በተቀመጡት ስሌቶች መሠረት ሊከፈሏቸው ይገባል ብለናል፡፡ የአመት እረፍትን በተመለከተ ግን አመልካች የወሰዱ መሆን ያለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተጣርቶ እንዲወሰን ማድረጉ ተገቢ ሆኖ ስለተገኘ በዚህ ረገድ የጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አጣርቶ እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ከድህረ ወሊድ ፈቃድ በኃላ ላለው ጊዜ አመልካች የሚከፈላቸው ደመወዝ የለም ብለናል፡፡
4. የሰበር ክርክር ወጪና ኪሳራን ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ::

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 98771

ሚያዝያ 24 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ታረቀኝ መኮንን } ጠበቃ - አቶ ጥጉ ደመመ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ፋንታነሽ አረጋ

ተጠሪ፡- አቢ ሚፍታህ ኤጀንሲ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው የአሁን አመልካቾች በስር ፍርድ ቤቶች የቀረበው ክስ እልባት ማግኘት የሚገባው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቀጥር 377/1996 መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 632/2004 የሚደነግግ በመሆኑ ጉዳዩ ልዩ ችሎት የተቋቋመለት ስለሆነ በመደበኛው ፍትሐ ብሔር ችሎት አይታይም በማለት መዝጋቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የአመልካቾች ልጅ ኩየት የቤት ሰራተኛነት ተቀጥራ ሄዳ አሰሪዎቿ ተገቢውን ጥንቃቄ ለድህንነትዋ ተገቢው እንክብካቤ ሳይደረግላት መቅረቱ በካርቦን ጭስ መርዝ ታፍና በሞት ተለይታለች፡፡ አመልካቾች በልጃቸው ሞት ምክንያት ኩየት ሆና በገንዘብ ትረዳቸው ስለነበር የተቋረጠባቸው ጥቅም ለማግኘት በኃላፊነት ወደ ኩየት አገር ለላካት በተጠሪ ላይ በፌ/የመ/ደ/ፍ/በት አራዳ ምድብ 2ኛ ፍ/ብሔር ችሎት ከውል ውጭ ኃላፊነት ክስ አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክሱ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሰረት የሚታይ ስለሆነ ለስራ ክርክር ችሎት የሚቀርብ ነው በማለት እንዲዘጋ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህን ትዕዛዝ በመቃወም አመልካቾች ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የሚሸፈን አይደለም፡፡ ይህ ጉዳይ ከውል ውጭ ኃላፊነት በተደነገገው በፍ/ብ/ህ/ቁ.2035፣2090፣2091 ነው መታየት ያለበት ስለዚህ የስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ

www.abyssinialaw.com

እንዲታረም በማለት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ በመመርመር ስህተት የለውም በማለት በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ትእዛዝ ላይ የሰጡት ዳኝነት መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባ ነው ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን በዚህ መሰረትም ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፤ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

አመልካቾች ጉዳዩ መታየት ያለበት ከውል ውጭ ኃላፊነት ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3(1)(2)(መ) በቤት ሰራተኛነት በትርፍ ላልተመሰረተ የአግልግሎት ቅጥር የማይሸፍን መሆኑ ህጉ በግልፅ ይደነግጋል፡፡ በተመሳሳይ ጉዳይም የፌዴራል ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 74111 ከውል ውጭ ኃላፊነት እንደሚታይ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በሌላ በኩል በመ/ቁ. 419560 ፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት መናገሻ ምድብ ችሎት 2ኛ ፍ/ብሔር ችሎት ክስ አቅረበን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 መሰረት አይሸፈንም በሚል መዝገቡ ተዘግቶብናል፡፡ በይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.130500 ጉድለት የለበትም በማለት ዘግቶታል፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች መሰረታዊ የህግ ክርክሮች ሳያዩትና ሳይመለከቱ ሳይመረምሩ መዝገብ በመዝጋት የሰጡት ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ጥሰት ነው ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤቶች ትእዛዝ በመሻር ጉዳዩ በመመሪያ ወደ ታች ፍርድ ቤት ተመልሶ ከውል ውጭ ኃላፊነት ታይቶ እንዲወሰን አመልክተዋል፡፡

በተጠሪ በኩል ደግሞ ግንኙነቱ የስራ ውል ነው፡፡ በስራ ላይ እንዳለች በደረሰባት ጉዳት መሞቷን የተገለፀ ስለሆነ አዋጅ ቁጥር 632/2001 አንቀጽ 4፤20 ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3፤110 መሰረት የሚስተናገድ ነው፡፡ የአመልካቾች ልጅ ከተጠሪ ጋር የሥራ ውል ስምምነት በማድረግ በውጭ ሀገር ለስራ ለሶስተኛ ሰው አገልግሎት እንድትሰጥ በህጋዊ መንገድ የሄደች በመሆኑ አመልካቾችም በስራ እንዳለች በደረሰባት ጉዳት መሞቷን የገለፁ ስለሆነ በመካከላችን የሚኖረው ክርክር አፈታት አዋጅ ቁጥር 632/2001 አንቀጽ 4 በግልፅ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ይታያል በማለት በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 632/2001 እና በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መታየት አለበት ማለታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክረዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 /2/መ/ መሰረት ለትርፍ በሚካሄድ ስራ ላይ ያልተመሰረተ የግል አገልግሎት ቅጥር ላይ ህጉ ተፈፃሚነት እንደሌለው በግልፅ የተደነገገ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 632/2001 አንቀጽ 3/2/ መሰረት ደግሞ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 /2/መ/ ቢኖርም ለትርፍ በሚካሄድ ስራ ላይ ላልተመሰረተ የግል አገልግሎት ስራ ላይ ለመቀጠር ወደ ውጭ አገር በሚሄድ ኢትዮጵያዊ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ሲል ተደንግጓል፡፡

ስለዚህ የቤት ሰራተኛ ወደ ውጭ የተላከ ከሆነ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ተፈፃሚነት ያለው በመሆኑ በዚህ ረገድ በአመልካቾች የቀረበው ተቀባይነት የለውም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 632/2001 አንቀጽ 4 መሰረት የግል ስራና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ እና በሰራተኛ የሚነሳ ማንኛውም የስራ ክርክር የሚፈታው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ እንደሚታይ ተመልክቷል፡፡ አዲስ በወጣው የኢትዮጵያ የውጭ አገር ስራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 አንቀጽ 71 በሰራተኛ መሰረት እና በአሰሪው ወይም በኤጀንሲው መካከል ካለው የስራ ግንኙነት በመነጨ ማንኛውም የመብትና የጥቅም ክርክር ጉዳይ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሰረት በተቋቋመ የስራ ክርክር ችሎት ይታያል በማለት ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ የአመልካቾች ጉዳይ በውል የስራ ግንኙነት የተመሰረተ በልጃቸው የደረሰው ጉዳት መስተናገድ ያለበት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሆኑን በዝርዝር ከላይ እንደተመለከተው ነው፡፡ ስለሆነም በአመልካቾች የሚቀርበው ጉዳዩ መታየት ያለበት ከውል ውጭ ኃላፊነት ነው የሚለው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች በመጀመሪያ ጉዳያቸው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሰረት አቅርበው ፍርድ ቤቱም በእንደዚህ አይነት የስራ ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 337/1996 አንቀጽ 2 እና 3 መሰረት ሊሸፈን የማይችል እና የክርክር መንፈስም ፍርድ ቤቱ የማየት ሥረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት የተዘጋ መሆኑን ከመ/ቁ.41956 ጥር 15 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከተሰጠው ትእዛዝ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ የሚያመለከተው ደግሞ አመልካቾች ጉዳያቸውን በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሰጣቸውና መብታቸውን ለማስጠበቅ በተለያየ ጊዜ ከመጠየቅ ያልተቆጠቡና ጥረት ያደረጉ መሆናቸውን ነው፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ትእዛዝ በህጉ አተረጓጎም ረገድ መሰረታዊ ስህተት የተፈፀመበት ነው የምንልበት ምክንያት አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መ/ቁ.147425 የካቲት 13 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠ ትእዛዝ እና የፌ/መ/ደ/ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.111396 ታህሳስ 11 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካቾች ክሱን ማቅረብ የሚገባቸው ለስራ ክርክር ችሎት ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዘገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 117862

ሰኔ 20 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች - ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

ፊይሳ ወርቁ

**አመልካች** - ጎል ኢትዮጵያ ነ/ፈ ሙስሐረድ ደሳለኝ ቀረቡ

**ተጠሪ** - አቶ ዲዲሞ ኦጋቶ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በጋምቤላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት በአመልካች ድርጅት ውስጥ በመዛኝ የስራ መደብ ተቀጥሬ እያገለገልኩ እያለ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1)(ለ) ከተደነገገው ውጭ የስራ ውሉን ያቋረጠ በመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 43(2) መሰረት ወደ ስራዬ እንዲመልሰኝ ወይም ጥቅማ ጥቅም ተከፍሎኝ እንዲያሰናብተኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ ለቅርብ አለቃቸው ሆነ ለሌላ ለሚመለከተው አካል ሳያሳውቁ ለቀሩባቸው ሰባት ቀናት በቂና ህጋዊ ምክንያት ባለማቅረባቸው ከስራ መባረራቸው በአዋጁ አንቀጽ 27(1) መሰረት ህጋዊ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ማስረጃውን መርምሮ ከሳሽ በአያቱ ሞት ምክንያት ሃዘን ላይ እንደነበር የሚያስረዳ ማስረጃ በማቅረቡ በሃዘን ምክንያት በአዋጁ አንቀፅ 81(1)(ለ) መሰረት የሚሰጠው ፈቃድ እና የሳምንት የእረፍት ፈቃድ ተካቶ ሲሰላ ከስራ ያለምክንያት ቀርቷል ሊባል የሚችለው ለሁለት የስራ ቀናት ብቻ በመሆኑ ስንብቱ ህገወጥ ነው፤ ስለሆነም ድርጅቱ ሰራተኛውን ወደ ስራው እንዲመልስ ወደ ስራው መመለስ ካልፈለገም ክፍያ እንዲፈፅም ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ቅሬታቸውን ለጋምቤላ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ጳጉሜ 2/2007 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ ተጠሪ 5 (አምስት) ቀናት በመደዳው ያለበቂ ምክንያት ከስራ መቅረቱ በተረጋገጠበት ስንብቱ ህገወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁን ዓላማ እና ይዘት በአግባቡ ያገናዘበ መሆኑን ለማጣራት ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ

www.abyssinialaw.com

መጥሪያውን ተረክበው መልስ በሚሰጥበት ቀን ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

ከላይ ባጭሩ ለመግለፅ የሞከርነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ቅሬታ በቀረበበት ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት ቢኖር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው አመልካች በሰበር ቅሬታቸው ተጠሪ ለድርጅቱ ሳያሳውቁ ከየካቲት 23 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ መቅረታቸውንና፣ በዚህም መነሻ ድርጅቱ ከየካቲት 27 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ከተጠሪ ጋር የነበረው የቅጥር ውል መቋረጡን የሚገልፅ ደብዳቤ መፃፉን በመካድ አልተከራከሩም፡፡ የስንብት ደብዳቤውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ከስራ ከቀሩ በአስራ ሁለተኛው ቀን ማለትም መጋቢት 4 ቀን 2007 ዓ.ም ወደ ድርጅቱ መመለሳቸውን እና ባቀረቡት የሀዘን ማስረጃ የሚሰጠው ሶስት የረፍት ቀናት እንዲሁም የበዓል እና እሁድ ቅዳሜ የረፍት ቀናት ቢቀነሱ በአዋጁ አንቀፅ 27(1)(ለ) ከተመለከተው ጊዜ በላይ ያለምክንያት ከስራ መቅረታቸውን ስለሚያሳይ ስንብቱ ህጋዊ ነው እንዲባል ተከራክረዋል፡፡

በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 27(1)(ለ) እንደተደነገገው በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት ያለበቂ ምክንያት ከስራ መቅረት አሰሪው የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ ያስችለዋል፡፡ ከድንጋጌው መረዳት እንደሚቻለው ሰራተኛው ከስራ የቀረበት ቀን የሚቆጠረው እና የቀረበትም ምክንያት በቂ መሆን አለመሆኑ የሚመዘነው የስራ ዉሉ ፀንቶ እስከቆየበት ጊዜ ድረስ ነው፡፡ ከዚህ በቀር የስራ ውሉ ከተቋረጠ በኂላ ላሉ ቀናት ሰራተኛው በስራው እንዲገኝ ስለማይጠበቅ የቀረበትን ጊዜ መቁጠር እና የቀረበትን ምክንያት በቂነት መመዘን አያስፈልግም፡፡

በመሆኑም በተያዘው ጉዳይ አመልካች ሠራተኛው ለድርጅቱ ሳያሳውቅ ከየካቲት 23 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ መቅረቱንና፣ በዚህ ምክንያት ድርጅቱ ከየካቲት 27 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ከተጠሪ ጋር የነበረው የቅጥር ውል መቋረጡን የሚገልፅ ደብዳቤ መፃፉን ሳይክዱ ሰራተኛው መጋቢት 4 ቀን 2007 ዓ.ም ወደ ድርጅቱ መመለሱን መሰረት በማድረግ ከየካቲት 23 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ሲታሰብ በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት ያለበቂ ምክንያት ከስራ መቅረቱን ያሳያል ስለሆነም ስንብቱ ህጋዊ ሊባል ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(ለ) የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ መሠረት ያላደረገ፣ ድንጋጌውን ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያበቁ ሁኔታዎችን ያላሟላ ክርክር በመሆኑ የምንቀበለው አይሆንም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት በሕጉ ከተደነገገው ውጭ እንዲሰናበት ተደርጓል ስለሆነም ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት ወደ ስራው እንዲመለስ ወይም ለዚህ ዓይነት ሕገ-ወጥ ስንብት ሊከፈል የሚገባው ክፍያ እንዲከፈል ያሳለፉት ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላላገኘነው በአብላጫ ድምፅ ተከታዩን ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የጋምቤላ ከተማ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00700/07 በቀን 8/10/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የጋምቤላ ከፍ/ፍ/ቤት በ14/11/2007 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በፍ/ሰ/መ/ቁ 00431/07 በ26/12/2007 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት መስከረም 12/2008 ዓ.ም አፈፃፀሙ እንዲታገድ ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

**<u>የልዩነት ሐሳብ</u>**

ተጠሪው ከ23/06/2007 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 03/07/2007 ዓ.ም በስራ ላይ ያልነበሩ መሆኑ እና ወደ ስራ ቦታው የመጡት በ04/07/2007 ዓ.ም መሆኑ የተረጋገጠ እና ክርክር ያልቀረበበት ጉዳይ ነው ። ተጠሪው ከስራ ከቀሩባቸው ቀናት መካከል የሀዘን ፈቃድ ነው ተብሎ በአመልካቹ ተቀባይነት ያገኘው ሶስት ቀን ሲቀነስ ተጠሪው ከስራ የቀሩት በመደዳው ከአምስት የስራ ቀናት በላይ ነው። ተጠሪው ከስራ የቀሩበትን ቀን በማስላት ከስራ የተሰናበቱት ከ23/06/2007 ዓ.ም ጀምሮ እንደሆነ አመልካች በስንብት ደብዳቤው የገለጸ ቢሆንም ደብዳቤው የተጻፈው በ09/07/2007 ዓ.ም ነው። አመልካቹ የሥንብት ደብዳቤውን ከ24/06/2007 ዓ.ም ጀምሮ መጻፍ ሲችል እስከ 09/07/2007 ዓ.ም ድረስ ያዘገየው ተጠሪው የቀሩበትን በቂ ምክንያት ያቀርቡ ቢሆን ለመጠባበቅ እና እድል ለመስጠት ነው ከሚባል በቀር በሌላ አግባብ ሊተረጎም የሚገባው ሆኖ አላገኘሁትም። የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ለ/ ድንጋጌ በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት ወይም በአንድ ወር ውስጥ በጠቅላላው ለአስር የስራ ቀናት ወይም በአንድ ዓመት ውስጥ ለሰላሳ የስራ ቀናት ያለበቂ ምክንያት ከስራ መቅረት ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውልን ለማቋረጥ የሚያስችል መሆኑን ከመደንገግ አልፎ አሰሪው በዚህ ድንጋጌ መሰረት ውሉን ስለማቋረጡ በደብዳቤው ካልገለጸ በቀር ከስራ መቅረቱ በራሱ የሥራ ውሉን አያቋርጥም የሚል ይዘት የለውም። በመሆኑም ሰራተኛው ያለበቂ ምክንያት በመደዳው ለአምስት የሥራ ቀናት ከስራ መቅረቱ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ ከላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት የስራ ውሉ ያለማስጠንቀቂያ የሚቋረጥ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ተብሎ ሊወሰን ይገባው ነበር በማለት ስማችን በተራ ቁጥር አንድ እና አራት የተመለከቱት ዳኞች የልዩነት ሀሳባችንን አስፍረናል ።

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 125004

ሰኔ 22 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- አዲስ ፋና ጠቅላላ ሸቀጣ ሸቀጥ እና ሆቴሎች ንግድ አ.ማ.

- ነ/ፈጅ ወንድሜነህ ተገኘ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሲቂ ብርሃኑ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ተጠሪው በባህርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት በ27/11/2007 ዓ.ም. አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ አመልካች ተጠሪን ይሰሩበት ከነበረው የባህርዳር ቅርንጫፍ ከ13/08/2007 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ጅማ ቅርንጫፍ ያዛወራቸው መሆኑን፣ የዝውውር ደብዳቤው በ07/08/2007 ዓ.ም. የተጻፈ ሆኖ ለተጠሪው የደረሰው በ09/08/2007 ዓ.ም. መሆኑን፣ ተጠሪው ወደ ተዛወሩበት ቦታ ሳይሄዱ በባህርዳር ቅርንጫፍ ሲሰሩበት የነበረው የስራ መደብ ሳይሰረዝ ወደ ጅማ ቅርንጫፍ እንዲዛወሩ የተደረገው አለአግባብ መሆኑን ገልጸው ዝውውሩን በመቃወም ለምዕራብ አማራ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በ16/08/2007 ዓ.ም. ክስ አቅርበው መጥሪያውን በ17/08/2007 ዓ.ም. ለአመልካች ማድረሳቸውን፣ተጠሪው ከ13/08/2007 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 17/08/2007 ዓ.ም. ድረስ በመደዳው ለአምስት ቀናት በተዛወሩበት ጅማ ቅርንጫፍ በስራ ላይ አልተገኙም በሚል የስራ ውላቸውን ስለማቋረጡ አመልካች 19/08/2007 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ለተጠሪው ያሳወቀ መሆኑን፣አመልካቹ በቦርድ ለቀረበበት ክስ ተጠሪውን ያሰናበታቸው በመሆኑ ከስራ የተሰናበተን ሰራተኛ ጉዳይ ቦርዱ የማየት ስልጣን የለውም የሚል

www.abyssinialaw.com

መቃወሚያ ማቅረቡን፣ቦርዱም የአመልካቹን የስንብት እርምጃ በ20/08/2007 ዓ.ም. በተሰጠ ትዕዛዝ ካገደው በኃላ ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለኝ በማለት በ04/09/2007 ዓ.ም. ብይን መስጠቱን፣አመልካቹ በዕግድ ትዕዛዙ መሰረት ተጠሪውን እስከ 29/09/2007 ዓ.ም. ድረስ ሲያሰራው ቆይቶ በቃል ትዕዛዝ ያሰናበተው መሆኑን፣በሌላ በኩል የቦርዱን ብይን በመቃወም አመልካች ለአማራ ብሔራዊ ክላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ቦርዱ ከስራ የተሰናበተን ሰራተኛ ጉዳይ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በሚል ብይኑን በመዝገብ ቁጥር 40770 በ03/11/2007 ዓ.ም. የሻረው መሆኑን፣ ተጠሪው ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡትም ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች በዝርዝር ገልጸው ስንብቱ ሕገ ወጥ በመሆኑ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደስራቸው እንዲመለሱ በመጠየቅ መሆኑን፣በፍርድ ቤት በቀረበበት ክስ አመልካቹ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በሰጠው መልስ የአዲስ አደረጃጀት እና ደመወዝ ስኬል ጥናት በማድረግ ከ01/11/2006 ዓ.ም. ጀምሮ አዲስ ምደባ እንዳካሄደ፣ ተጠሪውም እንዲዛወሩ የተደረገው በዚሁ መሰረት እንደሆነ፣ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገው ደግሞ በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት በተዛወሩበት ቦታ በስራ ላይ ባለመገኘታቸው እንደሆነ እና በተዛወርኩበት ቦታ በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት በስራ ላይ ያልተገኘሁት ዝውውሩን በመቃወም አቤቱታ እና ክስ በማቅረቤ ነው በሚል በሰራተኛው የሚቀርበው ምክንያት ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ስላለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት የስንብት እርምጃው የተወሰደው በአግባቡ እንደሆነ ገልጾ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ የተከራከረ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ የስራ መደቡ ባልተሰረዘበት ሁኔታ አመልካች ለ30 ዓመታት ያገለገሉትን ሰራተኛ ወደ ሌላ ቦታ ማዛወሩ ተገቢ አለመሆኑን፣ዝውውሩ ተገቢ ነው ቢባል እንኳ ተጠሪው በነበሩበት ባህርዳር ቅርንጫፍ ርክክብ የጨረሱት በ12/08/2007 ዓ.ም. ስለመሆኑ በተጠሪው ምስክሮች መረጋገጡን፣ ይህም ጉዞው ከሚፈጀው ጊዜ አንጻር ተጠሪው በ13/08/2007 ዓ.ም. በጅማ ቅርንጫፍ በስራ ላይ ሊገኙ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳልነበረ የሚያመለክት መሆኑን፣ የቦርዱ የዕግድ ጊዜ ካበቃ በኃላም ተጠሪው ወደ ተዛወሩበት ቦታ እንዲሄዱ አመልካች ዕድል ያልሰጣቸው መሆኑን ገልጾ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት አመልካች የአራት ወር ደመወዝ ከፍሎ ተጠሪ ወደ ስራ እንዲመልሳቸው በመዝገብ ቁጥር 39453 በ18/06/2008 ዓ.ም. ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው የባህርዳር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የቀረበላቸውን ይግባኝ እና አቤቱታ እንደቅደም ተከተላቸው በመዝገብ ቁጥር 0305653 በ05/07/2008 ዓ.ም. እና በመዝገብ ቁጥር 56209 በ07/07/2008 ዓ.ም. በትዕዛዝ ዘግተው በማሰናበታቸው ሲሆን የሰበር አቤቱታው

www.abyssinialaw.com

ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪው ለአምስት ተከታታይ ቀናት ከስራ በመቅረታቸው ተሰናብተዋል በማለት የቀረበው የፊርማ መቆጣጠሪያ ሰነድ በስር ፍርድ ቤቶች ሳይታይ የመታለፉን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. የስራ መደቡ ባልተሰረዘበት ሁኔታ አመልካች ለ30 ዓመታት ያገለገሉትን ሰራተኛ ወደ ሌላ ቦታ ማዛወሩ ተገቢ አይደለም በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት የደረሰበት መደምደሚያ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
2. ስንብቱ ሕገ ወጥ በመሆኑ ተጠሪው ወደስራ ሊመለሱ ይገባል በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም?
3. አመልካች የአራት ወራት ውዝፍ ደመወዝ ለተጠሪው እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

የመጀመሪያው ነጥብ በተመለከተ በመሰረቱ ተጠሪው ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት ዝውውሩን ሳይሆን የስራ ስንብት እርምጃውን በመቃወም ነው፡፡ ዝውውሩ እና ስንብቱ ተያያዥነት ያላቸው መሆኑን ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የዝውውሩን አግባብነት እንደ አንድ የክርክር ጭብጥ አድርጎ ውሳኔ ማሳረፉ ተገቢውን የክርክር አመራር ስርዓት መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለስራው አስፈላጊ መሆኑ ሲታመን አንድ ሰራተኛ ከአንድ የስራ መደብ ተመሳሳይ ደረጃ ወዳለው ሌላ የስራ መደብ ወይም ከአንድ ቅርንጫፍ ወደ ሌላ ቅርንጫፍ የማዛወር መብት በመሰረቱ የአሰሪው ነው፡፡ የሰራተኛው የአገልግሎት ዘመን መጠን እና የስራ መደቡ አለመሰረዝ በራሱ ሰራተኛውን ከአንድ ቅርንጫፍ ወደ ሌላ ቅርንጫፍ አዛውሮ ከማሰራት የሚከለክል አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የወረዳው ፍርድ ቤት የደረሰበት መደምደሚያ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ የወረዳው ፍርድ ቤት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ለማለት ከቻለባቸው ዓበይት ምክንያቶች አንዱ ተጠሪው ርክክብ የጨረሱት በ12/08/2007 ዓ.ም. እንደሆነ በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ጉዞው ከሚፈጀው ጊዜ አንጻር ሰራተኛው በ13/08/2007 ዓ.ም. በተዛወሩበት ጅማ ቅርንጫፍ ለመገኘት የሚችሉበት ሁኔታ አልነበረም የሚል ነው፡፡ በግራ ቀኙ በኩል ከተሰሙት ምስክሮች መካከል የተጠሪው 1ኛ ምስክር ተጠሪው ርክክብ የጨረሱት በ12/08/2007 ዓ.ም. እንደሆነ በመግለጽ የመሰከሩ ሲሆን የተጠሪው የቅርብ አለቃ መሆናቸውን የገለጹት

www.abyssinialaw.com

የአመልካቹ 2ኛ ምስክር በበኩላቸው ተጠሪው ርክክብ ያጠናቀቁት በ09/08/2007 ዓ.ም. እንደሆነ ገልጸው መመስከራቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ከዚህ ምስክርነት መካከል የወረዳው ፍርድ ቤት ተገቢ አድርጎ የተቀበለው በተጠሪው 1ኛ ምስክር የተሰጠውን ምስክርነት ነው፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው ላይ ርክክቡ የተፈጸመው በ09/08/2007 ዓ.ም. መሆኑን አስረድተን እያለ ተቀባይነት ያጣው አለአግባብ ነው ከማለት በቀር ተጠሪው ርክክቡን የፈጸሙት በ12/08/2007 ዓ.ም. ስለመሆኑ በተጠሪው ምስክር የተሰጠው ምስክርነት ተቀባይነት የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት ስለመኖሩ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ርክክቡ የተፈጸመበትን ሰነድ በማስረጃነት አቅርቦ የነበረ ስለመሆኑም የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታው ላይ ከስንብቱ ጋር የተያያዙትን ሰነዶች ፍርድ ቤት በማስረጃነት አቅርበን ነበር ከማለት በቀር ካቀረቧቸው ሰነዶች መካከል የርክክቡን ቀን የሚያመለክት ሰነድ ስለመኖሩ አልገለጸም፡፡ በሰበር አጣሪ ችሎት አቅርቦ ከመዝገቡ ካያያዛቸው ሰነዶች መካከልም ይህ ሰነድ የለም፡፡ ተጠሪው ከስራ የተሰናበቱት ከ13/08/2007 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 17/08/2007 ዓ.ም. ድረስ በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት በስራ ላይ አልተገኙም በሚል ሲሆን ርክክቡን ያጠናቀቁት በ12/08/2007 ዓ.ም. ከሆነ ደግሞ ከባህርዳር ወደ ጅማ የሚደረግ ጉዞ የሚፈጀው ጊዜ የሚታወቅ በመሆኑ ተጠሪው በ12/08/2007 ዓ.ም. በስራ ላይ አልተገኙም ሊባሉ የሚችሉበት አግባብ አይኖርም፡፡ ተጠሪው ርክክቡን ባህርዳር ላይ በ12/08/2008 ዓ.ም. አጠናቀው በ13/08/2007 ጅማ ቅርንጫፍ በስራ ላይ ለመገኘት የሚያስችላቸው ሁኔታ የነበረ ስለመሆኑም በአመልካቹ በኩል የቀረበ ክርክር የለም፡፡ በመሆኑም ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ ተጠሪው ወደስራ እንዲመለሱ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የወሰደው የዝውውር እርምጃ ተቀባይነት የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ እና ተጠሪውም ወደ ስራ መመለስ የሚገባቸው በጅማ ቅርንጫፍ በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪው ወደ ስራ የሚመለሱበትን ቅርንጫፍ ሳይለይ በደፈናው ወደስራ ሊመለሱ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ባለመሆኑ ውሳኔው በዚህ አግባብ ብቻ ሊታረም የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሶስተኛውን ነጥብ በተመለከተ ወደ ስራው እንዲመለስ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት የተወሰነለት ሰራተኛ ከስድስት ወራት የማይበልጥ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለው ፍርድ ቤቱ የሚወስን ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43 (5) የተመለከተ በመሆኑ ለተጠሪው የአራት ወራት ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈል መወሰኑ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ የሰራተኛው ወደስራ የመመለስ ውሳኔ ከፀና ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ውዝፍ ደመወዝ ፍርድ ቤቱ ለሰራተኛው የሚወስን ስለመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በዚህ ችሎት ከቆየበት ጊዜ አንጻር ለተጠሪው በተጨማሪ የሁለት ወራት ደመወዝ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

www.abyssinialaw.com

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በባህርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 39453 በ18/06/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ በባህርዳር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንደቅደም ተከተላቸው በመዝገብ ቁጥር 0305653 በ05/07/2008 ዓ.ም. እና በመዝገብ ቁጥር 56209 በ07/07/2008 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የስራ ስንብት እርምጃው ሕገወጥ በመሆኑ ተጠሪው የአራት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደስራ ሊመለሱ ይገባል በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. በስር ፍርድ ቤቶች ከተወሰነው በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43 (5) በተመለከተው መሰረት አመልካች የሁለት ወር ውዝፍ ደመወዝ ለተጠሪው ሊከፍል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
4. ወደስራ የሚመለሱበት ቅርንጫፍ ሳይለይ ተጠሪው ወደስራቸው ሊመለሱ ይገባል በሚል በደፈናው የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
5. ተጠሪው ወደ ስራ ሊመለሱ እና ውዝፍ ደመወዝም ሊከፈላቸው በተዛወሩበት ጅማ ቅርንጫፍ ነው በማለት ወስነናል፡፡
6. በባህርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 39453 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ09/07/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
7. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
8. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
9. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.119694

ሐምሌ 27 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንዳሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች.............ንብ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ. -የቀረበ የለም

ተጠሪ...................አቶ አለማየሁ ሁሉቃ -ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የሥራ ስንብትን የሚመለከት ክስን መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡--በሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች /የሥር ተከሳሽ/፣ የአሁን ተጠሪ /የሥር ከሳሽ/ ሆኖ ሲከራከሩ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የሥር ከሳሽ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ በተከሳሽ ኩባንያ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥራ አስኪያጅነት ተቀጥሬ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ሲስተም ፕሮጀክት ማናጀርነት በአጠቃላይ ብር 11,327.00 እየተከፈለኝ እየሰራሁ እያለ ምንም ዓይነት የሥራ ብቃት ማነስ ሳይኖርብኝ እና ከሥራ ገበታዬም የቀረሁበት ቀን ሳይኖር ተከሳሽ መጋቢት 17 ቀን 2005 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ከሕግ ዉጭ ከሥራ ስላሰናበተኝ ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ፣ ይህ ካልሆነ በአጠቃላይ ብር 219,439.56 እንዲከፍለኝ በማለት ከሷል፡፡ የሥር ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ከሳሽ ከሥራዉ ሊባረር የቻለዉ በሥራዉ ላይ ባሳየዉ በብቃትና በጥራት ለመስራት ያለመቻል የብቃት ማነስ በመሆኑ ከሥራ የተሰናበተዉ በሕጉ አግባብ ስለሆነ ያቀረበዉ ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም፣ ፍ/ቤቱ የሥራ ዉሉ የተቋረጠዉ ከሕግ ዉጭ ነዉ የሚል ከሆነ የተከሳሽ ኃላፊነት የ3 ወር ደመወዝ ብቻ ነዉ፣ ወደ ሥራ መመለስ የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን የሰዉ ምስክሮች በመስማት፣ የቀረበዉ የሰነድ ማስረጃዎች በማየት በመመዘን በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ ከሳሽን ከሥራዉ ያሰናበተዉ የሥራ ጥራት እና አቅም ማነስ እንዲሁም አለቃን ሳያሳዉቁ በሥራ ገበታ ላይ አለመገኘትን ሲሆን ይህን በማስረጃ ያስረዳዉ ነገር ስለሌለ ተከሳሽ ከሳሽን ያለ በቂ ምክንያት ከሥራዉ ያሰናበተዉ በመሆኑ፣ ከሳሽ ወደ ሥራ ሊመለስ አይገባም በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፣ ተከሳሽ በአጠቃላይ ብር 106,431.89 ዉሳኔዉ ከተሰጠ ቀን ጀምሮ ከ9% ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍለዉ በማለት

www.abyssinialaw.com

ወስኗል፡፡ የሥር ተከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፣ የሥር ከሳሽም የመስቀለኛ ይግባኝ ያቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤት የሥራ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነዉ መባሉን አግባብ እንደሆነ በማረጋገጥ፣ ክፍያዎችን በተመለከተ የስንብት ክፍያ ብር 35,146.23፣ የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ብር 21,400.66፣ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 /4/ /ሀ/ መሰረት ብር 59,862 ብር ዉሳኔዉ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ከ9% ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍለዉ በማለት በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ህዳር 3 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ ስድስት ገጽ አቤቱታ የአሁን ተጠሪ የሥራ ብቃትና ችሎታ የመመዘን ስልጣን የኩባንያዉ ዋና ስራ አስኪያጅ በመሆኑ በዚህ አግባብ የብቃት ማነስ ያለባቸዉ መሆኑ ከተገመገመ በኂላ ለሥራ አመራር ቦርድ ቀርቦም ከተጣራ በኂላ ከሥራ የተሰናበት በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪን እንደሰራተኛ በመቁጠር በአዋጅ ቁጥር 377/96 /አዋጅ ቁጥር 494/98 እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 39 /1/ /መ/ መሰረት የስንብት ክፍያ እንዲከፈለዉ መወሰናቸዉ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ የስንብት ክፍያዉ ይከፈል ቢባል እንኳን ብር 15,796.92 ብቻ ሆኖ ሳለ ብር 35,146.23 ብር እንዲከፈለዉ መወሰኑ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተዉ በአግባቡ ሆኖ ሳለ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 /4/ /ሀ/ መሰረት ብር 59,862.00 እንዲከፈለዉ መወሰኑ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ የተሰናበተዉ በችሎታ ማነስ ምክንያት በመሆኑ የፕሮቪደንት ፈንድ ብር 21,400 የተወሰነዉ የሕግ መሰረት የለዉም፡፡ የሥር ፍ/ቤት የሥራ ዉል የተቋረጠዉ ከሕግ ዉጭ ነዉ የሚል አቋም የሚይዝ ከሆነም የአመልካች ኃላፊነት የሶስት ወር ደመወዝ ብቻ የማያልፍ ሆኖ እያለ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት በማድረግ የወሰኑት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልኝ በቂ ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ይህን ጉዳይ በማየት ፣ተጠሪ በሥራ መሪነቱ ከ3 ወር በላይ ደመወዝ በላይ ሊከፈለዉ አይገባም በማለት አመልካች ያቀረበዉን አቤቱታ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘዉ መሰረት ጥር 6 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት፡--የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች ተጠሪ ከሕግ ዉጭ ከሥራ ያሳናበተዉ መሆኑን በማረጋገጥ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና በድርጅቱ የሰዉ ሃይል አስተዳደር፣ ግዢና ሎጂስቲክ ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር ማኑዋል መሰረት ዉሳኔዎችን የሰጡ በመሆኑ ዉሳኔዎቹ እንዲጸኑልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች መልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ መዝገቡን

www.abyssinialaw.com

እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች የተጠሪን የሥራ ዉል በማቋረጥ ከሥራ ያሰናበተዉ ተጠሪዉ በሥራዉ የብቃት ወይም የችሎታ ማነስ በማሳየቱ እና ከ19/3/2013--23/3/2013 እ.ኤ.አ. ያለ ፈቃድ ከሥራ ገበታዉ በመቅረቱ በሚል ምክንያት እንደሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች ያመለክታል፡፡ የአሁን ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበዉ ክስ ምንም ዓይነት የሥራ ብቃት ማነስ እንደሌለበት እና ከሥራዉም ያለፈቃድ ቀርቶ እንደማያዉቅ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ከዚህ አንጻር የአሁን አመልካች የአሁን ተጠሪን ከሥራዉ ያሰናበተበት ምክንያቶች መኖራቸዉን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ በዚህ አግባብ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረባቸዉ የሰዉ ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል የአሁን ተጠሪ በሥሩ ለነበረችዉ አንድ ሠራተኛ በሰጠዉ ዝቅተኛ የሥራ ግምገማ ዉጤት ምክንያት በአመልካች ዋና ሥራ አስኪያጅ እና በሠራተኛዉ መካከል አለመግባባት መፈጠሩን ከመግለጽ ዉጭ ተጠሪ በሥራዉ ላይ የብቃት ማነስ ሁኔታ ያሳየ መሆኑን ያላረጋገጡ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ያመለክታል፡፡ በተጠሪ በኩል የቀረቡት የሰዉ ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል ተጠሪ ላለፉት ሁለት አመታት በተደረገ የሥራ ግምገማ ከአጥጋቢ በላይ የሥራ አፈጻጸም እንደነበረዉ፣ በሥራዉ ዕዉቀት እና ችሎታ እንዳለዉ ማረጋገጣቸዉ ማስረዳታቸዉ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ያሳያል፡፡ በሶስተኛ ዓመት የሥራ ግምገማ ወቅት ከዋና ሥራ አስኪያጁ ጋር በተፈጠረዉ አለመግባባት ምክንያት ዋና ሥራ አስኪያጁ ዝቅተኛ የስራ አፈጻጸም ዉጤት የሰጡት መሆኑን መስክሯል፡፡ በሌላ በኩል የአሁን አመልካች ተጠሪን ከሥራዉ ያሰናበተበት ምክንያት የአሁን ተጠሪ ያለ ፈቃድ ከ19/3/2013--23/3/2013 እ.ኤ.አ. ከሥራ ገበታቸዉ ቀርተዋል የሚል ሲሆን አመልካች ይህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዳላቀረበ ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ማየት ይቻላል፡፡ የአሁን ተጠሪ ግን ያለ ፈቃድ ከሥራዉ እንዳልቀረ የህክምና ሠርትፍኬት እንዲሁም ለቅርብ አለቃዉ በማሳወቅ ሆስፒታል ሄዶ እንዲታከም ከአመልካች ኩባንያ ወደ ሆስፒታል መላኪያ ቅጽ እንደተሰጠዉ ባቀረበዉ ማስረጃ ያረጋገጠ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ያሳያል፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች ፍሬ ነገርን በማስረጃ አጣርቶ ለመወሰን በተሰጣቸዉ ሥልጣን መሰረት ይህን ጉዳይ በማጣራት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመመዘን በሰጡት ዉሳኔ የአሁን አመልካች የተጠሪን የሥራ ዉል ያቋረጠዉ ያለበቂ ምክንያት ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ እና ከኩባንያዉ ማንዋል ዉጭ መሆኑን በማረጋገጥ የሥራ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነዉ በማለት የሰጡት ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ ከማለት ዉጭ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚያስችል በቂ ምክንያት የለም፡፡

በመሆኑም የአሁን አመልካች የተጠሪን የሥራ ዉል በማቋረጥ ከሥራዉ የተሰናበተበት ሁኔታ ከሕግ ዉጭ በመሆኑ ስንብቱ ሕገ ወጥ በመሆኑ የዚህን ዉጤት በሕጉ አግባብ ማየቱ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 /2/ መሰረት መገንዘብ እንደሚቻለዉ ሕገ ወጥ የስራ ስንብት ዉጤት ሠራተኛዉን ወደ ሥራ መመለስ ወይም ተገቢ ክፍያዎች ተከፍሎት እንዲሰናበት ማድረግ እንደሆነ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የሥር ፍ/ቤቶች በሰጡት ዉሳኔ የአሁን ተጠሪ ወደ ሥራ

www.abyssinialaw.com

መመለስ የለበትም በማለት የወሰኑትን በተመለከተ የአሁን ተጠሪ በየደረጃዉ ላሉት ፍ/ቤቶች ቅሬታዉን በማቅረብ ያስለወጠዉ ነገር ስለሌለ ይህን ነጥብ ማየቱ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ስለሆነም መታየት ያለበት የአሁን አመልካች ተጠሪን ከሕግ ዉጭ ከሥራ በማሰናበቱ ለተጠሪዉ ሊከፍለዉ የሚገባዉ ክፍያዎች ምን እንደሆኑ ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ የሥራ መሪ ቢሆንም የአመልካች የሰዉ ሃይል አስተዳደር፣ ግዢና ሎጂስቲክ ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር ማንዋል በሚደነግገዉ አግባብ ተጠሪዉ የስራ ዉል የተቋረጠ እንደሆነ ከፍትሐብሔር ሕግ ከተደነገገዉ ይልቅ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ተጠቃሚ እንደሚሆን ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም ለተጠሪ ሊከፈል የሚገቡት ክፍያዎች መታየት ያለባቸዉ ይህን ማንዋል እና የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን ባማከለ መልኩ መሆን እንዳለበት የሚያከራክር አይደለም፡፡ የአሁን አመልካች በድርጅቱ ማንዋል መሰረት የሠራተኛዉን መብት ከፍትሐብሔር ሕጉ እና ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ በተሻለ ሁኔታ ተጠቃሚ የሚያደርገዉ እስከሆነ ድረስ ተፈጻሚ መሆን ያለበት ይህ ማንዋል እንደሆነ ግልጽ ነዉ፡፡ በዚህ አግባብ የአሁን አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰኑትን ክፍያዎች ማየቱ ተገቢ ነዉ፡፡

በዚህ መሰረት መጀመሪያ መታየት ያለበት የስራ ስንብት ክፍያ ሲሆን የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር በኩባንያዉ ማንዋል ክፍል 1-ሀ ተራ ቁጥር 13.4 መሰረት የአሁን ተጠሪ የስንብት ክፍያ ተጠቃሚ እንደሆነ ሳይክድ ፣ ተጠሪዉ ለአምስት አመት በኩባንያዉ ዉስጥ ስላላገለገለ የስንብት ክፍያ አይገባዉም የሚል ነዉ፡፡ ነገር ግን የአሁን ተጠሪ ከሥራዉ የተሰናበተዉ በራሱ ፈቃድ ሳይሆን በአመልካች አነሳሽነት ከሕግ ዉጭ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 /አዋጅ ቁጥር 494/98 እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 39 /1/ /ሸ/ ተፈጻሚነት የለዉም፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች ተጠሪዉን ከሥራ ያሰናበተዉ ከሕግ ዉጭ በመሆኑ የኩባንያዉ ማንዋል በሚያመለክተዉ አግባብ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሰረት የስንብት ክፍያ ለተጠሪ ሊከፈል ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ለተጠሪ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ አግባብ የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፍለዉ ይገባል በማለት የሰጡት ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን የአሁን አመልካች የሥራ ስንብት ክፍያ ስንት ብር ለተጠሪዉ መከፈል አለበት የሚለዉ ስሌቱ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ ብር 35,146.23 የጠየቀ ሲሆን፣ የአሁን አመልካች በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር በአጠቃላይ የሥራ ስንብት ክፍያ መክፈል የለብንም የሚል ነዉ፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ተጠሪዉ የጠየቀዉን ገንዘብ በሙሉ እንዲከፍለዉ ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበዉ ይግባኝ ለተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ መክፈል የለብንም ፣ መክፈል ካለብን ደግሞ ተጠሪዉ የጠየቀዉን ገንዘብ በሙሉ ሳይሆን ብር 15,796.92 ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ በተመለከተ በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን አመልካች የሥራ ስንብት ክፍያ መክፈል የለብንም ከማለት ዉጭ ስሌቱን በተመለከተ በሥር ፍ/ቤት

www.abyssinialaw.com

ያቀረበዉ ተቃዉሞ ባለመኖሩ በዚህ ፍ/ቤት ደረጃ ማቅረብ አይችልም በማለት ወስኗል፡፡ ነገር ግን የአሁን አመልካች ለተጠሪዉ ሊከፍለዉ የሚገባዉ የሥራ ስንብት ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 40 አግባብ መሆን አለበት እንጂ የአሁን ተጠሪ ዳኝነት ስለጠየቀ ብቻ እሱ የጠየቀዉ ገንዘብ በሙሉ ሊወሰንለት ይገባል ማለት አይደለም፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ለተጠሪዉ የሥራ ስንብት ክፍያ መክፈል የለብንም በማለት አጠቃላዩን እየተቃወመ በመሆኑ ስሌቱን በተመለከተ ያቀረበዉ መቃወሚያ የለም ለማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ የአሁን አመልካች ለተጠሪዉ መክፈል ያለበት የሥራ ስንብት ክፍያ በሕጉ አግባብ ተሰልቶ ሊከፈለዉ ይገባል እንጂ ተጠሪ የጠየቀዉ ገንዘብ በሙሉ ሊወሰንለት የሚገባበት አግባብ የለም፡፡ የአሁን ተጠሪ ደመወዝ በወር ብር 9,977 /ዘጠኝ ሺህ ዘጠን መቶ ሰባ ሰባት/ እና ተጠሪዉ በአመልካች ኩባንያ ሁለት አመት ከዘጠኝ ወር ያገለገለ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 40 /1፣ 2/ መሰረት ሲሰላ የአሁን አመልካች ለተጠሪዉ መክፈል ያለበት የሥራ ስንብት ክፍያ ብር 15,796.91 /አስራ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከዘጠና አንድ ሳንትም/ ነው፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች ይህን ገንዘብ መወሰን ሲገባቸዉ ተጠሪዉ የጠየቀዉን ገንዘብ በሙሉ አመልካች እንዲከፍል መወሰናቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ ስለዚህ የአሁን አመልካች የሥራ ስንብት ክፍያ ብር 15,796.91 /አስራ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከዘጠና አንድ ሳንትም/ ለተጠሪ መክፈል አለበት ብለናል፡፡

በሌላ በኩል የካሳ ክፍያን በተመለከተ የአመልካች ኩባንያ ማንዋል ክፍል 1-ሀ በተራ ቁጥር 13.4 መሰረት በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 /4/ /ሀ/ መሰረት የካሳ ክፍያ ሊከፈለዉ እንደሚገባ ስለሚደነግግ፣ የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2574 /2/ መሰረት የሶስት ወር ደመወዝ ብቻ ነዉ መከፈል ያለበት በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ ስለዚህ በዚህ ረገድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ሕግ ድንጋጌ አግባብ የካሳ ክፍያዉን በማስላት የአሁን አመልካች ብር 59,862 /አምሳ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ሁለት/ ዉሳኔዉ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠዉ ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አይቻልም፡፡

ሌላዉ መታየት ያለበት ፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካች ኩባንያ ደንብ ተራ ቁጥር 1.4.3.2 መሰረት በማስላት የአሁን አመልካች ብር 21,400.66 /ሀያ አንድ ሺህ አራት መቶ ብር ከስልሳ ስድስት ሳንቲም/ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት የሰጡት ዉሳኔዎች በሕጉ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥራ ስንብት ክፍያ የገንዘብ ስሌትን በተመለከተ ብቻ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሳ ኔ**

1. ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.147858 በ09/02/2008 ዓ.ም የተሰጠዉ ዉሳኔ የሥራ ስንብት ክፍያን በተመለከተ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአሁን አመልካች የሥራ ስንብት ክፍያን በተመለከተ ብር 15,796.91 /አስራ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከዘጠና አንድ ሳንትም ብቻ ለተጠሪ ሊከፍለዉ ይገባል ብለናል፡፡
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሌሎች ክፍያዎችን በተመለከተ የሰጠዉ ዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
5. ህዳር 23 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠዉ የአፈጻጸም እግድ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
6. ግራቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 127154

መስከረም 23 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነአ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካቾች ፡- የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት -ወኪል ነ/ፈጅ ይግረም ነጋሽ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ካሳሁን በዛብህ -ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይን የሚመለከትና ጡረታ ለመውጣት ከመጠየቅ ጋር የተያያዘ ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው የስር ከሳሽ የነበሩት የአሁን ተጠሪ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ደሴ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገርም በአጭሩ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ለ31 ዓመታት ሳገለግል ቆይቼ እድሜዬ 55 ሲሞላ ጡረታ ለመውጣት ማህበራዊ ዋስትና ብጠይቅም ማህበራዊ ዋስትና ለአመልካች ድርጅት የግል ማህደሬን እንዲልክ በደብዳቤ ብጠይቅም አመልካች ድርጅት ለመላክ ፍቃደኛ አይደለምና የግል ማህደሬን እንዲልክ ይታዘዝልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው የአሁን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ በስራ አጋጣሚ በእጁ የገባ የአመልካች ንብረት ሳያስረክብ የግል ማህደሩን ለመላክ አልችልም ስለሆነም የተጠሪ ክስ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኃላ ጉዳዩን በመመርመር ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ንብረት አልተረከብኩም አላሉም አስረክቤያለሁ ቢሉም ያቀረቡት ማስረጃ ካለመኖሩም በተጨማሪ ያቀረባቸው ምስክሮች ተጠሪ ሊያስረክቡ ሲሄዱ ቢሯቸው ክፍት ሆኖ ስላገኙት ተመለሱ ከማለት ውጪ ንብረት ስለማስረከባቸው አላስረዱም ብሎ ተጠሪ የአመልካችን ድርጅት ንብረት ሳያስረክቡ የግል ማህደሬ ለማህበራዊ ዋስትና ይላክልኝ ዘንድ ይታዘዝልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

www.abyssinialaw.com

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ቅሬታው መ/ሰጪ'ን መልስ እንዲያቀርብ በማድረግ አከራክረዋል ። ቀጥሎም ተጠሪ ከአመልካች የተረከበውን ንብረት እንዲያስረክብ የስር ፍ/ቤት መወሰኑ ተገቢ ቢሆንም ንብረት ባለማስረከቡ ብቻ ግን ለጡረታው አፈጻጸም ከማህበራዊ ዋስትና እንዲላክ የታዘዘውን የግል ማህደር አለመላክ የመንግስት ሰራተኛ ጡረታ አዋጅ ቁጥር. 345/95 አንቀጽ 47/2/ን የሚቃረን ነው በማለት የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር አመልካች የተጠሪን የግል ማህደር ለማህበራዊ ዋስትና ይላክ በማለት ወሰነ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁኑ አመልካች ለአማራ ክልል፤ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታውን ቢያቀርብም የዞኑ ከ/ፍ/ቤትን ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲያርም ጉዳዩ የቀረበለት የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ የሚጣራ መሰረታዊ የህግ ጭብጥ የለውም በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 /1/ን በመጥቀስ ሰርዞታል ።

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህን በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም እንዲታረም ሲሆን አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪ የአመልካችን ንብረት ሳያስረክብ አመልካች የተጠሪን የግል ማህደር የማስረከብ ግዴታ ከመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ. 345/95 አንጻር ተጠሪ ባለበት ለመመርመር ቅሬታው ተጠሪን ያስቀርባል ብሎ ግራ ቀኙ ቀርበው የጽሁፍ ክርክራቸውን አድርገዋል።

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን አቤቱታው ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ብቻ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል።

በመሰረቱ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ሲሰሩ በስራው አጋጣሚ በእጃቸው የገባውን የአመልካች ማንኛውም ንብረት የማስረከብ ግዴታ አለባቸው ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ተቀጥረው ሲሰሩ በስራ አጋጣሚ የገባ የአመልካች ንብረት እንዳለ የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪ አስረክቤያለሁ ሲሉ አመልካች አላስረከቡም ብለዋል።

ዋናው ጉዳይ ንብረት ማስረከብ ያለማስረከብ ጉዳይ ለተጠሪ ጡረታ መውጫ ፎርማሊቲ ከማህበራዊ ዋስትና የተጠየቀን የግል ማህደር አመልካች አልሰጥም ማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለው ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ነው አመልካች በህ/ስምምነታችን አንቀጽ 9/7/ መሰረት ሰራተኛ ያለበትን ንብረት ሳያስረክብ ከማህበራዊ ዋስትና የታዘዘው የተጠሪን የግል ማህደር መላክ ይከለክላል ሲል ተጠሪ በበኩላቸው የህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 9/7/ የሚከለክለው መሸኛና የስራ ልምድ ነው እንጂ በማህበራዊ ዋስትና የተጠየቀን የግል ማህደር አይደለም ብለዋል በመሆኑም ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሰው የህብረት ስምምነት በተዋዋዮች መሀከል ህግ

www.abyssinialaw.com

በመሆኑ ለማየት የሚቻል ቢሆንም ባለመቅረቡ አልታየም፡፡የህብረት ስምምነት አመልካች ክርክር የሚደግፍ ቢሆንም የህብረት ስምምነት በህግ ለሰራተኞች የሚሰጠው መብት የበለጠ የሚጠቅሞ ሆኖ ካልተገኘ ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 134/2/ ተፈጻሚ እንደማይሆን ይደነግጋል፡፡

ሌላው ግን የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ. 345/95ን ስንመለከት በአንቀጽ 47/2 ላይ ማንኛውንም አሰሪ /ግለሰብ/ ቀርቦ አስተያየትና መረጃ ወይም የጽሁፍ ማስረጃ እንዲሰጥ በማህበራዊ ዋስትና /በባለስልጣኑ/ ሲታዘዝ የመስጠት ግዴታ አለበት ይልና በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 44 ላይ  እንደተመለከተው የጡረታ አበል የማግኘት መብት የዕዳ መያዣ ሊደረግ ወይም በውርስ ወይም በማናቸውም መንገድ ሊተላለፍ አይችልም ብሎ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 55/2/ ላይም ይህንን አዋጅ የሚቃረኑ ህጎችና ማሚያዎች ይህንን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም ይላል፡፡

ይህንን ህግ መነሻ ስናደርግ ተጠሪ እንዳቀረቡት ዝርዝር የህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 9/7/ ሰራተኛው ንብረት ባላስረከበ ጊዜ አሰሪ ለመያዝ የሚችለው የስራ ልምድና መሸኛ ካልሆነ በስተቀር በማህበራዊ ዋስትና የሚታዘዘውን ማንኛውንም ለጡረታ መውጫ የሚያስፈልግ ማስረጃ የመስጠት ግዴታ በመንግስት ሰራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95 ላይ የተጣለበት ስለሆነ ይህንን ላለመስጠት መስማማት የማይችልና የጡረታ መብትን የማግኘት መብት በእዳ መያዣ ሊደረግ እንደማይገባ ከመደንገጉም በተጨማሪ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 55/2 ላይም ይህንን  ድንጋጌ የሚቃረን ህ/ስምምነት ተፈጻሚ እንደማይሆን የደነገገ በመሆኑ ተጠሪ የአመልካችን ንብረት ያልመለሰ ስለሆነ ሳይመልስ የተጠሪን የግል ማህደር ለማህበራዊ ዋስትና ሊልክ አይገባም በማለት የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ዉሳኔ በመሻር የስር ከ/ፍ/ቤት አመልካች የተጠሪን ማህደር ለማህበራዊ ዋስትና እንዲልክ መወሰኑንና የክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ጥሰት አለበት የሚያሰኝ ጉድለት ያላገኘን በመሆኑ ውሳኔው የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም

በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቀ 23359/ ታህሳስ 10 2008 ዓ.ም የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 03-13048 በቀን ሚያዚያ6 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ይህ ውሳኔ አመልካች በተጠሪ ላይ አለኝ የሚሉት ንብረት ካለ ከመጠየቅ አያግዳቸውም
3. በየደረጃ ለሚገኙ ፍ/ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ ይተላለፍ
4. በዚህ ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል ይጻፍ
5. ግራ ቀኙ የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ

መዝገቡ ተዘግቷል ተመላሽ ይደረግ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.125778

መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ክፍለጽዮን ማሞ

ሰናይት አድነዉ

አመልካች...........ሲዉ ኢንፍራስትራክቸር

ተጠሪዎች........... 1. አቶ መሳይ ወ/ገብርኤል

2. አቶ አሉላ አበጋዘአ

3. አቶ በፍርድ ጥላሁን

4. አቶ ዘሪሁን ከድር

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅን መነሻ ያደረገ የሥራ ስንብትን የሚመለከት ክርክር ነዉ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡--በሥር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች የሥር ከሳሾች፣ የአሁን አመልካች የሥር ተከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የሥር ከሳሾች በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከሳሾች በተከሳሽ ድርጅት በዳም ትራክ ኦፕሬተር ተቀጥረን ሥራችንን በቅንነትና በታማኝነት እየሠራን እያለ እኛ ደንብ በመጣስ የድርጅቱ ተሽከርካሪ ታንከር ነዳጅ እንዳይሰረቅ የሚያደርገዉን የተሻለ የነዳጅ መያዣ ታንከር መቆጣጠሪያ መሳሪያ /የደህንነት መጠበቂያ/ ላይ ሆን ብለን ያደረሰን ጉዳት ሳይኖር ጉዳት አድርሳችኋል በማለት የሥራ ዉላችንን በሕገ ወጥ መንገድ በማቋረጥ ስላሰናበተን ተከሳሽ ተገቢዉን ክፍያዎች እንዲከፍለን፣ የሥራ ልምድ እንዲሰጠን እንዲወሰንልን በማለት ከሷል፡፡ የሥር ተከሳሽ አሻሽሎ ባቀረበዉ መልስ 1ኛ ከሳሽ በ9/08/2007 ዓ.ም፣ 2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ከሳሾች በ10/08/2007 ዓ.ም እያንዳንዳቸዉ ለሥራ በተረከቡት ተሽከርካሪ ላይ የነዳጅ ስርቆትን ለመከላከል በታንኩ ላይ የተሰራዉን መሳሪያ ላይ ጉዳት ማድረሳቸዉ በድርጅቱ የቴክኒክ ክፍል ተጣርቶ የተረጋገጠ ሲሆን ከሳሾች ጉዳቱ የደረሰዉ በሌላ ሰዉ መሆኑን ባለማረጋገጣቸዉ፣ በድርጅቱ ንብረት ላይ ጉዳት በማድረሳቸዉ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 /1/ /ሸ፣ ቀ/ እና በድርጅቱ ዉስጠ ደንብ መሰረት ከሥራ የተሰናበቱ በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ ከሳሾች የጠየቁትን ክፍያዎች ለመክፈል ኃላፊነት የለብንም በማለት ተከራክሯል፡፡

www.abyssinialaw.com

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን የሰዉ ምስክሮች በመስማት፣ የሰነድ ማስረጃም በመመዘን፣ በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ የከሳሾችን የሥራ ዉል ያቋረጠዉ ከሕግ ዉጭ በመሆኑ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነዉ በማለት ለከሳሾች በሕጉ አግባብ ክፍያዎችን እንዲከፍላቸዉ ወስኗል፡፡

የሥር ተከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የሰበር አቤቱታ ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ቅሬታዉ ተቀባይነት ሳይገኝ ዉድቅ ተደርጎ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔን በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ24/07/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉም ይዘት፡-- የሥር ፍ/ቤት አመልካች መልሱን እንዲያሻሽል በፈቀደለት መሰረት በ22/12/2007 ዓ.ም የተጻፈዉን መልስ ያቀረበ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ግን መልሱን ከመሻሻሉ በፊት የተያያዘዉን የሰነድ ማስረጃ ከተሻሻለዉ የመከላከያ መልስ ማስረጃ ጋር እያነጻጸረ የሰነድ ማስረጃዎቹ እምነት የማይጣልባቸዉ ናቸዉ በማለት የአመልካችን ክርክር ዉድቅ ማድረጉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 /1/ ያላገናዘበ ዉሳኔ ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪዎች በመመሳጠር ለነዳጅ ስርቆት እንዲያመቻቸዉ የድርጅቱን አራት መኪኖች የነዳጅ ታንከር በተከታታይ ቀናት በ9/8/2007 ዓ.ም እና በ10/8/2007 ዓ.ም ሰብረዉት እና ቀደዉት ጉዳት ማድረሳቸዉን በሰነድ ማስረጃ እና በሰዉ ምስክሮች አረጋግጠዉ እያለ የሥር ፍ/ቤት እነዚህን የሰነድ ማስረጃዎች መርምሮ አስፈላጊም ከሆነ ገለልተኛ ባለሙያዎችን በተጨማሪ ማስረጃነት አስቀርቦ ምርመራ ማድረግ እየቻለ ማስረጃዉን በማለፍ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ መብት ማለፋቸዉ በመሆኑ እንዲሻርልን፡፡ ስለዚህ የአሁን አመልካች ተጠሪዎች በድርጅቱ መኪኖች የነዳጅ ታንከር ላይ ጉዳት እና ጥፋት በማድረሳቸዉ ስንብቱ ሕጋዊ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 /1/ /ሸ፣ ቀ/ መሰረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልን፣ ክፍያንም በተመለከተ ቅሬታዉን በማቅረብ አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ይህን ጉዳይ በማየት ፣ተጠሪዎች ጥፋት ለመፈጸማቸዉ አልተረጋገጠም ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች ስንብቱ ሕገ ወጥ ነዉ በሚል የመወሰኑን አግባብነት ከሰበር መ.ቁ.112733 አንጻር፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት የአሁን ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ በታዘዘዉ መሰረት ግንቦት 12 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት፡--የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች መኪኖች የነዳጅ መያዣ ክፍል ላይ ጉዳት ያላደረስን ሲሆን የአሁን አመልካች ያለጥፋታችን የሥራ ዉላችንን ማቋረጡ ያለአግባብ በመሆኑ የቀረበዉ ቅሬታዉ ዉድቅ እንዲደረግልን እና የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካችም የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች የተጠሪዎችን የሥራ ዉል በማቋረጥ ከሥራ ያሰናበታቸዉ ተጠሪዎች ከድርጅቱ መኪኖች ታንከር ላይ ነዳጅ እንዳይሰረቅ የሚከላከለዉን መቆጣጠሪያ መሳሪያ ላይ ጉዳት በማድረሳቸዉ በአመልካች ንብረት ላይ ሆን ብለዉ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ባደረሱት ጉዳት ምክንያት እንደሆነ ከሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች የተለያዩ ምክንያቶችን በመዘርዘር በመኪኖቹ የነዳጅ ታንከር ላይ ጉዳት አለማድረሳቸዉን እና ስንብቱ ሕገ ወጥ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረበዉን መልስ ለማሻሻል ጥያቄ አቅርበዉ ሲፈቀድለት፣ በተሻሻለዉ መልስ የአሁን ተጠሪዎች በመኪኖቹ የነዳጅ ታንከር ላይ ጉዳት አደረሱ በማለት መጀመሪያ ባቀረበዉ ክስ ላይ የጠቀሰዉን ቀን እና መጀመሪያ የተጻፈዉን የስራ የስንብት ደብዳቤ በመቀየር ሌላ የስራ የስንብት ደብዳቤ አያይዞ ያቀረበ መሆኑን በሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፡፡

በዚህ ረገድ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 /1፣ 3/ እንደሚደነግገዉ የክሱ ወይም የመከላከያ መልሱ ማሻሻል አስቀድመዉ የቀረበዉን ሁኔታ የሚያብራራ ወይም የቀረበዉን ክርክር በተሻሻለ ዓይነት ገልጾ የሚያስረዳ ወይም ትክክለኛ ፍትሕን ለመስጠት የሚረዳ መሆኑን ፍ/ቤቱ ከገመተ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት የቀረበዉን ክስ ወይም መልስ እንዲሻሻል እንደሚፈቅድ ያመለክታል፡፡ በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች መልስ ለማሻሻል አቤቱታ አቅርቦ የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ የፈቀደለት ሲሆን፣ አመልካችም በ22/12/2007 ዓ.ም የተጻፈ የተሻሻለ መልስ ያቀረበ መሆኑን ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን የአሁን አመልካች ባቀረበዉ መልስ አስቀድመዉ የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች መኪኖች የነዳጅ ታንከር ላይ ጉዳት አድርሰዋል በማለት ተጠሪዎችን ከሥራ ያሰናበተባቸዉን የስንበት ደብደቤ ሙሉ በሙሉ በመቀየር ሌላ የስንብት ደብዳቤ /ሌላ አዲስ ማስረጃ ፈጥሮ/ እንዳቀረበ ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ መረዳት ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት የአሁን አመልካች አስቀድመዉ ለተጠሪዎች የሰጣቸዉን የስንብት ደብዳቤ በመቀየር፣ ተጠሪዎች በመኪኖቹ የነዳጅ ታንከር ላይ ጉዳት አድርሷል ያለዉን ቀን በመቀየር ያቀረበ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች ክሳቸዉን ሲመሰርቱ የአሁን አመልካች የጻፈላቸዉን የስንብት ደብዳቤ እና በስንብት ደብዳቤዉ ላይ በድርጅቱ ንብረት ላይ ጉዳት አድርሳችኋል የተባለዉን ቀን እና ሁኔታ መሰረት በማድረግ እንደሆነ ግልጽ ነዉ፡፡ የአሁን አመልካች አሻሽሎ ባቀረበዉ መልስ ይህን ሁሉ ቀይሮ መልሱን አሻሽሎ አቀረበ ማለት ተጠሪዎችን ከሥራ ከማሰናበቱ በፊት በትክክል አጣርቶ እርምጃ መዉሰድ ሲገባዉ አሁን ክርክር ከተጀመረ በኋላ አስቀድመዉ ተጠሪዎችን ካሰናበታቸዉ ደብዳቤ ሌላ ደብዳቤ መጻፉ ከላይ የተመለከተዉን

www.abyssinialaw.com

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 /1፣ 3/ አላማ እና መንፈስ የሚያሟላ ሁኖ አይታይም፡፡ አመልካች ራሱ በጻፈዉ የስንብት ደብዳቤ መሰረት በማድረግ የአመልካችን እርምጃ በመቃወም ተጠሪዎች ክስ ከመሰረቱ በኋላ አመልካች ሌላ የስንብት ደብዳቤ በማዘጋጀት መልሱን አሻሽሎ ማቅረቡ በቀድሞ መልስ የቀረበዉን ሁኔታ የሚያብራራ ወይም የቀረበዉን ክርክር በተሻሻለ ዓይነት ገልጾ የሚያስረዳ ወይም ትክክለኛ ፍትሕን ለመስጠት የሚረዳ ሳይሆን አዲስ ክርክር እንደማቅረብ የሚገመት ነዉ፡፡ እንዲያዉም ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክር ተገቢ መከላከያ መልስ ማቅረብ ሳይሆን ሌላ የማይገናኝ አዲስ ክርክር እንደማቅረብ የሚቆጠር ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር ይህን ጉዳይ ማየቱ አስፈላጊ ነዉ፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች መኪኖች የነዳጅ ታንከር ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም አለማድረሳቸዉ በተመለከተ የግራ ቀኙን የሰዉ ምስክሮችን በመስማት የሰነድ ማስረጃ በመመዘን ዉሳኔ የሰጠ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ተጠሪዎች በድርጅቱ መኪኖች የነዳጅ ታንክር ላይ ጉዳት አድርሷል በማለት ከሥራ ያሰናብታቸዉ እንጂ የቀረበዉ የሰነድ ማስረጃ እና የሰዉ ምስክሮች እምነት የሚጣልባቸዉ እንዳልሆኑ በማረጋገጥ፣ የሥራ ስንበቱ ሕገ ወጥ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ማስረጃን በመመዘን ዉሳኔ መስጠቱን ችሎቱ ተገንዝቧል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ተጠሪዎችን በሕጉ አግባብ በጥፋታቸዉ የሥራ ዉላቸዉን በማቋረጥ ያሰናበታቸዉ እና ስንብቱ ህጋዊ መሆኑን የማስረዳት ሸክሙን ያልተወጣ መሆኑን ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ማየት ይቻላል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር መሰረት ተጠሪዎች በድርጅቱ መኪኖች የነዳጅ ታንከር መቆጣጠሪያ መሳሪያ ላይ ጉዳት ማድረሳቸዉን ባላረጋገጠበት የተጠሪዎች የሥራ ስንብት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 /1/ /ሸ፣ ቀ/ መሰረት ሕጋዊ ነዉ በማለት ያቀረበዉ ክርክር የድንጋጌዉን መንፈስና ይዘት ያላገናዘበ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ ያስቀርባል ሲባል በተያዘዉ ጭብጥ ጉዳዩን በሰበር መ.ቁ.112733 ላይ ከተሰጠዉ ዉሳኔ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ በሰበር መ.ቁ.112733 ላይ አመልካች ሲዉ ኢንፍራስትራክቸር ሲሆን፣ ተጠሪ አቶ ጴጥሮስ ስዩም በመሆን፣ ችሎቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በ4/6/2008 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን ተጠሪ ከአመልካች መኪና ነዳጅ እንዳይሰረቅ ለመከላከል የሚያገለግለዉን መቆጣጠሪያ መሳሪያ ላይ ጉዳት ማድረሱ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች የሥራ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነዉ በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነዉ በማለት የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ በመሻር የአሁን አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተዉ በሕጋዊ መንገድ ነዉ፣ የሥራ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ በማለት ወስኗል፡፡ በሰበር መ.ቁ.112733 እና አሁን በተያዘዉ መዝገብ ላይ ያለዉ ክርክር ሲታይ በዚህ መዝገብ የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች መኪኖች ነዳጅ እንዳይሰረቅ የሚያገለግለዉን መሳሪያ ላይ ጉዳት ማድረሳቸዉ በማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ በሰበር መዝገብ ቁጥር 112733 ውሳኔ ካገኘው

www.abyssinialaw.com

ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ጭብጥ ነዉ ለማለት ስለማይቻል በዚህ ጉዳይ ላይ አስገዳጅነት ያለዉ የሕግ ትርጉም አይደለም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች የአሁን ተጠሪዎችን ከድርጅቱ መኪኖች ታንከር ነዳጅ እንዳይሰረቅ ለመቆጣጠር የሚያገለግለዉን መሳሪያ ላይ ጉዳት ማድረሳቸዉ በማስረጃ ባልተረጋገጠበት የሥራ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነዉ በማለት አመልካች ለተጠሪዎች በሕጉ አግባብ ተገቢዉን ክፍያዎች እንዲከፍላቸዉ የሰጡት ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት ስለማይቻል የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>**ዉ ሳ ኔ**</u>

1. የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.07323 በ15/04/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.19019 በ13/05/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ እና የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.66951 በ20/7/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. ሚያዝያ 5 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠዉ የአፈጻጸም እግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.116038

ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብዩ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ፍራውን ኮንስትራክሽን ህንጻ ተቋራጭ -የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- 1. አቶ ካህሳይ ገ/ሄር
2. አቶ ተመስገን ዘነበ } የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀረመው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካች ላይ በመቐሌ ሰሜን ክፍለ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- 1ኛው ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በፎርማን ስራ መደብ ላይ ማናጀር ሁነው ተቀጥረው ከጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ/ም እስከ ሕዳር 30 ቀን 2006 ዓ/ም ድረስ በወር ብር 2,500.00(ሁለት ሺ.ህ አምስት መቶ ብር) እየተከፈላቸው ሰርተው የአስራ ሶስት ወራት ደመወዝ ብር 32,500.00(ሰላሳ ሁለት ሺ.ህ አምስት መቶ ብር) ያልተከፈላቸው መሆኑንና በዚህ ድርጅት ውስጥ ከፎርማን የስራ መደብ ማናጀር ሁነው ከመቀጠራቸው በፊት በነበራቸው የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ሞያ ስራ የአመልካቹ በሆነውና በአጉላዕ ከተማ ውስጥ በሚገኘው ግንባታ የኤሌክትሪክ ስራውን ለመስራት በቃል በአደረጉት ስምምነት መሰረት ስራውን ሰርተው አስረክበው እያለ አመልካች ብር 3000.00 ብቻ ከፍሏቸው ቀሪውን ብር 5260.00(አምስት ሺ.ህ ሁለት መቶ ስልሳ ብር) በስምምነቱ መሰረት ያልከፈላቸው መሆኑን ጠቅሰው በድምሩ ብር 37,760.0 (ሰላሳ ሰባት ሺ.ህ ሰባት መቶ ስልሳ ብር) እንዲከፍላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ባላቸው የብረታ ብረት ንግድ ድርጅት መነሻ ከአመልካች ድርጅት ጋር ሁለት መዝጊያ

www.abyssinialaw.com

በር በብር 7700.00(ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ብር) ለመስራት ስምምነት አድርገው ቀብድ ብር 300.00(ሶስት መቶ ብር) ተቀብለው ስራውን ሰርተው ሰኔ 26 ቀን 2005 ዓ/ም ያስረከቡ ቢሆንም ቀሪውን ገንዘብ ብር 7400.00(ሰባት ሺህ አራት መቶ ብር) አመልካች ያልከፈላቸው መሆኑን ጠቅሰው ይህንኑ ገንዘብ አመልካች እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስም ይርጋን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወያነት ያነሳ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ረገድ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ ጋር ምንም አይነት የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት የሌለው መሆኑን፣ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራ ሰርቼአለሁ በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄም ስራውን ለመስራት የሚያስችላቸው የንግድ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ሳይቀርብ የቀረበ መሆኑን፣የ2ኛ ተጠሪ ክስም የውል ግንኙነት ሳይኖር ተጠሪው የአመልካቹ ድርጅት ሰራተኛ ሁነው ለሰሩት ስራ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የማይገባ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በአመልካች በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አልፎ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት ጉዳዩን መርምሮ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ውስጥ የስራ መሪ ሁነው መስራታቸው መረጋገጡን፣ የስራ መሪ ሁነው ከመቀጠራቸው በፊት ደግሞ አመልካቹ ሲሰራ ከነበረው ግንባታ ንዑስ ስራ ተቆራጭ ሁነው ኤሌክትሪክ ኢንስቶል የማድረግ ስራ የሰሩና ለሰሩት ስራም አመልካችም መከፈል ያለበትን ክፍያ ያልከፈላቸው መሆኑ መረጋገጡን፣ የ2ኛ ተጠሪ ክስም በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ዘርዝሮና የአመልካች ድርጅት የ1ኛ ተጠሪን ደመወዝ ስድስት ወር ስላለፈው እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት ያቀረበው ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ሐ) ስር የተመለከውን የሁለት አመት ጊዜ ያላገናዘበ መሆኑን፣ የ2ኛ ተጠሪን የክፍያ ጥያቄ በተመለከተም አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472(3) ድንጋጌ መሰረት ስለመክፈሉ የሚያሳይ የጽሑፍ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን ጠቅሶ ውድቅ በማድረግ አመልካችን ለተጠሪዎች ክስ ኃላፊ አድርጎ በተጠየቀው ዳኝነት መሰረት ገንዘቡን ለተጠሪዎች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለመቐሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የወረዳው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ አጣሪ ችሎቱ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት በመዝጋቱ ይህንኑ የሰበር አቤቱታ ለዚሀ ችሎት አቅርቧል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ጋር የነበራቸው ግንኙነት የአሰሪና ሰራተኛ ሁኖ እያለ ተጠሪው የስራ መሪ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ መሆኑን፣ የደመወዝ ክፍያ ጥያቄው በይርጋ ይታገዳል እንዲሁም

www.abyssinialaw.com

ስድስት ወር ያለፈበት በመሆኑ እንደተከፈለ ይቆጠራል ተብሎ የቀረበው የአመልካች ክርክር በበታች ፍርድ ቤቶች መታለፉ ያላግባብ መሆኑንና 2ኛው ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ሁነው ክሱን በአንድ ላይ ለማቅረብ የሚያስችላቸው ህጋዊ ምክንያት ሳይኖር ክሱን አንድ ላይ ማቅረባቸውም ሆነ የተጠሪውንና የአመልካቹ ግንኙነት የአሰሪና ሰራተኛ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ሊታገድ የሚገባው መሆኑን ዘርዝሮ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲለወጥ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ጭብጦች፡-

1. አንደኛ ተጠሪ የስራ መሪ ናቸው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም?፣
2. 1ኛ ተጠሪ የስራ መሪ ከተባሉ የጠየቁት የአስራ ሶስት ወራት ደመወዝ ክፍያ ጥያቄ በይርጋ ወይም በክፍያ ግምት ቀሪ የሚሆንበት አግባብ አለ? ወይስ የለም?
3. ተጠሪዎች ክሱን በአንድ ላይ ማቅረባቸው ስነ ስርዓታዊ ነው ወይስ አይደለም የሚሉትን ነጥቦችን የሚመለከቱ ሁነው አግኝተናል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- 1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክስ ሲመሰርቱ ከአመልካች ድርጅት ከጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ/ም እስከ ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ/ም የስራ መሪ የነበሩ መሆኑንና በዚህ የስራ መደብ ከመቀጠራቸው በፊት ደግሞ በነበራቸው ሙያ መሰረት ከአመልካች ድርጅት ጋር የንዑስ ስራ ተቋራጭነት ውል አድርገው የኤሌክትሪክ "ኢንስታሌሽን" ስራ የሰሩ መሆኑን ገልፀው ሲሆን ይህ የተጠሪው የክስ ይዘት በግልጽ የሚያሳየውም ተጠሪው ከአመልካች ጋር በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ የግንኙነት አይነቶች የነበራቸው መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ይህንኑ የተጠሪን የክስ ፍሬ ነገር በመካድ ከተጠሪው ጋር የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ካልሆነ በስተቀር ሌላ አይነት ግንኙነት ያልነበረው መሆኑን ጠቅሶ የተከራከረ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር መሰረት አድርጎ ተገቢ ነው ያለውን ጭብጥ ይዞ ተጠሪው በአመልካች ድርጅት በሚከናወነው ግንባታ ላይ ንዑስ ስራ ተቋራጭ ሁነው የኤሌክትሪክ "ኢንስቶሌሽን" ስራ ከጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ/ም በፊት በነሐሴ ወር 2004 እና በመስከረም ወር 2005 ዓ/ም የሰሩ መሆኑንና ከጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ/ም እስከ ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ/ም ድረስ በአመልካች ድርጅት የስራ መሪ ሁነው የሰሩ መሆኑን ተጠሪው በማስረጃዎቹ ያስረዱ መሆኑን፣ አመልካች ድርጅት ግን

www.abyssinialaw.com

በተጠሪ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎች ለማስተባበል ያልቻለ መሆኑን በውሳኔው ላይ በግልጽ አስፍሮአል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተጠሪውን የስራ መሪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰውም ተጠሪው በአመልካች ድርጅት በነበራቸው የፎርማን ስራ መደብ ሰራተኛን የማሰናበት፣ የመቅጠር እንዲሁም አስተዳደራዊ ስራዎችን ያካሂዱ የነበሩ መሆኑ በምስክሮች ቃል መረጋገጡን መሰረት አድርጎና የአዋጅ ቁጥር 377/96 ማሻሻያ በሆነው አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀፅ 2(ሐ) ስር የሰፈውን ድንጋጌ ይዘት በመመልከት መሆኑን ውሳኔው ያሳያል፡፡ ይኼው የሥር ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ በስራ መደቡ ሲያከናውኗቸው የነበሯቸው ተግባራት፤ ሰራተኛን የማሰናበት፣ የመቅጠርና እንዲሁም ሌሎች አስተዳደራዊ ስራዎችን የመስራት ጉዳዮች የፍሬ ነገር ማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ያገኙ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያስገነዝባል፡፡

ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጧቸው እነኚህ ነጥቦች በዚህ ችሎት ሊለወጡ የማይችሉ መሆኑን ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች ከተሰጠው ስልጣን አድማስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በፎርማንነት ሲሰሩ ሰራተኛን የማሰናበት፣ የመቅጠርና እንዲሁም ሌሎች አስተዳደራዊ ስራዎችን የሚመለከቱ ተግባራትን ሲያከናወኑ ነበር ተብሎ ከተረጋገጠ ደግሞ ቀጥሎ መታየት ያለበት የሕግ ጥያቄ እነዚህ ተግባራትን ማከናወን አንድን ተቀጣሪ የስራ መሪ ነው ለማለት ያስችላል? ወይስ አያስችልም? የሚለው ይሆናል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከት ምላሽ ማግኘት የሚቻለው በሕጉ የተቀመጡትን መለኪያዎችን በመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሕግ የአዋጅ ቁጥር 377/96 በአዋጅ ቁጥር ቁጥር 494/98 እንደተሻሻለው ሲሆን የአዋጁ አንቀጽ 3(2(ሐ) ሲታይም የሥራ መሪ ማለት በሕግ ወይም እንደ ድርጅቱ የሥራ ፀባይ በአሠሪው በተሰጠ የውክልና ሥልጣን መሠረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣትና የማስፈጸም፣ ከእነዚሁ በተጨማሪ ወይም እነዚህኑ ሳይጨምር ሠራተኛን የመቅጠር፣ የማዘዋወር፣ የማገድ፣ የማሰናበት፣ የመመደብ ወይም የሥነ ሥርዓት ዕርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውንና የሚወስን ግለሰብን የሚመለከቱ ሲሆን፤ እንዲሁም እነዚህን የሥራ አመራር ጉዳዮች አስመልክቶ የአሠሪውን ጥቅም ለመጠበቅ አሠሪው ሊወስደው ስለሚገባው ዕርምጃ በራሱ የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብ ባለሙያ የሥራ ኃላፊንም ይጨምራል፤ በማለት ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ከዚሁ የሕጉ ድንጋጌና ከማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2(1) ድንጋጌ ይዘት መረዳት የሚቻለው አንድ ሠራተኛ የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የሚያወጣና የሚያስፈጽም፣ ሠራተኛን የሚቀጥርና የሚያሰናብት፣ የሠራተኞችን የሥራ ዕድገት የሚወስን ከደረጃ ዝቅ የሚያደርግ፣ በሠራተኞች ላይ የሥነ ሥርዓት ዕርምጃ የመውሰድ ተግባራትን የሚያከናውን ከሆነ ወይም

www.abyssinialaw.com

የሥራ አመራር ጉዳዮች አስመልክቶ ለአሠሪው የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብ ከሆነ የሥራ መሪ ሊባል የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ሠራተኛው ከእነዚህ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ሥራዎችን የሚሠራ መሆኑ በማስረጃ መረጋገጥ ያለበት ሲሆን በሕጉ አግባብ ማስረጃ ቀርቦ በሕጉ የተመለከቱት መስፈርቶች መኖራቸው ከተረጋገጠ ደግሞ በአሰሪውና በተቀጣሪው መካከል ያለው ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 377/96 የሚገዛበት አግባብ አይኖርም፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከመተው የበታች ፍርድ ቤቶች 1ኛ ተጠሪ በፎርማንነት ሲሰሩ ሰራተኛን የማሰናበት፣ የመቅጠርና እንዲሁም ሌሎች አስተዳደራዊ ስራዎችን የሚመለከቱ ተግባራትን ሲያከናወኑ የነበሩ መሆኑን በሚገባ አረጋግጠው ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አግባብ አይገዛም በማለት መደምደማቸው የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት ስላለገኘን በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- እንደሚታወቀው በአገራችን የሥራ መሪና የአሠሪ ግንኙነትን በአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች አግባብ የማይገዛ ስለመሆኑ ከመደንገጉ ውጪ ይህንኑ ግንኙነት እንዲገዛ ተብሎ ተለይቶ የተቀረፀ ሕግ የለም፡፡

የሥራ መሪን የሚመለከት ሕግ ከሌለ ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚችሉትና በተግባር እየተሰራባቸው ያሉት ደንቦች የሥራ ውል፣ የሥራ ደንብና የፍትሐ ብሔር ሕጉ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ የሥራ ውል አሠሪውና የሥራ መሪው በጽሑፍ በሚያርጉት ስምምነት የሚፈጸም ሁኖ ግራ ቀኙ በነፃ ፈቃዳቸው መብትና ግዴታቸውን የሚዘረዝሩበት ሰነድ በመሆኑ የሥራ መሪውን መሠረታዊ የሥራ መብቶች የሚያስጠብቅ እስከሆነ ድረስ ቀዳሚ ተፈጻሚነት ሊያገኝ የሚገባው ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ስምምነቶች የስራ መሪውን መብት ለማስጠበቅ የሚችሉትን ድንጋጌዎች ለይተው የሚያስቀምጡበትና በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ የተቀመጡ የሰራተኛ መብትና ጥቅሞችም ለስራ መሪው ተፈፃሚ እንዲሆኑ የሚያደርጉበት አግባብ መኖሩን በተግባር ይታያል፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 84661 የተሰጠው የዚህ ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉምም ይህንኑ የሚያሳይ ነው፡፡ የሥራ ደንብ ደግሞ የአሠሪውንና የሥራ መሪውን ግንኙነት የሚመለከት ራሱን የቻለ የውስጥ ደንብ ካለ ተፈጻሚ የሚሆንበትን አግባብ የሚመለከት ሁኖ ደንቡ በድርጅቱ የሥራ ፀባይ የሥራ መሪዎች የሆኑትን ሠራተኞች ገልጾ በመደንገግ ያላቸውን መብት፣ ግዴታና ልዩ ጥቅም በስፋት እንዲገዛ አድርጎ የሚዘጋጅ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሌላውና የመጨረሻው የአሠሪና የሥራ መሪ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው የህግ ማዕቀፍ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ከአንቀጽ 2512 እስከ 2593 ያሉት "ስለ ሥራ ውል በጠቅላላው" የተመለከቱ ድንጋጌዎችን የያዘው ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የፍትሐ ብሔር ሕጉ በወጣበት ጊዜ ያሉትን የሥራ ግንኙነቶች ለማስተዳደር የወጡ ሲሆኑ፣ በይዘታቸው የሥራ መሪ እንዳይገዛባቸው የሚከለክል ድንጋጌ ስላልያዙና ስላልተሻሩ የሥራ መሪን ግንኙነት እንደሚገዙ ይታመናል፡፡

www.abyssinialaw.com

በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 21329 ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም.፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 27704 ጥቅምት 5 ቀን 2000 ዓ.ም.፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 15531 የካቲት 6 ቀን 1999 ዓ.ም.፣በሰበር መዝገብ ቁጥር 15815 ታኅሣሥ 10 ቀን 1998 ዓ.ም. የተሰጡ አስዳጅ የሕግ ትርጉሞችን ሰጥቷል፡፡

የፍትሐ ብሔር ሕጉ የአሠሪና የሥራ መሪን ግንኙነት የሚገዛ ነው ከተባለ ደግሞ በሕጉ አግባብ የሚቀርቡ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክሮች እልባት ማግኘት ያለባቸው በዚሁ ሕግ አግባብ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ አመልካች የ1ኛውን ተጠሪ ክፍያ በተመለከተ ያቀረበው የይርጋና የክፍያ ግምት ክርክር ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤት አመልካች 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ ያነሳውን ይርጋን የሚመለከት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ማለፉን ውሳኔው የሚያሳይ ቢሆንም ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ሕግ ስለመለየቱ ግን የክርክሩ ሂደት አሳይም፡፡ 1ኛ ተጠሪ በዚህ ሰበር ደረጃ አጥብቀው የሚከራከሩትም አመልካች የተጠሪውን የደመወዝ ክፍያ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሚከራከረው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162(3) እና (4) ድንገጌዎችን በመጥቀስ ነው በማለት ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው አመልካች ይርጋ የሚለውን ቃል በስር ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ አግባብነት አለው በማለት የጠቀሰው ግን አዋጅ ቁጥር 377/96 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በሕጉ በተጠቀሰው አግባብ ተከራካሪ ወገን የይርጋ መከራከሪያ ካነሳ ፍርድ ቤቱ ተገቢውን ብይን መስጠት ያለበት ሲሆን ተከራካሪ ወገን ክሱ በይርጋ እንደሚቋረጥ ጠቅሶ ከመከራከር ውጪ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ሕግና ድንጋጌን ለይቶ እንዲከራከር በሕጉ ግዴታ ያልተጣለበት መሆኑን በስነ ስርዓት ሕጉ ስለ አቤቱታ አጻጻፍ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ድርጅት የ1ኛ ተጠሪ ለተሰራ ስራ ያልተከፈለ ደመወዝ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት መከራከሩ እስከታወቀ ድረስ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ሕግ መለየት የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት በመሆኑ በዚህ ረገድ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች በዚህ ረገድ የይርጋ ክርክሩን በሕጉ አግባብ ማንሳቱ ከተረጋገጠ ቀጥሎ መታየት ያለበት የይርጋ ክርክሩ ተቀባይነት አለው ወይስ የለውም የሚለው ጥያቄ ሲሆን ይህንኑ ጥያቄ ለመመለስ ደግሞ አስቀድሞ ለጉዳዩ ገዥነት ያለውን የሕግ ማእቀፍ መለየትን ይጠይቃል፡፡ በዚህም መሰረት ጉዳዩን ስንመለከተው ከላይ እንደተገለፀው የስራ መሪዎችን በተመለከተ የተለዩ ሕግ የሌለ ሲሆን በተግባር እየተሰራ ያለው በስራ ውል፣ በስራ ደንብ ወይም በፍትሃ ብሔር

www.abyssinialaw.com

ሕጉ አግባብ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል ያለውን ግንኙት የሚገዛ በመካካላቸው የተደረገ የስራ ውል ስምምነት ወይም እየተሰራበት ያለ የስራ ደንብ ስለመኖሩ በግራ ቀኙ ክርክር አልተገለፀም፣ በበታች ፍርድ ቤቶችም በዚህ ረገድ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ መገዛት ያለበት በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 2512 እስከ 2593 ድረስ በተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ሲታዩ ደግሞ የይርጋ ጊዜን በተመለከተ አስፍረው አይገኙም፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ሕግ የይርጋ ጊዜውን ለይቶ ያስቀመጠ ሁኖ አይታይም፡፡ ሆኖም አንድን መብትና ግዴታ የሚጠብቅ ልዩ ሕግ በይርጋ የማይታገድ ስለመሆኑ ለይቶ እስካላመለከተ ድረስ መብቱ ወይም ግዴታው የሚጠይቅበት የጊዜ ገደብ በልዩ ሕጉ ያለመመልከቱ ለጉዳዩ ገደብ የለሽ የይርጋ ጊዜ ተቀምጦአል ብሎ ለማለፍ የሚያስችል ያለመሆኑን ከይርጋ ሕግ ፅንሰ ሃሳብ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተውም የተያዘው ጉዳይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2512 እስከ 2593 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ይገዛል ከተባለ በእነዚህ ድንጋጌዎች አግባብ የስራ መሪ የሚያቀርባቸው የመብት ጥያቄዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677(1) እና 1845 ድንጋጌዎች አግባብ በአስር አመት ጊዜ ሊታገድ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ይህንኑ ይዘን የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከትም የአስር አመት ጊዜ ያላለፈበት በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ከጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ ያልተከፈላቸው የአስራ ሶስት ወራት ደመወዝ ብር 32,500.00 በይርጋ የሚታገድ ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች የ1ኛ ተጠሪ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2023 ድንጋጌ አግባብ በስድስት ወር ጊዜ እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው በማለት ይህንኑ ድንጋጌ ለጉዳዩ እንደ ይርጋ ሕግና እንደ ክፍያ ግምት ማስወሰኛ አድርጎ ክርክር አቅርቧል፡፡ ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2023 እና 2024 ስር የተመለተከቱት ድንጋጌዎች የማስረጃ እንጂ የይርጋ ደንቦች ያለመሆናቸውን ይህ ሠበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 15493 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ሐ) ድንጋጌ ለጉዳዩ መጥቀሱም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ይልቁንም አንድ የሥራ መሪ ለሰራው ስራ ደመወዝ መከፈሉን ማስረጃ ሁኖ ሊቀርብ የሚገባው ማስረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2593(1) በተመለከተው አግባብ የሚቀርበው ደረሰኝ ነው፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ ያቀረበው የደመወዝ ክፍያ ጥያቄ አስር አመት ሳያልፈበት የቀረበ በመሆኑ በይርጋ የሚታገድበት አግባብ የሌለ ሲሆን አመልካች ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ባለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2593(1) ድንጋጌ አግባብም 1ኛ ተጠሪ የፈረሙበት የቀሪ ሂሳብ የመጨረሻ ደረሰኝ በማቅረብ ደመወዙ ለተጠሪው ስለመከፈሉ ያስረዳበት አግባብ የሌለ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ ስለሆነም አመልካች ለተጠሪ ብር 32,500.00 ያልተከፈለ ደመወዝ እንዲከፍል መወሰኑ በውጤት ደረጃ የሚነቀፍ ሁኖ አልተገኘም፡፡

www.abyssinialaw.com

የመጨረሻውን ጭብጥ በተመለከተ፡- ተጠሪዎች በአመልካች ላይ በአንድ ላይ ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት 1ኛ ተጠሪ በሙያው ለስራው የኤሌክትሪክ ኢንስቶሌሽን ስራና በስራ መሪነቱ ስራ ሰርቶ ያልተከፈለውን ደመወዝ አመልካች እንዲከፈለው ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ በውል መነሻ ለአመልካች ድርጅት የገጠሙላቸውን ሁለት በር መሰረት አድርገው መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ያደረገው ከአመልካች ጋር በተናጠል ያደረጓቸውን የተለያዩ ውሎችን መሆኑ ግልፅ ሲሆን አመልካች ከተጠሪዎች ከነበረው ግንኙነት አንጻር ክሱ በአንድ ላይ መቅረቡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 35 (1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ከፍትሓ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ መሰረታዊ አላማ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለለም የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪዎችን ክስ አንድ ላይ በመቀበል አመልካችን እንደተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ ለይተው መወሰናቸው በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በመቐሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10912 በ30/04/2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በመቐሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 16742 በ14/07/2007 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 74550 በ14/08/2007 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. 1ኛ ተጠሪ ከጥቅምት 01 ቀን 2005 እስከ ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ/ም የስራ መሪ ነበሩ ተብሎ የተወሰነው ፍሬ ነገሩ በሕጉ አግባብ ተጣርቶና በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3(2(ሐ) ስር የተመለከቱት መመዘኛዎች መሰረት ተደርጎ ነው ብለናል፡፡
3. የስራ መሪን በሚመለከት የተለዬ የሕግ ማእቀፍ ስለሌለ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ካለው የፍትሃ ብሔር ሕጉ ስንነሳ የስራ መሪ የመብት ጥያቄ ላይ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባው የይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677(1) እና 1845 ድንጋጌዎች አግባብ የአስር አመት የይርጋ ጊዜ ነው ብለናል፡፡
4. የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2023 እና 2024 ያሉት ድንጋጌዎች የይርጋ ድንጋጌዎች ሳይሆኑ የክፍያ ግምት የሚወሰድባቸው በመሆኑና ለስራ መሪ ደመወዝ ጥያቄም አግባብነት የሌላቸው በመሆኑ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት የላቸውም ብለናል፡፡

www.abyssinialaw.com

5. ተጠሪዎች ክሳቸውን በአንድ ላይ ማቅረባቸው ተገቢ ነው፣ አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍል የተወሰነው የገንዘብ መጠንም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መሰረት ያደረገ ነው ብለናል፡፡
6. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 117070

ጥቅምት 22 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሰሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ ወይንሸት በቀለ ከጠበቃ ወይንሸት ከበደ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ኦሎምፒያኮስ ሄሌኒክ አትሌቲክስ ማህበር /ግሪክ ክለብ / የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስ፤በተጠሪ ድርጅት ከጥር 16/1990 ዓ.ም ጀምሮ እየሰሩ እንደሚገኙ ይሰሩት ከነበረው ተጨማሪ ስራ ደርበው እንዲሰሩ በተደረገ ጊዜ የደመወዝ ማሻሻያ እንዲደረግላቸው ጠይቀው በዚሁ መሰረት ከነሐሴ 1 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ደመወዛቸው ተሻሽሎ ያገኙት ከነበረው በተጨማሪ በየወሩ ከሚገኘው አጠቃላይ የመጠጥና የምግብ ሽያጭ ገቢ ላይ 3% /ሶስት በመቶ/ የደመወዝ አካል ሆኖ እንዲከፈል ወስኗል፡፡ በዚሁ ውሳኔ መሰረት ከነሐሴ 11 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ነሐሴ 2006 ዓ.ም ለ11 ዓመታት እየተከፈላቸው ሲሆን ምክንያቱ ባልተወቀ ከ3% /ሶስት በመቶ/ ቀንሶ 1% /አንድ በመቶ/ ብቻ እንዲከፈል በውሳኔ ያሳወቃቸው ስለሆነ ከነሐሴ 1 ቀን 2006 ዓ.ም እስከ ህዳር 2007 ዓ.ም በጠቅላላ 95,445.95 /ዘጠና አምስት ሺ አራት መቶ አርባ አምስት ከዘጠና አምስት ሳንቲም እንዲሁም ከታህሳስ 2007 ዓ.ም ጀምሮ ደመወዛቸውን 2% ኮሚሽን ክፍያውን አካቶ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በከተከሳሽነት ቀርበው አመልካች የመጠጥና ምግብ ሰራተኞችን የሚቆጣጠሩ ኃላፊ ስለሆኑ የስራ መሪ ናቸው ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለውም በማለት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ በፍሬ ነገር ላይም በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ አንቀጽ 53 መሰረት ኮሚሽን ደመወዝ አይደለም ስለሆነም ተጠሪ ከመጠጥና ከምግብ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ 3% /ሶስት በመቶ/

www.abyssinialaw.com

በፍቃደኝነት ቢወስንም እንደ አስፈላጊነቱ ደግሞ 1% /አንድ በመቶ/ እንዲከፈላቸው መወሰኑ እንደ ጥፋት ተቆጥሮ ኮሚሽን እንደ ደመወዝ ይቆጠርልኝ በማለት የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም መቃወሚያውን በብይን ወድቅ በማድረግ አመልካች የኮሚሽን ክፍያን እንደ ደመወዝ በመቁጠር ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በሚል ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ከደመወዛቸው በተጨማሪ 3% /ሶስት በመቶ/ ከጠቅላላው የምግብና የመጠጥ ሽያጭ እንደሚከፈላቸው በውላቸው የተቀመጠውን ተጠሪው ይህንን ገንዘብ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ምላሽ ማግኘት ያለበት ነጥብ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከተጠሪው ነሐሴ 11 ቀን 1995 ዓ.ም ለአመልካች የተፃፈ ደብዳቤ ይዘት መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ስለ ደመወዝ ማሻሻያ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ስለ ስራዎት ሁኔታ የክለቡ ኮሚቴ አባላት ተወያይተን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡ ታታሪ ሰራተኛ መሆንዎ እና በሙሉ ፍላጎት ስራዎትን የሚያከብሩ መሆኑን በመገንዘብ ከመስከረም 1995 ጀምሮ የክለቡ ተቆጣጣሪ እና ዋና ገንዘብ ያዥ መሆኖትን እና እንዲሁም ከአጠቃላይ የምግብና የመጠጥ ሽያጭ ላይ ኮሚሽን የደመወዝዎ አካል ሆኖ እንዲከፈሎት ወስነናል የሚል ነው፡፡ አመልካች የጠየቁት የደመወዝ ጭማሪ ነው፡፡ ተጠሪም ጥያቄቸው መሰረት በማድረግ ከምግብና የመጠጥ ሽያጭ 3% /ሶስት በመቶ/ ከሚሽን የደመወዝ አካል እንደሆነ በሚገልፅ ነው የፃፈላቸው፡፡ አመልካችም ያቀረቡት የደመወዝ ጭማሪ ምላሽ በማገኘቱ ተስማምተው ለ11 አመታት በዚሁ ስምምነት እየተከፈላቸው እንደነበረና መጠኑም በግራ ቀኙ ያልተካዱ ፍሬ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ከጅምሩ የአመልካች ጥያቄ የደመወዝ ጭማሪ እንጂ ኮሚሽን እንዲከፈላቸው ያልነበረ መሆኑን የደብዳቤው ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ ከምግብና መጠጥ ሽያጭ ከሚገኝ ገቢ 3% /ሶስት በመቶ/ የደመወዛቸው አካል መሆኑ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ ኮሚሽን ስለሆነ በፍቃድኝነት ያደረኩትን በፈለጉሁት ጊዜ ሁኔታዎች እየታየ የሚሰጥ እንጂ እንደ ደመወዝ በመቁጠር ሊጠየቅ አይገባም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም፡፡ ምክንያቱ ለአመልካች የተደረገው

www.abyssinialaw.com

ጭማሪ በተጠሪ ተነሳሽነት ሳይሆን አመልካች ባቀረቡት የደመወዝ ማሻሻያ ጥያቄ መሆኑ ከላይ በተገለፀው መሰረት የተረጋገጠ ነው፡፡ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ተስማምተውበት ለ11 ዓመታት የደመወዝ አካል አድርገው ተግባራዊ ያደረጉትን ኮሚሽን ነው የደመወዝ አካል አይደለም በማለት በተጠሪ የሚቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ በግልፅ የደመወዝ አካል አድርጎ ለአመልካች ከምግብና ከመጠጥ ሽያጭ ገቢ 3% /ሶስት በመቶ/ እየከፈላቸው የነበረው ኮሚሽን ስለሆነ ወደ 1% /አንድ በመቶ/ መቀነሱ ከስምምነታቸው ውጪ ሆኖ እያለ፣የስር ፍርድ ቤቶች የሚከፈለው መደበኛ ደመወዝ አለ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 53/2/መ/ ኮሚሽን እንደ ደመወዝ አይቆጠርም፣ደመወዝ የሚያስብል መደምደሚያ ላይ አያደርስም ሲል መወሰኑ በበቂ የህግ ምክንያት ያልተደገፈ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 17578 ጥር 26 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 156579 ሰኔ 4 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ከተጠሪ ድርጅት ከምግብና ከመጠጥ ሽያጭ ከሚገኘው ገቢ 3% /ሶስት በመቶ/ ኮሚሽን በስምምነታቸው መሰረት የአመልካች ደመወዝ አካል በመሆኑ ተጠሪ ብቻውን ሊቀንስ አይገባም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከነሐሴ ወር 2006 ዓ.ም ብር 23,907.19፣ ከመስከረም 2007 ዓ.ም 25,762.38፣ከጥቅምት 2007 ዓ.ም ብር 25,612.60፣ከህዳር 2007 ዓ.ም ብር 20,165.73 በጠቅላላ 95,445.95 /ዘጠን አራት ሺ አራት መቶ አርባ አምስት ከ0.95/100 /እንዲከፈላቸው እንዲሁም ከታህሳስ 2007 ዓ.ም ጀምሮ ወደፊት የተቀነሰውን 2% /ሁለት በመቶ/ ኮሚሽን ክፍያውን ከደመወዛቸው አካቶ ለአመልካች እንዲከፍል ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

# ፍትሐብሔር

# ሥነ-ሥርዓት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 103478

ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ኤልያስ ተፈራ - ጠበቃ ዳንኤል ፀጋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አንዋር ሁሴን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የተጀመረው በተጠሪ ከሣሽነት አመልካች ለተጠሪ ፈርመው የሰጡትን ቼክ ተጠሪ ቼኩን እንዲከፍላቸው ባንክ ሲያቀርቡ ቼኩ ሳይከፈል በመመለሱ ምክንያት ብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ) ከነ ሕጋዊ ወለዱ እና ሌሎች ተያያዥ ወጪዎች ጋር በአመልካች እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ተጠሪ በተፋጠነ ስነ ስርዓት በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡

አመልካች በመቃወሚያነት በቼኩ የተመለከተው ገንዘብ ለተጠሪ የተሰጠው ከተጠሪ ጋር በነበራቸው የኪራይ ውል ግንኙነት የተነሳ በሕገ ወጥ መንገድ ተጠሪ ጫና ፈጥረው ቼኩን የወሰዱ በመሆኑ ቼኩ እንዳይከፈል አመልካች ያሳገዱ መሆኑን ገልፀውና ይህንኑ ግንኙነት ለማስረዳት እንደሚችሉ ገልጸው በን/ሕ/ቁጥር 717 መሰረት ለመቃወም የሚያስችል የመከላከያ ማስረጃ ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው የቀረበውን ክስ ለመከላከል እንዲፈቀድላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የአመልካችን የማስፈቀጃ ጥያቄ መርምሮ አመልካች የሚያቀርቡትን የመከላከያ ማስረጃ መስማት አስፈላጊ ሆኖ ማግኙቱን ገልጾ የአመልካችን የመከላከያ መልስ እንዲቀርብ የፈቀደ ሲሆን በዚህም መሰረት አመልካች መከላከያ መልሳቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ በመልሳቸውም የተጠሪ እናት የሆኑት ወ/ሮ ከድጃ ሠዒድ ከመንግስት የተከራዩትን

www.abyssinialaw.com

ቤት ለአመልካች ከ1997 ዓ/ም ጀምሮ አከራይተው አመልካች የንግድ ስራ ሲሰሩበት የቆየ መሆኑን፣ በኋላም በመንግስት መመሪያ መሰረት ነጋዴዎች የንግድ ፈቃዳቸውን ለማሳደስ ዳግም ምዝገባ እንዲያደርጉ በሚደረግበት ጊዜ የሚሰሩበት የንግድ ቤት ከሌላ ሰው የተከራዩት ከሆነና አከራዩ በበኩሉ ቤቱን ከመንግስት የተከራየው እንደሆነ ከመንግስት ጋር ያደረገውን የኪራይ ውል እንዲያቀርቡ በተጠየቁት መሰረት ተጠሪ ከመንግስት ጋር ያደረገውን የኪራይ ውል እንዲያቀርቡ በተጠየቁት መስረት አመልካች ተጠሪን ከመንግስት ጋር ያደረጉትን የኪራይ ውል እንዲሰጡና ዳግም ምዝገባውን እንዲያካሂዱ በሚጠይቅበት ወቅት ተጠሪ የእናታቸው ወኪል ሆነው ቤቱን ለአመልካች አከራይተው የነበሩ በመሆኑ ተጠሪ በማያውቁት መንገድ አመልካች ቤቱን በስማቸው ለማዛወር የሚያደርጉት ጥረት ነው በሚል ምክንያት የኪራይ ውሉን አመልካች እንዲሰጣቸው ከፈለጉ አመልካች ቼክ ፈርመው ለተጠሪ እንዲሰጡ፣ያለዚያ የኪራይ ውሉን እንደማይሰጧቸውና ቤቱንም ታስረክባለህ ወይም ለቀህ ትወጣለህ በማለታቸው ምክንያት አመልካች ቼኩን ፈርመው ለተጠሪ የሰጡ መሆኑን በመዘርዘር ተጠሪ በሕገ ወጥ መልኩ የራሳቸው ባልሆነ የመንግስት ቤት የማይገባቸውን ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ ሌላ ከቤት ኪራይ ውል ውጪ ምንም ግንኙነት ከአመልካች ጋር ሳይኖራቸው አጋጣሚውን በመጠቀምና ጫና በማሳደር በአመልካች የተፈረመ ቼክ ነው በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆንላቸው ተከራክረዋል፡፡ ይህንኑ ለማስረዳትም አሉኝ ያሏቸውን የሰው ምስክሮች ቆጥረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በአመልካች የተቆጠሩት የሠው ምስክሮች ለጉዳዩ አግባብነት የላቸውም በሚል ምክንያት አልፎ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ከሰማ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ብር 500,000.00( አምስት መቶ ሺ.ህ ብር) ቼኩ ለክፍያ ከቀረበበት ከመጋቢት 18 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ከመቶ ሕጋዊ ወለድ(9%)፣ ከመቶ 1/3ኛ እንዲከፍሉና ተጠሪ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር ማቅረብ መብታቸውን በመጠበቅ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ  የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ነው፡፡ የአመልከች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የመከላከያ ማስፈቀጃ ጥያቄውን ከተቀበለ በኋላ ሕጋዊ ባልሆኑ ምክንያቶችና የን/ሕ/ቁጥር 717 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ አስገዳጅነት ካላው የሰበሩ ውሳኔ ጋር ባግባቡ ሳያገናዝብ በአመልካች የተቆጠሩትን የሠው ምስክሮችን ሳይሰማ ምንም ግንኙነት ሳይኖር ለተጠሪ አከራካሪው ገንዘብ እንዲከፈል በማለት የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ባለመሆኑ ተሽሮ የአመልካች ማስረጃዎች ተሰምተው በጉዳዩ ላይ ተገቢው ዳኝነት እንዲሰጥ የሥር ፍርድ ቤት ይታዘዝ ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የበታች ፍርድ ቤቶች ለን/ሕ/ቁጥር 717 አፈጻጸም የሰጡትን ትርጓሜ አግባብነት ለማየት ጉዳዩ ለዚህ ሰበር

www.abyssinialaw.com

ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አንፃርና በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 284 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት በአጭር ሁኔታ በሚወሰኑ ክርክሮች ላይ ስለሚፈፀም ሥነ ሥርዓት በሕጉ የተመለከቱ ሥርዓቶችን መሠረት በማድረግ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ በአጭር ሥነ ሥርዓት ዳኝነት ታይቶ እንዲወሰን ክስ የሚቀርብበት ጊዜ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 285/1/ እንደተመለከተው ከሕጉ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ቁጥር 2 መሠረት ተከሣሽ የሆነው ሰው መጥሪያ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በአሥር ቀናት ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ክሱን ለመከላከል እንዲፈቀድለት ፍ/ቤቱን ፈቃድ እንዲጠይቅ መደረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ አመልካች ቼኩ ለተጠሪ የተሰጠበት ምክንያት በኪራይ ውል ግንኙነት መሆኑንና ይኼው የኪራይ ውል በመንግስት በወጣው መመሪያ የተነሳ በአመልካችና በተጠሪ ያለመግባባት ፈጥሮ በዚሁ ምክንያት ቼኩን ባልተገባ መንገድና ሁኔታ ለተጠሪ ፈርመው የሰጡ መሆኑን በመጥቀስ ለመከላከል እንዲፈቀድላቸው በቃለ መሐላ የጠየቁ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህንኑ የአመልካችን ምክንያት በመቀበልም የስር ፍርድ ቤት አመልካች የመከላከያ መልስ እንዲያቀርቡ ፈቅዶላቸው አመልካች ሙሉ የሆነ መከላከያ መልስና አሉኝ የሚሏቸውን የሰው ምስክሮችን ቆጥረው የማስረጃ ዝርዝር መግልጫ ያቀረቡ መሆኑን የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘው የስር ፍርድ ዋና መዝገብ በግልጽ ያሳያል፡፡

የተጠሪ ዋና ክርክር በቼኩ ላይ ሐተታ ወይም ገደብ የለበትም የሚል ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለቼኩ መሰጠት መሰረቱ አመልካች ከተጠሪ እናት ጋር ያላቸው የመንግስት ቤት ላይ የተደረገ የኪራይ ውል የሚል ነው፡፡ በአመልካችና በተጠሪ እናት መካከል የኪራይ ውል መኖሩ አልተካደም፡፡ ከአመልካች ጋር የተጠሪ እናት ያደረጉትን የኪራይ ግንኙነትን የሚያስተዳድሩት ደግሞ ወኪላቸው የሆኑት የአሁኑ ተጠሪ መሆኑን አመልካች ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ እንዲሁም በአመልካች በመከላከያ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ ላይም ይህ ግንኙነት መኖሩ ተገልጿል፡፡ ይህንኑ ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶም የስር ፍርድ ቤት አመልካች መከላከያ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ አድርጓል፡፡ ምንም እንኳን ቼክ እንደ ገንዘብ ለተለያዩ ሰዎች በቀላሉ ሊተላለፍ የሚችል ባሕርይ ያለው የገንዘብ ሰነድ በመሆኑ ቼክ አከፋፈል ላይ ማንኛውም መቃወሚያ ሊቀርብበት እንደማይችል በንግድ ሕጉ የተደነገገ በመሆኑ ሕጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር የቼክ ክፍያ በማናቸውም ምክንያት ሊቆምና ሊታገድ የማይችል መሆኑ አከራካሪ ያለመሆኑን የን/ሕ/ቁጥር 717 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ በምንመለከትበት የምንረዳው

www.abyssinialaw.com

ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን በባለጉዳዮቹ መካከል ግልጽ የሆኑ ሁኔታዎች ወይም ግንኙነቶች በተፈጠሩ ጊዜ ብቻ ይህን መቃወሚያ ለማድረግ እንደሚቻል በን/ሕ/ቁ. 717/1/ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ይህን መሠረት በማድረግ ለመከላከል እንዲፈቀድለት ያቀረበውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ የተቀበለው ሲሆን በኋላ ግን በአመልካች የተቆጠሩትን የሠው ምስክሮች ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው ናቸው በማለት ሳይሰማ አልፎ የቼክ ክርክር በመሆኑ ብቻ የቼክን ባህርይ መሠረት በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡፡ ሆኖም በዚህ የፈቃድ ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ አመልካች መከላከያ መልስ እንዲያቀርብ ተደርጎ መልስና በሕግ አግባብ ምስክር ቆጥረው እያለ ምስክሮች ሳይሰሙ ይኼው ታልፎ የቼክ ባሕርይ ብቻ መሰረት ተደርጎ ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 286፣ 291 እና 717 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ በአንድ ላይ በማንበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ለመከላከል እንዲፈቀድለት ያቀረበው ምክንያት ፈቃድ የሚያሰጥ መሆኑ እስከታመነ ድረስ የቼክ ባህርይ መሰረት ተደርጎ ምስክሮችን የማሰማት መብታቸው ሊታለፍ የሚችልበት ምክንያት መኖሩን ከክርክሩ ሂደት ማግኘት አልተቻለም፡፡ ከፈቃድ በኋላ ያለው የፍሬ ነገር ክርክር ማስረጃ ተሰምቶ ሊነጥር የሚገባውና ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የማስረጃ ምዘና መርህ በመከተል የሚታይ ይሆናል እንጂ የተከሳሽን የመከላከል መብት ወደ ኃላ በመመለስ መብቱን ለማጥበብ የሚያስችል አይሆንም፡፡ ከዚህ አኳያ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የኪራይ ውል ግንኙነት መሠረት በማድረግ ለመከላከል እንዲፈቀድ ፍ/ቤቱን ጠይቆ ተቀባይነት ያገኘው ጉዳይ ማስረጃ ሳይሰማ ውድቅ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም በጉዳዩ የስር ፍ/ቤቱ በአጭር ሥነ ሥርዓት እንዲታይ የሚቀርቡ ክሶች አመራር ሥርዓትን ሳይሆን የቼክ ባሕርይን መሠረት በማድረግ ውሣኔ መደምደሚያ ላይ መድረሱ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም አመልካች ለመከላከል እንዲፈቀድለት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት በፍ/ቤቱ አግኝቶ የተጠየቀውን ገንዘብ ላለመክፈል በቂ ምክንያት መሆን አለመሆኑ የሚታወቀው ፍ/ቤቱ ከአጭር ሥነ ሥርዓት ወደ መደበኛ የክርክር ሥነ ሥርዓት ውስጥ በመግባት ግራ ቀኙን በአግባቡ በማስረጃ ካከራከረ በኋላ ነው፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 125412 ጥር 29 ቀን 2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 99239 ግንቦት 09 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 125412 ቀጥሎ ግራ ቀኙን በመደበኛ የክርክር ሥርዓት አከራክሮና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውንውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት መልሰናል፡፡ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ጌ**

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.109054

መጋቢት 26 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- አቶ ነገሰ ግዛው -ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ሒርጳ ቤኛ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካች አቶ ነገሰ ግዛው ጥር 15 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁጥር 187309 ጥር 14 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጡት ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የቀረበ ነው፡፡ ቅሬታውም በዋናው መዝገብ ቁጥር 21302 በቀን 9-4-2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተሰጠው ውሳኔ አዋሳኙ ተጠቅሶ 1 ቀርጥ የመሬት ይዞታ እንደሆነ በግልጽ ተጠቅሶ የቀረበ ሲሆን ሁለት ተኩል ቀርጥ መሬት እንድፈጽም መታዘዙ ተገቢ ባለመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ሜታ ሮቢ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 21780 የአሁን ተጠሪ ሂርጳ ቤኛ የአፈጻጸም ክስ አቅርቦ ፍ/ቤቱ የቀበሌው መስተዳድር የአፈጻጸም ተከሳሽ አቶ ነገሰ ግዛው ከመሬቱ ላይ ባህር ዛፎቹን ለማንሳት ፍቃደኛ ስላልሆነ ከባህርዛፎቹ ጋር ለአፈጻጸም ከሳሽ አስረክበናል፡፡ ባህርዛፎቹ 1 ዓመት የሞላቸው ሆኖ በሁለት ቀርጥ ተኩል መሬት ላይ የሚገኝ መሆኑን ገልጿል፡፡ የአፈጻጸም ተከሳሽ ለአ/ከሳሽ የተወሰነለት መሬት አንድ ጥማድ ብቻ በመሆኑ ሌላውን መፈጸም አይገባኝም ሲል የአ/ከሳሽ ደግሞ ክስ ያቀረብኩትና የተወሰነልኝ የመሬት አዋሳኝ ይሄው የተፈጸመልኝ መሬት በመሆኑ ባግባቡ የተፈጸመ ነው በማለት

www.abyssinialaw.com

የተከራከሩትን መዝገቦ የካቲት 6 ቀን 2006 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ የተሰጠው ውሳኔ የመሬቱን አዋሳኝና ስፋቱ በክሱ ውስጥ የተቀመጠው ነው በማለት ስለተወሰነ ለአፈጻጸም ከሳሽ የተፈጸመለት መሬት የተወሰነለትን ነው በማለት ወስደን ውሳኔው ፍጻሜ ስላገኘ መዝገቡን ዘግተነዋል ሲል አዟል፡፡ የአፈጻጸም/ ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ. ቁጥር 00164 ነሐሴ 22/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ የስር ፍርድ ቤት በዋናው ውሳኔ በመ.ቁጥር 21302 ታህሳስ 9/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ የመሬቱ አዋሳኝ በምስራቅ አቶ ጣፋ ሀይሉ እና አበራ ሃይሉ በምዕራብ እና በሰሜን በአፈጻጸም ተከሳሽ እና በደቡብ የመኪና መንገድ ሲሆን አንድ ቀርጥ መሬት ነው፡፡ ቀበሌው በውሳኔ ውስጥ የተጠቀሰውን አዋሳኝ መሬት 2 ቀርጥ ተኩል ያስፈጸመ መሆኑን በሪፖርቱ ጠቅሷል፡፡ የመሬቱ አዋሳኝ በውሳኔ በተጠቀሰው አዋሳኝ ውስጥ ያለው መሬት ሁሉ በመሆኑ ይግባኝ ባይ ቅሬታ ካለው በይግባኝ ማስተካከል ነበረበት እንጂ እንደውሳኔው በመፈጸሙ ቅር የሚያሰኝ አይደለም ሲል የወረዳ ፍ/ቤትን ትዕዛዝ አጽንቷል፡፡ አ/ተከሳሽ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁ. 187309 ጥር 14/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ የቀረበው አቤቱታ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ አቤቱታ አያስቀርብም ሲል ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ቀርበዋል፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ አመልካች በዋናው ፍርድ ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የተወሰነባቸው አንድ ቀርጥ መሬት መሆኑን የስር ፍ/ቤት በውሳኔው ላይ ገልጾ አመልካች ለተጠሪ ያስረከቡት ግን ሁለት ቀርጥ ተኩል መሆኑን የቀረበው ሪፖርት የሚያሳይ ሆኖ እያለ ከፍርዱ ውጪ አንድ ቀርጥ ተኩል መሬት በተጨማሪ ማስረከብ የለብኝም ሲል አመልካች ያቀረበውን ቅሬታ የስር ፍ/ቤት ሳይቀበለው የመቅረቱን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 26/2007 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ የወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች መብቱ ያልሆነውን እና በአዋሳኝ የማንገናኝ ይዞታየን ይዞ ባህር ዛፍ መትከሉ ተረጋግጦ ባህርዛፉን አንስቶ ይዞታዬን እንዲለቅልኝ በውሳኔው መሰረት የተፈፀመ በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ይሁንልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ሰኔ 18/2007 ዓ.ም. በተፃፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡ በዚሁ መሰረት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መዝገቡን እንደመረመርነው ፡ በዋናው መዝገብ ቁጥር 21302 የተሰጠው ውሳኔ አንድ ቀርጥ መሬት አዋሳኙ ተጠቅሶ የአሁን አመልካች ለተጠሪ እንዲለቅለት የተወሰነ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ ውሳኔ የተሰጠበት መሬት ስፋቱ አንድ ቀርጥ መሬት ሆኖ እያለ ሁለት ቀርጥ ተኩል መሬት ለአሁን ተጠሪ መፈጸሙን በተመለከተ የሥር ፍ/ቤት በዋናው መዝገብ ውሳኔ ሲሰጥ አዋሳኙ ተጠቅሶ

www.abyssinialaw.com

የተወሰነ በመሆኑና አሁንም ለተጠሪ (የአፈጻጸም ከሳሽ) የተፈጸመው በዚሁ አዋሳኙ በተጠቀሰው ክልል ውስጥ የሚገኘው መሬት በመሆኑ አፈጻጸሙ ተገቢ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ለዚህ ውሳኔያቸው ድምዳሜ ምክንያት ያደረጉት የዋናው መዝገብ ቁጥር 21302 ውሳኔ የመሬት አዋሳኝን መሰረት በማድረግ ብቻ እንደሆነ ከተደረገው ክርክር መረዳት የሚቻል ነው፡፡ ይሁንና በዋናው መዝገብ አንድ ቀርጥ የመሬት ይዞታ ውሳኔ ተሰጥቶበት ከእጥፍ በላይ ሁለት ቀርጥ ተኩል መፈጸሙ የመሬቱ አዋሳኝ በአንድ በኩል በደቡብ አቅጣጫ የአፈጻጸም ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) የሚያዋስነው ሆኖ እያለና በዚሁ አቅጣጫ ወደ አመልካች የመሬት ይዞታ ሊታለፍ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል የስር ፍ/ቤት በሚከተሉት 1. ክርክር ስላስነሳው የእርሻ መሬት አዋሳኝ እና መጠን ጉዳይ ተጠሪዋ ክሳቸውን ባቀረቡበት ጊዜ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 224(2) መሰረት የሰጡት መግለጫ ይዘት ምን እንደሆነ 2. በአመልካቹ መልስ ላይ የተሰጡት ትችት ምን እንደ ሆነ፡ 3. ክርክር ስላስነሳው የእርሻ መሬት አዋሳኝ እና መጠን ጉዳይ በስረ ነገሩ ፍርድ ላይ የተገለጸው የውሳኔ ክፍል የተሟላ ይዘት ምን እንደሆነ 4. ተጠሪዋ ክስ ያቀረቡበት እና የስረነገሩ ፍርድ ያረፈበት የእርሻ መሬት ይታወቅ የነበረው በቀርጥ በምን ያክል መጠን እንደ ሆነ፡ ከተጠቀሱት ነጥቦች በመነሳት በስረነገሩ ፍርድ ላይ በተገለጸው መጠን እና በአፈጻጸም ጊዜ በተለካው መጠን መካከል ልዩነት ሊከሰት የቻለበት አጠቃላይ ምክንያት ምን እንደሆነ ተጣርቶና ተለይቶ ከታወቀ በኃላ መፈጸም ነበረበት፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በዋናው መዝገብ ውሳኔ የተሰጠበት መሬት አንድ ቀርጥ ሆኖ እያለ ሁለት ቀርጥ ተኩል የሆነበት ምክንያት ሳይጣራ አዋሳኙን ብቻ መሰረት በማድረግ የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ እና ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁ. 187309 ጥር 14/2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ፣ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ. ቁ. 00164 ነሐሴ 22/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ የሜታ ሮቢ ወረዳ ፍ/ቤት በመ. ቁ. 21780 የካቲት 6/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሜታ ሮቢ ወረዳ ፍ/ቤት በዋናው መዝገብ ቁ. 21302 የተሰጠው ውሳኔ አንድ ቀርጥ መሬት አዋሳኙ ተጠቅሶ ለአሁን ተጠሪ አመልካች እንዲለቅለት ተወስኖ እያለ የተፈጸመው መሬት ሁለት ቀርጥ ተኩል የሆነበት ምክንያት ከላይ በፍርዱ ክፍል ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ተራ ቁጥር አራት የተጠቀሱትን እና ተያያዥ ነጥቦችን ከስረ

www.abyssinialaw.com

ነገሩ ፍርድ ይዘት እና ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጭምር በማጣራት ውሳኔውን እንዲያስፈጽም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡

3. የውሳኔው ቅጂ በዚህ ውሳኔ መሰረት እንዲከወን ለሜታ ሮቢ ወረዳ ፍ/ቤት እንዲያውቁት ደግሞ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እና ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ይላክ፡፡
4. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሳራ ተቻቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.102141

. መጋቢት 29 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ አደን ዩሱፍ ታኒ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አህመድ አብዱላሂ ተረቢ - ጠበቃ ሽፈራው በላይ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክሱ በቀረበበት የዶሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የተጠሪው አባት መሆኑ በተረጋገጠው ይዞታ ላይ ለገነቡት ቤት የቤቱን የዋጋ ግምት ብር 346,292 (ሶስት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሁለት) ወስደው ቤቱን ከነይዞታው ከሳሽ ለነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ለቀው እንዲያስረክቡ በዶሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር M/13/06 በ06/05/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 05-33/06 በ03/08/2006 ዓ.ም እና በመዝገብ ቁጥር 05-1-91/06 በ14/09/2006 ዓ.ም. የፀናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ አመልካች የተጠሪ አባት ይዞታ በሆነው ቦታ ላይ አላግባብ ቤት መስራታቸውን የሚገልጽ ሆኖ ይህንኑ ይዞታና ቤት ለቀው እንዲያስረክቡ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ፍርድ ቤቱ ይዘቱ ከላይ የተገለፀውን ውሳኔ የሰጠው የአመልካቹን መልስ የመስጠት መብት አልፎ የተጠሪውን ምስክሮች በመስማት እና ቀጥሎም ክሱን ከሰማ እና አመልካቹ በይዞታው ላይ የገነቡት ቤት በባለሙያዎች ተገምቶ እንዲቀርብ ካደረገ በኋላ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

www.abyssinialaw.com

አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪው ባዶ መሬት በብር 100,000 ገምተው ክስ ማቅረባቸውን፣የአመልካች ተወካይ ከክርክሩ እንዲሰናበቱ ተደርጎ አመልካች መልስ ለማቅረብ በቂ ጊዜ ሳይሰጣቸው መልስ አላቀረቡም በሚል መልስ የመስጠት መብታቸው የመታለፉን፣በኋላም ቀርበው የቃል ክርክር አድርገዋል ተብሎ ማስረጃ የማቅረብ ዕድል ሳይሰጣቸው የተጠሪ ምስክሮች ብቻ ተሰምተው አመልካች ከ35 ዓመት በላይ ሰርተው የሚኖሩበትን ቤት ለተጠሪው እንዲለቁ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመወሰኑን እና ውሳኔው በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች የመፅናቱን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በክርክሩ አልባት ማግኘት የሚገባው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዶሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካቹን መልስ የመስጠት መብት አልፎ የተጠሪውን ክርክር እና ማስረጃ ብቻ መሰረት አድርጎ ውሳኔ መስጠቱ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ነጥብ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው የዶሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለቀረበባቸው ክስ መልስ ይዘው እንዲቀርቡ በተሰጣቸው የ19/03/2006 ዓ.ም. ቀጠሮ አልቀረቡም በሚል በ30/03/2006 ዓ.ም. በተጻፈ መጥሪያ መልሳቸውን ይዘው እንዲቀርቡ ለ02/04/2006 ዓ.ም. ተለዋጭ ቀጠሮ የተሰጣቸው መሆኑን፣በዚህ ቀነ ቀጠሮ የአመልካቿ ልጅ እና ተወካይ የጽሁፍ መልሳቸውን ይዘው የቀረቡ መሆኑን፣ይሁን እንጂ መልሱ ስህተት አለበት በሚል አስተካክለው እንዲያቀርቡ በተነገራቸው መሰረት ለመፈጸም ተወካይዋ ፈቃደኛ ስላልሆኑ እና ችሎቱንም ስለሰደቡ በአመልካች የተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ተሰርዟል በሚል አመልካች ራሳቸው መልሳቸውን ይዘው እንዲቀርቡ ለ04/04/2006 ዓ.ም. ተለዋጭ ቀጠሮ የተሰጣቸው መሆኑን፣የአመልካቹ የጽሁፍ መልስ የመስጠት መብት የታለፈውም አመልካች በዚህ ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርቡ በመቅረታቸው መሆኑን፣ከዚህ በኃላ ፍርድ ቤቱ በ05/04/2006 ዓ.ም. ክርክር ያስነሳውን ቤት እና ይዞታ በአካል ሄዶ የተመለከተ መሆኑን፣በ07/04/2006 ዓ.ም. የተጠሪውን ምስክሮች የሰማ መሆኑን እና በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 ድንጋጌ መሰረት የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል የተባለውም ከላይ የተመለከተው ሂደት ሁሉ ከተከናወነ በኃላ በመጨረሻ ላይ በ15/04/2006 ዓ.ም. መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

በመሰረቱ ተገቢው የውክልና ስልጣን የተሰጣቸው እስከሆነ ድረስ የዋናው ባለጉዳይ ባለቤት፣ወንድም፣እህት፣ልጅ፣አባት፣አያት ስለዋናው ባለጉዳይ ሆነው በወኪልነት ለመከራከር፣

www.abyssinialaw.com

ለመሟጋትና ነገሩን ለመከታተል የሚችሉ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 58 (ሀ) ስር የተመለከተ ሲሆን የአመልካች ልጅም በዚሁ ስርዓት መሰረት ከአባታቸው በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን መሰረት በ02/04/2006 ዓ.ም. ቀነ ቀጠሮ የጽሁፍ መልስ ይዘው ቀርበው እንደነበረ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ ገልጿል፡፡መልሱ ስህተት አለበት ከመባሉ በቀር ስህተቱ ምን እንደሆነ እና ስርዓቱን ጠብቆ የተሰጠ የመልስ ይሻሻል ትዕዛዝ ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡የአመልካች ልጅ ከክርክሩ እንድትሰናበት የተደረገው አባቷን ወክላ ለመከራከር የሚያስችል ተገቢ የውክልና ስልጣን ስላልነበራት ነው በማለት ተጠሪው በሰበር መልሳቸው ያቀረቡት ክርክር የመዝገቡን ግልባጭ መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡ከላይ እንደተገለጸው ፍርድ ቤቱ ከክርክሩ ያሰናበታትም ለችሎቱ ያልተገባ ሥነ ምግባር አሳይታለች በሚል እንጂ ይዛው የቀረበችው የውክልና ስልጣን ማስረጃ ጉድለት አለበት በማለት አይደለም፡፡

በመሰረቱ የአመልካቹ ተወካይ ለችሎቱ ተገቢ ያልሆነ ስነ ምግባር አሳይተዋል የሚባል ከሆነ የችሎቱን ክብር ለማስጠበቅ ፍርድ ቤቱ በሕግ አግባብ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይችል የነበረ ከመሆኑ ውጪ አመልካች ለልጃቸው የሰጡትን የውክልና ስልጣን ለመሰረዝ ወይም ለመሻር የሚያስችል ስልጣን የለውም፡፡በሌላ በኩል ፍርድ ቤቱ ተገቢ ምክንያቶች ሲያጋጥሙት ምክንያቱን በማስፈር ዋናው ባለጉዳይ እራሱ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠት የሚችል ስለመሆኑ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተ ቢሆንም በተያዘው ጉዳይ አመልካች ራሳቸው መልሳቸውን አዘጋጅተው እንዲቀርቡ የተሰጣቸው የሁለት ቀናት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ይህ ጊዜ ደግሞ ከተለያዩ ሁኔታዎች አንጻር ሲታይ በቂ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡በመሆኑም የአመልካች ወኪል ያቀረቡት የጽሁፍ መልስ ተቀባይነት ያጣበት በቂ እና ሕጋዊ ምክንያት መኖሩ ባልተገለጸበት እና ስርዓቱን ጠብቆ የተሰጠ የመልስ ይሻሻል ትዕዛዝ በሌለበት ሁኔታ፣ እንዲሁም አመልካች እራሳቸው መልሳቸውን አዘጋጅተው ማቅረብ እንዲችሉ በቂ የሆነ ጊዜ እንዲሰጣቸው ባልተደረገበት ሁኔታ የአመልካቹ የጽሁፍ መልስ የመስጠት እና ማስረጃ የማሰማት መብት ታልፎ የተጠሪውን ክርክር እና ማስረጃ ብቻ መሰረት አድርጎ አመልካቹን ለክሱ ኃላፊ የሚያደርግ ውሳኔ መስጠቱ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በዶሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር M/13/06 በ06/05/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 05-33/06 በ03/08/2006 ዓ.ም እና በመዝገብ ቁጥር 05-1-91/06 በ14/09/2006 ዓ.ም. የፀናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቹ ለደረሳቸው ክስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 334 (1) ድንጋጌ መሰረት ተገቢ ነው የሚሉትን የጽሁፍ መልስ እንዲያቀርቡ ካደረገ በኃላ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት መሰረት አድርጎ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ ጭምር መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሰረት ለዶሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለዶሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቀው ደግሞ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
4. በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05-1-91/06 የተሰጠው ፍርድ አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ04/13/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 114816

ግንቦት 26 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች ፡- ዳዊት በለጠ የጠጠር አምራች ድርጅት -ጠበቃ እሸቱ አሰፋ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አብዱራዛቅ ሙሳ ኡስማን -አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ህግ ከደነገገው ውጭ አመልካች የስራ ውሌን አቋርጧል፤ ስለሆነም ለህገውጥ ስንበት በህጉ የተፈቀደው ልዩ ልዩ ክፍያዎች ይከፈለኝ በማለት የክፍያ አይነቶችን ዘርዝሮ ዳኝነት ሲጠይቅ፤ የአሁን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ከነሀሴ 30 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በመደዳ ከስራ የቀረ በመሆኑ የስራ ውሉ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ለ/ ስር በተመለከተው መሰረት እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህጋዊ ስለሆነ ክፍያ ልንጠየቅ አይገባም፡፡ የ25 ቀን የዓመት እረፍት እንከፍላለን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ምስክሮቹን ለማቅረብ በተያዘው ቀጠሮ ቀን ያላቀረበ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 199/1/ መብቱ የታለፈ መሆኑን በመግለፅ፤ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ ስለሌለ ስንብቱ ህገወጥ ነው በማለት ልዩ ልዩ ክፍያዎችን በማስላት በድምሩ ብር 23,000 ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት ስላለገኘ በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 17 ቀን 2007 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ:- ማስረጃ የማሰማት መብት የታለፈው በግልፅ የተካደ ፍሬ ነገር በማስረጃ ሳይነጥር አምነዋል ተብሎ ውሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተብሎ እንዲሻርልን ወጪና ኪሳራ እንዲተካልን የሚል አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አብቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርበዋል ፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካች ጥያቄ የማስረዳት መብት በማለፍ በማስረጃ ሳይረጋገጥ ውሳኔ መሰጠቱ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ደግሞ አመልካች አዲስ ነገር በማቀረቡ ክሱ የሚከፍተው ተከሳሽ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተከሳሽ የማሰረዳት ኃለፊነቱ ነው ማለቱ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት የአሁኑ አመልካች ምስክሮቹ እንዲያቀርብ በተያዘው ቀጠሮ አለመቅረቡን ነው፡፡

ክስን መክፈትና ሙግትን የመጀመር መብት የከሳሽ ነው፡፡ ነገር ግን ተከሳሹ ከሳሽ ያቀረበውን ክስ አምኖ ነገር ግን ሕግ ወይም ሌላ ፍሬ ነገር በመጥቀስ የቀረበብኝ ክስ ዋጋ የለውም ብሎ የሚከራከር ከሆነ ሙግቱን የሚጀምረው ተከሳሹ እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 258/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ ከሳሽ በማስረጃ አቀራረብ ረገድ ጀማሪ የሚሆነው ሁል ጊዜ እንዳልሆነ የስነ ስርዓት ህጉ በግልፅ ይደነግጋል፡፡

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ በተጠሪ የቀረበው ክስ የስራ ስንብቱ ህገወጥ ነው የሚል ሲሆን አመልካች ደግሞ ከስራ ያሰናበተው መሆኑን በማመን ነገር ግን በተከታታይ የስራ ቀናት በመቅረቱ ስንብቱ ህገወጥ ሊባል አይችልም የሚል ነው፡፡ እዚህ ላይ አመልካች ተጠሪን ከስራ ማሰናበቱን ከተቀበለ ፤ ለስንብቱ ምክንያት የሆነው የተጠሪ ጥፋት መሆኑን የማስረዳት ሸከሙ የስር ተከሳሽ የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ ተጠሪ በተከታታይ የስራ ቀናት መቅረቱን ማረጋገጥ ያለበት አመልካች እንጂ ተጠሪ እንዲያስረዳ አይጠበቅም፡፡ አመልካች ምስክሮቹን እንዲያቀርብ በተያዘው ቀጠሮ ባለማቅረቡ የታለፈበት መሆኑ ከስር መዝገብ ተመልክቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

ተጠሪ ከህግ ውጭ ከስራ ስላሰናበተኝ ተገቢውን ክፍያ ይከፈለኝ የሚል ክስ ያቀረበው አመልካች ያሰናበተው መሆኑን አምኖ የተሰናበተው በተጠሪ ጥፋት መሆኑን ገልፆ ስለተከራከረ መጀመሪያ ማስረዳት ያለበት አመልካች ነው፡፡ ነገር ግን በአመልካች ጉድለት ምክንያት ምስክሮቹን በማቅረብ ማስረዳት አልቻለም፡፡ በማስረጃ ያልተደገፈ የፍሬ ነገር ክርክር ረቺ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ ከላይ በተዘረዘሩ ምክንያቶች አመልካች ማስረጃ ሳይሰሙ መወሰኑ አግባብ አይደለም ሲል ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚሁ መሰረትም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.54094 ሚያዝያ 28 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ /ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10627 ሰኔ 4 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/በ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በፌ/መ/ደ/ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 57878 የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው አካል ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 117754

ሐምሌ 8 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አክሰስ ሪል ስቴት (አ.ማ)

ተጠሪ፡- ጋቢ ኢንቨስትመንት ኃ/የተ/የግል ማህበር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የይግባኝ መዝገብ በድህ ደንብ እንዲከፈትለት ያቀረበውን ማመልከቻ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውድቅ ያደረገው በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በሰበር አይቶ ለመወሰን ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 5 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የቃለ መሃላ ማመልከቻ፡-
   - በድርጅቱ ሠራተኞች፣ ቤት ገዥዎችና ሌሎች ባለመብቶች በፍርድ ቤት ክስ ቀርቦበት የፍርድ ባለዕዳ በመሆኑ፣
   - ድርጅቱ ማናቸውም የባንክ ሒሳብ እንዳይከፍትና እንዳያንቀሳቅስ ብሔራዊ ባንክ በሰጠው መመሪያ የታገደ በመሆኑ፣
   - ድርጅቱ በሊዝና በሌላ መንገድ የያዛቸውና ያለማቸው መሬቶች ላይ ማናቸውንም እንቅስቃሴ እንዳያደርግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ በሰጠው መመሪያ የታገደ በመሆኑ
   - ድርጅቱ በስሙ ያሉትን ንብረቶች እንዳይሸጥ እንዳያከራይና በዕዳ እንዳያሲዝ የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት በሰጠው መመሪያ የታገደ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ድርጅቱ ባለበት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ለዳኝነት የሚከፍለው ገንዘብ ስለሌለ የድርጅቱ

www.abyssinialaw.com

ሁኔታ ሲሻሻል የዳኝነቱን ገንዘብ የሚከፍል ሆኖ ለጊዜው የይግባኝ መዝገቡ በድሃ ደንብ ተከፍቶ እንዲታይ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ የሚል ጥያቄ አቅርቧል፡፡

2. ተጠሪ በበኩሉ ድርጅቱ በውጭ ኦዲተር ተመርምሮ ካለው ካፒታል 3/4ኛው የጠፋ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ አክሲዮን ማህበሩ በፍርድ ቤት የኪሣራ ውሳኔ አልተሰጠበትም፡፡ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በስሙ የሌለው መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ በአንፃሩ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ድርጅቱ በቂ የገንዘብ አቅም ያለው መሆኑንና ለቤት ገዥዎች ቤታቸውን አጠናቅቆ ሊያስረክባቸው እንዲችል የከፈሉት ገንዘብ እንዲመለስላቸው የሚጠይቁ የቤቱ ገዥዎች ገንዘባቸው የሚመለስላቸው መሆኑን ግልፅ የሆነ መግለጫ ሰጥተዋል ስለዚህ አክሲዮን ማህበሩ ደሃ ነው ለማለት ስለማይችል ይግባኙ በድሃ ደንብ ሊከፈትለት አይገባም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

3. ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ አመልካች ይግባኝ ባይ /አመልካች/ ካለው ካፒታል 3/4ኛው የጠፋ ስለመሆኑ በገለልተኛ ባለሙያ ተጣርቶ ያልቀረበ በመሆኑ በድሃ ደንብ ይግባኙ እንዲከፈትለት ያቀረበው ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ያለኝን ንብረት ሽጬ ወይም አከራይቼ ለዳኝነት እንዳልከፍል በተለያዩ አካላት በተሰጠ የዕግድ ትዕዛዝ ምክንያት የማልችል መሆኔን በገለፅኩበት ሁኔታ ፍትህ የማግኘት መብቴን የሚያሳጣ ብይን መሰጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚል የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው መሆኑን በመዘርዘርና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያቀረባቸውን መከራከሪያ ነጥቦች በማጠናከር መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የፍተሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 467 የዳኝነት የሚከፍለው ገንዘብ የሌለውና ለማግኘት የማይችል ሰው በነፃ ፋይል ማስከፈት እንደሚችል በንዑስ አንቀጽ 1 ደንግጓል፡፡ አመልካች የይግባኝ መዝገብ በነፃ እንዲከፈትለት ጥያቄ ያቀረበው ያለውን ንብረት እንዳይሸጥ፣ እንዳይለውጥና እንዳያከራይ በተለያዩ የመንግስት አካላት ለጊዜው የተላለፉ የዕግድ ትዕዛዞች ስላሉ ያለኝን ሀብት ሽጬ የባንክ ሒሳቤን አንቀሳቅሼ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መክፈል የሚገባኝን የዳኝነት ገንዘብ ለጊዜው ላገኝ አልቻልኩም በማለት ነው፡፡ ይህም በመንግስት አካላት በተሰጠ ትዕዛዝ አመልካች ያሉትን የማይንቀሳቀሱና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች እንዳይሸጥ፣ እንዳይለውጥ የባንክ ሒሳብ እንዳይከፍትና እንዳያንቀሳቅስ ተደርጎ ከሆነ አመልካች በንግድ ህጉ መሠረት ¾ የነበረውን ካፒታል የተጠቀመ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የከሰረ መሆኑ ባይረጋገጥም በፍተሐ ብሔር ህግ ቁጥር 1793 (ለ) መሠረት አመልካች ከአቅሙ በላይ

www.abyssinialaw.com

በሆነ የመንግስት አካላት ንብረቱን እንዳያንቀሳቅስ በሰጡት ዕግድና ጊዜያዊ ክልከላ ምክንያት ለጊዜው ይግባኙን ለማሳየት የዳኝነት የሚከፍለው ገንዘብ የሌለ መሆኑ ከተረጋገጠ ንብረቱን መሸጥ መለወጥ ሲፈቀድለት በቅድሚያ የዳኝነት ክፍያውን የሚከፍል ሆኖ ለጊዜው ይግባኙ በነፃ እንዲከፈትለት ከመጠየቅ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 467 እና ተከታይ ድንጋጌዎች እና የህገ መንግስቱ አንቀጽ 37(1) ድንጋጌ ይዘት፡- አመልካች አለኝ የሚለውን ንብረት እንዳላንቀሳቅስ ታግዶብኛል ከሚለው ክርክር ጋር በማገናዘብ ለመረዳት ችለናል፡፡ ከዚህ አንፃር ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ከነበረው ካፒታል ¾ኛ መጠቀሙ ስላልተረጋገጠ በነፃ ዳኝነት ሊከፈትለት አይገባም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

5. በሌላ በኩል አመልካች ለጊዜው ይግባኙን ለማሳየት የሚከፍለው የዳኝነት ገንዘብ ለመክፈል የማያስችለው በተለያዩ ንብረቶች ላይ የተለያዩ የመንግስት አካላት የሰጡት ዕግድ ያለመሆኑን የገለፀውን ፍሬ ነገር ይግባኝ ሰሚው ችሎት ዕውነትነት ያለው መሆኑን በጭብጥነት በመያዝ ያላጣራው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ አንፃር ይግባኝ ሰሚው ችሎት፡-
   ሀ) የድርጅቱ ሠራተኞች ገዥዎች የፍርድ ባለመብት በመሆናቸው በፍርድ ቤት የታገደ የአመልካች ገንዘብና የሚንቀሳቀስንና የማይንቀሳቀስ ንብረት፣
   ለ) አክስዮን ማህበሩ የባንክ ሒሳብ እንዳያንቀሳቅስና እንዳይከፍት ከብሔራዊ ባንክ ለሌሎች ባንኮች የተሰጠ መመሪያና ዕግድ ያለ መሆኑን፣
   ሐ) ድርጅቱ በሒሳብና በሌላ መንገድ የያዛቸውና ያለማቸው መሬቶች ላይ ማናቸውንም እንቅስቃሴ እንዳያደርግ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ለሌሎች አካላት የተሰጠ መመሪያና ዕግድ ያለ መሆኑንና
   መ) ድርጅቱ በስሙ ያሉትን የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች እንዳይሸጥ፣ እንዳይለውጥ፣ እንዳያከራይ፣ በዕዳ እንዳያሲዝ ከሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንስ የተላለፈ መመሪያና የተሰጠ ዕግድ ያለ ስለመሆኑ አመልካች ማስረጃውን እንዲያቀርብ በማድርግና ተጠሪም የአመልካችን ማስረጃ የሚያስተባቡሉ ማስረጃዎች እንዲያቀርቡ በማድረግ አመልካች በፍተሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ 1793 (ለ) በንብረቶች ላይ ባስተላለፈው ዕግድና ጊዛዊ ክልከላ መሠረት ይግባኙን በማሳየት መክፈል የሚገባውን የዳኝነት ገንዘብ ለጊዜው መክፈል የማይችልበት ሁኔታ አለ ወይስ የለም የሚለው ጭብጥ ላይ ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343 (1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 112204 ሰኔ 29 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ይግባኝ ሰሚው ችሎት በዚህ ፍርድ የተገለፁትን ነጥቦች በማጣራት የይግባኝ መዝገቡ በነፃ ሊከፈት ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 115892

ሐምሌ 4 ቀን 2008ዓ.ም

ዳኞች፡ አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ መሰረት አንዳርጌ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ይበልጣል ስመኝ
2. ወ/ሮ ትርንጎ ስመኝ
3. አቶ ታደሰ ስመኝ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ያቀረበችውን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ለመቀበልና ጉዳዩን በዳኝነት አይቶ ለመወሰን የሚያስችለኝ የዳኝነት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን ብይን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማጽናቱ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ አመልካችና ሌሎች የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅራቢዎች፣ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ያቀረቡት የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 13904 አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ከሳሽ ሶስተኛው ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረው መጋቢት 16 ቀን 2001ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንን በማሻሻል የሰጠውን ፍርድ በመቃወም ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

2. በመዝገብ ቁ. 13904 አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ቀርበው ተከሳሽ (3ኛ ተጠሪ) የወላጅ አባታችን አቶ ስመኝ ባይህ የውርስ ንብረት የሆነ ንብረት በመያዝ ጠቅላላ ግምቱ ብር 2,856.000 /ሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ ስድስት ሺ ብር/ የወሰደ በመሆኑ፣ ይህንን ገንዘብ ከነወለዱ ድርሻችንን እንዲያካፍለን ይወሰንልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተከሳሽ ያቀረቡትን ክስ በመቃወምና በመከላከል መልስ አቅርቧል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተከሳሹ (ሶስተኛ ተጠሪ) ግምቱ ብር 1,867,728 /አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሳ ሰባት ሺ ሰባት መቶ ሃያ ስምንት ብር/ የሚችን የውርስ ንብረት የያዙ በመሆኑ የከሳሾችን /አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪን/ ድርሻ ከነወለዱ እንዲከፍል በማለት መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

3. ሶስተኛ ተጠሪ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 13904 መጋቢት 16 ቀን 2001ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሶስተኛ ተጠሪንና የአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪን የይግባኝ ክርክር በይግባኝ መዝገብ ቁ. 24731 ከሰማ በኋላ፣ የከሳሾች (የአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ) የውርስ ንብረት ክፍያ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ሚያዚያ 11 ቀን 2002 ዓ.ም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁ. 24731 ሚያዚያ 11 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ የሰበር አመልካች ሶስተኛ ተጠሪ የሠበር ተጠሪ በመሆን ያቀረቡትን ክርክር በሰበር መዝገብ ቁ. 09914 ከሰማ በኋላ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች የውርስ ንብረት ለመካፈል ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ሽሮ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ወደ ፍሬ ጉዳዩ ገብቶ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ውሳኔ ይስጥበት በማለት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሰረት መልሶለታል፡፡

4. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል ዘግቶት የነበረውን የይግባኝ መዝገብ ቁ. 24731 ካንቀሳቀሰ በኋላ (የይግባኝ ባዩን/ ሶስተኛ ተጠሪንና) የመልስ ሰጭዎችን /አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች/ ክርከር ከሰማ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ባዩ /ሶስተኛ ተጠሪ/ ለመልስ ሰጭዎች (አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ) ግምቱ ብር 1,867,728 /አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሳ ሰባት ሺ ሰባት መቶ ሃያ ስምንት ብር/ ከሆነው የውርስ ንብረት ድርሻቸውን ያካፍላቸው በማለት የሠጠውን የውሳኔ ክፍል አፅንቶ፣ ሶስተኛ ተጠሪ ወለድ ሊከፍል ይገባል በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን

www.abyssinialaw.com

የውሳኔ ክፍል ብቻ በመሻር ሶስተኛ ተጠሪ የውርስ ንብረት ወለድ የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት በይግባኝ መዝገብ ቁ. 24731 ሚያዚያ 17 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

5. ሶስተኛ ተጠሪ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 24731 ሚያዚያ 14 ቀን 2005 ዓ.ም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ወለድን በተመለከተ የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር አጣሪ ችሎት አቅርቦ፣ የክልሉ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሶስተኛ ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር ችሎት አቅርቦ፣ ይኸ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁ. 96715 የሶስተኛ ተጠሪንና /የአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች/ ክርክር ከሰማ በኋላ የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 13904 መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 24731 ሚያዚያ 14 ቀን 2005 ዓ.ም እንደተሻሻለ አፅንቶታል፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁ. 24731 ሚያዚያ 14 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለቱ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይህ ሰበር ችሎት በአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች አመልካችነት መነሻ በሰበር መዝገብ ቁ. 98329 ከሰማ በኋላ የአንደኛና የሁለተኛ ተጠሪ የሰበር አቤቱታ በሰበር ለመታየት ብቁ አይደለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

6. አመልካችና በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆኑት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅራቢዎች የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች ከሳሽ ሶስተኛ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው በተከራከሩበት በመዝገብ ቁ. 13904 መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም ውሳኔ የሰጠበት የውርስ ንብረት ላይ እኛም ድርሻ ያለን በመሆኑ ወደ ክርክሩ ገብተን ድርሻችን ተረጋግጦ እንዲወሰንልን በማለት ያመለከቱ ሲሆን አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች የመቃወም አመልካችዎች የውርስ ንብረት ድርሻ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚልና ሌሎች መከራከሪያዎችን አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 24731 ሚያዚያ 14 ቀን 2005 ዓ.ም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ውሳኔ የሰጠበት በመሆኑ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻው መቅረብ ያለበት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነው በማለት የአመልካችንና የሌሎቹን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ይህንን ብይን በመቃወም ያቀረበችውን የይግባኝ ቅሬታ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ

www.abyssinialaw.com

መዝገብ ቁ. 40822 ሰኔ 30 ቀን 2007 ዓ.ም አይቶ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

7. አመልካች የሟች አቶ ስመኝ ባይህን የውርስ ንብረት በተመለከተ የሟች ተተኪ ወራሽ የሆንኩት አመልካች በክርክሩ ተሳታፊ ሳልሆን፣ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች ከሳሽ ሶስተኛ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረው የውርሱን ንብረት እንዲካፈሉ ውሳኔ የሰጠበት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ወለድን በተመለከተ ብቻ ከማሻሻል ውጭ የዞኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ ስለዚህ የፍርድ መቃወሚያው መታየት የሚገባው የውርስ ንብረቱን በተመለከተ አከራክሮ ውሳኔ ለሰጠው ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆን ሲገባው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን ስህተት አለበት በማለት ያመለከተች ሲሆን ተጠሪዎች ጉዳዩ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ድረስ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑን ገልጸው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ የፍርድ መቃወሚያ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡

8. ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው፣ አመልካች መብቴና ጥቅሜ በክርክሩ ተካፋይ ሳልሆን ውሳኔ ተሰጥቶበታል የምትለውን የሟች ስመኝ ባይህን የውርስ ንብረት በተመለከተ የአንደኛና የሁለተኛ ተጠሪን ክስና ማስረጃ የሶስተኛ ተጠሪን የመከላከያ መልስና ማስረጃ ሰምቶና የሟች ውርስ ብር 1,867,728 /አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሳ ሰባት ሺ ሰባት መቶ ሃያ ስምንት ብር/ እንደሆነ በመግለጽ፣ ይንን ገንዘብ ከነ ወለዱ ሶስተኛ ተጠሪ ለአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ ድርሻቸውን እንዲያካፍል በማለት ውሳኔ የሰጠው የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 13904 መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ የወለድ ክፍያን በተመለከተ ካልሆነ በስተቀር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 24731 ሚያዚያ 14 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔም ሆነ ይህ የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁ. 96715 እና በሰበር መዝገብ ቁ. 98329 በሰጠው ውሳኔ አልተለወጠም፡፡

9. ይህም የሚያሳየው አመልካች አጠቃላይ ግምቱ ብር 2,801,592 /ሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ አንድ ሺ አምስት መቶ ዘጠና ስምንት ብር/ በሆነው የሟች ስመኝ ባይህ የውርስ ንብረት ላይ ድርሻ እያለኝ የክርክሩ ተሳታፊ ሳልሆን መብትና ጥቅሜን የሚጎዳ ውሳኔ ተሰጥቶብኛል በማለት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ላይ መሰረታዊ የሆነ ውሳኔ የሰጠበት የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህንን ፍርድ በመቃወም አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት የምታቀርበውን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ተቀብሎና የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ቀደም ሲል የተሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360(2) መሰረት የማፅናት፣ የማሻሻል፣

www.abyssinialaw.com

የመሰረዝ ወይም የመሻር ስልጣን ያለው አመልካች በውሳኔው መብትና ጥቅሜ ተነክቷል የምትለው የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የፍርድ መቃወሚያዋን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ታቅርብ በማለት የሰጠው ውሳኔ በጉዳዩ በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ይዘትና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን ይዘትና ተግባራዊ አፈጻጸም ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን በትእዛዝ ማፅናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 13904 ግንቦት 13 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ብይንና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 40822 ሰኔ 30 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካች የፍርድ መቃወሚያ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት ተቀብሎና የግራቀኙን ክርክር ሰምቶ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን አለው በማለት ወስነናል፡፡
3. የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበችውን የፍርድ መቃወሚያና ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 115963

ሐምሌ 8 ቀን 2008 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** አቶ ኤሊያስ ታምራት - ጠበቃ መኮንን ኪዳነ ጋር - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ አስቴር መከተ - ቀረቡ

2. የቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

1. ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች አጥር አስደግፎ የገነባውን ግንባታ እንዲያፈርስና የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ በማለት የሰጡት ውሣኔ በህግ አግባብ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርባ ከአንደኛ ተከሳሽ /አመልካች/ ጋር ወሰንተኞች ነን፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ባለሁለት ፎቅ ህንፃ ለመገንባት ከክፍሉ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ ሲወስዱ እኔም ስምምነቴን ተጠይቄ ከድንበሩ 0.70 ሣንቲ ሜትር በመራቅ ህንፃውን እንዲገነባ ተስማምቸ ፈርሜያለሁ፡፡ ሆኖም አንደኛ ተከሳሽ የከሳሽን የአጥር ግንብ ግድግዳ በማድረግ የቤቱን ፍሳሽ ወደ ከሳሽ እንዲፈስ በማድረግ ግንባታ በመገንባት ጉዳት እያደረሰብኝ ይገኛል፡፡ ስለዚህ አንደኛ ተከሳሽ በከሳሽ አጥር ግንብ ላይ የገነባውን ግንባታ እንዲያፈርስና የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ ውሣኔ ይስጥልኝ በማለት ክስ አቅርባለች፡፡
2. አመልካች በበኩሉ በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ በመሆን ቀርቦ ህንፃውን የገነባሁት በራሴ ይዞታና በተሰጠኝ የግንባታ ፈቃድ መሠረት ነው፡፡ ከከሳሽ አጥር ላይ የሰራሁት

www.abyssinialaw.com

ግንባታ የለም፡፡ የከሳሽን ይዞታ አልገፋሁም በከሳሽ ላይ የፈጠርኩት ሁከት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችና አንደኛ ተጠሪ ክርክራችንን ይደግፋልናል በማለት በተለያየ ጊዜ በቀድሞው አሰራር ቀበሌ 01/09 አስተዳደር የቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የሚመለከተው ክፍል የፃፋቸውን የተለያየ ይዘት ያላቸውን ደብዳቤዎች በማስረጃነት የያዙ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው አስፍሮታል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ ከተሰጠው የግንባታ ፈቃድ ውጭ ህንፃ በመሥራት በከሳሽ ይዞታ ላይ ሁከት የፈጠረ መሆኑ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ ሰጥቶ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ የይዞታና አስተዳደር የሽግግር ጊዜ ፕሮግራም ጽ/ቤት ሀምሌ 8 ቀን 2005 ዓ.ም የባለሙያዎች ቡድን ከቦታው ድረስ በመላክ ባደረገው ማጣራት አንደኛ ተከሳሽ /አመልካች/ በከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ/ ይዞታ ውስጥ አልገቡም፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ከመንግስት ይዞታ 26 ካሬ ሜትር የገቡ መሆኑ ተረጋግጧል የሚል መግለጫ ለሥር ፍርድ ቤት በመላኩ አንደኛ ተከሳሽ በከሳሽ ይዞታ ላይ የፈጠረው ሁከት የለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4. በዚህ ውሣኔ አንደኛ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርባለች፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት አጣርቶ ውጤቱን እንዲልክ ትዕዛዝ ሰጥቶ ጥር 20 ቀን 2006 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የክፍለ ከተማው ግንባታና ፈቃድ ቁጥጥር ጽ/ቤት ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው መልስ አመልካች ከዋናው ቤት በስተጀርባ የገነባው ሰርቪስ ኳርተር በስተቀኝ ያለው ግድግዳ ገፅ በይግባኝ ባይና በመልስ ሰጭ መካከል ባለው አጥር ላይ የተገነባ መሆኑን አይተናል የሚል የፅሑፍ መግለጫ ልኳል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ማስረጃ መሠረት በማድረግ አመልካች በአጥሩ ላይ የገነባውን ኳርተር ሰርቪስ ግንባታ ይፍረስ በአንደኛ ተጠሪ ይዞታ ላይ የፈጠረው ሁከት ይወገድ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኃላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በድምፅ ብልጫ አጽንቶታል፡፡

5. አመልካችና ተጠሪ የተስማሙበት ሰነድ ዋናው ህንፃ የሚገነባበትንና ከዋናው መንገድ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን አጥር እንጂ ሰርቪስ ክፍሉ ተደግፎ የተሰራበትን አጥር የሚመለከት አይደለም፡፡ ሰርቪስ ክፍሉ ተደግፎ የተሰራበትን አጥር ያጠርኩት አመልካች 1984 ዓ.ም ሲሆን የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር አስቀምጨበት እኖር ነበር፡፡ የውሃ ታንከሩን በማውረድ ግንባታ አካሄጀበታለሁ፡፡ ይህንን በተመለከተ አንደኛ ተጠሪ ያቀረበችው ክስ ሳይኖርና የአጥሩን ባለቤት በተመለከተ በጭብጥነት ተይዞ የግራ ቀኛችን ማስረጃ ተሰምቶ ውሣኔ አልተሰጠም ስለሆነም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ ክስ ካቀረበበት ጭብጥ ውጭ በመውጣት የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 329 (1) በሚቃረን ሁኔታ የሰጠው ውሳኔ

www.abyssinialaw.com

መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ሰኔ 30 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልክቷል፡፡

6. አንደኛ ተጠሪ ጥር 23 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች በአጥሬ ላይ ግንባታ የገነባ መሆኑን በመግለፅ ክስ አቅርቤያለሁ፡፡ አመልካች ይህንን ክስ በግልፅ ክዶ ካለመከራከሩም በላይ የክፍለ ከተማው የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የባለሙያ ቡድን በመመደብ አመልካች አንደኛ ተጠሪ አጥር ላይ ግንባታ የፈጸመ መሆኑን ማረጋገጫ አቅርበዋል፡፡ ስለዚህ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያላነሳውን የአጥር ባለሀብትነት ክርክር አቅርቧል፡፡ ስለዚህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ በሥር ፍርድ ቤትና ጉዳዩ በይግባኝ በሚታይበት ጊዜ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት የታየው ሁለተኛ ተጠሪ አመልካች ከተሰጣቸው የግንባታ ፈቃድ ውጭ የገነባ በመሆኑ የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው በማለት ጥር 23 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች መጋቢት 12 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

7. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የክፍለ ከተማው ባለሙያዎች በተለያየ ጊዜ እቦታው ድረስ በመሄድ አንድ ጊዜ አመልካች ግንባታውን የገነባው ተሻሽሎ በተሰጠው የግንባታ ፈቃድ መሠረት ነው የሚል መግለጫ የሰጡ መሆኑንና በሌላ ጊዜ ደግሞ አመልካች ከግንባታ ፈቃድ ውጭ ህንፃውን በመሥራት ከአንደኛ ተጠሪን መብት እንደተጋፋ የሚገልጽ መግለጫ ያቀረቡ መሆኑን አመልካችና አንደኛ ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቧቸውን የሰነድ ማስረጃዎች ይዘትና ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመረዳት ችለናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ የይዞታ አስተዳደርና የሽግግር ፕሮግራም ጽ/ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በባለሙያ አጣርቶ እንዲልክለት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የባለሙያ ቡድን መድቤ አድርጌዋለሁ ባለው ማጣራት አመልካች የተጠሪን ይዞታ ያልተጋፋ መሆኑን በመግለጽ ሀምሌ 8 ቀን 2005 ዓ.ም የፅሁፍ መግለጫ ሰጥቷል፡፡ በአንፃሩ ጉዳዩ በይግባኝ በሚታይበት ጊዜ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥር 20 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የባለሙያ ቡድን መድቤ ጉዳዩን አጣርቻለሁ በማለት ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም የፅሑፍ መግለጫ የሰጠው የቂርቆስ ክፍለ ከተማ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት አመልካች የሰርቪስ ኳርተር የአንደኛ ተጠሪን አጥር አስደግፎ ገንብቷል የሚል መግለጫ ያቀረበ መሆኑን ተረድተናል፡፡

8. ከዚህ አንፃር ሲታይ የክፍለ ከተማው የተለያዩ አካላት የአንደኛ ተጠሪና የአመልካችን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ባለሙያ መድበው ባደረጉት ማጣራት የደረሱበት መደምደሚያና

www.abyssinialaw.com

የሰጧቸው ደብዳቤዎች ዕርስበርሳቸው የሚቃረን ይዘት ያላቸው መሆናቸውን ከበታች ፍርድ ቤቶች ተረድተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የክፍለ ከተማው የአስተዳደር አካላት ለፌዴራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት ለሰጠው ትዕዛዝ የባለሙያ ቡድን መድበውና አጣርተው ሀምሌ 8 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው መግለጫና በተመሣሣይ ጭብጥ ላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መነሻ ከቦታው ድረስ ሄደው አጣርተዋል የተባሉ ባለሙያዎች ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም ያቀረቡት መግለጫ ዕርስ በርሱ የሚቃረን ይዘት ያለው መሆኑ ሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሣኔ ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡

9. የክፍለ ከተማው የተለያዩ አካላት በተለያዩ ጊዜ የመደቧቸው ባለሙያዎች የተለያየ ውጤት ያለው ሙያዊ መግለጫ የሚያቀርቡት በመጀመሪያ ደረጃ የሥር ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በጭብጥነት ሊያዙና ሊጣሩ የሚገቡ የፍሬ ጉዳይና የህግ ጭብጦች ሣይመሰርቱና የባለሙያዎች ቡድን አጣርቶ መግለጫ ሊያቀርብባቸው የሚገቡትን አከራካሪ ፍሬ ነገሮች ማለትም፡-

   (ሀ) አመልካች ከአንደኛ ተጠሪ ይዞታ 70 ሣንቲ ሜትር ርቀ ለመገንባት የተስማማው ባለሁለት ፎቅ ህንፃውን ብቻ ነው ወይስ ሰርቪስ ቤቱን ከአጥሩ 70 ሣንቲ ሜትር ርቆ ለመገንባት ተስማምቷል? ወይስ አልተስማማም?

   (ለ) ለአመልካች የተሰጠው የግንባታ ፈቃድ ህጋዊ ሥልጣን ባለው አካል ተጠንቶ ተሻሽሏል ወይስ አልተሻሻለም?

   (ሐ) አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ከተገነባው አጥር ላይ አስደግፎ ሰርቪስ ቤት የማይሠራ መሆኑን ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ተስማምቷል ቢባል አመልካች ሰርቪስ ኳርተር አሰጠግቶ የገነባበትን የአጥር ክፍል የገነባችው አንደኛ ተጠሪ ናት ወይስ አመልካች?

   (መ) አመልካች ሰርቪስ ኳርተሩ የተገነባበትን የአጥር ክፍል አመልካች የገነባው መሆኑ ሲረጋገጥ አንደኛ ተጠሪ አመልካች አጥሩን አስደግፎ የገነባውን ሰርቪስ ኳርተር እንዲያፈርስ ለመጠየቅ የሚያስችላት የህግ መሠረት አለ ወይስ የለም?

   (ሠ) አመልካች ሰርቪስ ኳርተሩን የገነባበትን የአጥር ክፍል የሠራችው አንደኛ ተጠሪ መሆኗ ቢረጋገጥ አመልካች አጥሩን አስደግፎ የሠራውን ሰርቪስ ኳርተር እንዲያፈርስ አንደኛ ተጠሪ ለመጠየቅ የሚያስችላት የህግ መሠረት አለ ወይስ የለም?

   (ረ) አመልካች ባከናወነው ግንባታ የአንደኛ ተጠሪን መብትና ጥቅም የሚጎዳ ህገ ወጥ ተግባር በመፈፀም በአንደኛ ተጠሪ ላይ ጉዳት በማድረስ የሁከት ድርጊት ፈፅሟል ወይስ አልፈፀመም?

   (ሰ) በአጠቃላይ አመልካች ህጋዊ ሥልጣን ባለው አካል ከተሰጠው የግንባታ ፈቃድ ውጭ ፈፅሟል ወይስ አልፈፀመም? አመልካች ከግንባታ ፈቃድ ውጭ ገንብቷል ቢባል በዚህ ግንባታ አንደኛ ተጠሪ መብትና ጥቅሟ ተነክቷል፡፡ ከግንባታ ፈቃድ ውጭ

www.abyssinialaw.com

በተሠራው ግንባታ የአንደኛ ተጠሪ መብትና ጥቅም አልተነካም ቢባል ውጤቱ ምን ይሆናል? ከግንባታ ፈቃድ ውጭ በተሠራው ግንባታ የአንደኛ ተጠሪ መብትና ጥቅም ተነክቷል ቢባል ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚሉትን ጭብጦች በግልፅ በመያዝ ባለሙያዎች ቦታው ሄደው በማጣራት በተለያየ ጊዜ ለአመልካችና ለአንደኛ ተጠሪ በተለያዩ የክፍለ ከተማው የተለያዩ አካላት የተሰጣቸውን ሰነድ ማስረጃዎች ይዘት፡- አግባብነት ካለው የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት በማድረግ አጣርተው እንዲያቀርቡ ግልፅ ትዕዛዝ ባለመስጠታቸው ልዩነት የተፈጠረ መሆኑን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለክፍለ ከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ ፕሮግራም ጽ/ቤት ሀምሌ 8 ቀን 2005 ዓ.ም በባለሙያ አጣርቶ የሰጠውን መግለጫና ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክፍለ ከተማው የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ጽ/ቤት ባለሙያ ቡድን አጣርቶ ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም በጽሁፍ የሰጠውን መግለጫ ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

10. ይህም የሥር ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በባለሙያ ተጣርተው ሊቀርቡ የሚገባቸው አከራካሪ የፍሬ ጉዳይ ጭብጦች በግልጽ ሣይመሰርቱና መጣራት የሚገባቸውን ፍሬ ጉዳዮች በውል ሣይለዩና በግልጽ ሣይዘረዝሩ ባለሙያዎች አጣርተው ያቅርቡ የሚል ጥልቅ ትዕዛዝ በመስጠታቸው ተቃራኒ ይዘት ያላቸው ማስረጃዎች (Contradictory Evidence) ከክፍለ ከተማው የተለያዩ አካላት በተለያየ ጊዜ ቦታው ድረስ ሄደው አይተው የሰጡ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 246፣ አንቀጽ 247 እና አንቀጽ 248 መሠረት አከራካሪ ጉዳዮችንና ጭብጦችን በአግባቡ ሣይመሰርቱና ሣያጣሩ ውሣኔ በመስጠት መሠረታዊ የህግ ስህተት የፈፀሙ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

11. ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ የክፍለ ከተማው ባለሙያዎች በተለያየ ጊዜ ከቦታው ድረስ በመሄድና የሥር ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለሰጡት ትዕዛዝ ተቃራኒ ይዘት ያለው አስተያየት ካቀረቡ ተቃራኒ ይዘት ካላቸው አስተያየቶች አንደኛውን ተቀብሎ ሌላውን ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል ግልፅ መስፈርትና ምክንያት ሊኖር ይገባል፡፡ በተመሣሣይ የሙያ ብቃትና ልምድ ትይዩ የሆነ ሥልጣን ያላቸው የክፍለ ከተማው የተለያዩ አካላትና ባለሙያዎች አንድ መሠረታዊ ፍሬ ጉዳይ ላይ ያቀረቡት መግለጫ ዕርስ በርሱ የሚቃረን ሆኖ ዕውነታውን ለመለየት የማያስችል በሚሆንበት ጊዜ ተቃራኒ መግለጫውን ያየው ፍርድ ቤት ጉዳዩ በክፍለ ከተማው ካለ ባለሙያዎች የተሻለ ዕውቀትና የሥራ ልምድ ባላቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚመለከተው ቢሮ ባለሙያዎች ተጣርቶ እንዲቀርብና ዕውነታው እንዲረጋገጥ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 250 እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 136 (1) መሠረት ትዕዛዝ ሣይሰጥ አንደኛውን መግለጫ ተቀብሎ

www.abyssinialaw.com

ሌላውን ዕውነት ነው ብሎ ውሣኔ ለመስጠት የሚቻልበት የህግ መሠረት የለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ ያዩት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዚህ ፍርድ ተራ ቁጥር 8 የተገለፁት ጭብጦች በግልጽ ሣይዙና እንዲጣሩ ሣያደርጉና የክፍለ ከተማው ባለሙያዎች ከሰጡት ዕርስበርሱ የሚቃረን ሙያዊ ምስክርነትና መግለጫ ዕውነታው የትኛው እንደሆነ የተሻለ ሙያ ዕውቀትና ልምድ ባላቸው የአዲስ አበባ አስተዳደር ባለሙያዎች ተጣርቶ እንዲቀርብላቸው ሣያደርጉ የሰጡት ውሣኔ ከላይ የገለፅናቸውን የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 246፣ አንቀጽ 247፣ አንቀጽ 248 አንቀጽ 250 እና አንቀጽ 136 (1) ድንጋጌዎች ያልተከተለ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57471 ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 142629 ጥቅምት 20 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 108027 ሚያዝያ 22 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዚህ ፍርድ በተራ ቁጥር 9 የተገለፁትን ጭብጦች በመያዝና እነዚህ አከራካሪ የፍሬ ነገር ጭብጦች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚመለከተው አካል የካበተ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች መድቦ አጣርቶ ውጤቱን እንዲያሳውቀው በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 136 (1) መሠረት በማድረግና ዕውነታውን ለማረጋገጥ ይጠቅማሉ ያላቸውን ሰነዶች በማስቀረብና የምስክሮችን ቃል በመስማት ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343 (1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

ሰ/መ/ቁ.101277

መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ክፍለጽዬን ማሞ

ጸውሎስ አርሺሶ

**አመልካች፡-** የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ ተወካይ አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** ሚ/ር አቤቻንድ ፖፖትላል ሜታ ወራሽ ጠበቃ አቶ ታደሰ መንገሻ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጀመረው በፕራይቬታዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ያቀረቡት አቤቱታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቀድሞ ወረዳ 2 ቀበሌ 11 በአሁኑ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 የቤት ቁጥር 271 የሆነ የቡና ማጠቢያና ማከማቻ መጋዘን ከነቢሮዎቹ ከአዋጅ ውጭ ስለተወሰደብን ይመለስልን የሚል ነው፡፡ ኤጀንሲውም ጉዳዩን አጣርቶ በአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀጽ2(3) ድንጋጌ መሰረት ከአዋጅ ውጭ በቀላጤ የተወሰደ ንብረት በሚለው ትርጓሜ ስለሚሸፈን አቤቱታ የቀረበበት መጋዘን ከነቢሮዎቹ በመርህ ደረጃ እንዲመለስላቸው ሲወስን ንብረቱን ግን ተጠሪ የሚረከበው በተጨማሪነት ለተሰሩት ክፍሎች የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ በሚያቀርበው ወጪ መሰረት ክፍያውን ሲፈጽም ነው በማለት መጋቢት 20 ቀን 2004 ዓ/ም ወስኗል፡፡ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተርም መጋቢት 28 ቀን 2004 ዓ/ም የውሳኔውን ትክክለኛነት አረጋግጦ ለመንግሥት ቤቶች አጄንሲ ጽፏል፡፡ የመንግሥት ቤቶች አጄንሲ ይግባኝ ለፕራይቤታይዜሽን ቦርድ አቅርቦ ቦርዱም የአጄንሲውን ውሳኔ የሚያስለውጥ ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም በማለት ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ/ም አጽንቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የቤት ቁጥር 271 የቡና ማጠቢያና ማከማቻ መጋዘን ከነቢሮዎቹ በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሰው ከጥቅምት 1 ቀን

www.abyssinialaw.com

1972 ዓ/ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ ለሸቀጦች ጅምላ ንግድ አስመጪ ድርጅት /ጅንአድ/በማከራየት አመልካች እያስተዳደረ የሚገኘውን ለተጠሪ ይመለስ በማለት የተወሰነው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረምልን የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ከተመረመረ በኋላ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲም ሆነ ቦርዱ አከራካሪውን ቤት ለተጠሪ እንዲመልስ የወሰኑት አመልካች በክርክሩ ተጠርቶ በአግባቡ ተከራክሮ መሆን ያለመሆኑን እና በቤቶች ኤጀንሲ ስር ሆኖ የቆዬው የድርጅት ቤትና መጋዘን ለተጠሪ ይመለስ ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 193/92 አንቀጽ 7 አንጻር ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ታህሳስ 24 ቀን 2007 ዓ/ም የተጻፈ ተቃውሞና መልስ ያቀረበ ሲሆን ተቃውሞውም የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈ በመሆኑ ክርክሩ ሊቀጥል አይገባም የሚል ነው፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለውን የውሳኔ ይዘት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ከመመርመሩ በፊት የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ አልፏል ወይስ አላለፈም? የሚለውን በቅድሚያ ተመልክተናል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፕራይቤታይዜሽን ቦርድ ውሳኔ የሰጠው ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ/ም ነው፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው በ8/9/2006 ዓ.ም ነው፡፡ ይህም የይግባኝ ውሳኔ ከተሰጠ ከአንድ ዓመት ከአስራ አንድ ወር ከሰባት ቀን በኂላ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡ አመልካች ግን የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንስ ለፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈጻጸም ውክልና ታግዶ እንዲቆይ ካደረገ በኃላ የካቲት 25 ቀን 2006 ዓ/ም እግዱን ያነሳ በመሆኑ የይግባኝ ጊዜው ሊቆጠር የሚገባው ከዚህ ቀን ጀምሮ ነው በማለት ተከራክሯል፡ ይህ ችሎት የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ አፈጻጸሙን አግዷል የተባለውን ለማጣራት ማኅደሩን በትዕዛዝ አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡ ኤጀንሲው ነሐሴ 11 ቀን 2004 ዓ/ም ለአራዳ ክፍለ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጻፈው ደብዳቤ በኤጀንሲው ውሳኔ የተጠቀሰውን ቁጥር 271 የሆነውን መጋዘንና ቢሮዎች በአፈጻጸሙ መሰረት እንዲረከቡ በማድረግ ጅንአድ ለማስረከብ ፈቃደኛ ያልሆነባቸውን ቁጥር 006፣008/1 እና 008/2 የሆኑትን መጋዘኖች በሚመለከት በተለዋጭ ደብዳቤ ለፍርድ ቤቱ እስከምናሳውቅ ድረስ አፈጻጸሙ ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ የሚል ነው፡፡በዚህ ደብዳቤ መሰረት መጀመሪያ ውሳኔ ያረፈበት ቤት አፈጻጸም አልታገደም፡፡ ይልቁንም ደብዳቤው ውሳኔ የተሰጠውን ቤት የፍርድ ባለመብት እንዲረከብ ፍርድ ቤቱ እንዲያደርግ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የአመልካች የይግባኝ ጊዜ ሊቆጠር የሚገባው ከ8/9/2006 ዓ/ም ጀምሮ ነው የሚለው ክርክር ከዚህ አንጻር ሲታይ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 22(4) እንደተደነገገው ለሰበር ሰሚ ችሎት የሚቀርበው አቤቱታ ውሳኔ በተሰጠ 90 ቀን ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ የሰበር አቤቱታውን ለማቅረብ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካጋጠመ የሰበር አቤቱታው ከመቅረቡ

www.abyssinialaw.com

በፊት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 324 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት የይግባኝ ማስፈቀጃ ማመልከቻ ቀርቦ ሊወሰን ይገባል፡፡ ይህ ባልተደረገበት ሁኔታ አመልካች ጊዜ ያለፈበትን የሰበር አቤቱታ አቅርቦ ጭብጥ ተይዞ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የመልስ ልውውጥ ያደረጉ ቢሆንም የሰበር አቤቱታው የስነ ሥርዓት ግድፈት የተፈጸመበት በመሆኑ የክርክሩን ይዘት መመርመር ሳያስፈልግ የሰበር አቤቱታውን ሰርዘናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አመልካች በህግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሰበር አቤቱታውን ያላቀረበ በመሆኑ የሰበር አቤቱታውን ውድቅ አድርገነዋል፡፡
2. የሰበር አቤቱታው መሰረዙን እንዲያውቅ የፍርዱ ግልባጭ ለፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ይላክ፡፡
3. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ በተመለከተ የግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ጥር 28 ቀን 2007 የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡ የአከራካሪው ንብረት ማህደር በመጣበት አኳኋን ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 121387

መስከረም 26 ቀን 2009 ዓ.ም.

ዳኞች - አልማው ወሌ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች - አፍሮ ፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ነ/ፈ ዘላለም ብሩክ ቀረቡ

ተጠሪዎች - 1ኛ. አቶ ያሬድ ተሾመ
2ኛ. አቶ አድማሱ መርሻ
3ኛ. አቶ ገረመው አሰፋ
} አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የተጀመረው የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች ላይ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአጭር ሁኔታ የሚወሰኑ ክርክሮች በሚታዩበት ስርዓት ታይቶ እንዲወሰን ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡

የተጠሪዎች ክስ ይዘት ባጭሩ ተከሳሹ ከ1ኛ ተጠሪ ላይ የውሃ ቦቴ ተሽከርካሪ ፣ ከ2ኛ ተጠሪ ሎደር ተሽከርካሪ እና ከ3ኛ ተጠሪ ግሪደር እና ሎደር ተሽከርካሪ በመከራየት የኪራይ ዋጋ እንደ ቅደም ተከተላቸው ብር 34,757.21 (ሰላሳ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ሰባት ከ21/100) ፣ ብር 21,555.00 (ሃያ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ አምስት) እና ብር 302,201.42 (ሶስት መቶ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ አንድ ከ42/100) ስላልከፈላቸው ይህን ገንዘብ ከነወለዱ ወጪና ኪሳራ ጨምሮ እንዲከፍል እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ቀርቦ ክሱን ለመከላከል እንዲፈቀድለት በ09/02/2008 ዓ.ም በተፃፈ ጠይቆ ተፈቅዶለት መልስ አቅርቧል፡፡ ነገር ግን አመልካች በ22/03/2008 ዓ.ም በተፃፈ ባቀረበው መልስ የተከሰሰበት ገንዘብ ያለበት መሆኑን አምኖ መልስ ሰጥቷል ተብሎ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የተከሰሰበትን ገንዘብ ከነወለዱ፣ ወጪና ኪሳራ ጨምሮ ለተጠሪዎች እንዲከፍል ተወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክስ ባላስረዱበት አግባብ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ፣ እንዲሁም የአመልካች ጠበቃ ከቅን ልቦና ውጭ ክሱን ማመኑን ተከትሎ በተጨማሪ ማስረጃ

www.abyssinialaw.com

ሊረጋገጥ ሲገባው በማመን ብቻ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው እንዲሻርልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ታዞ በሰጡት መልስ በኪራይ ውሉ መሰረት በሚመለከታቸው የድርጅቱ ኃላፊዎች ድርጅቱ ባዘጋጀው የክፍያ ማዘዣ ፎርም ላይ ተፈርሞ በተሰጣቸው የገንዘብ አለብኝ መተማመኛ ሰነድ ተደግፎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 284(ሀ) መሰረት የቀረበ ክስ በመሆኑ፤ እንዲሁም ጠበቃው የሰጠውን መልስ ከመድገም ውጭ የአሁኑ የአመልካች ጠበቃ ለቀረበው ክስ መከላከያ መልሱ በእንዲህ አይነት መልኩ መሰጠት ይገባው ነበር ባላሉበት ሁኔታ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሚዛን የሚደፋ ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም ተብሎ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በሰጠው የመልስ መልስ በተጠሪዎች የክፍያ ማዘዣ ላይ የገንዘብ መጠኑን በመጥቀስ ሰነድ የሰጣቸው መሆኑን እና ይህንኑም ሰነድ ለክሱ በማስረጃነት አያይዘው ማቅረባቸውን በመግለፅ ሆኖም ግን የስር ፍርድ ቤት ክሱን ከማስረጃው አንፃር ትክክለኛነቱን እና ተገቢነቱን ሳይመረምር የአመልካች ጠበቃ አላግባብ በማመኑ ብቻ ተቀብሎ ውሳኔ ማስተላለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው የሚለውን ክርክር በማጠናከር አቅርቧል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ እና ግራ ቀኙ በሰበር ያደረጉትን ክርክር ሲሆን በበኩላችን ክርክሩን ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች አንፃር መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ለተጠቀመባቸው የተጠሪዎች ማሽነሪዎች የሚጠበቅበትን ክፍያ አልከፈለም በሚል የገንዘቡን መጠን በመጥቀስ እንዲከፈላቸው ተጠሪዎች ክስ አቅርበዋል፡፡ ክሱም ውልን እና የገንዘብ አለብኝ ሰነድን መሰረት በማድረግ በአጭር ሁኔታ እንዲወሰን የቀረበ ነው፡፡ የአመልካች (ሥር ተከሳሽ) ጠበቃ በተወካይነቱ ቀርቦ ለመከላከል ፈቃድ ጠይቆ ቢፈቀድለትም በሰጠው መልስ '.... ከሳሾች በክሳቸው ላይ ከተከሳሽ ጋር የስራ ውል በመዋዋል ስራ መስራታቸው የሚካድ አለመሆኑን፤ ከሳሾች ክፍያው እንዲከፈላቸው ያቀረቡት የክፍያ ጥያቄ አዲስ አበባ የሚገኘው የበላይ አካል መልስ እስኪሰጥ ድረስ እንዲጠብቁ ተነግሯቸው ትዕግስት በማጣት ክስ አቀረቡ እንጂ ተከሳሽ ክፍያውን ለመፈፀም ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ አይደለም፤ ስለዚህ ተከሳሽ ድርጅት አሁንም ለከሳሾቹ ክፍያ ለመክፈል አዲስ አበባ ከሚገኘው ዋና መስሪያ ቤት ምላሽ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፤ ስለሆነም ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ይገንዘብልን .....' በማለት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት እንደተጠሪዎች ጥያቄ ገንዘቡ እንዲከፈል የወሰነው ተከሳሽ የሰጠው መልስ ገንዘቡ የሌለበት መሆኑን አልካደም፤ እንዲያውም አምኖ መከራከሩን ያሳያል በሚል ነው፡፡

የአመልካች መሰረታዊ ቅሬታ ክርክሩ የተመራበትን እና ውሳኔ የተሰጠበትን አግባብ በተመለከተ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ክርክሩን የመራበት እና ውሳኔ ላይ የደረሰበት አካሄድ የህግ ስህተት

www.abyssinialaw.com

የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ የፍትሃብሄር ሥነ ሥርዓት ህጉ በቁ 235 እና 83 ስር የሚደነግገው በግልፅ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ ይቆጠራል በሚል ሲሆን ይህ ሥነ ሥርዓታዊ ድንጋጌ እንደተያዘው ጉዳይ በልዩ ስርዓት የሚመሩና ማስፈቀጃ ተጠይቆበት በፈቃድ ለቀረበ መልስም ተፈፃሚ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ተከሳሽ ካመነ በአመነው መሰረት ውሳኔ ለመስጠት የሚከለክል በቂ የህግ ምክንያት እስከሌለ ድረስ ውሳኔ መስጠት የሚገባ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች የጠየቁት ልኩ የታወቀ ገንዘብ መሆኑንና ክሱም የተመሰረተው በውል እንዲሁም በገንዘብ አለብኝ ደረሰኝ ምክንያት መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ጉዳዩ በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት እንዲቀርብ መፍቀዱ፤ አመልካች ቀርቦ ለመከላከል ያቀረበውን ማመልከቻ መቀበሉ እና በቀረበው መልስ መሰረት ውሳኔ መስጠቱን ከተደረገው ክርክር መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ከሥነ ሥርዓት ህጉ የሙግት አመራር መርህ አኳያ ጉድለት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ባሳለፉት ውሳኔ እና ትዕዛዝ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ የአመልካችን ቅሬታ ባለመቀበል ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 21704 በ24/03/08 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 233716 በ13/04/2008 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ፤ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በፋ/ቁጥር 232726 በ15/04/2008 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ በመ/ቁ 22293 የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ከዚህ ፍርድ ቤት ታህሳስ 22/2008 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

ሩ/ለ                    የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 122249

መስከረም 26 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡-. አልማው ወሌ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ በላይ አየለ - ከጠበቃ ዮሴፍ አስምሮ ጋር - ቀረቡ

ተጠሪ፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት አዲስ ዙ ፓርክ ማዕከል -

ነ.ፈጅ አብይ አስናቀ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ሁከት እንዲወገድ እና በሁከት ምክንያት የተቋረጠ ጥቅም ይከፈለኝ በማለት የቀረበን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ክስ ይዘት በአንበሳ ግቢ ውስጥ የሚገኘውን ቦታ ገንዘብ እና ንብረት በማፍሰስ የተለያየ የልጆች መጫወቻ የተከሉበት መሆኑን፤ ስራውን ሲሰሩ የነበረው ብር 3300 /ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ብር/ በመክፈል መሆኑን፤ ተከሳሹ በጨረታ አከራያለሁ በማለት ጨረታውን ያሸነፉ ግለሰቦች ባሸነፉበት ዋጋ መቀጠል ስላልቻሉ አመልካች በሰጡት የጨረታ ዋጋ በብር 10921 /አሥር ሺህ ዘጠኝ መቶ ሐያ አንድ ብር/ እየከፈሉ እንዲቀጥሉ እና የውል ቆይታ ጊዜውም በ6 ኪሎ የሚገኘው ጽ/ቤት አዲስ እያሰራ ወዳለው የፒኮክ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እስከሚዛወር ድረስ መሆኑን በመግለጽ ተከሳሹ የጻፈላቸው መሆኑን፤ ሆኖም ተከሳሹ የውለታው ጊዜ ሳያልቅ ግቢ ለቀህ ውጣ በማለት የጻፈላቸው መሆኑን፤ በመግለጽ ተከሳሽ የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ እና በሁከቱ ምክንያት የተቋረጠባቸው ጥቅም እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የጠየቁ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ አስቀድሞ ለአመልካች የተጻፈው ደብዳቤ በሚመለከተው አካል የተጻፈ አይደለም፡፡ ተጻፈ የተባለው ደብዳቤም በሌላ ደብዳቤ ተሽሯል፡፡ አመልካች ቀርበው ውል እንዲያድሱ ጥሪ ቢደረግላቸውም ቀርበው ውል አላደሱም፡፡ እንደውል ያቀረቡት ደብዳቤም የውል ሰነድ ተደርጎ ሊቆጠር አይችልም፡፡ ንብረቱን በተሻለ ገንዘብ ለማከራየት ለአመልካች ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉ እንዲቋረጥ መደረጉ የሁከት ተግባር አይደለም፡፡ የተቋረጠ ጥቅም በማለት የቀረበው ጥያቄም በማስረጃ የተደገፈ ስላልሆነ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

www.abyssinialaw.com

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ መጋቢት 9 ቀን 2005 ዓ.ም ለአመልካች የጻፈው ደብዳቤ እንደውል ማሻሻያ የሚታይ እንጂ ተራ ደብዳቤ አይደለም፡፡ ደብዳቤው የኪራይ ማሻሻያን የሚመለከት እና የውል ቆይታ ጊዜውም በስድስት ኪሎ የሚገኘው የአዲስ ዙ ፕሮጀክት በመሠራት ላይ ወዳለው ፒኮክ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እስኪዛወር የሚገልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የውል ጊዜው ሳይጠናቀቅ አመልካች እንዲለቅ መደረጉ የሁከት ተግባር ነው በማለት ተጠሪ ሁከቱን አስወግዶ አመልካች ሥራውን እስኪጀምር ድረስ ከጥቅምት ወር 2007 ዓ.ም ጀምሮ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤትም ለአመልካች መጋቢት 9 ቀን 2005 ዓ.ም የተጻፈ ደብዳቤ በአንድ ወገን የቀረበ ጥያቄ እንጂ አስቀድሞ የነበረውን ውል ያራዘመ አይደለም፡፡ ተጠሪው ጥር 9 2006 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤም አስቀድሞ የጻፈውን ደብዳቤ ሽሮታል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በተሠጠው ስልጣን መሠረት አመልካች ለቀው እንዲወጡ ማድረጉ የሁከት ተግባር አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሠጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው የነበረ ቢሆንም አቤቱታቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ተሰርዟል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- አመልካች በአዲስ አበባ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት መጋቢት 9 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈው የውል ማሻሻያ ሰነድ ተቀብዬ በሰነዱ ላይ የተገለጸውን የዋጋ ማሻሻያ ስከፍል ቆይቻለሁ፤ በሰነዱ ላይ የኪራይ ውሉ ቆይታ ጊዜ በስድስት ኪሎ የሚገኘው የአዲስ ዙ ፕሮጀክት ጽ/ቤት አዲስ እያሰራ ወዳለው ፒኮክ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እስኪዛወር ድረስ የሚቆይ መሆኑ ተመልክቷል፤ በድጋሚ ተጽፏል የተባለው ደብዳቤም የጸና ውል እያለኝ ድጋሚ የኪራይ ውል ለማድረግ የሚያስገድደኝ አይደለም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት ይህን በማለፍ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው የሚል ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ በመሆኑ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በሰበር የተያዘው ጭብጥ ከመወሰኑ በፊት ከመነሻውም ቢሆን የሥር ፍ/ቤቶች ክርክሩን ሁከት ይወገድልኝ በማለት በተጠየቀው ዳኝነት መምራት ነበረባቸው? ወይስ አልነበረባቸውም? የሚለውን ጭብጥ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ርዕስ ሁከት እንዲወገድ እና በሁከቱ ምክንያት የተቋረጠ ጥቅም ለማስከፈል በሚል የቀረበ ቢሆንም ዝርዝር ይዘቱ ሲታይ ከኪራይ ውል አፈፃፀም ጋር የተገናኘ ነው፡፡ በግራ ቀኝ ወገኖች የሚቀርብ የክርክር ይዘት ፍ/ቤቱ ለሚይዘው ጭብጥ መሠረት ነው፡፡ በአግባቡ ያልቀረበን ክስ መነሻ በማድረግ በፍ/ቤቶች የሚሠጥ ፍርድም ፍትሐዊ ሊሆን አይችልም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች ያቀረቡትን ክስ በመቀበል የተጠሪ ተግባር ሁከት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ውሳኔ ከመስጠቱ ውጪ የክሱን ዝርዝር ይዘት በማየት ክርክሩ ከኪራይ ውል አፈጻጸም ጋር የተገናኘ መሆኑን ተገንዝቦ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 91/1 በሚፈቅደው መሠረት ክሱ እንዲሻሻል አላደረገም፡፡

የፍ/ቤቶች ዋነኛ ሚና ክርክሮች በተገቢው የሕግ ሥርዓት እንዲመሩ ማድረግ ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት በክርክሩ ላይ ባለው የመሪነት ሚና ክሱ እንዲሻሻል ማድረግ ሲገባው የቀረበውን ክስ አከራክሮ ውሳኔ መስጠቱ እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182/2 በሚደነግገው መሰረት ጉዳዩ የሚመራበትን ሂደት ማረም ሲገባው ይህንኑ ሳያርም ተጠሪ የፈጠረው ሁከት የለም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 46548 ጥር 6 ቀን 2007 ዓ.ም የሠጠው ውሳኔ፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 166197 ጥቅምት 25 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 120477 ታህሳስ 05 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረቡት ክስ በሁከት ይወገድልኝ የሚታይ ሳይሆን ከውል አፈጻጸም ጋር የተገናኘ መሆኑን አውቆ አመልካች ክሱን እንዲያሻሽሉ እና ተገቢውን ዳኝነት እንዲከፍሉ በማድረግ ግራ ቀኙን አከራክሮ የመሠለውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1 መሠረት ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ.ቁ. 46548 የሆነው መዝገብ ወደ መጣበት ይመለስ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.105677

መስከረም 30 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ጥሩነሽ ገብረወልድ

2. ወ/ሮ ላቀች ገብረወልድ

3. ወ/ሮ ሽዋረግ ገብረወልድ

4. ወ/ሮ መዓዛ ገብረወልድ

5. ወ/ሮ ዘላለም ገብረወልድ

6. አቶ ሱልጣን ናስር

} ጠበቃ ኒቆዲሞስ ጌታሁን ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ መኮንን ገብረወልድ

2. ወ/ሮ አምሳለች ገብረወልድ

3. ወ/ሮ ትዕግስት ጌታቸው

} ጠበቃ መስፍን መኮንን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 137372 ሐምሌ 11 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር

www.abyssinialaw.com

ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልካቾች መስከረም 30 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ 03 ገጽ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ክርክሩ በውርስ የሚተላለፍ ቤትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በጀመረበት በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ተከሳሾች ሲሆኑ 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሾች እንዲሁም 3ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ለጉዳዩ መነሻ ምክንያት የሆነው የአሁን 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ ክስ በአሁን ተጠሪዎች ላይ በማቅረባቸው ሲሆን የክሱ ይዘት በአጭሩ እናታቸው በሲዳማ ዞን ሁላ ወረዳ ሀገረ ሰላም ከተማ ውስጥ ስድስት ክፍሎች ያሉት መኖሪያ ቤት ሠርተው በመኖር ላይ እንዳሉ ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን ገልፀው ይህ ቤት የውርስ ንብረት መሆኑን እያወቁ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉ አመልካቾች ያለ 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ስምምነት ለ6ኛው አመልካች ሸጠውላቸው የተገኙ ከመሆኑም በላይ 6ኛው አመልካችም 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች በህይወት ያሉ ወራሾች ለመሆናቸው እያወቁ ቤቱን የገዙ በመሆናቸው መስፈርቱን ሳያሟላ የተፈፀመው የሽያጭ ውል ፈርሶ ቅድሚያ የመግዛት መብት እንዲጠብቅላቸውና በክርክሩ ምክንያት ያወጡት ወጭና ኪሳራ እንዲከፈላቸው በመጠየቅ የቀረበ ነው፡፡

አመልካቾችም ክሱ ደርሷቸው ሚያዚያ 05 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቡት በተመሳሳይ ጉዳይ ከዚህ በፊት ተከራክረውበት እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደርሶ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ አሁን የቀረበው ክስ በድጋሚ የቀረበ መሆኑን ካነሱ በኋላ በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጡት መልስ አከራካሪው ቤት የውርስ ንብረት ሆኖ ሳይከፋፈል በ1ኛ አመልካች እጅ የቆየ ቢሆንም ወራሾች ተቀራርበው በመወያየት ለመሸጥ ያደረጉት ጥረት በ1ኛ ተጠሪ ቅድሚያ የመግዛት ፍላጎት ምክንያት ሳይሳካ መቅረቱን፤ ጉዳዩ በእንጥልጥል ላይ እያለም 2ኛው አመልካች በመታመማቸው ምክንያት ለህክምና ከፍተኛ ገንዘብ በማስፈለጉ የክርክሩ ቤት በብር 65,000 /ስልሳ አምስት ሺህ ብር/ ተሽጦ ብር 50,000/ሃምሳ ሺህ ብር/ ለ2ኛው አመልካች ህክምና መዋሉን፤ አመልካቾች ውሉን ካለመፈረማቸው ውጭ በሽያጩ የተስማሙና ምንም ጉዳት ያልደረሰባቸው መሆኑን ገንዘባቸውን ያልወሰዱ ወራሾችም አሁን መውሰድ እንደሚችሉ በመግለፅ ክርክር አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በአሁን አመልካቾች በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመግለፅ የሰጠው ዳኝነት የሁላ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻር በመሆኑ አሁን የቀረበው ክስ በድጋሚ የቀረበ ነው ለማለት አይቻልም በማለት ውድቅ አድርጎ በማለፍ

www.abyssinialaw.com

በፍሬ ጉዳዩ ላይ የግራቀኙን ወገኖች ክርክር እና ማስረጃዎች በመመርመር ውሉ ረቂቅ በመሆኑ ሊፈርስ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት ይግባኙን ሠርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ዳኝነት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የስር ፍ/ቤቶች ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ሲሆን አቤቱታው በአጭሩ የሥር ፍርድ ቤቶች አስቀድሞ ክርክር ተደርጎበት የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ በድጋሚ የቀረበ ክስ ተቀብለው በማከራከር መወሰናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልና ሌሎችንም ቅሬታዎች በመዘርዘር አቅርበዋል፡፡

ሰበር አጣሪው ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ ለቀረበባቸው የክስ አቤቱታ ከዚህ ቀደም በሲዳማ ዞን ሁላ ወረዳ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው ክርክሩ እስከ ፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርደ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ በውሳኔ በተቋጨ ጉዳይ ድጋሚ ክስ ሊቀርብ አይገባም በማለት ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በሥር ፍርድ ቤቶች ታልፎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪዎች መልሳቸውን አመልካቾችም የመልስ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ እኛም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ምላሽ ማግኘት የሚገበው ነጥብ በተያዘው ጉዳይ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው አመልካቾች አጠናክረው የሚከራከሩት በተመሳሳይ ጉዳይ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ሁላ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከራክረን የተወሰነ በመሆኑ አሁን የቀረበው ክስ በድጋሚ የቀረበ ነው በማለት ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው በተመሳሳይ ጉዳይ ክርክር የተደረገበት መሆኑን ሳይክዱ በድጋሚ ክስ ከማቅረብ አንከለከልም የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር ይከራከራሉ፡፡

በእኛ በኩል ይህንን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያከራከረበትን መዝገብ ቁጥር 176201 እንዲሁም ግራቀኙ ወገኖች አስቀድሞ እስከ ፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክርክር አድርገናል በማለት የጠቀሱትን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር

www.abyssinialaw.com

መዝገብ ቁጥር 63360 አስቀርበን ለሰበር አቤቱታው መቅረብ ምክንያት የሆነው ክስ በድጋሚ የቀረበ መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡ ከመዝገቦቹ ምርምራ እንደተረዳነውም የአሁን 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ህዳር 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈና ለሁላ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01984 በአሁን አመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ ለክርከሩ ምክንያት የሆነው ያልተከፋፈለ የውርስ ንብረት ከፈቃዳችን ውጭ በብር 65,000 ተሸጦብናልና ውሉ ሊፈርስ ይገባል ሲሉ ክስ አቅርበው የወረዳው ፍርድ ቤት ጥር 24 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሉ ሊፈርስ እንደማይገባ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች በዚሁ የሁላ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው በመዝገብ ቁጥር 17810 የካቲት 12 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ይግባኙን ሰርዞ ሲያሰናብታቸው ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው የነበሩ ሲሆን ሰበር ሰሚው ችሎትም ጉዳዩን ከተመለከተ በኋላ በመዝገብ ቁጥር 37450 ህዳር 30 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ክርክሩ በሁለት ክልል ነዋሪዎች መካከል የሚደረግ በመሆኑ ጉዳዩን በሰበር የማየት ሥልጣን እንደሌለው በመግለጽ ተጠሪዎች ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ጉዳያቸውን እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎችም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለኝም ማለቱ ቅር አሰኝቷቸው ቅሬታቸውን በዚሁ ነጥብ ላይ በማተኮር ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት አቅርበው የነበሩ ቢሆንም የክልሉ ሰበር ሰሚ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም ማለቱ የሚነቀፍበት መሠረታዊ የህግ ስህተት የለውም በማለት በሰበር መዝገብ ቁጥር 63360 ላይ በሰጠው ትዕዛዝ ጉዳዩ ለሰበር ሊቀርብ እንደማይገባ ወስኗል፡፡

አመልካቾችና ተጠሪዎች ለሰበር አቤቱታ መቅረብ ምክንያት ከሆነው ክርክር አስቀድመው በተመሳሳይ ጉዳዩ ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን የሁላ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገሩ ላይ የሰጠው ውሳኔ ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቀርቦበትም ይግባኙ የተሰረዘ በመሆኑ እንደፀና ለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪዎች የሚከራከሩት ጉዳዩን ለክልል ሰበር አቅርበን ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመግለፅ መዝገቡን የዘጋው ቢሆንም በፍሬ ነገሩ ላይ ጉዳዩን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበን ስላላሳየን በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቷል ሊባል አይችልም በማለት ነው፡፡

በመሠረቱ ተጠሪዎች የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመግለፅ ሰበር አቤቱታቸውን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት እንዲያቀረቡ ቢታዘዙም ቅሬታቸውን ለፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለው ተብሎ እንዲወሰንላቸው እንጂ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥላቸው አልነበረም፡፡ ይህ ደግሞ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ሰበር አቤቱታ

www.abyssinialaw.com

አለመቅረቡ በሁላ ወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠውንና በይግባኝ ያልተሻረውን ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሆን የሚከለክለው አይደለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች በሁላ ወረዳ ፍርድ ቤት ተወስኖ በከፍተኛው ፍርድ ቤትም ባልተሻረው የፍሬ ነገር ውሳኔ ላይ እስከመጨረሻው ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አቅርበው ውሳኔውን አላስለወጡም፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው ተከራካሪዎች የሁለት ክልል ነዋሪዎች ናቸው፡፡ መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልል በሆኑ ተከራካሪዎች መካከል የሚደረግ ክርክር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ለመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(2) ተደንግጓል፡፡ የክልል ወረዳ ፍርድ ቤቶች ደግሞ በውክልና የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ሥልጣን መመልከት እንደማይችሉ ከኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የሁላ ወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ያየው የሥረ ነገር ሥልጣን ሳይኖረው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ጉዳይ ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን በሌለው ፍርድ ቤት ታይቶ የተወሰነ ውሳኔ በይግባኝ ካልታረመ በስተቀር ውሳኔው በጉዳዩ ላይ የመጨረሻና አስገዳጅነት ያለው መሆኑ የሚቀርበት ምክንያት እንደሌለ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር መዝገብ ቁጥር 85718 እና በሌሎች የተለያዩ የቅርብ ጊዜ ውሳኔዎች ላይ በተሻሻለው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 454/1997 መሠረት አስገዳጅ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡ ስለሆነም ይህ በሁላ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01984 የተሰጠና የሥነ ሥርዓት ህጉን ተከትሎ ያልተሻረ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 212 መሠረት ተቀባይነት ያለውና የመጨረሻ ውሳኔ ነው፡፡

ቀጥሎ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ሥልጣን በሌለው ፍርድ ቤትም ቢሆን የተሰጠና በይግባኝ ያልተሻረ ውሳኔ እያለ ተጠሪዎች በተመሳሳይ ጉዳይ አዲስ ክስ ማቅረባቸው ተገቢ ነበር ወይ? የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትስ ክሱ በድጋሚ የቀረበ አይደለም በማለት ማለፉ ተገቢ ነበር ወይ? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ከላይ እንደገለፅነው አንድ የዳኝነት አካል የሥረ ነገር ሥልጣን ባይኖረውም እኳን የሰጠው ውሳኔ ሥርዓቱን ተከትሎ እስካልተሻረ ድረስ የፀናና የመጨረሻ በመሆኑ ይህ ውሳኔ እያለ አዲስ ክስ በተመሳሳይ ጉዳይ ማቅረብ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5 ሥር የሚሸፈን ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ አዲስ ክስ ማቅረብ መሆኑ አያከራክርም፡፡ ስለሆነም የአሁኑ ተጠሪዎች ለፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ አስቀድሞ በሁላ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01984 ከአመልካቾች ጋር በተከራከሩበት ጉዳይ ላይ በመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(1) ሥር የደነገገውን በሚቃረን ሁኔታ በድጋሚ የቀረበ ሆኖ እያለ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መቃወሚያውን ተገቢ ያልሆነ ምክንያት በመስጠት ማለፉና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ አለማረሙ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 176201 መጋቢት 02 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 137372 ሐምሌ 11 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ለሰበር አቤቱታው መቅረብ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ህዳር 24 ቀን 2002 ዓ.ም በሁላ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍርድ ያለቀ በመሆኑ ተጠሪዎች ይህንን ውሳኔ ሥርዓቱን ተከትለው ሳያሽሩ ሌላ ክስ ማቅረብ አይችሉም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5(1) መሠረት ወስነናል፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔያቸው የተሻረ መሆኑን እንዲያውቁት የዚህ ችሎት ውሳኔ ግልባጭ ይተላለፍላቸው፡፡
4. ከሥር ፍርድ ቤቶች የመጡት መዝገቦች ይመለሱ ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ክርክር ለወጣ ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 108647

ሕዳር 15 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሀ መሰለ

አብዩ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ወርቂቱ ገመዳ -አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ደመቀች ብርሃኑ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ውርስ እንዲጣራ በማለት የቀረበ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ አመልካች በዚህ የሰበር ክርክር የሌሉ አቶ ሳህሉ ብርሀኑ እና ወ/ት አባይነሽ ብርሃኑ እንደ ቅደም ተከተላቸው ተጠሪዎች፤ የአሁን አመልካች ደግሞ ጣልቃገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአመልካቾች ክስ ይዘት በአጭሩ ከሟች አባታቸው መቶ አለቃ ብርሃኑ አያኖ በውርስ የተላለፈላቸው በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ቤ.ቁ 389 የሆነው ቤት ከሥር ተጠሪዎች ጋር በጋራ ይዘው በአሳባው እየተጠቀሙበት መሆኑን፤ድርሻቸው ሳይለይ ቢቀጥል ችግር ሊገጥማቸው የሚችል መሆኑን በመጥቀስ ውርስ አጣሪ ተሹሞ ውርሱ እንዲጣራ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የሥር 1ኛ ተጠሪ ድርሻቸውን በስምምነት ይዘው እየተጠቀሙበት መሆኑን በመግለጽ ውርሱ ሊጣራ አይገባም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሥር 2ኛ ተጠሪም የይርጋ መቃወሚያ በማንሳት ውርሱ ሊጣራ አይገባም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ የአሁን አመልካች ተጠቃሹን ቤት ይዘው የሚያስተዳድሩት እና ተጠሪ በንብረቱ የማይጠቀሙ መሆኑን በመጥቀስ የተጠሪ ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል በማለት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤት አመልካች ወደ ክርክሩ ጣልቃ የገቡት ፈልገው ነው፤ በውርስ ማጣራቱ ሂደት የሚስትነት ድርሻ ካላቸው ለአጣሪው ማስረጃቸውን ከሚያቀርቡ በቀር የውርስ ሀብቱ እንዳይጣራ ለመቃወም የሚያስችል መብት የላቸውም፤ ያነሱት የይርጋ

www.abyssinialaw.com

ጥያቄም ከውርስ ማጣራት ጋር የሚገናኝ አይደለም በማለት አመልካች ያቀረቡትን የይርጋ መቃወሚያ በብይን ውድቅ በማድረግ የሟች መቶ አለቃ ብርሃኑ አያኖን የውርስ ሀብት የሚያጣራ ውርስ አጣሪ እንዲሾም አድርጓል፤ ውርስ አጣሪው ያቀረበውን ሪፖርት ከመረመረም በኃላ አመልካች የሟች ሚስት በመሆናቸው አከራካሪው ቤት የሟች እና የአመልካች የጋራ ሀብት እንደሆነ ይገመታል፤ የተጠሪ ምስክሮች ቤቱ የተሰራበትን ትክክለኛ ጊዜ አላስረዱም፤ ቤቱ በውርስ ወይም በሌላ መንገድ ለሟች የተላለፈ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፤ የስጦታ ውል ነው በማለት የቀረበው ሰነድም ቦታ እንጂ ቤቱ ለሟች የተላለፈ መሆኑን አያሳይም፤ የሟች አባት አቶ አያኖ አደራ ለሟች አቶ ብርሃኑ አያኖ ቤት መስራታቸውን ያሳያል የተባለው ሰነድም አዋሳኙን ያልገለጸ እና አከራካሪውን ቤት የሚመለከት ነው ሊባል የማይችል በመሆኑ ክርክር የቀረበበት በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ቤ.ቁ 389 የሆነው ቤት የሟች መቶ አለቃ ብርሃኑ አያኖ እና የአመልካች የጋራ ሀብት ነው፤ ቤቱን ተከፋፍለው በመኖሪያ ቤትነት እና በማከራየት ሲጠቀሙበት የነበረ በመሆኑ የቤት ኪራይን በተመለከተ በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ የተዘረዘሩት ነገሮች ተሰርዘዋል፤ ለበር ማሠሪያ ተጠሪ ያወጡትን ወጪ ድርሻቸው ተቀንሶ አመልካች እና የሥር ተጠሪዎች ሊከፍሏቸው ይገባል በማለት ውርስ አጣሪው ያቀረበውን ሪፖርት በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ በተጠሪ በኩል ቀርበው የተሰሙት ምስክሮች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ሟች መቶ አለቃ ብርሃኑ አያኖ አመልካችን ከማግባታቸው በፊት በአባታቸው አቶ አያኖ አደራ ተሰርቶ የገቡበት እና እየኖሩበት የነበረ መሆኑን ያስረዱ በመሆኑ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 389 የሆነው ቤት ሟች አቶ ብርሃኑ አያኖ አመልካችን ከማግባታቸው በፊት በግላቸው የነበራቸው ቤት ነው በማለት ተጠቃሹ ቤት የሟች አቶ ብርሃኑ አያኖ የውርስ ሀብት ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጓል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር በፍ/ቤት የተፈቀደለት ወገን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስቶ እንዳይከራከር የሚከለክል ሕግ በሌለበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረብኩትን የይርጋ መቃወሚያ በብይን ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም፤ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ሟች አባታቸው ከወላጅ እናታቸው በውርስ የተላለፈላቸው ይዞታ ላይ ቤት ሰርተው በስጦታ የተላለፈላቸው ነው በማለት ከሚከራከሩ በቀር አቶ አያኖ አደራ ቤቱን ሰርተው ለሟች አባታቸው የሰጡ መሆኑን በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር በሌለበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪ ካቀረቡት ክርክር ውጪ በመውጣት የሰጠው

www.abyssinialaw.com

ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱቱታ ተመርምሮ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ መደረጉን እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪ ካቀረቡት የክርክር መሥመር ውጪ በመውጣት አከራካሪው ቤት የአመልካች እና የሟች የጋራ ሀብት ነው በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ የመሻሩን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎ የጽሑፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ በብይን ውድቅ ካደረገው በኋላ በብይኑ ላይ በይግባኝም ሆነ በመስቀለኛ ይግባኝ አቤቱታ ቀርቦበት ይርጋውን በተመለከተ የተወሰነ ነገር ስለሌለ ይህ ችሎት በይርጋው ላይ የተያዘውን ጭብጥ የመመርመር ስልጣን የለውም፤አመልካች እና ተጠሪ በአከራካሪው ቤት ውስጥ የራሳችንን ክፍል ይዘን የምንኖርበት በመሆኑ ቤቱ በአመልካች እጅ ብቻ አይደለም፤ አመልካች መብታቸው በማይነካበት ሁኔታ የራሳቸውን መብት ለማስከበር ጣልቃ በገቡበት ክርክር የይርጋ መቃወሚያን ሊያነሱ አይችሉም፤ሟች የውርስ ሀብቱን ያገኙት ከማነው የሚለው ነጥብ የፍሬነገር ክርክር እና የማስረጃ ምዘና በመሆኑ ችሎቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተመለከተው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ወደ ዋናው ጉዳይ ከመገባቱ በፊት ጉደዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች ወደ ክርክሩ ጣልቃ የገቡት ፈልገው በመሆኑ በውርስ ማጣራቱ ሂደት የሚስትነት ድርሻ ካላቸው ለአጣሪው ማስረጃቸውን ከሚያቀርቡ በስተቀር የውርስ ሀብቱ እንዳይጣራ ለመቃወም የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ በአግባቡ ነው?ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች ውርሱ እንዳይጣራ ለመቃወም የሚያስችል መብት የላቸውም ከሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለው አመልካች ወደ ክርክሩ የገቡት ፈልገው ነው፤ በውርስ ማጣራቱ ሂደት የሚስትነት ድርሻ ካላቸው ለአጣሪው ማስረጃቸውን ከሚያቀርቡ በስተቀር የውርስ ሀብቱ እንዳይጣራ ለመቃወም የሚያስችል መብት የላቸውም በሚል መሆኑን ከሰጠው ብይን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሥር ፍ/ቤቱ የደረሰበት ይህ ድምዳሜ ተገቢ መሆን አለመሆኑ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች ይዘት ጋር በማገናዘብ ሊመረመር ይገባል፡፡በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት የሙግት ተካፋይ ስለመሆን አስመልክቶ ከተደነገጉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች ውስጥ ሦስተኛ ወገኖች በጣልቃ ገብነት

www.abyssinialaw.com

የክርክር ተካፋይ መሆን ስለሚችሉበት ሥርዓት የተደነገገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 ድንጋጌ ተጠቃሽ ነው፡፡

ይህ ድንጋጌ በአንድ ክርክር ያገባኛል የሚል ማናቸውም ሦስተኛ ወገን ከፍርድ ውሳኔ በፊት ጣልቃገብ ሆኖ ለመከራከር እንዲችል እንዲፈቀድለት ማመልከት ስለሚችልበት እና በክርክሩ ተካፋይ ለመሆን ሊፈቀድለት ስለሚችልበት ሥርዓት የሚደነግግ ነው፡፡የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማ ክርክርን በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ በመምራት ፍትሀዊ ውሳኔ መስጠት ነው፡፡ ተጠቃሹ ድንጋጌም ይህን ዓላማ የማሳካት ዓይነተኛ ሚና ያለው በመሆኑ የድንጋጌው አተገባበርም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማ ጋር በማገናዘብ ሊሆን ይገባል፡፡ የሥነሥርዓት ሕጉ ዓላማም ሊሳካ የሚችለው በድንጋጌው መሠረት ጣልቃ እንዲገባ የተፈቀደለት ተከራካሪ ወገን አለኝ የሚለውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያም ሆነ የፍሬነገር ክርክር ማቅረብ ሲችል ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በዚህ ድንጋጌ መሠረት ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ ጠይቀው ተፈቅዶላቸው የክርክሩ ተካፋይ እንደሆኑ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ያሳያል፡፡ አመልካች በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ከተፈቀደላቸው በኋላ ያላቸው መብት ለጉዳዩ ይጠቅመኛል ያሉትን መከራከሪያ ማቅረብ እንደሆነ ከድንጋጌው ይዘት እና ዓላማ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አከራካሪው ጉዳይ አመልካች ጣልቃገብ ተከራካሪ ወገን በመሆናቸው በሚያቀርቡት መከራከሪያ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ማቅረብ ይችላሉ? ወይስ አይችሉም? የሚለው ነው፡፡

አንድ ተከራካሪ ወገን አለኝ የሚለውን መከራከሪያ ሳያቀርብ የሚሰጠው ውሳኔ ፍትሐዊ ሊሆን አይችልም፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 234/1/ሐ ተከሳሽ በሚያቀርበው መከላከያ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካለው በመከላከያ መልሱ መግለጽ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ አመልካች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ እስከተፈቀደላቸው ድረስ ይህ ድንጋጌ በሚፈቅደው መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካላቸው ዘርዝረው የማቅረብ መብት ያላቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች ጣልቃገብ ተከራካሪ ወገን ስለሆኑ ውርሱ እንዳይጣራ ለመቃወም የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት ወደ ዋናው ጉዳይ በመግባት ውሳኔ መስጠቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 ድንጋጌን ትክክለኛ አተገባበር ያልተከተለ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ የሥር ፍ/ቤት የይርጋ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ በሰጠው ብይን ላይ በይግባኝ ወይም በመስቀለኛ ይግባኝ ቅሬታ ቀርቦበት ውሳኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ ይህ ችሎት በይርጋው ላይ የተያዘውን ጭብጥ የመመርመር ሥልጣን የለውም በማለት መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡ ሆኖም ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት ከመነሻውም ቢሆን አመልካች ውርሱ እንዳይጣራ ለመቃወም የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት የአመልካችን መቃወሚያ ያልተቀበለው እና ጉዳዩ በይርጋ ይታገዳል? ወይስ አይታገድም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ

www.abyssinialaw.com

ብይን ያልሰጠበት በመሆኑ አመልካች የይርጋ መቃወሚያውን መሠረት በማድረግ ይግባኝ ወይም መስቀለኛ ይግባኝ ማቅረብ ነበረባቸው የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ ተጠሪ በዚህ አግባብ ያቀረቡትን መከራከሪያ አልተቀበልነውም፡፡

በአጠቃላይ ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች ውርሱ እንዳይጣራ ለመቃወም የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት ብይን መስጠቱ፤ በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶችም ይህንኑ ሳያርሙ ማለፋቸው መሰረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ147733 ጥቅምት 03 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 107370 ታሕሳስ 15 ቀን 2007 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በውርስ ማጣራቱ ሂደት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 መሠረት ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር የተፈቀደለት ተከራካሪ ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሠረት አለኝ የሚለውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስቶ መከራከር ይችላል ብለናል፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ላይ በጉዳዩ ተከራካሪ የነበሩት ወገኖች የሚያቀርቡትን ክርክር በመስማት እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ ተገቢ የሆነ ብይን እንዲሰጥበት፤ የሚሰጠው ብይን የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የሚሰጥ ከሆነ በዋናው ጉዳይ ላይ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1 መሠረት ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ እና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## ትዕዛዝ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የመ.ቁ 147733 የሆነው መዝገብ ወደመጣበት ይመለስ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.105956

ህዳር 19 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሡናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡-አምሣሉ ወርቁ ኮንስትራክሽን ድርጅት

ተጠሪ፡- ትድሃር ኤስካቬሽንና ኤርዝ ሙቪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍትብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 188 መሠረት በመዝገብ ቁጥር 32664 ያጣራውን የገንዘብ መጠን ውድቅ በማድረግ፣ በራሱ የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማትና ተገቢውን ማጣሪያ በማድረግ፣ ተጠሪ ለአመልካች የሚከፍለው ብር 1,500,144/አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ አንድ መቶ አርባ አራት ብር/ ብቻ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ ይግባኝ ሰሚል ችሎት ማፅናቱ በህግ አግባብ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡
2. ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው በክልሉ ጠቅለይ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የክርክሩ መነሻ ከሳሽ/አመልካች/ ያቀረበው የክስ ማመልቻ ነው፡፡ ከሳሽ ከተከሳሽ ድርጅት ጋር ጥር 6 ቀን 2006 ዓ.ም በተዋዋልኩት የግንባታ ሥራ ውል 1,00,000 ሜትር ኪዩብ ድንጋይ ለማውጣት ተስማምቻለሁ በውሉ መሠረት በሰኔ 8 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ስራውን ቀጥዬ በቀን 1500 ሜትር ኪዩብ ድንጋይ ለማንሳት ተስማምቻለሁ፡፡ ተከሳሽ ሰኔ 16 ቀን 2004 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቶኛል፡፡ ነሐሴ 2 ቀን 2004 ዓ.ም ተቆጣጣሪ መሃንዲሱ ያለምንም ማስጠንቀቂያ ጥሎኝ ሄዷል እኔም ካለተቆጣጣሪ መሃንዲሱ መሥራት ስለማልችል 10 ቀናት

www.abyssinialaw.com

ያህል ማሽነሪዎችን ያቆምኩ ሲሆን ተከሳሹን ስጠይቀው ከዋናው ኮንተራክተር ጋር ያደረገው ንዑስ የሥራ ውል የተቋረጠ መሆኑን ገልጿል፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ ከሳሽ ለ30 ቀናት ሠርቼ 54,000 ሜትር ኪዩብ ያነሳሁበትንና ለአስር ቀናት ማሽኖች የቆሙበት በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጣራው መሠረት ብር 5,800,000 ማሽኖች ከቆሙበትና ከሻት ጋር የነዳጅ ወጪ በመቀነስ ተከሳሽ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

3. ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ ከሳሽ ብር 300,000የ/ሶስት መቶ ሺህ ብር/ ቅድሚያ ክፍያ ወስዶ 100,000 ሜትር ኪዩብ በስልሳ ቀናት ውስጥ አንስቶ እንዲጨርስ ከተከሳሽ ጋር ተስማምቷል፡፡ በውላችን መሠረት ከሳሽ በቂ ማሽነሪ በማሠማራት በቀን 5,500 ኪዩብ ድንጋይና አፈር ለማንሳት ተስማምቷል፡፡ ሆኖም ከሳሽ በውሉ የተገለፀውን ስልሣ ቀን ለማጠናቀቅ ስድስት ቀናት ሲቀረው የውል ግዴታውን ለመፈፀም ባለመቻሉ ውሉ እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ ከሳሽ በክሱ የገለፀውን 54,000 ሜትር ኪዩብ አፈርና ድንጋይ አላነሳም፡፡ ዋናው ኮንትራክተር ሲሲሲሲ ከተከሳሽ ጋር የነበረውን የሥራ ውል አቋርጦ ከሳሽ የሠራውን ሥራ ሲረከብ የተሠራው ጠቅላላ የእስካቬሽን ሥራ 8997 ሜትር ኪዩብ መሆኑንና ከዚህ ውስጥ ከሳሽ የሠራው 2416.79 ሜትር ኪዩብ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ከሳሽ ይህንን ሥራ ለመምራት የወሰደው 5021 ሊተር ነዳጅ ሲሆን ከሳሽ ከሠራው ሥራ የወሰደው የነዳጅ ዋጋ ሲቀነስ ቀሪው ብር 195,660.50/አንድ መቶ ዘጠና አምስት ሽህ ስድስት መቶ ስልሳ ብር ከሃምሣ ሣንቲም/ ነው፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ ያቀረቡት ገንዘብ የሌለ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልን በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

4. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር በገባው የሥራ ውል መሠረት ለሥራ ያሰማራቸው ማሽነሪዎች በቀን ሥምንት ሠዓት ሠርተው ምን ያህል መጠን ያለው የኢስካቬሽን ሥራ መሥራት እንደሚችሉ ከሙያ አንፃር መርመረው አስተያየት እንዲሰጡበት ለአራት የተለያዩ ድርጅቶች ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ የፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ከደረሳቸው መካከል የኦሮሚያ ክልል ከተማና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መሰረት ለመገመት እንደማይችል ገልፆ መልስ የሰጠ ሲሆን፣ ሳፍኮን ኮንስትራክሽን የተባለው ድርጅት በቀን ከ320 ሜትር ኪዩብ እስከ 384 ሜትር ኪዩብ ይሆናል በማለት በፅሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ አረጋ አባተ ኮንስትራክሽን የተበለ ድርጅት በቀን 1400 ሜትር ኪዩብ ሊያነሱ ይችላሉ በማለት መልስ የሰጠ ሲሆን የምስራቅ ሸዋ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ጽ/ቤት በቀን 1120 ሜትር ኪዩብ ማንሳት ይችላሉ በማለት በጽሑፍ መልስ የሰጠ መሆኑን የክልል ጠቅለይ ፍ/ቤት በውሣኔው በግልፅ አስፍሮታል፡፡

www.abyssinialaw.com

5. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሳፍኮን የተባለው ድርጅት ማሽነሪዎች በቀን 320 ሜትር ኪዩብ ያነሳሉ በማለት የሰጠውን መግለጫ በመወሰድ አመልካች በአርባ ስድስት ቀናት 14720 ሜትር ኪዩብ ድንጋይና አፈር ለማንሳት የሚችል በመሆኑ የአንድ ሜትር በብር 102 /አንድ መቶ ሁለት ብር/ ሒሳበ ተከሳሽ ለከሳሽ ብር 1,500,144/አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ አንድ መቶ አርባ አራት ብር/ ተከሳሽ ለከሳሽ ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቷል፡፡ አመልካች በይግባኝ ሰሚው ችሎት በመልስ ሰጭነት ቀርቦ ለይግባኝ ባይ /ተጠሪ/ ይግባኝ ቅሬታ መልስ ከመስጠቱ በተጨማሪ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 340 መሠረት መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን መስቀለኛ ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ በሌላ በኩል ይግባኝ ሰሚው ችሎት የተጠሪን ይግባኝ በመቀበልና ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር በመመርመር ይግባኝ ባይ /ተጠሪ/ ለመልስ ሰጭ የምከፍለው ብር 195,660.05 /አንድ መቶ ዘጠና አምሰት ሺ ስድስት መቶ ስልሣ ብር ከዜሮ አምስት ሣንቲም / ብቻ ከዚህ ውስጥ  መልስ ሰጪ /አመልካች /ከይግባኝ ባይ /ተጠሪ/ የወሰደው ብር 300000 /ሶስት መቶ ሺህ ብር/ ቅድመ ክፍያ ያለ በመሆኑ መልስ ሰጪ /አመልካች/ ከይግባኝ ባይ ከሰራው ስራ በላይ ገንዘብ የወሰደ በመሆኑ ይግባኝ ባይ ለመልስ ሰጪ የሚከፍለው ገንዘብ የለም በማለት  ሰጥቷል፡፡

6. አመልካች መስከረም 10 ቀን 2007 ዓ.ም ፅፎ ባቀረባቸው የሰበር አቤቱታ የምስራቅ ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዲተሮች መድቦ፣ አመልካች ከተጠሪ የሚጠይቀው ብር 5,828,590/አምስት  ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ብር/ ያለው መሆኑን በማረጋገጥ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረብኩት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 188 መሠረት ሒሳብ አስተሳስቦ የተሰጠውን ውሣኔ በማስረጀነት በማያያዝ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን ማስረጃ ውድቅ በማድረግ ሌላ የባለሙያ አስተያየት መጠየቅና ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ የሰጠው የቻይና መንገድ ሥራ ኩባንያ /CCCC/ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፃፈውን ደብዳቤ ነው፡፡ ሆኖም የቻይና መንገድ ሥራ ኩባንያ ደብዳቤውን የፃፈው ከተጠሪ ያገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ መሆኑን በደብዳቤ የገለፀውን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሣያገናዝብ  ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ  የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሮ የምስራቅ ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባፀደቀውና ተጠሪ በይግባኝ

www.abyssinialaw.com

ያላሻረው ብር 5,828,509.76 /አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ዘጠኝ ብር ከሰባ ስድስት ሣንቲም/ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

7. ተጠሪ የካቲት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ባቀረበው መልስ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና ስህተት የፈፀመበት መሆኑን በሰፊው በመግለፅ ነው፡፡ የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና ስህተት በዚህ ሰበር ችሎት የሚታይና የማይታረም በመሆኑ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ያሰናብተን፣ አመልካች የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሒሳብ ባለሙያዎችን በመመደብ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ተጠሪ የመክፈል ሃላፊነት ያለበት መሆኑ ተረጋግጧል በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ በመሠረቱ አመልካችና ተጠሪ የምንከራከርበት ጉዳይ የፌዴራል ጉዳይ ነው፡፡ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መጠኑ በአመልካች ክስ ማመልከቻ የተገለፀውን የፌዴራል ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን የለውም፡፡ በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዳኝነት የማየት ስልጣን በሌለው ጉዳይ ሒሳብ ታስቦ እንዲቀርብ ለኦዲተሮች የሰጠው ትእዛዝም ሆነ ኦዲተሮች ያቀረቡለትን ሪፖርት በማፅደቅ የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሣኔ ምንም አይነት የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ፡፡ አመልካች ይግባኝ ሰሚው ችሎት የቻይና መንገድ ሥራ ድርጅት የፃፈውን ደብዳቤ በአግባቡ ያልመዘነ መሆኑን በመግለፅ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የማስረጃ ምዘና ስህተት ክርክር ነው ይህም የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ሊደረግልኝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካች መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

8. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ይዘት ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትን ጉዳይ ለመወሰን፣ የሚከተሉትን የህግ ጭብጦች በዝርዝር ማየትና መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዝርዝር መታየት ያለባቸው ጭብጦችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ/የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን የሒሳብ ማስተሳሰብ ጥያቄ ተቀብሎ ኦዲተሮች በመመደብና ኦዲተሮች አጣርተው ያቀረቡለትን ሪፖርት በመዝገብ ቁጥር 32664 ታህሳስ 24 ቀን 2005 ዓ.ም በማፅደቅ የሰጠውን ውሣኔ እንደማናቸውም የሰነድ ማስረጃ መዝነው ውድቅ ማድረጋቸው ህጋዊ አሠራርን የተከተለ ነው ወይስ አይደለም? አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ሪፖርቱን በማፅደቅ የሰጠው ውሣኔ በይግባኝ ያልተሻረ

www.abyssinialaw.com

በመሆን ሙሉ በሙሉ ክሱን ለማስረዳት ተቀበይነት ያለው ማስረጃ ተደርጐ መወሰድ አለበት በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ መሠረት አለው ወይስ የለውም?

ለ/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቻይና መንገድ ሥራ ኩባንያ CCCC የዓፈውን ደብዳቤ ተቀበይነትና የአስረጅነት ብቃት ያለው ማስረጃ ነው በማለት ለውሣኔው መሠረት ማድረግ የማስረጃ አመዛዘን መርሆዎችን የተከተለ ነው ወይስ አይደለም? ይግባኝ ሰሚው ችሎት ደብዳቤውን የማስረጃ አቀባበልና አመዛዘን ሥርዓትና መርህ ተከትሎ አልመዘነም ቢባል ውጤቱ ምን ይሆናል?

ሐ/የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትና የፌራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አስገዳጅ የሆኑ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ድንጋጌዎችን በመከተል መጣራት የሚገባቸው አከራካሪ ጭብጦች በአግባቡ እንዲጣሩ በማድረግ ውሣኔ ሰጥተዋል ወይስ አልሰጡም?የሚሉትን ጭብጦች አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መመርመር የሚጠይቅ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

9. <u>የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 32664 ኦዲተሮች ያቀረቡትን ሪፖርት በማፅናት የሰጠውን ውሣኔ በተመለከተ፡-</u> አመልካች ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 32664 ያቀረበው ጥያቄ፤ ተጠሪ የሚፈለግበት ገንዘብ ተጣርቶ ቀርቦ እንዲከፈል ውሣኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው አይደለም፡፡ አመልካች ያቀረበው ጥያቄ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኦዲተሮች በመመደብ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 188 መሠረት ሒሳብ ያስተሳስበኝ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ይህም አመልካች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ጥያቄ ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 300 እስከ ፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 306 በተደነገገው ሥርዓት ወይም ከፍትሐበሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 307 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 314 በተደነገጉት ልዩ ሁኔታዎች የማይሸፈንና በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት /Accelerated procedures/ ታይቶ ውሣኔ የሚሰጥበት ጉዳይ እንዳልሆነ ከህጉ ድንጋጌዎች ዝርዝር ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

10. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪን ሒሳብ የሚያስተሳስቡ ኦዲተሮች የመደበውና የኦዲተሮች ሪፖርት ያፀደቀው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 188 መሠረት እንደሆነ በመዝገብ ቁጥር 32664 ታህሳስ 24 ቀን 2005 ዓ.ም የኦዲተሮችን ሪፖርት ባፀደቀበት ውሣኔ ጠቅሷል፡፡ ይህም በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 188 ሒሳብ አስተሳሳቢ የመመደብ ሥልጣን ያለው ዋናው ጉዳይ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለውና የግራ ቀኙን ክርክር የሰማው ፍርድ ቤት ነው ወይስ ዋናው ጉዳይ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን የሌለው ጥያቄ የቀረበለት ማናቸውም ፍርድ ቤት የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 188 በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ በምዕራፍ ስድስት ስለ ፍርድና ስለ ትእዛዝ በሚለው ርዕስ ውስጥ የተደነገገ ድንጋጌ ነው፡፡ ስለ ፍርድና ስለ ትእዛዝ የተደነገጉት ድንጋጌዎች በክፍል አንድና በክፍል ሁለት የተከፈሉ

www.abyssinialaw.com

ሲሆን በክፍል አንድ ሥር አጠቃላይ ድንጋጌዎች ከፍትሐበሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 180 እስከ ፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ 184 የተደነገተትን ድንጋጌዎች የሚያካተት ነው። የምዕራፍ ስድሰት ክፍል 2 በአንድ አንድ ውሣኔ ስለሚሰጥ የተለየ መመሪያ የሚደነገግበት ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 188 እስከ ፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር191 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የያዘ ነው።

11. ከላይ የገለፅነው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ምዕራፍ ስድስት በክፍል አንድና በክፍል ሁለት ሥር የተደነገጉት ድንጋጌዎች፣ ጉዳዩ በዳኝነት አይቶ፣ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ፍርድ ሲሰጥ ሊከተላቸው የሚገቡ ሥነ ሥርዓቶችንና በዋናው አከራካሪ ጭብጥ ላይ ፍርድ ከሰጠ በኂላ በቀጣይነት ሊሰጣቸው የሚገቡ የተለያዩ ትእዛዞችን የሚያሳዩ ድንጋጌዎች ናቸው።ከዚህ አንፃር በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ምዕራፍ ስድስት በጠቅላላውና ተከራከሪዎቹ ሒሳብ ተሰርቶ እንዲቀርብ በፍትሐብሔር ሥነ ሥዓርዓት ሕግ ቁጥር 188 መሠረት ልዩ ተፈፃሚነት ያለው ትእዛዝ ለመስጠት ፍርድ ቤቱ ከሳሽና ተከሳሽ ያቀረቡትን የተሟላ ክርክር ለማሰማትና ማስረጃ በመቀበልና በመመዘን ከሳሽና ተከሳሽ በሚከራከሩበት ጉዳይ ላይ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 3 መሠረት ፍርድ ለሚለው ቃልና ትአዛዝ ለሚለው ቃል በተሰጠው ትርጉምና ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 280 እስከ ፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 291 የተደነገጉትን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ጉዳዩን በዳኝነት አይቶ ፍርድ እና ልዩ ተፈፃሚነት ያለው ትእዛዝ የመስጠት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የሚመለከት ሥርዓት ነው።

12. ከዚህ አንፃር የፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 188 አንድ ሰው ጉዳዩን በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ለሌለው ማናቸውም ፍርድ ቤት ከተከሳሽ ጋር ሒሳብ እንድተሳሰብ ትእዛዝ ይሰጥልኝ የሚለውን ጥያቄ ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚያገለግል የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ አይደለም።የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 188 ድንጋጌ ይዘትም ሆነ መሠረታዊ ዓላማ አንድ ሰው ከሌላ ሰው አለኝ የሚለውን ሒሳብ በባለሙያ ተጣርቶ እንዲቀብር ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ሥልጣን ለሌለው ለማናቸውም ፍርድ ቤት ጥያቄ እንዲያቀርብ ለመፍቀድ የተደነገገ የስነ ስርዓት ህግ ድንጋጌ አይደለም። በአንጻሩ ጉዳዩን በዳኝነት የማየት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ፍርድ ከሰጠ በኃላ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ገንዘብ መተሳሰብን የሚጠይቅ ሲሆን፣ ሒሳቡ ተሰልቶ እንዲቀርብ ቀጣይ ትዕዛዝ ሊሰጥ ስለሚችልበት ሁኔታ የሚደነግግ ነው። ከዚህ አንጻር ሲታይ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበትን ጉዳዩ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ስልጣን የሌለው መሆኑ ህገ መንግስቱን አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 4 እና የአዋጅ ቁጥር 25/1988 ድንጋጌ በማየት ለመረዳት ይቻላል። ከዚህ አንጻር ሲታይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ

ቤት በዳኝነት አይቶ ለመወሰን በማይችለው ጉዳይ ላይ የሒሳብ ባለሙያዎች የአመልካችንና የተጠሪን ሒሳብ ሰርተው ሪፖርት እንዲያቀርቡለት የሰጠው ትዕዛዝና ሪፖርት ከቀረበለት በኋላ ሪፖርቱን በማጽደቅ የሰጠው ውሳኔ የፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 188 ደንጋጌ ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ ውጭ የሰጠውና በፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር “ፍርድ” “ውሳኔ” እና ትዕዛዝ ለሚሉት ቃላት የተሰጠውን ህጋዊ ትርጉም የማያሟላ መሆኑን ተረድተናል፡፡

13. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 32664 ኦዲተሮችን መድቦ፣ ኦዲተሮች አጣርተው ያመጡለትን ሪፖርት በማጽደቅ የሰጠው ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ፣ ህጋዊ አስገዳጅነትና ተፈጻሚነት እንዳለው የፍርድ ቤት ፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ለማየት የሚያስችል ባህሪም ሆነ ይዘት የለውም፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድምዳሜ ህጋዊ ስርዓትን የተከተለ አይደለም፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድምዳሜ የሚነጻጸረው ጉዳዩን የማየት ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ከሰጠው ፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ጋር ሳይሆን፣ ከፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 132 እስከ ፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 135 በተዘረጋው ስርዓት መሰረት አከራካሪ ፍሬ ጉዳይ በምትክ ዳኛ ተጣርቶ እንዲቀርብ በተሰጠ ትዕዛዝ መሰረት ምትክ ዳኞች በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 134 መሰረት ከሚያቀርቡት የሒሳብ ምርመራ ውጤት ጋር ነው፡፡

14. በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሒሳብ አጣርተው እንዲቀርቡ የተመደቡ ኦዲተሮች በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተመደቡ ምትክ ዳኞች ወይም ባለሙያዎች አይደሉም፡፡ አመልካችንና ተጠሪን የሚያከራክራቸው መሰረታዊ ጭብጥ አመልካች ከተጠሪ ጋር በገባው የኮንስትራክሽን ስራ ውል መሰረት፣ መንገድ ከሚሰራበት ስፍራ ቆፍሮ ያነሳው ድንጋይና አፈር ምን ያህል ኪዩብክ ሜትር ነው የሚለው የምህንድስና ሙያ የሚጠይቅ ሆኖ እያለ በሒሳብ ባለሙያዎች የኦዲት ምርመራ ውጤት የቀረበበት በመሆኑ፣ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ እና በይግባኝ የማየት ስልጣን ያላቸው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሌለው የዳኝነት ስልጣንና በህግ ከተደነገገው ስርዓት ውጭ ኦዲተሮች (ምትክ ዳኞች) መድቦ ያጸደቀውን ሪፖርት እንደማኛውም የሰነድ ማስረጃ ህጋዊ ተቀባይነት (legal admissibility) ያለውና ተዓማኒነት ያለው መሆኑን መዝነው ውድቅ በማድረግ ጉዳዩን በሌላ መንገድ የማጣራትና ሌላ ማስረጃን መሰረት በማድረግ ለመወሰን የተከተሉት ስርዓት የፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 135 እና ሌሎች የማስረጃ አቀባበልና አመዛዘን መርሆችን የተከተለ ምንም አይነት የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

15. የቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) የተጻፈው ደብዳቤ በተመለከተ፣ አመልካችና ተጠሪ አመልካች በሰራው ስራና ጨርሶ ባነሳው ድንጋይና አፈር መጠንና ተጠሪ ለአመልካች

www.abyssinialaw.com

ሊከፍል በሚገባው የገንዘብ መጠን ላይ ሰፊ ልዩነት ያላቸው በመሆኑ ግራ ቀኙ የሚካካዱበትን ጭብጥ ለመወሰን በጉዳዩ ገለልተኛ ሆኖ ትክክለኛ ማስረጃ ሊሰጥ ይችላል ተብሎ የተሰጠው የቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ፣ አከራካሪውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች የሰራው የኢስካቬሽን ስራ መጠን አጣርቶ እንዲያሳውቀው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የደረሰው የቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) በቁጥር CCCC(E) AA/2013/56 እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ህዳር 11 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መልስ ሰጥቷል፡፡

16. የቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ ከላይ ቁጥሩ በተገለጸው ደብዳቤ ለፍርድ ቤቱ በሰጠው ምላሽ ተጠሪ 241647 ሜትር ኩዩብ ትልቅ ድንጋይና 283 ሜትር ኩዩብ ቀላል ድንጋይ አነስቶ ገንዘቡ ተከፍሎት እንደተሰናበት ከገለጸ በኃላ በደብዳቤው መደምደሚያ ላይ "በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት ከኢትዮጵያ መንገዶች ስራ ጋር ኩባንያችን CCCC አንድ ላይ በመሆን እንዳንለካ ቦታው በሰብቤዝና በአስፓልት ተሸፍኗል፡፡ ስለሆነም የመርመርነው ከመልስ ሰጭው በተገኘው የጽሁፍ ማስረጃ ነው" በማለት ግልጽ አድርጓል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቻይና መንገድ ስራ ካንፓኒ በደብዳቤው የገለጻቸውን ፍሬ ነገሮች የራሱን የሰነድ ማስረጃዎች መነሻ በማድረግ ሳይሆን የስር ተከሳሽ (ተጠሪ) የቀረበለትን የሰነድ ማስረጃ መሰረት በማድረግ የሰጠው መረጃ መሆኑን በመገንዘብ ውድቅ አድርጎታል፡፡

17. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግን፣ የደብዳቤውን ሙሉ ይዘት ሳይመረምር በተለይም CCCC በደብዳቤው የገለጻቸውን ፍሬ ነገሮች ያገኘው የስር ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ የቀረበለትን የሰነድ ማስረጃ በመመልከት እንደሆነ የገለጸው መደምደሚያ ህጋዊ ውጤት ሳያገናዝብ ደብዳቤው የአስረጅነት ብቃት ያለው የሰነድ ማስረጃ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ የይግባኝ ሰሚው ችሎት አሰራር አንድ ማስረጃ ሊመዘን የሚገባው ከማስረጃው ውስጥ ከሳሽን ወይም ተከሳሽን የሚጠቅመውን ክፍል ነጥሎ በመወሰድ ሳይሆን የማስረጃውን ሙሉ ይዘት በመመርመርና በመመዘን መሆን ይኖርበታል የሚለውን መሰረታዊ የማስረጃ አመዛዘን መርህ የሚጥስ ነው፡፡ የቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) በደብዳቤው የገለጻቸውና ፍሬ ነገሮች ያገኛቸው ተከሳሽ (ተጠሪ) ከቀረበለት የሰነድ ማስረጃ መሆኑን እንደገለጸ ሳያገናዝብና CCCC የሰጠው መረጃ የተከሳሽን (ተጠሪን) የቀረበበት ሰነድ ላይ ብቻ የተመሰረተ መሆኑ በራሱ የተከሳሽን ማስረጃ በቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) በኩል ተጽፎ ቁጥር ተሰጥቶና ደብዳቤው የተጻፈበት ቀን ተገልጾና በማህተም ተረጋግጦ እንዲቀርብ ከማድረግ ውጭ የተለየ ህጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑን ሳያገናዝብ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ደብዳቤውን ለውሳኔው መሰረት አድርጎ መጠቀሙ ከላይ የገለጽነውን የማስረጃ አመዛዘን መርህ ያልተከተለ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

18. ከዚህ አንጻር ሲታይ የቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) የጻፈው ደብዳቤ ተጠሪ በመከራከሪያነት ያቀረባቸውን የሰነድ ማስረጃዎች በሌላ መንገድ የሚገልጽና የሚደግም ሰነድ እንጅ ስለአከራካሪው ጭብጥ በቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) ወይም በሌላ ሶስተኛ ወገን (ኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን) እጅ ያሉትን፣ ሰነዶች መሰረት በማድረግ የተጻፈ ደብዳቤ ባለመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይህንን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

19. <u>***መጣራት የሚገባቸው ፍሬ ጉዳዩች ስለመጣራቸው***</u>፣ከላይ እንደተገለጸው የቻይና መንገድ ስራ ድርጅት (CCCC) ተጠሪ የቀረበለትን ሰነድ መሰረት በማድረግ የጻፈውን ደብዳቤ ሙሉ ይዘት ሳይመዘን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ የማስረጃ አመዛዘን መሰረታዊ መርህ ያልተከተለ ነው፡፡ ይህም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠው መጣራት የሚገባቸውን አከረካሪ ፍሬ ጉዳዬች በአግባቡ በማጣራት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ እንድንመረምር የሚያስገደድ ነው፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሒሳብ ባለሙያዎች መድቦ ያገኘውን የኦዲት ሪፖርትም ሆነ የቻይና የመንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) የጻፈውን ደብዳቤ አከራካሪውን ጭብጥ ለማስረዳት ተቀባይነትና የአስረጅነት ብቃት ያላቸው ማስረጃዎች አይደሉም በማለት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አከራካሪውን ጭብጥ ሌሎች ባለሙያዎች የመንግስትና የግል ድርጅቶች በኩል ተጣርቶ እንዲቀርብለት የሰጠው ትዕዛዝ የፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 250 እና የፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 136(1) ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

20. አከራካሪው የህግ ጭብጥ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው ውል መሰረት የሰራው የኢስካቬሽን ስራ መጠንና ለዚህ ስራው ሊከፈለው የሚገባው ገንዘብ ምን ያህል ነው የሚለውን አጣርተው መግለጫ እንዲያቀርቡለት ያዘዛቸው አራት ድርጅቶች የተለያየና ተቃራኒ ይዘት ያለው አስተያየት አቅርበውለት እያለ የአንደኛውን "ሳፍኮን" የተባለው ድርጅት የሰጠውን የሙያ አስተያየት ተቀብሎና የሌሎቹን የሙያ አስተያየት ውድቅ አድርጎ ውሳኔ የሰጠበት ህጋዊ ምክንያት ምንድን ነው የሚለው ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለጉዳዩ አጥንተው የሙያ አስተያየት እንዲሰጥ ትዕዛዝ ከሰጣቸው ድርጅቶች አንደኛው ማለትም የኦሮሚያ ከተማና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ፣ ለመገመት እንደማይቻል የገለጸለት ሲሆን ሳፍኮን ኮንስትራክሽን የተባለው አመልካች በቀን 320 ኩዩቢክ ሜትር ያነሳል በማለት የገልጸ ሲሆን አርጋ አባተ ኮንስትራክሽን የተባለ ድርጅት አመልካች በቀን 1400 ኪዩብክ ሜትር አፈርና ድንጋይ ያነሳል በማለት ገልጿል፡፡ የምስራቅ ሸዋ ዞን ኢንዲስትና ከተማ ጽ/ቤት በበኩል አመልካች በቀን 1120 ኩዩቢክ ሜትር ያነሳል በማለት ጽፋል፡፡

www.abyssinialaw.com

21. ከላይ የገለጽነው ተቃራኒ ይዘትና የተለያየ የሙያ አስተያየት በተሰጠበት ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያለምንም ህጋዊ ምክንያትና መነሻ ሳፍኮን የተባለው ድርጅት የሰጠውን የሙያ አስተያየት በመቀበል አመልካች በቀን 320 ኩብቢክ ሜትር ስራ ይሰራል በማለት የሰጠውን አስተያየት በመቀበልና በሌሎች ድርጅቶች የሰጡትን የሙያ አስተያየቶች ውድቅ በማድረግ መወሰኑ ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ አንጻር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከተለያዩ የመንግስትና የግል ተቋማት የሚሰሩ በጉዳዩ ላይ በቂ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 136(1) መሰረት በመመደብ የተመደቡት ባለሙያዎች፡-

ሀ. አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገው ውል መሰረት የኤስካቬሽን ስራ ሲሰራ የተጠሪ አማካሪ ማህንዲስ ስራውን ሲቆጣጠርበት የነበረውን ሳይት ቡክ፣

ለ. አመልካችና ተጠሪ ማሽነሪዎች በየቀኑ ለምን ያህል ሰዓት እንደሰሩ የመዘገቡበትን ሰነድ፣

ሐ. አመልካች የተጠቀመው ነዳጅ 5021 (አምስት ሺ ሃያ አንድ ሊትር) ነዳጅ አመልካች ለስራ ባሰማራቸው ማሽነሪዎች ምን ያህል የኢስካቬሽን ስራ ሊያሰራ እንደሚችል በመገመት፣

መ. ተጠሪ ከቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) በአመልካችና በራሱ አቅም ለሰራው የኢስካቬሽን ስራ ምን ያህል ክፍያ እንደተከፈል በማጣራትና፣

ሠ. የተጠሪ አማካሪ መሀንዲስ፣ ስራው ከሚሰራበት ቦታ ለቅቆ ከመሄዱ በፊት፣ አመልካች ምን ያህል ኩዩብክ ሜትር አፈርና ድንጋይ እንዳነሳ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ይዞ በመቅረብ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 246(1) መሰረት ትዕዛዝ በመስጠትና ሌሎች አከራካሪውን ፍሬ ጉዳይ ለመወሰን የሚጠቅሙ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን በትዕዛዝ በማቅረብና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ አንቀጽ 246፣ አንቀጽ 247፣ አንቀጽ 248፣ አንቀጽ 145(1) አንቀጽ 136(1) እና  አንቀጽ 264(1) መሰረት አጣርቶ መወሰን ሲገባው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይ በገለጽነው ሁኔታ ጉዳዩን በማጣራት ሳይሆን ተቃራኒ ይዘት ካላቸው ሙያዊ አስተያየቶች የአንደኛውን ድርጅት አስተያየት መርጦ በመውሰድ መወሰኑ ከላይ የጠቀሰናቸውን የህግ ድንጋጌዎች ያልተከተለና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፈጸመውን ስህተት ሳያርም አመልካች ያቀረበውን መስቀልኛ ይግባኝ ውድቅ ማድረጉና የቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) የጻፈውን ደብዳቤ ብቻ መሰረት በማድረግ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 160114 ሚያዝያ 9 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 100383 ሀምሌ 28 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሙያው በቂ ዕወቀትና ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 136(1) መሰረት መመደብና በዚህ ፍርድ በተራ ቁጥር 20 ከ "ሀ እስከ ሠ" የተዘረዘሩ መሰረታዊ ጉዳዮች መነሻ በማድረግ አጣርተው እንዲያቀርበለት በማደረግ ትክክለኛ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚያስችሉ የሰነድ ማስረጃዎች በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 145(1) መሰረት በትዕዛዝ በማስቀረብና ተጠሪን በመወከል ስራውን ሲያሰራ የነበረውን አማካሪ መሃንድስና ሌሎች ጠቃሚ የምስክርነት ቃል ሊሰጡ የሚችሉ ሰዎች በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 264(1) መሰረት በምስክርነት ቀርበው ቃላቸውን እንዲሰጡ በማድረግ፣ አመልካች ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው ውል መሰረት የሰራው የኢስካቬሽን ስራ መጠኑ ምን ያህል ነው? ተጠሪ ለአመልካች መክፈል የሚገባው ክፍያ (ገንዘብ) ምን ያህል ሊሆን ይገባል የሚሉትን ጭብጦች አጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ጉዳዩን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 343(1) መሰረት መልስን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 109563

ሕዳር 26 ቀን 2009 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

**አመልካቾች፡-** 1. አሰፋ መንግስቱ ኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ኪራይ - የቀረበ የለም

2. ኒያላ ኢንሹራንስ ኩባንያ አክስዮን ማህበር (በሰበር መዝገብ ቁጥር 109563 አመልካች) ጠበቃ ጌታቸው ጎንፋ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አክስዮን ማህበር የቀረበ የለም

ይህንን መዝገብ ከሰበር መዝብ ቁጥር 109563 ጋር አጣምረን በመመርመር የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ተመልክቶ ይግባኙ ተቀባይነት የለውም በማለት መሰረዙ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ሊታረምልን ይገባል በማለት 1ኛ አመልካች ጥር 29 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ፤ 2ኛው አመልካች ደግሞ ጥር 22 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የየራሳቸውን የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ክርክሩ በመኪና አደጋ ለደረሰ ጉዳት ካሳን ለማስከፈል በመዳረግ የቀረበ ክስን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በጀመረበት በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ ሲሆኑ 1ኛ አመልካች ተከሳሽ 2ኛ አመልካች ደግሞ ጣልቃ ገብ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ለጉዳዩ መነሻ

www.abyssinialaw.com

ምክንያት የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ጥቅምት 27 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ ክስ በ1ኛው አመልካች ላይ በማቅረባቸው ሲሆን የክሱም ይዘት በአጭሩ፡-ንብረትነቱ የ1ኛ አመልካች የሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-31175 ኢት. መኪና ንብረትነቱ የተጠሪ ደንበኛ አቶ ሙላት ሳጃ የሆነውን የሰሌዳ ቁጥሩ 3-14981 የሆነ መኪና በመግጨት ላደረሰው ጉዳት ተጠሪው ለደንበኛቸው የከፈሉትን ብር 159,626.68 /አንድ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ስድስት ብር ከስልሳ ስምንት ሳንቲም/ የጉዳት አድራሹ መኪና ባለቤት የሆኑት 1ኛ አመልካች ለክርክሩ ከሚወጣ ወጭና ኪሳራ ጋር እንዲተኩላቸው ለማስወሰን የቀረበ ነበር፡፡

1ኛ አመልካችም ክሱ ደርሷቸው ህዳር 18 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ሰሌዳ ቁጥሩ 3-31175 ኢት. የሆነው መኪና የ1ኛ አመልካች ንብረት ስለመሆኑ አምነው አደጋው የደረሰው በ1ኛ አመልካች መኪና ጥፋት ሳይሆን በተጠሪ ደንበኛ መኪና ጥፋት መሆኑን፣ከፖሊስ የቀረበው ማስረጃ የሚታመን አለመሆኑን፣ በ1ኛ አመልካች መኪና ላይ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ከገለፁ በኋላ ተጠሪ ጥፋተኛውን በአግባብ ሳይለዩ ለደንበኛቸው የከፈሉትን ገንዘብ 1ኛ አመልካች የመተካት ኃላፊነት የሌለባቸው መሆናቸውን በመከራከሪያነት ካቀረቡ በኋላ ለጉዳቱ ኃላፊ የሚባሉበት ምክንያት ካለም ለ1ኛ አመልካች መኪና የኢንሹራንስ ሽፋን የሰጠው የአሁን 2ኛ አመልካች ኒያላ ኢንሹራንስ ኩባንያ አክስዮን ማህበር ወደ ክርክሩ ገብቶ እንዲከራከር እንዲታዘዝላቸው አመልክተዋል፡፡

የአሁን 2ኛ አመልካች የሆነው ኒያላ ኢንሹራንስ አክስዮን ማህበር ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ በሰጠው መልስ በማስረጃነት የቀረበው የፖሊስ ሪፖርት ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም የ1ኛ አመልካች መኪና የቀኝ መስመሩን ይዞ አሸዋ ሲጭን የተጠሪ ደንበኛ መኪና ከሌላ አቅጣጫ በፍጥነት መጥቶ የ1ኛ አመልካችን መኪና በመግጨቱ የደረሰ ጉዳት ነው፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የፖሊስ ሪፖርቱ በመርማሪው ባለሙያ ሳይዘጋጅ ያላግባብ የቀረበ ነው፡፡ በምርመራ ሂደቱ ላይ የተሳተፈው የፖሊስ አባል ቀርቦ ምስክርነት እንዲሰጥ ይደረግልን ካለ በኋላ የኢንሹራንስ ሽፋን መጠኑም ብር 100,000/አንድ መቶ ሺህ ብር/ መሆኑን በመግለፅ ክርክር አቅርቧል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራቀኙን ወገኖች የቃል ክርክር እና ማስረጃዎች በመስማት፣በጉዳዩ ላይ ቅሬታ ቀርቦበት ድጋሚ ምርመራ ተደርጓል የተባለ በመሆኑ ይኸው የፖሊስ የምርመራ መዝገብ እንዲቀርብ፣እንዲሁም ስለ ሁኔታው ያውቃሉ የተባሉት የፖሊስ አባል ቀርበው ምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ በማድረግ ካጣራ በኋላ አደጋው የደረሰው በ1ኛ አመልካች መኪና ጥፋት ለመሆኑ በቀረበው ምስክሮች ቃል ከፖሊስ መምሪያ በተጻፈ ደብዳቤ እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ያመች ዘንድ አስቀርቦ ከሰማው ምስክር ቃል መገንዘብ መቻሉን ገልፆ የመኪናው ባለቤት የሆኑት 1ኛ

www.abyssinialaw.com

አመልካች ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ፣ 2ኛው አመልካች በበኩላቸው ለ1ኛው አመልካች ተሽከርካሪ በሰጡት የኢንሹራንስ ሽፋን መነሻነት ኃላፊ ሆነው በመገኘታቸው ሁለቱም አመልካቾች በተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት ብር 159,626.68/አንድ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ስደስት ብር ከስልሳ ስምንት ሳንቲም/ ጉዳዩ ውሳኔ ካገኘበት ከጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ክፍያው ተፈፅሞ እስኪጠናቀቅ ከሚታሰብ 9% ወለድ እና ከክርክር ወጭ ብር 1,000/አንድ ሺህ ብር/ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካቾች ቅር በመሰኘት የየራሳቸውን የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት ይግባኙን ሠርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ዳኝነት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የስር ፍ/ቤቶች ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ሲሆን 1ኛ አመልካች በዚህ የሰበር መዝገብ እንዲሁም 2ኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 109563 ላይ የየራሳቸውን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የ1ኛው አመልካች የሰበር አቤቱታ በአጭሩ፡- የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ማስረጃን መሠረት ያደረገ አለመሆኑን፣ለውሳኔው መሰረት የሆነው የፖሊስ ሪፖርትም በሀሰት የተዘጋጀ መሆኑን፣ለደረሰው አደጋ ጥፋተኛው የተጠሪ ደንበኛ መኪና ስለመሆኑ የተረጋገጠ ማስረጃ አቅረበው በበቂ ሁኔታ ክሱን ማስተባበላቸውን፣ በድጋሚ የተሰራው የትራፊክ ምርምራ ለውሳኔው መሰረት መደረጉ ተገቢ አለመሆኑን፣የ1ኛ አመልካች ማስረጃዎች የታለፉበት ምክንያት በግልፅ አለመጠቀሱን፣ ኒያላ ኢንሹራንስ ወደ ክርክሩ ገብቶ እስከ ብር 100,000 ለ1ኛ አመልካች የኢንሹራንስ ሽፋን የሰጠ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሮ እያለ የ1ኛ አመልካች ኃላፊነት እስከ ብር 159,626.68 በአንድነትና በነጠላ መወሰኑ ተገቢ አለመሆኑን በመግለፅ እንዲታረምላቸው ያቀረቡት ነው፡፡ 2ኛው አመልካች በመዝገብ ቁጥር 109563 ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ደግሞ በይዘቱ ከ1ኛው አመልካች ቅሬታ ጋር የሚመሳሰል ሆኖ በአጭሩ፡- የሥር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ አለመወሰኑን፣የአመልካቾች ማስረጃ ውድቅ የተደረገው በተገቢው ምክንያት ላይ ተመስርቶ አለመሆኑን፣ተጨማሪ ማስረጃ ለማቅረብ የጠየቁበት የማስፈቀጃ ጥያቄ ያላግባብ ውድቅ መደረጉን የሚመለከት ነው፡፡

ሰበር አጣሪው ችሎቱም ሁለቱንም መዝገቦች መርምሮ በዚህ ጉዳይ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች አንፃር አመልካቾች የደረሰውን ጉዳት የመተካት ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ይህ የሚታለፍ ከሆነ የኃላፊነት መጠኑን አስመልክቶ

www.abyssinialaw.com

በአንድትና በነጠላ ይክፈሉ የተባለበትን አግባብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ መልሳቸውን አመልካቾችም የመልስ መልሳቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ እኛም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንፃር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካቾች የሚከራከሩት ጉዳት መድረሱን ሳይክዱ ጉዳቱ በተጠሪ ደንበኛ መኪና አሽከርካሪ ጥፋት የደረሰ በመሆኑ 1ኛው አመልካችም ሆነ ለእርሱ የኢንሹራንስ ሽፋን የሰጠው 2ኛው አመልካች ጉዳቱን ለመካስ ኃፊነት የለብንም፤ በዚህ ረገድ በማስረጃ ያረጋገጥነው ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ባግባቡ ታይቶ የተወሰነ አይደለም የሚል የጋራ ክርክር ያቀረቡ ሲሆን 1ኛው አመልካች ኃላፊነት አለብህ የምባል ቢሆን እንኳን ብር 100,000 በ2ኛው አመልካች ተሸፍኖ ቀሪውን 2ኛው አመልካች እንዲከፍል ሊወሰን ይገባል እንጂ ሁለቱ አመልካቾች በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ሙሉን ጉዳት እንድንክስ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም በሚል አቅርበዋል፡፡ 2ኛው አመልካችም ተጨማሪ ማስረጃ እንድናቀርብ ጠይቀን ሳይፈቀድ ቀርቷል የሚል ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ከግራቀኙ ወገኖች ክርክር አንፃር ሲታይ የሥር ፍርድ ቤት ኃላፊነት ያለበትን ወገን በመለየት ረገድ የፈፀመው መሰረታዊ የሆነ የክርክር አመራርና በማስረጃ የማጣራት ስህተት አለ ወይስ የለም? 1ኛ አመልካች ከ2ኛ አመልካች ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ሙሉውን የካሳ መጠን ለተጠሪ እንዲከፍሉ መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? በአጠቃላይ የሥር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የፈፀሙት መሠረታዊ የህግ ስህተት አለ ወይስ የለም? የሚሉት ነጥቦች ምላሽ ማግኘት ያለባቸው መሆናቸውን ተገንዝበናል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ ስንመለከት ከመዝገቡ እንደተረዳነው ንብረትነቱ የ1ኛው አመልካች የሆነው ሰሌዳ ቁጥሩ 3-31175 እና ንብረትነቱ የተጠሪ ደንበኛ አቶ ሙላት ሳጃ በሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-14981 በሆነው ተሽከርካሪ መካከል በተፈጠረ የግጭት አደጋ በተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ ሲሆን በአመልካቾች በኩልም ቢሆን የቀረበው ክርክር የተጠሪ ደንበኛ መኪና አልተጎዳም የሚል ሳይሆን የ1ኛ አመልካች ተሽከርካሪ ጥፋት የሌለበት በመሆኑ ካሳውን ለመክፈል ኃላፊነት የለብንም በማለት መከራከራቸውን ተገንዝበናል፡፡ ከሁለቱም አመልካቾች ክርክር መረዳት እንደተቻለው የተጠሪ ደንበኛ መኪና በፍጥነት መጥቶ ቆሞ አሸዋ ሲጭን የነበረውን የ1ኛ አመልካች መኪና በመግጨት የደረሰ ጉዳት ለመሆኑ ይከራከራሉ፡፡ በጉዳዩ ላይ በወቅቱ ፕላን የማንሳትና የምርመራ ሥራ ተከናውኖ እንደነበርና ይህ የትራፊክ ፕላን አነሳስ እና የምርመራ ተግባር ችግር እንዳለበት ለሚመለከተው የኦሮሚያ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን አቤቱታ ቀርቦ ሌላ ጉዳዩን በድጋሚ የሚያጣራ አምስት አባላት ያሉት ቡድን ተቋቁሞ ምርመራ ተደርጎ እንደነበር አመልካቾች ሳይክዱ አቅርበን ያሰማናቸው የመጀመሪውን ምርመራ ያከናወኑ አባላትን

www.abyssinialaw.com

በማስረጃነት አቅርበን አሰምተን እያለን ማስረጃችን ያለ ምክንያት ተቀባይነት አጥቷል በሚል ይከራከራሉ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው አስቀድሞ የተደረገው ምርመራ ችግር እንዳለበት ታምኖበት እንደገና እንዲጣራ በመደረጉ ምክንያት የኂለኛው መርማሪ ቡድን ያገኛቸውን ማስረጃዎች መሠረት አድርገው የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት ይከራከራሉ፡፡

በመሠረቱ ፍርድ ቤቶች ተገቢውን የክርክር አመራር መከተል እንዳለባቸው፣ጉዳዩን ባግባቡ በማጣራት የግራቀኙን ወገኖች ማስረጃ በማስማትና ለፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ በሆነም ጊዜ ተጨማሪ ማስረጃ አስቀርበው በመስማትና በማጣራት ውሳኔ ሊሰጡ እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ስ/ህ/ቁ 145፣264፣266፣267፣345 እና በሌሎችም በግልፅ ተመልክቶ የሚገኝ ቢሆንም በፍትሐብሔር ክርክር ማስረጃ የሚሰማውና ፍሬ ነገሩ እንዲነጥር የሚደረገውም በማስረጃ የሚነጥረው ፍሬ ነገር ለዳኝነት አሰጣጡ እጅጉን አስፈላጊና የግድ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ፍርድ ቤቶች እውነትን ለማውጣት ማስረጃ አስቀርበው መስማት አለባቸው ሲባል በቀረበው ማስረጃ እውነቱ እስከተረጋገጠ ድረስ የግድ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያስቀረቡ የሚገደዱበት ምክንያት ይኖራል ማለት አይደለም፡፡ ስለሆነም ተጨማሪ ማስረጃ ለማቅረብ ማስፈቀጃ አቅርበን መታለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው በሚል 2ኛው አመልካች የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

አመልካቾች ያቀረብነው ማስረጃ በምክንያት ውድቅ አልተደረገም በሚል የሚያቀርቡትን ክርክር በተመለከተ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት የሚያመለክተው በአመልካቾች በኩል የቀረበው ክርክርና ማስረጃ ከተጠሪ ክርክርና ማስረጃ በተሻለ ሁኔታ ሊታመን የማይችል መሆኑ ግምት ውስጥ ገብቶ ውድቅ የተደረገ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ ማስረጃን የማጣራት የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን ያለው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተገቢውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በማስረጃ ለማጣራት የግራቀኙን ወገኖች ማስረጃ ሰምቷል፡፡ አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትንና ሰነድና የሰው ምስክርም አስቀርቦ ሰምቷል፡፡ በአስፈላጊነቱ ላይ ያላመነበትን ማስረጃ ሳያስቀርብ ቀርቷል፡፡ ከዚህ በመነሳትም ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበትን ወገን ለመለየት በግራቀኙ ወገኖች የቀረቡትንና ለፍትህ አስጣጥ አመችነት ፍርድ ቤቱ ያስቀረባቸውን ማስረጃዎች መሰረት በማድረግ እንዲሁም የራሱን ምክንያት በመስጠት አደጋው ለመድረሱ ከማረጋገጡም በላይ አደጋውንም ያደረሰው የ1ኛ አመልካች መኪና የሆነው አሸዋ ሲጭን የነበረው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-31175 ኢት. የሆነው መኪና ለመሆኑ አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በመነሳትም በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2081(1) መሰረት የመኪናው ባለቤት የሆነው 1ኛው አመልካች ካሳውን ለመክፈል ኃላፊ መሆናቸውን ሲወስን 2ኛው አመልካች ከ1ኛው አመልካች

www.abyssinialaw.com

ጋር የኢንሹራንስ ውል ያላቸው ለመሆኑ ስላልተካደ ኃላፊነት ያለባቸው ለመሆኑ ወስኗል። ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤት ተገቢውን ጭብጥ በመመስረት በግራቀኙ ወገኖች የቀረቡትን ማስረጃዎች እንዲሁም አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትን ማስረጃ አስቀርቦ በመስማትና በመመርመር መወሰኑን መዝገቡ ስለሚያስረዳ በሥር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም።

አመልካቾች ኃላፊ መሆናቸው ከተረጋገጠ የኃላፊነት መጠናቸውን መመልከቱ ተገቢነት ያለው ይሆናል። ተጠሪ ለደንበኛቸው የከፈሉትን ብር 159,626.68/አንድ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ስድስት ብር ከስልሳ ስምንት ሳንቲም/ 1ኛ አመልካች እንዲተኩላቸው ዳኝነት ጠይቀው ላቀረቡት ክስ በ1ኛው አመልካች በኩል የቀረበ የካሳ መጠንን የሚመለከት ክርክር የለም። 2ኛው አመልካች በሰጡት መልስ ለ1ኛው አመልካች መኪና የሰጡት የኢንሹራንስ ሽፋን እስከ ብር 100,000/አንድ መቶ ሽህ ብር/ እንደሆነ ገልፀው መልስ አቅርበዋል። የ2ኛው አመልካች ኃላፊነት ለ1ኛው አመልካች ከሰጡት የኢንሹራንስ ውል የሚመነጭ ከመሆኑም በላይ መጠኑም በውሉ ልክ የሚወሰን ነው። ይህ ከሆነ የሁለቱ አመልካቾች ኃላፊነት መጠን የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት መመልከቱ ተገቢ ይሆናል። ከዚህ አንፃር 2ኛው አመልካች ለተጠሪ እስከ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሽህ ብር/ የኢንሹራንስ ሽፋን የሰጠ መሆኑ እስካልካደ ድረስ ከተወሰነው የካሳ መጠን በዚሁ ገንዘብ ልክ ሊከፍሉ የሚገባቸው ይሆናል። 1ኛው አመልካች ደግሞ ቀሪውን የውሳኔ መጠን ሊከፍሉ ይገባል ማለት ነው። ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች በተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት መጠን ብር 159,626.68/አንድ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ስድስት ብር ከስልሳ ሳንቲም/ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ሁለቱም አመልካቾች በአንድነትና በነጠላ ይህንኑ ገንዘብ ከጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድና ከብር 1,000 /አንድ ሺህ ብር/ የክርክር ወጭ ጋር ይክፈሉ የተባለበት አግባብ የ1ኛ አመልካችንና የ2ኛ አመልካችን የኢንሹራንስ ውል ግንኙነትና 1ኛ አመልካች 2ኛውን አመልካች ወደ ክርክሩ እንዲገቡላቸው የጠየቁበትን ዓላማ ያላገናዘበ በመሆኑ በመጠኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል።

በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ ማስረጃ የመመርመር፤ የማጣራትና መመዘን ሥልጣን የተሰጣቸው የሥር ፍርድ ቤቶች በግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች በኩል የቀረቡ ክርክሮችን መሠረት በማድረግ ተገቢውን ጭብጥ ይዘውና አጣርተው ከፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ማስረጃ ምዘና አንፃር በመመልከት አመልካቾች ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃ የሚያሳምን አለመሆኑን ጠቅሰው ውድቅ በማድረግ የተጠሪን ማስረጃ በመቀበል አመልካቾች የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ላይ የደረሱበት ድምዳሜ የሚነቀፍበት ምክንያት አልተገኘም። በሌላ በኩል 2ኛው አመልካች

www.abyssinialaw.com

ለ1ኛው አመልካች እስከ ብር 100,000 ኢንሹራን ሽፋን የሰጡ ለመሆናቸው በመልሳቸው አምነው አቅርበው እያለ ከተወሰነው የካሳ መጠን ውስጥ ብር 100,000 ከነወለዱ በ2ኛው አመልካች እንዲሸፈን ሆኖ ቀሪውን 1ኛው አመልካች እንዲከፍሉ መወሰን ሲገባው ሁለቱም አመልካቾች ሙሉውን ካሳ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ የተሰጠው ውሳኔ ክፍል ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 188781 ጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 147566 ሕዳር 01 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. አመልካቾች በተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለባቸው መባሉና በዚህ ጉዳት ምክንያት የመጣ ካሳ ብር 159,626.68 ከጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስኪያልቅ የሚታሰብ በዓመት 9% ህጋዊ ወለድና ብር 1,000 /አንድ ሺህ ብር/ የክርክር ወጭ ለተጠሪ ሊከፈል ይገባል መባሉ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡

3. አከፋፈሉን በተመለከተ ከዚሁ የካሳ መጠን ውስጥ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ከጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፋሎ እስኪያልቅ ድረስ ከሚታሰብ በአመት 9% ወለድ ጨምሮ በ2ኛው አመልካች የሚሸፈን ሆኖ ቀሪው የካሳ መጠን ከነወለዱና የክርክር ወጭ በ1ኛው አመልካች እንዲከፈል ወስነናል፡፡

4. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዚህ ችሎት ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈፅም ተወስኗል፤ ይጻፍ፡፡

5. በዚህ ችሎት ክርክር ለወጣ ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

6. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ የሰበር መዝገብ ቁጥር 109563 አካል ይሁን ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.107217

ህዳር 29 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሀመድ

ተኽሊትይመስል

ቀነዓ ቀጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የዳንግላ ወረዳ ውሃ ሃብት ልማት ፅ/ቤት ወኪል የፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ህግ አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ሙሉጌታ ገበየሁ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግንባታ ሥራ ውል የሚመለከት ሲሆን የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ ሲሆን በአሁን አመልካች የሥር ተከሳሽ ፅ/ቤት ላይ ለአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተከሳሽ ፅ/ቤት ባለ አራት መቀመጫ ሽታ አልባ መፀዳጃ ቤት ለመስራት ባወጣው ጨረታ ተወዳድሬ በማሸነፍ ተከሳሽ ጋር በገባው ውል መሠረት አምስት ሳይቶችን ሰርቼ በማስረከብ ክፍያ እንዲፈፅሙልኝ ብጠይቅና በፅ/ቤቱ መሀንዲስ ቢታዘዝም የአራት ሳይት ክፍያ ከፍለውኝ የአምስተኛውን ሳይት /የኳንች ኳኩርታን/ ሣይት ብር 68,776.71/ስልሳ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ብር ከሰባ አንድ ሣንቲም/ ያልከፍሉኝ ስለሆነ ይህንኑ ክፍያ እንዲከፍለኝ ይኸው ክፍያ በመሀንዲስ ከታዘዘበት ቀን ጀምሮ 379 ቀን ስለሆነ የብር 68,776.71 / ስልሣ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ስደስት ከ ሰባ አንድ ሣንቲም/1% x379 ቀን =ብር 260,663.93/ሁለት መቶ ስልሳ ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ሶስት ብር ከዘጠና ሦስት ሣንቲም/ መቀጫ ግንባታውን አጠናቅቄ ካስረከብኩኝ አንድ ዓመት ስለሞላ ለዋስትና የተያዘ ብር 3,725.38/ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ አምስት ብር ከሰላሳ ስምንት ሣንቲም/ የዳኝነት የጠበቃ አበል 10% እና ኪሣራ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ የሚል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

ተከሳሽ ፅ/ቤትም በወኪሉ አማካኝነት የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያ ቢያቀርብም የታለፈበት ሲሆን በአማራጭ ባቀረበው መልስ ከሳሽ በውሉ እና በተሰጣቸው የመሀንዲስ የስራ ዝርዝር መሠረት ግንባታውን ሰርተው ያስረከቡና በፅ/ቤት መሀንዲስ ሂሳቡ በትክክል ተሠርቶ በመስሪያ ቤቱ ፀድቆ ለወረዳው ፋ/ኢ/ል/ማ/ ፅ/ቤት ክፍያ እንዲፈፀም በደብዳቤ ብጠይቅም ክፍያ ሊፈፀም አልቻለም እንጂ ተከሳሽ ጽ/ቤት ክፍያ አልከለከላቸውም ካለ በኂላ መልሴን ላሻሽል ብሎ አሻሽሎ የሠጠው መልስ ከሳሽ በውሉ መሠረት ሽንት ቤቶቹ ሠርተው አስከርበው ክፍያ ያልወሰዱ ቢሆንም ክፍያ ያልወሰዱት ከሳሽ ከውል ዉጪ በተቆጣጣሪው መሀንዲስ ትእዛዝ የብር 17,358.46 /አስራ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሃምሣ ስምንት ከ አርባ ስድስት ሣንቲም/ሠርቻለሁ እና ይህንን ሂሳብ ካልረከፈለኝ ሌላውን አልበቀልም በማለታቸው ነው፡፡ የተጨማሪ ሥራ ክፍያ የሚፈፀመው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤቱ በግዢ አፈፃፀም መመሪያው ተጨማሪ ስራውን ሲያውቀው ነው፡፡ ባላወቀው ስራ ክፍያ ሊጠይቅ አይገባም፡፡ ለዋስትና ጉዳይ የተያዘውን ገንዘብ አልተከለከሉም ስለሆነም የወሰዱት ገንዘብ ተቀንሶ ቀሪ ካላቸው እንዲወስዱ ይወሰንልኝ ብሏል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ካዳመጠ በኂላ በግራ ቀኙ ክርክር የሚጠነጥነውን ለተጨማሪ ሥራ ክፍያ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በግራ ቀኙ ውል ገጽ 3 ተራ ቁጥር 5/3/ ሥር እንደተመለከተው በተመደበ ተቆጣጣሪ ወይም አማካሪ መሀንዲስ ሲደገፍ ተጨማሪ ሥራ ሊሰራ እንደሚችልና ተጨማሪ ክፍያ ሊፈፀም እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት ስራው ተሠርቶ መረከቡን ተከሳሽ ፅ/ቤት አምኗል ስለሆነም ለተጨማሪ ሥራ ክፍያ አልፈፅምም መባሉ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ክፍያ ለዘገየበት መቀጫን በተመለከተ ፅ/ቤት ክፍያው እንዲፈፀምለት ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት ያስተላለፈ ቢሆንም ክፍያውን ፈፃሚው ፅ/ቤት ከተሰራው ስራ ላይ በላይ ከውል ውጪ የሚታየውን ብር 17,358.46/አስራ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ሃምሣ ስምንት ብር ከ አርባ ስድስት ሣንቲም/በስተቀር ሌሎች ክፍያዎችን አልቀበልም ያሉት ከሳሽ መሆናቸው ሲገልፅ ከሳሽ እነዚህ ክፍያዎች በተከሳሽ ፅ/ቤት ምክንያት የዘገዩ ስለመሆናቸው አላስረዱም በማለት ከሳሽ የጠየቁትን ክፍያ ለዘገየበት ለ379 ቀን 1 ፐርሰንት ብር 260,663.93/ሁለት መቶ ስልሣ ሺህ ስድስት መቶ ስልሣ ሦስት ከ ዘጠና ሦስት ሣንቲም/ መቀጫ ተከሳሽ ፅ/ቤት ሊከፍል አይገባም በማለት የተቀሩትን ዋናውን ገንዘብ ብር 68,776.71/ስልሳ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ብር ከሰባአንድ ሣንቲም/ ለዋስትና የተያዘ ብር 3,725.38/ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ አምስት ብር ከሰላሳ ስምንት ሣንቲም/ በጠቅላላው ብር 72,502.09/ሰባ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሁለት ብር ከ ዜሮ ዘጠኝ ሣንቲም/ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ዳኝነት እና የጠበቃ አበል10% ተከሳሽ ለከሳሽ ሊከፍል ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን የቅሬታው ይዘትም በአጭሩ ክፍያ ለዘገየበት ለ379 ቀን መቀጮ ሊከፍል አይገባም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ ቅሬታው የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሥራው ተሰርቶ የተጠናቀቀ መሆኑንና ክፍያው ያለመፈፀሙ በተከሳሽ የታመነ ጉዳይ ነው ስለሆነም የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሳሽ ባቀቡት ክስ መሰረት አላስረዱም ማለቱ ተገቢ አይደለም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁ. 348/1/ መሰረት ውሣኔውን በመሻር ክፍያ ለዘገየበት ብር 260,663.73 /ሁለት መቶ ስልሣ ሺህ ስድስት መቶ ስልሣ ሦስት ብር ከ ሰባ ሦስት ሣንቲም /ተከሳሽ ጽ/ቤት ሊከፍል ይገባል በማለት ሲወሰን በአሁን አመልካች በበኩል የሠበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት ቅሬታው ተጠሪን አያስቀርብም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሠረት አቤቱታውን ሠርዞታል፡፡

ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሠበር አቤቱታውን ያቀረበው አመልካች ፅ/ቤት ሲሆን አቤቱታው ክፍያ አዘግይተናል ብለን በእምነት የሰጠነው ቃል የለም፡፡ ከተጨማሪ ሥራ በስተቀር የተቀሩትን አልወስድም ያሉት ተጠሪ ናቸው ስለሆነም ክፍያው ለዘገየበት ልንከፍል አይገባም፤ ክፍያ ለዘገየበት የምንከፍል ቢሆን እንኳን ክፍያ የዘገየበት የገንዘብ መጠን 1 ፐርሰንት ሳይሆን 0.1 ፐርሰንት ከመሆኑም በተጨማሪ በአማራ ክልል የግዢ መመሪያ መሠረት ክፍያው ከዋናዋ ገንዘብ 10% በላይ ሊሆን አይገባም የሚል ነው፡፡

አጣሪው ችሎትም የቀረበውን አቤቱታና የሥር መዝገብ መርምሮ የመቀጮ ክፍያ ከዋናው ገንዘብ 10%በላይ በስር ፍ/ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ያመች ዘንድ ተጠሪ ቀርበው መልስ እንዲሰጡ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በፅሑፍ በሰጡት መልስ የመቀጮ መብዛትንም ይሁን ማነስ የፍሬ ነገር ክርክር ባልሆነበት እና ይህን አስመልክቶ አመልካች ፅ/ቤት ያነሳው መከላከያ ነጥብ በሌለበት የሠበር አጣሪው ችሎት የያዘው ጭብጥ በሥር ያልተነሳ ክርክር ነውና የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ይፅናልኝ ብለዋል፡፡ እኛም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ በሥር ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክርና ማስረጃ አንፃር የሠበር አቤቱታው የቀረበበትን ውሣኔ የሰጠው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሠሚ ችሎት የሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን ያለመሆኑን ከተገቢው ህግ አንፃር መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም የአሁን ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ፅ/ቤት ላይ ባቀረቡት ክስ ከአመልካች ጋር በነበረን የግንባታ ውል ግንባታውን ከተጨማሪ የመሀንዲስ ትአዛዝ ጋር ሠርቼ ለፅ/ቤቱ ያስረከብኩኝ ቢሆንም አመልካች ፅ/ቤት ክፍያውን አጠናቆ አልከፈለኝምና ያልተከፈለኝ ገንዘብ ከነቅጣቱና ተያያዥ ያላቸውን ክፍያዎች እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን፣ የአሁን

አመልካች ፅ/ቤት በወኪሉ አማካኝነት በሰጠው መልስ ጽህፈት ቤቱ አልከፍልም አላለም የተጨማሪ ስራ ገንዘብ ካልተከፈለ አልቀበልም በማለት ዋናውን ገንዘብ ያልወሰዱት ተጠሪ ናቸው ስለሆነም ክፍያ ለዘገየበት ልጠየቅ አይገባም ብለዋል፡፡ ምንም እንኳን በሰበር አጣሪው ችሎት አቤቱታው ያስቀርባል የተባለበት ምክንያት ክፍያ ለዘገየበት መቀጫ ከዋናው ገንዘብ ከ10%በላይ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ቢሆንም ይህ ነጥብ ከታየቱ በፊት ክፍያ ለዘገየበት መቀጮ የአሁን አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ መመርመሩ ተገቢ ሆኖ አግኝተዋል፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 242 ስር እንደተደነገገው ማናቸውም ተከራካሪ ወገን በመከላከያ መልሱ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል የሚያምን መሆኑን የገለፀው እንደሆነ ወይም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241 መሠረት በሚደረግ ምርመራ የእምነት ቃሉን የሰጠን እንደሆነ ፍ/ቤቱ በታመነው ነገር ላይ ብቻ ፍርድ መስጠት እንዳለበት ይገልፅና በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 83 እና 234/1/ሠ ሥር እንደተደነገው በግልፅና በዝርዝር ያልተካዱ ነገሮች ሁሉ እንደታመኑ እንደሚቆጠር ደንግጓል፡፡

በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከአመልካች ፅ/ቤት በነበረው የግንባታ ውሉ ግንባታውን ጨርሼ ያስረከብኩኝ ቢሆንም አመልካች ፅ/ቤት ሊከፍለኝ ከሚገባው ገንዘብ ውስጥ ብር 68,776.71 /ስልሣ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ብር ከሰባ አንድ ሳንቲም/ያልከፈለኝ ስለሆነ ይኸው ዋናው ገንዘብና ተያያዠነት ያላቸው ክፍያዎች እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ የሚል ዳኝነት መጠየቃቸውን የአሁኑ አመልካች ጽ/ቤት በግራ ቀኙ መሀከል ውል መኖሩን ተጠሪ በውሉ መሠረት ግንባታውን አጠናቀው በተጨማሪም በመሃንዲስ ትእዛዝ ፅ/ቤቱ የማያውቀው የብር 17,358.43 /አስራ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሃምሣ ስምንት ብር ከአርባ ሦስት ሣንቲም/ ተጨማሪ ሥራ መሥራታቸውንና በዚህም ምክንያት አመልካች ጽህፈት ቤት የተጨማሪ ሥራውን ክፍያ አልከፍልም በማለቱ ተጠሪ ሁሉንም ክፍያ አልወስድም በማለታቸው ክፍያ መዘግየቱን መልስ በመስጠት መከራከሩን በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ከተደረገ የግራ ቀኙ ክርክር መረዳት ተችሏል፡፡

በዚህም ክርክር የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ፅ/ቤት በእርግጥም ተጠሪ ዳኝነት የጠየቁበት ገንዘብ ያልተከፈለው መሆኑን አምኗል ነገር ግን ያልተከፈለው በኔ ምክንያት አይደለም እስካለ ድረስ ታምኗል የሚያሰኝ አይደለም፤በተጨማሪም ተጠሪ ክፍያው የዘገየው በአመልካች ምክንያት ስለመሆኑ አላስረዱም ስለሆነም ክፍያ ለዘገየበት አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት ሲወስን፤ የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ጽህፈት ቤት ተጠሪ ስራውን ሰርተው ማስረከባቸውንና ጽ/ቤቱ ክፍያ ያለመፈፀሙን እስካመነ ድረስ ክፍያ የዘገየው

www.abyssinialaw.com

በአመልካች ጽ/ቤት ምክንያት መሆኑ ታምኗል በማለት አመልካች ጽ/ቤት ክፍያ ለዘገየበት ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔን በመሻር መወሰኑንና የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት መወሰኑ ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡

ነገር ግን ተጠሪ ክፍያ የዘገየው በአመልካች ጽ/ቤት ምክንያት ነው ሲሉ አመልካች ጽ/ቤት ክፍያ የዘገየው በተጠሪ ምክነያት ነው እስካለ ድረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.242 መሠረት የታመነ ጉዳይ ነው ወይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.234/1/ ሥር እንደተመለከተው ጉዳዩ በግልፅ ያልተካደ ጉዳይ ነው ሊባል የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም ክፍያ የዘገየው በማን ምክንያት ነው የሚለው ነገር አከራካሪው ነው፡፡ በፍትሐብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ የአሁን ተጠሪ ክፍያው የዘገየው በአመልካች ፅ/ቤት ምክንያት መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅባቸው ቢሆንም ያላስረዱ መሆኑ ከስር ፍርድ ቤት ክርክር መረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ ሁሉ ስንነሳ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ክፍያው የዘገየበት በአመልካች ፅ/ቤት ምክንያት ስለመሆኑ ተጠሪ አላስረዳም በማለት ክፍያ የዘገየበት የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ሲወስን የስር ጠቅላይ ፍ/ቤት ክፍያ የዘገየው አመልካች ጽ/ቤት መሆኑ ታምኗል በሚል የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አንኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 37313 ሰኔ 10 ቀን 2006 ዓ.ም ተሰጥቶ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 41544 ጥቅምት 29 ቀን 2007 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.07181 የካቲት 6 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 338/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙን ለዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸው ይቻሉ፡፡

## <u>ትእዛዝ</u>

1. በዚህ ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረው የአፈፃፀም እግድ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
2. የውሣኔው ግልባጭ በየደረጃው ለሚገኙ የስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ ብ/ግ

www.abyssinialaw.com

የ/ሰ/መ/ቁ. 114623

ቀን 22/06/2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

አይሸሹም መለሰ

ፀሃይ መንክር

አመልካችዎች፡- 1. ሀጅ ቢያ አባመጫ

2. አቶ ከሊፋ አባ ቆያስ } ጠበቃ ከድር መሐመድ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. የኦሮሚያ ክልል ደንና ዱር አራዊት ድርጅት አልቀረበም

2. መራዋ አርሶ አደሮች የህብረት ሥራ ማህበር ጠበቃ በላይ እሸቱ ቀረቡ

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካችዎች ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር የእርቅ ሥምምነት በማድረግ በፍርድ ቤት እንዲመዘገብና እንዲፀድቅ ካደረጉ በኃላ አንደኛ ተጠሪ ያቀረበውን የፍርድ መቃወሚያ በመቀበል የእርቅ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ውሳኔ የሰጠው በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም ?የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው ጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡
2. አመልካችዎችና ሁለተኛው ተጠሪ በፈረንጅ ዕድ ሽያጭ ውል በተመለከተ ባለመስማማታቸው አመልካቾች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች ከሳሽ፣ሁለተኛ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመከራከር ላይ እያሉ ጥር 5 ቀን 2001ዓ.ም ባደረጉት ዕርቅ ውል አመልካችዎች 1,200,000 /አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ብር) ለሁለተኛ ተጠሪ ሊከፍሉ ሁለተኛ ተጠሪም የክርክሩ መነሻ የሆነውን የፈረንጅ ዕድ ለአመልካችዎች ሊያስረክቡ ሥምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡ አመልካችዎችና ሁለተኛ ተጠሪ የዕርቅ ሥምምነታቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት

www.abyssinialaw.com

አቅርበው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14220 ህዳር 25 ቀን 2002ዓ.ም በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277(1) መሠረት የዕርቅ ውላቸውን በመቀበል ግራቀኝ በዕርቅ ውሉ መሠረት እንደፈፅሙ ትዕዛዝ በመስጠት መዝገቡን ዘግቶታል ፡፡

3. አንደኛ ተጠሪ አመልካችዎችና ሁለተኛው ተጠሪ ጥር 5 ቀን 2001ዓ.ም አድርገነዋል በማለት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ህዳር 25 ቀን 2002ዓ/ም ያፀደቁት የዕርቅ ውል የፈፀሙበት የፈረንጅ ፅድ የመንግስት ደን መሆኑን ገልፆ የዕርቅ ውሉ ፈራሽ ነው እንዲባልለት ጥር 27 ቀን 2005ዓ/ም የተፃፈ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳያቸውን በዕርቅ ያዘጉት አመልካችዎችና ሁለተኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ አንደኛ ተጠሪ ፍርዱን ለመቃወም የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የዕርቅ ስምምነቱ የፍርድ መቃወሚያ አመልካችን መብት የሚነካ በመሆኑ የዕርቅ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4. አመልካችዎች ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የፍርድ መቃወሚያ አቅርበው የዕርቅ ስምምነት በተደረገበት የፈረንጅ ፅድ ላይ መብት የሌለው መሆኑ በወቅቱ በተያዘው ቃለጉባኤ የተረጋገጠ ስለሆነ ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዕርቅ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ በመሻር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የዕርቅ ውል የተደረገበት የፈረንጅ ፅድ የመንግስት ደን በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዕርቅ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

5. አመልካችዎች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ እኛ የገዛነው የመንግስት ደን ሣይሆን የሁለተኛ ተጠሪ ንብረት የሆነ የፈረንጅ ፅድ ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ ከሻጭ ጋር ያለንን ልዩነት በዕርቅ ጨርሰን የዕርቅ ውሉ በፍርድ ቤት ከፀደቀ በኃላ ማስረጃ እንዲፃፍ በማድረግ የዕርቅ ውሉ እንዲፈርስ ማድረጉ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሰበር ታይቶ እንደታረምልኝ በማለት አመልክተዋል ፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ንብረቴን ነው የሸጥኩት ከአመልካችዎች ጋር የዕርቅ ውል የፈፀምኩት በንብረቴ ላይ በመሆኑ የሁለተኛ ተጠሪ የፍርድ መቃወሚያ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የአመልካችዎችን የሰበር አቤቱታ በመደገፍ መልስ ሰጥቷል ፡፡ አንደኛ ተጠሪ ግራቀኙ ዕርቅ የፈፀሙበት የመንግስት ደን በመሆኑ የአመልካችዎች የሰበር አቤቱታ

www.abyssinialaw.com

ተቀባይነት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል ። አመልካችዎች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል ። ጉዳዩን እንደመረመርነው ሁለት ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ቤት የሚከራከሩበትን ጉዳይ በዕርቅ መጨረስ እንደሚችሉና የእርቅ ውሉን ጉዳዩን ለሚያየው ፍርድ ቤት አቅርበው ማፅደቅ እንደሚችሉ ፍርድ ቤት ቀርቦ የፀደቀ የዕርቅ ውል ሥምምነት በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ ያህል አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ያለው መሆኑን ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 276 እና አንቀፅ 277(1) ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

7. አመልካችዎችና ሁለተኛው ተጠሪ የፈረንጅ ፅድ ሽያጭ ውል በተመለከተ ጥር 5 ቀን 2001ዓ.ም ያደረጉትና ለጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277(1) መሠረት ያፀደቁት የዕርቅ ውል የፍርድ ያህል አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ያለው በመሆኑ በዚህ ዕርቅ ውል ተካፋይ ያልሆነ መብቴ ተነክቷል የሚለው አንደኛ ተጠሪ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዕርቅ ውሉን በማፅደቅ የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት ፤የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ማቅረቡና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአንደኛ ተጠሪን የፍርድ መቃወሚያና ማመልከቻን ማስረጃ በመቀበል የዕርቅ ውሉ የመንግስት ደን የሚያስተዳድረውን የአንደኛ ተጠሪን መብትና ጥቅም የሚነካ በመሆኑ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሥነ ሥርዓት ሕግ ግድፈት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም ።

8. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አንደኛ ተጠሪ የፍርድ መቃወሚያ ለማቅረብ መሠረትና ማስረጃ የሆነውንና አመልካችዎች ከሁለተኛው ተጠሪ ጋር የዕርቅ ሥምምነት የፈፀሙበት የፈረንጅ ፅድ ጫካ የመንግስት ደን መሆኑን የሚያረጋግጠውን የቴክኒክ ኮሚቴ ሪፓርትና ማስረጃ ያለበቂ ምክንያት ውድቅ በማድረግ አከራካሪው የፈረንጅ ፅድ ዛፍ ጫካ በጨረታ ለአመልካችዎች ከመሸጡ በፊት የተያዘውን ቃለ ጉባኤ ነው መያዝ ያለበት በማለት አከራካሪው የፅድ ዛፍ የሁለተኛ ተጠሪ ሀብት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የማስረጃ አመዛዘን መርህን ያልተከተለና መሠረታዊ የማስረጃ ህግ ድንጋጌዎችን የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 250 እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 136(1) ያልተከተለና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመገንዘብ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም ። በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካችዎች እና አንደኛ ተጠሪ የዕርቅ ሥምምነት ያደረጉት የአንደኛ ተጠሪ መብትና ጥቅም ባለበት የመንግስት ደን ላይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ቀርቦለት እያለ

www.abyssinialaw.com

አንደኛ ተጠሪ የዕርቅ ሥምምነቱን መቃወምና ፈራሽ ለማስደረግ የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት የለውም በማለት የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሻሩ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 184867 መጋቢት 14 ቀን 2007ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

www.abyssinialaw.com

# ንብረት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 112190

መጋቢት 28 ቀን 2008 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

**አመልካች** ፡--አይከል ከተማ አገልግሎት ፅ/ቤት ዐ/ህ ዮሃኒስ ተገኘ ቀርበዋል

**ተጠሪ፡-** ሼክ ሸምሱ መሀመድ ተ/ይ አሚናት ሸምሱ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካች አይከል ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት የካቲት 30 ቀን 2007 ዓ.ም. በተጻፈ አቤቱታ የአማራ ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁጥር 41846 ታህሳስ 7 ቀን 2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የቀረበ ሲሆን ቅሬታውም የሥር ፍ/ቤት የማይንቀሳቀስ ንብረት በቅን ልቦና ባለሀብትነት ሊገኝ የማይችል ሆኖ እያለ የአይከል ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የተወረሰ ቤት በተመለከተ የመወሰን ስልጣን የሌለው ሆኖ እያለ የተወረሰን ቤት መብትና ጥቅም የሌለው አካል መሸጥ የማይችል በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የቤት ቁጥር 140 የተወረሰ መሆኑን አረጋግጦ ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ ) በቅን ልቦና ገዝተውታል ሲል የሰጠው ውሳኔ ስህተት በመሆኑ፣ ያከራከረውን ቤት ከ36 ዓመት በላይ ቀበሌው ሲያስተዳድር የቆየ ሆኖ እያለ ከሳሽ ገዛሁት የሚሉትን ቤት ካርታና ፕላን ያላወጡበትና ገዛሁ ካሉት ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ ቀበሌው እንዲያስረክባቸው ጠይቀው በማያውቁበት ሁኔታ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ሼክ ሸምሱ መሀመድ በአማራ ብ/ክ/መ/ ጭልጋ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ተከሳሽ እሙሃይ ማናለብሽ ጌታሁን ከሳሽ በአይከል 01

www.abyssinialaw.com

በካርታ ቁጥር 89911-92316 የሚታወቅ አዋሳኙን በመጥቀስ 4 ክፍል ቤት ያላቸው ሲሆን ተከሳሽ ባልታወቀ ምክንያት ቤቱ ውስጥ ገብተው የሚኖሩበት ሲሆን ጉዳዩ ለአይከል ከተማ መሪ ማዘጋጃ ቤት ቤትና ቦታ አስለቃቂ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቀርቦ ጉባኤው በቁጥር ደስ/26/2001 በቀን 27-5-2001 ዓ.ም. በተጻፈ ውሳኔ ቤቱ የተወሰነልኝ ቢሆንም ተከሳሽ ለመልቀቅ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ቤቱን ይልቀቁልኝ ሲሉ ከሰዋል፡፡ ተከሳሽም በሰጡት መልስ ቤቱን ለ35 ዓመት ያህል ለቀበሌ ኪራይ እየከፈልኩበት የኖርኩበት በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተወረሰ በቅጽ ተሞልቶ ከቀበሌ ተከራይቼ ለ35 ዓመት የኖርኩበት በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ ብለዋል፡፡ ጣልቃ ገቢ የአይከል ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር በአ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተወስኖ በመመለሱ ጣልቃ ገብቶ የሰጠው መልስ ከሳሽ ከ1988 ዓ.ም. እስከ 2003 ዓ.ም.ከፍያለሁ የሚሉት ግብር በ2003 ዓ.ም.የከፈሉትና ከመመርያ ቁጥር 4/2000 ጋር የሚጻረር ነው፡፡ ከሳሽ በዚህ ግብር ብቻ የቤቱ ባለቤት ሊሆን አይችልም፡፡ ቤቱ ከአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሶ ለተከሳሽ የተከራየና ተከሳሽ ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1983 ኪራይ ከፍለው የአይከል አውራጃ አስተዳደር በጻፈው ደብዳቤ ተከሳሽ የኪራይ ክፍያ አቋርጠዋል፡፡ ቤቱ የከሳሽ ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ ብለዋል፡፡

በአማራ ብ/ክ/መ/ ጭልጋ ወረዳ ፍ/ቤት በመ. ቁጥር 02912 አከራክሮ ሐምሌ 16 ቀን 2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ካሁን በፊት በዚህ ጉዳይ ውሳኔ ተሰጥቶ የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮ ጉዳዩን ከአዋጅ ቁጥር 47/67 ከቅጽ 001፣004 እና 003 ታይቶ ውሳኔ እንዲሰጥ በመለሰው መሰረት አይተነዋል፡፡ከሳሽ ያቀረቧቸው የተለያዩ የአስተዳደር ክፍል ሀላፊዎች የጻፏቸው የሰነድ ማስረጃዎችና የግብር ካሪኒዎች ይህ ክርክር የተነሳበት ቤት በመንግስት ያልተወረሰና የከሳሽ ህጋዊ ቦታ እና ቤት መሆኑን እጅግ ሚዛን በደፋ ከፍ ባለ ሁኔታ ያስረዳ በመሆኑ ተከሳሽ ቤቱን ለከሳሽ ይልቀቁለት ሲል ወስኗል፡፡ ጣልቃ ገብ የአይከል ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ለሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ. ቁጥር 01-17437 አከራክሮ ግንቦት 16 ቀን 2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ከሳሽ የገዙት ቤት አራት ክፍል ሲሆን የተገዛው ቤት ለወፍጮ ቤት የሚውል ነበረ፡፡

የጎንደር አስተዳደር አካባቢ ኢንዱስትሪና እደጥበብ ለአይከል ልዩ ከፍተኛ አንድ ጽ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ ቤቱ በባንክ ዕዳ ታግዶ የነበረና ቤቱ ተሸጦ ከባንክ ዕዳ ነጻ መሆናቸውን ገልጾ የጻፈው ደብዳቤ ማዘጋጃ ቤቱም ሽያጩን በማይንቀሳቀስ ንብረት ማስተላለፍያ ሰነድ ቅጽ 13(1) መዝግቧል፡፡ የቦታ እና የይዞታ የምስክር ወረቀት 8991 መዝገብ የያዘው መሆኑ የሚያስረዳ 1 ገጽ ጽሁፍ ቀርቧል፡፡ ከሳሽ የተወረሰ ቤት መሆኑን ሳያውቁ ከአራቱ ክፍል አንድ ክፍል ቤት

www.abyssinialaw.com

በቅን ልቦና የተወረሰ መሆኑን ሳያውቁ የገዙት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ከሳሽ የአራቱም ቤቶች ባለሀብት እንደሆነ የሚገመትና ይህን ግምት ሊያስተባብል የሚችል ነገር የሌለ መሆኑን አረጋግጠናል፡፡ ከሳሽ ያከራከረውን አንድ ክፍል ቤት የቅን ልቦና ባለሀብት ሊሆኑ እንደሚገባ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንተነዋል ሲል ወስኗል፡፡ ጣልቃ ገብ (የአሁን አመልካች) ለአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁጥር 41846 ታህሳስ 7 ቀን 2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ለቀረበው አቤቱታ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አላገኘንበትም አቤቱታውን አያስቀርብም ሲል ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ቀርበዋል፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ አመልካች ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ከ36 ዓመት በላይ እያስተዳደረው እንዳለ በተረጋገጠበት ቤቱ ለተጠሪ በሌሎች ግለሰቦች የተሸጠ ነው ተብሎ እንዲያስረክብ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም.በጻፈ መልስ ያከራከረውን ቤት ጥር 3 ቀን 1983 ዓ.ም. 4 ደጃፍ ቤት በሽያጭ ውል ህጋዊነቱ ተረጋግጦ ስመ ንብረቱ ወደ ተጠሪ እንዲዛወር ተወስኖ በአይከል ከተማ ማ/ቤት በኩል ተላልፎልኛል፡፡ በአመልካች በኩል የቀረቡት ሰነዶች አከራካሪ የሆነው የወፍጮ ድርጅት 1 ክፍል ቤት በአመልካች ይዞታ ስር ሆኖ ለ36 ዓመት በይዞታው አድርጎ እያከራየው የነበረ ስለመሆኑ ሰነዶቹ በእርግጠኝነት ስለማያስረዱ የበታች ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት ባለመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይሁንልኝ ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ነሐሴ 14 ቀን 2007 ዓ.ም. በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መዝገቡን እንደመረመርነው፡ በከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ክስ የቀረበበት ያከራከረው ቤት የስር ፍ/ቤት ተከሳሽ እሙሃይ ማናለብሽ ጌታሁን ከቀበሌ መስተዳድር ተከራይተው ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ ሲኖሩበት እንደነበር፣ ቤቱ በቀበሌ መስተዳድር ስር ሆኖ የቀበሌው መስተዳድር ሲያስተዳድረው የነበረ መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠና የተወረሰ ቤት ስለመሆኑ በሥር የአማራ ብ/ክ/መ. ሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍ/ፍ/ቤት አረጋግጦ የአሁን ተጠሪ ቤቱን የገዛው የተወረሰ መሆኑን ሳያውቅ በመሆኑ በቅን ልቦና የቤቱ ባለሀብት ይሆናል በሚል የወሰነ ሲሆን የአሁን ተጠሪ ያከራከረው ቤት ባለሀብት ነኝ ብለው የሚከራከሩት ደግሞ በግዥ ተላልፎልኛል በማለት ነው፡፡ ቤቱን ለአሁን ተጠሪ የሸጠለት አካል የቤቱ ባለሀብት አለመሆናቸውና የተወረሰ ቤት መሆኑ፣ ቤቱ በቀበሌው መስተዳድር ስር ገብቶ ቀበሌው ማስተዳደር ከጀመረና ለስር ተከሳሽ እሙሃይ ማንአለብሽ ጌታሁን ከተከራየ በኋላ የተመለሰለት ስለመሆኑ የሚያሳይ ነገር የሌለና የአሁን ተጠሪም ለሸጡለት ግለሰብ ከተመለሰ በኋላ የገዛሁት ነው ብሎ አይከራከርም፡፡ በመሆኑም ያከራከረውን ቤት የሸጠው ሰው የራሱ

www.abyssinialaw.com

ያልሆነውን እና የባለቤትነት መብት ሳይኖረው የተወረሰ ቤት ሽጦ ተጠሪም በመንግስት የተወረሰ ቤት ገዝቶት የቤቱ ባለቤት የሚሆንበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪ ቤቱ መወረሱን ሳያውቅ በቅን ልቦና ንብረቱ ካልሆነው ሰው ላይ ገዝቶም ከሆነ ካለአግባብ የሸጡለትን ሰዎች ከመጠየቅ ውጪ በመንግስት የተወረሰ ቤት መሆኑን ሳያውቅ መግዛቱ የቤቱ ባለቤት የሚያደርገው አይደለም፡፡ በመሆኑም የአሁን ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሰ ቤት መብቱ ከሌለውና ባለቤት ካልሆነው ሰው ገዝቻለሁ በማለት ቤቱ እንዲለቀቅለት ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የሌለውና የስር ፍ/ቤትም በመንግስት የተወረሰ ቤት መሆኑን መብቱ ከሌለው ግለሰብ ላይ የአሁን ተጠሪ የገዛ መሆኑ አረጋግጠው እያለ በቅን ልቦና ባለቤት የሚሆንበት የህግ መሰረት ሳይኖር የአሁን ተጠሪ ያከራከረው ቤት ባለቤት ስለሆነ ይለቀቅለት ብለው መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁ. 41846 ታህሳስ 7/2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣ የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ. ቁ. 01-17437 ግንቦት 18/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔና የአ/ብ/ክ/መ. ጭልጋ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 02912 ሐምሌ 11/2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡ የአሁን ተጠሪ ክስ ውድቅ በማድረግ ወስነናል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሳራ ተቻቻሉ ብለናል፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ቅጂ ለስር ፍ/ቤቶች እንዲያውቁት ይድረሳቸው፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 123056

ሰኔ 24 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- ወ/ሮ ትሁኔ አዳነ ጠበቃ አቶ ሙሉጌታ ዱላ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 ኮንስትራክሽንና ቤቶች አስተዳደር ልማት ፅ/ቤት

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው የአሁን አመልካች አ/አ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ሲሆን የክሱ ይዘት ጉለሌ ክ/ከ/ወረዳ 7 ቤ.ቁ 673 በሆነው የመንግስት መኖሪያ ቤት ውስጥ ከሟች ባለቤቴ አቶ አረጋ ካሳ ጋር ስንኖርበት ነበር፡፡ ባለቤቴ በሞት የተለየኝ በመሆኑ ተከሳሽ የቤቱን ኪራይ ውል ሊያዛውርልኝ ሲገባ ፈቃደኛ ባለመሆን ቤቱን ለቃችሁ እንድታስረክቡኝ በማለት ማስጠንቀቂያ ሰጥቶኛል ተከሳሽ የቤቱን ኪራይ ውል በስሜ እንዲያዋውለኝ የተሰጠኝ ማስጠንቀቂያም ይነሳልኝ የሚል ነው፡፡፡

ተከሳሽ ለክሱ በሰጠው መልስ በመጀ/ደ/መቃወሚያ ከሳሽ ክስ በቀረበበት ቤት ላይ መብት የላትም ክስ ማቅረብ አትችልም የሚል እና በፍሬ ጉዳይ መልሱ የከሳሽ ባለቤት የቤ.ቁ 734 የሆነ ሕጋዊ የግል መኖሪያ ቤታቸውን በግልፅ ኑዛዜ ከእነ ሙሉ ዕቃው የወረሷቸው በመሆኑ በመመሪያ ቁ. 3/07 መሰረት የመንግስት ቤት ከሳሽ ማስረከብ አለባቸው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱ መቃወሚያውን በብይን በማለፉ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃን መርምሮ ከሳሽ ከሌሎች ወራሾች ጋር በጋራ የወረሱት የግል ቤት እንዳላቸው የቀረበው ማስረጃ ያረጋግጣል፡፡ በመመሪያ ቁ. 3/07 የግል ቤት ያለው ግለሰብ በመንግስት መኖሪያ ቤት ላይ የኪራይ ውል ለመዋዋል አይቻልም በማለት ደንግጓል፡፡ የቀረበውን ክስ አልተቀበልነውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

ከሳሽ በዚህ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ለአ/አ/ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርበው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት የስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ የፀና ሲሆን ከሳሽ ለሰበር ሰሚው ችሎትም አቅርበው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የስር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች ከሚች ባለቤታቸው ጋር የመንግስት ቤ.ቁ 763 ተከራይተው ሲኖሩ በባለቤታቸው ሞት ምክንያት የግል ቤት ቁ. 734 ላይ ከሌሎች ወራሾች ጋር የኑዛዜ ወራሽ በመሆን ተጠቃሹን የመንግስት ቤት ሊለቁ ይገባል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እና አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ አቤቱታው እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመሰረቱ የመንግስት መኖሪያ ቤት ለኪራይ የሚገባው የመኖሪያ ቤት ለሌላቸው ነዋሪዎች ነው፡፡ ማንኛውም የቀበሌ መኖሪያ ቤት የተከራየ ሰው የራሱ ቤት ከገነባ ወይም የጋራ ሕንፃ ቤት ከገዙ ወይም የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ቤት ካገኘ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ቤቱን የለቀቁ ከሆነ ቤቱን ባለበት ሁኔታ ለአስተዳደሩ ማስረከብ ያለበት ስለመሆኑ የአ/አ/ከተማ አስተዳደር በወጣው የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁ. 3/2007 አንቀፅ 42/ሀ/ ተመልክቷል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ለክርክር ምክንያት በሆነው መኖሪያ ቤት አመልካች ከባለቤታቸው ጋር ሲኖሩበት የነበረ መሆኑ አልተካደም አመልካች ከሌሎች ወራሾች ጋር በጋራ ሟች ባለቤታቸው ባደረጉት ኑዛዜ የግል ቤት የወረሱ መሆኑ ስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተመልክቷል፡፡ አመልካች በክሱ መሰማት ወቅት ባለቤታቸው ቁጥሩ 734 የሆነ የግል ቤታቸውን የራሱን ድርሻ ከሌሎች 4 ልጆች ጋር እንዲወርሱ እንደተናዘዙላቸው ያመኑ መሆኑ ስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተመልክቷል፡፡ በሰበር አቤቱታቸውም ሟች ባደረጉት ኑዛዜ የራሳቸውን ግማሽ ድርሻ አመልካች ከአራት ወራሾች ጋር በመሆን 1/5 ኛ ለአመልካች እንዲሰጥ የተናዘዙ መሆኑን እና የሟች የውርስ ንብረት ተጣርቶ ድርሻዬ አልተለየም፡፡ የውርስ ድርሻ አለኝ ማለት ለመኖር የሚያስችለኝ ቤት አለኝ ማለት አይደለም፡፡ በኑዛዜው መሰረት ገንዘብ ወይም ቤት ይድረሰኝ አልታወቀም በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የአመልካች ባለቤት በኑዛዜ የራሳቸውን ድርሻ እና ሙሉ የቤት ዕቃ በቀጥታ ሰጥተዋቸዋል፡፡ ቤቱ ከ10 በላይ ሰርቪስ ቤት ያለው 720 ካ.ሜ ነው

www.abyssinialaw.com

ለአራት ሰዎች የተላለፈ በመሆኑ አመልካች ከዚህ የመኖሪያ ቤት አይደርሳቸውም ብሎ ማለት የሚቻል አይደለም ስር ፍ/ቤት ይህን በማጣራት ወስኗል፡፡ በማለት ተከራክሯል፡፡

በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ አመልካች ከሌሎች ወራሾች ጋር በኑዛዜ የወረሱትን ቤት ይዘት እና ከዚህ ቤት ለአመልካች ለመኖሪያ የሚሆን ቤት የሚደርሳቸው ስለመሆኑ መጣራቱን ውሳኔው አያመለክትም፡፡ የአመልካች ባለቤት ባደረጉት ኑዛዜ አመልካች ከሌሎች 4 ወራሾች ጋር የቤ.ቁ 734 የሆነውን የግል መኖሪያ ቤት በጋራ እንዲወርሱ ያሉ ቢሆንም ቤቱ ለወራሾች በዓይነት ተካፍሎ ለአመልካች ለመኖሪያ የሚሆን ቤት በክፍፍሉ ሊደርሳቸው የሚችል መሆን አለመሆኑን ስር ፍ/ቤት ሳያጣራ አመልካች ከሌሎች ወራሾች ጋር የግል ቤት በኑዛዜ አግኝተዋል በሚል ብቻ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን መመሪያ ቁ. 3/2007 ዓላማና መንፈስ የተከተለ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ፈፅሟል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአ/አ/ከ/አስ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 04308 በቀን 10/03/08 በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ፣ የአ/አ/ከ/አ/ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 24398 በቀን 1/4/08 እና ሰበር ሰሚ ችሎቱ በመ/ቁ 24659 በቀን 20/5/08 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአ/አ/ከ/አስ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት የተዘጋውን መ/ቁ. 04308 የሆነውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የአመልካች ባለቤት የነበሩት ሟች አቶ አረጋ ካሳ ቤ.ቁ 734 ላይ ባደረጉት ኑዛዜ መሰረት በኑዛዜ ወራሾች መካከል ክፍፍል ቢደረግ ለአመልካች መኖሪያ ቤት የሚደርሳቸው መሆን አለመሆኑን ተገቢውን ማጣራት በማድረግ እንዲወሰን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሰረት ጉዳዩን ወደ ስር ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ላስከተለው ወጭ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 111311

መጋቢት 23 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** በን/ስ/ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የግንባታ ፈቃድ ቁጥጥር ጽ/ቤት - አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** አቶ ሲሳይ ተስፋዬ -አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 65367 በቀን 7/11/06 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ላይ ያቀረቡትን ይግባኝ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሠሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 22512 በቀን 7/02/07 እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሠሚ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 22762 በቀን 02/06/07 ዓ.ም በማጽናታቸው መሠረታዊ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ የሠጠው የአሁን ተጠሪ በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 3 ክልል ውስጥ ከሚገኘው የቤት ቁጥር 1/17 የሆነ ቤታቸው ጋር በተያያዘ ከጉረቤት ጋር የወሰን ምልክት ይሆን ዘንድ አጥር ያጠሩበት ይዞታ መኖሩን በይዞታው ላይ ለ10 ዓመት ግብር የገበሩበት መሆኑን፣ አጥሩ በሊዝ ወደ ህጋዊ ይዞታቸው እንዲጠቃለል አመልካችን ጠይቀው ተከሳሽም ካርታ እንዲዘጋጅ በ07/10/2001 ዓ.ም የተጻፈ ደብዳቤ ለክ/ከተማ ፅፎ የነበረ ቢሆንም በ2004 ዓ.ም ካወጣው የሊዝ አዋጅ ሥርዓት ጋር በተገናኘ ጥያቄው መቆሙን፣ ይህ በእንዲህ እንዳለ የአሁን አመልካች በ20/02/2006 በተፃፈ ደብዳቤ አጥሩ በ3 ቀን

www.abyssinialaw.com

እንዲፈርስ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሁከት የፈጠረብኝ በመሆኑ ሁከት እንዲነሳ ይወሰንልኝ በማለት በ20/03/2006 ዓ.ም ያቀረቡትን ክስ መነሻ በማድረግ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በሰጠው መልስ ክርክር ያስነሳው አጥር ተጠሪ አስፋፍተው የያዙት ትርፍ ቦታ ላይ የሚገኝ መሆኑን፣ አጥሩን ለመስራት የግንባታ ፈቃድ አለማውጣታቸውን ማስጠንቀቂያው የተጣለብኝን ኃላፊነት የምወጣበት እንጂ ሁከት አለመሆኑን በመገለጽ ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ማስረጃዎችን ከመረመረ በኋላ ከክ/ከተማው የመጡት ምላሾች የአሁን ተጠሪ ያጠሩት ቦታ መንገድ መሆኑንና መንገድ ሆኖ አጐራባቾች ሲገለገሉበት ቆይተው በመሀል የተጠሪ መሆኑን የሚያስረዱ አይደሉም፡፡ መንገድ በከሳሽ ይዞታ ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም የአሁን አመልካች በሌላ አካሄድ መጠየቅ ከሚችል በቀር በማስጠንቀቂያ መጠየቅ አይችልም፡፡ የከተማ ልማት ጥናቱ /LDP/ ወደ ተግባር ያልተሸጋገረ በመሆኑ እሱን መሠረት በማድረግ ለባለይዞታው ሳይነግሩ ይዞታው እንዲፈርስ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል፡፡ ይህም ሁከት በመሆኑ ይወገድ በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡ ይህንኑ ውሳኔ የከተማዋ አስተደደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመደበኛ ይግባኝ እና በሰበር ችሎት ተመልክቶ አፅንቶታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአቤቱታው ይዘትም ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት መመስረት የነበረበትን ጭብጥ ሳይመሰርት፣ የአሁን ተጠሪ በግልፅ አከራካሪው ይዞታ ወደ ይዞታቸው እንዲጠቃለልላቸው የጠየቁ መሆኑን በማለፍ ከከተማው የአስተዳደር አካላት የመጣውን ምላሽ ያለአግባብ በመረዳት፣ በአሁን አመልካች የቀረቡትን ምስክሮች ሳይሰማ በዝምታ በማለፍ፣ በስራ ላይ የዋለውን የኤልዲ.ፒ ጥናት ስራ ላይ ያልዋለ ነው በማለት የመንግስት መሬት አያያዝ አዋጅና መመሪያዎችን ሳይመረምር ወደ ጐን በመተው የአሁን አመልካች ህጐችን ለማስከበር የሠጠውን ግዴታ የሁከት ተግባር ነው በማለት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ እንዲታረም የጠየቁ መሆኑን ያሳያል፡፡

ተጠሪም የአመልካች የሰበር አቤቱታ ደርሷቸው በሰጡት መልስ ክርክር ባስነሳው ይዞታ መሬት ይዞታን አስመልክቶ በወጡ ህጐች መብት ያገኙ መሆናቸውን የስር ፍ/ቤት ከከተማው አስተዳደር አካላት የመጡትን ምላሾች በትክክል ተረድቶ የተገበረ መሆኑንና የኤል.ዲ ፒ ጥናት ከ20 ዓመት በፊት ለተገነባ አጥር ተመልሶ ተግባራዊ መሆን የሌለበት መሆኑን በመግለፅ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ ፀንቶ አመልካች የተጠሪን ወጪና ኪሳራ እንዲሸፍን ይታዘዝልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቹም የመልስ መልስ አቅርቦ ክርክሩን አጠናክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም በዚህ ችሎት ዕልባት ማግኘት ያለበት የአሁን አመልካች ድርጊት የሁከት ተግባር ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሁከት ተፈጥሮብኛል ይወገድልኝ የሚል ተከራካሪ ወገን ሁከት ተፈጠረበት በተባለው ንብረት ላይ የተሻለ መብት ያለው መሆኑን የመለየት ግዴታ ያለበት መሆኑን ከፍ/ህ/ቁ 1149 ድንጋጌ መረዳት እንችላለን፡፡

በዚህ በያዝነው ጉዳይ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ አከራካሪ የሆነው አጥር የሚገኝበት ቦታ በሊዝ ሥሪት መሠረትም ወደ ይዞታቸው እንዲገባላቸው የጠየቁ መሆኑን፣ ቦታውን አጥር በማጠር የያዙት በራሳቸው የወሰን ምልክት ይሆነኛል በማለት እንደሆነ ነው፡፡

በመሠረቱ ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው አካል ፈቃድ ሳያገኝ በህጋዊነት ከያዘው ይዞታ ጐን ያለን የከተማ ቦታ አስፋፍቶ መከለልና መጠቀምም ሆነ በሊዝ አዋጁ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ የከተማ ቦታ መያዝ እንደማይችል የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 5/2/ እና /4/ ተቀምጧል፡፡

የአሁን ተጠሪ አከራካሪ የሆነውን ቦታ በሊዝ ወደ ይዞታቸው ለመቀላቀል አቅርበውት የነበረው ጥያቄም ተቀባይነት አግኝቶ ያልተፈፀመ መሆኑን ገልፀው ቦታውን የያዙኩት ከሊዝ አዋጁ መውጣት በፊት ሲሆን ነባር ይዞታን ወደ ሊዝ ስሪት በመቀየር ከቀድሞ ይዞታቸው ጋር እንዲካተትላቸው እየጠየቁ በሂደት ላይ ያለ ሁኔታ መኖሩን፣ የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡

የሚመለከታቸው የከተማዋ አስተዳደር አካላትም የሰጡት መልስ እንደሚያስረዳው በተጠሪ ካርታ ላይ በተጠናው የኤል.ዲ.ፒ ጥናት መሠረት በቦታው ላይ መንገድ ያለ መሆኑን ይገልጻል፡፡ የከተማ ቦታ አሰጣጥ ስርዓት ደግሞ የህዝቡንና የከተሞችን ጥቅም በቀዳሚነት በማስከበር የከተማ ልማትን በማፋጠንና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የዜጐችን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ የሀገሪቱን ልማት ቀጣይነት የሚያረጋጋጥ መሆን እንዳለበት የሊዝ አዋጁ አንቀጽ 4/4/ ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በቦታው ላይ የሊዝ ጥያቄ አቅርቤ በመጠየቅ ላይ እገኛለሁ ቢሉ እንኳን ቦታው የከተማዋ ልማት እንቅስቃሴ አካል የሆነው መንገድ የሚሠራበት መሆኑን መሠረት በማድረግ አመልካች ለተጠሪ አጥሩን እንዲያፈርሱ የሰጠው ትዕዛዝ በህግ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት የወሰደው እርምጃ ሆኖ እያለ በስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ አጥሩን እንዲያነሱ የፃፉው ደብዳቤ የአመልካችን ድርጊት የሁከት ተግባር ነው ያለው ያለአግባብ ስለሆነ ውሳኔውን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 05367 በቀን 7/11/06 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማዋ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 22512 በቀን 7/02/07 ዓ.ም እና በከተማዋ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 22762 በቀን 02/06/07 ዓ.ም ያፀናው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ከህጋዊ ይዞታ ውጭ ያለፈቃድ ያጠረውን አጥር እንዲያነሳ አመልካች የፃፈው ደብዳቤ የሁከት ተግባር አይደለም፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 107777

መጋቢት 28/2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- የሱሉልታ ከተማ አስተዳደር -አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- አቶ ደባልቄ ደምሴ -ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካች የሱሉልታ ከተማ አስተዳደር ታህሳስ 10/2007 ዓ.ም. በተጻፈ አቤቱታ ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) በመሬቱ ላይ የነበረውን የከሳሽ (የአሁን ተጠሪ ) ንብረት በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 25(5 እና 6) መሰረት ያለምንም ክፍያ ሊወሰድ እንደሚችል ደንግጎ እያለ የስር ፍ/ቤት ንብረቱ ይመለስ ብሎ መወሰኑ ካለአግባብ ነው፡፡ ከሳሽ የንብረቶቹን ትክክለኛ ግምትና አይነት የሚያስረዳ ማስረጃ ባልቀረበበት ንብረቱ ይመለስ መባሉ አግባብነት የለውም፡፡ ተከሳሽ በጽሁፍ በሰጠው ማስጠንቀቅያ ከሳሽን ያሳወቀው በመሆኑ ለንብረቱ መጥፋትና መበላሸት ሃለፊነት የለበትም፡፡ ተከሳሽ ንብረቶቹን ለማፍረስ ለተጠቀመው የሰው ሀይል ወጪ ታሳቢ ሳይደረግ የትኞቹ ንብረቶች መመለስ እንዳለባቸው ሳይለይ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ባለመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ ) አቶ ደባልቄ ደምሴ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ በፊንፊኔ ዙርያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍ/ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተከሳሽ የሱሉልታ ከተማ አስተዳደር የከሳሽ ጋራዥ የሆነውን በሱሉልታ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኝ ስፋቱ 1500 ካ/ሜ በካርታ ቁጥር 05-ስ-01/90 አዋሳኙን ጠቅሶ የካቲት 7/2001 ዓ.ም.

www.abyssinialaw.com

ስላፈረሰብኝ በሁከት ከስሼ ሁከት የለም ተብሎ ቢወሰንም አፍርሶ የወሰደብኝን ንብረት ግምት ለመጠየቅ ስለምችል ግርግዳው በቆርቆሮ እና በእንጨት የተሰራ 2 ቤቶች፣ የተከልኳቸው ባህር ዛፎች፣ 120 ቢያጆ ድንጋይ፣ በቆርቆሮ የተሰራ አጥር፣ የአየር ኮምፕሬሰር ከነ ዕቃው፣ አንድ የብረት መበየጃ፣ አንድ ግራይንደር፣ ትራንስፎርመር ጨምሮ የተለያዩ መፍቻዎች ሁለት የብረት ሳጥኖች በአጠቃላይ ብር 1,330,100 እንዲከፍለኝ ሲል ከሷል፡፡ ተከሳሽም በሰጠው መልስ ከሳሽ በተጠቀሰው መሬት ላይ ለ3 ዓመት ከ1990 ዓ.ም. እስከ 1993 ዓ.ም. ድረስ ለመጠቀም ከተከሳሽ ላይ በሊዝ ውል ወስዶ እያለ ለ7 ዓመት ለመልቀቅ ፍቃደኛ ስላልሆነ በአዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 25(5 እና 6) እና አንቀጽ 16(1እና2) እንዲሁም በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 25(5 እና 8 ) መሰረት ንብረቱን የማንሳት ስልጣን ስላለን ቦታውን ለህዝብ አገልግሎት እንዲውል ማድረጋችን ህጋዊ በመሆኑ ከሳሽ የጠየቀውን ንብረት ግምት የመክፈል ግዴታ የለብንም፡፡ ሃላፊነት አለባቸው ቢባል እንኳ ከመሬቱ ላይ የተወረሰው ንብረት ከጭቃ እና እንጨት የተሰራ 2 ቤት እና 2 ቢያጆ ድንጋይ በአጠቃላይ ግምቱ 50000 ብር የማይበልጥ ሆኖ ሳለ በከሳሽ የቀረበው ግምት የተጋነነ በመሆኑ ውድቅ ይሁንልኝ ብሏል፡፡ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ፊንፊኔ ዙርያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ. ቁጥር 09981 አከራክሮ ነሐሴ 15/2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ከሳሽ ለክርክር ምክንያት የሆነው መሬት ከ1990 ዓ.ም. እስከ 1993 ዓ.ም. ድረስ ተከራይቶ የክራዩ ዘመን ያበቃ ቢሆንም ለ7 ዓመት ይዞ ለመልቀቅ ፍቃደኛ ባለመሆኑ ተከሳሽ ከመሬቱ ላይ ንብረቱን ስላነሳ በሁከት ከሶት ሁከት የለም ተብሎ ተወስኗል፡፡ በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 25(5) መሰረት የኪራይ ውል ከተጠናቀቀ በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ንብረቱን ካላነሳ የሚመለከተው አካል መሬቱን በላዩ ላይ ካለው ንብረት ጋር ካለክፍያ መውሰድ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 25(6) በመደንገጉ የከሳሽ የሊዝ ውል ኪራይ በ1993 ዓ.ም. ካለቀ በኋላ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ንብረቱን አንስቶ መሬቱን ማስረከብ ሲገባው እስከ 7 ዓመት ይዞ በመቆየቱ ተከሳሽ ያለ አንዳች ክፍያ ንብረቱን አንስቶ መሬቱን መውሰድ ስለሚችል ተከሳሽ ለተጠየቀው ክፍያ ሃላፊነት የለበትም ሲል ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁጥር 170402 ታህሳስ 1/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ለቀረበው የይግባኝ ቅሬታ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ጉድለት ያለበት ሆኖ አልተገኘም ሲል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁን ተጠሪ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁጥር 183036 አከራክሮ መስከረም 19/2007 በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ከሳሽ ከ1990 ዓ.ም. እስከ 1993 ዓ.ም. በሊዝ ኪራይ የያዘውን መሬት ጊዜው ተጠናቆ

www.abyssinialaw.com

የውሉ ዘመን የሚታደስ ካልሆነ ንብረቱን አንስቶ ይዞታውን ለተከሳሽ መመለስ እንደሚገባው አያከራክርም፡፡ ከሳሽ ውሉ ሳይታደስ እስከ 2001 ዓ.ም. ድረስ መቆየቱ ታውቋል ተከሳሽ ታህሳስ 3/2001 ዓ.ም. እስከ የካቲት 26/2001 ዓ.ም. ድረስ ለከሳሽ የማስጠንቀቅያ ደብዳቤ መፃፉ ተረጋግጧል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 15(5) እና 16(1 እና 2) እንዲሁም በመሬት ሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 25 (5 እና 6) ከመሬቱ ላይ የነበረውን ንብረት ከሳሽ ለማንሳት ፍቃደኛ ባለመሆኑና ተከሳሽ በማንሳቱ ካሳ ለመክፈል የሚገደድ አይደለም፡፡ ይሁንና ተከሳሽ በመሬቱ ላይ የነበረውን ንብረት ለመውሰድ የሚፈቅድለት ህግ ባለመኖሩ የወሰደውን ንብረት ለአመልካች መመለስ አለበት ሲል የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አሻሽሎ ተከሳሽ የወሰደውን ንብረት ይመልስ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ አመልካች ለተጠሪ በኪራይ የሰጠውን ቦታ የኪራይ ዘመኑ ካለቀ በኂላ ተጠሪ መሬቱን ለአመልካች ለመመለስ ፈቃደኛ ሳይሆን በመቅረቱ አመልካች በቦታው ላይ የነበረውን ቤት አፍርሶ መውሰዱ አያስጠይቀውም በማለት በክልሉ የስር ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሽሮ አመልካች የወሰደውን ንብረት ይመልስ በማለት የሰጠውን ውሳኔ ከአዋጅ ቁጥር 272/1994 አንቀጽ 25(5) ድንጋጌ አንጻር ለማጣራት ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ሚያዚያ 15/2007 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ የአመልካች አቤቱታ በተሻረ አዋጅ ቁጥር 272/94 ን በመጥቀስ ከአዋጅ ቁጥር 721/2004 ጋር በመጻረር የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ይሁንልኝ፡፡ አመልካች ከአዋጁ ድንጋጌ ውጪ ንብረቱን የወሰደብኝ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ይህንኑ በመጥቀስ የሰጠው ውሳኔ ተገቢና ቅር የማያሰኝ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሆኖ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ግንቦት 9/2007 ዓ.ም. በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

በዚሁ መሰረት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መዝገቡን እንደመረመርነው፡ የአሁን ተጠሪ የ3 ዓመት የሊዝ ኪራይ ውል ማብቃቱ እና በቦታው ላይ ያከናወነውን ግንባታ በህግ በተቀመጠው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያላነሳና ከዚያም በላይ እስከ 7 ዓመት የቆየ መሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ የአሁን አመልካች በአዋጅ ቁጥር 721/2004 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ቦታውን ከነንብረቱ ያለምንም ክፍያ ሊወስድ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 25(6) ስር ተደንግጓል፡፡ የአሁን ተጠሪ በአዋጁ አንቀጽ 25(5) መሰረት ቦታውን የሊዝ ጊዜው እንዳለቀ በአንድ ዓመት ውስጥ ንብረቱን አንስቶ ቦታውን ለሚመለከተው አካል ያላስረከበ መሆኑ በመረጋገጡ አመልካች በቦታው ላይ የነበሩትን ግንባታ አፍርሶ መውሰዱ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 25(6) መሰረት

www.abyssinialaw.com

ሃላፊነት የሚያስከትልበት አይደለም፡፡ በአዋጁ ቁ. 721/2004 አንቀጽ 25(5 እና 6) መሰረት ተጠሪ በሊዝ የያዘውን መሬት ጊዜው አልቆና ባለመታደሱ በቦታው ላይ ያሰፈረውን ንብረት አንስቶ ቦታውን ለሚመለከተው አካል ባለማስረከቡ አመልካች በቦታው ላይ የሰፈረውን ንብረት አንስቶ መውሰድ ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡ ይሁንና በቦታው ላይ የሰፈረ ንብረት ሲባል ግን ቦታውን ለተፈለገው ሥራ ጉዳይ እንዳያስቸግሩ ምቹ ለማድረግ በቦታው ላይ የተሰሩ ግንባታዎችንና ከዚሁ ጋር የሚያያዙ የመሳሰሉትን ንብረቶች ለማንሳት እንጂ በቀላሉ የሚነሱ የሥራ መገልገያዎችን ጨምሮ የሚወረስ መሆኑን አያመለክትም፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች በቦታው ላይ በተጠሪ የተገነቡ ግንባታዎች ቤቶች፣ ድንጋዮች፣ ባህር ዛፎች እና አጥር አንስቶ መውሰዱ በአዋጁ መሰረት ሃላፊነት ያለበት አይደለም፡፡ ከዚህ ውጪ ያሉትን ግን ተጠሪ በአመልካች ተወስደውብኛል ሲል የከሰሰውና አመልካቾ በመልሱ መውሰዱን ያላመነውን የሥራ መገልገያ ንብረቶችን በተመለከተ ለመውረስ በአዋጁ የሚሸፈን ባለመሆኑ ተጣርቶ ለተጠሪ ሊመለስ የሚገባ ነው፡፡ የስር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካች ንብረቱን ከቦታው ላይ ማንሳቱ ተገቢነቱን ተቀብሎ ንብረቱን ግን ለመውረስ የሚፈቅድለት ህግ የለም የወሰደውን ንብረት ይመልስ ሲል መወሰኑ በአዋጁ በግልጽ ተቀምጦ ባለና የሚመለሱ ንብረቶችንም ሳይለይ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ሊታረም የሚገባ ነው፡፡ በአዋጅ ቁ. 721/2004 አንቀጽ 25(6) አመልካች ከቦታው ላይ የሰፈሩ ንብረቶችን አንስቶ መውሰድ እንደሚችል ደንግጎ እያለ ተጠሪ ተወስደውብኛል ሲል የከሰሰውና የአሁን አመልካችም ወስጃለሁ ያላላቸውን ንብረት በማስረጃ ሳይጣራና ሣይለይ በደፈናው አመልካች የወሰደውን ንብረት ይመልስ ብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁ. 193036 መስከረም 19/2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ. ቁ. 170402 ታህሳስ 1/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣ በፊንፊኔ ዙርያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ. ቁ. 09981 ነሐሴ 13/2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ፊንፊኔ ዙርያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች(ተከሳሽ) ተወስደውብኛል ሲል በክሱ እንዲመለሱለት ከጠየቀው ንብረቶች ውስጥ ቤቶቹን፣ ድንጋዮች፣ ባህርዛፎች እና አጥርን ሳይጨምር የተጠሪ ስራ መገልገያ ንብረቶች የማይወረሱ ያልናቸው እንደ የአየር ኮምፐሬሰር፣ የብረት መበየጃ፣ ግራይንደር ትራንስፎርመርን ጨምሮ፣ የተለያዩ መፍቻዎች እና የብረት ሳጥኖች

www.abyssinialaw.com

ያላቸውን እና በአመልካች መወሰዳቸው ያልታመኑ በመሆኑ በአመልካች መወሰድ አለመወሰዳቸው በማስረጃ በማጣራት ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡

3. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሳራ ተቻቻሉ ብለናል፡፡
4. ለኦ/ብ/ክ/መ/ ፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በዚህ ውሳኔ መሰረት እንዲከወን የዚህ ውሳኔ ቅጂ ይድረሰው ለሌሎች የስር ፍ/ቤቶች ደግሞ እንዲያውቁት ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 106436

ሚያዚያ 25 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- አቶ ተክኤ ፀጋይ ተስፋይ -ቀርበዋል

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ንግስቲ ገ/መድህን - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካች አቶ ተክኤ ፀጋይ ተስፋይ ጥቅምት 11/2007 ዓ/ም. በተጻፈ አቤቱታ ከተጠሪ ጋር ያደረግነው የመሬት ይዞታ ልውጫ በፍላጎታችን ተስማምተን ያደረግነውና ለ3 ዓመት ቆይቶ የሚፈርስበት ምክንያት ሳይኖር መሬቱን ይመላለሱ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ ተጠሪ የመሬት ለውጥ ውል መኖሩን እያመነች በሥር ፍ/ቤት ወደነበሩበት ይመለሱ መባሉ አለአግባብ በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ወ/ሮ ንግስቲ ገ/መድህን በትግራይ ብ/ክ/መንግስት በፅምብላ ወረዳ አስተዳደር በደብረአባይ ቀበሌ መሬት አስተዳደር ዳኝነት አካል ባቀረቡት ክስ ከሳሽና ተከሳሽ አቶ ተክኤ ፀጋይ መሬት ተለዋውጠን በኔ የመሬት ይዞታ ላይ ቤት ሰርቶበት የራሱን ግን ያላስረከበኝ በመሆኑ መሬቴን ይመልስልኝ ስትል ከሳለች ተከሳሽም በሰጠው መልስ መሬት ተለዋውጠናል ከተለዋወጥን ከ3 ዓመት በኋላ እና ቤት ሰርቼበት ካለማሁ በኋላ ይመልስልኝ ማለቷ ተገቢ ባለመሆኑ ክሷ ውድቅ ይሁንልኝ ብሏል፡፡

www.abyssinialaw.com

የደብረ አባይ ቀበሌ መሬት አስተዳደር የዳኝነት አካል አከራክሮ ጥር 14/2006 ዓ/ም. በሰጠው ውሳኔ ከሳሽና ተከሳሽ መሬት እንዲለዋወጡ የቀበሌው የመሬት አስተዳደር ድጋፍ ሰጥቷቸው እና በመሬት አስተዳደር ዴስክ እንድትጨርሱ ተብሎ የነበረ ቢሆንም ሳይጨርሱ ቀርተዋል። የከሳሽ መሬት በተከሳሽ እጅ ያለው ወሰኑን በመጥቀስ ለከሳሽ ይመለስ በማለት ወስኗል። ተከሳሽ ለፅምብላ ወረዳ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የፅምብላ ወረዳ ፍ/ቤት በመ. ቁጥር 04232/06 አከራክሮ ሚያዚያ 15/2006 ዓ/ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የግራ ቀኙ ምስክር ተሰምቶ ከሳሽና ተከሳሽ የተለዋወጡት መሬት ተከሳሽ ሁለት ቤት የሰራበት ቢሆንም የመሬት ለውጡ በሚመለከተው አካል አልፀደቀም። በመሆኑም ልውጫው ህጋዊነት የሌለው በመሆኑ ወደየራሳቸው ይመለሱ ተከሳሽ የሰራውን ቤት በተመለከተ የቤቱን ዋጋ ተስማምተው ለተከሳሽ ይከፈለው። ካልሆነ ¼(አንድ አራተኛ) ከሳሽ ለተከሳሽ ትክፈለው ሲል ወስኗል።ተከሳሽ ለሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 18282/06 አከራክሮ ግንቦት 29/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ግራ ቀኙ መሬት መለዋወጣቸውን አይካካዱም እየተከራከሩ ያለው የመሬት ልውጫው በሚመለከተው አካል አልፀደቀም በሚል ነው። የመሬት መለዋወጡ ከህግ ጋር እስካልተቃረነ ድረስ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም። ከዚህም በላይ ውል ይፍረስ ቢባል እንኳ ወደ ነበሩበት መመለስ የሚችሉ አይደለም ተከሳሽ በመሬቱ ላይ በብር 70000 የሚገመት ቤት ሰርቶበታል። በመሆኑም የተለዋወጡትን መሬት ይዘው ይቆዩ ሲል የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ወስኗል። ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ ) ለትግራይ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርባ የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁጥር 68037 አከራክሮ ጳጉሜ 3/2006 ዓ/ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ በተከራካሪዎቹ መሀከል የመሬት ልውጫ የተባለው ህጉ በሚያዘው በአዋጅ ቁ. 239/06 እና ደንብ ቁ. 48/2000 መሰረት በውልና ማስረጃ ፀድቆ የወረዳው የመሬት ዴስክ አውቆ በቅፅ ተሞልቶ የተለዋወጡ ካልሆነ ህጋዊ ልውጫ አይደለም። ይህ ሆኖ እያለ ከፍ/ፍ/ቤት የወረዳውን ውሳኔ እና የቀበሌውን ውሳኔ መሻሩ ስህተት ነው በማለት የከፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮ የወረዳውንና የቀበሌውን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል።

የአሁን አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል። መዝገቡ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ግራ ቀኙ ይዞታቸውን ተለዋውጠው ከቆዩ በኋላ ልውውጡ በሚመለከተው አካል አልፀደቀም በሚል ብቻ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ቀርቧል። መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል። ተጠሪ የካቲት 25/2007 ዓ/ም. በተፃፈ መልስ በኔና አመልካች ተደርጎ የነበረውን የመሬት ለውጥ የመሬት ውል አፅዳቂው አካል አመልካች የመሬት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሌለው ስለሆነ አላጸደቀውም። በመሬቱ ላይ የሰራቸው

www.abyssinialaw.com

ስራዎች እየተቃወምኩት የሰራው ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር የሚያሰኝ ባለመሆኑ ይጽናልኝ ብለዋል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ባለመቅረቡ ታልፏል፡፡

በዚሁ መሰረት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መዝገቡን እንደመረመርነው፡ በትግራይ ብ/ክ/መ. የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 239/06 የተመለከተውን አሟልቶ የመሬት ይዞታ መለዋወጥ አልተከለከለም፡፡ ይሁንና አመልካች ከተጠሪ ጋር ተለዋወጥን የሚሉት የመሬት ይዞታ በአዋጅ ቁ. 239/06 መሰረት በውልና ማስረጃ ጸድቆ የወረዳው የመሬት ዴስክ ያልመዘገበው በመሆኑ የክልሉ የመሬት አስተዳደርና እና አጠቃቀም አዋጅና ደንቡ በሚደነግገው መሰረት ያላሟላ በመሆኑ የመሬት ይዞታ ልውጫ በአመልካችና ተጠሪ መሀከል ተፈጽሟል ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም የትግራይ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁጥር 68037 ጳጉሜ 3/2006 ዓ/ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ የፅምብላ ወረዳ ፍ/ቤት በመ. ቁጥር 04232/06 ሚያዚያ 15/2006 ዓ/ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሳራ ተቻቻሉ ብለናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ መጋቢት 23/2007 ዓ/ም. በዋለው ችሎት የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይጻፍ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነብ የአምስት ዳኞች ፊራማ አለበት፡፡

ት/ጌ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 119557

ሐምሌ 19 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች ፡- አቶ ማናለው ተካ - ተወካይ ታዴ ተካ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እቴነሽ ተካ - ተወካይ አቶ ተስፋው ከቤ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳዩ የተጀመረው በምስራቅ ጎጃም ዞን እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ወላጅ አባቴ አቶ ተካ አንተነህ በስጦታ ያስተላለፉልኝን መሬት አመልካች በጉልበት በመያዝ እየተጠቀመበት ስለሚገኝ እንዲለቅልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች የሰጠው መልስ ክስ የቀረበበት መሬት ላይ ለተጠሪ የስጦታ አስተላላፊ ከሆኑት ከአቶ ተካ አንተነህ ጋር አስቀድሞ የካቲት 7 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ የእርቅ ስምምነት ያለቀ በመሆኑ የተጠሪ ስጦታ አድራጊ በስጦታ ለማስተላለፍ የማይችሉ ከመሆኑም በላይ መሬቱ ለአመልካች እናት ጭምር የተሰጠ ስለሆነ የተጠሪ ክስ የአመልካችን መብት የሚነካ ስለሆነ ውድቅ እንዲደረግ በማለት መልሱን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አቶ ተካ አንተነህ አስቀድሞ ያደረጉት የእርቅ ስምምነት መሬቱን በስጦታ ከማስተላለፍ የሚከለክል ባለመሆኑ አመልካች መሬቱን ለተጠሪ ሊለቅ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታ ለምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤቱም አቶ ተካ አንተነህ መሬቱን በተመለከተ አስቀድመው በእርቅ የጨረሱ

www.abyssinialaw.com

ስለሆነ መሬቱን ለሌላ ሰው የማስተላለፍ መብት የላቸውም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

ተጠሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአ/ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲሁም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው የክልሉ ሰበር ችሎት አባ ተካ አንተነህና አመልካች ያደረጉትን ስምምነት ይዘት የአባ ተካ አንተነህ የይዞታ መሬት አመልካች ይዞ እያረሰ ሰብል እንዲሰጥ የተስማሙበት እንጂ የአባ ተካን መሬት ወደ አመልካች የማስተላለፍ ህጋዊ ውጤት ያለው ስምምነት አይደለም፤ የክፍሉ መሬት አስተዳዳርም አስቀድሞ የአባ ተካ መሬት ለአመልካች ያለማስተላለፉን በመገንዘብ ለተጠሪ የተሰጠውን ስጦታ መዝግቦታል በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ጥቅምት 30 ቀን 2008 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በክልሉ ሰበር ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ:- በአባ ተካ አንተነህ እና በአመልካች መካከል የካቲት 7 ቀን 2003 ዓ.ም የተደረገው እርቅና በፍርድ ቤት የፀደቀው ስምምነት ባለበት ሁኔታ እንዲሁም በዚሁ ስምምነት መሰረት እንዲፈፀም የአፈፃፀም ትእዛዝ ባለበት ሁኔታ ያደረጉት ስምምነት መሬቱን ወደ አመልካች የማስተላለፍ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይህ ውሳኔ ተሽሮ የካቲት 7 ቀን 2003 ዓ.ም የተደረገው ስምምነት እንዲፈፀም ለተጠሪ የተደረገው ስጦታ እንዲሻር በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት የካቲት 2 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካች ጥያቄ ለክርክር መነሻ የሆነው መሬት በእርቅ ስምምነት ያገኙሁት ለተጠሪ ልለቅ አይገባም የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል ደግሞ በስጦታ ያገኘሁትና በአግባቡ በማስረጃ ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ለክርክሩ መነሻ የሆነው የመሬት ይዞታ አመልካች ከስጦታ አድራጊ አባ ተካ የእርቅ ስምምነት የነበራቸው መሆኑ እና ተጠሪም በስጦታ የተሰጣቸው መሆኑ አከራካሪ ነጥብ አይደለም፡፡ የሚያከራክረው

www.abyssinialaw.com

በአመልካችና በአባ ተካ መካከል የተደረገው የእርቅ ስምምነት ይዘት ላይ ነው፡፡ ስለሆነም የእርቁ ስምምነት አመጣጥ መመርመሩ ተገቢ ነው የሚሆነው፡፡

አመልካች ለአባ ተካ የመሬት ይዞታ እያረሰ በአላባ እንዲጠቀም በነበራቸው ስምምነት አለመግባባት በመፈጠሩ ጉዳያቸው ወደ ፍርድ ቤት ደርሶ ሲከራከሩ ከቆዩ በኂላ ባደረጉት የእርቅ ስምምነት ሊቋጭ እንደቻለ ነው፡፡ ከዚያ በኂላ አባ ተካ የአማራ/ብ/ክ/መ/ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ አንቀጽ 15/1/፣17 ማንኛውም ሰው የይዞታ መብቱን በስጦታ ለማስተላለፍ በሚፈቅደው መሰረት በሚመለከተው አካል ቀርበው ለአሁን ተጠሪ በስጦታ መስጠታቸውን በክፍሉ ተመዝግቦ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው መሆኑ የፍሬ ነገር የማጣራትና የማስረጃ የመመዘን ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋጋጠ ነው፡፡

የእርቁ ስምምነት ይዘት አባ ተካ የመሬት ባለይዞታ በመሆን አመልካች ደግሞ በጉልበቱ እያረሰ የአላባ የመጠቀም መብት የሚሰጥ ነው፡፡ ይህ የእርቅ ስምምነት ለአባ ተካ የመሬት ይዞታቸው በስጦታ ለፈለጉት ሰው የማስተላለፍ መብታቸውን የሚገድብ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ስምምነቱ አመልካች የአባ ተካ ይዞታ እስካለ ድረስ የአላባ የመጠቀም መብት የሰጠ ነው፡፡ ይዞታው ለሌላ ሰው ከተላለፈ ተጠሪ በአላባ የመጠቀም መብቱም የማቋረጥ ውጤት ነው ያለው፡፡ አመልካች ሌላ መከራከሪያ ነጥብ አባ ተካ ለተጠሪ ያደረጉት ስጦታ የእናቴ ይዞታ ጭምር ነው በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የመሬት ይዞታው ለአባ ተካ ተለክቶ የተሰጣቸው መሆኑን ባደረጉት ማጣራት የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ ችሎትም በፍሬ ነገር የማጣራትና የመመዘን ስልጣን በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ስልጣን ያልተሰጠው ስለሆነ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሲጠቃለል በተያዘው ጉዳይ ላይ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአ/ብ/ክ/መ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.03-40156 ጥቅምት 9 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0116362 ታህሳስ 25 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የአ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.37155 ሚያዝያ 2 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠ ትእዛዝ በመሻር የእነብሴ ሳርምድር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.01-012499 ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. ከዚህ ፍርድ ቤት የእነብሴ ሳርምድር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0112499 የተጀመረው አፈፃፀም ተላልፎ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስተዋል፡፡ የሚመለከው አካል ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገብ ተዘግተዋል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 118191

መስከረም 24 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነአ ቂጣታ

ክፍለፅዮን ማሞ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- አቶ ድጋፌ ክፍሌ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ጎሣ ገድል - የቀረበ የለም

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የእርሻ መሬት ስጦታ ውል ክርክር የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በአ/ብ/ክ/መ/ሰሜን ሸዋ ዞን የምንጃር ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በ22/03/2007 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 011010715/07 ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- አመልካች ካላቸው የመሬት ይዞታ ለተጠሪ አዋሳኙ በምስራቅ ወንድአፈራሽ ፣በምዕራብ ገደል፣ በደቡብ ጎደና በሰሜን ወንዝ የሚያዋስነው 3 ጥማድ መሬት በሽተኛ በመሆናቸው ተጠሪ መሬቱን፣ በመሬቱ ላይ ያለ ዛፍ እና ድንጋዮች እንዲቆጠርላቸው የመሬት ግብር በየዓመቱ ተከታትሎ እንዲገብር በቀን 18/07/2005 ዓ.ም በተፃፈ የስጦታ ውል አድርገው በስጦታ ይዞታ መሬቱን አስተላልፈውለት ተጠሪው የመሬት ግብር እንኳ ሳይገብር ለከፍተኛ ጉዳት መዳረጉን፣ በመሬቱ ላይ ያሉ ዛፎችም ያልተንከባከባቸው የተቆራረጡ እንዲሁም የመሬቱ አጥርም መፍረሱን፤ አመልካችን ሊጠይቃቸውና ሊያስታምማቸው አለመቻሉን በመግለጽ የመሬት ስጦታ ውሉ ፈራሽ እንዲሆንላቸውና ወደነበሩበት እንዲመለሱ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በሰጠው መልስም ከአመልካች ጋር የስጋ ዝምድና እንዳላቸው አመልካችን ለረጅም ዓመታት ያለጥቅም እያረሰ ምርት ሲሰጣቸው እንደነበር ውለታውም ማንም ሳያስገድዳቸው በጤናማ አዕምሮ በራሳቸው ፍላጎት የአካባቢ ሰዎች ሰብስበው በ03/07/2005 ዓ.ም በተፃፈ የስጦታ ውል መስጠታቸው፤ የስጦታ ውሉ በሚመለከተው አካል ከመመዝገቡ በፊት ለአካለ

www.abyssinialaw.com

መጠን ያልደረሱ ሕፃናት ወይም የቤተሰብ አባል እንዳሉ፣ መሬቱ ለ3ኛ ወገን ተላልፎ ወይም በኮንትራት የተሰጠ ከሆነ ከክትቻ ቀበሌ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት እንዲጣራ ተደርጎ መጋቢት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በወረዳው የመሬት አስተዳደር አጠቃቀም ፀድቆ ማስረጃ እንደተሰጠው የስጦታ ውሉ ከህግም ከሞራልም ተቃራኒ አለመሆኑን ስጦታው በሚመለከተው አካል ፊት የተደረገና በስጦታ በተላለፈለት መሬት በስሙ መገበሩን በይዞታ መ/ቁ. A/I/83/17/850 በሆነ ቋሚ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንደወጣለት በመግለፅ አመልካች ያቀረቡት የስጦታ ውል ይፍረስልኝ ክስ ተገቢ ባለመሆኑ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክራል፡፡

የሥር ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም ለክርክሩ መነሻ የሆነው የስጦታ ውል በማስቀረብ ከመረመረ በኋላ ውሉ የመሬት አዋጅ በሚያዘው አግባብ ስለመደረጉ፤ ተጠሪ በስጦታ ባገኘው መሬት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ማውጣቱን፣ አመልካች ውሉን ለማፍረስ እንደመከራከሪያ ያቀረቡት ምክንያት በማስረጃ ያልተደገፈ፣ ውሉ በክልሉ የመሬት አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 17 አግባብ ተደርጎ በሚመለከተው አካል የፀደቀ እና ሕጋዊ እውቅና ያለው በመሆኑ የሚፈርስበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የአ/ብ/ክ/መ/ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/98 ሆነ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣው የደንብ ቁጥር 51/99 የእርሻ መሬት ስጦታ የሚፈርስበት ምክንያት ያልደነገገ በመሆኑ አግባብነት ያለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2436 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ መመልከቱ ተገቢ እንደሆነ፣ በእነዚህ ድንጋጌዎች የስጦታ ውል የሚጸናው ስጦታ አድራጊው ወዶና ፈቅዶ ስጦታ በአደረገበትና የስጦታ ተቀባዩም ውሉን በተቀበለበት ቅጽበት መሆኑን የፍ/ህ/ቁ. 2436(1) በግልጽ የሚያስነብብ ስለመሆኑ ውሉ ሊፈርስ የሚችለው ስጦታ አድራጊው ስጦታው ያደረገው ጤነኛ ባልሆነ አእምሮ ያደረገው መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ ወይም ስጦታው የተደረገው በህግ ከተፈቀደው ውጭ የሆነ እንደሆነ ወይም ስጦታ የተደረገበት ነገር ግብረገብ ካልሆነ ወይም ስጦታ አድራጊው የመንፈስ መጫን ደርሶበት እንደሆነ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2437፣ 2438፣ 2439 ድንጋጌዎች እንደሚያመለክቱ፣ በተያዘው ጉዳይ እነዚህ ተግባራት መከናወናቸው አልተረጋገጠም፡፡ ይልቁንም ስጦታ አድራጊው በጤነኛ አዕምሯቸው ስጦታው ያደረጉ መሆኑን ስልጣን በአለው አካል ህጋዊነት ተረጋግጦ የስጦታ ውሉ በጽሑፍ ከተደረገ በኃላ የጸደቀ የተመዘገበ ስለመሆኑ፣ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በአንድ ግቢ ጋር የሚኖሩ መሆኑንና የአመልካች መሬት በነፃ እያረሰ የቆየ መሆኑን የምንጃር ሸንኮራ ወረዳ አካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር አጣርቶ ስጦታውን ያጸደቀ ከመሆኑም በላይ በስር ፍ/ቤትም ይህንኑ በሰው ማስረጃ የአረጋገጠ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የሰጦታ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት በማጽናት ወስኗል፡፡

www.abyssinialaw.com

አመልካች የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታው መሠረታዊ ይዘትም የአሁኑ ተጠሪ አመልካችን እየጦረና እየተንከባከበ ስለመሆኑ አላስረዳም፣ የመሬት ይዞታ ስጦታ ውል በፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መታየት የለበትም፤ አመልካች አቅመ ደካማና በሽተኛ በመሆናቸው ውሉ ፈርሶ ወደነበሩበት እንዲመለሱ መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት ይቅረብ በመባሉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ ተጠሪ በሰጠው መልስም አመልካች ካላቸው 20 ጥማድ መሬቱ 3 ብቻ እንደሰጡት፤ ስጦታው ተጠሪ ለረጅም ጊዜ ባበረከተው አገልግሎት የተሰጠው ስለመሆኑ ውሉም ገደብ እንደሌለበት፣ በሚመለከተው አካል ተጣርቶ የተመዘገበ በመሆኑ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይህ ችሎትም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ ግራ ቀኙ አደረጉት የተባለው የስጦታ ውል በማስቀረብ ተመልክቶታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ “በዚህ ጉዳይ አመልካች በተጠሪ ለመጦር የሰጡት የመሬት ስጦታ ውሉ ይፍረስልኝ ሲሉ ያቀረቡት ክስ ውሉ አይፈርስም የመባሉን አግባብነት ከክልሉ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 አንፃር” ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር የሚል ሆኖ አገኝቶታል፡፡

ከሥር የክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የስጦታ ውል ማድረጋቸው ሳይክዱ የአሁኑ ተጠሪ መሬቱ እንዳልተንከባከበ ሊያስታምማቸው አለመቻሉን በመግለጽ የስጦታ ውሉ ፈራሽ እንዲሆን መጠየቃቸውን ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የስጦታ ውሉ በሕጉ አግባብ የተደረገ በመሆኑ የሚፈርስበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች የመሬት ስጦታው ፈራሽ የሚሆንበት ምክንያት አልተገኘም በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ አድርገውታል፡፡ አመልካች የስጦታ ውሉ ለማፍረስ እንደምክንያት የጠቀሱዋቸው ነጥቦች በስጦታ ውሉ ላይ የተመዘገቡ ቅድመሁኔታዎች /Conditions/ ስለመሆናቸው የግራ ቀኙ ያደረጉት የውል ስምምነት አያሳይም፡፡ አመልካች ያደረጉት ስጦታ የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 15 እና 17 መሰረት መደረጉ በትዕዛዝ ከቀረበው ሰነድ መመልከት ይቻላል፡፡ አመልካች እንደውል ማፍረሻ የዘረዘሩዋቸው ምክንያቶች በስጦታ ውሉ ላይ ያልተመዘገቡ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመሬት ስጦታ ውል ክርክር በቀረበበት ሁኔታ ፈራሽ መሆን ያለመሆኑን ለመወሰን የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 ሆነ አዋጁን ለማስፈጸም የወጣው ደንብ ቁጥር 51/99 ግልጽ

www.abyssinialaw.com

ድንጋጌ እንደሌላቸው በውሳኔው አስፍሯል፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክርክር ጉዳዩ ከፍትሐብሔር ሕግ አንፃር መታየት የለበትም ያሉ ቢሆንም የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው እንዳሰፈረው የስጦታ ውል የሚፈርስበት ሁኔታ ካለ አግባብነት ካላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች አስተሳስሮ ማየቱ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በእርግጥ የገጠር መሬት የክርክር ይዘትና ባሕሪ እንዲሁም ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ በመለየት ረገድ ተገቢ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ ይሁንና አመልካች ያነሱዋቸው የስጦታ ውሉ ያፈርሳሉ የተባሉ ምክንያቶች የሕግና የውል መሰረት ያላቸው መሆን ያለመሆኑን መርምሮ መወሰን ተገቢ ነው፡፡

አመልካች ለተጠሪ ያደረጉት ስጦታ በነፃ ፍላጎት እና በትክክለኛ የአእምሮ ሁኔታ እንደነበር እንዲሁም ውሉ አግባብ ባለው አካል መመዝገቡን የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የስጦታ ውሉ ሕገወጥ በሆነ ምክንያት ወይም የመንፈስ መጫን እንደነበረ አመልካች አላስረዱም፡፡ አመልካች የስጦታ ውሉ በገደብ የማድረግ መብት የነበራቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2455(1) ያስገነዝበናል፡፡ ይሁንና አመልካች በስጦታ ውሉ ላይ ያስቀመጡት ቅድመሁኔታ ስለመኖሩ ውሉ አያሳይም፣ ያቀረቡዋቸው ምስክሮችም ስጦታ ውሉ በገደብ /ግዴታ/ ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን ፍሬ ነገር በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሥልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ከድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ በአንፃሩ የአሁኑ ተጠሪ ለረጅም ጊዜ ያገለገላቸው ስለመሆኑ፣ ፍርድ ቤቱ ግንዛቤ መወሰዱን መዝገቡ ያሳያል፡፡ በመሆኑም አመልካች በገዛ ፈቃዳቸው 3 ጥማድ መሬት መስጠታቸው እና ውሉም ሥልጣን ባለው አካል ተረጋግጦ መመዝገቡን ባለተካደበት አመልካች በውሉ ላይ ያልተመዘገበ ቅድመ ሁኔታዎች በመዘርዘር ውሉ ፈራሽ እንዲሆን ያቀረቡት ክርክር የሕግም ሆነ የውል መሰረት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪ ያደረጉት የእርሻ መሬት ስጦታ ለማፍረስ የሚያስችል የሕግ ድጋፍ ያለው ክርክር አለማቅረባቸው ተረድተናል፡፡

አመልካች ለተጠሪ ከሰጡት 3 ጥማድ መሬት ውጭ ሌላ የመሬት ይዞታ ያላቸው ስለመሆኑ በትዕዛዝ ቀርቦ ከታየው የአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በእርግጥ አመልካች ስጦታ ከሰጡት መሬት ውጭ ሌላ መሬት እንደሌላቸው ወይም ራሳቸው መቀለብ በማይችሉበት ደረጃ የሚኖሩ ከሆነ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2458(1) በሚያዘው አግባብ ቀለብ የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ተጠሪም ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለው በመሆኑ መብታቸውን በሕጉ አግባብ ማስከበር የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩን ችሎቱ ይገነዘባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ውሉን ለማፍረስ እንደምክንያት የጠቀሱዋቸው ቀለብ ከመጠየቅ ጋር በቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው ከመሬቱ እንክብካቤና ግብር መክፈል የተያያዙ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን 3 ጥማድ መሬት በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የወጣበት በመሆኑ የሚመለከተው አካል ከሚጠይቀው በስተቀር አመልካች ስለግብር መክፈልና መሬቱ ላይ መደረግ ያለበት እንክብካቤ የሚጠይቁበት ሥርዓትና የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በእነዚህ ሁሉ

www.abyssinialaw.com

ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ያደረጉት የስጦታ ውል የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ ማድረጋቸው ሕጉን በአግባቡ ተፈፃሚ አድርጓአል ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸማቸውን የማያሳይ በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የምንጃር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 01010775/07 በ15/05/2007፣ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 0116800 በ13/08/2007 የሰጡት ፍርድ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 030-6216 በ22/10/2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ያደረጉት የ3 ጥማድ መሬት ስጦታ ውል በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/98 ይዘትና መንፈስ የተደረገ በመሆኑ የሚፈርስበት የሕግ አግባብ የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.100395

ህዳር 29 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሡናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ አማረች ማሬ ………………. ጠበቃ ማስታወል ሀብታሙ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሜሪ ታደሰ

2. ወ/ሪት ፈጣኑ ታደሰ

3. ወ/ሪት ሮማን ነስሩ

} ጠበቃ ሀይሉ ዓይናለም ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪዎች እየኖሩበት ያለውንና በ 300 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ ቤት ለቀው እንዲያስረክቧት የመጠየቅ መብት የላትም ንብረቱን የሸጠችላትን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ከሳ ትጠይቅ በማለት የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል ፡፡
2. ከሳሽ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የመፈላም ክስ ነው ከሳሽ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 287 የግል ሀብቴ ስለመሆኑ በክፍሉ አስተዳደር የባለሀብትነትና ባለይዞታነት ማረጋገጫ ማስረጃ (ካርታ) በእጁ ይገኛል፡፡ ተከሳሾች ከቤቴ ውስጥ በጥገኝነት እንዲኖሩ ፈቅጄላቸው ሲኖሩ ቆይተዋል ፡፡ አሁን ግን ቤቴን እንዲለቁ ብጠይቃቸው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ፍርድ ቤቱ ተከሳሾች ቤቴን እንዲለቁና እንዲያስረክቡ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርባለች ፡፡

www.abyssinialaw.com

3. ተጠሪዎች በተከሳሽነት ቀርበው እኛ በከሳሽ ቤት በከሳሽ ፈቃድ በጥገኝነት የምንኖር ሰዎች አይደለም ፡፡ ተከሳሾች በእጃችን አድርገን ይዘን እየኖርንበት ያለው ቤትና ይዞታ አያታችንና እናታችን ከዛሬ አርባ ዘጠኝ ዓመት ጀምሮ ይዘውት ሲኖሩበት የነበረ ቤት ነው፡፡ተከሳሾች ከአያታችንና ከእናታችን ጋር ክስ ያቀረበበትን ቤት ይዘን ስንኖር ፣ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በአያታችን ባዶ የይዞታ ቦታ ላይ በአንድ በኩል ቤት ሠርታ ስትጠቀም ቆይታ ፣ቤቱን ለአሁን ከሳሽ ሽጣለታለች ሆኖም እኛ የምንኖርበት ቤት ወ/ሮ ሂሩት አበራሽ በእጇ አድርጋ ይዛው የማታውቅና የራሱ የሆነ ይዞታና የወሰን አጥር ያለው በመሆኑ ከሳሽ ቤቱን ለከሳሽ የሸጠችውም ሆነ ከሳሽ የእኛን ቤትና ይዞታ በማጠቃለል እንዴት ካርታና ፕላን እንዳወጡ የክፍሉ አስተዳደር እንዴት የእኛን ቤትና ይዞታ በማጠቃለል እንዴት ካርታና ፕላን እንደሰጠ ይጠየቅልን በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የክፍሉ አስተዳደር ተገቢዉን ማጣሪያ በማድረግ መግለጫ እንዲሰጥ ትዕዛዝ የቤቱ ስመ ሀብትና ከወ/ሮ እህተ ገብረማርያም ሂሩት አበራሽ ስም ሂሩት ስም የተዛወረዉ በስር ትዕዛዝ ፋይል ቁጥር 139/84 መስከረም 25 ቀን 1985 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት እንደሆነና ከዚያ በኃላ ሂሩት አበራሽ በውልና ማስረጃ ከከሳሽ ጋር በተዋዋለችው የቤት ሽያጭ ውል 1189 ሜትር ካሬ ላይ ያረፈው ቤትና ይዞታ በከሳሽ ስም እንዲዘዋወር ተደርጎ ከሳሽ የባለሀብትነት ማስረጃ የሰጠ መሆኑን ተረጋግጧል ፡፡

4. የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ወ/ሮ እህተ ገብረማሪያም ጋር ባደረጉት የቤት ሽያጭ ውል የገዙት ዋናውን ቤት የቤት ቁጥር 287 እንደሆነ የሚገልፅ ቢሆንም ገዥ ይህንን ዋናውን ቤት ተረክበውና በእጃቸው አድርገውት አያውቁም ፡፡ ወ/ሮ ሂሩት አበራሽ ገብተውና ከሻጭም ተረክበው ይኖሩ የነበሩት ሰርቪስ ቤትና በባዶ ይዞታ ላይ ራሳቸው የሠሩትን ቤት ነው ፡፡ ገዥ ገዝቻለሁ የሚሉትን የቤት ቁጥር 287 በ 300 ካሬ ሜትር ላይ 1984 ዓ.ም ጀምሮ ተረክበውና በእጃቸው አድርገውት አያውቁም ነገር ግን የሻጭን መሞት ምክንያት በማድረግ ይህንን 1984 ዓ.ም ተረክበውና ይዘው የማያውቁትን ቤት ጨምሮ በሽያጭ ውሉ መሠረት ተረክበው የሚኖሩበትን ይዞታ ላይ ያለው ቤት ስመሀብት እንዲዛወርላቸው በማድረግ የባለሀብትነት ማስረጃ ተሰጥቷቸዋል ፡፡ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በፍርድ ቤት ውሣኔ መነሻ የተሰጣቸውን የባለሀብትነት ሰነድ በማየት ፣ከሟች እህተ ገ/ማሪያም ቤቱን ከገነባች ጀምራ ተረክባና በእጇ አድርጋ የማታውቀውን የቤት ቁጥር 287 ዋናውን ቤት በ 300 ካሬ ሜትር እንዳረፈ ፣በእጇ አድርጋ ስታካብት ከኖረችው ቤት ጋር አንድ ላይ ለከሳሽ ሽጣ ቤቱና ይዞታው በተከሳሾች እጅ ባለበት ከሳሽ በሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት እጅ ባልነበረና ሆኖ በማያውቅ ቤትና ይዞታ ላይ ጭምር የባለሀብትነት ማስረጃ አውጥታለች ፡፡ ይህም ለከሳሽ ቤቱን የሸጠችው ወ/ሮ ሂሩት አበራሽ ተከሳሾች ይዘው የሚኖሩበትን ቤትና የይዞታ ቦታ በሽያጭ ውሉ መሠረት ያላስረከበቻትና ቤቱና ይዞታው

www.abyssinialaw.com

በተከሳሽ እጅ ባለበት የሰነድ ርክክብ ብቻ ያደረገች መሆኑን ስለሚያሳይ ከሳሽ ሻጭዋን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት እንጂ ተከሳሾች ቤቱን እንዲያስረክቧት መክሰስ አትችልም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል ። ይህንን ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንዲያየው አመልካች ጠይቃ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቶታል።

5. አመልካች ሚያዝያ 27 ቀን 2008 ዓ.ም አመልካች አከራካሪውን ቤት በውል ገዝታ የንብረት ባለሀብት መሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላት ይህ ከሆነ ንብረቷ እንዲለቀቅ የመክሰስ መብት የላትም በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው። የበታች ፍርድ ቤቶች ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ጭብጦችን አልመሰረቱም ተጠሪዎች ቤቱን በጥገኝነት ስለመያዛቸው ለቀበሌ ለአስተዳደር አመልክተዋል በሻጭና በከሳሽ መካከል የተደረገው ውል ተጠሪዎችን የሚመለከት አይደለም ። አመልካች የቤቱ ሻጭ በዋቢነት እንድትቀርብላት ሣትጠራ ፣ንብረቱ ላይ ያገኛቸው የባለሀብትነት መብት ለማስከበርና ለመፋለም የሚከለክላት ህግ በሌለበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክታለች ።

6. ተጠሪዎች በመጀመሪያም ሂሩት አበራሽ ከሟች አያታችን እህተ ገ/ማሪያም ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል አስመልክቶ ለአውራጃው ፍርድ ቤት ክስ ስታቀርብ ሟች የሸጠችላትን ቤት እጇ አድርጋና ተረክባ እየኖረችበት መሆኑን ገልፃለች። ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት እኛ የምንኖርበትን ቤትና በአዋሳኝ አጥር ታይቶ ያለውን 300 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ተረክባም ሆነ ይዛው አታውቅም ። እኛ በማናውቀው ሁኔታ የእኛን ቤትና ይዞታ ካርታና ፕላን ማውጣቷና ለከሳሽ መሸጧ ከሳሽን የቤቱ ባለመብት አያደርጋትም ። የባለሀብትነት ካርታና ማስረጃውም በክፍሉ አስተዳደር የታገደ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል ። አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበዋል ። ግራቀኙ የሚያከራክራቸውን ጭብጥ ለመረዳት ችሎቱ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምቶ የቃል ክርክሩ ከትራንስክራይበር ማሽን ተገልብጦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል ። የክፍሉ አስተዳደር በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የፃፈውን መግለጫ ለማየት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 135280 እንዲቀርብ በታዘዘው መሠረት መዝገቡ ቀርቦ ተያይዟል ።

7. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ግራቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩ እንደመረመርነው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ቤቱና ይዞታው እንዲለቀቅላቸው ክስ ያቀረቡት ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና ይዞታ ከሻጭ ተረክበው የያዙትን ቤትና ይዞታ በድምሩ 1139 ካሬ ሜትር ላይ ያሉትን ቤቶችና ይዞታ በብር 120,000 የካቲት 3 ቀን 1997 ገዝቼ የቤቱ ስመሀብት የተዛወረልኝ በመሆኑ ተከሳሾች (ተጠሪዎች) የግል ሀብቴና ንብረቴ የሆነውን ቤትና ይዞታ ይለቀቁልኝ በማለት ነው። ተጠሪዎች የሚከራከሩበት ከሳሽ የቤትና ይዞታውን ባለቤትነት መብት በሽያጭ

www.abyssinialaw.com

አስተላልፋልኛለች የሚሉት አበራሽ ሂሩት እኛ የያዝነውን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ለከሳሽ በሽያጭ ለማስተላለፍ መብት የላትም ፡፡ ከሳሽ እኛን ከመጠየቋ በፊት በሽያጭ ውሉ መሠረት እኛ የምንኖርበትን ቤትና 300 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ሻጭ ነፃ አድርጋ እንድታስረክባትና የሽያጭ ውሉን እንድትፈፅምላት ከምትጠይቅ በስተቀር ከሳሽ የሽያጭ ውሉ ሙሉ በሙሉ እንደተፈጸመላትና ንብረቱንም ከሻጭ እንደተረከበች አድርጋ በመቁጠር በቀጥታ እኛን ከቤት እንድንወጣ የመጠየቅና ክስ የማቅረብ መብት የላትም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተረድተናል፡፡

8. ግራቀኙ በሥር ፍርድ ቤትና በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር አመልካችና ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት የካቲት 3 ቀን 1997 ዓ.ም የተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ውል ሻጭ ሙሉ ለሙሉ ፈፅማለች ወይስ አልፈፀመችም ሻጭ በሽያጭ ውሉ መሠረት ግዴታዋን ሙሉ በሙሉ ካልፈፀመችና ውሉን በከፊል የፈፀመች መሆኑ ቢረጋገጥ ገዥዋ ሻጭ ቀሪውን ግዴታዋን እንድትፈፅምላት በሻጭ ላይ ክስ ሣታቀርብ ወይም በተከሳሽነት አጣምራ ሳትከስ የውሉ ተዋዋይ ያልሆኑ ሶስተኛ ወገኖች ላይ በቀጥታ ክስ ለማቅረብ ትችላለች ወይስ አትችልም ?የሚሉት ነጥቦች መታየት ያለባቸው ናቸው፡፡

9. ከላይ ከተገለፁት ነጥቦች አንፃር ስንመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሸጠ ሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል የገባውን ግዴታ የሚፈፅምባቸው ሁለት መሠረታዊ ኃላፊነቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ሻጭ በሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በአንዱ ወይም በሌላ መልኩ በስፍራው የሚገኙ ሰዎች የተሸጠውን የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲለቁ በማድረግ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ይዞታ ከሌሎች ሶስተኛ ወገኖችና ከሻጭ ቁጥጥርና ይዞታ ነፃ በማድረግ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ለገዥ ማስረከብ እንደሆነ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2875 እና ከፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 2274 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ለመረዳት ይቻላል ሻጭ ከዚህ በተለየ ሁኔታ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ርዕስ መዝገብ ላይ የተመዘገበና ገዢውንም ሊያስገድዱ የሚችሉ የሶስተኛ ወገኖች መብት በሰጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ካሉ ይህንኑ የሶስተኛ ወገኖች መብት ካለ ሻጭ ለገዥ ማስታወቅ ያለበት መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2880 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2881 ተደንግጓል ፡፡

10. የሻጭ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ከሶስተኛ ወገን ይዞታና ቁጥጥር ነፃ በማድረግ የማስረከብ ግዴታ ገዥ ለሻጭ ከሚሰጠው የመነቀል ዋስትና ግዴታ የተለየ ነው ፡፡ ሻጭ በንብረቱ ላይ ያሰፈሩና በንብረቱ መዝገብ የተመዘገበ መብት የሌላቸውን ሰዎች የማይንቀሳቀሰውን ንብረት እንዲለቁ በማድረግ ለሻጭ የማስረከብ ግዴታ የማይንቀሳቀስ ንብረት ውል በመፈፀም ሂደት ገዥ ሻጭ ሊያከናውነው የሚገባ የመጀመሪያ ግዴታ ሲሆን በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2882 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት ሻጭ ለገዥ የሸጠለት የማይንቀሳቀስ ንብረት የማይነቀል ስለመሆኑ የሚሰጠው ዋስትና ገዥ የገዛውን የተረከበውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሌሎች

www.abyssinialaw.com

ሰዎች ቁጥጥር ነፃ ሆኖ ከተረከበ በኃላ ንብረቱ የእኔ ነው ባይ ቢመጣ ሻጭ በዋቢነት ሊቆምለት የሚገባ መሆኑን የሚያመለክቱ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

11. የማይንቀሳቀስ ንብረት የሸጠ ሰው ንብረቱን ከሌሎች ሰዎች ቁጥጥር ይዞታ ሥር ነፃ አድርጎ ለገዢ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2875 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2274 መሠረት የማስረከብ ግዴታ ያለበት ከመሆኑ በተጨማሪ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ባለሀብትነት ለማስተላለፍ የሚችሉ አስፈላጊ ሰነዶች ለገዢ የማስረከብና የማይንቀሳቀሰዉን ንብረት የማይነካ የባለሀብትነት መብት ለገዥ ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆነ ተግባራትን የመፈጸም ግዴታ መሆኑ በፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 2875 በፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 2879 ንሁስ አንቀጽ 1 እና የፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 2281 ድንጋጌዎችን በጣምራ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

12. ከላይ በዝርዝር ካየናቸው የህግ ድንጋጌዎች አንጻር ሲታይ 1139 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ላይ ያረፈውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሙሉ በሙሉ ለአመልካች የሸጠችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት፣በሽያጭ ውሉ መሰረት የማይንቀሳቀስውን ንብረትና ይዞታውን ከሌሎች ሰዎች ቁጥጥርና ይዞታ ስር በማስለቀቅ የማይንቀሳቀስ ንብረትና ይዞታውን በፍትሃብሄር ሕግ ቁጥር 2875 በፍትሃብሄር ሕግ ቁጥር 2274 እና በፍትሃብሄር ሕግ ቁጥር 2888 መሰረት ለገዥ(ለአመልካች)የመፈጸም ግዴታውን የተወጣችው ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በከፊል ነው፡፡ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ከተጠሪዎች አውራሽ ንብረቱን ገዛሁ ከምትልበት 1984 ዓ.ም ጀምሮ ተረክባውና በእጇ አድርጋው የማይታወቅ መሆኑና፣ቤቱን ለአመልካች ከሸጠችላት በኂላ ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና ይዞታ፣ ተጠሪዎች በህግ አግባብ እንዲለቁ በማድረግ ለአመልካች ያላስረከበችበት አመልካችም በሽያጭ ውሉ የተገለጸውን ቤትና ይዞታ ሙሉ በሙሉ ሳይሆን፣ሻጭ(አበራሽ ሂሩት)ይዛው የነበረውን ቤትና ይዞታ ብቻ ከሻጭ የተረከበች መሆኑን ተረድተናል፡፡

13. ገዥ ሻጭ በሽያጭ ውሉ የገለጸችውን የማይንቀሳቀስ ንብረትና ይዞታ፣ ተጠሪዎች የሚኖሩበት ቤትና ይዞታ ሳይጨምር በሻጭ እጅና ይዞታ ስር ያለውን ቤትና ይዞታ የተረከበች ቢሆንም፣ሻጭ የሰጠቻትን ሰነድ በመጠቀም በሽያጭ ውሉ ላይ የተመለከተውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለመብት መሆኗን የሚሳይ ማስረጃ ከክፍሉ አስተዳደር ተሰጥቷታል፡፡ይህም ገዥዋ(አመልካች)ከሌሎች ሰዎች ይዞታና ቁጥጥር እንደዚሁም የመብት ጥያቄ ነጻ ሆኖ ከሽያጭ ያልተረከበችውን ተጠሪዎች የሚኖሩበት ቤትና ይዞታ ባለመብት መሆኗን የሚያረጋግጥ የባለህብትነት ማስረጃ የተሰጣት መሆኑን ያሳያል፡፡አመልካች የቤቱ ባለሃብትነት መብት በሽያጭ ውል ከወ/ሮ አበራሽ ሂሩት የተላለፈላት መሆኑን የሚያሳይ የሽያጭ ውል ሰነድና በሽያጭ ውሉ መሰረት በማይንቀሳቀሰው ንብረት ባለሀብትነት

www.abyssinialaw.com

የተዛወረላት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ በማያያዝ በፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 1206 መሰረት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም አላት፡፡ነገር ግን አመልካች ባቀረበችው የክስ መነሻ አከራካሪ ሆኖ የተገኘው ጭብጥ፤(ሀ) ቤቱን ንብረቴ ነው ካለች ለአመልካች የሸጠችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት አከራካሪውንና ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና ይዞታ ባለሃብትነት መብት ለአመልካች የማስተላለፍ እርግጠኛ የሆነ የባለሀብትነት መብት በንብረቱ ላይ አላት ወይስ የላትም?

(ለ)ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ተጠሪዎች የሚኖርበትን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ጨምራ የባለሀብትነትን ማስረጃና ካርታ ያሰራችው በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም?አመልካችስ 1139 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያለው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትና ባለይዞታ መሆኗን የሚያረጋግጥ የባለህብትነት ማስረጃና ካርታ የተሰጣት በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም?(ሐ)ተጠሪዎች እየኖሩበት ያለውን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ቦታ ለአመልካች የመልቀቅና የማስረከብ ግዴታ አለባቸው ወይስ የለባቸውም?የሚሉት ለአመልካች 1139 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ላይ ያለውን የማይንቀሳቀስ ንብረት በሽያጭ ውል አስተላልፋለች የተባለችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በክርክሩ ተሳታፊ ሳትሆን ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚችሉ ጭብጦች አይደሉም፡፡

14. የስር ፍርድ ቤት አመልካች የቤቱ ሻጭ የሆነችውን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ከሚከሱ በስተቀር በቀጥታ ተጠሪዎች ቤቱን እንዲለቁላት ክስ ማቅረብ አትችልም በማለት የሰጠው ውሳኔ ሻጭ በሽያጭ ያስተላለፈው ንብረት ላይ ያለውን መብትና ጥቅም ለማስከበር ገዥው ከውል የመነጨ መብት ያለው መሆኑን ያላገናዘበና የፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 1195 የፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 1206 እና የፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 33(2) ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ ስህተት ያለበት ነው፡፡ነገር ግን የበታች ፍርድ ቤቶች ቤቱን ለአመልካች የሸጠችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በክርክሩ ተከሳሽ መሆን አለባት በማለት የደረሱበት ድምዳሜ የፍትሃብሄር ህግ አንቀጽ 2875፣ አንቀጽ 2274፣አንቀጽ 2888 እና የፍትሃብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በጉዳዩ ተከሳሽ መሆን አለባት በማለት የደረሱበት መደምደሚያ በውጤት ደረጃ የሚነቅፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

15. የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የቤቱን ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት መክሰስ አለባት ካሉ በኋላ፣ይህ ውሳኔአቸው የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት ሳይመዝኑ ተጠሪዎችን ከክስ ማሰናበታቸው አግባብነት ያላቸውን የስነ-ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም አመልካች ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በሽያጭ ውሉ መሰረት ተጠሪዎች የያዙትን ቤት አስለቅቃ ታስረክበኝ የሚል ክስ ስታቀርብ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ በማናቸውም ሁኔታ የሚገኙ ሰዎችን በተከሳሽነት አጣምራ መክሰስ እንዳለባት የፍትሃብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 36

www.abyssinialaw.com

ንዑስ አንቀጽ 4 አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ይደነግጋል፡፡ይህም አመልካች ሻጭዋን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩትን በምትከስበት ጉዳይ ተጠሪዎች የግድ በተከሳሽነት እንዲሳተፉ ማድረግ የሚገባ መሆኑ በህግ የተደነገገ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ዳኝነት ከፍላ ያቀረበችውን ክስ የቤቱ ሻጭ በጉዳዩ የመጀመሪያ ተከሳሽ መሆን አለባት በሚል ምክንያት ዘግቶ አመልካችን ከሚያሰናብት፣በጉዳዩ የቤቱ ሻጭ በክርክሩ በተከሳሽነት ተሳታፊ እንድትሆን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ትዕዛዝ መስጠት በዚህ ፍርድ አንቀጽ ተራ ቁጥር 13 በተመለከቱና በሌሎች ጭብጦች ላይ አመልካች (የቤቱ ገዥ)፣ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ሻጭና በአከራካሪው ቤትና ይዞታ ይዘው የሚኖሩት ተጠሪዎች የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ መወሰን ሲገባው፣አመልካች ተጠሪዎችን የመክሰስ መብት የላትም በማለት መዝገቡን መዝጋቱና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ማጽናቱ ከላይ በዝርዝር የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎችና የዳኝነት አካሄድ ስርዓት ያልተከተለና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 66605 የካቲት 29 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 135280 መጋቢት 2 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሸሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በተከሳሽነት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በመጨመር፣በዚህ ፍርድ በተራ ቁጥር 13 የተመለከቱትንና ሌሎች አከራካሪ ጭብጦች ላይ ግራ ቀኙ የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ በማሰማትና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 343(1) መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

www.abyssinialaw.com

# የዳኝነት ስልጣን

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 117819

መጋቢት 15 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- በወላይታ ዞን የበሌ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ዓ/ሕግ ኤርገና ቆልቻ - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ታደለች ዳባራ - ተወካይ ታደለ ወ/ሚካኤል - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ በዉል ያገኘሁትን የከተማ ይዞታ እንዲያስረክበኝ በማለት የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ክርክር ነዉ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡ የአሁን አመልካች የሥር 1ኛ ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ በመሆን ሲከራከሩ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የአሁን ተጠሪ በኪንዶ ኮይሻ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ 1ኛ ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ በበሌ ቀበሌ 02 በግብርና ሰፈር በኮድ ቁ.0443፣ 300 ካ.ሜ ይዞታ ለጨረታ አዉጥቶ እኔ ተወዳድሬ አሸንፌ ተገቢዉን ክፍያ ሁሉ ፈጽሜ ዉል ተዋዉዬ እያለሁን፣ 2ኛ ተከሳሽ ተወዳድሮ ያሸነፈዉ ኮድ 0024፣ 200 ካ.ሜ ይዞታ ሁኖ እያለ የመጀመሪያዉን ዉል አስቀርድዶ በቦታዉ ላይ የተለጠፈዉን ታፔላ በመቀያየር ሌላ ክፍያ በመፈጸም ለ2ኛ ተከሳሽ አሳልፎ የሰጠ በመሆኑ፣ 1ኛ ተከሳሽ ይህን ይዞታ ከ2ኛ ተከሳሽ አስለቅቆ ለከሳሽ እንዲያስረክበኝ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ መልስ ከሳሽ በተወዳደረችበት ቦታ ላይ ያቀረበችዉን የጨረታ ሰነድ በሰም ያልታሸገ በመሆኑና ሕጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ አሰጣጥን ያልተከለተለ ስለመሆኑ በመረጋገጡ በ1ኛ ተከሳሽ ማኔጅመንት በሕግ አግባብ የከሳሽ ዉል እንዲመክን ተደርጓል፤ ከሳሽ ይህን ክስ ያቀረበችዉ ከቅን ልቦና በመሆኑ ዉድቅ እንዲደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር 2ኛ ተከሳሽ /አቶ ማቴዎስ ማያ/ ባቀረበዉ መልስ ይህን ይዞታ በሕጋዊ መንገድ ተወዳድሬ ያገኘሁት በመሆኑ የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በኂላ ፍ/ቤቱ ክርክሩን በማጣራት በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን አመልካችን ክርክር በመቀበል የአሁን ተጠሪን ክስ ዉድቅ በማድረግ፣ የአሁን ተጠሪ ከጨረታዉ ጋር በተያያዘ የከፈሉት ገንዘብ ብር 3600 /ሶስት ሺህ ስድስት መቶ ብር/ የአሁን አመልካች እንዲከፍላቸዉ ወስኗል፡፡ የአሁን

www.abyssinialaw.com

ተጠሪ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በሰጠዉ ዉሳኔ መደበኛዉ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለዉም በማለት የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኙን ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ጉዳዩ በአስተዳደር በኩል ታይቶ እልባት እንዲሰጣት አቤቱታዋን በየደረጃዉ ላሉት የመንግስት መዋቅር አቅርበዉ ምላሽ በማጣታቸዉ ይህን ክስ ለፍ/ቤት ያቀረቡ በመሆኑ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለዉ፤ የሥር 2ኛ ተከሳሽ ተወዳድረዉ ያሸነፉት በ200 ካ.ሜ ሲሆን፣ ከሳሽ በ300 ካ.ሜ ላይ በጨረታ ተወዳድረዉ አሸነፊዉ ዉልም ተዋዉለዉ ክፍያ ከፈጸሙ በኋላ የአሁን አመልካች በሰም የታሸገ ኤንቨሎፕ አላቀረብሽም በሚል ምክንያት ዉሉን ዉድቅ ማድረጉ አግባብነት የለዉም፣ በዉሉ በተጠቀሰዉ መሰረት በጨረታ ያሸነፈችዉን ይዞታ 300 ካ.ሜ ለከሳሽ እንዲያስረክባት በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች አሁንም ይህን ዉሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታዉን ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለዉም በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ነሐሴ 20 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ አራት ገጽ አቤቱታ ተጠሪዋ ያሰነፈችበትን ዉጤት እንዲሰረዝ ዉሳኔ የሰጠዉ የወረዳዉ ማኔጅመንት ኮሚቴ በመሆኑ የሊዝ አዋጁን ለማስፈጸም በወጣዉ መመሪያ መሰረት ቅሬታዋን ለሚመለከተዉ አስተዳደር ማቅረብ ነበራባት እንጂ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለዉም፡፡ የአሁን ተጠሪ በጨረታ ሂደት አለአግባብ መብቴ ተነክቷል የምትል ከሆነ የሊዝ ኮሚቴ ወይም የመሬት ማኔጅመንት ኮሚቴ ቅሬታዋን አቅርባ በሚሰጠዉ ዉሳኔ ካልተስማሙ ይግባኝ ለዞን ይግባኝ ሰሚ ወይም ለክልሉ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ እንዳለባቸዉ በሊዝ አዋጅ ቁ.721/2004 መሰረት ክልሉ ባወጣዉ መመሪያ ቁ/01/2005 አንቀጽ 74 መሰረት መሆን አለበት፡፡ የሥር ፍ/ቤት በዚህ መቃወሚያ መሰረት የቀረበዉን ክስ ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ አይደለም፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች የተጠሪዋን መሬት ለሌላ ግለሰብ አሣልፎ ለመስጠት ነዉ ዉጤቱን የሰረዘዉ፣ የተወዳደሩበትን ታፔላ ቀያይሯል የሚል ሲሆን ይህ ስለመሆኑ በተጨባጭ ማስረጃ ያጣራዉ ነገር የለም ወይም ወደ ስር ፍ/ቤት መልሶት እንዲጣራ ያደረገዉ ነገር በሌለበት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ ስለዚህ ይህን ጉዳይ የመደበኛዉ ፍ/ቤት ለማየት ስልጣን ስለሌለዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሻርልን፣ የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በማየት የሚጣራ ጉዳይ አለ በማለት አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት በ10/02/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሁለት ገጽ መልስ

www.abyssinialaw.com

አቅርበዋል፡፡ የመልሱም ይዘት፡ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለዉ በመሆኑ እንዲጸናልኝ ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብት እንዲጠበቅልኝ ወይም በቁርጥ እንዲወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ፣ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉን ጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች በበሌ ቀበሌ 02 በግብርና ሰፈር በኮድ ቁ.0443፣ 300 ካ.ሜ ይዞታ ለጨረታ ባቀረበዉ መሰረት የአሁን ተጠሪ ተወዳድረዉ አሸንፈዉ ተገቢዉን ክፍያ ፈጽመዉ ዉል ያደረጉ መሆኑን ግራ ቀኙ የሚካካዱት ጉዳይ አይደለም፡፡ በሌላ በኩልም የአመልካች መ/ቤት በዚህ አግባብ ተጠሪ ጨረታዉን አሸንፈዉ ተገቢዉን ሁሉ ፈጽመዉ ዉል ከተዋዋሉ በኋላ ለጨረታዉ ሲወዳደሩ በሰም የታሸገ ኤንቨሎፕ አላቀረቡም የሚል ምክንያት በማንሳት በኮሚቴ በማየት ዉሉን የሰረዘ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ ባቀረቡት ክስ አመልካች ይህን ዉል ያለአግባብ የሰረዘ በመሆኑ በዉሉ ላይ በተመለከተዉ መሰረት ይዞታዉን እንዲያስረክበኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁን አመልካች ይህ ጉዳይ በአስተዳደር አካል መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ እንጂ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በዚህ አግባብ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማየት መደበኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ የማየት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም የሚለዉን ጭብጥ መመልከቱ ተገቢ ነዉ፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይ የአሁን አመልካች የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004 እንዲሁም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ መሰረት ለክርክር ምክንያት የሆነዉን ይዞታ ለጨረታ አቅርቦ፣ የአሁን ተጠሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 /1-6/ መሰረት ተወዳድረዉ የጨረታ ሂደቱን አልፈዉ አሸንፈዉ በአንቀጽ 16 መሰረት የሊዝ ዉል የፈጸሙ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የአሁን ተጠሪ በሕጉ የተመለከተዉን ሂደት ሁሉ አልፈዉ ዉል ከፈጸሙ በኋላ አመልካች ወደ ኋላ በመመለስ ለዉድድር ሲቀርቡ ተጠሪ በሰም የታሸገ ፖስታ ወይም ኤንቨሎፕ ባለማቅረባቸዉ የጨረታዉን ዉጤት የሆነዉን ዉል መሰረዙን ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን የአመልካች መ/ቤት ተጠሪዋ በጨረታዉ ለመሳተፍ የሚያስፈልገዉን መስፈርቶች ሁሉ ያሟሉ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ በጨረታዉ እንዲሳተፉ ያደረጋቸዉ መሆኑ የሚያከራክር አይሆንም፡፡ የአሁን ተጠሪ አስፈላጊዉን መስፈርት ባያሟሉ ኖሩ በጨረታዉ ላይ እንዲሳተፉ ያደረጋል ተብሎ አይገመትም፡፡ ስለዚህ የአሁን አመልካች ተጠሪዋ በአግባቡ የጨረታ ሂደቱን አልፈዉ ዉል ከተዋዋሉ በኋላ በሰም የታሸገ ኤንቨሎፕ አላቀረቡም በማለት ይህን ዉል መሰረዙ ከጨረታ ሂደት

www.abyssinialaw.com

አልፎ አስገዳጅ የዉል ግዴታ በተገባበት ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ መታየት ያለበት ከላይ የተመለከተዉ የሕግ ድንጋጌ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የዉል ሕግ ድንጋጌ እንደአግባብነቱ ተፈጻሚነት የሚኖረዉ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በግራ ቀኙ መካከል በሕግ ፊት የሚጸና መብት ግዴታ የሚፈጥር ዉል እስከተደረገ ድረስ ይህን ዉል የማፍረሱ ጉዳይ በአመልካች መ/ቤት ብቻ የሚተዉ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ ማለት በግራ ቀኙ መካከል ይህ ዉል በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1731 መሰረት እንደሕግ የሚቆጠር ነዉ፡፡ ግራ ቀኙ በዚህ ዉል መሰረት መብትና ግዴታቸዉን መወጣት እንደሚጠበቅባቸዉ ግልጽ ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ይህ ዉል የሚፈርስባቸዉ ሕጋዊ ምክንቶች አሉ ወይስ የሉም የሚለዉን አይቶ ለመወሰን ለተዋዋይ ወገኖች ብቻ የሚተዉ ጉዳይ ሳይሆን ገለልተኛ በሆነ ፍ/ቤት ታይቶ መዳኘት ያለበት ጉዳይ ሁኖ ይታያል፡፡ ይህን ዉል ለማፍረስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1808 ሥር የተመለከቱት ዉልን ለማፍረስ ተገቢ የሆኑ ምክንያቶች መሟላት ይጠበቅበታል፡፡ ይህ በመሆኑ እነዚህ ምክንያቶች ወይም ሁኔታዎች መሟላታቸዉን አለማሟላታቸዉን በመደበኛ ፍ/ቤት ታይቶ እልባት ሊሰጥበት የሚገባ ጉዳይ ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ ጉዳይ በህጋዊ መንገድ የተቋቋመዉን ዉል ከማፍረስ ጋር የሚመለከት በመሆኑ መደበኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ የማያይበት ምክንያት የለም፡፡ የአሁን አመልካች መ/ቤት ማናቸዉንም ምክንያት በመፈለግ በፈለገ ጊዜ እያነሳ ይህን በሕግ አግባብ የተቋቋመዉን ዉል ለመሰረዝ የሚያስችለዉ የሕግ አግባብ የለም፡፡

የአሁን አመልካች ይህን ዉል ለመሰረዝ የጠቀሰዉ ምክንያት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1808 /2/ ሥር የሚወድቅ ሁኖ ስለማይታይ ዉሉን ለመሰረዝ በቂ ምክንያት ነዉ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች መደበኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን አላቸዉ በማለት የአሁን አመልካች ያለ በቂ ምክንያት ዉሉን መሰረዙ ተቀባይነት የለዉም አመልካች በዉሉ ላይ የተጠቀሰዉን ይዞታ ለአሁን ተጠሪ እንዲያስረክብ በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.06872 በ13/09/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 07874 በ29/11/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለዉ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. በ29/12/2007 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.114622

ግንቦት 9 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ አወል አማን } ተወካይ ሙስጠፋ አዋል ቀርበዋል
2. ወ/ሮ ሩቅያ ሙሳ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ አሳለፈች አንዳግቤ } ተወካይ አቶ ግርማ ጥላሁን ቀርበዋል
2. አቶ አስራት ግርማ
3. የአዳማ ከተማ የመሬት ልማት እና ማናጅመንት ኤጀንሲ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ክስ መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡ የአሁን አመልካቾች /የሥር ጣልቃ ገቦች/፣ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች /የሥር ከሳሾች/፣ የአሁን 3ኛ ተጠሪ /የሥር ተከሳሽ/ ሆኖ ሲከራከሩ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ለእያንዳንዳችን 200 ካ.ሜ ቦታ እንዲሰጠን ተወስኖ በዚሁ መሰረት ካርታ የተሰጠን ቢሆንም 1ኛ ከሳሽ በእጄ የደረሰዉ ቦታ 90 ካ.ሜ ሲሆን፣ 2ኛ ከሳሽ ደግሞ በእጄ የገባዉ 110 ካ.ሜ ብቻ በመሆኑ ተከሳሽ እና ማዘጋጃ ቤት የተቀነሰዉን ቀሪ ቦታ አሟልቶ እንዲያስረክበን በማለት ከሷል፡፡ የሥር ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን በማየት በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሾች ለእያንዳንዳቸዉ 200 ካ.ሜ እንዲሰጣቸዉ ተወስኖ ካርታ ተሰጥቷቸዉ መሬት ቢሰጣቸዉም በካርታ ላይ የተጠቀሰዉ ሙሉ ይዞታ በእጃቸዉ ስላልገባ ተከሳሽ እና ማዘጋጃ ቤት የተቀነሰዉን ቀሪ ቦታ አሟልቶ እንዲያስረክባቸዉ በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት ባቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ ከሳሾች እና ተከሳሽ

www.abyssinialaw.com

የተስማሙበት ይዞታ ጣልቃ ገቦች ከኃ/ስላሴ ጊዜ ጀምሮ በገጠር መሬት ይዘን የቤት ቁጥር 188 እና ግምቱ 500,000.00 የሚያወጣ ቤት ሰርተንበት እየተጠቀምን ያለን በመሆኑ፣ ተከሳሽ ንብረታችንን ለከሳሾች እንዳያስክረብብን፣ ካልሆነ ካሳ የመጠየቅ መብታችን እንዲጠበቅልን በማለት አመልክተዋል፡፡ የሥር ከሳሾች እና የሥር ተከሳሽ ለየብቻ ባቀረቡት መልስ ከሳሾች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም በማለት ወስኗል፡፡

የወረዳዉ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የሰዉ ምስክሮች በመስማት በሰጠዉ ዉሳኔ የከተማዉ አስተዳደር በጣልቃ ገቦች ይዞታ ላይ ለከሳሾች ካርታ ሰርቶላቸዉ እንደሆነ ወይም መሬቱን በሕጋዊ መንገድ ወስዶ እንደሆነ ከመሬት ጉዳይ ጋር በተያያዘ በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 26፣ 29፣ 30 በደንብ ቁጥር 155/2005 እና የኦሮሚያ ከተማ በሊዝ ለማስተዳደር የወጣ መመሪያ ቁጥር 9/2005 መሰረት በአስተዳደራዊ መንገድ እዛዉ የሚታይ እንጂ በፍ/ቤት የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም፣ የካሳ ጥያቄም ከሆነ መጠኑን ለይተዉ ለብቻ ክስ ማቅረብ ስለሚቻል፣ ጣልቃ ገቦች ያቀረቡት ክስ የክስ ምክንያት የለዉም በማለት የቀረበዉን የመቃወሚያ አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የቀድሞዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካቾች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ከሳሾች የተጓደለዉ ይዞታ ተሟልቶ እንዲሰጣቸዉ በማለት ያቀረቡት ክስም ሆነ የሥር ጣልቃ ገቦች ያቀረቡት አቤቱታ ፍ/ቤት የማየት ስልጣን የለዉም በማለት ለሥር ፍ/ቤት ቀድሞ እና በኋላ የተሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የሥር ከሳሾች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ፍ/ቤት የሥር ከሳሾች ያቀረቡትን ጥያቄ ለማየት ስልጣን የለዉም የሚያስብል ነገር የለም፣ የወረዳዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ ጸንቷል፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ተሽሯል በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ጣልቃ ገቦች ይህን ዉሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸዉ ተቀባይነት ሳያገኝ ዉድቅ ተደርጎ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካቾች በ11/10/2007 ዓ.ም በተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የጎደለዉን መሬት አሟልቶ 3ኛ ተጠሪ እንዲሰጣቸዉ ያቀረቡት ዳኝነት ፍ/ቤቶች በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 እና የኦሮሚያ ክልል የከተማ መሬትን አስተዳደር ያወጣ ሊዝ አዋጅ ቁጥር 55/2006 ለመወሰን ያልተፈቀደላቸዉ ሆኖ ሳለ ያለስልጣን የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ የአሁን አመልካቾች በዋናነት ያቀረብነዉ የዳኝነት ጥያቄ ለረጅም ዓመታት በእጃችን የቆየዉን ይዞታንና ንብረትን 3ኛ ተጠሪ ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ማስረከብ አይገባዉም እንዲሁም በአማራጭ ማስረከብ አለበት የሚባል ከሆነ ካሣ የመጠየቅ መብታችን እንዲጠበቅልን በማለት አመልክተን እያለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጥያቄያችን የመሬት ካሳ ጥያቄ ስለሆነ በፍ/ቤት የሚታይ አይደለም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት

www.abyssinialaw.com

የተፈጸመበት ነዉ፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ተሽሮልን፣ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በማየት የሚጣራ ነጥብ አለ በማለት አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ በታዘዘዉ መሰረት የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ሐምሌ 16 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ መልስ እና የአሁን 3ኛ ተጠሪ በ15/01/2007 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ሶስት ገጽ አቅርበዉ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ የመልሱም ይዘት፡ የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለዉ ትክክለኛ ዉሳኔ ስለሆነ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካቾችም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ያላቸዉን የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ፣ እንዲሁም መደበኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ የማየት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉን እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነዉ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ሲሆን፣ የዳኝነት ጥያቄአቸዉም በካርታ ላይ ተጠቅሶ ለእያንዳንዳችን የተሰጠዉ ቦታ 200 ካ.ሜ ቢሆንም በእጃችን የገባዉ የቦታ መጠን ከዚህ የሚያንስ በመሆኑ የጎደለዉ ይዞታ ተሟልቶ እንዲሰጠን በማለት 3ኛ ተጠሪን የከሰሱ ሲሆን፣ የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን የዳኝነት ጥያቄ መሰረት በማድረግ ዉሳኔ የሰጠ በመሆኑ፣ የአሁን አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይዞታችን ማስረከብ የለበትም ካልሆነ ካሳ ሊሰጥን ይገባል የሚል መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት ጥየቄ የጎደለዉ ይዞታ ተሟልቶ እንዲሰጥን የሚል ሲሆን፣ የአሁን አመልካቾች ደግሞ ያለምንም ምትክ ቦታ ወይም ካሳ ይዞታችን ሊወሰድብን አይገባም የሚል መቃወሚያ ማቅረባቸዉን ማየት ይቻላል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር የሚያተኩረዉ በአዳማ ከተማ አስተዳደር ሥር ያለውን የከተማ ቦታን የሚመለከት ነዉ፡፡ የአዳማ ከተማ አስተዳደር በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ዉስጥ የሚገኝ እንደመሆኑ መጠን ይህን የከተማ ቦታ የሚያስተዳድረዉ የከተማ መሬት የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004፣ ይህን አዋጅ መሰረት በማድረግ ክልሉ ያወጠዉ የከተማ መሬትን በሊዝ ለማስተዳደር የወጣ ደንብ ቁጥር 155/2005 እና የከተማ መሬትን በሊዝ ለማስተዳደር የወጣ መመሪያ ቁጥር 9/2005 በተመለከቱ መርሆዎች መሆን እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከከተማ ቦታ ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ጥያቄዎች እንዲሁም ቦታን ከማስለቀቅ እና ተያያዥነት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚስተናገዱት በዚህ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ መሆን ይገባል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ አግባብነት ያላቸዉ የአዋጁ ድንጋጌዎች አንቀጽ 26፣ 27፣ 28፣ 29፣ እና 30 ሲሆን፣ የከተማ ቦታን ከማስለቀቅና ምትክ ቦታ እና ካሳን ከመክፈል አንጻር ጉዳዩ የሚታይ መጀመሪያ በሕግ አግባብ በከተማዉ አስተዳደር

የተዋቀረዉ አካል እንደሆነ ያመለክታል፡፡ የደንብ 155/2005 አንቀጽ 26፣ 55 እና 56 እንዲሁም የመመሪያ አንቀጽ 33 እና 36 ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት እንዳለዉ ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ አግባብ ስልጣን የተሰጠዉ የአስተዳደር አካል የከተማ ቦታ ጋር በተያያዘ ለሚነሱ የመብት ጥያቄዎች፣ ይዞታን ለማስለቀቅ ትዕዛዝ ከመስጠት፣ ምትክ ቦታ እና የካሳ መጠን ወስኖ ከማሳወቅ አንጻር ስልጣን የተሰጠዉ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በዚህ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለዉ አካል አቤቱታዉን እዛዉ በሕግ አግባብ በተዋቀረዉ አካል ዘንድ ማቅረብ እንዳለበት ነዉ፡፡ ይህ አካል በአቤቱታዉ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለዉ አካል ይግባኙን በከተማ አስተዳደር ደረጃ በተዋቀረዉ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ መብት እንዳለዉ ከአዋጁ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ አካሄድ ጉባኤዉ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ካሳን በተመለከተ ካልሆነ በስተቀር ሌሎች ምትክ ቦታን ጨምሮ በሌሎች በሕግም ሆነ በፍሬ ነገር ክርክሮች ላይ ጉባኤዉ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ የካሳ ጥያቄም ቢሆን በይግባኝ ለመደበኛ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊቀርብ እንደሚገባ እንጂ ቀጥታ ክስ ሊቀርብ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡ ይህ የሚሆነዉ ግን እነዚህ አካላት በሕጉ አግባብ ተዋቅረዉ ከከተማ መሬት ጋር በተያያዘ የሚነሱትን ክርክሮች የሚያስተናግዱበት ሥርዓት የተዘረጋ እንደሆነ ነዉ፡፡ የአሁን አመልካቾችም ሆኑ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ይህ አስተዳደራዊ አካል በህጉ አግባብ ስላልተዋቀረ በመደበኛ ፍ/ቤት ክስ ማቅረባቸዉን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ አስደግፈዉ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ስለዚህ ከዚህ አንጻር ሲታይ በግራ ቀኙ መካከል ያለዉን የጎደለዉ ይዞታ እንዲሟላልን የሚል የዳኝነት ጥያቄ፣ ምትክ ቦታ እና ካሳ ሳይከፈለን ከይዞታችን ልንነቀል እና ማስረከብ የለብንም የሚለዉ የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ በቀጥታ ክስ ለመደበኛ ፍ/ቤት ሊቀርብ የሚገባ ጉዳይ አይደለም፡፡ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት ስልጣን ላለዉ የአስተዳደር አካል የሚቀርብ ጉዳይ ነዉ፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ አግባብ በማየት ከግራ ቀኙ የቀረበዉን የዳኝነት ጥያቄዎች ለመወሰን ስልጣን ስለሌላቸዉ የቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.244 /2፣ ሀ/ እና 245 /2/ መሰረት ዉድቅ ማድረግ ሲገባቸዉ፣ ጥያቄዉን በመቀበል የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለዉ በመሆኑ የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.68317 በ06/12/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.200569 በ13/08/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.204835 በ25/09/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.19245 በ04/03/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
3. መደበኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ በቀጥታ ክስ ተቀብሎ አከራክሮ ዉሳኔ ለመስጠት ስልጣን የለዉም ብለናል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤት ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 110901

ግንቦት 24 ቀን 2008ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሹ ሺርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ድጋፌ ታደሰ - ጠበቃ ሞገስ ናደው ቀርቧል

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ፍቅርተ ታደሰ ጠበቃ ክፍ አማከለው ቀርቧል

2. አቶ ወንድዬ ታደሰ - ቀርቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለክርክር መነሻ የሆነው የአሁኑ አመልካች የውርስ ሃብት ይጠራልኝ ሲሉ ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መናገሻ ምድብ ችሎት ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ፡- አባታቸው አቶ ታደሰ አበበ ሐምሌ 11 ቀን 1974 ዓ.ም ከዚህ አለም የተለዩ ሲሆን ወራሽነታቸው የካቲት 11 ቀን 1975 ዓ.ም በመ/ቁ. 830/75 ያረጋገጡ መሆናቸው፣ ተጠሪዎች የወላጅ አባታቸው በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ውስጥ የሚገኘውን የቤት ቁጥር 092 የሆነውን መኖሪያ ቤት ይዘው ስለሚገኙ የውርስ ሃብት ይጣራልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ የቀረበውን አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የውርስ ሃብት ይጣራልኝ ጥያቄ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000/1/2/ መሰረት የውርስ ሃብቱ በተጠሪዎች መያዙን ካወቁ ሶስት አመት ካለፈ በኋላ የቀረበ ስለሆነ በይርጋ ይታገዳል፡፡ በፍሬ ጉዳዩ ላይም የውርስ ሐብቱ ተመዝግቦ የሚገኘው በተጠሪዎች ስም እንጂ በአባታችን አይደለም፡፡ በዚህ ንብረት ላይ ከፍተኛ ንብረት አፍስሰውበት ይዘው እንደሚገኙ በመግለፅ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግላቸው መከላከያ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአሁን 2ኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ በመፍቀድ ክርክር ካከሄደ በኋላ አመልካች አባታቸው ከሞቱ በኋላ በ1975 ዓ.ም ወራሽነታቸው ያረጋገጡት በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000/1/ የተጠቀሰው የ3 ዓመት ይርጋ ጊዜ ሳያልፍ ስለሆነ የቀረበው መቃወሚያ በብይን ውድቅ በማድረግ፤ የውርስ አጣሪ በመሾም ከዚያም በውርስ አጣሪው የቀረበውን ሪፖርቱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ስላልሆነ በማለት ተቀብሎ መዝግቦታል፡፡

ይህ ውሳኔ በመቃወም የአሁኑ ተጠሪዎች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤትም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000/1/ መሰረት በ3 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት የስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይንና ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታው ቢያቀርብም በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስሕተት የተፈፀመበት ስለሆነ እንዲታረም በማለት የቀረበ ነው፡፡ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ያቀረብኩት አቤቱታ ወራሽነቴን አረጋግጫለሁ በማናቸውም ጊዜ ውርስ ሀብቱን ለመካፈል የፍ/ብ/ህ/ቁ.1060 እስከ 1113 ባለው ህግ ስር የተሸፈነ ስለሆነ በይርጋ የማይተገድ እያለ ይታገዳል ተብሎ የተሰጠ ውሳኔ የተፈፀመው መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማፅናት እንዲወሰንለት አቤቱታውን አቅርበዋል፡፡

የቀረበው የሰበር አቤቱታ በመመርመር አመልካች በወቅቱ ወራሽነቱን ማረጋገጡ አልተካደም ተጠሪዎችም የውርስ ንብረቱን በስማቸው በማዞር ካርታ ያሰሩት በ2004 ዓ.ም ከመሆኑ አንፃር የአመልካችን የውርስ ንብረት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው የመባሉን አግባብነትና የይርጋ ጊዜው መቆጠር ያለበት ተጠሪዎች ንብረቱን በሰማቸው አድርገው ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ ነው ወይስ ሟች ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ነው የሚለውን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረትም ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ 2 ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በበኩሉ ጥር 26 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች ያቀረብኩት አቤቱታ ወራሽነቴን አረጋግጫለሁ

www.abyssinialaw.com

በማናቸውም ጊዜ የውርስ ሀብቱን ለመካፈል የፍ/ብ/ህ/ቁ.1060 እስከ 1113 ባለው ህግ ስር የተሸፈነ ስለሆነ በይርጋ አይታገድም የሚል ነው፡፡ በተጠሪዎች በኩል ደግሞ አመልካች በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1060 ተጠቃሚ የሚሆነው በወቅቱ ውርስ አጣርተው የዉርሱ ንብረት በወራሾች የጋራ ስም ተመዝግቦ ወይም ታውቆ የተቀመጠ የውርስ ሀብቱን እንከፋፈል ብሎ ለሚጠይቅ እንጂ የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ ለሚያቀርብ አይደለም፡፡ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው የውርስ ሃብት ይጣራልኝ ስለሆነ አቤቱታና ሪፖርት በይርጋ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተጠሪዎች የውርስ ሀብት ስለያዙ የውርስ ሀብት ይጣራልኝ የሚል መሆኑ በስር መዝገብ ተመልክቷል፡፡ ከቀረበው አቤቱታ በመነሳት ነው በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የውርስ ሀብት የሚያጣራ በመሾም ሪፖርት ሊቀበል የቻለው፡፡ ስለሆነም አመልካች የውርስ ይጣራልኝ ሳይሆን የውርስ ሀብት ክፍፍል ስለሆነ በይርጋ የሚታገድ አይደለም የሚል ክርክር፤ በስር ያልተነሳና ክርክር ያልተካሄደበት በዚህ ደረጃ መነሳቱ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 83 እና 329/1/ መሰረት ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡

በሌላ በኩል የአመልካች አቤቱታ ይዘት ሲመረመር ለአቤቱታ መነሻ የሆነው የውርስ ሀብት ነው የተባለው ቤት ይዘው የሚኖርበት ወይም በኪራይ በሌላ አግባብ ተጠቃሚ መሆናቸው የሚያመለክት ክርክር የለም፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ጥያቄ የወራሽነት እንጂ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000/1/ መሰረት በሶስት ዓመት ዋጋ የሚታገድ ነው፡፡ ወራሾች ተለይተው የውርስ ሀብቱ ድርሻ ታውቆ ግን ደግሞ ክፍፍል ሳይደረግ የቆየውን የውርስ ሀብት በማናቸውም ጊዜ መጠየቅና በይርጋ የሚታገድ እንዳልሆነ ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1060 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ውርስ ማጣራት በመሆኑ ወራሾች መለየት፤ኑዛዜ መኖሩን አለመኖሩን፤ ዕዳ ጠያቂዎች መኖራቸው አለመኖራቸው፤ የእያንዳንዱ ወራሽ ድርሻ የሚታወቅበትና የሚጣራበት ነው፡፡ በመሆኑም የወራሽነት ጥያቄ አንድ ወራሽ በሌላ በወራሽነት የውርስ ሀብት በያዘው ሰው ላይ ክስ ሲያቀርብ ተፈፃሚነት ባላው የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1000/1/ ድንጋጌ ስር በተመለከተው በሶስት አመት ይርጋ የሚገደብ በመሆኑ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ የፈጸሙት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለ ለማለት አልተቻለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.107852 ጥር 15 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠ ትእዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.151632 ህዳር 18 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለ ችሎት የፌ/የመ/ደ/ ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የተሰጠ ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዘገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 119704

ሀምሌ 22 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች ፡- የአማራ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት - ነ/ፈ አብርሃም ጌቴ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ዳንኤል ከፋለ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል ፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ተጠሪ በስራ ገበታቸው ባለመገኘታቸው የዲሲፕሊን ቅጣት ተቀጥተው እያለ በዚህ ሳይታረሙ ሃሰተኛ የህክምና ፈቃድ ማስረጃ በማቅረብ ከባድ የድሲፕሊን ጥፋት ፈፅመዋል ተብሎ ከስራ እንዲሰናበቱ በአመልካች ድርጅት የበላይ አካል የተሰጠው ውሳኔ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ታይቶ ውሳኔው መሻሩን በመቃወም አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ይመለከታል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የአሁን ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ እንደማንኛውም ታካሚ ካርድ አውጥቼ የታከምኩ በመሆኑና ማስረጃውን ከፈለገ ህይወት ሆስፒታል መቀበሌ ባልተካደበት ሁኔታ በካርዱ ላይ የበሽታው አይነት አልተጠቀሰም በሚል ምክንያት የህክምናው ማስረጃ በሃሰት የቀረበ ነው ተብሎ ጥፋተኛ ተብየ መቀጣቴ አግባብ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በሰጡት መልስ የይ/ባይ ቅሬታ የፍሬ ነገር እንጅ የህግ ስህተት ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፤ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም ይ/ባይ በሃሰት የተዘጋጀ የህክምና ፈቃድ ማስረጃ ያቀረበ ለመሆኑ ማስረጃውን ሰጠ የተባለው ሆስፒታል ያረጋገጠና ጥፋቱ ከባድ ከመሆኑም በላይ ከዚህ በፊትም በዲሲፕሊን የተቀጣ በመሆኑ ከስራው እንዲሰናበት መወሰኑ ተገቢ ነው ተብሎ ውሳኔው እንዲፀና ተከራክረዋል፡፡

የይግባኝ ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተሻሻለው የክልሉ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 200/2005 አንቀፅ 13(2) መሰረት ቦርዱ በፍሬ ነገር ረገድ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ሲሆን ውሳኔው የህግ ስህተት ያለበት ከሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ለማየት ስልጣን እንዳለው መደንገጉን፤ ከዲሲፕሊን መመሪያው አንፃር ከስራ ሊያሰናብተው የሚችል ጥፋት ፈፅሟል/አልፈፀመም የሚለው ጭብጥ የህግ ክርክር በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንዳለው፤ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም በድርጅቱ የሥነ ምግባር እና የድስፐሊን መመሪያ ቁጥር 002/2006 አንቀፅ 24(3) መሰረት ሃሰተኛ ማስረጃ ማቅረብ ከባድ

www.abyssinialaw.com

የዲሲፕሊን ጥፋት መሆኑ መደንገጉን፣ ማስረጃውን ሰጠ የተባለው ሆስፒታል የማስረጃውን ትክክለኛነት እንዲያረጋግጥ ተጠይቆ የህክምና ካርዱን አውጥቶ በመመልከት ህመሙን የሚያስረዳ ነገር ካርዱ ላይ ያልተገለፀ በመሆኑ የህክምና ማስረጃው ህጋዊ አይደለም የሚል ምላሽ መፃፉን፣ ነገር ግን የህክምና ፈቃድ ማስረጃው ከሆስፒታሉ የተሰጠ ለመሆኑ ባልተካደበት ሁኔታ በካርዱ ላይ የበሽታው አይነት አልተገለፀም በሚል ምክንያት ተጠሪ ሀሰተኛ ማስረጃ አቅርቧል ተብሎ ጥፋተኛ መባሉ አግባብ አይደለም በማለት የዲሲፕሊን ኮሚቴው እና ዋና ስራ አስኪያጁ እንዲሁም ቦርዱ የሰጡትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ ያልተከፈለው ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራው እንዲመለስ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ችሎት ቅሬታውን ሳይቀበል ቀርቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይህን በመቃወም ነው፡፡ ህዳር 3/2008 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ የፈለገ ህይወት ሆስፒታል ተጠሪ ያቀረበው የሐኪም ማስረጃ ህጋዊ አይደለም በማለት እያረጋገጠ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ሐሰተኛ ሰነድ አላቀረበም በማለት ወደ ስራው እንዲመለስ የመወሰኑን አግባብ ለማጣራት ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፅሁፍ እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከፍ ሲል በተጠቀሰው የድርጅቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃውን ለመመዘን ስልጣን የተሰጠው የድርጅቱ የበላይ አካል ተጠሪ በተደጋጋሚ በስራ ገበታው የማይገኝ፣ በምክር እና በቅጣትም ሊመለስና ሊማር ያለመቻሉን፣ እንዲሁም ከስምሪትና ከተቋሙ ፈቃድ ውጪ ሰቆጣ መሄዱ እና እዚያ የታየ ስለሆነ ለዚሁ እንዲረዳው ከፈለገ ህይወት ሆስፒታል የ10 (አስር) ቀን የህክምና ማስረጃ ማምጣቱን፣ ሆስፒታሉም ስለማስረጃው ትክክለኛነት ተጠይቆ የተሰጠው የሀኪም ማስረጃ ትክክለኛ አለመሆኑን ገልጾ መፃፉን ፣ ይህም በተቋሙ የዲሲፕሊን መመሪያ አንቀፅ 23 መሰረት ከስራ የሚያሰናብት ከባድ ጥፋት መሆኑን በማረጋገጥ ከ19/05/2007 ዓ.ም ጀምሮ ከተቋሙ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህን ውሳኔ የሻረው የህክምና ፈቃድ ማስረጃው ከሆስፒታሉ የተሰጠ ለመሆኑ አልተካደም፣ በካርዱ ላይ የበሽታው አይነት ሳይገለፅ መገኘቱም ተጠሪ ሀሰተኛ ማስረጃ አቅርቧል አያሰኝም በማለት ነው፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ስልጣን ያለው አካል በፍሬ ነገር ረገድ ያረጋገጠውን ሳይቀበል ማለፉና ማስረጃውን በመመዘን የራሱ መደምደሚያ ላይ መድረሱ በህጉ የተሰጠውን ስልጣን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን ይመዝን ቢባል እንኳ የህክምና ማስረጃው ወጣ የተባለበት የፈለገ ህይወት ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር በቁጥር 959/2687/06 በ26/12/06 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ከሆስፒታሉ ተወሰደ የተባለው የሀኪም ዕረፍት

www.abyssinialaw.com

ማስረጃ በተመለከተ አጣርቶ ህጋዊ አለመሆኑን እያረጋገጠ ፍርድ ቤቱ ማስረጃው ከሆስፒታሉ የተሰጠ ለመሆኑ እስካልተካደ ሀሰተኛ ሊባል አይችልም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢ አይደለም፡፡ መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ሲባል አንድን ፍሬ ነገር ለማረጋገጥ የሚያስችሉ በማስረጃነት የሚቀርቡ ፅሁፎችን (ሰነዶችን) በሃሰት መፍጠርም ሆነ በእነዚህና መሰል ፅሁፎች መገልገል የድሲፕሊን እና የወንጀል ጥፋተኝነትን የሚያስከትል በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የደረሰበት ውሳኔ በህጉ የተደነገገውን መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን በተመለከተ የሰጠው ትርጉምና የደረሰበት መደምደሚያ እንዲሁም ይህን ተከትሎ ያሳለፈው ውሳኔ ህጋዊ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ የአመልካች ድርጅት የበላይ አካል (ቦርዱ) በፍሬ ነገር ረገድ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ በመሆኑ ይኸው አካል በፍሬ ነገር ረገድ በደረሰበት መደምደሚያ ላይ ተመስርቶ ያሳለፈውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተመልክቶ ውሳኔው የህግ ስህተት ያለበት ከሆነ ማረም ሲገባው ከዚህ አልፎ ፍሬ ጉዳዩን ለማጣራት ማስረጃውን መመዘኑ ህጉን የተከተለ ካለመሆኑም በላይ ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን በመመዘን የደረሰበት መደምደሚያም የተሻሻለውን የክልሉ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 200/2005 አንቀፅ 13(2) እና አመልካች ያወጣውን የሥነ ምግባር እና የዲስፕሊን መመሪያ ቁጥር 002/2006 አንቀፅ 24(3) ድንጋጌዎች እንዲሁም በሃሰተኛ ማስረጃ ስለመገልገል በህጉ የተደነገገውን የጣሰና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ሰላገኘነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያሳለፈው ውሳኔ እና የሰበር ችሎቱ የሰጠው ትዕዛዝ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአማራ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 40498 ጥቅምት 02 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/አ/መ/ቁ 51812 ጥቅምት 18 ቀን 2008 ዓ/ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአማራ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ በ7/5/2007 ዓ.ም፤ እንዲሁም ቦርዱ በ22/7/2007 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 116154

ህዳር 13 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-1. አቶ ሚሪንዳ ዋሲሁን
2. አቶ መንግስቱ በለጠ
3. አቶ ፍቃዱ
4. አቶ ሰይፉ ለማ
5. አቶ ውድነህ ዘለቀ
6. ወ/ሮ አመለወርቅ ባቾሌ
7. ወ/ሮ ገነት አድነው
8. አቶ አብነት ዩሐንስ
9. ወ/ሮ ብርቂ መሻሻ
10. አቶ ሱልጣን ኡስማን

} የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ኢትዩ ቴሌኮም - ነ/ፈጅ አደመ አየለ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር ከአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የተጀመረ ነው፡፡ ክርክሩ የበርሃ አበል ከደመወዝ ጋር ተደምሮ የገቢ ግብር እንዲከፈልበት መደረጉ ያላግባብ ነው በሚለው የአመልካቾች ክስ መነሻ የተጀመረ ነው፡፡

አመልካቾች ለስራ ወደ ጉጂ ዞን ሊበን ወረዳ ነገሌ ከተማ አስተዳደር በነገሌ ቦረና ሾፕ ስር ተጠሪ መድቧቸው በመስራት ላይ እያሉ በዚሁ አካባቢ ለሚሰሩ ሰራኞች 30% የበረሃ አበል ምክንያት እስከ ግንቦት ወር 2004 ዓ/ም ድረስ ሲከፈላቸው መቆየቱንና ከግንቦት ወር 2004 ዓ/ም በኋላ ግን ባልታወቀ ምክንያት ይከፈላቸው የነበረው የ30% የበርሃ አበል ላይ በወር ከሚያገኙት ደመወዝ ጋር በመደመር ያላግባብ ግብር እየተቆረጠባቸው ከፍተኛ የመብት ጉዳት እየደረሰባቸው መሆኑን ገልፀው ይኼው የተጠሪ እርምጃ ተገቢ ያለመሆኑ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው የመከላከያ መልስ ክርክርም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በመጀመሪያ

www.abyssinialaw.com

ደረጃ መቃወሚያት ያነሳውም ጉዳዩ በቦርዱ ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም የሚል ሲሆን መቃወሚያው የቀረበለት ቦርድም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 147(1(ሀ)) ስር ስልጣኑ በግልጽ መደንገጉንና የአመልካቾች ጥያቄ ደግሞ በዚህ ድንጋጌ ስር የማይወድቅ መሆኑን ገልጾ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ አመልካቾች ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን ስር እንደሚወድቅ አምነው በቦርዱ ላይ ክስ ከአቀረቡና ተጠሪም ይህንኑ በመቃወሙ በተሰጠው ብይን ላይ ይግባኙ መቅረብ ያለበት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 139 (ለ) መሰረት በክልሉ ላለው የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሳይሆን በአዋጁ አንቀፅ 154 በተደነገገው መሰረት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው በማለት ይግባኛቸውን ሰርዞታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካቾች ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበውም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ጉዳዩ የወል የሥራ ክርክር ሁኖ እያለ ቦርዱ በስልጣኔ ስር አይወድቅም ማለቱም ሆነ የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙ የሚቀርበው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው በማለት ብይን ሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መፅናቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ የጹሑፍ መልስ የሰጠ ሲሆን በመልሱ ላይም ጉዳዩ በቋሚ ቦርድ ስልጣን ስር እንደማይወድቅና ጉዳዩን ለማየት የሚችል አካልም በአዋጅ ቁጥር 466/97 አግባብ በክልሉ ያለ ቋሚ ቦርድ ያለመሆኑን፣ ተጠሪ እጅግ አስፈላጊ ከሚባሉት መንግስታዊ የልማት ድርጅቶች መካከል አንዱ በመሆኑ የአመልካቾች ጥያቄው በክስ ሊታይ የማይችል መሆኑን ዘርዝሮ በአመልካቾች የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይህም ችሎት በቅድሚያ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው አቢይ የህግ ነጥብ ላይ ብቻ በማተኮር መዝገቡን መርምሯል፡፡ በዋነኛነት ሊፈታ የሚገባው የነገሩ ጭብጥ፡- አንድ ጉዳይ የወል የስራ ክርክር ነው በሚል እምነት በቋሚ ቦርዱ ከቀረበ በኋላ ቋሚ ቦርዱ በስልጣኑ ስር የማይወድቅ መሆኑን ገልፆ መዝገቡን ሲዘጋው ይግባኙ መቅረብ ያለበት ለየትኛው ፍርድ ቤት ነው? የሚለው ጉዳይ ነው፡፡

ለተያዘው ጭብጥ ምላሽ የማግኘቱ ጉዳይ ስለ ስራ ክርክር፣ ስለ ቦርድና ስለ ፍርድ ቤት ሥልጣን የሚገልጹትን የአዋጅ ቁ. 377/96 ድንጋጌዎችን ተመስርቶ ጭብጡን መመርመርን ይጠይቃል፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/96 ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 በኋላ የወጣ ሲሆን በአንቀጽ 136(3) ስለ ስራ ክርክር ምንነት ትርጓሜ የሚሰጥ ድንጋጌ ከመያዙም በላይ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 137 ደግሞ የስራ ክርክር ችሎት መቋቋማቸውን በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ በዚህም መሰረት የአዋጁ አንቀጽ 147

www.abyssinialaw.com

ስለቦርድ ሥልጣን የሚደነግገው ሲሆን የፍ/ቤት ስልጣን ደግሞ የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 138/2/ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 138/1/ የተዘረዘሩትንና መሰል የግል የሥራ ክርክሮችን የመዳኘት ሥልጣን ለፍርድ ቤት መስጠቱን ከዚህ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ አዋጁ የስራ ክርክርን የክልልና የፌዴራል ጉዳይ ነው የሚል መለኪያ በመስጠት የስነ-ነገር የዳኝነት ስልጣን መከፋፈሉን በግልፅ አያሳይም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 322/95"ም" ሆነ በሕገ መንግስቱ መሰረት የክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስራ ክርክርን አስመልክቶ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን በውክልና ሊመለከት ይችላል የሚባልበት አግባብም የለም፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 138(1) ድንጋጌ መሰረት ለፍርድ ቤት የተሰጡትን የስራ ክርክሮችን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት(የወረዳ ፍርድ ቤት) መሆኑ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 139(1(ሀ)) ደግሞ በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በስራ ክርክር ችሎት የተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት የይግባኝ ስልጣን እንዳለው ያሳያል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 138 መሰረት በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚታዩት ጉዳዮች ላይ የይግባኝ ስልጣን ያለው መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 139(1(ሀ)) በግልፅ ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል በክልል በተቋቋሙ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዶች በሚሰጡ ብይኖች እና ውሳኔዎች ይግባኙ የሚቀርበው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 154 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣውን አዋጅ ቁጥር 466/97 ድንጋጌዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 154 እንደተመለከተው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በተሰጠ ብይን ወይም ውሳኔ ላይ ይግባኝ መቅረብ ያለበት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 322/95 ከተደነገገው ውጪ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በመደበኛነት የተዋቀሩት በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች መሆኑ ይታወቃል፡፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ- መንግሥት አንቀጽ 78/2/ እንደተደነገገው ክርክር የተነሣበትን ክልል ጨምሮ በአፋር፣ በጋምቤላ፣ በቤንሻንጉል፣ በሱማሌና በደቡብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመደራጀቱ በአዋጅ ቁጥር 322/95 አንቀጽ 2 ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይህ ማለት ግን በአዋጅ ቁጥር 377/96 የተዘረጋውን የይግባኝ ስርዓት ቀሪ የሚያደርግ አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 113675 ላይ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም ሰራተኞች ተጠሪን ከሚመስሉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጋር በክልሎች የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዶች በሚያቀርቧቸው ክሶች የሚነሱ የይግባኝ ቅሬታዎች ላይ ይግባኝ ማቅረብ ያለባቸው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 154(1) ስር የተቀመጠውን መሰረት በማድረግ በአዋጅ ቁጥር 322/95 የተደነገገውን ስርዓትና በሕገ መንግስቱ በተሰጠው የውክልና ስልጣን አግባብ ሳይሆንን በአዋጀ ቁጥር 377/96 በተዘረጋው የይግባኝ አቀራረብ ስርዓት ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

ከዚህ አንጻር ሲታይ በአዋጅ ቁጥር 322/95 አግባብ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተደራጀባቸውና ባልተደራጀባቸው ክልሎች ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሚነሱ ይግባኞች መቅረብ ያለባቸው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(2) ድንጋጌ መሰረት ከፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጋር አቻ ስልጣን ላላቸው ለክልሉ ላሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 154 መገንዘብ የሚቻል ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም አመልካቾች ጉዳዩ የወል የስራ ክርክር ነው የሚል የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ባደረገ መልኩ ክስ ያቀረቡ ስለመሆናቸው የክርክሩ ሂደት ስለሚያሳይ እና ይኼው ጥያቄ የቀረበት ቦርድ ደግሞ ተገቢ ነው ያለውን ብይን ከሰጠ በዚሁ ብይን ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኙን ማቅረብ ያለበት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 154(1) እና ለዚህ ድንጋጌ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 113675 በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነው፡፡ የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የተነሳ መሆኑን የተገነዘበና ራሱ ይግባኙን አላይም በማለት ብይን መስጠቱ ተገቢ ቢሆንም ጉዳዩ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት በማለት ብይን መስጠቱ ግን ከላይ የተዘረዘረውን የሕግ ማዕቀፍና ስለሕግ ማዕቀፉ ትክክለኛ አተገባበር ይህ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በዚህ ረገድ የተፈጸመውን የሕግ ስህተት ሳያርም ብይኑን ማፅናቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈጸሙን የሚያሳይ ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 64715 ሰኔ 01 ቀን 2007 ዓ/ም የጸናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ጉዳዩ በይግባኝ ስልጣን ደረጃ ሊታይ የሚገባው በክልሉ በተደራጀው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሳይሆን በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነው ብለናል፡፡ አመልካቾች አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

# ጉምሩክ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 101462

ሐምሌ 20 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ነጂብ አደም አቡበከር - ጠበቃ ጌቱ ሶሬሳ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐቃቤ ሕግ - ነስሪያ ሡልጣን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ ያቀረበባቸውን ሁለት የወንጀል ክሶች የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሁለቱም ክሶች ጥፋተኛ በማለት በመዝገብ ቁጥር 179576 በ14/02/2006 ዓ.ም. እና በ22/02/2006 ዓ.ም. የሰጠባቸው እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 143236 በ08/07/2006 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት በአሁኑ አመልካች እና የተጠሪ ተቋም ሰራተኛ በነበሩት የስር 2ኛ ተከሳሽ አቶ ስዩም በላቸው ላይ በ15/03/2004 ዓ.ም. አሻሽሎ ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡- በአንደኛ ክስ ተከሳሾቹ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 (1) (ሀ) እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 95 (1) (ሐ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ 1ኛ ተከሳሽ ረዳት የጉምሩክ አስተላላፊ፣2ኛ ተከሳሽ ደግሞ የጉምሩክ መጋዘን ሰራተኛ ሆነው ሲሰሩ በ17/08/2003 ዓ.ም. ተለይቶ ባልታወቀ ሰዓት 1ኛ ተከሳሽ ቁጥሩ C-5446/2011 የሆነ ሀሰተኛ ዲክላራሲዮን እና ሀሰተኛ የናሙና መጠየቂያ ፎርም ይዞ ወደ መጋዘን ቁጥር 8 በመቅረብ እና የዚሁ መጋዘን ሰራተኛ የነበረው 2ኛ ተከሳሽም በዚሁ ድርጊት በመተባበር በግል ተበዳይ ለትውልድ ምስክር አስመጪነት በመጋዘኑ ውስጥ የነበረውን ኮንቴይነር ቁልፍ ገንጥለው ቀረጥና ታክስን ጨምሮ የዋጋ ግምታቸው ብር 54,733.07 የሆነ ሁለት ቴሌቪዥኖችን የወሰዱ በመሆኑ አግባብ ካለው የባለስልጣኑ ሹም ፈቃድ ሳያገኙ እሽጎችን የመፍታት እና ምልቶችን የማንሳት ወንጀል አድርገዋል፤በሁለተኛ ክስ ተከሳሾቹ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 (1) (ሀ) እና

www.abyssinialaw.com

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 94 (1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ የባለስልጣኑን ሰነዶች እና መለያዎች ወደ ሀሰት የመለወጥ ወንጀል አድርገዋል የሚል ነው፡፡

አመልካቹ ያቀረቡት መቃወሚያ ውደቅ ተደርጎ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ወንጀሉን አላደረግሁም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ የግል ተበዳይን ጨምሮ በተጠሪው በኩል የተቆጠሩትን ስምንት ምስክሮች ከሰማ እና የተጠሪውን የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ አመልካቹ እንዲከላከሉ በሰጠው ብይን መሰረት ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን ሶስት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው ያሰሙ ከመሆኑም በላይ የተለያዩ ሰነዶችንም በመከላከያ ማስረጃነት አቅርበዋል፡፡ፍርድ ቤቱም አመልካቹ ባሰሟቸው ምስክሮች እና ባቀረቧቸው ሰነዶች በተጠሪ ማስረጃ የተመሰከረባቸውን ማስረጃ ማስተባበል አለመቻላቸውን ገልጾ በሁለቱም ክሶች በተጠቀሱባቸው ድንጋጌዎች ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠባቸው በኃላ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ ወንጀሎቹ በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ደረጃ ያልወጣላቸው መሆኑን ገልጾ በሁለቱም ክሶች ወንጀሉን በዝቅተኛ ደረጃ መድቦ ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ የሆነውን እንደቅደም ተከተሉ ሰባት ዓመት እና አምስት ዓመት ደምሮ የ12 ዓመት ጽኑ እስራት መነሻ አድርጎ በመያዝ፣ይህ የቅጣት መጠን የሚወድቀው በአባሪ አንድ በእርከን 29 ስር መሆኑን በመግለጽ፣ወንጀሉ የተደረገው በግብረአበርነት መሆኑን በምክንያትነት ይዞ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 84 (1) (መ) መሰረት ቅጣቱን በአንድ ማክበጃ ወደ እርከን 30 ከፍ በማድረግ እና ቀጥሎም የቀድሞ ጸባይ መልካምነትን እና የቤተበሰብ አስተዳዳሪነትን በሁለት የማቅለያ ምክንያትነት ተቀብሎ ቅጣቱን ወደ እርከን 28 ዝቅ በማድረግ እና ለሁለቱ ወንጀሎች የተቀመጠውን መነሻ መቀጮ እንደቅደም ተከተላቸው ብር 5,000 እና ብር 10,000 ደምሮ ተከሳሾቹ እያንዳንዳቸው በዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 15,000 (አስራ አምስት ሺህ) መቀጮ እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሁለቱ ተከሳሾች በተለያዩ መዝገቦች ያቀረቡትን ይግባኝ አጣምሮ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በስር 2ኛ ተከሳሽ ላይ በ2ኛ ክስ ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመሻር እና በ1ኛ ክስ ስር የተሰጠበትን የቅጣት መጠን በማሻሻል በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር ሁለት ሺህ መቀጮ እንዲቀጡ ሲወስን የአሁኑን አመልካች ይግባኝ ግን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የስር 2ኛ ተከሳሽ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ያቀረቡት አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101241 በ25/10/2006 ዓ.ም. በተሰጠ ትዕዛዝ ውድቅ የተደረገ መሆኑንም መዝገቡን አስቀርበን ተመልክተናል፡

አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በ1ኛው ክስ ስር ጥፋተኛ መባላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ 2ኛውን ክስ በተመለከተ ግን ድርጊቱን መፈጸሙ ግምት

www.abyssinialaw.com

የሚያስወስድ ነው የመባሉን አግባብነት ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

1. አመልካቹ በሁለቱም የወንጀል ክሶች ጥፋተኛ የተባሉት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም?
2. ቅጣቱ ሊሻሻል ይገባል ወይስ አይገባም?

የሚሉትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካቹ ወንጀሎቹን አላደረግሁም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ተጠሪው ያቀረበው የሰው እና የሰነድ ማስረጃ አጠቃላይ ይዘት ሲታይ አመልካቹ ረዳት የጉምሩክ አስተላላፊ ሆነው ይሰሩ የነበረ መሆኑን፣በስራው ደንብ መሰረት እሽጎች ተከፍተው ናሙና ሊወሰድ የሚችለው ባለዕቃውን፣የጉምሩክ ሹምን እና የመጋዘን ኃላፊውን ጨምሮ አግባብነት ያላቸው አካላት በተገኙበት መሆኑን፣አመልካች ሀሰተኛ የናሙና መጠየቂያ ቅጽ ይዘው በመቅረብ እና ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር በመተባበር ለናሙና ነው በሚል እሽጉን ከፍተው ሁለት ቴሌቪዥኖችን የወሰዱት ከእርሳቸው እና ከመጋዘን ጠባቂው ውጪ ሌላ ሰው ባልተገኘበት መሆኑን፣በግል ተበዳይ አስመጪነት ከመጣው ዕቃ ውስጥ ናሙና እንዲወሰድ በባለስልጣኑ የተሰጠ ትዕዛዝ አለመኖሩን፣ ቴሌቪዥኖቹ ከተወሰዱ በኃላ አመልካች ሞባይል ስልካቸውን አጥፍተው ከግል ተበዳይ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ያቋረጡ መሆኑን እና መሰል ፍሬ ነገሮችን የሚያረጋግጥ ሲሆን ከተሰሙት የተጠሪ ምስክሮች መካከል በተጠሪ ተቋም መጋዘን የገቢ እና የወጪ ዕቃዎች መዝጋቢ መሆናቸውን የገለጹት 8ኛው ምስክር አመልካቹ ሰነዱን በማቅረብ የስር 2ኛ ተከሳሽ ከሚጠብቁት መጋዘን ቴሌቪዥኖቹን ይዘው ሲወጡ ማየታቸውን በማረጋገጥ የመሰከሩ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካቹ ወንጀሎቹን አለማድረጌን ያስረዱልኛል በማለት ያቀረቡት የሰው እና የሰነድ ማስረጃ የተጠሪን ማስረጃ ሊያስተባብል ያልቻለ ስለመሆኑ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው ሁለቱ የስር ፍርድ ቤቶች የተስማሙበት ጉዳይ ሲሆን በ1ኛ ክስ የተሰጠባቸውን የጥፋተኝነት ውሳኔ አስመልክቶ አመልካቹ ያቀረቡት የአቤቱታ ነጥብ በአጣሪው ችሎትም ቢሆን ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን ከማስቀረቢያ ጭብጡ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡2ኛውን ክስ በተመለከተ አመልካች ድርጊቱን መፈጸሙ ግምት የሚያስወስድ ነው የመባሉን አግባብነት ለማጣራት በሚል በአጣሪው ችሎት የተያዘውን ነጥብ በተመለከተ በመሰረቱ ይህ አነጋገር የተገለጸው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ሲሆን የተገለጸውም የአሁኑን

www.abyssinialaw.com

አመልካች በሚመለከት ሳይሆን የስር 2ኛ ተከሳሽን በሚመለከት ሆኖ ከድርጊቱ አጠቃላይ አፈጻጸም አንጻር 2ኛ ተከሳሽ በ1ኛው ክስ በተመለከተው ወንጀል ከአሁኑ አመልካች ጋር ወንጀሉን በመተባበር ያደረገው ስለመሆኑ ግምት የሚወሰድበት ነው ተብሎ ነው፡፡በሌላ በኩል አመልካች ቴሌቪዥኖቹን ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር መሆኑን እሽጉን ከፍቶ የወሰደው ሀሰተኛ የሆነ የናሙና መጠየቂያ ፎርም ለተጠሪ 8ኛ ምስክር በማቅረብ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ይህ በሁለተኛ ክስ የተመለከተው የባለስልጣኑ ሰነዶችን ወደ ሀሰት የመለወጥ ተግባር ራሱን ችሎ በአዋጁ በወንጀልነት የተደነገገ በመሆኑ በማስረጃ በተረጋገጠው መሰረት አመልካቹ በ2ኛው ክስ ጭምር ጥፋተኛ መባሉን የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ በግልጽ መገንዘብ እንደሚቻለው የስር 2ኛ ተከሳሽ ከ2ኛው ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ የተደረገው የሰነዱን ሀሰተኛነት ያውቁ የነበረ ወይም ማወቅ ይገባቸው የነበረ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል እንጂ የሰነዱ ሀሰተኛነት ጉዳይ ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኖ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካቹን በሁለቱም ወንጀሎች ጥፋተኛ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ድንጋጌዎች ሲሆን ጉዳዩ በስር የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ካገኘ በኃላ በዚህ የሰበር ደረጃ በክርክር ላይ ባለበት ሂደት አመልካቹ ጥፋተኛ ተብለውበት የነበረው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ከ30/03/2007 ዓ.ም. ጀምሮ ተሽሮ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ተተክቷል፡፡ አመልካች የተከሰሱባቸው ድርጊቶች በአዲሱ አዋጅም ቢሆን እንደቀደም ተከተላቸው በአንቀጽ 170 (1) እና በአንቀጽ 167 (1) ስር በወንጀልነት ተደንግገዋል፡፡ለ2ኛው ክስ በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ ሕግ የተደነገገው የእስራት ቅጣት መጠን ተመሳሳይ ሲሆን በ1ኛው ክስ በቀድሞው ሕግ በአንቀጽ 95 (1) (ሐ) ስር ከሰባት ዓመት እስከ አስር ዓመት ጽኑ እስራት ሊደርስ ይችል የነበረው የቅጣት መጠን ግን በአዲሱ ሕግ ከአምስት ዓመት ወደማያንስ እና ከአስር ዓመት ወደማይበልጥ ጽኑ እስራት ዝቅ የተደረገ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በአንድ በኩል አዲሱ የወንጀል ሕግ እንዲጸና ከተደረገ በኃላ አድራጊው ሕጉ ከመጽናቱ በፊት ላደረገው ወንጀል ሲፈረድበት ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ በስራ ላይ ከነበረው ሕግ ይልቅ አዲሱ ሕግ ቅጣትን የሚያቃልለት በሆነ ጊዜ ተፈጻሚ መደረግ የሚገባው በአዲሱ የወንጀል ሕግ የተመለከተው ቅጣት ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ጠቅላላ ክፍል በአንቀጽ 6 ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ከጸናበት ቀን በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች ፍጻሜ የሚያገኙት በነበረው ሕግ መሰረት ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 182 ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በመሰረቱ ድርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ የወጣ ሕግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው ድርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ የወጣው ሕግ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.

www.abyssinialaw.com

ሕገ መንግስት አንቀጽ 22 (2) ስር የተደነገገ ከመሆኑም በላይ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ከጸናበት ቀን በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች ፍጻሜ የሚያገኙት በነበረው ሕግ መሰረት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 182 ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው ክርክር ስላስነሳው ጉዳይ በሌሎች ሕጎች የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በማይነካ ሁኔታ ስለመሆኑ ከላይ ከተጠቀሰው የአዋጁ አንቀጽ 182 ድንጋጌ አነጋገር መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ በአዋጁ አንቀጽ 182 የተመለከተው ድንጋጌ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ጠቅላላ ክፍል በአንቀጽ 6 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተፈጻሚነት የማያስቀር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም በ1ኛው ክስ በአመልካቹ ላይ ለሚጣለው ቅጣት መሰረት ተደርጎ መያዝ የሚገባው በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 በአንቀጽ 170 (1) ስር የተመለከተው የቅጣት መጠን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል አመልካቹ ወንጀሎቹን ያደረጉት በ17/08/2003 ዓ.ም. ሲሆን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸው ደግሞ እንደቅደም ተከተሉ በ14/02/2006 ዓ.ም. እና በ22/02/2006 ዓ.ም. ነው፡፡ይህንኑ ጊዜ መሰረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች ቅጣቱ የተሰላውም ከጥቅምት 1 ቀን 2006 ዓ.ም. ጀምሮ በስራ ላይ በዋለው የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በማድረግ ነው፡፡የጥፋተኝት እና የቅጣት ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ በስራ ላይ ከነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ይልቅ ለተከሳሽ ወገን ቅጣቱን የሚያቀለው ወንጀሉ በተደረገበት ጊዜ በስራ ላይ የነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ከሆነ ለቅጣቱ አወሳሰን መሰረት ተደርጎ መያዝ የሚገባው ይኸው መመሪያ ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 95440 እና በሌሎችም መዝገቦች በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ለቅጣቱ አወሳሰን መሰረት ተደርጎ መያዝ የሚገባው የቀድሞው መመሪያ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ከላይ በተገለጸው ሁኔታ በሁለቱ ወንጀሎች በአመልካቹ ላይ ሊጣል የሚገባው መነሻ ቅጣት የአስር ዓመት ጽኑ እስራት ሲሆን ይህም በአባሪ አንድ በእርከን 27 ስር የሚወድቅ ነው፡፡ይህ የቅጣት መጠን በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ባገኘው አንድ የማክበጃ ምክንያት ወደ እርከን 28 ከፍ ከተደረገ በኃላ በተመሳሳይ ሁኔታ በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ባገኙት ሁለት የማቅለያ ምክንያቶች ወደ እርከን 24 ዝቅ የሚደረግ በመሆኑ በአመልካቹ ላይ ለሚጣለው ቅጣት መነሻ ተደርጎ መያዝ የሚገባው በእርከን 24 ስር የተመለከተው የቅጣት ፍቅድ ስልጣን ነው፡፡በተመሳሳይ ምክንያት በመቀጮው መጠን ላይም ተገቢው ማሻሻያ ሊደረግበት የሚገባ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል በአመልካቹ ላይ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ባይሆንም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በአመልካቹ ላይ ተጥሎ የነበረው የቅጣት መጠን ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. በአመልካቹ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሁለቱም ክሶች በመዝገብ ቁጥር 179576 በ14/02/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 143236 በ08/07/2006 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በአመልካቹ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሁለቱ ክሶች በመዝገብ ቁጥር 179576 በ22/02/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 143236 በ08/07/2006 ዓ.ም. በፍርድ የጸናውን የዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት የብር አስራ አምስት ሺህ መቀጮ የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት በማሻሻል አመልካቹ በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ጊዜ ሁሉ ታስቦላቸው በሰባት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር ስምንት ሺህ መቀጮ እንዲቀጡ ወስነናል፡፡
3. በተሻሻለው የጽኑ እስራት ቅጣት ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከመሸኛ ትዕዛዝ ጋር አመልካቹ ለሚገኙበት የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ይላክ፡፡ ለአመልካቹም በዚያው በኩል ይድረስ፡፡
4. እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 111960

ህዳር 06 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዐ/ህግ - አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** ሰይፈ አበበ ንጉሴ - በሌለበት ታይቶ የተወሰነ በመሆኑ አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የአሁኑ አመልካች ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ተከሳሽ (ተጠሪ) አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 በመተላለፍ የኮንትሮባንድ እቃ የጉምሩክ ስርዓት ያልተፈጸመበት መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ እያለበት 21 ጀሪካን ዘይት ቀረጥና ታክስ መጠኑ በአጠቃላይ ብር 6025.45 (ስድስት ሺህ ሃያ አምስት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም) የሆነ በመኖሪያ ቤት ውስጥ ሽንት ቤት ክፍል ውስጥ ተከማችቶ እጅ ከፍንጅ ስለተያዘ የኮንትሮባንድ እቃ ይዞ በመገኘት ወንጀል ፈጽሞ ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ፍቃድ እያለኝ ከእኔ ላይ የተያዘው ስለሆነ ህጋዊ ነኝ ጥፋት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ከሳሽ የአሁኑ አመልካች የሆነው ዐቃቤ ህግ ሁለት ምስክሮችን ያሰማ ሲሆን ተከሳሽም ሁለት መከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ አስመስክሯል፡፡ የጽሁፍ መከላከያ ማስረጃ በቀን 30/01/2004 ዓ/ም የተሰጠ እስከ 2007 ዓ/ም የታደሰ የምግብ ዘይት የንግድ ፈቃድ ተከሳሽ አቅርቧል፡፡

www.abyssinialaw.com

ጉዳዩን የተመለከተው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽን (የአሁኑ ተጠሪን) ተከላክሏል በማለት በወንጀል ስነስርዓት ህግ ቁጥር 149(2) መሰረት በነጻ እንዲሰናበት በማለት የአሁኑ አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ በወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 195(1) መሰረት በመ/ቁ.200935 በቀን 01/07/2007 ዓ/ም ዘግቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ፡-

1. የስር ፍርድ ቤቶች በጅምላ ተጠሪው የታደሰ የንግድ ፍቃድ መኖሩን በማረጋገጡ ብቻ ከኮንትሮ ባንድ ወንጀል ሃላፊነት ያድናል ማለት መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት ነው፣
2. የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 መሰረት ማንኛውም ስሪት ሃገሩ የውጪ የሆነ እቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት በነጻ ዝውውር እንደማይለቀቅ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ተጠሪው ከኮንትሮ ባንድ ወንጀል ሃላፊነት ነጻ ለመሆን ለእቃው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መከፈሉን የሚያስረዳ የእቃው ጉምሩክ ዲክላራሲዮን (ሰነድ) የማቅረብ ህጋዊ ግዴታ እያለበት የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው ታክስ ከፍሎ ንግድ ፍቃድ አውጥቷል በማለት በነጻ ማሰናበታቸው የህግ ሰህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልን እንጠይቃለን የሚል ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ትዕዛዝ ተሰጥቶ አመልካች ተጠሪን ፈልጎ ያለማግኘቱን ገልጾ ጥሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡ በዚሁ መሰረት ሀምሌ 6 ቀን 2007 ዓ/ም በታተመ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ ስላልቀረበ በሌለበት ታይቶ እንዲወሰን ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

የክርክሩ ሂደት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን ጉዳዩን ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ፤አመልካች ካቀረበው አቤቱታ እንዲሁም አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነውም በተጠሪ መኖሪያ ቤት ውስጥ በሚገኘው ሸንት ቤት ውስጥ በክሱ የተጠቀሰው 21 ጀሪካን ዘይት ተይዟል፡፡ በክሱ ውስጥ የተጠቀሰ መጋዘን እየታደሰ ዘይቱ አዲስ ሸንት ቤት ውስጥ ከሌሎች የሱቅ እቃዎች ጋር መገኘቱን የከሳሽም ሆነ የተከሳሽ ምስክሮች በተመሳሳይ ሁኔታ መስክረዋል፡፡ ተከሳሽ (ተጠሪ) በ2004 ዓ/ም የተሰጠ የዘይት ንግድ ፍቃድ እስከ 2007 ዓ/ም ድረስ የታደሰውን ማቅረቡ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጧል፡፡ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ተከላክሏል በማለት በነጻ አሰናብቷል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 መሰረት ተጠሪው ከተከሰሰበት ወንጀል ሃላፊነት ነጻ ለመሆን ለእቃው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መከፈሉን የሚያስረዳ የዕቃው ጉምሩክ ዲክላራሲዮን (ሰነድ) የማቅረብ ህጋዊ ግዴታ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪው የዘይት ንግድ ፈቃድ አለው ከመባሉ በስተቀር ዘይቱን

www.abyssinialaw.com

ከማንና ከየት እንደገዛ እንዲሁም ለገዛበት ዘይት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መከፈሉን የሚያስረዳ የእቃው ጉምሩክ ዲክላራሲዮን (ሰነድ) ተጠሪ አቅርቦ አላረጋገጠም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ተጠሪ ተከላክሏል ለማለት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሆኖም ግን አከራካሪ ሆኖ የታየው ተጠሪ በተከሰሰበት አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 "ህገ ወጥ እቃዎች ይዞ ስለመገኘት" ተብሎ የተደነገገው ድንጋጌ ይህን አዋጅ በተካው በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ላይ ወንጀል ሆኖ ተደንግጓል ወይስ አልተደነገገም? የሚለውነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ላይ አልተደነገገም፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 168 የተደነገገው "የኮንትሮ ባንድ ወንጀል" በሚል ነው፡፡ ይህም በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ የተደነገገነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 የተደነገገው በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ካልተደነገገ ህጋዊ መፍትሔ (legal remedy) ምንድነው? የሚለው ምላሽ ሊያገኝ ይገባል፡፡ ይህ አዋጅ ግን ይህንን ጥያቄ የሚመልስ የህግ መርህ አይደነግግም፡፡ በዚህ ጊዜ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት የተደነገገው መሰረታዊ መርህ እንዲሁም በወንጀል ህጉ በመርህነት የተደነገገው ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በሌላ አነጋገር በኢፌዲሪ ህገ መንግስትና በወንጀል ህግ ከተደነገገው መሰረታዊ መርህ አንጻር ታይቶ መተርጎም ይኖርበታል፡፡ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 22 የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 5 በተመሳሳይ መልኩ ደንግጎታል፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22(2) ድርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ የወጣ ህግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኃላ የወጣ ህግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል በማለት ተደንግጓል፡፡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 5(3) የተሻረው ህግ ይሰራ በነበረበት ጊዜ የተፈጸመ ወንጀል ሲኖርና በዚህ ህግ ግን እንደወንጀል ያልተቆጠረ ሲሆን ሊያስከሰሰም ሆነ ሊያስቀጣ አይችልም፤ ክሱም ተጀምሮ እንደሆነ ይቋረጣል ተብሎ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የፈጸመው ድርጊት ምንም እንኳን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 ላይ ወንጀል ሆኖ የተደነገገ ቢሆንም በዚህ አዋጅ ምትክ በተተካው አዋጅ ቁጥር 859/2006 ወንጀል ሆኖ አልተደነገገም፡፡ ስለዚህ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት እና በወንጀል ህጉ በተደነገገው መሰረታዊ መርህ አንጻር ሲደመደም ተጠሪ ጥፋተኛ ተደርጎ ቅጣት የሚወሰንበት የህግ አግባብ የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 44610 በቀን 22/04/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 200935 በቀን 01/07/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ከላይ በፍርድ ሀተታው የተገለጸውን የኢፌዲሪ ህገ መንግስቱንና የወንጀል ህጉን መሰረታዊ መርህ መሰረት ያደረገ ባይሆንም በውጤት ደረጃ ግን ልዩነት ስለሌለው በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 195(2) (ለ) (2) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤትይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

www.abyssinialaw.com

# ውል

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 109392

ቀን 28/7/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- አቶ ሶፎኒያስ ሀብተማርያም ጠበቃ ሀ/ማርያም መልካ

ተጠሪ፡- ካልዲስ ኮፊ ኃላ/የተ/የግ/ማ- ጠበቃ አሰፋ መኮንን - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካች አቶ ሶፌኒያስ ሀብተማሪያም ጥር 9/2007 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 104228 ጥቅምት 2/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የቀረበ ሲሆን የአሁን አመልካች የዋስትና ስምምነት 1ኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ ቢኒያም አሰፋ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በእስቶር ኪፐር ወይም ዕቃ ግምጃ ቤት ሰራተኛ የሥራ ቅጥር መደብ ተመድቦ ሲሰራ ለሚደርሰው የንብረት ጉድለት ዋስ መሆኔ እየታወቀ 1ኛ ተከሳሽ የገንዘብ ያዥነት ስራ እንዲያከናውን ከተመደበበት ስራ ውጪ ከ100000 ብር በላይ በመስጠት በተላላኪነት ተጠሪ እራሱ አሰማርቶት በደረሰው የገንዘብ ጉድለት አመልካች ተጠያቂ ነው ተብሎ መወሰኑ አለአግባብ በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ካልዲስ ኮፊ የኃ/የተ/የግ/ማ በፌ.የመ.ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ 1ኛ ተከሳሽ አቶ ቢኒያም አሰፋ በከሳሽ ድርጅት በቦሌ ቅርንጫፍ ለንብረት ክፍል ሲቀጠሩ 2ኛ ተከሳሽ አቶ ሶፌኒያስ ሀብተማሪያም እስከ ብር 50000 የዋስትና ግዴታ ነሐሴ 8/2004 ዓ.ም በተጻፈ የዋስትና ግዴታ ውል ገብቷል፡፡ 1ኛ ተከሳሽ በንብረት ክፍል ተቀጥረው በሚሰሩበት ጊዜ መስከረም 2/2005 ዓ.ም ወደ ባንክ እንዲያስገባ ከሳሽ የሰጠውን ብር 111552 ይዘው በመሰወራቸው 2ኛ ተከሳሽ በተገኙበት የንብረት ቆጠራ ተደርጎ የብር 5643.49

www.abyssinialaw.com

ንብረት ጎሏል፡፡ ተከሳሽ በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ሆነው የ1 ዓመት ከ7 ወር ቅጣት ተወስኖባቸዋል፡፡ ስለዚህ 1ኛ ተከሳሽ እና 2ኛ ተከሳሽ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1995 መሰረት በገቡት የዋስትና ውል ግዴታ ብር 117195.49 ከህዳር 2/2005 ዓ.ም በሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉኝ ሲል ከሷል፡፡ የተከሳሾች መልስ የ1ኛ ተከሳሽ መልስ የስራ ኃላፊነቴ የንብረት ክፍል ተቆጣጣሪ እንጂ ገንዘብ የማንቀሳቀስ ኃላፊነት የለብኝም፡፡ ስለዚህ ለብር 111552 በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1928(1) መሰረት ተጠያቂ ልሆን አይገባም፡፡ የብር 5643.49 የንብረት ጉድለት ለተባለው ተጠያቂ ነኝ ሲል 2ኛ ተከሳሽም በሰጠው መልስ የብር 5643.49 ንብረት ጉድለት ለተባለው ብቻ በገባሁት የዋስትና ውል ግዴታ መሰረት ተጠያቂ እሆናለሁ፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ከተቀጠረበት ስራ ውጪ አሰማርተውት ለደረሰው ጥፋት ሀላፊነት የለብኝም ብለዋል፡፡

የፌ.የመ.ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 07408 ግንቦት 27/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው 1ኛ ተከሳሽ አቶ ቢኒያም አሰፋ ብር 111552 በሰነድ ተረክበው ለባንክ ገቢ ያላደረጉና የብር 5643.49 ንብረት ያጎደሉ መሆኑን በቀረበው የሰነድ ማስረጃና 1ኛ ተከሳሽም በጽሁፍና በቃል ክርክር ያመኑ በመሆኑ ተጠያቂ ናቸው፡፡ 2ኛ ተከሳሽ የዋስትና ግዴታቸው 1ኛ ተከሳሽ የንብረት ክፍል ሰራተኛ ሆነው ሲቀጠሩ ለንብረት ጉድለት ኃላፊነት እንጂ ከጥሬ ገንዘብ ብር ጋር በተገናኘ እንዳልሆነ የቀረበው የዋስትና ግዴታ ውል ያስረዳል፡፡ በመሆኑም 2ኛ ተከሳሽ ለብር 5643.49 ንብረት ለጎደለው ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1933(1) እና 1897 መሰረት በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ነው 1ኛ ተከሳሽ ለብር 111552 ከህዳር 2/2005 ዓ.ም ጀምሮ በሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለከሳሽ ይክፈለው፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በአንድነትና በነጠላ ለብር 5643.49 ከግንቦት 27/2005 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጨምሮ ለከሳሽ ይክፈሉት ሲል ወስኗል፡፡ ለፌ.ከፍ/ፍ/ቤት ከሳሽ ይግባኝ አቅርቦ የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 140236 አከራክሮ ሰኔ 16/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ 1ኛ ተከሳሽ አቶ ቢኒያም አሰፋ ተቀጥረው በሚያገለግሉበት ወቅት ለደረሰው የንብረት መጉደል ብቻ ሳይሆን ለገንዘብ መጥፋትና የንብረት መጉደል 2ኛ ተከሳሽ (የአሁን መልስ ሰጪ) በገቡት የዋስትና ግዴታ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የስር ፍ/ቤት የመልስ ሰጪን (2ኛ ተከሳሽን) የዋስትና ግዴታ ወሰን በግልጽ ከተጻፈው የግዴታ ዝርዝር አንጻር ተመልክቶ መወሰን ሲገባው 1ኛ ተከሳሽ የስራ መደብ ባልተቀየረበት እና የዋስትና ውሉን ከሰራተኛው የስራ መደብ ብቻ በማያያዝ አለአግባብ መተርጎሙ የዋስትናውን ግዴታ ወሰን አላማ ያላገናዘበ በመሆኑ የደረሰበት የውሳኔ መደምደሚያ ስህተት ያለበት ነው በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን አሻሽሎ 2ኛ ተከሳሽ (መልስ ሰጪ) 1ኛ ተከሳሽ ብር 111552 ለጎደለው እና በስር ፍ/ቤት የተወሰነውን ብር 5643.49 ጨምሮ እስከ ብር 50000 ብቻ ተጠያቂ ነው ሲል ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች (2ኛ ተከሳሽ) ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 104228 ጥቅምት

www.abyssinialaw.com

24/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ይግባኝ የተባለበት ውሳኔ ጉድለት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ቀርበዋል፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ አመልካች ዋስ የሆነለት አቶ ቢኒያም አሰፋ ሲቀጠር በዋስትና ውሉ ላይ የንብረት ክፍል ሰራተኛ መሆኑ በተገለጸበት ከስራ መደቡ ውጪ ባንክ እንዲያስገባ በተጠሪ የተሰጠውን ገንዘብ ይዞ በመጥፋቱ አመልካች ሃላፊነት አለበት ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 28/2007 ዓ.ም በተጻፈ መልስ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል ነሐሴ 8/2004 ዓ.ም በተደረገው የዋስትና ውል የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ በተጠሪ ድርጅት ተቀጥረው በሚያገለግሉበት ወቅት ለሚያደርሱት የገንዘብና የንብረት መጥፋትና መጉደል እስከ ብር 50000 በጋራ እና በተናጥል የዋስትና ግዴታ ውል ገብተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ቅር የሚያሰኝ ባለመሆኑ ይጽናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን አጠንክረው ተከራክረዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መዝገቡን እንደመረመርነው የአሁን አመልካች (የስር ፍ/ቤት 2ኛ ተከሳሽ) አጥብቀው የሚከራከሩት የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ አቶ ቢኒያም አሰፋ በተጠሪ ድርጅት ሲቀጠሩ የንብረት ክፍል ሰራተኛ ሆነው ሲሆን የዋስትና ግዴታዬም የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ በንብረት ክፍል ሰራተኛነት ለሚያጎድሉት ንብረት እና ገንዘብ እንጂ ከተቀጠሩበት ስራ ውጪ እንዲሰራ ተደርጎ ለደረሰው ጉድለት ሃላፊነት ሊኖርብኝ አይገባም በሚል ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ አቶ ቢኒያም አሰፋ አጉድለዋል የተባለውን በአጠቃላይ ብር 117193.49 ያጎደሉት የስራ መደባቸው ሳይቀየር የንብረት ክፍል ሰራተኛ ሆነው እየሰሩ በነበሩበት ወቅት ነው፡፡ የአመልካች የዋስትና ውል ግዴታ ሰራተኛው ተቀጥረው በሚያገለግሉበት ወቅት ለሚደርሰው የገንዘብና የንብረት መጥፋትና መጉደል ተጠያቂ ለመሆን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የገቡት የዋስትና ግዴታ ሰራተኛው በስራቸው ወቅት ለሚያደርሱት የገንዘብና የንብረት መጥፋትና መጉደል እንጂ ለሚከራከሩበት የንብረት መጉደል ብቻ ተብሎ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ ያጎደሉትን ገንዘብ የድርጅቱ ሰራተኛ ሆነው በሚሰሩበት ወቅት በእጃቸው የገባ ገንዘብ መጉደሉ አመልካች ከገቡት የዋስትና ግዴታ ውል ውጪ የሚባል አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት አመልካችን በገቡት የዋስትና ግዴታ ውል መሰረት ሃላፊነት አለባቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 104228 ጥቅምት 24/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣ የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 140236 ሰኔ 16/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሳራ ተቻቻሉ ብለናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ሐምሌ 29/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው እግድ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ቅጂ የስር ፍ/ቤቶች እንዲያውቁት ይድረሳቸው፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 107542

ቀን 14/08/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** አሻም ትሬዲንግ ኤንድ ኢንደስትሪ ስራ ኃ/የተ/የግል ማህበር - ስራ አስከያጅ አሸበር ውንድሦስሽ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የንግፋን ሞተርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ ደባስ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች ተጠሪ የሸጠልኝ ሊፋን መኪና ከአዲስ መኪና የማይጠበቅ በተደጋጋሚ ብልሽት ምክንያት ወደ ተከሳሽ ጋራዥ የምትገባና መሰረታዊ ጉድለት ያለባት በመሆኑ ተከሳሽ (ተጠሪ) በሌላ አዲስ መኪና እንዲተካ ወይም መኪናዋን ለመግዛት የከፈለኩትን ገንዘብ እንዲመልስ ውሳኔ ይስጥልኝ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ የበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የተያው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡
2. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ሆኖ ቀርቦ ከተከሳሽ LF7132 የሞተር ጉልበት 1300 cc የሆነ አዲስ መኪና ጥር 4 ቀን 2002 ዓ/ም በተዋዋልነው ውል ሸጦልኛል፡፡ ተከሳሽ መኪናዋን የሸጠልኝ በብር 189,800 (አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ብር) ሲሆን ተከሳሽ ብር 94,900 (ዘጠና አራት ሺ ዘጠኝ መቶ ብር) በቅድመ ክፍያ፣ ቀሪውን መኪናዋን ስረከብ ከፍያለሁ፡፡ ተከሳሽ ለከሳሽ የሸጠልኝ መኪና በሃያ አራት ወራት ውስጥ 3000 ኪሎ ሜትር ሳትነዳ ጉድለት ቢገኝበት በራሱ ወጭ ለማስተካከል ወይም ለመቀየር የውል ግዴታ ገብቷል፡፡ ሆኖም መኪናዋን ከተረከብኩበት ጊዜ ጀምሮ ባለበት መሰረታዊ ጉደለት በተደጋጋሚ ወደ ተከሳሽ ጋራዥ የገባች ሲሆን ጉድለት

www.abyssinialaw.com

ከአዲስ መኪና የማይጠበቅ በመሆኑ በሌላ አዲስ መኪና እንዲቀይርልኝ ብጠይቀው ፈቃደኛ አልሆነም። ስለዚህ የሽያጭ ውሉ ፈርሶ መኪናዋ ፍርድ በተሰጠበት ቀን ከምታወጣው ዋጋ ለከሳሽ ከወጭና ኪሳራ ጋር እንዲመልስ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል።

3. ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ መኪናዋ የነበረባት አነስተኛ ጉደለቶች በተከሳሽ ጋራዥና ወጭ ተስተካክላ በአዲስ ሁኔታ ላይ ትገኛለች። ከሳሽ መኪናዋን ተረክቦ ወስዶ አገልግሎት ላይ ለማዋል የሚችል በመሆኑ ውሉ ፈራሽ ይሁን በማለት ያቀረበው ክስ የህግ መሰረት የለውም። ከሳሽ መኪናዋን በጋራዣችን ትቶ የሄደ በመሆኑ መኪናዋ በጋራዥ ለቆየችበትና ወደፊት ለምትቆይበት ኪራይ የመጠየቅ መብታችን ይጠበቅልን በማለት ተከራክሯል። የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመር በኃላ መኪናዋ መንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ባለሙያዎች ተመርምራ መግለጫ እንዲቀርብለት ካደረገ በኃላ መኪናዋ መሰረታዊ ችግር ያለበት መሆኑ በማስረጃ ስላልተረጋገጠ የከሳሽ ክስ የህግ መሰረት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል። አመልካች ይግባኝ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል። የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል።

4. አመልካች ህዳር 30 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የሸጠልን መኪና ሶስት ሺ ኪ.ሜትር ሳይነዳ ለአምስት ጊዜ ያህል ሞተሩ ጭምር በድንገትና ሳይታሰብ እየቆመ ለከፍተኛ አደጋ ጭምር ያጋለጠን መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃና ተጠሪ መኪናዋን በተደጋጋሚ በራሱ ጋራዥ ቢጠግናትም መኪናዋ የአመራረትና የጥራት ጉድለት ያለባት በመሆኑ ሊስተካከል አለመቻሉን ለስር ፍርድ ቤት በማስረጃ አስርድተን እያለ የስር ፍርድ ቤት መኪናዋ መሰረታዊ ጉድለት የለባትም በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል።

5. ተጠሪ ሚያዝያ 12 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ መልስ፣ መኪናዋ መሰረታዊ ጉደለት የሌለበት መሆኑን የባለሙያ ማስረጃ በማቅረብ ጥያቄ አቅርበን ነበር በመኪናዋ ላይ የተከሰተው ችግር መሰረታዊና የማይጠገን ችግር አይደለም ተጠሪ መኪናዋን አስተካክሎ ለመስጠት በውል የገባውን ግዴታ ሲፈጽም ቆይቷል። አመልካች ለተጠሪ መኪናዋን ማስተካከል ከአቅሙ በላይ መሆኑን ሳይገልጽላት መኪናዋን ከተጠሪ ጋራዥ ጥሎ ጠፍቷል። መኪናዋ የአመራረት ጉድለት የለባትም ስለዚህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል። አመልካች ሚያዝያ 26 ቀን 2007 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል።

6. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ጽሑፍ ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ለአመልካች በክሱ አይነት የተገለጸቸውን መኪና በብር 189,800 ( አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ

ሺ. ብር) የሸጠ መሆኑንና በመኪናዋ ላይ ለሚታይ ጉድለትም ዋስትና የሰጠ መሆኑ አከራካሪ ጭብጥ አይደለም፡፡ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት አመልካች መኪናዋ ሶስት ኪሎ ሜትር ሳትነዳ የሞተርና ሌሎች ጉድለቶች ተከስተው ለአምስት ጊዜ ከሻጭ ጋራዥ ገብታ፣ ሻጭ(ተጠሪ) የመኪናዋን ጉድለት ለማስተካከል አልቻለም፡፡ አመልካች በገዛት መኪና በአዲስ መኪና ሊያገኝ የሚገባውን አገልግሎት ያላገኘ በመሆኑ መኪናዋ መሰረታዊ ችግር ያለበት ስለሆነ ውሉ ፈራሽ ነው ይባልልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በተቃራኒው በመኪናዋ ላይ የተከሰቱ ብልሽቶች በማንኛውም አዲስ መኪና ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ቀላል ብልሽቶች ናቸው፡፡ አመልካች በመኪናዋ ላይ አሉ የሚላቸውን ጉድለቶች ሙሉ በሙሉ ያስተካከልኩ በመሆኔ አመልካች መኪናዋን ወሰዶ ከመጠቀም በስተቀር የሽያጭ ውሉ የሚፈርስበት ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

7. ከላይ ከተገለጸውና ግራ ቀኙ ከተካካዱባቸው ነጥቦች ለመረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ ለአመልካች በሸጣት መኪና ላይ የታዩ ብልሽቶችና መኪናዋ ወደ ሊፋን ጋራዥ እየገባች ጥገና ያገኘችበት ሁኔታ ከአዲስ መኪና የሚጠበቅ ነው ወይም አይደለም? ብልሽቱ ከአዲስ መኪና የሚጠበቅ አይደለም ከተባለ ውሉን ፈራሽ ለማድረግ በቂ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ነጥቦች መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከላይ የተገለጹትን ነጥቦች፣ ላይ ውሳኔ ለመስጠት እንዲመቸው የስር ፍርድ ቤት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.136 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሰረት ለጉዳዩ ገለልተኛ በሆኑ በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ጉዳዩ ተጣርቶ የሙያ አስተያየት እንዲቀርብለት ትዕዛዝ ሰጥቶ፣ የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ዕወቀትና ክህሎት አላቸው የሚላቸውን ሶስት ባለሙያዎች መድቦ ባለሙያዎቹ መኪናዋን በአካል ከፈተሸና ከመርመሩ በኃላ ጥር 25 ቀን 2004 ዓ/ም ሪፖርት ያቀረቡ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡

8. የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ባለሙያዎች መኪናዋን በአካል በፈተሸበትና በመረመሩበት ወቅት አመልካች መኪናዋን ሊፋን ጋራዥ እንዲያስገባት ምክንያት የሆኑ ጉድለቶች ሊፋን ጋራዥ ያስተካከላቸው መሆኑን ከሪፖርታቸው የገልጸ ሲሆን፣ ባለሙያዎች የመኪናዋን ፋይል በማስቀረብ የተመለከቱ መሆኑንና መኪናዋ 3000 ኪሎ ሜትር ሳትነዳ ከአምስት ጊዜ በላይ ወደ ሊፋን ጋራዥ እየገባች የተለያዩ የጥገና አገልግሎት የተሰጣት መሆኑን እንዳረጋገጡ ገልጸው አንድ አዲስ መኪና 3000 ኪሎ ሜትር ሳይነዳ እንዲዚህ አይነት የበዛ ችግሮች ማጋጠም ስለሌለበት ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ከአዲስ መኪና የሚጠበቁ ችግሮች አይደሉም በማለት ሙያዊ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

9. ተጠሪ ለአመልካች በሸጣትና በአገር ውስጥ ተጠሪ ባቋቋመው የመኪና መገጣጠሚያ ፋብሪካ በተገጣጠመችው አዲስ መኪና ላይ በተደጋጋሚ የተከሰተው ብልሽት በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2344 መሰረት የሽያጭ ውሉ ፈራሽ ለማድረግ በቂ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም

www.abyssinialaw.com

የሚልውን ተመልክተናል፡፡ "የተሸጠው ነገር ጉድለት" የሚል ርዕስ ያለው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2344 "የተሸጠው ነገር ሻጩ ለገዥው ዋቢ ሲሆንለት የሚገባው ጉድለት የተገኘበት እንደሆነ ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል በንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ደነግጋል፡፡ አንድ ሻጭ የሸጠው ነገር ለደንበኛው አገልግሎት ወይም ንግድ ሬገድ ለመጠቀሚያነት ጥሩነት የሌለው ሲሆንና የሸጠው ነገር በውሉ ውስጥ በግልጽ ወይም በውስጣዊ ሀሳብ ለተነገረው ልዩ አገልግሎት የሚሆኑ አስፈላጊ የሆኑ ጥሩነት የሌለው በሆነ ጊዜ ሻጭ ለገዥው ዋቢ እንደሚሆን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2289 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡

10. ከዚህ አንጻር ተጠሪ በሸጠው አዲስ መኪና ላይ እስከ 3000 ኪሎ ሜትር ለሚደርስ ብልሽት ዋቢ በመሆን ዋስትና የሰጠ ሲሆን፣ መኪናዋ 3000 ኪሎ ሜትር ሳትነዳ የተለያየ ብልሽት እያጋጠማት ከአምስት ጊዜ በላይ ሊፋን ጋራዥ እየገባች ተጠግና መውጣቷ ተረጋግጧል፡፡ ይህም ገዥው አዲስ ከፋብሪካ የወጣ መኪና በመግዛትና በመረከብ ከገዥው የአጠቃቀም ጉድለት ካልፈጸመ ወይም አደጋ ካላጋጠማት በስተቀር ቀላልና መለስተኛ የሆኑ ጥገና ለትንሽ ቀናት ብቻ እያቆመች መኪናዋን ለትራንስፖርት እገለገልባታለሁ በሚል ሀሳብ የገዛ መሆኑንና ተጠሪ ለአመልካች የሸጣት መኪና ግን ለአመልካች መስጠት የሚገባትን መደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት ሳትሰጥ በየወቅቱ የተለያዩ ክፍሎቿ እየተበላሹ ሊፋን ጋራዥ ለጥገና ስትገባ የቆየች መሆኑን በገለልተኛ ባለሙያዎች የቀረበው ሪፖርት ያሳያል፡፡

11. በተሸጠው ነገር ላይ የተገኘው ጉድለት ለውል ማፍረሻ ምክንያት የማይሆነው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2344 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ሁኔታ ሲሟላ ነው፡፡ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2344 ንዑስ አንቀጽ 2 የአማርኛ ቅጅ ቃል በቃል ሲነበብ "እንዲህም በሆነ ጊዜ ጉድለቱ እጅግም የማይጎዳ እንደሆነና ገዥው ጉደለቱን አውቆ ኖሮም ቢሆን ጉደለት የተገኘበትን ነገር ሳይገዛው የማይቀር እንደነበር ሲታይ ውሉን ለማፍርስ አይችልም" የሚል ይዘት ያለው ሲሆን የዚህ ድንጋጌ የእንግለኛው ቅጅ፣ "the contract may however not be cancelled where the defect is of small importance and it oppears that buyer would have bougut the thing had he known the defect" የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

12. በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ለአመልካች በሸጠለት መኪና ላይ በየወቅቱ የታዩ ብልሽቶች ከሞተር አሰራር ጀምሮ የፍሪስዮንና ሌሎች ችግሮች እየጋጠሙ መኪናዋ 3000 ኪሎ ሜትር ሳትነዳ ከአምስት ጊዜ በላይ ለጥገና ወደ ሊፋን ጋራዥ የገባች መሆኑ ግራ ቀኙ ካደርጉት ክርክርና ከስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ካስፈራቸው ነገሮች ተረድተናል፡፡ ተጠሪ የሚያከራከረው ከዚህ በፊት በመኪናዋ ላይ የታዩ ጉድለቶችና ብልሽቶች ቀላል በመሆናቸው በተጠሪ በቀላሉ ተስተካክለዋል በማለት ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪ ለአመልካች የሸጠው ያገለገለ መኪና ሳይሆን ከፋብሪካ ተገጣጥሞ የወጣ አዲስ መኪና ከመሆኑ አንጻር መኪናው ትንሽ ኪሎ ሜትር እየተነዳ በሚያጋጥመው ብልሽት ምክንያት አመልካች በመኪናው ሊያገኝ የሚገባውን መደበኛ

www.abyssinialaw.com

የትራንስፖርት አገልግሎት ማግኘት ያልቻሉና በየወቅቱ መኪናዋን ወደ ሊፋን ጋራዥ እየወሰደ ጉድለቶችን በመዘርዘርና የስራ ትዕዛዝ በመስጠት፣ መኪናዋ በጥገና ለመስተካከል የምትችል መሆኗን ምክሮ ያልተሳካ በመሆኑ ውሉ እንደፈርስ የጠየቀ መሆኑን፣ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

13. ይህም ተጠሪ ለአመልካች የሸጣት መኪና ከአዲስ መኪና የማይጠበቅ ተደጋጋሚ ብልሽት የጋጠማትና ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2289 ንዑስ አንቀጽ 1 በዋቢነት ሊያልፍበት የሚገባውን ለመደበኛው ትራንስፖርት አገልግሎት ጥሩነት የሌላት መሆኑን የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ አመልካች መኪናዋ 3000 ኪሎ ሜትር ሳትነዳ ከአምስት ጊዜ በላይ ጋራዥ እየገባች ለጥገና የምትቆም መሆኑን መኪናዋን ከመግዛቱ በፊት ቢያወቅ ኖሮ መኪናዋን ይገዛታል ተብሎ የማይገመትን በመኪናዋ ላይ የታዩት ብልሽቶች ቀላል ሊባሉ የማይችሉ እንደሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡

14. ከዚህ አንጻር አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገውን የመኪና ግዥ ውል እንዲፈርስለት ለመጠየቅ የሚያስችለውና ውለንም ፈራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2289 ንዑስ አንቀጽ 1 በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2344 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጹት ጉደለቶች ተጠሪ በሸጣት መኪና ላይ የታዩ መሆኑን፣ የስር ፍርድ ቤት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 136 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በመደባቸው የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ባለሙያዎች ተጠሪ በሸጣት መኪና 3000 ኪሎ ሜትር ሳትነዳ ያጋጠሙ ብልሽቶችና ችግሮች በአዲስ መኪና ሊታዩ የሚገቡ ችግሮች አይደሉም በማለት የሙያ አስተያየት የሰጡበት ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት መኪናዋ በተደጋጋሚ ጋራዥ መግባቷ ውሉን ለማፍረስ በቂ ምክንያት አይደለም በማለት መወሰኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2344 ንዑስ አንቀጽ 1 የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2289 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2344 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ ሳያገናዝብ የተሰጠና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

15. ተጠሪ አመልካች ጋር ያደረገው የመኪና ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው ከተባለ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለውን በማስከተል መመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ መኪናዋ ሊፋን ጋራዥ የቆመችና ተጠሪ የተረከባት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች መኪናዋን ለመግዛት የከፈለው ብር 189,800 (አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ብር) ተጠሪ ለአመልካች የመመለስ ግዴታ አለበት አመልካች ተጠሪ በአሁኑ ወቅት መኪናዋ የምታወጣውን ዋጋ እንዲከፍለው ጥያቄ ያቀረበ ቢሆንም፣ ይህ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአንጻሩ ተጠሪ አመልካች የከፈለውን ብር 189,800 (አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ ሰምንት መቶ ብር) አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ክስ ካቀረበበት መጋቢት 14 ቀን

www.abyssinialaw.com

2003 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ሊመልስ ይገባል በማለት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1815 እና በፍታብሔር ቁጥር 1751 መሰረት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 176453 ግንቦት 14 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 137600 ጥቅምት 17 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. በተጠሪና በአመልካች መካከል የተደረገው የመኪና ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው በማለት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2289 ንዑስ አንቀጽ 1፣ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2344 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ወስነናል፡፡
3. ተጠሪ ሊፋን ጋራዥ ገብታ የቆመችውን መኪና ተረክቦ ለሚፈልገው አገልግሎት ሊውል ይችላል ብለናል፡፡
4. ተጠሪ አመልካች መኪናዋን ሲገዛ የከፈለውን ብር 189,800 (አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ብር) ከመጋቢት 14 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ይክፈል በማለት ወሰነናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 115981

ግንቦት 26 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካቾች፡- 1ኛ. ሕፃን መይሙና ሀሰን
2ኛ. ሕፃን መሳይ ሀሰን
3ኛ. ሕፃን ረሂማ ሀሰን } ጠበቃቸው ጌታቸው አለሙ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የሕፃን ሳሊሃ ሀሰን ሞግዚት ወ/ሮ ፀሃይ አድማሱ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ የሚመለከት ክርክር ሲሆን የተጀመረው በደ/ብ/ብ/ሕ/ ክልል ዲላ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡በስር ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኗ ተጠሪ አመልካች፤አመልካቾች ፤ተጠሪዎች፤ የአመልካቾች ሞግዚት ወ/ሮ ዙልፋ ከማል ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡የተጠሪ ሞግዚት ወ/ሮ ፀሐይ አድማሱ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ባጭሩ፡- ሟች ሀሰን አዲል የህፃን ሳሊሃ ሀሰን ወላጅ አባት ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውንና ህፃን ሳሊህ ሀሰን ወራሽ መሆኗ የተረጋገጠበትን ማስረጃ አያይዘው በማቅረብ ሟች በህይወት እያሉ ያፈሯቸውን ንብረቶች ዝርዝር አቅርበው የውርስ አጣሪ ተሹሞ ተጠርተው የህጻን ሳሊህ ሀሰን ድርሻ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁኑ አመልካቾች ሞግዚት በሰጡት መልስም ጉዳዩ ከአሁን በፊት በፍርድ ያለቀ ስለመሆኑ፤ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትም የግላቸው መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ አመልክቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

የስር ፍርድ ቤትም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ ለክርክሩም ምክንያት የሆነው ቤት በጣልቃ ገብ ስም የሚታወቅ ነው፡፡ተጠሪ የሟች ንብረት ስለመሆኑ አላስረዳችም፡፡ንብረት በአመልካቾች ሞግዚት ስለመኖሩ ተጠሪ አላረጋገጠችም፡፡ሌሎች የቤት ቁሳቁሶች በአመልካቾች ሞግዚት ስለመኖሩ ተጠሪ በሰው ይሁን በሰነድ ማስረጃ አላስረዳችም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡የአሁኗ ተጠሪ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙ ከአከራካሪ እና ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት ከአደረገ በኋላ ሟች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የቤት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቁጥር 1303 የተሰጠው በ1988 ዓ.ም ለአሁኗ የአመልካቾች ሞግዚት ተሰጠ ከተባለ በኋላ በ1992 ዓ.ም የእድሳት ፍቃድ ጠይቆ ማሳደሱን፤ስጦታ ተሰጠ የተባለው ቤትም መኖሪያ ቤቴ ነው በሚል ሲገብርበት እንደነበረ ማስረጃ በመቅረቡ የስጦታ ውሉን በዝምታ በመሻር ቦታውንና ቤቱን በባለቤትነት ስር አድርጎ ሲጠቀምበትና ሲገለገልበት የነበረ መሆኑን ያሳያል፡፤የስር ፍርድ ቤት በአግባቡ ሳያጣራና ሳይመረምር የደረሰበት መደምደሚያና የሰጠው ውሳኔ የሕግና የማስረጃ ድጋፍ የሌለው ነው በማለት ውሳኔውን ሽሮ በይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቁጥር 1303 ላይ ያለውን ይዞታና ቤት ሟች አቶ አዝጊ (ሀሰን) አዲል እና የአመልካቾች ሞግዚት ወ/ሮ ዙልፋ ከማል የጋራ ንብረት በመሆኑ ሟች አቶ አዝጊ አዲል ድርሻ የውርስ ሀብት ነው፡፡የሟች ልጆች የአባታቸው የውርስ ድርሻ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡የአሁኑ አመልካቾች ሞግዚት የጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 የተሰረዘ ሲሆን በሰበር ስልጣኑ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የሚያከራክረውን ንብረት ላይ ድርሻ የላቸውም ያለ አለመሆኑን የአመልካቾች ሞግዚት ባለቤቷን በፍቺ ስለተለያዩ የደረሰኝ ነው ትበል እንጂ ፍቺና የንብረት ክፍፍል መኖሩን አላስረዳችም፡፡በይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቁጥር 1303 የሆነውን የአመልካቾች ሞግዚት ድርሻ ከተለየ በኋላ የሟች ልጆች ይክፈሉ መባሉ በአግባቡ ነው በማለት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ ያቀረበውም የስር ከፍተኛ እና በየደረጃውን ጉዳዩን የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤትና ይዞታ የግላቸው ስለመሆኑ፤የስጦታ ውሉም እንዳልተሻረ፤የተጠሪ ሞግዚት ከአሁን በፊት ክስ አቅርበው ውድቅ የተደረገባቸው ስለመሆኑ፤ተጠሪ በማይመለከታት ንብረት አጣርታ እንደቀረበች በመግለጽ ውሳኔው እንዲሻር የሚጠይቅ ነው፡፡የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ግራ ቀኙ የፁሁፍ ክርክር አድርጓል፡፡ተጠሪ በሰጠችው መልስም ሟች ልጅን መሻር

www.abyssinialaw.com

እንደማይችል፤የተወለደቺው ከስጦታ በኋላ ስለመሆኑ ፤ስጦታውን በዝምታ የተሻረ መሆኑን በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና አመልክቷል፡፡የመልስ መልስም ቀርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጹሁፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ "በዚህ ጉዳይ አመልካች አከራካሪውን ንብረት ከሟች ጋር በጋብቻ ተሳስረው በነበሩበት ወቅት በስጦታ ያገኙት እና ጋብቻቸው ሲፈርስ የንብረት ክፍፍል አድርገው መለያየታቸው እየገለጹ ተጠሪ /ህጻን/ ሳሊህ ሀሰን ድርሻ አለው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ከሰ/መ/ቁ 77735 አንጻር ለመመርመር" የሚል ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከስር ፍርድ ቤት አንስቶ አጥብቀው የሚከራከሩት ከሟች አቶ ሀሰን አዲል የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የንብረት ክፍፍል መደረጉን፤በይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት 1303 የሚታወቀው ቤትና ይዞታ በ1988 ዓ/ም ከሟች በስጦታ ያገኙትና የግላቸው ቤትና ይዞታ ስለመሆኑን ነው፡፡የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት በበኩላቸው ከአሁን በፊት የተደረገው ክርክር ሚስት መሆናቸውን መሰረት ያደረገ እንጂ ተጠሪ ወራሽ በመሆኗ ምክንያት የቀረበ ክስ አለመሆኑን ክርክር የተደረገበት በቁጥር 1303 የሚታወቀው ቤት የአመልካቾች ሞግዚት የግል ቤት አለመሆኑን መከራከራቸውን ተመልክተናል፡፡የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህን ጉዳይ በይግባኝ እና ሰበር የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች ቤቱ በመጀመሪያ የአሁን ተጠሪዎች ሞግዚት በስጦታ ያገኙት መሆኑን ገልጸው፤ነገር ግን ሟች ከስጦታ በኋላ በአከናወኗቸው ድርጊቶች ስጦታቸው በዝምታ ተሽሯል ከሚል መደምደሚያ ደርሰዋል፡፡

ከመዝገቡ ጋር ከተያያዙ ሰነዶች መገንዘብ የተቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት 1303/83 የሚታወቀው የሟች ንብረት ስለመሆኑ ሐምሌ 17 ቀን 1988 ዓ.ም በተደረገው ስጦታ ለወ/ሮ ዙልፋ ከማል መስጠታቸውን፤ስጦታውም በስረ ፋይል መዝገብ ቁጥር 156/88 ፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቁን ነው፡፡በሌላ በኩል የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት በጌዴኦ ዞን ወናጎ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ 00726 ክስ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ጥር 30/05/2003 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ይዘትም የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት በይዞታ ማረጋገጫ ቁጥር 1303/83 በሚታወቀው ቤት ላይ ድርሻ እንዳላቸው የጠየቁ ቢሆንም የአሁን አመልካቾች ሞግዚት በስጦታ ያገኙት ነው በማለት የተጠሪ ሞግዚት ክስ ውድቅ ማድረጉን የሚያሳይ ነው፡፡ይህ ውሳኔም ጉዳዩን በየደረጃው ባዩት ፍርድ ቤቶች የጸና ሲሆን፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰመ/ቁ 77735 በ12/08/2004 ዓ.ም መሰረታዊ

www.abyssinialaw.com

የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት ድርሻ አለኝ በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ከመደረጉ በተጨማሪ የአሁን አመልካቾች ሞግዚት ቤትና ይዞታውን ያገኙት በስጦታ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ከክርክሩ ይዘት መገንዘብ የተቻለው የስጦታ ውሉ የጸና ስለመሆኑ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት መወሰኑን ነው፡፡የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት በ2003 ዓ.ም በአመልካቾች ሞግዚት ላይ ክስ አቅርበው ውድቅ ከተደረገ በኂላ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪን ወክለው በ2005 ዓ.ም ክስ ማቅረባቸው መዝገቡ ያሳያል፡፡የስር ፍርድ ቤቶች ሟች የስጦታ ውሉን በዝምታ ሽሮታል ከሚል ድምዳሜ የደረሱ ቢሆንም በ2003 ዓ.ም አስቀድሞ በተሰጠው ውሳኔ የስጦታ ውሉ የጸና ስለመሆኑ በየትኛውም ፍርድ ቤት ያልተሻረ ውሳኔ መስጠቱን ካቀረቡት የውሳኔ ግልባጮች መገንዘብ ተችሏል፡፡

የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት በስር ፍርድ ቤት ይሁን በሰበር ደረጃ ባደረጉት ክርክር ወላጅ ልጅን ከስጦታ መሻር አይችልም የሚል ነው፡፡ስጦታው የአሁኗ ተጠሪ ከመወለዷ በፊት የተሰጠ ስለመሆኑ አልተካደም፡፡ስጦታው በፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቁም ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ሟች ባደረጉት ስጦታ በምስክር ወረቀት ቁጥር 1303/83 በስማቸው ተመዝገቦ የሚታወቀውን 27x12፡ 324 ካሬ ሜትር ላይ የተሰራውን አንድ ክፍል ቆርቆሮ ክዳን ቤት ከነቦታው ለወ/ሮ ዙልፋ ከማል መስጠታቸው አረጋግጠዋል፡፡በመሰረቱ የስጦታ ውል በፍ/ብ/ሥ/ስ/ሕ/ቁ 2427 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የሚመራ ሲሆን ሟች ያደረጉት ስጦታ በህጋዊነቱ ይሁን ፎረማሊቲ የተነሳ ክርክር የለም፡፡ የተጠሪ ሞግዚት ስጦታው ውድቅ ለማድረግ እንደ ምክንያት ያቀረቡት ከስጦታ መደረግ በኂላ የተጠሪ መወለድን ነው፡፡የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት ክርክር ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2450 አንጻር እንደተመለከተው ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡የድንጋጌው ሙሉ ይዘት "በተደረገው የስጦታ ውል ውስጥ ተቃራኒ የሚሆን ቃል ከሌለ በቀር ስጦታ ከተደረገ በኂላ ልጅ በመውለዱ ምክንያት ስጦታውን ለመሻር አይቻልም"፡፡በማለት የተደነገገ ሲሆን የእንግሊዝኛው አቻ ትርጉም " unless otherwise provided in the contract of donation, a donation may not be revoked where a child is born to the donor" በሚል ተቀምጧል፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት እንደተመለከተው የስጦታ ውል ተቃራኒ ቃል ከሌለው በቀር የልጅ መውለድ የስጦታ ውሉን ለመሻር በቂ ምክንያት አለመሆኑን በግልጽ ተደንግጓል ሟች ሐምሌ 17 ቀን 1988 ዓ/ም ያደረጉት የስጦታ ውልም ለወ/ሮ ዙልፋ ከሚል ከመስጠት ውጭ ሌላ ቅድመ ሁኔታ የተቀመጠበት ስለመሆኑ ከመዝገቡ ጋር የተያያዘው የስጦታ ውል አያሳይም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የአሁኗ ተጠሪ በመውለዷ ምክንያት የስጦታ ውሉ የሚሽርበት የህግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ እና ሰበር ሰሚ ችሎት የስጦታ ውሉ የጸና ስለመሆኑ የፍርድ ቤት የጸና ውሳኔ በቀረበበት /ባለበት/ እና ልጅ መውለድ ስጦታ ለመሻር

www.abyssinialaw.com

ምክንያት እንደማይሆን በፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2450 በግልጽ በተደነገገበት ሁኔታ የሟች ስጦታ በዝምታ ተሽሯል ከሚል ድምዳሜ የደረሰው የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻራቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸማቸውን የሚያሳይ ነው ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የጌዶኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 09588 በሀምሌ 17 ቀን 2006 በዋለው ችሎት የዲላ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሐሮ ወለቡ ምድብ ችሎት በመ/ቁ/ 00670 በ18/02/2006 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ በመሻር የሰጠው ፍርድ፤ የደ/ብ/ብ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/63836 በ20/06/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 64413 በ18/09/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሮአል፡፡
2. በይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቁጥር 1303 ላይ ያለውን ይዞታና ቤት የአመልካቾች ሞግዚት ወ/ሮ ዙልፋ ከማል የግል ቤትና ይዞታ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የዲላ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 00670 በ18/02/2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ጸንቷል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.108638

ግንቦት 22 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡-አቶ መህቡብ ከድር -ጠበቃ ሂሩት ሂላይ ቀረቡ

ተጠሪ፡-የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ -ነ/ፈጅ መብራቱ ግርማይ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ክሳቸውን ውድቅ በማድረግ ፍርድ ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 209236 በ12/07/2006 ዓ.ም. የሰጠው እና በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 150986 በ05/02/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

አመልካች በ02/01/2006 ዓ.ም. አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘት በአራዳ ክፍለ ከተማ በወረዳ 2 የሚገኝ ቁጥሩ 507 የሆነውን የንግድ ቤት ከ18/12/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ከተጠሪ ተከራይተው ሲገለገሉበት ከቆዩ በኃላ የውሉ ዘመን ሲጠናቀቅ ውሉን ለማደስ አመልካች በ17/12/2005 ዓ.ም. ብር 246.00 የቴምብር ቀረጥ፣እንዲሁም እስከ ጥቅምት ወር 2006 ዓ.ም. ድረስ ያለውን የሁለት ወር ኪራይ የከፈሉ መሆኑን፣በዚህ ሁኔታ ተጠሪ ውሉን አራዝሞ ኪራይ ከተቀበላቸው በኃላ በ28/12/2005 ዓ.ም.በተጻፈ ደብዳቤ ውሉን ከ30/12/2005 ዓ.ም. ጀምሮ እንዳቋረጠ የገለጸላቸው መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ተጠሪ የውል ማደሻ እና የወደፊቱን ኪራይ ከተቀበለ በኃላ የፈጸመው የውል ማቋረጥ ተግባር ተገቢ አይደለም ተብሎ ውል እንዲቀጥል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ በ18/03/2006 ዓ.ም. በሰጠው

www.abyssinialaw.com

መልስ በ18/12/2004 ዓ.ም. የተደረገው የኪራይ ውል የሚቆየው ለአንድ ዓመት ብቻ መሆኑን፣ውሉ ከዚህ በኃላ ላለው ጊዜ የታደሰ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩን፣ የውሉ ዘመን ሲጠናቀቅ ተጠሪው ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን ለማቋረጥ የሚችል መሆኑን፣የቴምብር ቀረጥ የተከፈለውም ውሉን ለማራዘም ታስቦ ነው የሚያሰኝ አለመሆኑን እና አመልካች የቤቱን ኪራይ የከፈሉት በራሳቸው አነሳሽነት በመሆኑ የኪራዩ መከፈል የውሉን መታደስ የሚያረጋግጥ አለመሆኑን ገልጾ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክሱን ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ የመጀመሪያው ውል የጊዜ ቆይታ የተጠናቀቀ መሆኑን፣ውሉ የታደሰ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩን፣የውሉ ዘመን ካበቃ በኃላ የሁለት ወር ኪራይ ተከፍሎ መገኘቱም ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚያስቆጥር መሆኑን እና ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገን ውል ደግሞ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2966 በተመለከተው መሰረት አከራዩ ማስጠንቀቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ የሚችል መሆኑን ገልጾ የኪራይ ውሉ እንዲቀጥል እንዲወሰን የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ የኪራይ ውል ማደሻ ቅጽ ተሞልቶ የቴምብር ቀረጥ ክፍያ ከተፈጸመ በኃላ ጥፋት ተፈጽሟል ሳይባል ቀደም ብሎ የነበረው የኪራይ ውል እንዲታደስ አመልካች ካቀረቡት ክስ አንጻር የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በአግባቡ ያስተናገዱ መሆን አለመሆኑን ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ክርክሩ የተስተናገደበትን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ በማስቀረብ ጭምር አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርመረናል፡፡

በዚህም መሰረት በ18/12/2004 ዓ.ም. ለአንድ ዓመት ተደርጎ የነበረው የኪራይ ውል የቆይታ ጊዜ ያለቀ መሆኑ ያላከራከረ ሲሆን አመልካች ውሉ ለተጨማሪ አንድ ዓመት ታድሷል በማለት ቢከራከሩም ውሉ በዚህ አግባብ የታደሰ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ተጠሪው በ28/12/2005 ዓ.ም. ለአመልካች በጻፈው የውል ማቋረጫ ደብዳቤ ላይ ውሉን ማቋረጡን ከመግለጽ በቀር ውሉን ያቋረጠበትን ምክንያት አልገለጸም፡፡ተጠሪው በስር ፍርድ ቤት በሰጠው የጽሁፍ መልስ የውሉ ዘመን ሲያልቅ ውሉን የማቋረጥ መብት አለን በማለት የተከራከረ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው የውሉ ዘመን ካበቃ በኃላ የሁለት ወር ኪራይ ተከፍሎ መገኘቱ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚያስቆጥር መሆኑን እና ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገን ውል ደግሞ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2966 መሰረት አከራዩ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ የሚቻል መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ተጠሪው በሰበር ደረጃ በሰጠው መልስ የውሉን አንቀጽ 10 (2) እና (4) ድንጋጌዎች ጠቅሶ የተከራከረ ሲሆን እነዚህ

www.abyssinialaw.com

ድንጋጌዎችም የውሉ ዘመን ሲያልቅ ውሉ የሚቋረጥ መሆኑን እና የውሉ ዘመን ያላለቀ በሆነ ጊዜ ደግሞ አንደኛው ወገን በሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ውሉ ሊቋረጥ የሚችል መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

በመሰረቱ ቤቱ በኪራይ የተሰጠው ለንግድ ዓላማ ሲሆን ከተጠሪ ድርጅት ስልጣንና ተግባር መካከል አንዱ በይዞታው ስር የሚገኙትን የመንግስት ቤቶች ማከራየት እና ኪራይ መሰብሰብ ስለመሆኑ ኤጀንሲውን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6 (1) ስር ተመልክቷል፡፡ይህም ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችሉ ያልተጠበቁ ምክንያቶች ካልተከሰቱ እና በተለይ ደግሞ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል በተከራይ ወገን በኩል ጥፋት ተፈጽሟል ካልተባለ በቀር በተጠሪው ድርጅት እና በተከራዮች መካከል የሚደረጉ ውሎች በየዓመቱ እየታደሱ ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆዩ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡በመሆኑም በውሉ ውስጥ የተመለከቱት ከላይ የተጠቀሱት የውል ማቋረጫ ድንጋጌዎች፣እንዲሁም ተጠሪው በሕግ ያለው የመዋዋል መብትና ነጻነት ለኤጀንሲው በሕግ ከተሰጠው ስልጣን እና ተግባር አንጻር በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን የውሉ ዘመን ሲያልቅ ያለማስጠንቀቂያ፣እንዲሁም የውሉ ዘመን ያላለቀ በሆነ ጊዜ ደግሞ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ለተጠሪው ያለተገቢ እና ሕጋዊ ምክንያት የኪራይ ውሎችን ለማቋረጥ መብት እንደሚሰጡት ተደርገው ሊተረጎሙ የሚገባቸው አይደሉም፡፡በመሆኑም ተጠሪው በዚህ ረገድ ያቀረበው መከራከሪያ በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው በአግባቡ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪው ለዚህ ሰበር ችሎት በሰጠው መልስ ላይ አመልካች የንግድ ድርጅቱን የገዙት አቶ ድራር ገዛኢ ከተባሉ ኤርትራዊ ዜጋ መሆኑን እና ውሉም እንዲቋረጥ የተደረገው አመልካች የንግድ ድርጅቱን ካልተፈቀደለት ግለሰብ የገዙት በመሆኑ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ይሁን እንጂ ተጠሪው ይህንን የክርክር ነጥብ በስር የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በጽሁፍ መልሱም ሆነ ክሱ በተሰማበት ጊዜ አንስቶ ያልተከራከረበት መሆኑን ቀርቦ ከተያያዘው የስር መዝገብ ተገንዝበናል፡፡በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ እና ለውሳኔው መሰረት ያልተደረገ ክርክር ደግሞ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 329 (1) መሰረት አሁን በሰበር ደረጃ ሊስተናገድ የሚችልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተጠሪው ውሉን ስላቋረጠበት ምክንያት በውል ማቋረጫ ደብዳቤው ላይ የገለጸው ነገር ባይኖርም በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሉን ያቋረጠው ቤቱን ስለፈለገው እንደሆነ በመግለጽ የተከራከረ መሆኑን የስር መዝገብ ያመለክታል፡፡ይሁን እንጂ ተጠሪው በመደበኛ ሁኔታ የንግድ ቤቶችን የሚያስተዳድረው ለሶስተኛ ወገን በኪራይ እየሰጠ እንደመሆኑ መጠን ውሉን ያቋረጠው በርግጥም ቤቱን ለሌላ ተገቢ እና ሕጋዊ ምክንያት ፈልጎት ከሆነ

www.abyssinialaw.com

ይህንኑ ምክንያት  ጠቅሶ መከራከር የሚጠበቅበት ሆኖ ሳለ በደፈናው ውሉን ያቋረጥኩት ቤቱን ስለፈለግሁት ነው ከማለት በቀር የፈለገው ለምን ዓላማ እንደሆነ በግልጽ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ውሉን ያቋረጥኩት ቤቱን ስለፈለግሁት ነው የሚለውን የክርክር ነጥብ በዚህ ሰበር ደረጃ በሰጠው መልስ ውስጥም አላካተተም፡፡በመሆኑም ተጠሪው ውሉን ያቋረጠው ቤቱን ለማስለቀቅ የሚያስችል ተገቢ እና ሕጋዊ ምክንያት ኖሮት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 209236 በ12/07/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 150986 በ05/02/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት  ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪው ከአመልካቹ ጋር የነበረውን የኪራይ ውል ያቋረጠው በአግባቡ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 116961

ሐምሌ 19 ቀን 2008 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

**አመልካች** - ወ/ሮ አስቴር አርአያ

**ተጠሪ** - ወ/ሮ አወጣሽ መሐሪ - ጠበቃ ሐየሎም በቀለ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው የአሁን አመልካች ሰኔ 9 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ነው፡፡

የክሱ ይዘት፡- ባላቸው የጥብቅና ሙያ ተከሳሽ ከባለቤታቸው ከአቶ ወርቁ ወ/ማርቆስ ጋር የነበረባቸውን የፍች ክርክር እና የንብረት ክፍፍል ጉዳይ እንዲከታተሉላቸው በመፈለግ ታህሳስ 19 ቀን 1999 ዓ.ም በተደረገ የጥብቅና አገልግሎት ውል በንብረት ክፍፍሉ ተከሳሽ ከሚደርሳቸው ድርሻ 10% (አስር በመቶ) ለመክፈል ተስማምተው ስራውን በመጀመር የፍች ውሳኔ በማሰጠት፤ የንብረት ክፍፍል አቤቱታ በማቅረብ እና በአፈፃፀም ጉዳዩ እስከ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ሁለት ጊዜ ደርሶ ሲመለስ ተከታትለው የተከሳሽን መብት ለማስከበር ከ8 ዓመት በላይ ስራውን በአግባቡ በመስራት ግዴታቸውን እንደተወጡ፤ ተከሳሽ መጋቢት 25/2006 ዓ.ም ባደረጉት የዕርቅ ስምምነት ድርሻቸውን ብር 11,000,000.00 (አስራ አንድ ሚሊዮን) በመቀበል ክርክሮችን በሙሉ እንዳቋረጡ፤ ከዚህ በኋላ ግራ ቀኙ ባላቸው የአገልግሎት ውል ስምምነት መሰረት ክፍያ እንዲፈፅሙ እና መዝገቦችን እንዲረከቡ ቢጠየቁም ፈቃደኛ ስላልሆኑ በውሉ መሰረት ካገኙት ገንዘብ አስር በመቶ ብር 1,100,000.00 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ.ህ) ከነወለዱ እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ ከከሳሽ ጋር የጥብቅና አገልግሎት ውል እንደነበራቸው፤ በውሉ እንደተመለከተውና በክሱም እንዳልካዱት ብር 65,000.00 (ስድሳ አምስት ሺ.ህ) የወሰዱ በመሆኑ ይህን ሳይቀንሱ የጠየቁት ክፍያ አግባብነት እንደሌለው፤ እንዲሁም ከሳሽ በገቡት ግዴታ መሰረት ባለመወጣታቸው ጉዳዩ ረጅም ጊዜ ስለተጓተተና በአግባቡ እንዲከታተሉ ሲጠየቁም ግዴታዬን ተወጥቻለሁ በማለት ዶክመንቶችን ጥለው በመሄዳቸው ሌላ ጠበቃ በመቅጠር ክርክር የቀጠሉ መሆኑን፤ ከዚያ በኋላ ብር 11,000,000.00 (አስራ አንድ ሚሊዮን) በመውሰድ ጉዳዩን

በዕርቅ እንደጨረሱት፤ ተከሳሽም ከሳሽ በውሉ መሰረት ጉዳዩን ሳይጨርሱ ቢያቋርጡም እስከሰሩበት ጊዜ ሊከፈላቸው የሚገባ መሆኑን በማመን ከሳሽ ብር 800,000.00 (ስምንት መቶ ሺ.ህ) ጠይቀው በመጨረሻ ብር 750,000.00 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) ለመክፈል በመስማማት ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ልደታ ቅርንጫፍ በመሄድ ተከሳሽ ቁጥሩ 1000043340011 ከሆነ የቁጠባ ሂሳባቸው ሚያዝያ 16 ቀን 2006 ዓ.ም ብር 750,000.00 (ሰባት መቶ ሃምስ ሺ.ህ) ወጪ አድርገው ከሳሽ በዚያው ባንክ ሂሳብ እንዲከፍቱ ተደርጎ ብር 600,000.00 (ስድስት መቶ ሺ.ህ) ወደ ሂሳባቸው እንዲተላለፈላቸው የተደረገ ሲሆን ቀሪውን ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) በእጃቸው እንደተሰጡ፤ በዚህ መልኩ ተከፍሏቸው እያለ ከሳሽ አልተከፈለኝም በማለት የጠየቁት አግባብነት እንደሌለው፤ በውሉ መሰረት ከተከሳሽ ድርሻ 10% (አስር በመቶ) ለከሳሽ ሊከፈል የሚገባው ጉዳዩን ተከታትለው አስጨርሰው ንብረት ሲያስረክቡ ብቻ እንደሆነ በመግለፅ ከሳሽ በአጠቃላይ ብር 815,000.00 (ስምንት መቶ አስራ አምስት ሺ.ህ) የተቀበሉ በመሆኑ እና ቀሪውም ሊከፈላቸው የማይገባ በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተከሳሽ ብር 65,000.00 (ስድሳ አምስት ሺ.ህ) አስቀድመው የከፈሉ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረቧቸው ምስክር ተከሳሽ ገንዘቡን ለከሳሽ ከፍያለሁ በማለት በስልክ ሲነጋገሩ መስማታቸውን ከሚገልፁ በቀር ስለመክፈላቸው ሌላ ማስረጃ ስላላቀረቡ ተከሳሽ ከሚጠበቅባቸው ክፍያ ውስጥ ብር 65,000.00 (ስድሳ አምስት ሺ.ህ) እንዲከፍሉ፤ በባንክ ቀርበው ክፍያ መፈፀሙን በተመለከተ የቀረበውን ክርክር ለማጣራት ፍርድ ቤቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ልደታ ቅርንጫፍ ስለጉዳዩ ማብራሪያ እንዲሰጥ ጠይቆ ባንኩ በቁጥር ልደ/ዳአ/026/1/15 በቀን 18/5/2007 ዓ.ም በሠጠው ምላሽ ተከሳሽ ሚያዝያ 16 ቀን 2006 ዓ.ም ብር 750,000.00 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) ከሂሳባቸው እዳወጡ እና በዕለቱም በከሳሽ ስም ሂሳብ ተከፍቶ ብር 600,000.00 (ስድስት መቶ ሺ.ህ) ወደ ሂሳባቸው ገቢ እንደተደረገ መግለፁን፤ ይህም የተከሳሽን ክርክር የሚያጠናክር አስረጅ ሆኖ መገኘቱን፤ ከዚህም ሌላ ገንዘቡ በከሳሽ ሂሳብ ገቢ መደረጉን እና ቀሪው ገንዘብ በእጃቸው የተሰጣቸው መሆኑን ያውቃሉ ተብለው በእለቱ የገንዘብ ልውውጡን የሰሩት የባንክ ባለሙያ አቶ ደረጀ ካሳ ቀርበው በሚያዝያ ወር 2006 ዓ.ም ተከሳሽ በባንኩ ቀርበው ብር 750,000.00 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) ከሂሳባቸው አውጥተው ብር 600,000.00 (ስድስት መቶ ሺ.ህ) በዕለቱ ወደተከፈተው የከሳሽ ሂሳብ ገቢ እንደተደረገና ብር 150,000.00 (መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) በጥሬ ገንዘብ ለከሳሽ የተሠጠ መሆኑን እንደሚያውቁ መመስከራቸውን፤ ስለሆነም ባንኩ በሰጠው መግለጫ እና ሂሳቡን የሰሩት ባለሙያ ከሰጡት የምስክርነት ቃል ተከሳሽ በአጠቃላይ ብር 750,000.00 (ሰባት መቶ ሃምስ ሺ.ህ) የከፈሉ መሆኑ በመረጋገጡ ይኸው ገንዘብ ከሳሽ ከጠየቁት ክፍያ ሊቀነስ እንደሚገባ፤ በሌላ በኩል ከሳሽ ጉዳዩን ተከታትለው ያላስጨረሱ በመሆኑ ቀሪው ክፍያ ሊከፈላቸው እንደማይገባ ተከሳሽ ቢከራከሩም ፍርድ ቤቱ ክርክር የተደረገባቸውን መዝገቦች በትዕዛዝ አስቀርቦ እንደተመለከተው ከሳሽ

www.abyssinialaw.com

በየቀጠሮው ይከራከሩ እንደነበር እና ከሳሽ ውሉን ከፈረሙበት 1999ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ ለ 7 ዓመታት ተከሳሽን በመወከል የተከራከሩ መሆኑ ስለተረጋገጠ ተከሳሽ በውሉ መሰረት አገልግሎት አልሰጡኝም በማለት የሚያቀርቡት መከራከሪያ ተቀባይነት እንደሌለው፤ ስለሆነም ቀሪውን ክፍያ ብር 285,000.00 (ሁለት መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ) ሊከፍሉ ይገባል ብሏል፡፡ በአጠቃላይ ተከሳሽ ብር 285,000.00 + ብር 65,000.00 = ብር 350,000.00 (ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ) ተከፍሎ እስኪጠናቀቅ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍሉ፤ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን እንዲቻቻሉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ለአመልካች ብር 750.000.00 (ሰባት መቶ ሃምስ ሺህ) ስለመክፈላቸው በፍ/ብ/ህ/ቁ/2472(2) እና (3) በተደነገገው መሰረት ሊቀርብ በሚገባው ማስረጃ ማለትም ደረሰኝ ወይም የሰነድ ማስረጃ አቅርበው ሳያረጋገጡ ይኸው ገንዘብ መከፈሉ ተረጋግጧል ተብሎ መወሰኑ ስህተት በመሆኑ ታርሞ ገንዘቡን ከነወለዱ እንዲከፍሉ እንዲወሰን፤ እንዲሁም የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብቴ ሊጠበቅ ሲገባ ይቻቻሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉን ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ ዝርዝር የማቅረብ መብቴ ተጠብቆ ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካች ቀደም ሲል የተከፈላቸውን ብር 750.000.00 (ሰባት መቶ ሃምስ ሺህ) ሙያዊ ኃላፊነታቸውን ወደ ጎን በመተው ለሁለተኛ ጊዜ እንዲከፈላቸው ክስ ማቅረባቸው የሚያሳዝን እና የሙያውን ክብር የሚያዋርድ በመሆኑ፤ ወጪና ኪሳራን በተመለከተ ያቀረቡት ጥያቄም እንደነገሩ ሁኔታ ለመወሰን ፍርድ ቤቱ ሙሉ ስልጣን ያለው በመሆኑና በጉዳዩም ረችና ተረቺ ባለመኖሩ ይኸው ግምት ውስጥ ገብቶ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ተብሎ መወሰኑ ምንም ስህተት ስላልተፈፀመበት ቅሬታው ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ክርክራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከላይ ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ እና በሰበር የተደረገውን ክርክር ሲሆን ክርክሩን ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌ ጋር በማያያዝ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው የአመልካች መሰረታዊ ክርክር ብር 750.000.00 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ) ስለመከፈሉ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባልቀረበበት መከፈሉ ተረጋግጧል ተብሎ በስር ፍርድ ቤት መወሰኑን የሚመለከት ነው፡፡ በመሰረቱ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን የመጨረሻ ውሣኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን እንዳለው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እንዲሁም በፌዴራሉ ፍርድ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ሥር ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን የሰበር ችሎቱ የግራ ቀኝ ማስረጃዎችን ጥንካሬ በመመዘንና በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥ የቀረበው አቤቱታ

www.abyssinialaw.com

መሠረታዊ የህግ ስህተት ለማረም ከላይ በተጠቀሱት ህጎች ለችሎቱ የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት የተከተለ ባለመሆኑ የምንቀበለው አይሆንም፡፡

በሌላም በኩል አመልካች ገንዘቡ ስለመከፈሉ በፍ/ብ/ህ/ቁ/2472(2) እና (3) በተደነገገው መሰረት ሊረጋገጥ እንደሚገባ የተከራከሩ ሲሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የጥብቅና አገልግሎት ውል እንጂ የብድር ውል ባለመሆኑና የፍ/ብ/ህ/ቁ 2472 ከብድር ውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ከተከፈለ ገንዘብ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚ የሚሆንበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ ይኸው ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 64397 እና ሌሎችም ተመሳሳይ መዛግብት የሠጠው አስገዳጅ ትርጉም ለተያዘውም ጉዳይ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው ከአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2 ድንጋጌ መረዳት ስለሚቻል በዚህም ረገድ የቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

በአጠቃላይ ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በህግ ስልጣኑ የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት ከተጠየቀበት ገንዘብ ውስጥ ብር 750.000.00 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) ለአመልካች አስቀድሞ ስለመከፈሉ በማስረጃ በማረጋገጥ ውሳኔ ላይ መድረሳቸውን ተገንዝበናል፡፡ አግባብነት እና ተቀባይነት ባለው ማስረጃ የተረጋገጠው ገንዘቡ አስቀድሞ መከፈሉ ከሆነ ደግሞ ይኸው ገንዘብ አመልካች ከጠየቁት ክፍያ ሊቀነስ እንደሚገባ በመወሰኑ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚያሰኝ አይሆንም፡፡

የስር ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ በማለት ያሳለፈው ውሳኔም የስነ ስርዓት ህጉን የተከተለ አይደለም በሚል ውሳኔው እንዲታረም ቅሬታ ቀርቧል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 462 እንደተደነገገው በክርክር ምክንያት የወጣን ወጭና ኪሣራ ማን እንደሚከፍልና ምን ያህል እንደሚከፍል ፍ/ቤቱ በመሰለው ሊወስን እንዲችል ፍቅድ ስልጣን ተሰጥቶታል ፡፡ ፍርድ ቤቱ በህጉ የተሰጠውን ፍቅድ ስልጣን ተጠቅሞ ሲወስን ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸውን ጉዳዮች ሁሉ ተመልክቶና አረጋግጦ ሊወስን እንደሚገባ በህጉ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች እንዲከፈላቸው ከጠየቁት ገንዘብ ከፊሉን አስቀድመው ስለወሰዱ በሙሉ ሊከፈላቸው እንደማይገባ፤ በአንፃሩ ተጠሪ ብር 350,000.00 (ሶስት መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) ከነወለዱ እንዲከፍሉ በመወሰኑ ባለዕዳ መሆናቸውን፤ አመልካች በራሳቸው ተጠሪ ደግሞ በጠበቃ ተወክለው መከራከራቸውን እና የነገሩን አጠቃላይ ሁኔታ በማየት ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ውሳኔ እና ትዕዛዝ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ/ 153169 ሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 116173 ሐምሌ 27/2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በተጠሪ ቤት ላይ በዚህ ፍርድ ቤት የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ.ም የተላለፈው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው ሁሉ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 114553

ሐምሌ 29ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ኤልያስ ስሜ ተሰማ ………… አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዘነበች ተመስገን ጫካ………….. አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 198148 በቀን 08/09/2005 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 140263 በቀን መጋቢት 15/2007 ዓ.ም ያፀናው በመሆኑ መሠታዊ ስህተት ያለበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የብድር ውልን የሚመለከት ነው በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት ተጠሪ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የክሱ ይዘት ጥቅምት 28/2004 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል አመልካች ነሐሴ 30/2004 ዓ.ም ለመመለስ ብር 200,000 ተበድረው ወስደው ሊመልሱ አልቻሉም ስለዚሀ ዋናውን ገንዘብ፣ ወለድ፣ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍሉኝ የሚል ሲሆን አመልካች በሰጡት መልስ ከተጠሪ ጋር ገንዘብ ሊያስበድር የሚችል ትውውቅ የለንም አመልካች በመ/ቁ 198149 በተጠሪ ባለቤት ክስ የቀረበባት ወ/ሮ መስከረም አሰግድ ሰፊ ቦታ ገዝተን አርት ጋለሪ መስራት በመፈለጋችን በኮሚሽን ሠራተኞች አማካኝነት በተጠሪ ባለቤት አቶ ደጁ አበራ ስም የተመዘገበውን በብር 700000 ለመግዛት ተስማምተን በተፈራረምነው የቤት ሽያጭ ውል ላይ ግን ብር 400000 በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት የተገዛው ብር 500000 ቢሆንም በውልና ማስረጃ በተደረገው የሽያጭ ውል የተጻፈው ብር 300000 ሲሆን ከዚህ በኋላ የከረረ ፀብ ውስጥ ነን

www.abyssinialaw.com

ውሎቹ በአንድ ኮምፒውተር መጻፋቸው ሙሉ ፊርማዬ በሰነድ ላይ ያለው አይደለም፡ ብፊርም ኖሮ ሙሉ ስሜን ከጐን እጽፍ ነበር አጭር ፊርማዬን ለማስመሰል የተሞከረ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ማጣራት ይችላል ስለሆነም ክሱ በሀሰት የቀረበብኝ በመሆኑ ኪሳራ ተከፍሎ በነፃ ልሰናበት ብለዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ የአመልካች ፊርማ በፌደራል ፖሊስ ፎረንሲክ ምርመራ መምሪያ እንዲጣራ ተደርጐ ምስክሮችን ሠምቷል፡፡ በአመልካች በብድር ውሉ ሊገደዱ የሚችሉት የብድር ውሉን ከፈፀሙ ነው፡፡ በጽሁፍ የተደረገውን የብድር ውል በሰው ማስረጃ ማስተባበል አይቻልም፡፡ አመልካች የብድር ውሉን አልፈፀምኩም የሚሉት ፊርማውን በመካድ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ፊርማው እንዲመረመር አዞ በአመልካች የተፈረመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በተጠሪና በአመልካች መካከል የብድር ውል መደረጉን የሚያረጋግጥ ሲሆን በውሉ ላይ ያሉ ምስክሮቹም የብድር ውሉ መደረጉን አረጋግጠዋል፡፡ ስለሆነም ክስ የቀረበበትን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ብር 200000 ከነሐሴ 30 ቀን 2004 ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ እንዲሁም ወጪና ኪሳራ ብር 4850 ለቴምብርና ቀረጥ ብር 10 ለጥብቅና አገልግሎት ብር 15,000 እንዲከፍል ብሏል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንን በመቃወም መሠረታዊ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ሲሆን ይዘቱም ሙሉ ፊርማዬ በሰነዱ ላይ ያለው አይደለም፡፡ አጭር ፊርማ ስፈርም ስሜን ከጐን አልጽፍም ስለዚህ አጭር ፊርማዬን ለማስመሰል የተደረገ ጥረት መኖሩን ሠነዱ ያስረዳል በፍ/ሕ/ቁ 1728/1/ ፊርማ በውሉ ተገዳጅ የሆነ ሰው እጅ መጻፍ እንዳለበት የተደነገገ በመሆኑና የሠነድ ምርመራ ውጤትም የመጨረሻ ማስረጃ ባለመሆኑ ባልተሟላ ፊርማ የተወሰነ በመሆኑ መሠረታዊ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በሠነዱ ተዓማኒነት ላይ የተነሱትን ክርክሮች የስር ፍርድ ቤት ሳይመረምር ማለፉ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182/2/ መሠረት የውል ስምምነቱ አጠራጣሪ በሚሆንበት ጊዜ ተገዳጅ የሆነውን በሚጠቅም መልኩ መታየት እንዳለበት ከተደነገገው አኳያ ሳይታይ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ የቀረቡት ምስክሮች አመልካችና ተጠሪ የብድር ውሉን አለመፈፀማቸውን፣ አመልካችም ከተጠሪ ገንዘብ መበደር ደረጃ የሚያደርስ ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ይግባኙን የተመለከተው ፍርድ ቤትም ከቀረበው ክርክርና ማስረጃ ውጭ ስለጭብጥ አመሠራረት የተደነገገውን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የአመልከች ፊርማ የለም እየተባለ በግራ ቀኙ መካከል የብድር ውል አለ መባሉንና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ለመመርመር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በሰጡት መልስ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የብድር ውል እና የሽያጭ ውል በተመሳሳይ ቀን ተደርጓል ምስክሮቹም አንድ ናቸው፡፡ፍርድ ቤቱም እነዚህኑ አስቀርቦ ሰምቷል፡፡ አመልካች እኔ ስፈርም

www.abyssinialaw.com

ከጉኑ ስሜን እጽፋለሁ ብለው ክደው ቢከራከሩም ፊርማው በፎረንሲክ ተመርምሮ ፊርማቸው መሆኑ ተረጋግጧል ፍርድ ቤቱ በተጨማሪ በውሉ ላይ የተመለከቱትን ምስክሮችንም ሠምቶ አረጋግጧል፡፡ ይህንን አላስተባበሉም አመልካች ከተጠሪ የተሻለ እውቀት ያላቸው ባለሙያ ናቸው የውል ክፍሉ ሳያነቡላቸው እና ሳያረጋግጡ የሚፈርሙ አይደሉም ፊርማው የአመልካች መሆኑ እስከተረጋገጠ ሙሉ ፊርማ እና አጭር ፊርማዬ በማለት ከኃላፊነት ማምለጥ አይችሉም ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ይጽናልኝ ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘበ የሚቻለው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ጥቅምት 28 ቀን 2004 ዓ.ም ተደርጓል የተባለውን የብር 200000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ ብድር ውል ላይ አመልካች ከተጠሪ ገንዘብ ለማስበደር የሚያደርስ ትውውቅ የለንም በውሉ ላይ የተመለከተው ፊርማ የኔ አይደለም ልገደድ አይገባም ሲሉ ተጠሪ በመካከላችን በነበረው መኖርያ ቤት ሽያጭ ውል ከአጠቃላይ ገንዘቡ 100000 /አንድ መቶ ሺ ብር ከፍለውኝ/ ቀሪውን ብር 200000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ በብድር ውል ለነሐሴ 30/2004 ዓ.ም ለመመለስ ተስማምተናል የሚል ነው፡፡ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ውል አለ ለማለት ከሚያስችሉት ነጥቦች አንዱ ደግሞ በፍ/ሕ/ቁ 1728 እንደተመለከተው በውሉ ተገዳጅ የሆነው ሠው እጅ የተጻፈ ፊርማ መኖር ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ደግሞ ፊርማው የተካደ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ እዚህ ላይ ተበዳሪው በፍትሐብሔር ህግ ቁ. 2472/1/ መሠረት የብድር ውሉን ለማስረዳት በቀረበው የሰነድ ማስረጃ ላይ ያለው ፊርማ የእኔ አይደለም በማለት የካደ በሆነ ጊዜ ፊርማው የተበዳሪ መሆኑን ለማረጋገጥ ምን ዓይነት ማስረጃ ተቀባይነት አለው የሚለው በሰነድ ላይ ያሉ ፊርማዎችን ለማረጋገጥ /Authenticate/ ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

በሰነድ ላይ ያለ ፊርማ በተካደ ጊዜ ፊርማውን የማረጋገጫው የመጀመሪያው መንገድ የቴክኒክ ምርመራ እንዲደረግ ማድረግ ነው፡፡ ሆኖም ፊርማው በቴክኒክ ምርመራ የማን እንደሆነ ለማረጋገጥ ባልተቻለ ጊዜ ፊርማው ሲፈረም የነበሩ ምስክሮችን ቃል በመስማትና በሌሎች ማስረጃዎች ፊርማው የማን እንደሆነ በመመዘን ማረጋገጥ እንደሚቻል ከማስረጃ ምዘና ጠቅላላ መርሆዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ፊርማውን በመካዳቸው ምክንያት ለፌደራል ፖሊስ ፎረንሲክ ምርመራ መምሪያ በኩል የቴክኒክ ምርመራ እንዲደረግ አዞ የአመልካች ፊርማ ስለመሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን ገልጿል ፍርድ ቤቱ በአመልካች የተፈረመ መሆኑ በቴክኒክ ምርመራ መረጋገጡ ሳያበቃ ሁለተኛውን አማራጭም በመከተልም በውሉ ላይ

www.abyssinialaw.com

ያሉትን ምስክሮች በመስማት ፊርማው በአመልካች የተፈረመ ስለመሆኑ ፍሬ ነገርንና ማስረጃን በሚመዝንበት ወቅት አረጋግጧል፡፡ አመልካች ፊርማው አጭር እና ረጅም ሲሆን የሚፈጥሯቸውን ልዩነቶች በመግለጽ ከመከራከር ውጭ ፊርማውን የፈረመው በሌላ ህጋዊ ተጽዕኖ ወይም ግዴታ ምክንያቶች መሆኑን መሠረት በማድረግ አልተከራከረም፡፡ ፊርማ ሀሳብን ወይም ፈቃድ መስጠትን የሚረጋገጥበት በመሆኑ በአመልካች የተፈረመ መሆኑ ከተረጋገጠ አጭር እና ረጅም መሆኑ ደግሞ በውጤቱ ላይ ልዩነት አያመጣም፡፡ በሌላው በብድር ውሉ ስምምነት ላይ የመክፈያ ጊዜው ተወስኖ የተቀመጠ በመሆኑ አመልካች በፍ/ሕ/ቁ 2482/2/ /3/ መሠረት የመመለሻ ጊዜው ከማለፉ በፊት የመክፈል ግዴታ ያለበት በመሆኑ አለመክፈሉ እስከተረጋገጠ ጊዜ ድረስ የብድሩን ገንዘብ ህጋዊ ወለድ ጋር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የብድር ውል አለ በማለት በውሉ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ ከነወለዱ አመልካች እንዲከፍል በማለት የደረሱበት ድምዳሜ መሠረታዊ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 198148 በቀን 08/09/2005 እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 140263 መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

## ትእዛዝ

የስር ፍርድ ቤት በአፈ/መ/ቁ 23365 የጀመረው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በ17/02/2008 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ሩ/ለ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 117036

ህዳር 12 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ፀጉብርሃን ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ኮሎኔል ይትባረክ አማረ - ከጠበቃ ኃይለስላሴ ገ/መድህን ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የሽያጭ ውሉን በወቅቱ ባለመፈፀሙ በኃላፊነት ይጠየቃል በማለት አመልካች የመኪና ሽያጭ ውሉን ባለመፈፀሙ ተጠሪ ላይ የደረሰበት ጉዳት ተጣርቶ እንዲቀርብ በማለት የሰጡት ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ /ከሳሽ/ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡
2. ከሳሽ ለስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል፣ ከተከሳሽ ሁለት ተሽከርካሪዎችን ለመግዛት ተዋውሎ፣ የሁለቱን መኪኖች ዋጋ ብር 2,300,000 /ሁለት ሚሊዬን ሶስት መቶ ሺህ ብር/ ገቢ አድርጌአለሁ፡፡ ተከሳሽ መኪኖቹን ውሉን ከተፈራረምንበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት የስራ ቀናት ማለትም እስከ ነሐሴ 27 ቀን 2006 ዓ.ም ሊያስረክበኝ የውል ግዴታ ገብቷል፡፡ ከሳሽም መኪኖቹ ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሰጥቶኛል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ በውሉ መሠረት መኪኖቹን ያላስረከበኝ በመሆኑ፣ ከሳሽ የከፈልኩትን ገንዘብ እንዲከፍል

ይወሰንልኝ፡፡ ከሳሽ ከነሐሴ 27 ቀን 2006 ዓ.ም መኪኖቹን እረከባለው በሚል እምነት አንድ ተሽከርካሪ በወር ብር 3000 /ሶስት ሺህ ብር/ ሁለቱን በብር 6000 /ስድስት ሺህ ብር/ አከራይቼ አገኝ የነበረውን ጥቅም ስለቀረብኝና በዚህ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ብር 354,000 /ሶስት መቶ ሀምሳ አራት ሺህ ብር/ እንዲከፍልና ዕዳው ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ በወር ብር 6000 /ስድስት ሺህ ብር/ እየተሰላ ካሣ እንዲከፍል፤ የወሰደውን ገንዘብ ወለድ እንዲከፍልና፣ የገደብ መቀጮ ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡

3. አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ለከሳሽ ሁለት መኪኖች ለመሸጥና የመኪኖችን ዋጋ ከሳሽ መክፈሉ የሚካድ አይደለም፡፡ ተከሳሽ ለከሳሽ መኪኖችን ለማስረከብ የተለያዩ ተግባራትን ከከሳሽ ሰራተኞች ጋር በመተባበር ሲፈጽም ቆይቷል፡፡ መኪኖችንም በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ለማስረከብ ፈቃደኛ ነበር፣ ነገር ግን በመዝገብ ቁጥር 24172 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ.ም በመኪኖቹ ላይ የዕግድ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የዕግድ ትዕዛዙን በመቃወም ተከሳሽ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቤ በመዝገብ ቁጥር 157145 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ አፅንቶታል፡፡ በመሆኑም በሽያጭ ውሉ መሠረት ያልተፈፀመው ተከሳሽ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት የፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ በመሆኑ ከሳሽ ለውሉ አለመፈፀም ተከሳሽ ኃላፊ እንዲሆንና ካሣ እንዲከፍል ለማለት ያቀረበው ክስ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ በሽያጭ ውሉ አለመፈፀም ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ የሚያስቀጣ መሆኑ ከሳሽ ካሣ ይክፈለኝ በማለት የጠየቀው ተገቢ አይደለም የሚሉና ሌሎች መከራከሪያዎችን በማንሳት መልስ ሰጥቷል፡፡

4. የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተከሳሽ ለከሳሽ ከሰጣቸው ሁለት መኪኖች መካከል የአንደኛው መኪና የሳንሲ ቁጥር lzz5ewd77n847969 እና የሞተር ቁጥር 131107038497 መሆኑ ከሳሽ ባቀረበው የሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ ከከሳሽ ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም በመሸጥ ሙሉ ዋጋውን የተቀበለበት የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተጠቀሰውን መኪና ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገ ውል ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠው መኪና መሆኑ ተረጋግጣል፡፡ ይህም ተከሳሽ ለከሳሽ የሸጠውን አንደኛው መኪና የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ ተለይቶ የታወቀውን መኪና ለከሳሽ በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚያስችል መብት ሳይኖረው የፈፀመው የሽያጭ ውል በመሆኑ ለውሉ አለመፈፀምም ሆነ በከሳሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ተከሳሽ ኃላፊነት አለበት፡፡ በሌላ በኩል ተከሳሽ ብር 3000,000 /ሶስት ሚሊዬን ብር/ አስይዞ ዕግዱን በማስነሳት መኪኖቹን ለከሳሽ ማስረከብ እየቻለ ይህንን ያላደረገ በመሆኑ ለሽያጭ ውሉ ኃላፊ ነው በማለት ከሳሽ የከፈለውን የመኪኖቹን ዋጋ ከዘጠኝ ፐርሰንት

www.abyssinialaw.com

ወለድ ጋር እንዲመልስ በውሉ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ እንዲከፍልና በውሉ አለመፈፀም ምክንያት በከሳሽ ላይ የደረሰበት ኪሣራና /ጉዳት ተጣርቶ/ እንዲቀርብ በማለት በመዝገብ ቁጥር 153576 ሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ከፊል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአመልካችን ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

5. አመልካች ነሐሴ 5 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ከሸጣቸው ሁለት መኪኖች አንደኛው ቀደም ሲል ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠው መሆኑን በመግለጽ ውሳኔ የሰጠው በማስረጃ ያልተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪም ጋር ሆነ ከአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ ጋር በተዋዋለው የመኪና ሽያጭ ውል ላይ የመኪና የቫንሲ ቁጥርና የሞተር ቁጥር አልጠቀሰም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 223፤አንቀጽ 137/1 እና አንቀጽ 256 መሠረት ያላቀረበውን የሰነድ ማስረጃ በመቀበል አመልካች አንደኛውን መኪና ለተጠሪ ያላስረከበው ቀደም ብሎ መኪናውን በሽያጭ ለሌላ ሰው ስለሸጠው ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የማስረጃ አቀራረብ ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ የሰጣቸውን ሁለት መኪኖች ለተጠሪ ሳያስረክብ የቀረው በባልና ሚስት ክርክር መነሻ መኪኖቹ እንዳይሸጡ እንዳይለወጡና ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ በመስጠቱና የዕግድ ትዕዛዙን ለማስነሳት አመልካች ጥረት ቢያደርግም ጥረቱ ውጤት አልባ በመሆኑ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ስለገጠመው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የከፈለውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል ውሣኔ ከሰጠ በኃላ የሽያጭ ውሉ ያለመፈፀሙ ተጠሪ ላይ ያደረሰውን ኪሳራ አመልካች የመሸፈን ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች ተጠሪ ወሉን ያልፈፀመ ወገን ምንያህል ገንዘብ መክፈል እንዳለበት ውል ተዋውለዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በውሉ የተረጋገጠውን የገደብ መቀጫ ማስከፈል ሲገባው ከገደብ መቀጫው አልፎ ለተጠሪ አመልካች ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

6. ተጠሪ በበኩሉ ህዳር 8 ቀን 2008 ዓ.ም በተሰጠ መልስ አመልካች ለተጠሪ ነሀሴ 7 ቀን 206 ዓ.ም በተደረገው የሽያጭ ውል ከሸጣቸው መኪናዎች ውስጥ የአንደኛውን የሻንሲና የሞተር ቁጥር በመግለጽ ለገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን ያሳወቀ በመሆኑ ተጠሪ ከገዛቸው መኪናዎች ውስጥ የአንደኛው መኪና የሻንሲ እና የሞተር ቁጥር ተለይቶ የታወቀ ነው፡፡ ሆኖም አመልካች በተጠሪ ከሰጣቸው መኪናዎች ውስጥ ይህንን የሻንሲና የሞተር ቁጥሩን ለይቶ ያሳወቀውን መኪና ቀደም ሲም ሲል ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም

www.abyssinialaw.com

በተደረገ ውል ለአቶ ግደይ ገ/ፃድቅ የሸጠውና ይህንኑ መኪና ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ ለማስረከብ የሚችል መሆኑን ገልጾ የፃፈው ደብዳቤ የአመልካች ስራ አስኪያጅ በፈፀመው የማታለል ወንጀል ክስ የቀረበበት መሆኑንና አቶግደይ ገ/ፃዲቅ አመልካች የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተገለፀውን መኪና እንዲያስረክባቸው ከፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 153390 ክስ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ጳጉሜ 5 ቀን 2006 ዓ.ም እና መስከረም 12 ቀን 2007 ዓ.ም የዕግድ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎች መኖራቸውን ያወቅነው ክሱንና የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ለፍርድ ቤቱ ካቀረብን በኃላ በመሆኑ ማስረጃዎቹን የስር ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 256 መሠረት እንድናቀርብ ፈቃድ ጠይቀን በፍርድ ቤቱ ፍቃድ መሠረት ያቀረብናቸው የሰነድ ማስረጃዎች በመሆናቸው አመልካች የስር ፍርድ ቤት ከሥነ-ሥርዓት ሕግ ውጭ ማስረጃ እንደተቀበለ በመግለጽ ያቀረበው አቤቱታ የህግ መሠረት የለውም፡፡ ሌላውን መኪና በተመለከተ አመልካች ብር 3000,000 /ሶስት ሚሊዬን ብር/ በማስያዝ ዕግዱን ማስነሳትና የውል ግደታውን መወጣት እየቻለ ይህንን ሳያደረገም አመልካች ውሉን ያልፈፀመው በፍርድ ቤቱ ዕግድ ምክንያት አይደለም ስለሆነም ውሉን ያልፈፀምኩት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የወሰደውን ገንዘብ ወለድ ተጠሪ በውሉ አለመፈፀም የደረሰበትን ኪሳራና በውሉ ላይ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ እንዲከፍል የተወሰነው በአግባቡ ነው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሰ አቅርቧል፡፡

7. ይኸ ሰበር ችሎት አመልካችና ተጠሪ በቃል ሊከራከሩባቸው የሚገቡ ነጥቦችን ሰኔ 22 ቀን 2008 ዓ.ም ለይቶ ለግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲደርሳቸው ካደረገና በተለያየ ምክንያት የቃል ክርክር ለማስማት የሰጠውን ቀነ ቀጠሮ ከተለወጠ በኃላ የቃል ክርክሩን የመጨረሻ ቀነ ቀጠሮ በሰጠበት ጥቅምት 24 ቀን 2009 ዓ.ም አመልካች ወኪል ወይም ጠበቃ ባለመቅረቡ የተጠሪን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ አመልካች ስለ ማስረጃ አቀራረብ ሥርዓትና ሌሎች ነጥቦች የቀረበውን የሰበር ክርክር ለማረጋገጥና ለማገናዘብ እንዲቻል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 153516 እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ መዝገቡን በትዕዛዙ መሠረት በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡

8. ከስር የክርክር አመጣጥና ግራቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው ሁለት ገልባጭ መኪኖች ሽያጭ መሠረት ለተጠሪ የሚያስረክበው መሆኑን ገልጾ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በፃፈው ደብዳቤ የገለፀውና ያሳወቀው የሻንሲ ቁጥር lzz5ewd77n847969 የሆነውና የሞተር ቁጥሩ

www.abyssinialaw.com

131107038497 የሆነውን መኪና ቀደም ብሎ ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠውና ይህንኑ መኪና ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ ለማስረከብ እንደሚችል ገልጸ ደብዳቤ የፃፈበት መሆኑን በአጠቃላይ መኪናውን ለሁለት ሰው በመሸጥ ዋጋ የተቀበለበት መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተረጋግጧል፡፡

9. አመልካች ተጠሪ የሻንሲ ቁጥሩና የሞተር ቁጥሩ ተለይቶ የተገለፀው መኪና ለሌላ ሰው የተሸጠ መሆኑን ተጠሪ የፍትሐብሔር ሥን-ሥርዓት ሕግ በሚደነግገው መሠረት የሰነድ ማስረጃዎቹን አላቀረበም በማለት ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታና ክርክር ተገቢነት መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እኛም የስር ፍርድ ቤቶች መዝገብ በትዕዛዝ በማስቀረብ የስር ከሳሽ /ተጠሪ/ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የገለፀውን መኪና ቀደም ሲል ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ ይሸጠው መሆኑንና ይህንኑ መኪና ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ ለማስረከብ የሚችል መሆኑን ገልጸ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ደብዳቤ ጽፎ እንደነበር የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃዎች ተጠሪ ክሱን ሲያቀርብ የማያውቃቸውና ያላገኛቸው መሆኑን በመግለጽ ፍርድ ቤቱ ሰነዶቹን በተጨማሪ ማስረጃነት ለማቅረብ እንዲፈቅድለት የካቲት 12 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ከሳሽ /ተጠሪ/ ባቀረበው የተጨማሪ ማስረጃ የማቅረብ ጥያቄ ላይ ተከሳሹ /አመልካች/ አስተያየቱን እንዲያቀርብ የካቲት 12 ቀን 2007 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝና አባሪውን የካቲት 16 ቀን 2007 ዓ.ም የደረሰው መሆኑ በድርጅቱ ማህተም ካረጋገጠ በኃላ ተከሳሽ /አመልካች/ ከሳሽ /ተጠሪ/ ባቀረበው የተጨማሪ ማስረጃ የማቅረብ ጥያቄ ላይ አስተያየቱን ባለማቅረቡ የሰነድ ማስረጃዎች የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 256 መስፈርት የሚያሟሉ መሆኑን በማረጋገጥ ማስረጃዎቹ እንደቀረቡና ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዙ ሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ብይን ከሰጠ በኃላ የሰነድ ማስረጃዎችን በመቀበል ለፍርድ በግብዓትነት የተጠቀመባቸው መሆኑን ተረድተናል፡፡

10. ይኸ ሰበር ችሎት በትዕዛዝ ካስቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 153516 እንደተረዳነው የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪን ተጨማሪ ማስረጃዎች በተጨማሪ ማስረጃነት ከመቀበሉ በፊት አመልካች አስተያየት የመስጠትና የመከራከር መብቱን ጠብቆ አመልካች ዕድሉን ተጠቅሞ አስተያየቱን ባለማቅረቡ ይህንኑ ምክንያቱን በግልጽ በመዝገብ ላይ በማስፈር ትዕዛዝ ሰጥቶ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ሰነዶቹ በተጨማሪ ማስረጃነት ሊቀርቡ አይገባም የሚልበትን ምክንያት ለሥር ፍርድ ቤት ያላቀረበውን ክርክርና አስተያየት ለዚህ ሰበር ችሎት ማቅረቡ ተገቢ ሆኖ

www.abyssinialaw.com

አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ የማቅረብ ጥያቄው ላይ አመልካች አስተያየትና ክርክር የማቅረብ መብቱን መጠበቁ ብቻ ሳይሆን ከሳሽ /ተጠሪ/ በተጨማሪ ማስረጃነት ለማቅረብ ጥያቄ ያቀረበባቸው የሰነድ ማስረጃዎች በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 256 የተደነገገውን መስፈርት የሚያሟሉ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለውን ነጥብ በአግባቡ በመመርመር ማስረጃዎቹን ለመቀበል ብይን የሰጠ መሆኑን ተረድተናል፡፡

11. ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት በተጨማሪ ማስረጃነት ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ሲያቀርብ ተገቢውን ትጋት በማድረግ ሊያውቃቸውና ሊያገኛቸው የማይችላቸው ማለትም አመልካች ለተጠሪ የሸጠው መሆኑን ገልጾ ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቁጥር TB.TP116/48/14 ነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተገለፀውን መኪና ቀደም ሲል አመልካች ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርጫፍ ጽ/ቤት ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠው መሆኑን ቁጥሩ TB.TB1606/14 ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩን የተገለፀውን መኪና መሆኑን ይህንን መኪና ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም አመልካች ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠ መሆኑ ገልፀው አቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 153390 ክስ ማቅረባቸውን በመጀመሪያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጳጉሜ 4 ቀን 2006 እስከ መስከረም 9 ቀን 2007 የሚቆይ የዕግድ ትዕዛዝ መስጠቱንና መስከረም 9 ቀን 2007 ዓ.ም መኪናው ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ የዕግድ ትዕዛዝ የሰጠመሆኑን የሚያሳዩ የሰነድ ማስረጃዎች እንደሆኑ ተረድተናል፡፡ እነዚህ በአመልካችና በሌላ ሶስተኛ ወገን እጅ የነበሩ ማስረጃዎች ተጠሪ ክስ ሲያቀርብ የማያውቃቸውና ሊያገኛቸው የማይችል ማስረጃዎች በመሆናቸው በስር ፍርድ ቤት የሰነድ ማስረጃዎች በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀርቡ በማድረግ መርምሮና መዝኖ ውሳኔ የሰጠው የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 256 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት በመሆኑ በዚህ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታና ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

12. አመልካች ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር ባደረገው የመኪና ሽያጭ ውል በአመልካች የሸጠው የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተገለፀው አንደኛው መኪና አመልካች ቀደም ብሎ ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ የሰጠው መሆኑንና አመልካች መኪናውን ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ የሰጠ መሆኑን ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩን ጠቅሶ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያሳወቀ መሆኑ የሕጉን ሥርዓት በመከተል ተጠሪ ባቀረባቸው ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው የሚለውን ነጥብ ተመልክተናል፡፡ ከላይ በዝርዝር እንደተገለፀው አመልካች ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም

www.abyssinialaw.com

በተደረገ የሁለት መኪናዎች ሽያጭ ውል መሠረት ሙሉ ዋጋውን የተቀበለበትና እስከ ነሐሴ 25 ቀን 2006 ዓ.ም ለተጠሪ ለማስረከብ የውል ግዴታ የገባበት የሞተር ቁጥሩ 131107038497 እና የሻንሲ ቁጥሩ lzz5ewd77n847969 የሆነው መኪና አመልካች ቀደም ብሎ ለሌላ ሰው የሸጠው መሆኑንም ለገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ያረጋገጠው የመኪናውን ባለሀብትነት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2273 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2281 በተደነገገው መሠረት ለማስተላለፍ የማይችል መሆኑን እያወቀ የተዋዋለው የሽያጭ ውል ነው።

13. ከዚህ አንፃር ሲታይ ከላይ ከሞተረኛ የሻንሲ ቁጥር የተገለፀውን መኪና በተመለከተ አመልካች በሽያጭ ውሉ መሰረት ያልፈፀመው በባልና ሚስት ክርክር ምክንያት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ/ም የዕግድ ትዕዛዝ በመስጠቱ ምክንያት ነው በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር በማስረጃ የተረጋገጡትን ኩነቶች /ፍሬ ነገሮች/ መሰረት ያደረገ አይደለም አመልካች ለተጠሪ ከሸጣቸው መኪናዎች ውስጥ ሲታይ የሞተር ቁጥር የሻንሲ ቁጥር የተጠቀሰውን መኪና ሙሉ የባለሃብትነት መብት ለተጠሪ ለማስተላለፍ የማይቻልበት የሶስተኛ ወገን መብትና ጥያቄ በመኪናው ላይ ያለ መሆኑን ተረጋግጧል። የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ባይኖር ወይም የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቶ ቢሆንም አመልካች በሽያጭ ውሉ መሰረት የመኪናውን ውል ባለመብትነት ሊያስተላልፍ እንደማይችልና መኪናውን በቀዳሚነት ገዝቸ ዋጋ ከፍየበታለሁ የሚለው አቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ያሳገደው መሆኑን ፣የአመልካች ድርጅት ሥራ አስኪያጅ መኪናውን ለሌላ ሻጭ ከሸጠ በኃላ ያንኑ መኪና ለተጠሪ መሸጥ የማታለል ተግባር የፈፀመ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመወሰን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል ።

14 .ይህም አመልካች የተጠሪን መብት በሚነካ ጉድለት ምክንያት የሞተርና የሻንሲ ቁጥር የተገለፀልን መኪና መኪናውን ከአመልካች ቀድሞ ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ/ም በተደረገው ውል ከገዛው አቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ መብትና ጥያቄ ነፃ አድርጎ ለተጠሪ ሊያስረክበው እንደማይችል እያወቀ የሽያጭ ውሉን ከተጠሪ ጋር በመዋዋሉ ምክንያት ውሉ ፈራሽ እንዲሆን ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል ተጠሪ ውሉን የተዋዋለው መኪናውን ለሌላ ሰው አመልካች የሸጠው መሆኑን ሳያውቅ በመሆኑና አመልካች የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣና ሊወጣ እንደማይችል እያወቀ የፈፀመው የሽያጭ ውል በመሆኑ ተጠሪ ውሉ ፈራሽ እንዲሆን ፣ ተጠሪ የተቀበለውን የመኪናውን ዋጋ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲመለስለትና አመልካች መኪናውን በውሉ መሰረት ባለመፈፀሙ

www.abyssinialaw.com

ያደረሰበት ኪሣራ እንዲከፍል ያቀረበው ጥያቄ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀፅ 1 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2360 ንዑስ አንቀፅ 2 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ሆኖ አግኝቶታል ።

15 ከዚህ አንፃር አመልካች የሞተርና የሻንሲ ቁጥር የተገለፀውን መኪና ሙሉ ባለሀብትነት ለተጠሪ ሊያስተላልፍ እንደማይችልና መኪናውን ለሌላ ሰው አስቀድሞ የሸጠው መሆኑን እያወቀ ከተጠሪ ጋር የመኪና ሽያጭ ውል በመዋዋል የመኪናውን ሙሉ ዋጋ ከተቀበለ በኃላ የመኪናውን ሙሉ ባለሀብትነት ለተጠሪ ለማስተላለፍ የማይችል በመሆኑ ምክንያት የሽያጭ ውል ያፈረሰው በተጠሪ ጥፋት ምክንያት መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች ከተጠሪ የወሰደውን ብር 1,150,000 ( አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር ) ነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ፣ ውሉን ባለመፈፀሙ በውሉ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ ብር 5,000 (አምስት ሺ ብር ) እና ውሉ ባለመፈፀሙ በተጠሪ ላይ የደረሰበት ኪሣራ ተጣርቶ ለአመልካች እንዲከፍል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ከላይ የገለፅናቸውን ስለ ሽያጭ ዉሉ የተደነገጉትን ልዩ ድንጋጌዎች ማለትም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀጽ 1 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2360 ንዑስ አንቀፅ 2 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ያደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

16 አመልካች ከተጠሪ ጋር ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ/ም በተዋዋለው ውል የሸጠለት ሌላውን አንድ መኪና በተመለከተ በባልና ሚስት ክርክር መነሻ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 25 ቀን 2006 ዓ/ም የዕግድ ትዕዛዝ ባይሰጥና የዕግድ ትዕዛዙን ለማስነሳት አመልካች በይግባኝ አቅርቦ የዕግድ ትዕዛዝ ባይፀናበት በወሉ መሰረት ለመፈፀም የማያስችለው ሌላ ምክንያት የሌለው መሆኑ የስር ፍ/ቤትና በውሳኔው ካሰፈራቸው ፍሬ ነገሮች ለመረዳት ይቻላል የሥር ፍርድ ቤት አመልካች መኪናውን ለተጠሪ ባለማስረከቡ ሃላፊነት አለበት ያለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ አመልካች ብር 3,000.000 (ሶስት ሚሊዮን ብር) በማሲያዝ አስነስቶ መኪናውን ለተጠሪ ለማሰረከብ የሚችልበት ሁኔታ ነበር በማለት ነው ሆኖም የስር ፍርድ ቤት በወቅቱ የባንክ ሂሳቡን በነፃነት ለማንቀሳቀስና ብር 3,000.000 (ሶስት ሚሊዮን ብር) የባልና የሚስት ክርክር ሲያይ የነበረውና የዕግድ ትዕዛዙን በሰጠው ፍርድ ማስያዝ አቅም እና ችሎታ የነበረው ለመሆኑ በተጠሪ በኩል የቀረቡለት ማስረጃ ስለመኖሩና ስለመረጋገጡ በውሳኔው አላሰፈረም።

www.abyssinialaw.com

17 ይህም አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን ሌላውን አንድ መኪናን በተመለከተ በሽያጭ ውሉ መሰረት ያልፈፀመው በአመልካች ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ሳይሆን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793/ለ/ መሰረት አመልካች በገባው የውል ግዴታ መሰረት መኪናውን ለተጠሪ ሆነ ለሌላ ሶስተኛ ወገን እንዲያስተላለፍ ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ/ም ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክልከላ የተደረገበት ወይም የዕግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት በመሆኑ ምክንያት ለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በተጠሪ የሸጠውን አንድ መኪና ያላስረከበውና እንደ ውሉ ያልፈፀመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም በማለት የሰጠውን ውሳኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793/ለ/ ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

18 አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን አንድ መኪና ያላስረከበውና እንደ ውሉ ያልፈፀመው ከእሱ አቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት በመሆኑ አመልካች የወሰደውን የመኪናውን ዋጋ ብር 1,150.000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ከነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ከመመለስ ውጭ ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት በተጠሪ ላይ የደረሰውን ኪሣራ /ጉዳት/ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት እንዲከፍል የሚገደድበት የሕግ መሰረት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን አንደኛውን መኪና በተመለከተ በውሉ መሰረት ባለመፈፀሙ ተጠሪ የደረሰበት ጉዳት የመክፈል ኃላፊነት አመልካች አለበት በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል ፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 153516 ሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ከፊል ፍርድና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 115897 ሐምሌ 23 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የሞተር ቁጥር 131207038497 የሆነውና የሻንሲ ቁጥር LZZ5 ELND77NB 847969 የሆነውን መኪና ለተጠሪ ለመሸጥ ውል የተዋዋለውና የመኪናውን ሙሉ ዋጋ የተቀበለው የመኪናውን ሙሉ ባለህብትነት መብት ለተጠሪ ሊያስተላልፍለት እንደማይችልና መኪናውን ለሌላ ሰው አስቀድሞ የሸጠው መሆኑን እያወቀ በመሆኑ የመኪናውን ዋጋ ብር 1,150.000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ

www.abyssinialaw.com

ሺ. ብር ) ከነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ከሚወልደው ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር በውሉ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ ብር 5,000 (አምስት ሺ. ብር) እና አመልካች የሽያጭ ውሉን ባለመፈፀሙ ተጠሪ የደረሰበት ኪሳራ / ጉዳት / ካሳ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተጣርቶ ቀርቦ ሊከፍል ይገባል በማለት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀፅ 1 በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2360 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

3. አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን ሌላውን አንድ መኪና በሽያጭ ውሉ መሰረት ያልፈፀመው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793 /ለ/ በተደነገገው መሰረት በፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ በመከልከሉ ምክንያት በመሆኑ የመኪናውን ዋጋ ብር 1,150.000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ሺ. ብር) ከነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር የመመለስ ግዴታ አለበት በማለት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793 /ለ / እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ወስነናል፡፡ ይህንን መኪና ለተጠሪ ባለማስረከቡ አመልካች ለተጠሪ ኪሳራ /ካሣ/ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ጥቅምት 3 ቀን 2008 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.109061

ሕዳር 19 ቀን 2009 ዓ/ም

*ዳኞች፡-* አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዩ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ነጋሪት ሰለሞን ሞግዚት ለሆኑለት ሕፃን የአብስራ ቴዎድሮስ- ጠበቃ ሙሉታ ደበል ቀርቡ

**ተጠሪ**፡- ስካይ ባስ ትራንስፖርት ሲስተም አ.ማ - ጠበቃ በላይ ከተማ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ግንኙነቱ የመጓጓዣ ውልን መሰረት ያደረገ ቢሆንም የጉዳት ካሳ ክፍያው ከውል ውጪ ኃላፊነትን መሰረት አድርጎ ሊከፈለን ይገባል የሚለውን የአመልካችን ጥያቄ መነሻ አድርጎ የታየውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ንብረትነቱ የአሁኑ ተጠሪ የሆነና የታርጋ ቁጥር 3-40411ኢት በሚል የሚታወቀው የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ የአመልካች ባለቤትና ሞግዚትና አስተዳዳሪ ለሆኑለት ህጻን ደግሞ ወላጅ አባት የሆኑት አቶ ቴዎድሮስ ጌታቸው ተሳፍረውበት ጥር 08 ቀን 2004 ዓ/ም ከአዲስ አበባ ወደ ጎንደር እየተጓዙበት እያለ አባይ በርሃ ላይ ከአሽከርካሪው ጥንቃቄ ጉድለት የተነሳ ለሕልፈት የተዳረጉ መሆኑን፣ ሟች በሕይወት እያሉ በወር ብር 3136.00 ገቢ በሚያስገኙ ስራ ላይ ተሰማርተው በሚያገኙት ገቢ አመልካችን ያስተዳድሯቸው እንደነበር፣የህጻኑንና የሟች እድሜ በመግለጽ እንዲሁም የሕሊና ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን በመጥቀስና የተቋረጠባቸውን ጥቅም በመዘርዝር በድምሩ ብር 395,816.00(ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ስምንት መቶ አስራ

www.abyssinialaw.com

ስድስት ብር) ለክሱ ከአወጡት ወጪና ኪሳራ ጋር ተጠሪ ኃላፊ ተብሎ እንዲከፍል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በሰጠው መከላከያ መልስም፡-ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የግዛት ስልጣን የሌለው መሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ከአስቀደመ በኋላ በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ ተጠሪ ጉዳቱን አምኖ መረጃዎችን በማሰባሰብ ወደ መድን ድርጅት በማስተላለፍ የሚጠበቅበትን ማድረጉን፣ አመልካች የሚፈለግባቸውን አሟልተው ከመድን ሰጪው ጋር ከመነጋገር ውጪ ተጠሪው ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን፣ ካሳው በአሰሪውና በሰራተኛው አዋጅ መሰረት በኢንሹራንስ ወይም በመጠባበቂያ ጡረታ ገንዘብ የሚሸፈን መሆኑን፣ መጠኑ ከጉዳቱ ጋር ተመጣጣኝ መሆን ያለበት መሆኑን፣ ለወደፊቱ ሊደርስ ይችላል ተብሎ በሚገመተው ጉዳት የተረጋገጠ መሆን ያለበት መሆኑን፣ ሟች በሕይወት ሳለ ለሕጻኑ ይህን ያህል ወጪ ያወጣ ነበር ተብሎ በማስረጃ ተደግፎ ያለመቅረቡን፣ በመተዳደሪያ በኩል የተቋረጠ ገቢ ሳይኖር የቀረበ ክስ መሆኑን፣ የቀረበው መጠን በማስረጃ ያለመረጋገጡን ዘርዝሮና በአጠቃላይ የአስራ ሰባት አመት የተጠየቀው የሕግ መሰረት የለውም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን ለመኪናው መድን ሽፋን የሠጠው አካል ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባለትም ለፍርድ ቤቱ አመልክቷል፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎም የሃላፊነት መጠኑ እስከ ብር 40,000.00(አርባ ሺ.ህ) መሆኑን፣አመልካች የህጻኑ እናት ስለመሆናቸውና ከሟቹ ጋር የነበራቸው ምን እንደሆነ እንደማይታወቅ፣ሕጻኑ ሲወለድ ሟች በሕይወት ስለሌሉ ህጻኑ ሊያገኘው የሚገባው ጥቅም ተቋርጧል የተባለው ከእውነት የራቀ ምክንያታዊነት የሌለው መሆኑን፣ የሟች ደመወዝ ብር 3,136.00 የተባለው ተጣርቶ የሚደርሳቸውን ያለመሆኑን፣ የተቋረጠው የጥቅም መቋረጥ የተጋነነ እና ከሟች ችሎታ እንዲሁም ከመሰረታዊ ፍላጎት ውጪ የሆኑትን ያካተተ መሆኑን ዘርዝሮ ኃላፊነት የለብንም፣ አለ ቢባል እንኳን ያላግባብ የቀረበ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ተደርጎ ልንሰናበት ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት የአሁኗ አመልካች በራሳቸው በኩል ያቀረቡት የካሣ ጥያቄ የሌለ መሆኑን ገልፆና ህጻኑ ግን ወራሽነቱ ተረጋግጦ በሞግዚቱ በኩል ክስ የአቀረበ በመሆኑ ክስ ለማቅረብ መብት እንዳለው ገልፆ በዚህ ረገድ ተጠሪና ጣልቃ ገቡ ያቀረቡትን ክርክር በማለፍ በፍሬ ነገሩ ደግሞ ሟች ከተጠሪ ጋር የመንንዣ ውል ግንኙነት የነበረው መሆኑ መረጋገጡን፣ በዚህ ምክንያትም ለደረሰው የሞት አደጋ ተጠሪ በን/ሕ/ቁጥር 596 መሰረት ኃላፊነት አለበት በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የካሣ መጠኑን በተመለከተ ደግሞ አደጋው በመደበኛ የመኪና ክስተት የደረሰ በመሆኑ በን/ሕ/ቁጥር 597 ከተመለከተው የካሳ መጠን በላይ ሊያልፍ የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ጠቅሶና ሟች

በየወሩ ያገኙ ከነበረው ደመወዝ ውስጥ ለህጻኑ ብር 500.00(አምስት መቶ ብር) ወጪ ሊያደርጉ ይችሉ እንደነበር፣ ህፃኑ በወቅቱ የነበረው ዕድሜ አንድ አመት ሁኖ ቀለቡ ለምግብ፣ ለልብስ፣ ለትምህርት፣ ለጤና እና ለሌሎች ለመልካም አስተዳደግ የሚበጁ ፍላጎቶች ለቀጣይ አስራ ሰባት አመት ድረስ የሚያስፈልገው መሆኑን ጠቅሶ በድምሩ ብር 102,000.00(አንድ መቶ ሁለት ሺህ ብር) ሊደርስ እንደሚችል ከገለፀ በኋላ በፍ/ሕ/ቁጥር 597 ድንጋጌ መሰረት የጉዳት ካሳ መጠኑ ከብር 40,000.00(አርባ ሺህ) ሊበልጥ አይችልም በማለት ይህንኑ ብር ተጠሪና ጣልቃ ገብ ባልተነጣጠለ ሁኔታ እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን ኃላፊነት በተመለከተ አደጋው በተለመደው የማሽከርከር ሂደት የተከሰተ ነው የሚለውን ድምዳሜ ያላግባብ ማስፈሩንና መረዳቱን፣ መኪናው መንገዱን ስቶ መግባቱ በፍ/ሕ/ቁጥር 599 ድንጋጌን መሰረት ተጠያቂነትን የሚያስከትል አይደለም በማለት ለህጻኑ በቀለብ ረገድ እንዲከፈል ካሳው ሲወሰን መጠኑ ከብር 40,000.00 ሊበልጥ አይችልም መባሉ የአመልካችን ክስና ማስረጃ እንዲሁም የተጠሪን ክርክር ይዘት ያላገናዘበ ነው በማለት የተጠሪ ኃላፊነት በፍ/ሕ/ቁጥር 599 ታይቶ የካሳው መጠንም በተጠየቀው አግባብ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዙት ጭብጦች መገንዘብ የተቻለው፡-

1. የአመልካችን ኃላፊነት አስመልክቶ ከንግድ ሕጉ አንቀጽ 599 አንጻር የሚታይ አይደለም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም?፣እና
2. የካሳ መጠን አወሳሰኑ ሕጉን መሰረት ያደረገ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉ ነጥቦች በጭብጥነት ሊታዩ የሚገባቸው መሆኑን ነው፡፡፡ በመሆኑም እነዚህን ጭብጦችን መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ ዳኝነት የተሰጠበትን አግባብ ከንግድ ሕጉና ስለካሳ ክፍያ ከተደነገጉት ሌሎች ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንዲሚከተለው አይተነዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

**<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>**ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች የሕዝብ ማመላለሻ በሆነው የአመልካች መኪና በመጓጓዝ ላይ እንዳሉ መኪናው አባይ በርሃ ተብሎ በሚታወቀው አከባቢ ተገልብጦ ለሕልፈተ-ሕይወት የተዳረጉ መሆኑ መረጋገጡን፣ አመልካች አሁን አጥብቀው የሚከራከሩት የተሽከርካሪው አሽከርካሪ መንገድ ስቶ መግባቱ ተረጋግጦ እያለ አመልካች አሽከርካሪው የፈፀመው ጥፋት ስለመኖሩ የሚያሳይ ክርክርና ማስረጃ በአመልካች አልቀረቡም ተብሎ በተጠሪና እና በሟች መካከል ያለው ግንኙነት የመጓጓዣ ውልን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የካሳ መጠኑ ከብር 40,000.00 ሊበልጥ አይችልም በሚል መወሰኑ ያላግባብ ነው በሚል መሆኑን ነው፡፡

በሟች ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደረገው የአመልካች መኪና የሕዝብ መጓጓዣ የሚሰጥ መሆኑን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክስ ሲመሰርቱ ከመግለጻቸውም በላይ አደጋው የደረሰበትን ሁኔታ ለማስረዳትም የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ዘርዝረው ማቅረባቸውን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ በገጽ ሁለት በግልጽ ያሳያል፡፡ አመልካች በሕጉ አግባብ የቆጠሩአቸው ምስክሮች ያልተሰሙት በምን ምክንያት እንደሆነ የስር ፍርድ ቤትም ሆነ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጮች የሚያሳዩት ነገር የሌለ ሲሆን ለጉዳዩ ቀረበ የተባለው የሰነድ ማስረጃ ግን ተሽከርካሪው መንገዱን ስቶ በመግባቱ አደጋው መድረሱን እንደሚገልጽ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የተቀበሉት ጉዳይ መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ተሽከርካሪው መንገዱን ስቶ ገድል መግባቱ መረጋገጡን ተቀብለው ይህ ክስተት በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ ተጠያቂነት አያስከትልም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት እንዲዚህ አይነት አደጋ በመደበኛ የመኪና ክስተት የደረሰ መሆኑን የሚያስረዳ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንድ አሽከርካሪ የመኪናውን መንገድ ስቶ የሚገባው በመደበኛው የማሽከርከር ሂደት ነው ተብሎ ድምዳሜ የሚያዝበት አግባብ የሌለ ሲሆን በማሽከርከር ሂደት መንገድ መሳት ሊከሰት የሚችለው በመኪናው ላይ በሚያጋጥመው የቴክኒክ ችግር ወይም በሹፌሩ የአነዳድ ችግር ወይም ሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ትክክለኛውን መስመር ይዞ ለማሽከርከር የማያስችል ሁኔታ ሲያጋጥም መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ አደጋው መደረሱን አምኖ መኪናው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በሌላ ሕጋዊና አሳማኝ ምክንያት አደጋው የደረሰ ስለመሆኑ ገልፆ ያቀረበው ክርክር የሌለ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩ ሲታይ መኪናው መንገዱን ስቶ ገደል የገባው በሹፌሩ በተፈፀመው የጥንቃቄ ጉድለት መሆኑን የሚያስረዳ እንጂ በተለመደበው የመኪና ክስተት ነው ሊባል የሚችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ የተጠሪ መኪና አሽከርካሪ ጥፋት የነበረበት ስለመሆኑ በዚህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 130972፣ 115724፣ እና 122676 በቀረቡት ጉዳዮች ላይም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም መኪናው መንገድ ስቶ ገድል መግባቱን የሚያሳይ ማስረጃ አመልካች ከማቅረባቸውና ተጠሪ ደግሞ

www.abyssinialaw.com

ለአመልካች ክስ በሰጠው መልስ መኪናው መንገድ ስቶ ገደል የገባው ከአሽከርካሪው ጥንቃቄ ጉድለት ስለመሆኑ ገልጾ ያልተከራከረ የመሆኑ ጉዳይ አደጋው በአሽከርካሪው ጥፋት የደረሰ ስለመሆኑ ተመሳሳይ በሆኑ መዝገቦች ተረጋግጧል ተብሎ ድምዳሜ ከመያዙ ጋር ተዳምሮ ሲታይ በዚህ ጉዳይም የአመልካች ኃላፊነት መጠን በን/ሕ/ቁጥር 597 የሚገደብበትን አግባብ አላገኘንም፡፡

ሚቹን ለሕልፈት የዳረገው ተሽከርካሪ ሚቹ የመጓጓዣ ውል የመሰረቱበትና በጉዞ ላይ እንዳሉ ተገልብጦ ጉዳቱ መድረሱ ከተረጋገጠ ጉዳዩ መገዛት ያለበት በንግድ ሕጉ ስለሰዎች መጓጓዣ በሚደነግጉት ድንጋጌዎች አግባብ ስለመሆኑ በመርህ ደረጃ በንግድ ሕጉ የተደነገገ ጉዳይ ነው፡፡ የመንገደኛውን ግዴታ በሚደነግገው በን/ሕ/ቁጥር 687 ስር መንገደኛው በውሉ ላይ የተወሰነውን ዋጋ መክፈል፣ ጉዞውን በሚጀምርበትን ስፍራ በተወሰነው ሰዓት መድረስና እንዲሁም በጉዞው ጊዜ ሁሉ አጓዡ የሚሰጠውን ትዕዛዝና በሕግ የታዘዘውን ማክበር እንደሚገባው በአስገዳጅ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡ አጓዡ ደግሞ መንገደኛውን በመልካም ይዞታና ጥበቃ እንዲሁም ስለ ምቾቱና ስለጉዞው በውሉ በተወሰነው ጊዜ አክብሮ እንደተወሰነው መድረሻው ስፍራ የማድረስ ግዴታ ያለበት መሆኑን የን/ሕ/ቁጥር 588 በግልጽ ያሳያል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የመንገደኛውን እና የአጓዡን ተነፃፃሪ ግዴታዎችን የሚደነግጉ ሲሆን አጓዡን ኃላፊነት ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 547/1999 የተሻሻሉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሁነው ከቁጥር 589 እና ተከታይ ድንግጌዎች ስር አስፍሯል፡፡ በመንገደኛው አካል እና ሕይወት ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የአጓዡን የኃላፊነት መጠን በን/ሕ/ቁጥር 597 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ስር ያሉት የአላፊነት አይነቶች የሚከሰቱት በሕግ አግባብ የተቋቋመ የመጓጓዣ ውል መኖሩ ሲረጋገጥ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 547/1999 ያልተሻረውን የሰው መጓጓዝን መሰረት አድርገን ስናየው የመጓጓዣ ውል የሚባለው አጓጓዥ ዋጋ በመቀበል ሰውን የተወሰነ ስፍራ ለማድረስ ግዴታ የገባበት ስምምነት ስለመሆኑ በን/ሕ/ቁጥር 561 ስር የተደነገገ ሲሆን የን/ሕ/ቁጥር 567(1) ድንጋጌ ሲታይም ሰውን ለማጓጓዝ የሚደረግ ውል በሁለቱ ወገኖች ስምምነት መሰረት ስለመሆኑና አጓዡ መንገደኛው የማጓዣ ሰነድ ትኬት ወይም የደንበኛነት ቲኬት እንዲቀርብና ጉዞውን እስኪፈጽም ድረስ ጠብቆ መያዝ የሚገባው መሆኑን ሊያስታውቀው እንደሚችል ደንግጓል፡፡ የን/ሕ/ቁጥር 567(2) ድንጋጌ ደግሞ የመጓዣ ሰነድ ሳይኖረው የሚጓዝ መንገደኛ ከዋጋው በላይ ተጨማሪ ገንዘብ ይከፈላል የሚል ማስታወቂያ ሊደረግ እንደሚችል ሲደነግግ ለመንገደኛው በሚሰጠው ቲኬት ላይ የሚከፈለው ዋጋና የሰዓቱ መነሻና መድረሻ የተመለከተ መሆን እንዳለበትም የተጠቃሹ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር ሶስት ስር በግልጽ አስፍሯል፡፡ ጉዳዩን የሚገዛው ልዩ ሕግ የንግድ ሕጉ ነው ከተባለ ደግሞ የጉዳት ካሳ የሚሰላውም በዚሁ ሕግ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ነው፡፡

በመሰረቱ በንግድ ህግ ቁጥር 596 መሠረት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ በመንገደኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት በሀላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን የንግድ ሕግ ቁጥር 597 ድንጋጌ

www.abyssinialaw.com

ያሳያል፡፡ የሀላፊነት መጠንን በተመለከተ ደግሞ ለአንድ መንገደኛ ከብር 40,000 /አርባ ሺ ብር/ እንደማይበልጥ የንግድ ህግ አንቀጽ 597 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በንግድ ህግ አንቀጽ 597 የተደነገገው የሀላፊነት መጠን አጓዡ በንግድ ህግ አንቀጽ 596 የተደነገጉትና ከሀላፊነት ነጻ የሚያደርጉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ለማስረዳት ባልቻለበት ሁኔታና መንገደኛው በንግድ ህግ አንቀጽ 599 በሚደነገገው መሠረት አጓዡ አደጋ ሊያደርስ የሚችል መሆኑን እያወቀ በፈጸመው ተግባር ወይም ጉድለት ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ባልቻለበት ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡

በንግድ ህግ ቁጥር 588 በሚደነግገው መሠረት የመንገደኛውን መልካም ይዞታ ደህንነትና ምቾት በመጠበቅ መንገደኛውን የማጓጓዝ ሀላፊነቱን ሊወጡ የሚገባቸውን ወገኖች የመኪና ባለቤት፣ ሹፌር፣ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ መኖሩን፣ በንግድ ህግ አንቀጽ 599 "አጓዡ የተፈፀመው ተግባር ወይም ጉድለት" የሚለው ሀረግ አጓዡ በግሉ የፈጸመውን ተግባር ወይም ጉድለት የሚመለከት ሣይሆን የአጓዡ ሰራተኞች አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጠር እንደሚችል እያወቁ የፈጸሙትን ተግባር ወይም ጉድለት የሚያካትት ስለመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 67973 በሆነው መዝገብ ላይ በቀረበው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በማናቸውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያሰገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተያዘው ጉዳዩ ሲታይም አደጋው የደረሰው የአመልካች መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር ባጠፋው ጥፋት ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የክርክር ሂደት የተረጋገጠ በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የን/ሕ/ቁጥር 599 ሁኖ አግኝተናል፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው በላይ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት የለብንም በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ መሠረት ያለው አደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው የሀላፊነት መጠን በላይ ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት እንዳለባቸው የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ድንጋጌ የሚያስገነዝበን በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የካሳው መጠን ብር 40,000.00 ሊሆን ይገባል ሲሉ የደረጎት ድምዳሜ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ምክንያቱም የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ድንጋጌ በን/ሕ/ቁጥር 597 ስር የጉዳት ካሳ ከብር 40,000.00 እንደማይበልጥ በመርህ ደረጃ የተቀመጠውን የሀላፊነቱን መጠን በልዩ ሁኔታ የደነገገ፣ መንገደኛው ከአጓዡ ከብር 40,000 በላይ ካሣ ለመጠየቅና ለማግኘት የሚችልበትን ልዩ ሁኔታ የሚደነግግ ድንጋጌ ነውና፡፡ በን/ሕ/ቁ. 599 ድንጋጌ መሠረት ለመንገደኛው ካሣ የመክፈል ሀላፊነት ያለበት አጓዥ ለመንገደኛው የሚከፍለው የካሣ መጠን ለመወሰን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና 2092 የተደነገጉት የካሳ አከፋፈል መርሆች አግባብነት ያላቸው ስለመሆናቸውም ይህ ችሎት ከላይ በተጠቀሰው የሰበር መዝገብ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

በተያዘው ጉዳይ ግን የተጠሪ ንብረት የሆነውን የህዝብ ማመላለሻ ያሽከረክር የነበረው የተጠሪ ሰራተኛና የመኪናው ሹፌር በፈጸመው ከባድ ጥፋት ምክንያት አደጋው መድረሱ በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ተጠሪ በዚህ ሰበር ደረጃ አጥብቆ የሚከራከረው የተጠሪ ንብረት የሆነውን የህዝብ ማመላለሻ መኪናን ያሽከረክር የነበረው የተጠሪ ሰራተኛና የመኪናው ሹፌር የሆነው ከባድ ጥፋት የነበረበት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚመለከተው ፖሊስ አልቀረበም፣ ተሽከርካሪው ፍጥነት የነበረው ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፣ አመልካች ባቀረቡት የሰነድ ማስረጃ መኪናው መንገድ ስቶ ገደል ገብቷል ተብሎ መጠቀሱ የአሽከርካሪውን ጥፋት የሚያሳይ አይደለም በማለት ስለመሆኑም ተገንዝበናል፡፡

ይሁን እንጂ የክፍሉ ፖሊሲ በሰ/መ/ቁጥር 130972፣ 122676፣115724 በቀረቡት ጉዳዮች ለስር ፍርድ ቤቶች በቁጥር 01514 በቀን 26/06/2007 ዓ/ም በላከው ማስረጃ ስለአደጋው በወቅቱ የተደራጀ የምርመራ መዝገብ እንደሌለ፣ በተሽከርካሪው ላይ የቴክኒክ ምርመራ ባለመደረጉ እና ፕላን ባለመነሳቱ በወቅቱ የነበረውን የተሽከርካሪውን ፍጥነት ለማወቅ ያለመቻሉን በመግለፁ የሥር ፍርድ ቤቶች በእነዚህ መዛግብት በከሳሾች የተቆጠሩትን ምስክሮች መስማታቸውን የክርክሩ ሂደት በግልጽ የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ የስር ከሳሾች በዚህ ረገድ ለይተው ያሰሟቸው ምስክሮች በወቅቱ ተሳፋሪ የነበሩና መኪናው የነበረውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በጊዜውና በቦታው ሁነው በስሜት ሕዋሳቶቻቸው በአዩት እና በተገነዘቡት መጠን የመሰከሩ መሆናቸውን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ስለአደጋው የተደራጀ የትራፊክ ማስረጃ የሌለ መሆኑና በአሁኗ አመልካች በኩል ቀረበ የተባለው የሠነድ ማስረጃም መኪናው መንገድ ስቶ ገድል መግባቱን የሚያሳይ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን የተደራጀ የትራፊክ ማስረጃ ቢቀርብ እንኳን ማስረጃው የባለሙያ ማስረጃ እንደመሆኑ መጠን ባለሙያው መጨረሻ ላይ የሚደርስበት መደምደሚያ /ግኝት/ ሙያዊ አስተያየት /opinion/ ከመሆን አልፎ ፍሬ ነገር /fact/ መሆን እንደማይችል፣ ኤክስፐርቱ የሚደርስበት የመጨረሻ አስተያየት ከሚኖረው ሙያዊ ዕውቀት አድማስ ከሚታገዝበት መሣሪያና ከመሳሰሉት ጋር የተሟላና ሙሉ ዕምነት የሚጣልበት ማስረጃ /conclusive evidence/ ሊሆን ስለማይችል በዓይን ምስክሮች የተነገረን ፍሬ ነገር ለማስተባበል የሚያበቃ አቅም ሊኖረው አይችልም፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም ቀደም ሲል በሰበር መ.ቁ. 14981 የኤክስፐርት ማስረጃ ሙሉ ዕምነት ሊጣልበት የሚችል ማስረጃ እንዳልሆነ የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡ ከዚህም ሌላ የኤክስፐርት ማስረጃ በማስረጃነት በቀረበ ጊዜ ይበልጥ ተቀባይነት የሚኖረው ከቀጥተኛ ማስረጃ ጋር በተጣጣመ ጊዜ እንጂ ቀጥተኛ ማስረጃውን በሚፃረር ጊዜ የበለጠ ክብደት የሚሰጠው ለቀጥተኛ ማስረጃው ስለሆነ የኤክስፐርት ማስረጃው ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይችል መገንዘብ ስለሚቻል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን በቀጥተኛው ማስረጃ በማጣራት የተጠሪን

www.abyssinialaw.com

የሕዝብ ማመላለሻ መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር በማሽከርከር ሂደቱ ከመጠን በላይ ፍጥነት ጨምሮ ሲያሽከረክር የነበረ በመሆኑ ጥፋት መፈፀሙን ተረጋግጦ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ከማስረጃ አቀራረብና አመዛዘን መሠረታዊ መርህ ውጪ በሆነ ሁኔታ አመልካች ካሳው በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ የሚታይበትን ሁኔታ አላስረዱም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ተጠሪ ያቀረበውን ክርክር ባለመበቀል ተጠሪ በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ ለጉዳዩ ኃላፊ አለበት ብለናል፡፡

<u>**ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-**</u>ከላይ እንደተገለጸው የተጠሪ ሃላፊነት መታየት ያለበት በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ ነው ከተባለ ይህ ድንጋጌ የካሳ መጠኑ በብር 40,000.00 የማይገደብ መሆኑንና ካሳው ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚገዛው የሕግ ክፍል ስር ባሉት ድንጋጌዎች አግባብ መሰላት እንደለአበት ያስገነዝባል፡፡እንዲህ ከሆነ ተጠሪ በሚች ላይ ለደረሰው ጉዳት በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው በላይ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት የለብንም በማለት የሚያቀርበው ክርክርም ሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንኑ የተጠሪን ክርክር በመቀበል የሰጡት ዳኝነት የህግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ስለዚህ በን/ሕ/ቁ ህግ ቁጥር 599 ድንጋጌ መሠረት ለመንገደኛው ካሣ የመክፈለ ሀላፊነት ያለበት አጓዥ ለመንገደኛው የሚከፍለው የካሣ መጠን ለመወሰን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና 2092 የተደነገጉት የካሳ አከፋፈል መርሆች አግባብነት አላቸው፡፡

በመሰረቱ ካሳ የሚከፈለው ጉዳት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን የካሳ አተማመን ፣መጠንና አከፋፈልን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090፣2091፣2092 ፣ 2095 እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሲሆን ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም ካሳው በተቻለ መጠን ከጉዳቱ ጋር መመጣጠን ያለበት መሆኑን ነው፡፡

ከውል ውጪ ኃላፊነትን በተመለከተ የሚገዙት የፍትሓብሔር ሕጋችን ድንጋጌዎች መንፈስ የጉዳትን ጠቅላላ ባህርይና የካሣ ልክ አተማመን ሁኔታዎችን ያስገነዝቡናል፡፡ በዚህም መሠረት ጉዳት በሰው ጥቅም ላይ ችግር የሚያደርስ መሆኑን፣ ይህም ጥቅም ማቴሪያላዊ /በሰው አካል ወይም ንብረት የደረሠ/ ወይም ሞራሊዊ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጎዳ ሰው ደግሞ መካስ እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡ የካሣውን አተማመን በተመለከተም መጠኑ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ የጉዳት ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ ሲመዘንም በተጎጂው ላይ በእርግጠኝነት መድረሱ የታወቀ /actual damage/ ወይም ወደ ፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳትን/future damage/ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የግድ የሚል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091/1/ እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል፡፡ በእነዚህ ድንዳጌዎች የጉዳት ካሣ ሊተመን የሚገባ መሆኑን ሕጉ በግልጽ

www.abyssinialaw.com

ከማስቀመጡም በተጨማሪ የአተማመኑ ሥርዓትም እንደጉዳቱ ዓይነትና ማስረጃ አቀራረብ ውስብስብነት ሊለያይ የሚችል መሆኑን የሕጉ መንፈስ ያስገነዝባል፡ ፡በዚህም መሠረት የጉዳት ካሣ መጠን አጥጋቢና በቂ ማስረጃን ወይም ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን የካሣ አከፋፈሉን ልክ በሚደነግገው የሕጉ ክፍል የተቀመጡ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡

በመሆኑም ጉዳት መድረሱ በማስረጃ ከተረጋገጠና ጉዳቱ እርግጠኝነት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ ካሣ መወሰን ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ አኳያ አግባብነት ያለው ነው፡፡ጉዳቱ መድረሱና የጉዳቱ መጠን ከታወቀ ተጎጂው በጉዳቱ ልክ ሊካስ የሚገባው መሆኑን በአጠቃላይ ከውል ውጪ ኃላፊነትን ከሚገዛው ሕግ አላማ ጋር አንድ ላይ የሚሄድ ነው፡፡ ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች የህፃን የአብስራ ወላጅ አባት የሆኑት ቴዎድሮስ ጌታቸው ከዚህ አለም በሞት በመለየታቸው ሕፃኑ ለወደፊቱ የተቋረጠበትንና ሊቋረጥበት የሚችል ጥቅም ያለው መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም ህፃኑ ለወደፊቱ የተቋረጠበት ጥቅም ምን ያህል እንደሆነ ከወዲሁ በትክክል ማስቀመጥ የማይቻል መሆኑ የክርክሩ ሂደትና ባህርይ ያስገነዝባል፡፡ ሟች በወቅቱ የብር 3136.00 ወርሃዊ ደመወዝተኛ የነበሩ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ከዚህ ገቢ ውስጥ ለህጻኑ ቀለብ ሊውል ይችላል ያለው መጠን ብር 500.00(አምስት መቶ) ነው፡፡ ይህንኑ መጠን ሲይዝም የቀለብ ወጪ ሲታሰብ ግንዛቤ ውስጥ የሚገቡ የልብስ፣ ምግብ፣ትምህርት፣ ጤና እና ሌሎች ለመልካም አስተዳደግ የሚበጁ ፍላጎቶች ወጪዎችን ሊያካትት እንደሚገባ በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡ በእርግጥ በልጅ ቀለብ አወሳሰን ጊዜ ሊታዩ የሚገባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች በህጉ በግልጽ ባይመለከቱም የልጆችን ጥቅም ቀዳሚ ማድረግ፣መሰረታዊ የሆኑ ነገሮችን ታሳቢ ማድረግንና መሠረታዊ ፍላጎቶችና ልዩ ወጪዎች ታሳቢ ማድረግን የሚጠይቁ መሆኑን ከቀለብ ባህርይና ከህጉ መሰረታዊ አላማ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ወላጆች ለራሳቸው መሰረታዊ ፍላጎቶች ሊያሟሉ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባትም የግድ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከትም የስር ፍርድ ቤት ሟች አቶ ቴዎድሮስ ጌታቸው በወቅቱ ያገኙ ይችሉ የነበረውን ወርሃዊ ደመወዝ ለሟቹ ፍላጎቶች ሊወጣ ከሚችለው ወጪና ከሕጻኑ መሰረታዊ ፍላጎቶችና ልዩ ወጪዎች ጋር ለማገናዘብ የሞከረ ቢሆንም ሟቹ በሕይወት ቢኖሩ ኑሮ ለወደፊቱ አቅማቸውን ገንብተውና ተገቢውን ጥረት በማድረግ የተሻሻለ ደመወዝ ላይ ሊደርሱ የሚችሉበትን ሁኔታንና ለመሰረታዊ ፍላጎቶች የሚወጣው ወጪ መጠን በየጊዜው ከፍ እያለ የሚሄድበት አጋጣሚ የሚከሰት ስለመሆኑ ማገናዘቡን ግን የውሳኔው ግልባጭ አያሳይም፡፡ ይህም ለህጻኑ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት መልካም አስተዳደግን በተቻለ መጠንና አቅም በሚፈቅደው ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የወጪ መጠን ለመወሰን ግንዛቤ ውስጥ መገባት ያለባቸው አጠቃላይ ከባባዊ ሁኔታዎች ያለመያዛቸውን የሚያሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

ከዚህ አንጻር ሲታይ ለሕጻን የአብስራ ቴዎድሮስ በወር ሊወጣ የሚችለው የቀለብ ገንዘብ መጠን ብር 500.00(አምስት መቶ) ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤት ተይዞ የነበረው መነሻ በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 197 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ስለቀለብ መጠን አወሳሰን የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ ያላገናዘበ ሁኖ አግኝቶናል፡፡ ሟች በሕይወት ቢኖሩ ኑሮ ከፍ ወደ አለ ደረጃ በመድረስ የተሻለ ደመወዝ ሊያገኙ የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩና ለህጻኑ የወደፊት ኑሮ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ፍላጎቶች ሊያስወጡ የሚችሉት የወጪ መጠን ወደፊት ሊኖር ከሚችለው አጠቃላይ የህብረተሰቡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኑሮ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ቢገባ እንኳ በእርግጠኝነት የቀለቡን መጠን ከወዲሁ ለመወሰን የሚያስችል ነው ለማለት የሚያስደፍር አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ለህፃኑ የቀለብ መጠኑን ለመወሰን አስቸጋሪ ሁኔታ ያለ መሆኑ ተገንዝበን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102 ድንጋጌ መሰረት በርትዕ መወሰኑ ተገቢ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ለህጻኑ በወር ለወደፊቱ የሚያስፈልገው ወጪ ብር 1000.00(አንድ ሺህ) ነው በማለት ህጻኑ አባቱ በመኪናው አደጋ በሞተበት ጊዜ የአንድ አመት እድሜ የነበረው መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በተረጋገጠው መሰረት አስራ ስምንት አመት እስኪሞላው የቀረበት የቀለብ ጥቅም ታስቦ የሚመጣው ውጤት ማለትም ብር1000.00x12x17= 204,000.00(ሁለት መቶ አራት ሺህ) ለአመልካች ሊከፈላቸው የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ የቀለቡን አከፋፈል በተመለከተም አመልካች የህጻኑ ወላጅ እናትና ሞግዚት በመሆናቸው ተገቢውን ግዴታቸውን እንደሚወጡና ለተሻለ ጥቅምም ገንዘቡን ሊያወሉ የሚችሉበት ነባራዊ ሁኔታዎች መኖራቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2154 ድንጋጌ ለፍርድ ቤቶች የሚሰጠውን ስልጣን በማገናዘብ በአንድ ጊዜ ተጠቃልሎ እንዲከፈል ማድረጉ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪን በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ ተጠቂነት የለበትም በማለት የካሳ መጠኑን ብር 40,000.00(አርባ ሺህ ብር) አድርገው የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወሰነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 09275 ጥቅምት 08 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 142838 ጥቅምት 17 ቀን 2007 ዓ/ም የፀናው፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
   የአመልካች ሞግዚት የሆኑት ህጻን የአብስራ ቴዎድሮስ በደረሰው የሞት ጉዳት ምክንያት የጉዳት ክሳ በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ ሊከፈለው ይገባል ብለናል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. ለህፃኑ ሊከፈለው የሚገባው የጉዳት ካሳ መጠን ብር 204,000.00(ሁለት መቶ አራት ሺህ) ሁኖ አካፋፈሉም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2154 ድንጋጌ አግባብ በአንድ ጊዜ ሊሆን ይገባል ብለናል፡፡
3. አመልካች በህጻኑ ስም የባንክ ሂሳብ ከፍተው ገንዘቡን የሞግዚትነት ስልጣን በሚፈቅደው አካሄድ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲያውሉም ብለናል፡፡
4. የኢትዩጵያ መድን ድርጅት በሰጠው የመድን ሽፋን እስከ ብር 40,000.00(አርባ ሺህ) ለመሸፈን የተስማማ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ ብር 40,000.00(አርባ ሺህ ብር) ተጠሪና የኢትዩጵያ መድን ድርጅት ባልተነጣጣለ ሃላፊነት ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡ ቀሪውን ብር 164,000.00(አንድ መቶ ስልሳ አራት ሺህ) ደግሞ ተጠሪ ብቻውን ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ኪሳራና የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 105752

ህዳር 26/2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- አቶ አዲሱ ግርማሁን የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች አከራይ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ጉዝ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ስራ አስኪያጅ አቶ ተስፋዬ ታዴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ፡- የኪራይ ውልን መሰረት ያደረገ ሲሆን የአሁን ተጠሪ የሆነው የስር ከሳሽ በአሁን አመልካች የስር ተከሳሽ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ በኦሮሚያ ክልል በአርሲ ዞን በሺርካ ወረዳ ለሶሎ ዳጋሎና ጎልቤሳ ሴሩ መንገድ ስራ አገልግሎት የሚውል ሞዴሉ D7H CAT ዶዘር በሰዓት በብር 2,127.50 /ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃያ ሰባት ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ ሂሳብ ለ 200 ሰዓት ሊያቀርብልኝ ተዋውለን ህዳር 28/2005 ዓ.ም ብር 422,500.00 /አራት መቶ ሃያ ሁለት ሺኅ አምስት መቶ ብር/ ከፍየዋለሁ፡፡ ተከሳሽም ዶዘሩን አቅርቦ ከታሕሳስ 4/2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 6/2005 ድረስ ለ 13 ሰዓት ያህል ከሰራ በኂላ ተበላሽቶ በመቆሙ ምክንያት ከተከሳሽ ጋር ውላችንን አሻሽለን ታህሳስ 17/2005 ዓ.ም CAT 322L ኤክስካቫተር በሰዓት 1,322.50 /አንድ ሺኅ ሶስት መቶ ሃያ ሁለት ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ በጠቅላላ ለ 301 ሰዓት በብር 398,072.50 /ሶስት መቶ ዘጠና ስምንት ሺኅ ሰባ ሁለት ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ ሊያቀርብልኝ ተዋውለናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከሳሽ ኤክስካቫተሩን አቅርቦ ታህሳስ 23/2005 ዓ.ም ለ 3፡45 የሰራና ታህሳስ 26/2005 ለ 4፡45 በድምሩ 8፡30 ሰዓት ብቻ ሰርቶ በብልሽት ቆሟል፡፡

www.abyssinialaw.com

ተከሳሽ በዶዘሩ ማሽን ለ 13 ሰዓት ብቻ ያገለገለ በመሆኑ የ 13 ሰዓት ክፍያ 13X 2,127.50= 27657.50 /ሃያ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ ሲሆን በኤክሳካቫተሩ ለ 8፡30 ያገለገለ በመሆኑ 8፡50 X በ 1,322.50= 11,241.25 በድምሩ ብር 38,898.75 /ሰላሳ ስምንት ሺኅ ስምንት መቶ ዘጠና ስምንት ብር ከሰባ አምስት ሳንቲም/ ተቀንሶ ቀሪው ብር 386,601.30 /ሶስት መቶ ሰማኒያ ስድስት ሺኅ ስድስት መቶ አንድ ብር ከሰላሳ ሳንቲም/ እንዲመልስልኝ ብጠይቀው ፍቃደኛ አይደለምና ዋናውን ገንዘብ ከነህጋዊ ወለዱ ይክፈለኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ተከሳሽ ኢንተርፕራይዝም በሰጠው መልስ ከከሳሽ ጋር ውል መኖሩን አምኖ መጀመሪያ ለዶዘሩ የተዋዋልነውን ውል በስምምነት ታህሳስ 17/2005 ዓ.ም በተጻፈ ውል ወደ ኤክስካቫተር ለውጠነዋል ኤክስካቫተሩ እስከ ታህሳስ 26/2005 ዓ.ም ሰርቶ ተበላሽቶ ለመቆሙ የማውቀው ነገር የለም ከሳሽም በብልሽት ለመቆሙ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ቢበላሽ እኳን በውላችን አንቀጽ 5 ላይ ማሽኑ ለአስር ተከታታይ ቀናት ካልሰራ የተከፈለው ገንዘብ እንደሚመለስ እየታወቀና በ 26/4/2005 ዓ.ም ማሽኑ አገልግሎት መስጠቱን በከሳሽ እየታወቀ አስር ቀን ሳይሞላው በ 2/5/2005 ዓ.ም ከሳሽ ውለታ አቋርጠናል ማለቱ አግባብ አይደለም፤ በተጨማሪም ከተከሳሽ ብር 422,500.00 /አራት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር/ የተቀበልኩ ቢሆንም አስራ አምስት ፐርሰንት ተጨማሪ እሴት ታክስ ለመንግስት የከፈልኩ ስለሆነ የከሳሽ ትክክለኛ ገንዘብ 370,000.00 /ሶስት መቶ ሰባ ሺኅ ብር/ ብቻ ነው ብሏል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተከሳሽ የመጀመሪያው ውል በሁለተኛው ውል የተተካው በዶዘሩ ብልሽት ሳይሆን በግራ ቀኙ ስምምነት ነው ቢልም የግራ ቀኙ ስምምነት የተደረገው በዶዘሩ መበላሸት ምክንያት መሆኑን ከማሻሻያው ውል መረዳት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ተከሳሽ ማሽኖቹን በራሴ ወጪ አጓጉዤ ለማምጣት ወጪ አውጥቻለሁ ቢልም በውላቸው ላይ ተከሳሽ በራሱ ወጪ አጓጉዞ ለማስገባት እና ማሽኑ በቀን ስምንት ሰዓት በሳምንት ስድስት ቀን ሊሰራና ማሽኑ ሳይበላሽ ስራ ካልሰራ ሃላፊ ከሳሽ መሆኑን፤ መስማታቸውንና፤ ማሽኑ ለተከታታይ አስር ቀናት በብልሽት ቢቆም የሰራበት ታስቦ ያልሰራበትን ተከሳሽ ሊመልስ የተስማሙ ቢሆንም ሁለተኛው ማሽንም በብልሽት ምክንያት ከ 23/4/2005 ዓ.ም ጀምሮ በየቀኑ አስር ሰዓት ሊሰራ አለመቻሉ በሰዓት መመዝገቢያ ላይ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የከሳሽ ምስክሮች በወቅቱ በማሽኑ መበላሸት ስራ ያለመስራታቸውን ሲገልጹ የተከሳሽ ምስክሮች ማሽኑ ስራውን ያልሰራው በመበላሸት ምክንያት ሳይሆን በገና በዓል ምክንያት ኦፕሬተሩና ረዳቱ ወደ ቤተሰብ በመሄዳቸው ነው ብለዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

በተጨማሪም ማሽኑ ባለመስራቱ ከሳሽ ለተከሳሽ በ 2/5/2005 ዓ.ም በጻፈው ማስጠንቀቂያ ከጥር 3/2005 ዓ.ም ጀምሮ ውሉ መቋረጡን መግለጹን በተከሳሽም ታምኗል በማለት አትቶ ተከሳሽ ከተከፈለው ገንዘብ ውስጥ ማሽኑ የሰራበት ብር 38,818.70 ሳ ተቀንሶ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያን ጨምሮ ብር 386,601.30 ከሚታሰብ ወለድ እና ተያያዥ ከሆኑ ክፍያዎች ጋር ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ቅሬታው የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቅሬታው መልስ ሰጭን አያስጠራም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበው የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታልና ሊታረም ይገባል በሚል አመልካች በመጠየቃቸው ነው፡፡ የሰበር አጣሪው ችሎትም በግራቀኙ መካከል ያለው ውል በአንቀጽ 5 ላይ ኤክስካቫተሩ ለአስር ተከታታይ ቀናት በብልሽት ምክንያት ካልሰራ ውሉ እንደሚቋረጥና የተከፈለው ገንዘብ እንደሚመለስ የተስማሙና ማሽኑ እስከ ታህሳስ 26/2005 ዓ.ም ድረስ የሰራ መሆኑ እየታወቀ አመልካች የከፈለውን ገንዘብ በተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያን ጨምሮ ሊከፍል ይገባል በማለት የተወሰነበትን አግባብነት ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ያስችል ዘንድ ተጠሪን ያስቀርባል ብሏል፡፡

ተጠሪም በወኪሉ አማካኝነት በጽሑፍ በሰጠው መልስ ተጠሪ በውለታችን መሰረት መጀመሪያ ያቀረበው ማሽን በብልሽት ምክንያት ባለመስራቱ ውለታችንን አሻሽለን ሌላ ማሽን እንዲያስገባ ብንስማማም 2ኛው ማሽንም በውላችን መሰረት በቀን 8 ሰዓት በሳምንት 6 ቀን ሊሰራልኝ አልቻለም፡፡ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለም ቢሆን በማሽኑ ብልሽት ምክንያት ስራ ላልተሰራበት ያልተከፈለ መሆኑን በማሳወቅ ተጠሪ ገንዘቡን ማስመለስ ይችላል በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተገቢ ነውና ሊጸና ይገባል ብሏል፡፡

አመልካችም የጽሑፍ የመልስ መልስ አቅርቧል የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ችሎት ግራቀኙ ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረነዋል፡፡ እንደመረመርነውም ተጠሪ በገባው ውል መሰረት በቀን ለስምንት ሰዓት በሳምንት ለስድስት ቀናት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ማሽን ማቅረብ ሲገባው ያቀረበው ማሽን በብልሽት ምክንያት ሊሰራ አልቻለም በሚል የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ለአመልካች የከፈለውን ገንዘብና ተያያዥ ክፍያዎችን እንዲመልስ መወሰናቸው አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

በመሰረቱ አመልካችና ተጠሪ የማሽን ኪራይ ውል ያላቸው መሆኑን በዚህም መነሻ ተጠሪ ብር 422,500 ለአመልካች የከፈለ መሆኑን አመልካችም በውለታው መሰረት ማሽን ማቅረቡንና ማሽኑ ለ 3 ቀንና ለ 13 ሰዓት መስራቱ በግራቀኙ የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር በስምምነት ውለታውን ወደ ኤክስካቫተር ቀይረናል ሲል ተጠሪ ውሉን ልንቀይር የቻልነው በማሽኑ ብልሽት ምክንያት ነው ብሏል፡፡ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በውሳኔ ላይ እንዳተተውም ውለታቸው የተሻሻለው በዶዘሩ መበላሸት ምክንያት መሆኑን ውለታቸው የሚገልጽ መሆኑን ነው፡፡ በመቀጠልም አመልካች በተሻሻለው ውለታ መሰረት ኤክስካቫተሩን ያቀረበ ቢሆንም ይህም ማሽን ለሁለት ቀን በድምሩ ለ 8:30 አገልግሎት መስጠቱን በግራቀኙ የታመነ ጉዳይ ሲሆን ስራው የቆመው ግን አመልካች የገና በዓል ስለነበረ የማሽኑ ኦፐሬተርና ረዳቱ ለበዓል ወደ ቤተሰብ እንዲሄዱ ከተጠሪ ጋር በተነጋገርነው መሰረት ነው ሲል ተጠሪ በብልሽት ምክንያት መሆኑን ገልጾ በዚሁ ምክንያት መሆኑን በሰውና በሰነድ ማስረጃ መረጋገጡን የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክርና ማስረጃ መረዳት ተችሏል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ዋናው ምክንያት በውለታችን አንቀጽ 5 ላይ ማሽኑ በቀን ለስምንት ሰዓት በሳምንት ለስድስት ቀን አገልግሎት መስጠት እንዳለበት ተዋውለን እያለ ማሽኑ ታህሳስ ታህሳስ 23/2005 ዓ.ም ለ 3:45 ታህሳስ 26/2005 ዓ.ም ለ 4:45 ሰዓት የሰራ ሆኖ እያለ ማሽኑ መስራት ካቆመ አስር ቀን ሳይሞላ ጥር 2/2005 ዓ.ም ተጠሪ ለአመልካች የውል ማቋረጫ ማስጠንቀቂያ በመላክ በቀን 3/5/2005 ዓ.ም ውሉ መቋረጡ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ እኛም ይህን ጭብጥ አስመልክቶ እንደመረመርነው በግራቀኙ ውል አንቀጽ 5 ስር እንደተመለከተው ማሽኑ በቀን ለስምንት ሰዓት በሳምንት ለስድስት ቀን ሊሰራ እንደሚገባና በዚህ በተቀመጠው መለኪያ /እስታንዳርድ/ መሰረት ለአስር ተከታታይ ቀናት አገልግሎት ካልሰጠ ውሉ ፈርሶ አመልካች በውሉ ምክንያት የተቀበለውን ገንዘብ እንዲመልስ መስማማታቸውን ከግራቀኙ ክርክር በመታመኑ ከመረጋገጡም በተጨማሪ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ መሆኑን ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳ ተጠሪ የውለታውን ገንዘብ መክፈሉ ግልጽ እስከሆነ ድረስ አመልካች በውለታው መሰረት ማሽን አቅርቦ አገልግሎቱን የመስጠቱን ጉዳይ ሲታይ በውላቸው የተስማሙት ማሽኑ በቀን 8 ሰዓት በሳምንት 6 ቀን አገልግሎት ሊሰጥ የነበረ ቢሆንም ማሽኑ በውሉ መሰረት አገልግሎት ያለመስጠቱን በግራቀኙ የታመነ ሆኖ አመልካች በበአል ምክንያት ነው ቢልም በዚህ መልኩ ያለማስረዳቱ ከስር ክርክር መረዳት ተችሏል፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1786 ስር እንደተመለከተው በአንድ ውል ውስጥ ውልን የሚያፈርሱ የስምምነቶች ቃል ተገልጾ ከተጻፈበትና የዚህም ስምምነት አፈጻጸም ጉዳይ ተሟልቶ ከተገኘ አንደኛው ተዋዋይ ውል ፈርሷል ሲል ለመግለጽ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ስንነሳ አመልካች በገባው የውል

www.abyssinialaw.com

ግዴታ መሰረት ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑ ተጠሪ ውሉን ያቋረጠ መሆኑን መግለጹ ከውለታቸውም ሆነ ከሕጉ የወጣ አሰራር አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ በጠየቀው ዳኝነት መሰረት ውሉ ስለፈረሰ ለአመልካች ከተከፈለው ክፍያ ውስጥ አገልግሎት የሰጠበት ሰዓት ክፍያ ብር 38,818.70 /ሰላሳ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ስምንት ብር ከሰባ ሳንቲም/ ተቀንሶ የተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ አመልካች ክፍሎ ከሆነ በሚያቀርበው ማስረጃ ለከፈለው አካል ከሚጠይቅ በስተቀር ተጠሪ ላላገኘው አገልግሎት ሊከፍል አይገባም በማለት ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለ ክፍያን ጨምሮ ብር 386,601.30 /ሶስት መቶ ሰማኒያ ስድስት ሺኅ ስድስት መቶ አንድ ብር ከሰላሳ ሳንቲም/ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9 ፐርሰንት ህጋዊ ወለድ ጋር፤ ውሳኔ ያገኘበት የገንዘብ መጠን 8 ፐርሰንት የጠበቃ አበል ብር 30,934.50 /ሰላሳ ሺኅ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ አራት ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ ለዳኝነት የተከፈለ ብር 6716.05 /ስድስት ሺኅ ሰባት መቶ አስራ ስድስት ብር ከዜሮ አምስት/ አመልካች ለተጠሪ ይመልስ፤ በማለት ሲወሰን የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ውሳኔ በማጽናት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የስር የፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 10332 የካቲት 20 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 150808 በቀን ሐምሌ 23 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ለዚህ ፍ/ቤት ክርክር ግራቀኙ ያወጡት ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## <u>ትእዛዝ</u>

- በዚህ ፍ/ቤት የተሰጠው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል ይጻፍ፡፡
- የውሳኔው ግልባጭ በየደረጃው ለሚገኙ የስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

# ከውል ውጪ ኃላፊነት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 117506

ግንቦት 8 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች ፡- የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ነገረ ፈጅ ኦስኒ በከር ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- አቶ አዲሱ ገዛኸኝ በሌሉበት ታይቷል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበው የዳርጎት ክስ ተጠሪ ኃላፊ የሚሆነው ለግማሹ ብቻ ነው? በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አይቶ ለመወሰን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች በተጠሪ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ ተጠሪ የአመልካች ሠራተኛ ሆኖ ንብረትነቱ የአመልካች የሆነውንና የመለያ ቁጥር 4-01647 ኢት የሆነ መኪና እያሽከረከረ እያለ አቶ ሚልኬሣ ደበላ የተባሉ ሰው ገጭቶ የሞት አደጋ በማድረሱ የአቶ ሚልኬሣ ደበላ ወራሾች በአመልካች ላይ የጉዳት ካሳ ክስ አቅርበው አመልካች ለክሱ ኃላፊ መሆኑ በፍርድ ተረጋግጧል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከወሰነው የካሣ ክፍያ ውስጥ ብር 38,704 (ሰላሣ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ አራት ብር) የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለአቶ ሚልኬሣ ደበላ ቤተሰቦች የከፈለ ሲሆን አመልካች በበኩሉ ወጭና ኪሳራን ጨምሮ ብር 11234 /አስራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሣ አራት ብር) ለሟች ወራሾች በፍርድ አፈፃፀም ተገዶ ከፍሏል፡፡ አመልካች ሟች ላይ የደረሰው አደጋ በሹፌሩ (በተጠሪ) ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት መሆኑ ተረጋግጦ ተጠሪ በወንጀል መዝገብ ቁጥር 08383 በከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ

www.abyssinialaw.com

መሆኑን ገልፆ አመልካች የመኪናው ባለ ሀብት በመሆኑ ምክንያት ለሟች ቤተሰቦች የከፈለውን ብር 11234 /አስራ አንድ ሺ ሁለት መቶ ሰላሳ አራት ብር) ሙሉ በሙሉ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ተከሳሽ (ተጠሪ) በመሆኑ ገንዘቡን እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት ከታየ በኃላ ተከሳሽ መክፈል ያለበት የራሱን ድርሻ ብር 5617 /አምስት ሺህ ስድስት መቶ አስራ ሰባት ብር) ብቻ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

3. አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች አደጋው የደረሰው በተጠሪ ጥፋት መሆኑ ተረጋግጦ ፤ ተጠሪ በወንጀል የተቀጣ በመሆኑ ጉዳዩን ሙሉ በሙሉ የመካስ ኃላፊነት ያለበት ተጠሪ ነው፡፡ ሆኖም የበታች ፍርድ ቤቶች አግባብነት የሌለውን የህግ ድንጋጌ በመጥቀስ ተጠሪ አመልካች የከፈለውን ቀሪ ገንዘብ ግማሹን ብቻ ነው የሚሸፍነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካቷል፡፡ ተጠሪ ታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ/ም ታትሞ በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ተጠርቶ ያልቀረበ በመሆኑ መልስ የመስጠት መብቱ እንዲታለፍ ይህ ሰበር ችሎት ጥር 18 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ ንብረትነቱ የአመልካች የሆነውን ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲያሽከረክር አቶ ሚልኬሣ ደበላን ገጭቶ የሞት አደጋ ያደረሰበት መሆኑ በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 45630 ህዳር 9 ቀን 2006 ዓ/ም በተሰጠው ውሳኔ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በሟች ላይ የሞት አደጋ ያደረሰው ተሽከርካሪ ባለሀብት የተጠሪ አሰሪ በመሆኑ በሟች ላይ ለደረሰው ጉዳት በእሱ በኩል የተፈፀመ ድርጊት ወይም ጥፋት ባይኖርም በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2081 (1) እና በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2130 መሠረት በኃላፊነት ተጠያቂ ሆኗል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ የአመልካችን መኪና ሲያሽከረክር በፈፀመው ጥፋት የሆነ ቸልተኝነት በሟች ላይ የሞት አደጋ በማድረሱ ለጉዳቱ በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2029 (1) እና በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2035 መሠረት ኃላፊነት አለበት፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ አመልካችና ተጠሪ ለጉዳቱ በአንድነትና በነጠላ በኃላፊነት የሚጠየቁ መሆኑን ከፍተብሔር ህግ ቁጥር 2155 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

5. በአንድ ሰው ላይ ለደረሰ ጉዳት ኃላፊነትን በሚጥሉ የተለያዩ የህግ ድንጋጌዎች ምክንያት ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ለጉዳቱ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ በሚሆኑበት ጊዜ ኃላፊ ከሆኑት ሰዎች አንዱ ብቻ ጥፋት የሠራ እንደሆነ በመጨረሻ የተወሰነውን ዕዳ ዕርሱ እራሱ ብቻ የመቻል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የፍተብሔር ህግ ቁጥር 2157 በግልጽ ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ በሟች ላይ ለደረሰው የሞት አደጋ አይነተኛው ምክንያት የተጠሪ ቸልተኝነት መሆኑ ተረጋግጦ ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 08383 ህዳር 11 ቀን 2005 ዓ/ም በሰጠው የወንጀል ፍርድ ተረጋግጧል፡፡ ይህም አመልካች የባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤትና የተጠሪ አሠሪ በመሆኑ በሟች ሚልኬሣ ደበላ ላይ ለደረሰው የሞት አደጋ ከተጠሪ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ነው ተብሎ በፍተብሔር የተወሰነበት ቢሆንም አደጋው የደረሰው በተጠሪ ጥፋት የሆነ ቸልተኛነት ምክንያት መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በጉዳት ምክንያት አመልካች የከፈለውን ወጭ ሙሉ በሙሉ የመሸፈን ህጋዊ ግዴታ ያለበት ተጠሪ መሆኑን ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2157 ድንጋጌ ይዘት መሠረታዊ ዓላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡

6. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ተጠሪ በፈጸመው ጥፋት ምክንያት ለሟች ቤተሰቦች የከፈለውን ብር 11234 /አስራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሣ አራት ብር) ተጠሪ ሙሉ በሙሉ እንዲተካለት አመልካች በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2161 መሠረት ያቀረበውን ክስ የስር ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2157 ድንጋጌዎች ይዘትና ህጋዊ ውጤት በአግባቡ ሣያገናዝብ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍተብሔር ህግ ቁጥር 2083 በመጥቀስ ተጠሪ የመሸፈን ግዴታ አለበት አመልካች ለሟች ወራሾች የከፈለውን ገንዘብ ግማሹን ብር 5617 /አምስት ሺ ስድስት መቶ አስራ ሰባት ብር ነው) በማለት የሰጠው ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማፅናቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 08383 ህዳር 11 ቀን 2005 በተጠሪ ላይ ያስተላለፈው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2157 መሰረት የሚያስከትለውን ውጤት ያላገናዘበ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 51830 ጥር 29 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 10501 ሀምሌ 9 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ አመልካች ለሟች ሚልኬሳ ደበላ ቤተሰቦች የከፈለውን ብር 11234 /አስራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሣ አራት ብር ) ሙሉ በሙሉ ለአመልካች የመክፈልና የመተካት ኃላፊነት አለበት በማለት በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2157 እና በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2161 ድጋጌዎች መሠረት ወስነናል፡፡
3. አመልካች በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭ ለራሱ ይቻል

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 119563

መስከረም 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

አብዩ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል አገልግሎት የአሉቶ ላንጋኖ ጂኦተርማል

አሉቶ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ -- ነ/ፈጅ ቦንቱ ቢራቱ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ሐጂ ነገዎ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በእርሻ መሬት ይዞታ ላይ ለደረሰ ጉዳት በኃላፊነት ስለመጠየቅና የካሳ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክሯል፡፡

የተጠሪ ክስ አመልካች በ2001 ዓ.ም መንገድ ሲሰራ ለውሃ መውረጃ ቦይ ሳያወጣ በመቅረቱ ውሃው 4 ቀረጥ የእርሻ መሬትን ስላበላሸ የ7 አመት የእርሻ ገቢ በመቋረጡ የ7 ዓመት ምርት 178 ኩንታል ስንዴ በ900 ብር ሒሳብ 151,200 / አንድ መቶ ሃምሳ አንድ ሺ ሁለት መቶ ብር / ያጣሁ ስለሆነ አመልካች በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1254፤ 2027 እና 2092 መሰረት እንዲከፍለኝ ሲሉ ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ጉዳቱ ከደረሰ 7 ዓመት ስለሞላው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.2143 መሰረት በይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ በፍሬ ነገሩም የመከላከያ መልሱን አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም ክርክሩ የአላባ ስለሆነ በማለት በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ በአመልካች ጥፋት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት የ6 ዓመት ምርት ብር 151,200 / አንድ መቶ ሃምሳ አንድ ሺ ሁለት መቶ ብር / እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር

www.abyssinialaw.com

በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምስራቅ ምድብ ችሎት አቅርበዋል፡፡ በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤቱም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 ካሳ የሚመለከት ሲሆን ካሳ ለመጠየቅ ደግሞ በሁለት አመት ውስጥ የሚል ስለሆነ በሁለት አመት አልጠየቀም፡፡ የሰባት ዓመት ሊጠይቅ አይችልም ስለሆነም የሁለት አመት ብቻ ነው መጠየቅ የሚችለው በማለት የሶስት አመት እንዲከፈለው ይኸውም የ151,200 ብር ግማሽ አመልካች እንዲከፍል ሲል የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በሚል ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካች ጥያቄ በ2001 ዓ.ም ይህን መንገድ በከፍተኛ ወጪ ሲሰራ የቀበሌውም ነዋሪዎች ከሳሽን ጨምሮ የወረዳውና የቀበሌው መስተዳድር አንድ ላይ በመሆን ከአዳሚ ቱሉ አስከ አለታ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ድረስ የሚሰራው መንገድ ለአከባቢው ህብረተሰብ ጠቃሚ መሆኑን አምኖበት በደስታ ተቀብለው መንገዱን እየተገለገሉበት ለ7 ዓመት ያህል ምንም አይነት ቅሬታ ለአመልካች ሆነ ለሌሎች ጉዳዩን ስልጣን ላላቸው የመንግስት አካል ሳያቀርቡ ዛሬ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የሌለው፤ በሁለት አመት ይርጋ ጊዜ የታገደ ነው በሚል የቀረበው ክርክር ውድቅ በማድረግ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበውን ግምት ሙሉ በሙሉ ይከፈል ብሎ ሲወስን የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም የ3 ዓመት ይከፈለው ሲል በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ደግሞ የቀረበው የይርጋ ጥያቄ ከጉዳዩ ጋር ስለማይገናኝ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ትክክለኛና ህገ መንግስታዊ መብቴን ያረጋገጠልኝ ስለሆነ ምንም የህግ ስህተት የለበትም ይህ የሚታለፍ ከሆነ በአማራጭ የጠቅላይ ፍርድ ቤትን ውሳኔ እንዲያፀናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ ቅድሚያ መታየት ያለበት ለክርክር ምክንያት የሆነው ጉዳት ደርሷል የተባለው በ2001 ዓ.ም ከመሆኑ አኳያ አመልካች ያነሳው የይርጋ ጥያቄ በስር ፍርድ ቤቶች በትክክል የመታየት ያለመታየቱን ይህ ቢታለፍ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚነት ያለው የሁለት አመት ይርጋ ነው ካለ በኋላ ተመልሶ የ3 አመት የታጣ ጥቅም የመወሰኑን አግባብነት ነው፡፡ አመልካች ለሚያሰራው የአሉቶ ላንጋኖ ጂኦተርማል አሉቶ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ የሚወስድ መንገድ ስራ ምክንያት በተጠሪ መሬት ይዞታ ላይ ጉዳት መድረሱ ፍሬ ነገሩን የማጣራት ስልጣን ባለቸው በስር ፍርድ

www.abyssinialaw.com

ቤቶች የተረጋገጠ ነው፡፡ በተጠሪ ክስ እንደተመለከተው በይዞታቸው ጉዳት የደረሰው ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑና እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ሳገኝ የነበረውን ጥቅም ማጣታቸውን ገልፀዋል፡፡ የተጠሪ ጥያቄ በቀጥታ ከውል ውጭ ኃላፊነት ጋር የሚገናኝ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በዚሁ መሰረትም ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ በአመልካች እየተነሳ ያለው ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል መቃወሚያ ነው፡፡ ከውል ውጭ ኃላፊነት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ ክስ ማቅረብ እንዳለበት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 ተመልክቷል፡፡ ይህ ማለት ከሁለት አመት በኂላ የሚቀርብ ክስ በይርጋ የሚታገድ ይሆናል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ በተጠሪ ሀብት ወይም ጥቅም ጉዳት የደረሰው ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑ አከራካሪ ጉዳይ አይደለም፡፡ በአመልካች ተግባር ምክንያት ለደረሰባቸው ጉዳት ካሳ የሰባት ዓመት ማግኘት የነበረባቸውን የምርት ዘመን ገምተው ክስ የመሰረቱት መጋቢት 23 ቀን 2007 ዓ.ም ነው፡፡ ክሱ የቀረበው ከስድስት ዓመት በኂላ መሆኑ ነው፡፡ ተጠሪ በመሬት ይዞታቸው ላይ ጉዳት መድረሱን ከማወቅና በወቅቱ ከመጠየቅ ያገዳቸውን ምክንያት አቅርበው የተከራከሩበት ሁኔታ የለም፡፡ በመሬት ይዞታቸው በየአመቱ ምርት የሚያገኙበት ላይ ጉዳት ለመድረሱ ወይም የቀረባቸውን ጥቅም ለማወቅ አንድ የምርት ዘመን ጊዜ በቂ ነው፡፡ በተጠሪ በኩል ያቀረበው ክርክር ጉዳቱ በየአመቱ እየጨመረ የሄደ እንጂ በአንድ ጊዜ የተከሰተ አይደለም በማለት ላቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም የጉዳቱ መጠን ሊጨምር እንደሆነ እንጂ ጉዳት ስለመድረሱ ላለማወቅ በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ክሱ ከውል ውጭ ኃላፊነት ለሚደርስ ጉዳት ካሳ ክስ መቅረብ ያለበት በህጉ በግለፅ የተቀመጠውን በማለፍ ከስድስት አመት በኂላ የቀረበ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ ሆኖ እያለ ይህንኑ በማለፍ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚሁ መሰረትም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.40951 ግንቦት 11 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ በመ/ቁ.225865 መስከረም 27 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ ክስ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2143 መሰረት ጉዳት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በሁለት አመት ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ስለሆነ አመልካች ሊጠየቅ አይገባም ብለናል፡፡ በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዘገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዘገብ ቤት ይመለስ፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

# ቤተሰብ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.116950

መጋቢት 23 ቀን 2008 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አስቴር በቀለ ጭጭ አይበሉ ሞግዚት አድራጊ ህፃን ማህደር የማነህ በሽህ

**ተጠሪ ፡-** የለም ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የማይንቀሳቀስ ንብረት (ቤት) ለመሸጥ የሚያስችል የሞግዚትነት ስልጣን ይሰጠኝ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በመ/ቁ 562/07 ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ባጭሩ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር 1590 የሆነው መኖሪያ ቤት ከሌሎች ወራሾች ጋር የሚካፈል ድርሻ ያላቸው በመሆኑ አመልካች ቤቱን መሸጥ መለወጥ እንዲችሉ ተጨማሪ የሞግዚትነት ስልጣን እንዲሰጣቸው መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤትም ምስክሮች አስቀርቦ እንደሰማ አመልካች ቤቱን በማከራየት በሚያገኙት ገቢ እንደሚተዳደሩ ቤቱን የሚወርሱ ሌሎች ልጆችም እንዳሉ ከእነዚህ የተወሰኑት ራሳቸውን ችለው እንደሚኖሩ አመልካች ሞግዚት የሆኑላት ዕድሜዋ 15 ዓመት እንደሆነ ከዚህ ቤት ውጪ ሌላ መኖሪያ ቤት እንደሌላቸው በመግለጽ መመስከራቸውን ፍ/ቤቱ መመዝገቡን የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ፍርድ ቤቱም አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ከመረመረ በኋላ ህፃን ማህደር የማነ ከሞግዚት ለመውጣት የተቃረበች ሲሆን ሌላ መኖርያ ቤት ስለሌላቸው እንዲሁም በዚሁ ቤት ኪራይ

www.abyssinialaw.com

እየተማረች እንደምትገኝ አስቀድሞ ቤቱ ቢሸጥ አካለመጠን ስላላደረሰኝ ድርሻዬ ሊጠፋበት እንደሚችል ፍ/ቤቱ ግምት በመውሰድ እንዲሁም ቢሸጥ ሌላ መኖሪያ ቤት እንደሌላቸው ፍ/ቤቱ የተገነዘበ ስለሆነ የአመልካችን አቤቱታ ፍ/ቤቱ ባለመቀበል መዝገቡን በብይን ዘግቶታል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እንዲሁም ለሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶችን ብይን ትዕዛዝና ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የጤና ችግር ያለባቸው በመሆኑ የህፃን ማህደር የማነን መሠረታዊ የኑሮ ወጪ ማሟላት እንዳልቻሉ ቤቱ ተሸጦ የቀለብ የልብስ የትምህርት ወጪ ካልተሸፈነ በቀር ቤቱን በማከራየት በሚያገኙት ገቢ ማሟላት አለመቻላቸውን ሌሎች ወራሾችም ቤቱ ቢሸጥ እንደማይቃወሙ በተገለጸበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው በሕጉ አግባብ አይደለም የሚል ክርክር ማቅረባቸውን የሚያሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 562/07 በ12/02/2007 ዓ/ም የማህደር የማነ በሻህ ሞግዚትና አስተዳዳሪ መሆናቸውን ፍ/ቤቱ እውቅና መስጠቱን በኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ነሐሴ 01 ቀን 2007 ዓ/ም የውክልና ስልጣን መውሰዳቸውን የሚያሰይ ማስረጃ ከመዝገቡ ጋር አያይዟል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት መጋቢት 16/2008 ዓ/ም በሰጠው ትዕዛዝም ህፃን ማህደር የማነ በሻህ በችሎት ቀርባ እንድታስረዳ ያደረገ ሲሆን መጋቢት 19 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠችው ቃል ወላጅ እናቷ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ማሟላት ከማይችሉበት ደረጃ የደረሱ በመሆኑ ቤቱ ተሸጦ ከዚህ የሚገኘው ገንዘብ ለቀለብ፣ ለትምህርት፣ ልብስ እና ሌሎች ወጪዎች እንዲሸፈኑላት ተቃውሞ እንደሌላት አስረድታለች፡፡ የአሁኑ አመልካችም ከቤቱ የሚያገኙት ገቢ ሌሎች ወራሾችም የሚካፈሉት እንደሆነ የጤና ሁኔታቸውም በጥሩ ሁኔታ የሌለ በመሆኑ ቤቱ እንዲሸጥ አመልክተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ይዘት ያለው ሲሆን ይህ ችሎትም አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

www.abyssinialaw.com

ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ በአመልካች የቀረበው ተጨማሪ የሞግዚትነት ስልጣን ይሰጠኝ ጥያቄ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ከህፃኗ የተሻለ ጥቅም /Best interest of the child/ አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን መመርመር መሆኑን ተረድተናል፡፡

አመልካች ከስር ፍርድ ቤት አንስቶ አጥብቀው የሚከራከሩት የሞግዚት አድራጊያቸውን መሠረታዊ ፍላጎቶች ማሟላት ባለመቻላቸው ከአባቷ በውርስ የምታገኘው የማይንቀሳቀስ ቤት ተሸጦ ለቀለብ ፣ትምህርት፣ ልብስና ተያያዥ ወጪዎች መሸፈኛ እንዲሆን ጠይቀው የስር ፍርድ ቤት ተማሪ (ህፃን) ማህደር የማነ ከሞግዚት ነፃ ለመውጣት ጥቂት ዓመት የቀራት መሆኑ ሌላ ቤትም የሌላቸው መሆኑ በመረጋገጡ ቤቱ ሊሸጥ አይገባም ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ አመልካች አሁን ያላቸው ህመም ቤተሰቡን ማስተዳደር የሚችል ገቢ ለማመንጨት የሚያስችላቸው እንዳልሆነና ቤቱ ካልተሸጠ በቀር የህፃን ማህደር የማነን የኑሮ ወጪ መሸፈን እንደማይችሉ ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ ባቀረቡት ክርክር የገለጹ ሲሆን አሁን ለአከለ መጠን ያልደረሰችውን ልጅ ጨምሮ ሁሉም ልጆቻቸው ቤት ቢሸጥ ተቃውሞ እንደሌላቸው የሚያሳይ ክርክር አቅርበዋል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያነጋገራት ተማሪ ማህደር የማነም እናቷ ቤተሰቡ የሚያስፈልገውን መሠረታዊ ነገሮች ለማሟላት በማይችሉበት ደረጃ በመድረሳቸው ቤቱ ቢሸጥ እንደማትቃወም አስረድታለች፡፡

በመሰረቱ አካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ሀብት በህጉ አግባብ ሊተዳደር እንደሚገባ ከፍ/ህ/ቁ. 280 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘት ያስገነዝቡናል፡፡ አካለ መጠን ያልደረሰው ሀብት ሊሸጥ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 289 (1) የተመለከተ ሲሆን መቃወሚያ የሚቀርብበት ስርዓትም በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 2 ተመልክቷል፡፤ ፍርድ ቤቶች ስለህፃናት መብትና ጥቅም ሲወስኑ የጉዳዩ ዓይነት ይዘትና ባህሪ ያገናዘበ መሆን እንዳለበት በየትኛውም መልኩ መብትና ደሕንናታቸው ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 36 (2) ሥር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ፍቺ በሚወሰንበት ጉዳይም የህፃናቱ አያያዝና የቀለብ ጉዳይ ትኩረት ከሚሹ ነጥቦች አንዱ ስለመሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213 /1992 አንቀጽ 113 ስር ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የህፃን ማህደር የማነ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ መሸፈን አለመቻላቸውን በዝርዝር ምክንያት አሰደግፈው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ህፃን ማህደር የማነ ለአካለ መጠን እየደረሰች እንደሆነና ቤቱ ከተሸጠ ለወደ ፊቱ ችግር ሊያጋጥም ይችላል በሚል እሳቤ ስለመሆኑ ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች ቤቱን በማከራየት የሚያገኙት 2000 ብር ለሌሎች ወራሾችም ድርሻ ድርሻቸው እንደሚያከፋፍሉ ገልጸው ይህ ቤት ከማከራየት የሚያገኙት ገቢ በየትኛውም መልኩ አሁን ያለውን ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ፍላጎት የማያሟላ ስለመሆኑ መከረከራቸውን ተረድተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

የአመልካች መሰረታዊ ጥያቄ ሞግዚት የሆኑለት ልጅ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ቤቱን በማከራየት ከሚገኘው ገቢ የማይሸፈን ከሆነ ሌላ ህጋዊ መፍትሔ መስጠቱ የህፃን ማህደር የማን ቀጣይ ሕይወት በተደለደለ መሠረት ለማኖር ወሳኝ ነው፡፡ ህፃን ማህደር የማነ የ10ኛ ክፍል ተማሪ እንደሆነች በችሎቱ ቀርባ አስረድታለች፡፡ ከዚህ መገንዘብ የምንችለው እስከ ኮሎጅ መግቢያ ድረስ ያለው ጊዜ ረጅም መሆኑን ነው፡፡ ወላጅ እናቷም ካላቸው የጤና እክል የህፃን ማህዳር የማን መሰረታዊ ፍላጎት ማሟላት በማይችሉበት ደረጃ መድረሳቸውን ችሎቱ ገልጿል የስር ፍ/ቤት የተማሪ ማህደር የማነ ከሚግዚት አስተዳደር ነፃ ለመውጣት የቀራት ጊዜ አጭር መሆንና ለወደ ፊቱ ያለው ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገበ ቢሆንም ህፃን ማህደር የማን አሁን ያለው ተጨባጭ የኑሮ ሁኔታ መሸፈን የሚችል አስተማማኝ የገቢ ምንጭ ያላት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ የህፃን ማህደር የማነ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ፍላጎት የማሟት ጉደይ የማይታለፍ መሰረታዊ ጥያቄ ከሆነ ቤቱን በመሸጥ ኑሮ እንድትደጉም ከማድረግ ውጭ ሌላ ህጋዊ መፍትሔ ያለውም፡፡ ህፃን ማህደር የማነ ትምህርቷን ሳይስተጓጎል መቀጠል የምትችለው መሰረታዊ የሆነውን ምግብ፣ ልብስ ፣ህክምና የተለያዩ የትምህርት መረጃ መፃሕፍት ማግኘት ስትችል ብቻ ነው፡፡ ህፃኗ ለወደፊቱ ራሷን መቻል የምትችለው አሁን በሚሰራው ስራ ነው፡፡ ህፃን ማህደር የማነ ትምህርቷን ሳታቋርጥ እስከ ዩኒቨርስቲ መዝለቅ የምትችለው ከወዲሁ በሚደረግ ድጋፍ ክትትልና እንክብካቤ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ህፃን ማህደር የማነ እና ሌሎች ወራሾች የሚጋሩት ቤት ሁሉም ባለመብቶች በተሳተፉበት አግባብ ሊሸጥ የሚገባው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካች የቀረበው ቤቱን በመሸጥ የህፃን ማህደር የማነ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ፍላጎት ላሟላ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ያለበቂ ምክንያት ውድቅ መደረጉ በጉዳዩ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን የሚያሳይ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

አመልካች ህፃን ማህደር የማነ እና ሌሎች ወራሾች የሚጋሩት ቤት እንዲሸጥ መወሰኑ ተገቢ መሆኑ ከታመነ ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ የህፃን ማህደር የማነ ድርሻ ገንዘብ በምን ሁኔታ ሊቀመጥ ይገባል የሚል ነው፡፡ ቤቱ ከተሸጠ በኃላ የህፃን ማህደር የማነ ድርሻ የሚታወቅ ሲሆን ገንዘቡ ለረጅም ጊዜ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አግባብ እንድትጠቀምበት ሞግዚት አድራጊዋ በህፃኗ ስም የሂሣብ ቁጥር ከፍተው ገንዘቡን ሊያስቀምጡ ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት የአሁኗ አመልካች በህፃን ማህደር የማነ የባንክ ሂሣብ ደብተር ከፍተው ቤቱ ከተሸጠ በኃላ ገንዘቡን በሙሉ ገቢ ካደረጉ በኃላ ለልጅቷ ተፈጥሮአዊና ሰብአዊ ፍላጎቷ ለቀለብ፤ ለትምህርት፤ለመኖሪያ ቤት ለጤና አጠባበቅ እና ለልዩ ልዩ ወጪዎች በየወሩ 1,000 (አንድ ሺህ/ ብር ወጪ እያደረጉ ሊጠቀሙ ይገባል ብለናል፡፡ በየወሩ ወጪ የሚደረገው 1,000 ብር የህፃን ማህደር የማነ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ፍላጎት የማያሟላ ከሆነና ይኸውም በበቂ ምክንያት ተደግፎ ከቀረበ የስር ፍ/ቤቶች ተገቢ ህጋዊ ትዕዛዝ የሚሰጡበት ሁኔታ በዚህ ውሳኔ የሚገደብ አይሆንም፡፡

www.abyssinialaw.com

በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቡት ቤት ለመሸጥ ይፈቀድልኝ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ የህፃን ማህደር የማነ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ፍላጎት ያላገናዘበ በመሆኑ ተገቢ አይደለም ብለናል፡፡ ቤቱም በንብረቱ መብት ያላቸው ወገኖች በተሳተፉበት ይሸጥ በማለት ወስነናል፡፡ ቤቱ ከተሸጠ በኃላ የህጻን ማህደር የማነ ድርሻ በስሟ በተከፈተ የሂሣብ ቁጥር ገቢ ሆኖ በየወሩ አንድ ሺህ ብር ወጪ ይደረግ ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ.562/07 በ19/09/2007 ዓ/ም የሰጠው ብይን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23752 በ8/10/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ የአስተዳደሩ ሰበር ሰሚ ችሎት በወ/ቁ. 23834 በ14/11/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ተሸሯል፡፡
2. አመልካች የህፃን ማህደር የማነ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ፍላጎት ማሟላት ባለመቻላቸው አመልካች እና ሌሎች ወራሾች የሚጋሩት በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር 1590 የሆነውን መኖሪያ ቤት ሁሉም ባለመብቶች ባሳተፈ መልኩ ይሸጥ ብለናል፡፡
3. ለክርከሩ ምክንያት የሆነው ቤት ከተሸጠ በኃላ የአመልካች ህፃን ማህደር የማነ ድርሻ በስሟ በተከፈተ የሂሣብ ቁጥር ገቢ ይሁን ብለናል፡፡ ህፃኗ በየወሩ ለሚያስፈልጋት መሠረታዊ የኑሮ ወጪ 1,000 (አንድ ሺህ /ብር በሞግዚቷ በኩል ወጪ እየተደረገ ይከፈል በማለት ወስነናል፡፡ በየወሩ ወጪ እንዲሆን የታዘዘው መጠን ገንዘብ የህፃኗ መሰረታዊ የኑሮ ወጪ የማይሸፍን መሆኑ ከተረጋገጠ ለመሻሻል የሚቀርበውን ጥያቄ ይህን ውሳኔ አያግድም ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.105694

መጋቢት 27 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች-፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ተሾመ ጎርፌ - ወራሽ ወ/ሮ መቅደስ ተሾመ - ጠበቃ አብርሃም ሀዲስ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፌሰሰች ወንድማገኝሁ - ወራሽ አቶ ጣሰው ተሾመ - ጠበቃ ሃልማ አቻሜ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታን አስመልክቶ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአመልካች ባለቤት የነበሩት ልጃቸው ወ/ሮ ተናኘ ተሾመ በሞት መለየታቸውን እና በጋብቻ ውስጥ ያፈሩት ንብረት በአመልካች እጅ የሚገኝ መሆኑን ገልጸው ውርስ እንዲጣራላቸው ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ08/08/2004 ዓ.ም. አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ ሲሆን አመልካቹም በ02/02/2005 ዓ.ም. በሰጡት መልስ በአመልካች እጅ ይገኛል የተባለው ንብረት የሟች ወ/ሮ ተናኘ ተሾመ የጋራ ንብረት ሳይሆን የአመልካቹ የግል ሀብት በመሆኑ ውርሱ ሊጣራ አይገባም ተብሎ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡ፍርድ ቤቱም ውርሱ ተጣርቶ እንዲቀርብ አጣሪ የመደበ ሲሆን አጣሪውም በተመራለት መሰረት ውርሱን አጣርቶ በ14/05/2005 ዓ.ም. የተጻፈ ሪፖርት አቅርቧል፡፡ የሪፖርቱም ይዘት በአዲስ አበባ ከተማ በቦሌ ክፍለ ከተማ በወረዳ 7 የሚገኘው ቁጥሩ 1177 የሆነው ቤት የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት መሆኑ ስለተረጋገጠ የቤቱ አጋማሽ እና ከኪራዩ የተገኘው ገንዘብ ብር 35,400 ውስጥ አጋማሹ ብር 17,700 የውርስ ሀብት ነው፣ለቤቱ ዕድሳት ወጣ የተባለው ብር 4,400 አጋማሽ የውርሱ ዕዳ አይደለም የሚል መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

www.abyssinialaw.com

ፍርድ ቤቱም በሪፖርቱ ላይ የግራ ቀኙን አስተያየት ከተቀበለ በኃላ የአሁኑ አመልካች ቤቱ የአመልካቹ የግል ሀብት በመሆኑ ሪፖርቱ ሊመዘገብ አይገባም በማለት ያቀረቡትን የመቃወሚያ አስተያየት ውድቅ በማድረግ ሪፖርቱን ተቀብሎ በመመዝገብ በመዝገብ ቁጥር 78124 በ26/09/2005 ዓ.ም. ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይግባኙን የተመለከተው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከቤቱ ኪራይ የተገኘውን ገቢ ወደ ብር 29,400 ዝቅ አድርጎ የውርስ ሀብት ሊሆን የሚገባውን የኪራይ ገንዘብ ወደ ብር 14,700 ዝቅ በማድረግ እና ለቤቱ ዕድሳት የወጣ ነው ከተባለው ብር 4,400 ውስጥ አጋማሹ ብር 2,200 የውርሱ ዕዳ መሆን ይገባዋል በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በዚህ አግባብ በማሻሻሉ የሁለቱም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ በተጠሪ አውራሽ እና በአመልካች መካከል በ1975 ዓ.ም. ባህላዊ ጋብቻ ስለመፈጸሙ የተረጋገጠ ነገር እንደሌለ ከመንግስት ተቋም ተገናዝቦ የተሰጠ ማስረጃ ስላለመኖሩ ከመንግስት ተቋም ለስር ፍርድ ቤት ከተሰጠው ምላሽ እና በባህል ጋብቻ ውሉ ላይ በእማኝነት የፈረሙት ግለሰቦች በ1975 ዓ.ም. ከፊሎቹ ያልተወለዱ እና ከፊሎቹም በወቅቱ ለአካለመጠን ያልደረሱ በመሆናቸው በግራ ቀኙ መካከል በ1975 ዓ.ም. ጋብቻ መፈጸሙ አልተረጋጠም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገውን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በምስክሮች ተረጋግጧል የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ የመሻሩን አግባብነት ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት እና ለሰበር ክርክሩ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ በስር ፍርድ ቤቶች የተደረገውን የክርክር ጭብጥ መሰረት ያደረጉ ናቸው ወይስ አይደሉም?
2. የአከራካሪው ቤት አጋማሽ እና የኪራይ ገቢው አጋማሽ የውርስ ሀብት ነው በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 78124 በ26/09/2005 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ በከፊል በማሻሻል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ

www.abyssinialaw.com

ቁጥር 137902 በ28/11/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ነው።ይህንንም አመልካቹ በ12/12/2006 ዓ.ም. አዘጋጅተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መግቢያ ላይ በትክክል አስፍረዋል።አመልካቹ ይህንን በትክክል ካሰፈሩ በኃላ ግን ዝርዝር አቤቱታቸውን ያቀረቡት በሁለቱ የስር ፍርድ ቤቶች ከላይ በተጠቀሱት መዝገቦች በተሰጡት ውሳኔ ላይ ሳይሆን ይልቁንም የአመልካች እና የተጠሪዋ አውራሽ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ተገቢውን ስርዓት አሟልቶ የተሰጠ ባለመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል በማለት የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05087 በ02/04/2006 ዓ.ም. ከሰጠው ውሳኔ ጋር አያይዘው ነው።

በመሰረቱ ይህ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ አመልካቹን ተጠቃሚ የሚያደርግ ሲሆን በይግባኝ የተለወጠ ስለመሆኑም የመዝገቡ ግልባጭ የሚጠቁመው ነገር የለም። በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05087 በ02/04/2006 ዓ.ም. በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ የተሰማው ወገን ካለ ጉዳዩ ስርዓቱን ጠብቆ ሲቀርብ ከሚታይ በቀር በስር ሁለቱ ፍርድ ቤቶች ከነበረው ክርክር ጋር ግንኙነት የሌለውን ውሳኔ መሰረት አድርገው አመልካች የሰበር ክርክር ሊያቀርቡ የሚችሉበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም። በውርስ ማጣራቱ ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ቤቱን ያፈራሁት ከጋብቻው በፊት ነው ከማለት በቀር የተጠሪዋ አውራሽ ባለቤታቸው የነበሩ ስለመሆኑ አመልካች ክደው ያቀረቡት ክርክር ባለመኖሩ ምክንያት በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በውርስ ማጣራቱ ጉዳይ በስር ፍርድ ቤቶች ከነበረው የክርክር ጭብጥ እና ከተሰጠው ውሳኔ ጋር ግንኙነት የሌለው መሆኑ እና ውሳኔው ተጠቃሚ የሚያደርገውም አመልካቹን መሆኑ እየታወቀ፣እንዲሁም በይግባኝ የተለወጠ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ የሚጠቁመው ነገር ሳይኖር ውሳኔው የሰበር ክርክሩ መነሻ እንደሆነ እና በበላይ ፍርድ ቤትም እንደተሻረ ተወስዶ በአጣሪው ችሎት የተያዘው ጭብጥ የመዝገቡን ግልባጭ መሰረት ያደረገ አለመሆኑን ተገንዝበናል። በመሆኑም አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት እና ለሰበር ክርክሩ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ በስር ፍርድ ቤቶች የተደረገውን የክርክር ጭብጥ መሰረት ያደረጉ ናቸው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም።

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ከላይ እንደተገለጸው በውርስ ማጣራቱ ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ቤቱን ያፈራሁት ከጋብቻው በፊት ነው ከማለት በቀር የተጠሪዋ አውራሽ ባለቤታቸው የነበሩ ስለመሆኑ አመልካች ክደው ያቀረቡት ክርክር አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ በግልጽ ያመለክታል። ይህንን ክርክር በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርቤ ነበር በማለት አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃም ቢሆን ያቀረቡት ክርክር የለም። አከራካሪው ቤት በአመልካች እና በተጠሪዋ አውራሽ በጋራ የተሰራ ስለመሆኑ በተጠሪዋ ብቻ ሳይሆን አመልካች ራሳቸው ካሰሟቸው ምስክሮች መካከል በከፊሎቹ ጭምር የተረጋገጠ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ

www.abyssinialaw.com

ያመለክታል፡፡አመልካች ከስርዓት ውጪ የተሰጠ ነው የሚለትን የጋብቻ የምስክር ወረቀት በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲሰረዝ ካደረጉ በኃላ ይኸው ውሳኔ በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲታይላቸው በይግባኝ ሰሚው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ጠይቀው የነበረ መሆኑን ከመዝገቡ ግልባጭ ማረጋገጥ የተቻለ ቢሆንም በመሰረቱ በስር ፍርድ ቤት ክደው ያልተከራከሩበትን ነጥብ በይግባኝ ደረጃ ክደው እና ክርክራቸውንም ለውጠው የሚከራከሩበት አግባብ በስነ ስርዓት ሕጉ በአንቀጽ 329 (1) ድንጋጌ መሰረት ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጨማሪ ማስረጃ ጥያቄያቸውን አልፎ የመዝገቡን ግልባጭ መሰረት በማድረግ ውሳኔ መስጠቱ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት ካለመኖሩም በላይ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሰጡት መልስ ይዘት እና በግራ ቀኙ ምስክሮች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አንጻር የጋብቻ የምስክር ወረቀቱ ተገቢውን ስርዓት ተከትሎ የተሰጠ አይደለም ተብሎ መሰረዙ በአመልካች እና በተጠሪዋ አውራሽ መካከል ጋብቻ አልነበረም ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ባለመሆኑ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05087 በ02/04/2006 ዓ.ም. ከሰጠው ውሳኔ ጋር አያይዘው የሚያቀርቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 78124 በ26/09/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 137902 በ28/11/2006 ዓ.ም. ተሻሽሎ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
3. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 225588 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ19/09/2007 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ፣እንዲሁም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 207228 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ26/09/2007 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ ሃ/ወ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 114279

መጋቢት 30 ቀን 2008ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ ደስታ ታከለ - ወኪል አቶ ታከለ በቀለ ቀርቧል /VC/

ተጠሪ፡- አቶ ፀጋ ታዲየስ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በባልና ሚስት በገጠር የእርሻ ይዞታ ላይ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበረችው የአሁኗ አመልካች በአንከሻ ጓግሳ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረበችው ክስ ነው፡፡ ከሳሽ በ6/10/2006 ዓ.ም አዘጋጅታ ያቀረበችው ክስ ይዘትም ባጭሩ ከተጠሪ ጋር በባልና ሚስትነት ስንኖር ጋብቻው በፍቺ የፈረሰ ሲሆን የጋራ የሆነ 8 ቃዳ መሬት በድርሻዬ እንዲያካፍለኝ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቃለች፡፡

ተከሳሽ በበኩሉ በ13/10/2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ማመልከቻ በስሜ የተመዘገበ የግሌ እንጂ አመልካችን የሚመለከታት አይደለም ልትካፈል አትችልም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ሲል ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ 4 ቃዳ መሬት መኖሩን በማረጋገጥ ግራ ቀኙ በጊዚያዊ የይዞታ መረጋገጫ ደብተርና በጋብቻ ውል ያደረጉ ስለመሆኑ ተረጋግጠዋል፡፡ የአ/ብ/ክ/መ ቤተሰብ ህግ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 53/1/ የመሬት ይዞታ በአንዱ ስም ከተሰጠ በኋላ ጋብቻ ሲፈፀም ተጋቢዎች መሬትን የጋራ ለማድረግ ሊሰማሙ እንደሚችሉ አዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 24/3/ ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ 4 ቃዳ ግማሹ ይሰጥ ወይም ያካፍል

ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ይኸው ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ተቀባይነት በማግኘቱ የግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይህ ጋብቻ ሲመሰረት የጋራ የማድረግ ስምምነት የለም፡፡ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት በአዋጅ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 58 መሰረት ጋብቻ የማደስ ሁኔታ መኖሩን ይደነግጋል፡፡ ይህ ውል ፍርድ ቤት ቀርቦ መፅደቅ አለበት ካልፀደቀ ግን ፈራሽ ይሆናል፡፡ ግራ ቀኙ ያደረጉት ጋብቻ የማደስ ውል በፍርድ ቤት አልፀደቀም ስለሆነም ፈራሽ ነው በማለት በስር ፍርድ ቤቶች አመልካች 4 ቃዳ ግማሽ ልትካፈል ይገባል በማለት የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ ክስ የቀረበባቸውን መሬቶች ሊያካፍል አይገባም ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 11 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የምትልበትን ምክንያቶች ዘርዝራ አቅርባለች፡፡

የቀረበውን የሰበር አቤቱታ በመመርመር በዚህ ጉዳይ ግራ ቀኙ ተጠቃሹን የመሬት ይዞታ በጋራ ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑ ባልተካደበት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጋብቻ ውሉ ለፍርድ ቤት ቀርቦ አልተመዘገበም በማለት የእርሻ መሬቱ የተጠሪ የግሉ ነው ሲሉ የመወሰናቸውን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ጥሪ የተደረገለት ቢሆንም ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው መሬት አመልካችና ተጠሪ 18 ዓመት በጋራ ሲጠቀሙበት ከዚያም ጋብቻቸው ጥር 23 ቀን 2005 ዓ.ም በተደረገው የማደስ ስምምነት የጋራ እንደሆን ያደረጉ መሆናቸው በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠና በተጠሪም የተካደ አይደለም፡፡ ከስምምነት በኋላ በይዞታ ማረጋገጫ ላይ በጋራ በስማቸው የተቆጠረ መሆኑ የተረጋገጠ ነው፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ትዳር ፀንቶ ባለበት የትዳር ውል በፍርድ ቤት ያልተመዘገበ ስለሆነ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያለውና የሌለው መሆኑን መመርመር ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የተሻሻለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 24/3/ መሰረት የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በአንዱ ስም ተዘጋጅቶ ከተሰጠ በኋላ ጋብቻ ከተፈፀመ ተጋቢዎቹ መሬቱን የጋራ ለማድረግ ሊስማሙ እንደሚችሉ በግልፅ ተመለክቷል፡፡ ይህ

www.abyssinialaw.com

አዋጅ ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 20/6/ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በአንዱ ስም ተዘጋጅቶ ከተሰጠ በኂላ ጋብቻ የተፈፀመ እንደሆነ ተጋቢዎች ይህንኑ ፍሬ ነገር አግባብ ላለው የቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃመም ኮሚቴ በወቅቱ ገልፀው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ ተሻሽሎና በሁለቱም ስም ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው ማመልከት እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡ አመልካችና ተጠሪ ህጉን ተከትለው በተጠሪ ሰም የነበረውን የጋራ ማድረግ በመሰማማት ለሚመለከተው አካል ጥያቄ አቅርበው በሁለቱ ተጋቢዎች ስም የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የተሰጣቸው መሆኑን ፍሬ ነገር የማጣራትና መመዘን ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን በተመለከተ ባለው ልዩ ባህሪ ራሱን ችሎ ሕግ የወጣለት ሲሆን የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በአንዱ ስም ተዘጋጅቶ ከተሰጠ በኂላ ጋብቻ ከተፈፀመ ተጋቢዎቹ መሬቱን  የጋራ ለማድረግ ሲፈልጉ እንዴት ሊለወጥ እንደሚችል ስርዓት የተዘረጋለት መሆኑን ከህጉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የገጠር መሬትን በሚመለከት በሚነሱ ጉዳዮች ህጉ ግልፅ እስከሆነ ድረስ ተግባራዊ ማድረግ የግድ ይላል፡፡ የገጠር መሬትን እንደ ሌላው ንብረት በመቁጠር በቤተሰብ ህጉ አንፃር የሚታይ አይደለም፡፡ መታየት ያለበት የግራ ቀኙ ተጋቢዎች በገጠር መሬት አዋጁ መሰረት በአንድ ተጋቢ ሰም ብቻ የነበረውን የጋራ ለማድረግ ስምምነት መኖሩን ወይም አለመኖሩን ነው፡፡

ስለዚህ አመልካችና ተጠሪ የገጠር መሬት አዋጅና ደንብ ተከትለው በመስማማት የጋራ ያደረጉትን በሁለቱ ስም የይዞታ መረጋገጫ ደብተር የተሰጣቸውን በፍርድ ቤት ያልፀደቀ ነው በማለት አግባብነት የሌለው የቤተሰብ ህግ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 58 በመጥቀስ ውሉ ፈራሽ ነው ሲል የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.38441 ግንቦት 10 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአንከሻ ጓግሳ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.2743/05 የካቲት 12 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ እና በአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መ/ቁ. 01-08191 መጋቢት 5 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠ ትእዛዝ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪ 4 ቃዳ መሬት ግማሹን ለአመልካች ያካፍል ብለናል፡፡
4. የአንከሻ ጓግሳ ወረዳ ፍርድ ቤት በዚህ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈፅም የውሳኔው ቅጂ ይላክለት፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.113002

ሚያዚያ 28 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ባልቻ አበበ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አልማዝ ዓሊ - ቀርበዋል

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የሎሜ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 44429 በ12/12/2006 የሰጠውን ብይን የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 38920 በቀን 09/04/2007 ዓ.ም የሻረው ቢሆንም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምስራቅ ችሎት በመ/ቁ 200327 በቀን 01/07/2007 የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ የሻረ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 204019 በ17/07/2002 ዓ.ም መሠረታዊ ስህተት አልተፈፀመም በማለቱ በዚህ ሰበር ችሎት ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበው የጡረታ አበልን አስመልክቶ ከፍቺ በኂላ ስለሚኖረው ውጤት ነው በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት ተጠሪ ሲሆኑ አመልካች ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የክሱ ይዘት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከተጠናቀቀ በኂላ የንብረት ክፍፍል አድርገዋል ፣አመልካች በተጠሪ ኪራይ ቤት ላይ የተደገፈውን ቤትና ሱቅ አፍርሶ ያንሳልኝ የጡረታ አበልም እንድንካፍል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡፡ አመልካችም በሰጠው መልስ ሱቁን አስመልክቶ በ5/11/2006 የተጻፈ የስምምነት ደብዳቤ አለ በዚሁ መሠረት ቀበሌው አካፍሎን ተለያይተናል፡፡ የጡረታ አበልን አስመልክቶ የማግኘት መብት የላትም ብሏል፡፡ ፍርድ ቤቱም መርምሮ የሞጆ ከተማ ቀበሌ 02

www.abyssinialaw.com

አስተዳደር በቁጥር 602/930/2006 በ07/11/2006 በተጻፈ ደብዳቤ በ5/11/2006 ዓ.ም የተስማሙ መሆኑን የገለፀ በመሆኑ ቤቱን አፍርሶ እንዲያነሳ በማለት የቀረበውን አልተቀበልኩም የጡረታ አበል አመልካችና ተጠሪ አብረው በቆዩ ወቅት ከደመወዝ ላይ ተቆርጦ ሲከማች የኖረ በመሆኑ እንደጋራ ሀብት የሚወሰድ ነው ስለዚህ እኩል ይካፈሉ በማለት ሲወስን አመልካች በዚህ ውሳኔ ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በጡረታ የሚኖር በመሆኑ በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 78/1/ መሠረት አብረው ሠርተው የሚያገኙትን እንጂ የጡረታ አበልን አይጨምርም በአዋጅ ቁ 45/95 አንቀጽ 44 የጡረታ አበልን እኩል ይካፈሉ የሚል መሠረታዊ ህግ ያለው ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም የቀበሌ ቤት በስምምነት በኪራይ የሚገኝ ነው የግል ንብረት አይደለም ተጠሪ የግል ቤት እንዳላት ከሞጆ ከተማ ቀበሌ 02 የተጻፈ ደብዳቤ ያለ በመሆኑ የቀበሌውን ኪራይ ቤት እንድትለቅ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምስራቅ ምድብ ችሎት ያቀረቡትን ይግባኝ ፍርድ ቤቱ ተመልክቶ የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አዋጅ 83/96 አንቀጽ 78/1/ ባልና ሚስት በጋብቻ ውስጥ እያሉ የግልም ሆነ የጋራ ንብረት ከጋራ ንብረት ላይ የሚገኝ ገቢ ሁሉ የጋራ ንብረት እንደሆነ አስቀምጧል፡፡ በግል ጥረት የሚገኘው ደመወዝ ላይ የሚቆረጠው የጋራ ንብረት እንዲሆን ነው ጡረታ አዋጅ 345/1995 አንቀጽ 7 የጡረታ ገንዘብ ከደመወዝ የሚቆረጥ ነው ሠራተኛው የሞተ እንደሆነ ሚስት የሚከፈላት ጡረታ ገንዘብ ግማሹን እንደሆነ አንቀጽ 35 ደንግጓል ስለዚህ ከ1960 ጀምሮ ባልና ሚስት ሆነው ከጋራ ደመወዝ ሲቆረጥ የቆየው ገንዘብ ጡረታ በሚወጣ ጊዜ የሚከፈለው ገንዘብ ስለሆነ የጋራ ነው እኩል ይካፈሉ የመንግስት ቤትን በተመለከተ ደሀ ለሆኑ የግል ቤት መስራት ለማይችሉ አቅመ ደካማ ተከራይተው እንዲኖሩ ነው ተጠሪ የግል ቤት እንዳላት አላስተባበለችም ስለዚህ ቤቱ ለአሁን አመልካች ሊሆን ይገባል በማለት የቀበሌ ቤት እንድታስረክብ ብሏል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም መሠረታዊ ስህተት የለውም በማለት አፅድቋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንን በመቃወም ሲሆን የሰበር አቤቱታው በአጭሩ አመልካች የመንግስት ሠራተኛ ሆኜ የተቀጠርኩት ተጠሪን ከማግባቴ 2 ዓመት በፊት ሲሆን ተጋብተን ብዙ ልጆች ወልደን ጋብቻችን በፍቺ ከተቋረጠበት 2006 ዓ.ም በፊት በጡረታ ተገልዬ ኖረናል፡፡ አብረን በመኖር ላይ ሳለን እኔ ቀድሜ ብሞት ግማሽ ጡረታ የማግኘት መብት እንዳላት የማይካድ ቢሆንም ከፍቺ በኋላ በእኔ ድካም የተገኘውን የጡረታ አበል እንድትካፈል የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም ይህንን አቤቱታ መርምሮ ባልና ሚስት ጋብቻቸው ከፈረሰ በኋላ ለአንደኛው ወገን ይከፈል የነበረ ጡረታ ለሌላኛው ወገን ሊከፈል የሚገባ መሆን አለመሆኑን ከአዋጅ ቁ 345/95 አንቀጽ 7

www.abyssinialaw.com

እና ከቤተሰብ ህጉ ዓላማ አንጻር ለመመርመር ያስቀርባል በማለት ተጠሪ በሰጠችው መልስ ስለቀበሌ ቤት እና ውርስ ቤት በተመለከተ የተነሳው ክርክር በሌላ ፍርድ ቤት እየታየ መሆኑን በመግለጽ ያስቀርባል ከተባለው ነጥብ አንጻር ሲመረመር አመልካች የ9 ወር ደመወዝ ከወሰደ በኋላ ነው ጋብቻ የመሰረትነው፣ በአመልካች መ/ቤት በጡረታ ተመዝግቦ የጡረታ አበሉን 7 ዓመት ሙሉ አብረን ተጠቅመናል ስለዚህ የጋራ በመሆኑ ልንካፈል የሚገባ ሲሆን በህይወት መኖርና ከዚህ ከጡረታ አበል ድርሻዬን ብቻ እንጂ የአመልካችን የሚመለከት አይደለም። የሚል ነው አመልካችም የመልስ መልስ አቅረበዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ያስቀርባል ከተባለው ነጥብ አንጻር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረነዋል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች እና ተጠሪ በባልና ሚስትነት ተጋብተው አብረው በሞጆ ከተማ ውስጥ ከ40 ዓመት ላላነሰ ጊዜ የኖሩ ቢሆንም ጋብቻቸው በፍቺ በመጠናቀቁ የፍቺ ውጤት በሆነው የንብረት ክፍፍል ክርክር አድርገዋል። ተጠሪ እና አመልካች በዚሁ የንብረት ክፍፍል ላይ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እያገኙ በመጣው የቀበሌ የኪራይ ቤት ባለ ይዞታነት አስመልክቶ በሌላ ፍርድ ቤት ክርክር ላይ በመሆናቸው በዚህ መዝገብ አልተመረመረም ሆኖም የአመልካችን የጡረታ ክፍያ አስመልክቶ የስር ፍርድ ቤት የጋራ በመሆኑ ሊከፈል ይገባል በማለት የሰጡትን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ተመርምሯል። አመልካችና ተጠሪ አመልካች ከጋብቻ በፊት በመንግስት ሥራ ላይ የጡረታ መዋጮ እየከፈሉ የቆዩበትን ጊዜ በተመለከተ 2 ዓመት እና 9 ወር በማለት ከመለያየታቸው ውጭ በጋብቻ የቆዩበትን ጊዜ እና በጋብቻ ውስጥ እያሉ አመልካች በጡረታ ከሥራው መገለሉን አስመልክቶ ልዩነት የላቸውም። ስለሆነም በዚህ ላይ ምላሽ ማግኘት የሚገባው ከተጋቢዎቹ አንዱ በጡረታ የሚተዳደር በሆነ ጊዜ ጋብቻው በፍቺ ቢጠናቀቅ የጡረታ አበል ክፍያው በጋብቻ ወቅት በተደረገ መዋጮ ወደፊት የሚከፈል በመሆኑ የጋራ ሆኖ ለተጋቢዎች የመከፈል ውጤት ይኖረዋል ወይስ አይኖረውም የሚለው ነው።

የጡረታ ገንዘብ ምንጩ ምን እንደሆነ በወቅቱ ተፈፃሚነት በነበረው በመንግስት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 5 እንደተመለከተው ከአሰሪው ስድስት በመቶ /6%/ ከመንግስት ሠራተኛው አራት በመቶ /4%/ ነው። እዚህ ላይ የአሁን ተጠሪ መከራከሪያ በጋብቻ ውስጥ በነበርን ጊዜ ከአመልካች ደመወዝ እየተቀነሰ የሚከፈለው 4% በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 83/96 አንቀጽ 78/1/ መሠረት የጋራ ከሆነው ደመወዝ በመሆኑ የጡረታ አበሉ የጋራ ሊባል ይገባል በሚል ሲሆን አመልካች ደግሞ የሚከራከረው የጡረታ አበል የሚከፈለው ለአመልካች ነው ተጠሪ ልትካፈል የምትችለው በጋብቻ ውስጥ ሳለን ብሞት ብቻ ነው ከፍቺ በኋላ

www.abyssinialaw.com

ግን ልትካፈል የሚያስችል መብት የላትም በማለት ነው፡ በመሠረቱ ለጡረታ ተብሎ ከህግ በመነጨ ቅድመ ሁኔታ የሚከማች ገንዘብ ባል ወይም ሚስት ካከማቹት ተጠራቅሞ እራሱን ችሎ ለክፍያ ይውላል ወይም ይሸፍናል ተብሎ መደምደሚያ ሊያሰጥ የሚችል አይደለም፡፡የጡረታ አበል ለአንድ ሠራተኛ የሚከፈለው ዕድሜው በገፋበት እና ጉልበቱ በደከመ ጊዜ መጦሪያ የሚሆነው ለመኖር የሚያስፈልገውን ወጪ በከፊልም ቢሆን በመሸፈንና ማህበራዊ ደህንነቱን ዋስትና ለመስጠት መንግስት ካለው የማህበራዊ ደህንነት ዋስትና ፖሊሲ የመነጨ በመሆኑ እንደማንኛውም ገቢ የጋራ ንብረት ነው የሚባል እንዳልሆነ የሰበር ችሎት በመ/ቁ 34384 አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ በነበሩ ጊዜ አመልካች ጡረታ አበል ማግኘት መጀመሩን 7 ዓመት መኖራቸውን ከዚህ በኋላ ፍቺ የተፈፀመ መሆኑ በስር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ የሚገኝ ፍሬ ነገር ነው፡፡ አመልካች በጡረታ ከተገለሉ በኋላ ፍቺ መፈፀሙን ምክንያት በማድረግም የጡረታ አበል ሊካፈል አይገባም የሚለውን መከራከሪያ ያነሳሉ በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ 345/95 አንቀጽ 35 ለሚች ሚስት ወይም ባል የሚከፈለውን የጡረታ አበል ሲደነግግ ሟች ያገኝ የነበረውን የጡረታ አበል 50% /ሃምሳ በመቶ/ የሚሆን እና ሆኖም ይህንን በመቀበል ላይ እያለ ካገባ በመከፈል ላይ ያለ አበል እንደሚቋረጥ ያመለክታል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው ባልና ሚስት በጋብቻ ውስጥ ሳሉ የጡረታ ባለመብት የሆነው ባል ወይም ሚስት ከሞቱ ስለሚኖር የጡረታ አበል ክፍያ ነው ስለሆነም ባል ወይም ሚስት የጡረታ አበል ተጠቃሚ ሆነው ባሉበት ፍቺ ቢከሰት የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነው ባልና ወይም ሚስት የጡረታ አበል ለባል ወይም ለሚስት ሊያካፍል የሚገባ ስለመሆኑ አይደለም፡፡ስለሆነም የአመልካች የጡረታ አበል ለተጠሪ ሊከፈል ይገባል በማለት የስር ፍ/ቤቶች የደረሱበትን ድምዳሜ መሠረታዊ ስህተት ያለበት በመሆኑ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የሎሜ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 44429 በ12/12/2006 የኦሮምያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምስራቅ ችሎት በመ/ቁ 200327 በቀን 01/07/2007 ዓ.ም እና የኦሮምያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 204019 በቀን 17/07/2002 የሰጡት ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 38920 በቀን 04/04/2007 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች የሚያገኘው የጡረታ አበል የጋራ ንብረት ተደርጐ ለተጠሪ ሊካፈል አይገባም ብለናል፡፡ ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ ት/ጌ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 116119

ቀን 22/09/08ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሙሉ በዳዳ -አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡-

1. ወ/ሮ ኩሪ በዳዳ -ቀረቡ
2. ወ/ሪት መስከረም በዳዳ
3. ወ/ሪት ውድነሽ በዳዳ

(2.–3.) አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች ለአ/አ/ከ/አስ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበውት በነበረው አቤቱታ መሰረት አመልካች የሟች አቶ በዳዳ ባቱ ህጋዊ ወራሽ ናቸው፡፡ በማለት የወሰነ ሲሆን ተጠሪዎች ይህን ውሳኔ በመቃወም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት ባቀረቡት መቃወሚያ የመቃ/ተጠሪ የሟች አቶ በዳዳ ባቱ ልጅ አይደሉም፡፡ የተሰጣቸው የወራሽነት ውሳኔ ይሻርልን ብለዋል፡፡ የመቃ/ተጠሪ በበኩላቸው ሟች አባቴ ናቸው የተወለድኩት ሟች ከእናቴ ጋር በትዳር አብረው ሲኖሩ በነበሩበት ጊዜ ነው፡፡ የወራሽነት ውሳኔው ሊሻር አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራቀኙን ክርክር ከቀረቡት ማስረጃ ጋር በመመርመር ለመቃ/ተጠሪ ቀደም ሲል የሰጠው የወራሽነት ውሳኔ እንዳይፈጸም በማገድ የመቃ/ተጠሪ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ልጅነታቸውን አረጋግጠው በመጡ ጊዜ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብታቸው ተጠብቋል ብሎ መዝገቡን ዘጋው፡፡

www.abyssinialaw.com

የመቃ/ተጠሪ (የአሁን አመልካች) በዚህ ትእዛዝ ላይ ቅሬታቸውን በየደረጃው ለይግባኝ ሰሚ ችሎቱ እና ለሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የስር ፍ/ቤትን ትእዛዝ ለማሳረም ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች አቶ በዳዳ ባቱ ልጅ መሆናቸው ተረጋግጦ የወራሽነት ማስረጃ ካገኙ በኋላ ተጠሪዎች በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 167 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት የመካድ ክስ ባላቀረቡበት ሁኔታ በሌላ የመቃወም ዘዴ ተጠቅመው የአመልካችን የወራሽት ማስረጃ ውድቅ እንዲሆን ያደረገበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከዚህ በላይ የተመዘገበው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ የሰበር አቤቱታው እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም፡- በአባት በኩል ያለን መወለድ መቃወም የሚቻለው የልጁ አባት ነው ተብሎ በህግ ግምት የሚሰጠው ሰው፤ እሱ የሞተ ወይም ችሎታ ያጣ እንደሆነ ከተወላጆቹ አንዱ የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ስለመሆኑ ከተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/1992 አንቀጽ 167፣174 እና 179 ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች ስር ፍ/ቤት የመቃወም አቤቱታ ያቀረቡት የአሁን አመልካች የሟች አቶ በዳዳ ንጋቱ ልጅ ሳይሆኑ የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልን በሚል ሲሆን የአሁን አመልካች የተወለድኩት በጋብቻ ውስጥ ነው፡፡ ይህን መቃወም የሚቻለው የመካድ ክስ በማቅረብ ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት ክርክር ያደረጉ መሆኑን ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ የአሁን አመልካች ስር ፍ/ቤት በነበረ ክርክር እና በዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት ክርክር በጋብቻ ውስጥ የተወለዱ መሆኑን ጠቅሰው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎች ይህን በማስተባበል በሰበር መልሳቸው በግልጽ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ አመልካች በጋብቻ ውስጥ የተወለዱ መሆኑ ካልተካደ ደግሞ ልጅነታቸውን እንዲያረጋግጡ አይጠበቅም፡፡ የአሁን ተጠሪዎች የአመልካችን ተወላጅነት ለመካድ ክስ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ የሚገባቸው ሲሆን የስር ፍ/ቤት ከዚህ በላይ በተጠቀሱ የቤተሰብ ህጉ ድንጋጌዎች መሰረት ጉዳዩን ለማየት በህግ ስልጣን በተሰጠው ፌ/ፍ/ቤት የመካድ ክስ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጥቶ የመቃወም አቤቱታውን ውድቅ ማድረግ ሲገባው የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ተመልክቶ ለአሁን አመልካች የተሰጠውን የወራሽነት ውሳኔ እንዳይፈጸም በማገድ የአሁን አመልካች ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ልጅነታቸውን አረጋግጠው ባቀረቡ ጊዜ መዝገቡን

www.abyssinialaw.com

የማንቀሳቀስ መብታቸው ተጠብቋል በማለት የሰጠው ትእዛዝ ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር አቤቱታ የተመለከተው የአ/አ/ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ይህን ሳያርም ማለፉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአ/አ/ከተማ የመጀ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 893/07 በቀን 19/09/07 ዓ.ም በዋለው ችሎት፣ የአ/አ/ከ/አስ/ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 23748 ሰኔ 16 ቀን 2007ዓ.ም እና ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰ/መ/ቁ. 23837 በቀን 26/10/2007ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች የአመልካችን ተወላጅነት መካድ የሚችሉት የመካድ ክስ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት በማቅረብ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ግራቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 120844

መስከረም 27 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ሃንደግባ ሽኩር - ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አለምቱ ኢብራሂም - ወኪል ለይላ ሃንዳግባ - ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመ/ቁ. 66280 ህዳር 20 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ በተመሳሳይ ጥያቄ በሰ/መ/ቁ.120843 አመልካች የሆኑት ወ/ሮ መኪያ ሐጂ ማመጫ ያለው ክርክር ጭብጥ ተመሳሳይና አንድ አይነት በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.11/1/ መሰረት እንዲጣመሩ ተደርገዋል፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ በትዳር የቆዩ ሲሆን ለዚህ ክርክር መነሻው ጋብቻው በፍቺ በመፍረሱ የተጀመረው የጋራ ንብረት ክፍፍል ጉዳይ ነው፡፡ በአመልካች እና ተጠሪ የነበረው ጋብቻ በመፍረሱ የአሁኗ ተጠሪ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በማቀርቧ ወ/ሮ ሚኪያ ሐጂ ሁለተኛ ሚስት ጣልቃ መግባቷን በስር መዝገብ ተመልክቷል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ ተጠሪ በክስዋ ከተራ ቁጥር 1ኛ-4ኛ ድረስ አዋሳኝ ተጠቅሶ በአራት ቦታዎች የሚገኙ መሬቶች በአጠቃላይ 0.85 ሄ/ር ይካፈሉ፡፡ ጣልቃ ገብ/2ኛ ሚስት/ለአሁን አመልካች በሚደርሰው የመሬት እርሻ መጠን ላይ ግማሽ መብት አላት፡፡ እልፍኝ እና የሳር ክዳን ቤት የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ንብረት በመሆኑ ቢቻል በአይነት አሊያም በገንዘብ ተገምቶ እኩል ይካፈሉ፡፡ በጓሮው የሚገኘውን ጫትና ቡና ሌሎች አትክልቶች ከብቶች እና እንስሳቶችን አመልካች እና ተጠሪ እኩል ይካፈሉ እንዲሁም በ2004 ዓ.ም ለመንገድ ስራ ምክንያት የተከፈለ ብር 20,000 /ሃያ ሺ ብር/ የንብረት ካሳን በተመለከተ 1ኛ አመልካች እና ተጠሪ እኩል እኩል ከተካፈሉ በኋላ

www.abyssinialaw.com

ጣልቃ ገብ ከአመልካች ድርሻ ላይ ግማሽ ወይም ከአጠቃላዩ የካሳ ብር ላይ 1/4ኛ ሊደርሳት ይገባል በማለት ውሳኔ ስጥተዋል፡፡

ይህን ውሳኔ በመቃወም የአሁኗ አመልካችና ጣልቃ ገብ የየራሳቸውን ለስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ሁለቱንም ይግባኝ መዝገቦች አጣምሮ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ አድረጎ ከመረመረ በኋላ በስር ፍርድ ቤት በተገቢው ዳኝነት ሳይከፈልበት የቀረቡትን ቅሬታዎች ዳኝነት ከፍለው የመጠየቅ መብታቸው ከጠበቀ በኋላ በተቀሩት ላይ በመንገድ ስራ ምክንያት ንብረት ካሳ የተከፈለ ሙሉ በሙሉ ለጋራ ጥቅም አለመዋሉን በበቂ ሁኔታ በተጠሪ ማረጋገጥ ሳይቻል የተሰጠ ውሳኔ ነው በማለት ሽሮታል፡፡ በ2006 ዓ.ም የተገኘ መሬት ላይ ተጠሪ 2.5 ኩንታል ስንዴ ይድረሳት ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የተወሰነውን አጽንቶታል፡፡ እንዲሁም እልፍኝ ቤት የስር ፍርድ ቤት ለሶስት እኩል ይካፈሉ የተባለው ውሳኔ የሚነቀፍበት ነጥብ የሌለው ሆኖ ለአፈፃፀም እንዲመች የእልፍኝ ቤቱን 1/3ኛ ግምት ለተጠሪ እንዲከፈል በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ሁለቱ ሚስቶች በየጓሯቸው ያለውን አንድ ጥማድ እንሰት፤ጫት እንዲሁም አቡካዶ ያላቸው መሆኑን በወረዳ ፍ/ቤት በሰው ምስክር ያረጋገጡ ቢሆንም እንዲሁም ጣልቃ ገብ ከ21 አመታት በላይ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ስትፈጽም ተጠሪ ሳትቃወም እና በጋራ ስትኖር መቆየቷ እየታወቀ በጋራ የሚጠቀሙበትን አጠቃላይ መሬት 1/4ኛ ብቻ ይገባታል በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ የወረዳው ውሳኔ ተሽሯል ካለ በኋላ እያንዳንዳቸው ሚስቶች በይዞታቸው በስተጀርባ ያለውን እንሰትና አትክልት ከአመልካች ጋር እኩል ይካፈሉ፤ ቀሪውን ሁለት መሬት እና መሬቱ ላይ የሚገኙ ዛፎች ደግሞ ሶስቱም እያንዳንዳቸው 1/3ኛ መጠን ይካፈሉ፡፡ በሬና ፈረስ እንዲሁም እልፍኝ የሳር ቤቱን በተመለከተ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔውን በማጽናት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ አፈፃፀሙ ግን እያንዳንዳቸው 1/3ኛ ይካፈሉ ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለደ/ብ/ብ/ህ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ብታቀርብም የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ላይ ጉድለት የሌለው መሆኑን ገልፆ የተጠሪን ይግባኝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

በተጠሪ አመልካችነት ቀጥሎ በሰበር የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ አስቀርቦ ከሰማቸው በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ቤት ጓሮ ያለው የእርሻ ይዞታ ብቻ ከስር ተከሳሽ ጋር ይካፈሉ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተጠሪ በሌሎች ይዞታዎች ላይ ያላትን መብት ያላገናዘበ በመሆኑ በመሻር የምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በአራቱ የተለያዩ አዋሳኛቸው የተጠቀሱት ስፋታቸው 0.85 ሄ/ር ከሳሽና ተከሳሽ እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ እልፍኝ የሳር ክዳን ቤት የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ለሶስት

www.abyssinialaw.com

ይካፈሉ ለአፈፃፀም ያመች ዘንድ ተጠሪ ግምት ትውሰድ በማለት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪና የስር አመልካች እኩል እንዲካፈሉ የሚለውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

አሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች ታህሳስ 6 ቀን 2008 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት በመግለፅ ስህተቱ እንዲታረምላቸው ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪም ሳትቃወም ጣልቃ ገብ ከስር ተከሳሽ ጋር ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ ተሳስረው ንብረት ሁሉ በጋራ ማፍራታቸው እየታወቀ አሁን በተጠሪና ተከሳሽ መካከል የነበረው ጋብቻ ፈርሶ የጋራ ንብረት ሲደረግ አመልካች በጋብቻ ላይ ጋብቻ የፈፀመች ስለሆነ ድርሻዋን ከስር ተከሳሽ ግማሹን ታግኝ በማለት በክልሉ ሰበር ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ አመልካቾችና ተጠሪ ክርክራቸውን በፅሁፍ አቅርበዋል፡፡
የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን በዚህ መሰረትም አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ አመልካቾች በጣልቃ ገብና ተከሳሽ ስም የተመዘገበ በደማላ ደስይበር ቀበሌ ስፋቱ 0.486 ሄ/ር ይዞታ መኖሩ ተረጋግጦ ከግብርና ለፍርድ ቤት ተልኳል፡፡ ከተከሳሽ እናት ለወ/ሮ ሚኪያ ሓጂ ጎጆ መውጫ መቋቋሚያ ይሆን ዘንድ ከ21 አመት በፊት የሰጠችን ይዞታ ላይ ከወ/ሮ ሚኪያ ሓጂ ጋር የሰራነው ቤት እና በጓሮው በቆጮና በሌሎች ቋሚ ሰብሎች በማልማት የቆየንበት የአሁኗ ተጠሪም ይዞታዋና ልማቷን የማይነካ በመሆኑ ጋብቻችንን ሳትቃወም 21 አመት የቆየች ስትሆን የወ/ሮ መኪያ ሓጂ የራሷን ይዞታ እና መሬት በስሟ ግብር እየገበረች ቆይታ በ1997 ዓ.ም በስሟ ቁጥር 0316623 የሆነ የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርቲፍኬት የሁለታችን ፎቶ ያለበት አውጥታበተለች፡፡ ይህን ማስረጃ ስታወጣ ተጠሪ ተቃውሞ አልነበራትም እስከ ዛሬ ድረስ ተቃውሞ አቅርባ ደብተሩን አላሰረዘችም፡፡ በስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሕጉን ተከትሎ አጣርቶ የሰጠው ውሳኔ የክልሉ ሰበር ችሎት በቂና አሳማኝ ምክንያት ሳይሰጥ መሻሩ እንዲሁም ከወ/ሮ መኪያ ጋር ያለ ጋብቻ ሳይፈርስ ሁላችንም እንድንከፋፈል የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የቤተሰብ ህግ መርህ የጣሰ በመሆኑ የክልሉ ሰበር የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተሽሮ እንዲወሰልን የሚል ነው፡፡
በተጠሪ በኩል ደግሞ ከአመልካች ጋር በ1970 ዓ.ም ጋብቻ ከፈፅምን ጀምሮ መጠኑ 0.85 ሄ/ር በጋራ ማፍረታችን በማስረጃ ተረጋግጦ ከዚሁ ግማሽ ድርሻ እንድታገኝ የሰጠው ውሳኔ ስህተት የለውም፡፡ አመልካች ከወላጅ እናቱ ለማቋቋሚያ የተሰጠው አስመስሎ ያቀረበው በስር ወረዳ ፍ/ቤት ክርክር ያልተነሳና በጭብጥነት ያልተያዘ ከስነ-ስርዓት ህጉ ውጭ አዲስ የቀረበ ክርክር ስለሆነ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ፡፡ አመልካችና ተጠሪ እኩል ድርሻ እንድናገኝ የሰጠው ውሳኔ ጣልቃ ገብ አመልካች በደረሰው ድርሻ ላይ መብት እንዳላት በመግለፅ የቤተሰብ ህግ እና

www.abyssinialaw.com

የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር በመ/ቁ. 45548 የሰጠው አስገዳጅ ትርጉም መሰረት አድርጎ የተሰጠ ትክክለኛና ፍትሓዊ ነው፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ የተገኘበት መንገድ የህግን አግባብ ያልተከተለ መሆኑ በማረጋገጥ ሰነዱን ውድቅ በማድረግ የስር ተከሳሽና የተጠሪ ንብረት መሆኑን ማስረጃ የመስማትና የመመዘን ስልጣን በተሰጠው የስር ፍርድ ቤት ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ ነው፡፡ ጋብቻ ሲፈርስ የንብረት ክፍፍል ሲደረግ የሁለተኛ ሚስት ጋብቻ በፀናበት በንብረቶቹ ላይ ያለን ድርሻ መወሰኑ የቤተሰብ ህግ መርህ የሚጥስ አይደለም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአመልካችና ተጠሪ የተመሰረተው ጋብቻና አከራካሪው የእርሻ መሬት ይዞታዎች በምሪት የተሰጣቸው አመልካችና ጣልቃ ገብ ከመጋባታቸው በፊት መሆኑ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የተካደ አይደለም፡፡ አመልካች እና በስር ጣልቃ ገብ በመሬት ይዞታቸው ይገባናል የሚሉት በስጦታ የተሰጠን በሌላ በኩል ደግሞ በስማችን ተመዝግቧል፤መቃወሚያ በማቅረብ አልተሰረዘም የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህ መከራከሪያ ነጥቦች በስር ክርክር ሂደት ያልነበሩና ያልተረጋገጡ ናቸው፡፡ በክርክር አመራር ስርአት አንድ ተከራከሪ ወገን ማንሳት የሚገባው በመጀመሪያ በሚሰጠው የመከላከያ መልስ በግልፅ ማቅረብ እንዳለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.234 ስር ተመልክቷል፡፡ በስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃ የመመዘንና የማጣራት ስልጣን ባለቸው ቀርቦ ውሳኔ ያልተሰጠበት ነጥብ በዚህ ደረጃ ማንሳቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.329 እንዲሁም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ሀ/ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 አንፃር ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካች እና ተጠሪ የተሰጣቸው የእርሻ መሬት ይዞታ ከአመታት በኂላ ወ/ሮ መኪያ ሐጂ በሁለተኛ ሚስትነት ጋብቻ መመስረት የነበረው የመሬት ይዞታ ላይ ተጠሪ ስምምነት ባላደረገችበት በቀጥታ እኩል የምታገኝበት የህግ ድጋፍ የለውም፡፡ ተጠሪ አመልካች ሁለተኛ ሚስት ሲያገባ መቃወሚያ ባለማቅረብዋ በንብረቶችዋ ላይም ተስማምታለች ለማለት አይቻልም፡፡ ስለሆነም በክልሉ ሰበር ችሎት በእርሻ መሬት ይዞታዎችና እልፍኝ የሳር ክዳን ቤት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 66280 ህዳር 20 ቀን 2008 ዓ.ም በክስ ተራ ቁጥር 1-4 የተዘረዘሩት የመሬት ይዞታዎች 0.85 ሄክታር እና እልፍኝ የሳር ክዳን ቤት በተመለከተ የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.11537መስከረም 7 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሌሎች ጉዳዮች የተሰጠ ውሳኔ አልተነካም፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከመ/ቁ.120843 ጋር እንዲያያዝ ይደረግ፡፡
4. ከዚህ ፍርድ ቤት በቀን 19/04/2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት በምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ በመ/ቁ. 03867የተጀመረው አፈፃፀም ላይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰበር መ/ቁ 105125

ሕዳር 05 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ክፍለፅዮን ማሞ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- አቶ አህመድ ዑመር

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ተስፋዬ አብራሃ

2ኛ. አቶ ኃይለ ማሪያም አብራሃ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነውን ጭብጥ የመሬት ባለይዞታ ሳይቃወም የተሰራ ቤት የሚኖረው ሕጋዊ ውጤት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት፣ የፍትሐብሔር ሕግ አንቀፅ 1179/1/ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔዎች አንፃር አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በትግራይ ክልል ምስራቃዊ ዞን ዓዲግራት ወረዳ ፍርድ ቤቶች የአሰበሰበያ ምድብ ችሎት የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በፍ/መ/ቁ 020212 ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰው 490 ካሬ ሜትር የመሬት ይዞታ ያላቸው ሲሆን ተጠሪዎች በጉልበታቸው በሕጋዊነት ሳይሰጣቸው በኃይል በ1998 አንዳንድ ሰርቪስ ሁለት ክፍል ቤት እንደሰሩ፣ እንዲሁም በ2006 ዓ.ም በቀበሌ በታገደበት ሁኔታ ፊት ለፊት ባለው ይዞታ ላይ በክብ ድንጋይ ቆርቆሮ ተክለው በሕጋዊ መንገድ ከተሰጣቸው ይዞታ ላይ ከሕግ ውጭ ስለወሰዱባቸው ተጠሪዎች የሰሩቷ ቤት በራሳቸው ወጪ አፍርሰው ይዞታውን እንዲመልሱ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪዎች በሰጡት መልስም በ1998 ዓ.ም ቤቱን መስራታቸውን ሳይክዱ ከዛ በኋላ ግን ምንም እንዳልሰሩና የሰሩት ቤትም አስተዳደር በሰጣቸው ቦታ ስለመሆኑ ተከራክረዋል፡፡

የስር ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ አጠቃላይ ይዘት በመዝገቡ ካሰፈረ በኋላ የአሁኑ ተጠሪዎች የሰሩት ሰርቨስ ቤት በ1998 ዓ.ም መሆኑ እንዳልተካደ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40/6/ እና የፍትሐብሔር ሕግ አንቀፅ 1179/1/ መሰረት በማድረግ አመልካች ሳይቃወሙ የተሰሩት ሁለት ሰርቪስ ሆነ አጥር ግቢው ለመቃወም የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የላቸውም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች በስር የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር

www.abyssinialaw.com

አቤቱታ ያቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ የአመልካች ሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- አከራካሪው ይዞታ ለቆዳና ሌጦ ድርጅት እንደተሰጣቸው የተጠሪዎች ሕገ ወጥ ተግባር ይቃወሙ እንደነበር በመግለፅ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ እንዲሻር ማመልከታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አከራካሪው ይዞታ የአሁኑ የሰበር አመልካች መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ከመሆኑ አንፃር የሰበር አመልካች ተጠሪዎች ቤቱን ሲሰሩ ሳይቃወም ነው ቤቱ የተጠሪ ነው በሚል አግባብ ተጠሪዎች ቤት የሰሩበትን ይዞታ መልቀቅ የለባቸውም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1179/2/ እና /3/ እና ፍ/ብ/ሕ/ቁ 1180 ድንጋጌዎች አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪዎችን ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ተጠሪዎች የካቲት 06 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና አመልክቷል፡፡ ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በፅሁፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ተገቢ ከሆነው ድንጋጌ በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች በሚመለከተለው የአስተዳደር ክፍል 490 ካሬ ሜትር የተሰጣቸው ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች አከራካሪ በሆነው ይዞታ ላይ ቤት እንዲሰሩ በሚመለከተው አስተዳደር የተፈቀደላቸው መሆኑን በመግለፅ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ባያገኝም ለክርክሩ መነሻ የሆኑ ቤቶች በ1998 ዓ.ም ስለመስራታቸው ግን በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች በአከራካሪው ይዞታ ላይ ቤት ሲሰሩ አመልካች ያቀረቡት ተቃውሞ እንደነበረ ቢከራከሩም በስር ፍርድ ቤት በተደረገው የማጣራት ሂደት ግን መቃወሚያ ስለማቅረባቸው አልተረጋገጠም፡፡ አንድባለይዞታ ሳይቃወም የተሰራ ቤት ቤቱን የሰራው ሰው ባለመብት እንደሚሆን በፍ/ሕ/ቁ 1179/1/ ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡ አመልካች እየተከራከሩ ያሉት የይዞታ ባለቤት በማንኛውም ጊዜ ተጠሪዎችን የማስለቀቅ መብት አለው በሚል እሳቤ ነው፡፡ በእርግጥ የይዞታ ባለመብት በይዞታው የተሰራው ቤት እንዲነሳለት ወይም ከ ¼ ኛ የማይበልጥ ካሳ ከፍሎ ቤቱን የማስቀረት መብት እንዳለው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1179/2/ እና 1180 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ ይሁንና የፍትሐብሔር ሕግ በታወጀበት ዘመን መሬት በግል ባለሀብትነት የሚያዝ በመሆኑ በየትኛውም መልኩ በመሬቱ ላይ ከሁሉም የሰፋ መብት ያለው በመሆኑ በባለቤቱ መቃወሚያ ሳይቀርብ የተሰራ ቤት ጭምር እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት እንዳለው ተደንግጎ ነበር፡፡ ከላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች የሕዝብና የመንግስት መሆኑን ከደነገገው አንቀፅ 40/3/ ጋር በተጣጣመ መልኩ ነው፡፡ በዚሕም መሰረት የመሬት ባለይዞታ በፍትሐብሔር ሕግ አንቀፅ 1179/2/ እና 1180 በተደነገገው አግባብ በይዞታ ላይ ምንም ተቃውሞ ሳያቀርብ የተሰሩ ቤቶች ላይ የፈለገው እርምጃ የመውሰድ መብት የለውም፡፡ መሬት የሕዝብና የመንግስት ከመሆኑ አንፃር በባዶ መሬት ላይ የተሰራው ቤት ላይ የመሬት ይዞታ መብት አለኝ

www.abyssinialaw.com

የሚለው ወገን ቤቱን ከሰሩ ሰዎች የተሻለ መብት ሊኖረው አይችልም፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በ490 ካሬ ሜትር ላይ የይዞታ ባለመብት ሁኖ የነበረ ቢሆንም አመልካች ሳይቃወም ተጠሪዎች በባዶ መሬት ላይ ቤት ገንብተዋል፡፡ ተጠሪዎች በሕጉ አግባብ አልተሰጣቸውም ቢባል እንኳ የሚመለከተውን አስተዳደር ከሚጠይቅ በቀር በባዶ የመሬት ይዞታ ላይ ጉልበትና ገንዘባቸውን በማፍሰስ የሰሩበት ቤት ላይ ከአመልካች የተሻለ መብት እንዳላቸው ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40/7/ እንደተመለከተው ተጠሪዎች በአከራካሪው ይዞታ ላይ የገነቡት ቤት ባለይዞታ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

አመልካች በአከራካሪው ይዞታ አለኝ የሚሉትን መብት ለማስከበር ተገቢ ጥረት ባለማድረጋቸው ተጠሪዎች ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ቤት ሰርተው እየኖሩ እንደሚገኙ ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀፅ 1179/2/ እና 1180 የተመለከቱትን መሬት በግል መያዝ በተፈቀደበት ስርዓት በነበረው አካሄድ በማንኛውም ጊዜ ተጠሪዎችን ከሰሩት ቤት ማፈናቀል እንደሚችሉ በመግለፅ ያቀረቡት ክርክር የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40/2/ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 30101፣ 36638 እና በሌሎች መዝገቦች የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የአሁኑ ተጠሪዎች አመልካች ሳይቃወሙ የሰሩት ሁለት ሰርቪስ ቤት ሆነ አጥር ግቢው ባለይዞታ መሆናቸውን በማረጋገጥ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40/3/ እና /7/ እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 30101 እና 36638 የሰጣቸው ገዥ ውሳኔዎች መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር በጉዳዩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን አያሳይም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አመልካች ሳይቃወሙ የተሰሩ ቤቶች እንዲፈርሱ የመጠየቅ መብት የላቸውም ብለናል፡፡ ተጠሪዎች አመልካች ሳይቃወሙ የሰሯቸው ቤቶች ባለመብት ናቸው ብለናል፡፡

በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዓዲግራት ወረዳ ፍርድ ቤቶች የአሰበሰበያ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 02012 በቀን 8/07/2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 17820 በቀን 13/09/2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 66911 በ23/10/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በድምፅ ብልጫ ፀንቷል፡፡
2. ተጠሪዎች አመልካች ሳይቃወሙ የሰሩት ሁለት ሰርቪስ ቤት እና አጥር /ግቢው/ ባለመብት ናቸው በማለት ወስነናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

www.abyssinialaw.com

## የልዩነት ሐሳብ

እኛ ስማችን በ2ኛ እና 4ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰዉ ዳኞች አብላጫዉ ድምጽ ከሰጠዉ ዉሳኔ በመለየት የሚከተለዉን የልዩነት ሐሳባችንን እናስቀምጣለን፡፡

በዚህ ጉዳይ መታየት ያለበት አሁን በአገራችን ባለዉ ሥርዓት እና የሕግ ማዕቀፍ ግለሰቦች ወይም ዜጎች የመሬት ነክ ንብረት ጋር በተያያዘ ያላቸዉ መብት ነዉ፡፡ የኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት የመሬት ነክ ንብረት በግለሰብ ደረጃ በግል መያዝ እንደሚቻል በወቅቱ በሥራ ላይ የነበሩት የሕግ ማዕቀፍ የሚያመለክት ጉዳይ ነዉ፡፡ የኃይለ ስላሴ መንግስት ከወቀደ በኋላ የመሬት ነክ ንብረት በግለሰብ በግል የመያዝ ሁኔታ በደርግ መንግስት ቀሪ መደረጉ ይታወቃል፡፡ በአገራችን ከደርግ መንግስት ዉድቀት በኋላ እና የኢህአዴግ መንግስት ስልጣን ከያዘ ወዲህ የመሬት ነክ ንብረት ባለቤትነት የኢትዮጵያ መንግስትና ሕዝብ ሀብት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በዚህ መሰረት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት በ1987 ዓ.ም ከመዉጣቱ በፊት የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት የመንግስትና የሕዝብ ሀብት መሆኑን ባረጋገጠ መልክ የሕግ መዕቀፍ ወጥቶ ሲሰራበት እንደነበር ይታወቃል፡፡ በዛን ወቅት የከተማ መሬትን በተመለከተ የከተማ ቦታ በኪራይ ስለመያዝ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 80/1986 ዓ.ም መሰረት የሚመራ ነበር፡፡ በመቀጠል በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 /3/ መሰረት የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነዉ፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነዉ፡፡ በማለት ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት ባለቤትነት የመንግስትና የሕዝብ እስከሆነ ድረስ ግለሰቦች በመሬቱ ላይ ሊኖራቸዉ የሚችለዉ የባለይዞታነት መብት እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም፡፡

ይህን በሕገ መንግስቱ የተመለከተዉን መርህ ተከትሎ የመንግስትና የሕዝብ የመሬት ባለቤትነትን ባረጋገጠ መልኩ እና ግለሰቦች ደግሞ የመሬት ባለይዞታነት መብት የሚያገኙበት ሥርዓት እና ይህ መብት የሚከበርበት የሕግ ሥርዓት ተዘርግቶ እየተሰራበት ይገኛል፡፡ የከተማ መሬትን በተመለከት የከተማ ቦታን በሊዝ መያዝን እንደገና ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 272/1994 ዓ.ም በሚደነግገዉ አግባብ ሲመራ የነበረ ሲሆን፣ ይህ አዋጅ ከተሻረ በኋላ በአሁኑ ወቅት የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ዓ.ም እና ይህን አዋጅ ተከትሎ በወጣዉ ደንብ መሰረት እየተሰራበት መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ ግለሰቦች ወይም ዜጎች የመሬት ነክ ንብረትን በተመለከተ የባለይዞታነት መብት ለማግኘት የሚችሉት እነዚህ ሕገ መንግስቱን ተከትሎ በወጡት ዝርዝር ሕጎች መሰረት ስልጣን ባለዉ የመንግስት አካል መሆን አለበት፡፡ ከዚህ ዉጭ ግን የከተማ መሬት መያዝ እንደማይቻል እና ከዚህ ሕግ አግባብ ዉጭ ማንም ግለሰብ የከተማ መሬትን በመያዝ ሕጋዊ የባለይዞታነት መብት ሊያገኝ አይችልም፡፡ በዚህ ሕግ አግባብ አንድ ግለሰብ የከተማ መሬት ስልጣን ባለዉ የመንግስት አካል የተሰጠዉ እንደሆነ ይህ መብት ሊከበርለት ይገባል፤ ከሕግ ዉጭ የባለይዞታነት መብቱን በመንግስትም ሆነ በሌላ አካል ወይም

www.abyssinialaw.com

ግለሰብ ሊነጠቅ አይገባም፡፡ ይህ ማለት በዚህ አግባብ ባገኘዉ የከተማ መሬት ላይ የግል ንብረት የማፍራት መብት አለዉ፡፡ አንድ ሰዉ በሕጉ አግባብ ባገኘዉ የከተማ መሬት ላይ በጉልበቱ፣ በእዉቀቱ ወይም በገንዘቡ ንብረትን ያፈራ እንደሆነ የንብረቱ ባለሀብት እንደሆነ የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 /2/ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አንድ ግለሰብ የከተማ መሬት መያዝ የሚችለዉ በሕጉ አግባብ ሲሆን፣ በዚህ አግባብ ባገኘዉ የመሬት ይዞታ ላይ የግል ሀብት ማፍራት ይችላል፡፡ ከዚህ ዉጭ የከተማ መሬትን በሕገ ወጥ መንገድ በመያዝ በመሬቱ ላይ ንብረት ስላፈራ ብቻ የባለይዞታነት መብት ሊሰጠዉ የሚችል አይሆንም፡፡ ሕግ የዘረጋዉን ሥርዓት ተከትሎ የተገኘዉን የባለይዞታነት መብት በዚህ ይዞታ ላይ ከተፈራ ንብረት መብት አንጻር በአግባቡ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ የመሬት ባለይዞታነት መብት ትልቅ መብት በመሆኑ በሕገ ወጥ መንገድ ተይዞ ንብረት ስለተፈራ ብቻ ከባለይዞታነት መብት ይልቅ ለንብረት መብት የበለጠ ክብደት በመስጠት ያነሰ ዋጋ ሊሰጠዉ አይገባም፡፡ ይህ ደግሞ የመሬት ባለይዞታነት መብትን ተገቢ ክብደት የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ ሕገ ወጥ የሆነ የከተማ መሬት ወረራን ለመከላከልም የሚያግዝ ነዉ፡፡

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች ለክርክር ምክንያት የሆነዉን 490 ካ.ሜ የከተማ መሬት በሕጉ አግባብ ስልጣን ባለዉ የመንግስት አስተዳደር አካል የተሰጠዉ እና የባለይዞታነት መብት ያገኘ መሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ይህ በመሆኑ የአሁን አመልካች በዚህ መሰረት ያገኘዉን የባለይዞታነት መብት የሕግ አግባብ ተከትሎ ስልጣን ባለዉ አካል ከሚወስነዉ ዉሳኔ ዉጭ ይህን የባለይዞታነት መብቱን ሊያጣ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡ የአሁን አመልካች ይህን ይዞታ ለታለመለት ዓላማ ያላዋለ እንደሆነ የሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል በሕግ አግባብ በሚወስደዉ እርምጃ ይህን የባለይዞታነት መብቱን ከሚያጣ በስተቀር ማንም ግለሰብ ይህን ይዞታ ከሕግ ዉጭ ይዞበት ንብረት ስላፈራ አመልካች መብቱን የሚያጣበት አግባብ የለም፡፡ የአሁን ተጠሪዎች በዚህ ይዞታ ላይ ሁለት ሰርቪስ ቤቶችን መስራታቸዉ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ነገር ግን የአሁን ተጠሪዎች በዚህ ይዞታ ላይ ሰርቪስ ቤቶች ይስሩ እንጂ በይዞታዉ ላይ የባለይዞታነት መብት በሚመለከተዉ የመንግስት አስተዳደር አካል ማግኘታቸዉን በሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ነገር የለም፡፡ በመሆኑም የአሁን ተጠሪዎች ይህን የከተማ መሬት የባለይዞታነት መብት የሕጉን አግባብ ተከትለዉ ባላገኙበት ሁኔታ በዚህ ይዞታ ላይ ቤት በመሥራታቸዉ ብቻ የባለይዞታነት መብት የሚያጎናጽፋቸዉ ነገር የለም፡፡ ከላይ የተመለከቱትን የከተማ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ እና ደንብ ሲታይ በሕግ አግባብ ባልተገኙ ይዞታ ንብረት ማፍራት የባለይዞታነት መብት የሚያጎናጽፍ መሆኑን የሚያመለክተዉ ነገር የለም፡፡

ከዚህ አንጻር በ1952 ዓ.ም በኃይለ ስላሴ መንግስት የታወጀዉን የፍትሐብሔር ሕግ አሁን ያለዉ የመሬት ነክ ንብረት ተፈጻሚነት አለዉ ወይ? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህ

www.abyssinialaw.com

ሕግ የታወጀበት ወቅት መሬት እንደግል ሀብት የሚታይ እና በግል መያዝ እና እንደግል ሀብት እንደሚቆጠር የሚያመለክት ነዉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ሕግ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ሲታዩ መሬት በግል ሀብትነት የሚያዝ መሆኑን በሚያመለክት መልኩ ‹‹ባለመሬቱ›› በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ረገድ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1178፣ 1179 እና 1180 ማየት ይቻላል፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ሲታይ መሬት በግለሰብ እንደግል ሀብት መያዝ በሚችልበት ሥርዓት ዉስጥ እንደሆነ ግልጽ ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት እና ሕገ መንግስቱን ተከትሎ ከወጡት ዝርዝር ሕጎች አንጻር ሲታይ እነዚህ የፍትሓ ብሔር ድንጋጌዎች የከተማ መሬት ነክ ንብረትን በተመለከተ ተፈጻሚነት የላቸዉም፡፡ ሆኖም ግን በአሁኑ ወቅት የከተማ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ለመቆጣጠር የወጡት ሕጎች አንድ ሰዉ ሕጋዊ ባለይዞታ መብት ሳይኖረዉ ሕጋዊ ባለይዞታዉ ሳይቃወም በሌላ ሰዉ ይዞታ ላይ ቤት ወይም ንብረት ያሳረፈ ወይም ያፈራ እንደሆነ ይህ ጉዳይ በምን አግባብ ይታያል? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡

በዚህ ረገድ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስትን ተከትለዉ የከተማ መሬት ነክ ንብረትን ለማስተዳደር የወጡት ሕጎች የሚሉት ነገር ባለመኖሩ በግለሰቦች መካከል የተፈጠረዉን አለመግባባት ለመፍታት የፍትሓ ብሔር ሕግ እንደአግባብነቱ ተፈጻሚነት ሊኖረዉ ይገባል የሚባል ከሆነ የግራ ቀኙን መብት ፍትሓዊና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በሚያስጠብቅ ሁኔታ ተፈጻሚ መደረግ አለበት እንጂ የአንዱን ወገን ተጠቃሚነት ብቻ በሚያረጋግጥ መንገድ ተፈጻሚ መደረግ የለበትም፡፡ ይህ ማለት የባለይዞታዉን መብት ብቻ ወይም በይዞታዉ ላይ ንብረት ያፈራዉን ወገን መብት ብቻ ባስጠበቀ መልኩ ተፈጻሚ መሆን የለበትም፡፡ የሁለቱንም ወገኖች መብት ፍትሓዊና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ባስጠበቀ ሁኔታ ተፈጻሚ ማድረጉ ተገቢ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የአሁን አመልካች በይዞታዉ ላይ ተጠሪዎች የሰርቪስ ቤቶችን ሲሰሩ ባለመቃወሙ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1179 /1/ ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል የሚባል ከሆነ፣ የአንቀጹ ሌሎች ንዑስ አንቀጾችም ተፈጻሚነት ሊኖራቸዉ ይገባቸዋል፡፡ የድንጋጌዉ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደሚደነግገዉ ‹‹ባለመሬቱ ሳይቃወም በሌላ ሰዉ መሬት ሕንጻ የሠራ ሰዉ የዚሁ ሕንጻ ባለሀብት ነዉ›› የሚል ነዉ፡፡ አሁን ለተያዘዉ ጉዳይ ይህን ድንጋጌ ብቻ ተፈጻሚ አድርጎ መተዉ፣ የተጠሪዎችን የንብረት መብት ብቻ ባስጠበቀ መንገድ ተፈጻሚ መደረጉን እንጂ የአመልካችን የባለይዞታነት መብት ከግምት ያስገባ ሆኖ አይታይም፡፡ ይህን ድንጋጌ ፍትሓዊ በሆነ ሁኔታ ተፈጻሚ ማድረግ ካስፈለገ ለንብረት መብት ብቻ ሳይሆን ለባለይዞታ መብትም ተገቢዉ ክብደት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ ሊረጋገጥ የሚችለዉ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1179 ሥር የተመለከቱትን ንዑስ አንቀጾች በአጠቃላይ ተፈጻሚ በማድረግ ነዉ፡፡ ይህ ማለት የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1179 እና 1180 እንደሚደነግገዉ ባለይዞታዉ በሕጉ በተዘረጋዉ ሥርዓት ሕንጻዉን ለገነባዉ ሰዉ ተገቢዉን የካሳ ግምት በመክፈል ይዞታዉን የማስለቀቅ መብቱ ሊጠበቅለት ይገባል፡፡

www.abyssinialaw.com

አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች በዚህ ድንጋጌ በተዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት ለአመልካቾች ተገቢዉን የንብረት ካሳ ግምት በመክፈል ይዞታዉን የማስለቀቅ መብቱ ሊጠበቅለት ይገባዉ ነበር፡፡ ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶችም የአሁን አመልካች ለክርክር ምክንያት በሆነዉ ይዞታዉ ላይ ተጠሪዎች የሰሩት ቤቶች ግምት ምን ያህል እንደሆነ በባለሙያ አስገምተዉ አመልካች ተገቢዉን ካሳ ከፍሎ ይዞታዉን እንዲያስለቅቅ ማድረግ ሲገባቸዉ የተጠሪዎችን መብት ብቻ በሚያስጠብቅ መልክ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1179 /1/ ተርጉመዉ ተፈጻሚ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሯል፡፡ እንዲሁም የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን ድጋሚ በማየት በባለሙያ ቤቱን በማስገመት አመልካች ይህን ግምት ለተጠሪዎች እንዲከፍል በማድረግ ይዞታዉ ለአመልካች እንዲለቀቅ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 /1/ መሰረት ሊመለስለት ይገባ ነበር በማለት ወስነናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

# ውርስ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ/ 110040

የካቲት 3 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ እሴተማርያም አክሎግ

2. ወ/ሪት ወይንሸት አክሎግ

3. አቶ መክብብ አክሎግ

} የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ውርስ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካቾች ለአ.አ.ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የአያታቸው ወ/ሮ ደብረወርቅ ሀ/ሚካኤል ወራሽነት ይረጋገጥልን በማለት አቅርበዋል፡፡የአባታቸው ሻለቃ አክሎግ አድማሱ ወራሽነት ያረጋገጡ ሲሆን የወላጅ አባታቸውን እናት ወራሽነት ለማረጋጥ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡ወላጅ አባታቸው በ1981 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት የተለዩ ሲሆን አያታቸው ወ/ሮ ደብረወርቅ ሀብተ ሚካኤል የሞቱት ደግሞ በ1978 ዓ/ም ነው፡፡ በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤቱም አያታችህ ከአባታችሁ ቀድመው የሞቱ ስለሆነ ተተኪ ወራሽ ልትሆኑ አትችሉም በማለት ብይን ሰጥተዋል፡፡ በዚህ ብይን ባለመስማማት አቤቱታቸውን ለአ.አ.ከተማ ይግባኝ ሰሚና ለሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ሳያገኝ በትእዛዝ ሰርዞውታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች ተወካይ የካቲት 10 ቀን 2007 ዓ/ም በፃፉት የሰበር

www.abyssinialaw.com

አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ብይን ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ወላጅ አባታችን እናቱ ከሞቱ ጀምሮ እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ በህመም ላይ እንደነበር ለስር ፍርድ ቤቶች አስረድተን እያለን የአያታች ወራሽነት አታረጋግጡም መባሉ ከፍተኛ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ወላጅ አባታችን ለ3 አመት የአልጋ ቁራኛ ሆኖ የእናቱን ወራሽነት ሳያረጋግጥ ቢቀርም አመልካቾች ተተኪ ወራሾች የአያታችንን ወራሽነት የሚከለክለን አንዳችም ህግ የሌለ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ብይንና ትእዛዝ በመሻር የአያታቸውን ወራሽነት እንዲረጋገጥላቸው አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተተኪ ወራሾች ሊሆኑ አይችሉም በማለት የተሰጠ ብይን ከፍ/ብ/ህ/ቁ/ 830፣831/3/844 እና 839 አንፃር ለመመርመር በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ሊቀርብ የቻለው የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ብይን እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካቾች ጥያቄ ወላጅ አባታቸውን ተክተው የአያታቸው ወራሽነት እንዲረጋጥላቸው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ደግሞ ተተኪ ወራሾች ልትሆኑ አትችሉም በማለት ብይን ሰጥተዋል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 842/3/ ስር እንደተመለከተው የሟች ልጆች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ሲሆኑ ልጆች ቀድመው ከሞቱና ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ ትተው ከሆነ ተወላጆቹ ወላጃቸውን ተክተው ሟችን እንደሚወርሱ ያመላክታል፡፡ የተተኪ ወራሽነት የተፈፃሚነት ወሰን ወደ ታች የሚቆጥሩ ተወላጆች እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ወላጅ አባታቸው የእናታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ናቸው፡፡ አመልካቾችም የወላጅ አባታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች እንደሆኑ የህጉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተተኪ ወራሽ ለመሆን ከፍ/ብ/ህ/ቁ/ 842/3/ አንፃር ሲታይ የአመልካቾች ጥያቄ የሚያሟላ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ወላጅ አባታቸው የእናታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ በመሆን የወረሱ ስለሆነ የምትክ ጉዳይ ሊነሳ አይችልም፡፡ በሌላ አነጋገር አመልካቾች አባታቸውን ተክተው አያታቸውን መውረስ የሚችሉት አባታቸው ከአያታቸው በፊት የሞቱ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይንና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች የሟች አባታቸውን ወራሽነት ስለማረጋገጣቸው ከክርክሩ ስለተረዳን አባታቸው የወረሱትን ንብረት ለመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡ በዚሁ መሰረትም የሚከተለው ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪየ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 1118/07 ጥር 6 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ብይን፤ የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ/23073 ጥር 21 ቀን 2007 ዓ/ም እና የአ/አ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 23140 የካቲት 2 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጡት ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሀ/ቁ/ 348/1/መሰረት በአብላጫ ድምጽ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የልዩነት ሀሳብ

የአመልካቾቹ መሰረታዊ የአቤቱታ ነጥብ ወላጅ አባታችን ሻለቃ አክሎግ አድማሱ ከወላጅ እናታቸው ከወ/ሮ ደብረወርቅ ሀብተ ሚካኤል በኃላ የሞቱ በመሆኑ አባታችን የነበራቸው እናታቸውን የመውረስ መብት ለእኛ ለሻለቃ አክሎግ አድማሱ ልጆች እና ወራሾች የሚተላለፍ መሆኑ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠን የሚል መሆኑን ከስር ጀምሮ ከሚያቀርቡት ክርክር መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሰረቱ ለአንድ ውርስ ወራሽ የሆነ አንድ ሰው ውርሱ ከተከፈተ በኃላ የሞተ እንደሆነ የወራሽነቱ መብቶች ለርሱ ወራሾች የሚተላለፉ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 833 ተመልክቷል፡፡ ከአውራሹ አስቀድሞ የሞተን ወራሽ ተክቶ መውረስ (ቁጥር 844 (2) እና ከአውራሹ በኃላ የሞተን ወራሽ ተክቶ መውረስ (ቁጥር 833) የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆም ለአቤቱታው አግባብነት ያለው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌ ቁጥር 844 (2) ሳይሆን 833 ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በቁጥር 833 ድንጋጌ መሰረት ከአውራሹ በኃላ የሞተ ወራሽ ተተኪ ወራሾች መሆናቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው አመልካቾቹ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ ተሽሮ በአመልካቾቹ አቤቱታ መሰረት ሊወሰን ይገባው ነበር በማለት ስሜ በተራ ቁጥር ሁለት የተመለከተው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን አስፍሬአለሁ፡፡

መ/ተ

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 113529

የካቲት 28 ቀን 2008 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-**ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

**አመልካቾች:**

1. ወ/ሮ እቴቱ ከንባው
2. አቶ ኃይሉ ከንባው } ከጠበቃ ወንደሰን ሽዋረጋ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ቀለሚ ዓለማየሁ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ይገባኛል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁኖቹ አመልካቾች የአባታቸው እናት ማለትም የሴት አያታቸው የሚች ወ/ሮ ላቀች ቸርነት ታፋይ ውርስ እንዲጣራላቸው በአሁኗ ተጠሪ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ተጠሪዋን መልስ ከተቀበለ በኃላ ውርሱ ተጣርቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠቱ በ19/07/2006 ዓ.ም. የተዘጋጀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ የሪፖርቱ ይዘትም የአመልካቾቹ አባት አቶ ከንባው ወርቅነህ ሟች እናታቸው (የአመልካቾች አያት) ወ/ሮ ላቀች ቸርነት በሞቱበት ጊዜ በሕይወት የነበሩ ሆኖ ነገር ግን የእናታቸው ወራሽ መሆናቸውን ሳያረጋግጡ ቆይተው የሞቱ በመሆኑ አመልካቾቹ በአባታቸው እግር ተተክተው አያታቸውን ሊወርሱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ ባለመኖሩ ውርሱን ከእናታቸው ወ/ሮ ላቀች ቸርነት በኃላ ነገር ግን የእናታቸው ወራሽ መሆናቸውን አረጋግጠው በሞቱት ሟች የሽዋመብራት ወርቅነህ እግር ተተክተው የእኒሁ የሽዋመብራት ወርቅነህ ልጅ እና ወራሽ የሆኑት ተጠሪ፣እንዲሁም የወ/ሮ ላቀች ቸርነት ሌላ ወራሽ ካለ እንዲቀርብ አጣሪው ባወጣው ማስታወቂያ

www.abyssinialaw.com

ተጠርተው የቀረቡት ወ/ሮ የማርያምወርቅ ወርቅነህ በጋራ ይወርሳሉ የሚል ነው፡፡በሪፖርቱ ላይ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡ የተደረገ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የአሁኖቹን አመልካቾች አስተያየት ውድቅ አድርጎ የአጣሪውን ሪፖርት በማጽደቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾቹ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ የተደረገ ቢሆንም ተጠሪዋ በምስክሮች ፊት መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸው በመሀላ ቃል በመረጋገጡ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፎ ጉዳዩ ለምርመራ እንዲቀጠር የተደረገ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የአመልካቾቹ ወላጅ አባት አቶ ከንባው ወርቅነህ ከሚች እናታቸው ወ/ሮ ላቀች ቸርነት የሚያገኙት ውርስ ለአመልካቾቹ ሊተላለፍ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የአመልካቾቹ አባት እናት (የአመልካቾቹ አያት) የሆኑት ወ/ሮ ላቀች ቸርነት ታፋይ በሞት የተለዩት በ14/02/1979 ዓ.ም. መሆኑን፣የአመልካቾቹ አባት አቶ ከንባው ወርቅነህ የሞቱበትን ጊዜ የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክት ባይሆንም የሞቱት ከእናታቸው ሞት በኃላ ረዥም ጊዜ ቆይተው መሆኑን፣የተጠሪዋ እናትም የሞቱት በተመሳሳይ ሁኔታ ከእናታቸው ከወ/ሮ ላቀች ቸርነት ሞት ከ24 ዓመታት በኃላ በ2003 ዓ.ም. መሆኑን፣ የአመልካቾቹ አባት የሞቱት የእናታቸው ላቀች ቸርነት ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይወስዱ መሆኑን፣በአንጻሩ የተጠሪዋ እናት የሞቱት የእናታቸው ወ/ሮ ላቀች ቸርነት ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በ1997 ዓ.ም. ከወሰዱ በኃላ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡እናታቸው በሞቱበት ጊዜ የአመልካቾቹ አባት በሕይወት የነበሩ እና ለወራሽነት አይገቡም ያልተባሉ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 830 ድንጋጌ መሰረት እናታቸውን የመውረስ መብት አላቸው፡፡አንድ ሰው የሞተ እንደሆነ በሞተበት ጊዜ ዋናው መኖሪያው ስፍራ በሆነበት ቦታ የሚቹ ውርስ የሚከፈት ስለመሆኑ እና በሚቹ ሞት ምክንያት የሚቋረጡ ካልሆኑ በቀር በውርሱ ውስጥ የሚገኙት የሚቹ መብቶች እና ግዴታዎች ለወራሾቹ እና የኑዛዜ ባለስጦታዎች የሚተላለፉ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 826 የተመለከተ ሲሆን ለአንድ ውርስ ወራሽ የሆነ አንድ ሰው ውርሱ ከተከፈተ በኃላ የሞተ እንደሆነ የወራሽነቱ መብቶች ለእርሱ ወራሾች የሚተላለፍ ስለመሆኑም በቁጥር 833 ተደንግጎ ይገኛል፡፡በመሆኑም ከላይ በተጠቀሰው ቁጥር 833 ድንጋጌ መሰረት የወ/ሮ የሽዋመብራት ወርቅነህ ድርሻ ወራሻቸው ለሆኑት የአሁኗ ተጠሪ እንደተላለፈው ሁሉ የአመልካቾቹ አባት አቶ ከንባው ወርቅነህ ከእናታቸው ከሚች ላቀች ቸርነት የሚያገኙት

www.abyssinialaw.com

የውርስ ድርሻ ለሚች ከንባው ወርቅነህ ወራሾች የሚተላለፍ ከሚሆን በቀር አቶ ከንባው ወርቅነህ በሕይወት እያሉ የእናታቸው ላቀች ቸርነት ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ባለመውሰዳቸው ብቻ የአቶ ከንባው ወርቅነህ የውርስ ድርሻ ለሌሎች የሚች ላቀች ቸርነት ወራሾች እንዲተላለፍ ሊደረግ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም የአመልካቾቹ አባት ከእናታቸው የሚያገኙት የውርስ ድርሻ ወደ አሁኖቹ አመልካቾች ሊተላለፍ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ከላይ የተጠቀሱትን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ከላይ የሰፈረው ትችት እንደተጠበቀ ሆኖ በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ተጠሪዋ በአመልካቾቹ ላይ የይርጋ መቃወሚያ አላነሱም፡፡ከመዝገቡ መገንዘብ እንደሚቻለው ወ/ሮ ላቀች ቸርነት ከሞቱበት ጊዜ ጀምሮ የአመልካቾቹ አባት በዚሁ የውርስ ቤት ውስጥ ሲኖሩ የነበረ በመሆኑ እና አመልካቾቹም እየኖሩ የሚገኙት በዚሁ ቤት በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያ ሊነሳ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ውርሱ እንዲጣራላቸው አመልካቾቹ ላቀረቡት አቤቱታ ተጠሪዋ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾቹ ከቤቱ የውርስ ድርሻ እንዳላቸው በማመን ውርሱ ቢጣራ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ መልስ የሰጡ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡ በመሰረቱ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካሪዎቹ ወገኖች በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልጽ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ መስጠት የማይችል ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 182 (2) በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም የአመልካቾቹ አባት ከእናታቸው የሚያገኙት የውርስ ድርሻ ወደ አሁኖቹ አመልካቾች ሊተላለፍ አይገባም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የተሰጠው ከተጠሪዋም ሆነ ከሌላኛዋ ወራሽ ምንም ዓይነት ተቃውሞ ባልቀረበበት እና ይልቁንም የአመልካቾቹ የመውረስ መብት በግልጽ በታመነበት ሁኔታ ጭምር በመሆኑ አመልካቾቹን ከውርሱ በማግለል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት መሰረት አድርጎ የተሰጠ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

# ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43731 በ03/01/2007 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 162716 በ30/06/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የውርስ አጣሪው በ19/07/2006 ዓ.ም. ባቀረበው ሪፖርት ላይ ተገቢው ማስተካከያ ተደርጎ የሟች ወ/ሮ ላቀች ቸርነት ውርስ ከሆነው በጉለሌ ክፍለ ከተማ በወረዳ 5 ከሚገኘው ቁጥሩ 147 ከሆነው ቤት ውስጥ የአሁኗ ተጠሪ ወ/ሮ ቀለሟ ዓለማየሁ አንድ ሶስተኛ፣ወ/ሮ የማርያምወርቅ ወርቅነህ አንድ ሶስተኛ፣የአሁኖቹ ሁለቱ አመልካቾች ደግሞ በጋራ አንድ ሶስተኛ ድርሻ አላቸው በማለት ወስነናል፡፡
3. እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. በዚህ መዝገብ በ24/02/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 108328

መጋቢት 13 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጫልቱ ዋቀዬ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ፊቃዱ ዋቀዬ - ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው በኦሮሚያ ክልል የወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ በቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘት ባጭሩ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ የሟች አባታቸው አቶ ዋቀዬ ነገአ እና ወላጅ እናታቸው ወ/ሮ እሼቱ አባላቱ እንደነበረ፤ ወላጅ እናታቸው በ2001 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኃላ የቤተሰብ አባላት የውርስ ንብረት የማጣራት ሥራውን በስምምነት ማከናወን ባለመቻላቸው በፍ/ቤት በኩል በመ/ቁ.20782 ጠይቀው ወራሾች እንዲቀርቡ በሚኖርበት አካባቢ በማስታወቂያ ጥሪ ቢደረግም የቀረበ ሰው እንዳልነበረ፤ የውርስ አጣሪዎች የውርስ ንብረቱን ለይተው የየድርሻቸውን እንዳስረከቡዋቸው፤ በዚሁም አመልካች የድርሻቸውን 2262 ካሬ ሜትር ይዞታ ሳይረሱት አክርመውት የአሁኑ ተጠሪ ያለ አመልካች ፈቃድ በ2004/2005 ዓ.ም መሬቱን በማረስ ገብስ የዘራ በመሆኑ መሬቱን ለቆ የሰብል ግምት የ4 ኩንታል ብር 4,000 እንዲከፍል እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በፍሬ ጉዳዩም መልስ አቅርበዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ መሬቱን ለ5 ዓመታት የተጠቀሙበት መሆኑን በመግለጽ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1000/1/ መሠረት የይርጋ መቃወሚያ እንዲሁም ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው የሚል ክርክር ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩም

www.abyssinialaw.com

አመልካች ያቀረቡት የውርስ ንብረትና ወራሾችን በግልጽ ያላስቀመጠ እንደሆነ ይዞታው ከተጠሪ እጅ በመውጣት በአመልካች ይዞታ ሥር አለመግባባቱን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ አመልክቷል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የይርጋ እና ጉዳዩን ውሳኔ ያገኘነው የሚል ክርክር ሳይቀበል በፍሬ ጉዳዩ ለክርክር ምክንያት የሆነውን የመሬት ይዞታ በተጠሪ እጅ ያለ ስለመሆኑ አልተካደም፤ የተጠሪ ምስክሮች ይህ የውርስ ንብረት አለመክፈሉን አላየሁም ይበሉ እንጅ በአመልካች የቀረቡ ምስክሮች በሚያሳምን መልኩ አሁን ክርክር ያስነሳው ይዞታ የአቶ ዋቀዬ ነገአ ወራሾች ሃብት ሲከፋፈል ለአመልካች ድርሻቸው የተሰጣቸው ስለመሆኑ ያረጋገጡ በመሆኑ ተጠሪ አመልካች በውርስ ያገኙትን 2666 ካሬ ሜትር በእጃቸው የሚገኘውን እንዲለቁ አመልካች በ2004 ዓ.ም ያጡት የ2004 ዓ.ም ምርት 4,000 እንዲከፍሉ ወስነዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፍንፍኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ በውርስ አጣሪዎች ቀረበ የተባለው ሪፖርት የውርስ ንብረት እና ወራሾች በአግባቡ የለየ አለመሆኑን የእያንዳንዱ ወራሽ ድርሻ ተለይቶ ባልተወሰነበት፤ ፍርድ ቤትም የቀረበለትን ሪፖርት አጣሪው በሥልጣኑ መሠረት አጣርቶ ያቀረበው ስለመሆኑ በማረጋገጥ ያፀደቀው የአሁኑ ተጠሪ ይዞታ እንዲለቅ እና የሰብል ግምት እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ አለመሆኑን፤ አመልካች አቤቱታቸው የይርጋ ጊዜ ሳያልፈው ያቀረቡት በመሆኑ የእናታቸውን የውርስ ድርሻ የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ ነው ሲል የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርመሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ አንኳር ነጥቦች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የመሬት ይዞታ በእጃቸው ገብቶ የነበረ ስለመሆኑ የወራሾች ድርሻ የተከፋፈለ ነው፣ ለአመልካች ከሚደርሳቸው በላይ እንዳልተሰጣቸው በመግለጽ የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሻር የሚጠይቅ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው የማጣራት ሥራው ወራሾች ባልተሳተፉበት ሁኔታ እንደተከናወነ፤ አጣሪዎች በሕግ ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ በይዞታው እየተጠቀሙ ያሉት ተጠሪ ስለመሆናቸው በመግለጽ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና አመልክተዋል፡፡ የመልስ መልስም አቅርበናል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የውርስ አጣሪዎች ሪፖርት ነው ተብሎ በሥር ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20782 ቀርቦ የተመዘገበው ቃለ-ጉባኤ የግራ ቀኙን ተከራካሪዎች በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህ ችሎት ዕልባት የሚያሻው ዓብይ ነጥብ የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው የውርስ ንብረት በአግባቡ ተጣርቶ የተወሰነ አይደለም በማለት የሥር ወረዳ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔንና ትዕዛዝ መሻሩ በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ሆኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች ባቀረቡት ክስ በውርስ አጣሪዎች ድርሻቸው ተለይቶ ከታወቀ በኃላ የአሁኑ ተጠሪ ከሕግ ውጪ በመያዝ እየተጠቀመበት መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ ይዞታውን እንዲለቁ እንዲሁም የሰብል ግምት አራት ሺህ ብር እንዲከፈላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን ነው፡፡ ተጠሪ ጉዳዩ በይርጋ እንደሚታገድ፤ ከአሁን በፊትም በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ስለመሆኑ እንዲሁም የወራሾች ድርሻ በሕጉ አግባብ አለመወሰኑን መከራከራቸውን ተመልክተናል፡፡ አመልካች የውርስ ሃብት ለወራሾች በአግባቡ ተከፋፍሏል ይበሉ እንጂ በሥር ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 20782 ተመዘገበ የተባለው የውርስ አጣሪዎች ሪፖርት ወራሾች እነማን አንደሆኑ፤ የአውራሾቻቸው የሚንቀሳቀስና የማይቀሳቀስ ንብረት ምን እንደሆነ፤ እያንዳንዱ ወራሽ የሚደርሰው የሃብት መጠን ምን ያህል እንደሆነ? በግልጽና በማያሻማ መልኩ ያስቀመጠ ስለመሆኑ ሰነዱ አያሳይም፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የውርሰ አጣሪዎች የተባሉ ሽማግሌዎችም ወራሾች በማጣራት ሂደት እንዲሳተፉ በማስታወቂያ ጥሪ አድርገን ነበር ያሉ ቢሆንም በእርግጥ ከአመልካች ውጭ ያሉ ወራሾች በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጐላቸው ውርስ እንደሚጣራ አውቀው በዳታኝነት የቀሩ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡

በመሰረቱ ውርስ የሚጣራው በወራሾች ሲሆን ስምምነት ከሌለ ወይም ሌላ ሕጋዊ ምክንያት ካለ አጣሪዎች በፍ/ቤት እንደሚሰየሙ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 946 እና 950 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡ የውርስ ሃብት ማጣራት በሕጉ አግባብ ከተከናወነም ወራሾች ድርሻቸውን የመጠየቅ መብት ያላቸው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1062 ተመልክቷል፡፡ የክፍፍል ሥርዓቱም በወራሾች ስምምነት ሊሆን እንደሚችል፤ በውርስ ክፍፍል ጊዜ ያልተወከለ ወራሽ ካለም በፍ/ቤት እንደሚፀድቅ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1079 እና 1080 ተደንግጓል፣ የውርስ ሀብት የክፍፍል መርህም በዓይነት እንደሚሆን፤ ንብረቱን በዓይነት ለማከፋፈል ባልተቻለበት ሁኔታ በማቻቻል ሕጋዊ መፍትሄ እንደሚያገኝ የፍ/ሕ/ቁ. 1086 እና 1087 ድንጋጌዎች ያስገነዝቡናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት ቀረበ ያለውን የውርስ አጣሪዎች ቃለ ጉባኤ ከማፅደቁ በፊት በእርግጥ የውርስ ሃብት የማጣራት ሕጋዊ ሂደት ተከትሎ ወራሾች እና የውርስ ሀብት በአግባብ የተካሄደ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት ነበረበት፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት የሚኞች የውርስ ሀብት ምን ምን እንደሆነ፤ ወራሾች እነማን እንደሆኑ እና ድርሻቸውን በሕጉ አግባብ በመለየት

www.abyssinialaw.com

ስለመወሰኑ መዝገቡ አያሳይም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የውርስ ሀብት በሕጉ አግባብ ተጣርቶ የተወሰነ አይደለም በማለት የወረዳውን ውሳኔ እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ውድቅ ማድረጉ በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡ ምክንያቱም የወረዳው ፍርድ ቤት ወራሾችና የውርስ ሀብት በአግባቡ በመለየት ውሳኔ አልሰጠም፡፡ በዚህ ረገድ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡

የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች የውርስ ሃብት ድርሻቸውን ከሰው የመጠየቅ መብታቸውን የጠበቀ ስለመሆኑ የውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ይሁንና አመልካች የውርስ ሃብት ድርሻቸውን ለመጠየቅ ክስ እንዳቀረቡ መዝገቡ ስለሚያሳይ አመልካች ሌላ ክስ ማቅረብ ሳይጠበቅባቸው አለኝ የሚሉትን ድርሻ በሕጉ አግባብ ክሳቸውን እንዳያሻሽሉ በማድረግ እና ተገቢ ዳኝነት በመክፈል በሥር መ/ቁ. 46789 ክርክራቸውን የመቀጠል መብታቸው ሊነፈግ አይገባም፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች አዲስ ክስ እንዲያቀርቡ በሚጋብዝ አግባብ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ዓላማ አንፃር ሲታይ ተገቢ አይደለም ብለናል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ወረዳ ፍ/ቤት ወራሾችና የውርስ ሀብት በመለየት ውሳኔ አልሰጠም በማለት የውርስ አጣሪ ሪፖርት ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ሆኖ አመልካች አዲስ ክስ እንዲያቀርቡ በመፍቀድ የሰጠው የውሳኔ ክፍል ግን ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኤሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 185583 በ26/01/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የወልመራ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 46789 በ14/06/2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤ የአዲስ አበባ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 72261 በ6/09/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በመሻር የሰጠው ፍርድ ተሻሽሏል፡፡
2. የውርስ አጣሪዎች ሪፖርት ወራሾች እና የውርሰ ሀብት በአግባቡ ለይቶ ያላስቀመጠ ነው ተብሎ ውድቅ መደረጉ በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ሌላ ክስ ማቅረብ ሳይጠበቅባቸው ድርሻ አለኝ ካሉ በሕጉ አግባብ ክሳቸውን አሻሽለውና ተገቢ ዳኝነት ከፍለው ክርክሩን የመቀጠል መብታቸው የተጠበቀ ነው ብለን ወስነናል፡፡ የወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤትም የመ/ቁ. 46789 በመክፈት የውርስ ሀብት ክርክር ከቀረበ በሕጉ አግባብ ለማጣራት ተገቢ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

www.abyssinialaw.com

4. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማየነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 118105

መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ.ም

**ዳኞች** ፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳዉሎስ አርሺሶ

**አመልካች፡-** አቶ ተስፋዬ በቀለ .......ቀርበዋል

**ተጠሪዎ** ፡- 1. ወ/ሮ እሸቷ ጎሽዬ........ቀርበዋል

2. አቶ ሀብታሙ በቀለ.......ቀርበዋል

3. ወ/ሮ መብራት በቀለ......ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ኑዛዜን መነሻ ያደረገ የዉርስ ክርክርን የሚመለከት ነዉ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡- በሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች /የሥር ተጠሪ/፣ የአሁን ተጠሪዎች /የሥር አመልካቾች/ ሁኖው ሲከራከሩ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የሥር አመልካቾች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ሟች ሻምበል በቀለ ደምሴ ጥር 13 ቀን 1988 ዓ.ም የሞተ ሲሆን፣ ሟች በሕይወት በነበረ ጊዜ በ22/11/1982 ዓ.ም የተጻፈ ኑዛዜ ያደረገ ስለሆነ የዉርስ አጣሪ ተሹሞ እንዲያጣራልን በማለት አመልክተዋል፡፡ የሥር ተጠሪ ባቀረበዉ መልስ አመልካቾች የዉርስ ንብረቱን ሙሉ ለሙሉ ይዘዉ እያሉ ተጠሪን ተከሳሽ ማድረጋቸዉ አግባብነት የለዉም፣ እኔም ወራሽ ስለሆንኩኝ የዉርስ ንብረቱ ቢጣራ አልቃወምም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የዉርስ አጣሪ በማሾም የዉርስ አጣሪዉ የዉርስ ሀብቱን በማጣራት በ28/02/2006 ዓ.ም የተጻፈ ሪፖርት ያቀረበ ሲሆን ግራ ቀኙ በሪፖርቱ ላይ አስተያየት አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ሪፖርት እና አስተያየት በማየት በሰጠዉ ዉሳኔ ግራ ቀኙ ሟች ያደረገዉን ኑዛዜ በጋራ ፍ/ቤት አቅርበዉ የፀደቀ በመሆኑ የዉርስ ማጣራት ሥራዉ እና ክፍፍሉም መካሄድ ያለበት በዚህ አግባብ ነዉ፡፡ ይህ ኑዛዜ ገደብ ያለበት በመሆኑ 1ኛ

www.abyssinialaw.com

አመልካች ወ/ሮ እሸቷ ጎሽዬ በሕይወት እስካሉ ድረስ በዚህ ቤት የመጠቀም መብት ስላላቸዉ ወራሾች የመኖሪያ ቤት፣ የቤት ኪራይ እንዲሁም የቤት ዉስጥ ቁሳቁስ ለመጠየቅ መብት አይኖራቸዉም ፡፡ ነገር ግን ከ1ኛ አመልካች ህልፈተ ሕይወት በኋላ ከጠቅላላ ንብረት 50% የ2ኛ አመልካች አቶ ሀብታሙ በቀለ በመሆኑ፣ ቀሪዉ 50% የተጠሪ አቶ ተስፋዬ በቀለ እና 3ኛ አመልካች ወ/ሮ መብራት በቀለ ድርሻ እያንዳንዳቸዉ 25% ድርሻ ይኖራቸዋል፣ ስለዚህ በኑዛዜዉ መሰረት ሪፖርቱ በዚህ አግባብ ተሻሽሏል በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ተጠሪ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 መሰረት ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔን በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች መስከረም 6 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ ሁለት ገጽ አቤቱታ ሟች አባታችን በ22/11/1982 ዓ.ም ያደረገዉ ኑዛዜ በግል ሀብት ላይ ሳይሆን በአጠቃላይ በዉርስ ሀብት ላይ የተደረገ ኑዛዜ በመሆኑ ኑዛዜዉ ተሽሮ የዉርስ ሀብት ሳይናዘዝ እንደሞተ ሰዉ ተቆጥሮ የዉርስን ሀብት በሕግ አግባብ እንድንካፈል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ኑዛዜዉን ወደጎን በመተዉ የዉርስ ሀብት እንዲጣራላቸዉ በሥር ፍ/ቤት ባመለከቱት መሰረት ኑዛዜዉ የማይሰራ በመሆኑ የዉርስ ሀብቱን ድርሻዬን 25% እንዳገኝ እንዲወሰንልኝ፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች 1ኛ ተጠሪ በሕይወት እስካሉ ድረስ ምንም ዓይነት የዉርስ ድርሻ መጠየቅ አትችልም በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልኝ እንዲሁም ኑዛዜዉ ተሽሮ የዉርስ ሀብቱን ሳይናዘዝ እንደሞተ ሰዉ የዉርስ ሀብት ድርሻ በሕግ አግባብ እንዲካፈል እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በመመርመር ፣የዉርስ ይጣራ ጥያቄ የቀረበዉ በኑዛዜዉ ተጠቃሚዎች ከመሆኑ አንጻር የግራ ቀኙ የዉርስ ድርሻ ጭምር እንዲጣራ ያለመደረጉን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ በታዘዘዉ መሰረት የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ ሁለት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት፡-የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ እንዲጸናልን፣ አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ እንዲደረግልን፣ በዚህ ምክንያት የደረሰዉን ወጪና የጠበቃ አበል እንዲወሰንልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለአቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነዉ ሟች ሻምበል በቀለ ደምሴ

www.abyssinialaw.com

በሕይወት በነበሩ ጊዜ በ22/11/1982 ዓ.ም የተጻፈ ኑዛዜ ማድረጋቸዉ ግራ ቀኙ የሚካካዱት ጉዳይ አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንደሚያመለክተው የአሁን አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ የሟች አባታቸዉ ወራሽ፣ 1ኛ ተጠሪ ደግሞ የሟች ሚስት እንደሆኑ እና 3ኛ ተጠሪ የኑዛዜ ወራሽ እንደሆነች ተመልክቷል፡፡ ከግራ ቀኙ ክርክር እና ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ መገንዘብ እንደሚቻለዉ ሟች ይህን ኑዛዜ ያደረገዉ ጠቅላላዉን ንብረት በሚመለከት ሲሆን የአሁን 1ኛ ተጠሪ በሕይወት እስካሉ ድረስ ሀብቱን የመጠቀም መብት እንዳላቸዉ እና ማንም ተወላጅ የአባቴ ዉርስ ይገባኛል በማለት መጠየቅ እንደማይችል እና ከ1ኛ ተጠሪ ህልፈተ ሕይወት በኂላ ከጠቅላላ ሀብቱ 2ኛ ተጠሪ 50% እንዲካፈል፣ አመልካች እና 3ኛ ተጠሪ ቀሪዉን ሀብት 50% ለሁለት እንዲካፈሉ (እያንዳንዳቸዉ 25%) እንዲካፈሉ በማለት የተናዘዘ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ግራ ቀኙ ይህን ኑዛዜ በመቀበል እንዲጸድቅላቸዉ በጋራ ለፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበዉ በፍ/ቤት ዉሳኔ የጸደቀ መሆኑን ተማምነዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረበዉ ክርክር ሲታይ ሟች ያደረገዉ ኑዛዜ በፍ/ቤት ቀርቦ ሲጸድቅ ያልተቃወመ መሆኑን፣ የዉርስ ማጣራትም ሆነ ክፍፍሉ መሆን ያለበት በኑዛዜዉ አግባብ መሆን እንዳለበት ተከራክሯል፡፡ በሌላ በኩል የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት ክርክር የኑዛዜዉ ይዘት ላይ የተለያየ ክርክር ቢያቀርቡም የዉርስ ማጣራት ሂደትም ሆነ ክፍፍሉ በዚሁ አግባብ መሆን እንዳለበት ገልጸዉ ተከራክረዋል፡፡ እንዲሁም የሥር ፍ/ቤት የዉርስ አጣሪዉን ሪፖርት በማሻሻል ክፍፍሉ በኑዛዜዉ አግባብ መሆን እንዳለበት ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያቀረቡት ቅሬታ የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ኑዛዜዉ ገደብ ያለበት መሆኑን በመገንዘብ 1ኛ ተጠሪ በሕይወት እስካሉ ድረስ ተጠሪዎች የዉርስ ሀብት መጠየቅ እንደማይችሉ እና ከ1ኛ ተጠሪ ህልፈተ ሕይወት በኂላ ከጠቅላላ ሀብቱ 2ኛ ተጠሪ 50% እንዲካፈል፣ አመልካች እና 3ኛ ተጠሪ ቀሪዉን ሀብት 50% ለሁለት እንዲካፈሉ እያንዳንዳቸዉ 25% እንዲካፈሉ በማለት የወሰነ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ የአሁን ተጠሪዎች የሥር ፍ/ቤት የኑዛዜዉን ይዘት በማየት ተርጉሞ የሰጠዉን ዉሳኔ በተመለከተ ሟች ኑዛዜዉን የሰጠዉ በአጠቃላይ ሀብት ላይ ሳይሆን በንብረቱ ግማሽ የግል ሀብታቸዉ ላይ ነዉ ተብሎ እንዲወሰን ያቀረቡት ክርክር የሥነ ሥርዓት ሕጉን ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡ የአሁን አመልካች ሟች በሰጠዉ ኑዛዜ መሰረት ዉርስ ቢጣራ እና ክፍፍል ቢደረግ እንደማይቃወም እንዲሁም ኑዛዜዉ መጀመሪያ በፍ/ቤት ሲጸድቅ እንዳልተቃወመ በመግለጽ ሲከራከር እንደነበር የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ያሳያል፡፡ እነዚህ ሁሉ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መሆናቸዉ ግልጽ ነዉ፡፡ እነዚህ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮችን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ ተመርምሯል፡፡

www.abyssinialaw.com

የአሁን አመልካች በኑዛዜዉ አግባብ የዉርስ መጣራት ሂደቱም ሆነ ክፍፍል ቢደረግ እንደማይቃወም እየገለጸ፣ ይህ ኑዛዜ በፍ/ቤት እንዲጸድቅ ከተጠሪዎች ጋር ለፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበዉ ኑዛዜዉ በማጽደቅ ከጨረሰ በኂላ አሁን በኑዛዜዉ አግባብ የተሰጠዉን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ኑዛዜዉን እንዲሻርልኝ በማለት ያቀረበዉ ክርክር በሥር ፍ/ቤት ያልቀረበ አዲስ ክርክር በመሆኑ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበዉ ቅሬታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.329 /1/ መሰረት ተቀባይነት የለዉም ፡፡ ሌላዉ የአሁን አመልካች የሀብቱ 25% ድርሻ እንዲሰጠኝ በማለት ያቀረበዉ ክርክር ሲታይ የአሁን አመልካች ከጠቅላላ ሀብት 25% እንደሚገባዉ የሥር ፍ/ቤት በዉሳኔዉ ያረጋገጠ ሲሆን የአሁን አመልካች ኑዛዜዉ ገደብ ያለበት ነዉ በማለት እየተከራከረ እያለ አሁን ደግሞ ድርሻዬ አሁን እንዲሰጠኝ በማለት ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤት ሟች የሰጠዉን ኑዛዜ እና በግራ ቀኙ ተቀባይነት ያገኘዉን ኑዛዜ መሰረት በማድረግ ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን አመልካች በሥር ፍ/ቤት አሁን እንደቅሬታ ያቀረባቸዉን ነጥቦች ያላቀረበ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች በሕጉ አግባብ የተሰጡ ናቸዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ነዉ ለማለት ስለማይቻል የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.42390 በ17/06/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.167257 ሰኔ 19 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ለደረሰባቸዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 120841

መስከረም 23 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ክፍለጽዮን ማሞ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ካባ ተካ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ድሪባ ዳዲ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለዉ ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአሁን አመልካች አባቷን ተክታ ሟች አያቷን ወራሽ መሆኗን መሰረት በማድረግ ያቀረበችው የውርስ ንብረት የመካፈል ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ውድቅ በመደረጉ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በወልመራ ወረዳ ፍ/ቤት መናገሻ ችሎት ሲሆን ፍ/ቤቱ ከተጠሪ የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ በመቀበል እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 የተቀመጠውን የ10 ዓመት የጊዜ ወሰን መሰረት በማድረግ ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፊኒፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ብታቀርብም ፍ/ቤቱ የይግባኙ ቅሬታ መ/ሰጪን ያስቀርባል በማለት አከራክሮ ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1000/1/ መሰረት በ 3 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት የስር መጀመሪያ ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታው የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታው መልስ ሰጪን አያስጠራም በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337ን ጠቅሶ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች ታህሳስ 5/2008 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ አቤቱታ ባቀረበችበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የምትልበትን ምክንያት ገልጻ ስህተቱን የሚያርም ውሳኔ ይሰጥላት ዘንድ ጠይቃለች፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፤ ክርክሩ የተሰማው የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ የሆነው በአግባቡ ነው አይደለም የሚለው ጭብጥ መሰረት ተደርጎ ነው፡፡ በዚሁ መሰረትም ግራ ቀኙ ወገኖች ጭብጡን በማስመልከት ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

www.abyssinialaw.com

ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ክስ የመሰረተችው የወራሽነት መብትን መነሻ በማድረግ ነው ለክስ ምክንያት የሆነው ንብረት ባለሀብት የነበሩ የአመልካች አያት የሞቱት ነሐሴ 10/1997 ዓ.ም ሆኖ አመልካች የውርስ ንብረቱ እንዲሰጣት ክስ የመሰረተችው ደግሞ መስከረም 23 ቀን 2007 ዓ.ም እንደሆነ ከመዝገቡ ተረድተናል ተጠሪ የይርጋ መቃወሚያ ያቀረበው ከዚህ በመነሳት ሲሆን ስር ፍ/ቤቶችም ተመሳሳይ ምክንያት በመስጠት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ወስነዋል፡፡ አመልካች ግን ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ ትክክል አይደለም በሚል ክርክሩን በመግፋት የሰበር አቤቱታ አቅርባለች በዚህ ረገድ የሰጠችው ምክንያት ሟች አያቴ የሞተችው በ1997 ዓ.ም ሲሆን በዚህ ወቅት እኔ የ9 ዓመት ልጅ ነበርኩ የሚል ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በወቅቱ ክስ ለማቅረብ እድሜዬ አልደረሰም ነበር ብላለች፡፡ ተጠሪም የአመልካች አያት የእኔ እናት የሞቱት በ1997 ዓ.ም ሳይሆን በ1992 ነው ከማለት በስተቀር ሟቹ ሲሞቱ አመልካች 9 አመቷ አልነበረም በሚል የቀረበው መከራከሪያ የለም፡፡

በተጨማሪም አመልካች ሟች የሞቱት በ1997 ዓ.ም ነው ስትል ተጠሪ ሟች የሞቱት በ1992 ዓ.ም ነው ቢሉም አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ከማቅረቧ በፊት መስከረም 8/2007 ዓ.ም ወራሽነቷን በፍ/ቤት ውሳኔ ስታረጋግጥ ሟች የሞቱት በ1997 መሆኑን ጭምር ማረጋገጧን ያሳያል፡፡ ከዚህ መነሻ ሲደረግ ሟች የሞቱት በ1997 ዓ.ም ሆኖ አመልካች በወቅቱ 9 አመቷ እንደነበር አመልካች ስትገልጽ ተጠሪ ያልተቃወሙ በመሆኑ ሟች በ1997 ዓ.ም መሞታቸውንና አመልካች 9 አመቷ የነበረ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ስለሆነም በ2007 ዓ.ም አመልካች ወራሽነቷን ባረጋገጠችበት ጊዜና አመልካች መብቷ ላይ ክስ ባቀረበችበት ጊዜ የ19 ዓመት ልጅ መሆኗን ተረድተናል፡፡ አመልካች የወራሽነት መብቷን ለመጠየቅም ሆነ ለመጠቀም ወይም ማናቸውንም ህጋዊው ተግባራት ለማድረግ ችሎታ የሚኖራት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.198 በተገለጸው መሰረት 18 ዓመት ሲሞላት ነው፡፡ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ወራሽነት መብቱን አላለ መጠን ካደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/2/ መሰረት በአሥራ አምስት ዓመት ውስጥ በፍ/ቤት ካረጋገጠ ንብረቱን ለመጠየቅ በይርጋ እንደማይታገድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 57114 እና በሌሎች መዛግብት አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በ19 አመቷ አቤቱታ ማቅረቧ ግልጽ ሲሆን ከዚህ መነሻ ሲደረግ አመልካች በመብቷ መጠቀም ከጀመረችበት ጊዜ አሥራ አምስት ዓመት ሳያልፍ ወራሽነቷን ያረጋገጠች ስለሆነ ያቀረበችው ክስ በይርጋ ሊታገድ የማይገባ ሆኖ ሳለ ስር ፍ/ቤቶችም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/1/ እና 1845ን በመጥቀስ የአመልካች አቤቱታ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሳኔና የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ማረም ሲገባው ሳያርም ማለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ብለናል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሳ ኔ**

1. የወልመራ ወረዳ ፍ/ቤት መናገሻ ችሎት በመ/ቁ. 54576 ታህሳስ 27/2007 ዓ.ም የፊኒፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24039 ሰኔ 8 ቀን 2007 ዓ.ም የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 229962 ጥቅምት 8 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች አቤቱታ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ብለናል፡፡
3. የወልመራ ወረዳ ፍ/ቤት መናገሻ ችሎት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ፍሬ ክርክሩን ሰምቶ እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/3/ መሰረት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በየደረጃው ላሉ ፍ/ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ተመላሽ ይደረግ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 117435

መስከረም 24 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ክፍለጽዮን ማሞ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች ፡- አቶ ተስፋዬ መኮንን …….. ጠበቃ አቶ ጥባቡ ምህረቴ ቀረበ

ተጠሪዎች ፡- 1ኛ. ወ/ሮ ሰብለ ለማ…… ቀረበ

2ኛ. ወ/ሮ ፀሐይ ለገሰ ….. አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ ፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ የውርስ ሀብት ይጣራልኝ ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ በፌደራል የመ/ደ/ፍ/ቤትና በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ነው:: የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ ሆኖ ይዘቱም እናቴ ወ/ሮ አየለች ገ/ማርያም በ1989 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩና እኔ ብቸኛ ወራሽ ስሆን ተጠሪዎች የሟች የእህት ልጆች ሆነው ሳለ ሟች እናቴ ልጅ የላትም በማለት እራሳቸውን ምትክ ወራሽ በማድረግ የምትክ ወራሽነት ማስረጃ ከፍርድ ቤት ከመውሰዳቸውም በተጨማሪ የሟች እናቴ ውርስ እንዲጣራ በማድረግ የውርሱ ባለሀብት ሆነዋል፡፡ እኔም ይህንኑ እንዳወኩኝ የፍርድ መቃወሚያ የተጠሪዎችን ምትክ ወራሽነት ተቃውሜ ማስረጃቸው ተሰርዞ ለእኔ ህጋዊ ወራሽነቴ ተረጋግጦ ማስረጃ ተሰጥቶኛል ስለሆነም በዚሁ መዝገብ የፍርድ መቃወሚያ ተጠሪዎች የጸደቀላቸው የውርስ አጣሪ ሪፖርት እንዲሻርና የሟች እናቴ የውርስ ሃብት እንደ አዲስ እንዲጣራልኝ ወጪና ኪሳራም የመጠየቅ መብቴ እንዲጠበቅልኝ የሚል ነው ፡፡

www.abyssinialaw.com

ተጠሪዎችም በሰጡት መልስ አመልካች የሟች ወ/ሮ አየለች ገ/ማርያም ልጅ መሆኑን አምነው አመልካች የሟች እናቱ ውርስ ሲጣራ የሚያውቅና በዚሁ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.39542 ውርሱ ሲጣራ መቃወሚያ አቅርቦ ውድቅ የተደረገበት ስለሆነ 2 ጊዜ መቃወም አይችልም በተጨማሪም ወላጅ እናቱ ከሞቱ 21 ዓመት ያለፋቸው ስለሆነ መቃወሚያው በይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌደ/መጀ/ደረጃ /ፍ/ቤት  የአመልካች የፍርድ መቃወሚያ በይርጋ ይታገዳል ወይስ አይታገድም የሚለውን ጭብጥ መስርቶ ከመረመረ በኃላ የአመልካች እናት የሞቱት ህዳር 29 ቀን 1989 ዓ.ም ሲሆን አመልካች ወራሽነታቸውን ያረጋገጡት ጥር 25 ቀን 2004 ዓ.ም በመሆኑ 15 ዓመት ካለፈ በኃላ ከመሆኑም በተጨማሪ ሟች በሞቱ በ3 ዓመት ውስጥ ወራሽነታቸውን ያላረጋገጡ ስለሆነ የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታው በይርጋ ይታገዳል በማለት ሲወስን ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ እንዲያርም የይገባኝ ቅሬታ የቀረበለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታው መ/ሰጪን ያስጠራል በማለት ያከራከረ ቢሆንም በውሳኔ ረገድ የስር የመ/ደ/ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ሲሆን በቡኩላችንም አመልካች ነሐሴ 18 ቀን 2007 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበዉን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አቅርበን ክርክሩን ሰምተናል በመቀጠልም ከግራ ቀኙ ወገኖች የቀረበውን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በመሆኑም በዚህ ሰበር ችሎት የሚመረመረው ጭብጥ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ወራሽ የሆኑበት ውሳኔ እንዲሰረዝ ሲያስደርግና የሱን ወራሽነት  ሲያረጋግጥ የይርጋ መቃወሚያ ሳይነሳ ታልፎ የተጠሪዎችን ወራሽነት አሰርዞና የሱን ወራሽነት አረጋግጦ የውርስ ማጣራት ሂደቱ ላይ በይርጋ ይታገዳል የተባለበትን አግባብነት ለማጣራት ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበው የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካች አቤቱታ በይርጋ ይታገዳል ማለታቸው ተገቢ ነው ሲሉ አመልካችም በበኩላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ በመልስ መልሳቸው አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

ከክርክሩ መረዳት የተቻለው የአመልካች እናትና የተጠሪዎች አክስት ወ/ሮ አየለች ገ/ማርያም ህዳር 29 ቀን 1989 ዓ.ም ህይወታቸው ያለፈ መሆኑን የአሁን አመልካች የእናቱን ወራሽነት ጥር 25 ቀን 2004 ዓ.ም ያሳወጀ መሆኑን ተጠሪዎች ሚያዚያ 15 ቀን 2005 ዓ.ም ሟች ልጅ የላቸውም በማለትና የእናታቸው ተተኪ ወራሽ መሆናቸውን ማስወሰናቸውንና መጋቢት 9 2005 ዓ.ም የሟች ወ/ሮ አየለች ውርስ ይጣራልን ብለው ባቀረቡት አቤቱታ ፍርድ ቤቱ በ2/9/2005 ዓ.ም የውርስ አጣሪው ያቀረበውን ሪፖርት በማጽደቅ መወሰኑን ነው፡፡ በመቀጠልም የአሁን አመልካች በሐምሌ 22 ቀን 2005 ዓ.ም ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪዎች የወራሽነት

www.abyssinialaw.com

አቤቱታ ሲያቀርቡ ሟች ልጅ የላትም ያሉት በሐሰት ነውና እኔም ልጅና ወራሽ ስለሆንኩኝ ለእነሱ የተሰጠው የወራሽነት ማረጋገጫ ይሰረዝልኝ በማለቱ ፍ/ቤቱ አጣርቶ ጥቅምት 4 ቀን 2006 ዓ.ም የተጠሪዎችን የወራሽነት ማስረጃ በመሰረዝ መወሰኑን ነው፡፡

በመቀጠልም የአሁን አመልካች ተጠሪዎችን አቅርበው ያስወሰኑት የውርስ ሀብት ባለቤትነት ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ማቅረቡንና ተጠሪዎች የአመልካች አቤቱታ በይርጋ የሚታገድ ነው ማለታቸውን የስር ፍርድ ቤቶችም ክርክሩ በይርጋ ይታገዳል ማለታቸውን ነው፡፡

ይህንን መነሻ ስናደርግ የተጠሪዎች ወራሽነት ማረጋገጫ የተሰረዘ መሆኑና በይግባኝ ያለመሻሩ ግልጽ እስከሆነ ድረስ ከወራሽነት ውሳኔው ጋር ተያይዞ የቀረበው የተሰጠ ውሳኔ ይሰረዝልኝና የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ በይርጋ ይታገዳል በማለት የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲወስን የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ብለናል በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መናገሻ ምድብ ችሎት በመ/ቁ 42445 በቀን 9/1/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 163312 ግንቦት 27 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካች የቀረበው የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ በይርጋ አይታገድም ባልነው መሰረት የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን አቅርቦ የግራ ቀኙን የፍሬ ነገር ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1/ መሰረት ይመለስ ብለናል ይጻፍ፡፡
3. ለዚህ ውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊነት ከፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመጣው መ/ቁ.42445 የሆነ መዝገብ ይመለስ፡፡
4. ለዚህ ፍ/ቤት ክርክር ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ወጪ ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዝግቷል ተመላሽ ይደረግ ፡፡

ሩ/ለ                                                   የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.110680

ጥቅምት 30 ቀን 2009 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-ወ/ሮ ጽጌረዳ በቀለ

ተጠሪ፡-ወ/ሮ ፍቅርተ በቀለ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ውርስን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የተጀመረውም የሟች አቶ በቀለ ካሣ ውርስ ይጣራልኝ ሲሉ የአሁኗ አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡የአሁኗ ተጠሪም በጉዳዩ በጣልቃ ገብነት ተከራክረዋል፡፡ግራ ቀኙ ከተለያዩ እናቶች የተወለዱ የአንድ አባት ልጆች መሆናቸውን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

ፍርድ ቤቱም በጣልቃ ገቧ አቤቱታ ላይ የአመልካቿን አስተያየት ከተቀበለ በኃላ ጉዳዩን ወደ ውርስ አጣሪ የመራው ሲሆን አጣሪዋም ውርሱን ካጣሩ በኃላ አከራካሪ ሆኖ የቀረበውን በጉለሌ ክፍለ ከተማ በወረዳ 3 የሚገኝ በቤት ቁጥር 460 የሚታወቀውን ቤት ሟች አቶ በቀለ ካሣ ግማሹ የጣልቃ ገቧ እናት የወ/ሮ በቀለች ጎሽሜ ሆኖ ግማሹ ግን የእርሳቸው መሆኑን ገልጸው የራሳቸውን ድርሻ በ19/11/1997 ዓ.ም. በአዋዋይ ፊት በተደረገ የድርሻ መልቀቅ ውል ለጣልቃ ገቧ እንደለቀቁ ከቀረቡት ማስረጃዎች አጣሪዋ መገንዘብ መቻላቸውን፣ይሁን እንጂ የቤቱን አጋማሽ ከእናታቸው በውርስ ያገኙት ሆኖ ቀሪው ግማሽ ደግሞ በሟች አባታቸው በተደረገላቸው የድርሻ መልቀቅ ውል መሰረት የቤቱን ስመ ሀብት ወደ ራሳቸው አዛውረው እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ በአንድ በኩል የአሁኗ ተጠሪ መከራከራቸውን፣በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች የድርሻ መልቀቅ ውሉ ተደረገ የተባለው አመልካችን ሆነ ብሎ ከውርስ ለመንቀል በመሆኑ ተቀባይነት እንደሌለው እና ሟች የድርሻ መልቀቅ ውሉን አደረጉ ከተባለ በኃላም ቤቱን በስማቸው አድርገው

www.abyssinialaw.com

ሲጠቀሙበት እንደቆዩ በመግለጽ የድርሻ መልቀቅ ውሉ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ መከራከራቸውን ገልጸው በጉዳዩ ላይ ፍርድ እንዲያርፍበት በሚል፣ እንዲሁም ከቤቱ ኪራይ የተገኘው ገንዘብ የውርስ ሀብት ነው የሚል እና ሌሎችም ፍሬ ነገሮች የተገለጹበትን በ18/09/2005 ዓ.ም. የተዘጋጀ ሪፖርት አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በሪፖርቱ ላይ የግራ ቀኙን አስተያየት ተቀብሎ ጉዳዩን ከመረመረ በኃላ የቤቱ አጋማሽ በእናታቸው በኩል ለተጠሪዋ በውርስ የተላለፈ ሆኖ ቀሪውን ግማሽ ደግሞ ሟች በድርሻ መልቀቅ ውሉ መሰረት ለተጠሪዋ ማስተላለፋቸው የተረጋገጠ በመሆኑ ቤቱ የውርስ ሀብት አካል አይደለም፣ቤቱ የውርስ ሀብት አይደለም ከተባለ ደግሞ ከቤቱ የተገኘው የኪራይ ገንዘብም የውርስ ሀብት ሊሆን ስለማይችል አጣሪዋ ከዚሁ ቤት የተገኘው የኪራይ ገንዘብ የውርስ ሀብት ነው በማለት ሪፖርት ማቅረባቸው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ ሪፖርቱን በዚህ አግባብ በማሻሻል በመዝገብ ቁጥር 40838 በ29/09/2006 ዓ.ም. ውሳኔ የሰጠ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካቿ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን በመዝገብ ቁጥር 154581 በ06/04/2007 ዓ.ም. ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመሮምሮ በዚህ ጉዳይ አከራካሪው ቤት የውርስ ሀብት ሳይሆን የተጠሪዋ የግል ሀብት ነው በሚል በስር ፍርድ ቤቶች ተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ሟች በ19/11/1997 ዓ.ም. ለተጠሪ ጥቅም አድርገውት የነበረውን ስጦታ በ26/12/1997 ዓ.ም. ባደረጉት ኑዛዜ የተኩት እና ኑዛዜው ደግሞ አመልካችን ከውርስ የነቀለ ነው ተብሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 88358 በ30/11/2007 ዓ.ም. ከተሰጠው ገዥ ውሳኔ አንጻር ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የአንድ ሰው መብትና ግዴታ ለተወላጆቹ በውርስ ሊተላለፍ የሚችለው በሟቹ ሞት ምክንያት የሚቋረጡ ካልሆነ በቀር ሟቹ በሞተበት ቀን የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች ስለመሆናቸው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 (2) ድንጋጌ ይዘት ያመለክታል፡፡በተያዘው ጉዳይ ሟች የአከራካሪው ቤት አጋማሽ ድርሻ የሟች ባለቤታቸው ማለትም የአሁኗ ተጠሪ እናት መሆኑን በማረጋገጥ በቤቱ ላይ ያላቸውን ግማሽ ድርሻ በ19/11/1997 ዓ.ም. በአዋዋይ ፊት በተደረገ የድርሻ መልቀቅ ውል ለአሁኗ ተጠሪ ያስተላለፉ ስለመሆኑ እና በሞት የተለዩትም በ28/08/2004 ዓ.ም. ስለመሆኑ በአመልካቿም ያልተካደ እና በክርክሩም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር

www.abyssinialaw.com

ነው፡፡ሚች በአከራካሪው ቤት ላይ የነበራቸውን ግማሽ ድርሻ አስቀድመው በ1997 ዓ.ም. ለተጠሪዋ በውል ማስተላለፋቸው ከተረጋገጠ ደግሞ ይህ ቤት በሞቱበት 2004 ዓ.ም. የእርሳቸው ንብረት ነበር ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

አመልካቿ አጥብቀው የሚከራከሩት ሟች አድርገውት የነበረው የድርሻ መልቀቅ ውል ከአንድ ወር በኃላ አካባቢ በ26/12/1997 ዓ.ም. በተደረገ ኑዛዜ የተተካ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 900 እና 901 ድንጋጌዎች መሰረት የድርሻ መልቀቅ ውሉ ውጤት እንደሌለው መቆጠር አለበት በማለት መሆኑን የሰበር አቤቱታቸው ይዘት ያመለክታል፡፡በቁጥር 900 የተመለከተው ድንጋጌ በኑዛዜ የተሰጠን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ተናዛዡ ፈቅዶ ለሌላ ሰው ያስተላለፈ በሆነ ጊዜ አስቀድሞ ተደርጎ የነበረው ኑዛዜ ፈራሽ እንደሚሆን የሚደነግግ ሲሆን በቁጥር 901 የተመለከተው ድንጋጌ ደግሞ አንድ ተናዛዥ አስቀድሞ አንድ ኑዛዜ ካደረገ ከተወሰነ ጊዜ በኃላ ሌላ ኑዛዜ አድርጎ መገኘቱ የሚያስከትለውን ሕጋዊ ውጤት የሚመለከት ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ ኑዛዜው የተደረገው ከድርሻ መልቀቅ ውሉ በኃላ እንጂ በፊት ባለመሆኑ እና ሟች ኑዛዜ አድርገዋል የተባለውም አንድ ጊዜ ብቻ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ በቁጥር 900 እና 901 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው አይደሉም፡፡ሟች በ26/12/1997 ዓ.ም. ባደረጉት ኑዛዜም ቀደም ሲል አድርገውት የነበረው የድርሻ መልቀቅ ውል እንደተጠበቀ መሆኑ ከመገለጹ ውጪ ሟች የድርሻ መልቀቅ ውሉን በኑዛዜው የመተካት ሀሳብ የነበራቸው መሆኑን የሚጠቁም እንዳልሆነ በዚሁ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 88358 ውስጥ ተያይዘው ከሚገኙት የድርሻ መልቀቅ ውል እና የኑዛዜ ሰነዶች ይዘት ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ሟች ቀደም ሲል አድርገውት የነበረውን የድርሻ መልቀቅ ውል በኑዛዜው እንደተኩት ተደርጎ በማስቀረቢያ ትዕዛዙ ላይ የሰፈረው ፍሬ ነገር የመዝገቡን ግልባጭ መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

የኑዛዜ ይሰረዝልኝ ጉዳይን አስመልክቶ በግራ ቀኙ መካከል በመዝገብ ቁጥር 88358 በነበረው ክርክር በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በ30/11/2007 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ በተመለከተ ግራ ቀኙ ሲከራከሩ የነበረው የኑዛዜ ሰነዱን ብቻ መሰረት በማድረግ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር ከሕጉ አንጻር መርምሮ በኑዛዜው ለአሁኗ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኝ ቤት በተሰጠበት ሁኔታ ለአመልካቿ ብር አንድ ሺህ ብቻ መሰጠቱ ከውርስ እንደተነቀሉ የሚያስቆጥር በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 938 እና 939 ድንጋጌዎች መሰረት ግራ ቀኙ የአከራካሪው ቤት እኩል ወራሽ ናቸው በሚል በስር ሁለቱ የበላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በመዝገብ ቁጥር 88358 በነበረው ክርክር የአሁኗ አመልካች መቃወሚያ ያቀረቡትም ሆነ በየእርከኑ ባሉ ፍርድ ቤቶች አከራካሪ ጭብጥ ሆኖ ቀርቦ የነበረው የኑዛዜው ዋጋ እና ሕጋዊ ውጤት እንጂ የድርሻ መልቀቅ ውሉ

www.abyssinialaw.com

ሕጋዊነት ጉዳይ ጭምር አይደለም፡፡በክርክሩ አመልካች የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ "...በሕግ አግባብ የተደረገ ስጦታ አለ የሚሉ ከሆነ በዚህ ረገድ የሚያቀርቡትን ክርክር ይህ ውሳኔ አያግደውም.."በሚል ተፈጻሚነት ባለው የውሳኔው ክፍል በተራ ቁጥር ሁለት ስር በግልጽ የሰፈረውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡በመሆኑም በመዝገብ ቁጥር 88358 የተሰጠው ውሳኔ በስጦታ /በድርሻ መልቀቅ/ ውል ላይ በቀጣይ ሊነሳ የሚችለውን ክርክር ታሳቢ አድርጎ የተሰጠ እንጂ የድርሻ መልቀቅ ውሉ በኑዛዜ ስለተተካ ሕጋዊ ውጤት የለውም ከሚል ድምዳሜ ላይ የተደረሰበት አይደለም፡፡አመልካቿ በሕጉ አግባብ ያላፈሩት እስከሆነ ድረስ ደግሞ የድርሻ መልቀቅ ውሉ ዋጋ የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ የስር ፍርድ ቤቶች የቤቱ አጋማሽ በእናት መስመር በውርስ ለተጠሪዋ የተላለፈ ሆኖ ቀሪውን ግማሽ ደግሞ የግራ ቀኙ አባት በ19/11/1997 ዓ.ም. በአዋዋይ ፊት በተደረገ የድርሻ መልቀቅ ውል ለአሁኗ ተጠሪ ያስተላለፉ በመሆኑ ቤቱ የሟች አቶ በቀለ ካሣ የውርስ ሀብት አይደለም በሚል የደረሱበት ድምዳሜ እና ይህንኑ ድምዳሜ መሰረት በማድረግ የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡አከራካሪውን ቤት የግራ ቀኙ አባት የአሁኗን ተጠሪ እናት ከማግባታቸው በፊት ያፈሩት ነው ከማለት በቀር በእናት መስመር ከቤቱ የውርስ ድርሻ አለኝ በማለት አመልካቿ በስር ፍርድ ቤቶችም ሆነ በዚህ ሰበር ደረጃ ያቀረቡት ክርክር አለመኖሩን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የውርስ አጣሪዋን ሪፖርት በማሻሻል በመዝገብ ቁጥር 40838 በ29/09/2006 ዓ.ም. የሰጠው እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 154581 በ06/04/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

**<u>የሐሳብ ልዩነት</u>**

አብላጫው ድምጽ የቤቱ አጋማሽ በእናት መስመር በውርስ ለተጠሪ የተላለፈ ሆኖ ቀሪውን ግማሽ የግራቀኙ አባት ሐምሌ 19 ቀን 1997 ዓ.ም በአዋዋይ ፊት በተደረገ የድርሻ መልቀቅ ውል ለአሁን ተጠሪ ያስተላለፉ በመሆኑ ቤቱ የሟች አቶ በቀለ ካሳ የውርስ ሀብት አይደለም ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ ሆኖም ሟች ሐምሌ 19 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገ የድርሻ መልቀቅ ውል ስምምነት አከራካሪውን ቤት ከሟች ባለቤታቸው ወ/ሮ በላይነሽ ጎሽሜ ጋር በጋራ ያፈሩት መሆኑን በመጥቀስ ድርሻቸውን ለተጠሪ የለቀቁ መሆኑን የሚያሳይ ቢሆንም ሟች ይህንኑ ቤት በተመለከተ ነሐሴ 26 ቀን 1997 ዓ.ም ባደረጉት ግልጽ ኑዛዜ ድርሻቸውን ለተጠሪ የተናዘዙላት መሆኑን የኑዛዜው ሰነድ ያሳያል፡፡ በዚህ የኑዛዜ ሰነድ ላይ ክርክር ተደርጎበት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 88358 ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ አመልካችን በተዘዋዋሪ መንገድ በዝምታ ከውርስ የነቀለ በመሆኑ አመልካች ከጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ በመሆን የውርስ ንብረቱን ሊከፋፈሉት ይገባል በማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆኑን ጠቅሶ ውሳኔውን በማጽናት ተጠሪ በሕግ አግባብ የተደረገ ስጦታ አለ የሚሉ ከሆነ በዚህ ረገድ የሚያቀርቡትን ክርክር ውሳኔው አያግደውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ሟች ነሐሴ 26 ቀን 1997 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ሐምሌ 19 ቀን 1997 ዓ.ም ያደረጉት የድርሻ መልቀቅ ውል ስምምነት የተጠበቀ ነው በማለት የገለጹ ቢሆንም የሟች ኑዛዜ አመልካችን ከውርስ የነቀለ ነው በማለት አመልካች ከጠቅላላ የኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ እንድትሆን በዚሁ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ ሟች በቤቱ ላይ አስቀድሞ ያደረጉት የድርሻ መልቀቅ ውል ስምምነት ውጤት ያበቃለት ነው፤ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች እና ተጠሪ እኩል ወራሽ ናቸው በማለት በሰጠው ውሳኔ መሰረት የሟች ድርሻ ሊከፋፈል ይገባል በማለት ስማችን በተ.ቁ. 3 እና 5 ላይ የተጠቀሰው ዳኞች አብላጫው ድምጽ ከደረሰበት ድምዳሜ በሃሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

# ባንክና ኢንሹራንስ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 88135

ሐምሌ 16 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አምልካች፡- ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ (አ.ማ) - ነ/ፈጅ ወርቅነህ ዘውዱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ነፃነት ሀቤቤ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፤

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ተሽከርካሪ የሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የተሰጠ የመድን ሽፋን ኃላፊነትን የሚመለከት ነው፡፡ ከስር ፍርድ ቤት በዚህ ክርክር ወ/ሮ አለምነሽ ገብረ ማርያም በራሷና ሞግዚት በሆነችላቸው እነ ህፃን አዲስ ብርሃኑ(አራት ሕፃናት) ስም ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ አመልካች ደግሞ ሶስተኛ ወገን ተከራካሪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ወ/ሮ አለምነሽ ገብረማርያም በተጠሪ ላይ ያስቀረበችው ክስ ነው ወ/ሮ አለምነሽ ገብረማርያም የተጠሪ ንብረት ቁጥር 3-178887 የሆነ መኪና የልጆች አባት የሆነውን አቶ ብርሃኑ ጥላሁንን የግጭት ጉዳት አድርሶበታል ባለቤቴና የልጆቼ አባት በአደጋው በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ስለሞተ በእኔና ልጆቼ በመተዳደሪያ እረገድ ለደረሰብን ጉዳት ብር 541,538 (አምስት መቶ አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር) ካሳ እንዲከፈል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርባለች ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርባ የተጠየቀውን የካሳ መጠን በመቃወም ክርክር ያቀረበች ሲሆን አመልካች የመድን ሽፋን

የሰጠ በመሆኑ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ እንዲሰጥላት ጠይቃለች አመልካች በክርክሩ ገብቶ የተጠሪ መኪና በሶስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ለአንድ ሰው እስከ ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) የመድን ሽፋን የሰጠ መሆኑን ከገለፀ በኃላ ተጠሪ በመድን ታሳቢ መሠረት አደጋው የደረሰ መሆኑን የማሳወቅ ግዴታዋን አልተወጣችም፡፡ ስለዚህ በመድን ውሉ መሰረት ሽፋን እንድሰጥ አልገደድም፡፡ በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ ተጠሪ ለወ/ሮ አለምነሽ ገብረማርያና ልጆቻቸው ብር 222,538 ወይም /ሁለት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ ስምንት እንድትከፍል ወስኗል፡፡ ከዚህ የካሳ ገንዘብ አመልካች ብር 40.000 (አርባ ሺህ) እንዲከፍል ወስኗል፡፡

2. አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች መጋቢት 10 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ አደጋው የደረሰ መሆኑን በአስር ቀን ውስጥ ለአመልካች የማሳወቅ ግዴታ በመድን ውሉ ገብታለች፡፡ ተጠሪ በ10 ቀን ውስጥ አደጋ የደረሰ መሆኑን ያላሳወቀች በመሆኑ አመልካች በመድን ውል መሠረት ብር 40.00 የመክፍል ግዴታ የለበትም የበታች ፍርድ ቤቶች በግልፅ የተቀመጠውን የውል ቃል በመተላለፍ አመልካች በመድን ውል መሠረት ኪሳራውን እንዲጋራ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

3. ተጠሪ ሚያዝያ 21 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈው መልስ ተጠሪ በአስር ቀን ውስጥ አደጋው የደረሰ መሆኑን ለአመልካች አለማሳወቁ አመልካች በመድን ውል መሰረት ለሶስተኛ ወገኖች የመድን ሽፋን የሰጠበትን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነቱን አያስቀርም፡፡ ስለሆነም የአመልካች ክርክር የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክራለች አመልካች ግንቦት 15 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፤

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች የመድን ሽፋን የሰጣት የመለያ ቁጥር 3-17887 የሆነችው መኪና በሟች ብርሃን ጥላሁን ላይ ባደረሰው የሞት አደጋ ተጠሪ ከተወሰነባት የካሳ ገንዘብ ውስጥ አመልካች ብር 40,000 (አርባ ሺህ) ለሟች አቶ ብርሃን ጥላሁን ሚስትና ልጆች እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የተጠሪ መኪና በሌላ ሰው አካል ወይም ህይወት ላይ ለሚያደርሰው አደጋ እስከ ብር 40,000 (አርባ ሺህ) ኃላፊነቱን ለመጋራት የመድን ሽፋን የሰጠ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ አመልካች የመድን ሽፋን የሰጣት መኪና በሟች ብርሃን ጥላሁን ላይ የሞት አደጋ ማስከተሏና ተጠሪ ለጉዳቷ ኃላፊ መሆኗ በፍርድ ቤት ውሳኔ

www.abyssinialaw.com

ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የሚከራከረው በሰጠሁት የመድን ሽፋን መሰረት ገንዘቡን ለከሳሾች የምከፍለው ተጠሪ በመድን ውሉ መሰረት በአስር ቀን ውስጥ አደጋው የደረሰ መሆኑን ብታሳውቀኝና ግዴታዋን ብትወጣ ነበር፡፡ ተጠሪ የውል ግዴታዋን ያልተወጣችና በአስር ቀን ውስጥ አደጋው መድረሱን ያላሳወቀችው በመሆኑ የመድን ሽፋን የሰጠሁበትን ገንዘብ ለከሳሾች የመክፈል ግዴታ የለብኝም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ አደጋው የደረሰ መሆኑን በአሰር ቀን ውስጥ ለአመልካች ለማሳወቅ የውል ግዴታ የገባች መሆኑን በመካድ ያቀረበችው ክርክር የለም፡፡ ተጠሪ የምትከራከረው እኔና አመልካች በቅድመ ሁኔታነት በመድን ውል የተዋዋልነው ሃይለ ቃል በህግ ያልተፈቀደ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ነው፡፡

6. ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በቀር ተዋዋዮች ሁሉ የሚዋዋሉበትን ጉዳይ የመወሰን መብት ያላቸው መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1711 ተደንግጓል፡፡ የመድን ሥራ የሚሰሩ የመድን ኩባንያዎች በመድን ፖሊሲ ውስጥ ፖሊሲውን ተጠያቂነትን አያስከትልም ወይም በፖሊሲው መሰረት የካሳ ክፍያ ጥያቄ መነሻ የሆነው ክስተት ከደረሰ በኃላ የተወሰነ ድርጊት ከተፈፀመ ወይም ሳይፈጸም ከቀረ ኃላፊነቱ ቀሪ ይሆናል የሚል የውል ሁኔታ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑ ስለተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ዋስትና የወጣው አዋጅ ቁጥር 559/2000 በአንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ የህግ ድንጋጌ አንፃር ሲታይ አመልካች ተጠሪ አደጋው ከደረሰ በኃላ በአስር ቀን ውስጥ ካላሳወቀችኝ በመድን ፖሊሲው መሰረት ገንዘቡን ለተጎጂዋ (ለከሳሾች) የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበው ክርክር ከላይ ይዘቱ የተገለፀውን የህግ ድንጋጌ የሚጥስና የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች በመድን ፖሊሲው መሠረት ብር 40,000 (አርባ ሺህ) ብር ለከሳሾች እንዲከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት መጋቢት 16 ቀን 2005 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 117608

መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ/ም

**ዳኞች:-** ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሡናይት አድነው

ጳውሎስ ኦርሺሶ

**አመልካች:-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነገረ ፈጅ ጂሲያክን ቀረቡ

**ተጠሪ** :- የኖሌ ካባ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ተወካይ ተስፋዬ ተሾመ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመድን ዋስትና ክፍያ የሚመለከት ክርክር ሲሆን የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በመዝገብ ቁጥር 29030 በአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች ንብረትነቱ የተጠሪ ለሆነው ሰሌዳ ቁጥር 4-02912 ኦሮ በውል ቁጥር 5041112020046113 ተጠሪ ባቀረበው ጥያቄ የኢንሹራንስ ዋስትና የብር 38,431.80 መስጠቱን የመድን ዋስትናውም በንግድ ህጉ መሠረት ተሟልቶ ተፈርሞ ከየካቲት 9 ቀን 2005 ዓ.ም እስከ የካቲት የ9 ቀን 2006 ዓ/ም ድረስ የሚቆይ የአንድ ዓመት ዋስትና ተጠሪ የገዛ ቢሆንም የሚፈለግበትን ክፍያ እንዲከፍል ሲጠየቅ ፈቃደኛ ባለመሆኑ አመልካች ክስ ለማቅረብ እንደተገደደ በመግለጽ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 24704 ከዚህ ጉዳይ ጋር ተመሳሰይነት ባለው ጉዳይ አስገዳጅ ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ ተጠሪ የሚፈለግበትን ክፍያ እንዲፈጽም እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ የመድን ዋሰትና ከአመልካች ጋር የገባ መሆኑን ሳይክድ ንብረትነቱ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የሆነ መኪና በኦሮሚያ ኢንሹራንስ ኩባንያ ስር ውሉ እንዲገባ ከኦሮሚያ ምክር ቤት በቀን 29/11/2005 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ውሳኔ ስለተላለፈ ውሉን

www.abyssinialaw.com

ሊቀጥልበት አይገባም፣ ተጠሪም አያስገድድም፡፡ በዚህ ውል ግዴታም የተፈፀመልኝ ነገር የለም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆንለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ. 24704 የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ ከተያዘው ጉዳይ ተመሳሳይነት እንደሌለው፣ በንግድ ሕግ አንቀጽ 664 መሠረት ክፍያ ለኢንሹራንስ ከተከፈለ በኃላ ቀጥሎ ቢሆንም ኖሮ ውል ተቀባይ ጉዳት በንብረቱ ላይ የሚደርስ ከሆነ ውሉ እንደ አዲስ መቀጠል እንዳለበት የውሉን ቀጣይነት ለማረጋገጥ እንጂ አመልካች በፈለገበት ጊዜ ከሶ ክፍያ ማስፈጸም ወይም ውል እንዲያቋርጥ ገደብ የሌለው መብት ለማጎናፀፍ አይደለም፡፡ አመልካች በዚህ ውል የሚኖሩት መብቶች ካሉ ክፍያ ፈፀሞ አንድ ወር ካለፈ ውሉ እንደተቋጠ ስለሚቆጠር የሚመጣው ኀላፊነት ለመውሰድ አይገደድም፡፡ በዚህ ክርክር ውስጥ ደግሞ ተጠሪም ክፍያ ያቋረጠው ከዓመት በላይ ከመሆኑም በላይ የመድን ውል ጊዜ ገደቡም በቀን 09/06/2006 ዓ/ም የተጠናቀቀ ስለሆነ ተጠሪ የመድን ዋስትና ውል ገንዘብ እንዲከፍል የሚገደድበት ሁኔታ ስለሌለ የቀረበውን ክስ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 33/2/ መሠረት ውድቅ በማድረግ ተጠሪ በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡

አመልካች በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሰርዞታል የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ሠረታዊ ይዘትም የተጠሪ ንብረት የሆነውን የሰሌዳ ቁጥር 4-02912 ኦሮ አምቡላንስ ተሽከርካሪ ለአንድ ዓመት የሚቆይ በዱቤ ማስታወሻ የመድን ሽፋን የሰጠ ስለመሆኑ የአርቦን ክፍያ ጊዜው በስምምነት ያልተገለጸ ስለሆነ መድን ሰጪ መብቱን ያለ ምንም ቅደመ ሁኔታ በ2 ዓመት ውስጥ ከሶ መጠየቅ እንደሚችል የውል ግዴታውም ተጠሪ ሽፋን ለተሰጠበት ጊዜ የ11 ወር ከ11 ቀን አርበን ተሰልቶ ሊከፈል እንደሚገባ የሚያስገደድ ስለመሆኑ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ ተሽሮ ተጠሪ የመድን ሽፋኑ ለተገለገለበት ጊዜያት አርበን ተሰልቶ እንዲከፈለው እንዲወሰን የሚጠይቅ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

ይህ ችሎትም መዝገቡን ከመረመረ በኋላ ግራ ቀኙን ሐምሌ 27/2008 ዓ/ም በቃል ከማነጋገሩ በተጨማሪ በተጠሪ ተፃፉ የተባሉትን የኢንሹራንስ ውል ማቋረጫ ደብዳቤዎች ወደ አመልካች መቼ ገቢ እንደተደረጉ ለመለየት ደብዳቤዎቹን በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡

ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ከላቸው ድንጋጌዎች ጋር

www.abyssinialaw.com

በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያሻው ዓብይ ነጥብ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ለአመልካች የመድን ውሉ ሽፋን ለመክፈል አይገደድም በማለት የሰጡት ውሳኔ በሕጉ አግባብነት ወይስ አይደለም? የሚል ሆኖ አገኝቶታል፡፡

ከስር የክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች እና ተጠሪ ለአንድ ዓመት ጸንቶ የሚቆይ የመድን ዋስትና ውል ስምምነት ያደረጉ ስለመሆናቸው ያከራከራ ጉዳይ አይደለም፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የመድን ዋስትና ከአመልካች ጋር መግባቱን ላይክድ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ውሳኔ መሠረት በክልሉ ያሉ የመንግስት መኪናዎች ከኦሮሚያ ኢንሹራንስ ኩባንያ ጋር ውል እንዲገቡ በመወሰኑ ከአመልካች ጋር የነበረውን ግንኙነት ማቋረጡን በስር ፍርድ ቤትና በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ካቀረበው ክርክር ተረድተናል፡፡ አመልካች በበኩሉ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የንግድ ህግ ቁጥር 666 የተረጎመበት አግባብ ተገቢ አለመሆኑን፤ የኢንሹራንስ ውል ማቋረጫ ደብዳቤ ሁለት ጊዜ ቢፅፉም በአንድ ቀን ጥር 22/2006 ዓ/ም የደረሰው ስለመሆኑ፤ የአርቦን ክፍያውም በዱቤ ማስታወሻ የተሰጠ እንጂ ከመጀመሪያውኑ የመክፈያ ቀን ያልተቆረጠለት ስለመሆኑ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ ተገቢነት እንደሌለው መከራከሩን ተገንዝበናል፡፡

የስር ፍርድ ቤት አመልካች የአርቦን ክፍያው በአንድ ወር ጊዜ ባለመጠየቁ ውሉ እንደተቋረጠ ስለሚቆጠር ክፍያውን መጠየቅም ሆነ ጉዳት ከደረሰም ኂላፊነት ለመውሰድ አይገደድም ከሚል ድምዳሜ ላይ መደረሱን የውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ አደረጉት የተባለው የመድን ውል ቆይታው አንድ ዓመት እንደነበር አላከራከረም ተጠሪ አመልካች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የአርቦን ክፍያውን መጠየቅ ነበረበት የሚል ክርክር ያቀረበ ቢሆንም የግራቀኙ ስምምነት ክፍያው በአንድ ወር ካልተጠየቀ ቀሪ እንደሚሆን ስለመስማማታቸው በህግ የተደገፈ ክርክር አላቀረበም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገው የመድን ውል ስምምነት በዱቤ ማስታወሻ የተሰጠ ስለመሆኑ ካቀረበው ክርክር ተመልክተናል፡፡ ተጠሪ በግራ ቀኙ የነበረው የመድን ውል ስምምነት በዱቤ ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን በመካድ ያቀረበው ህጋዊ ክርክር የለም፡፡ የግራ ቀኙ ግንኙነት በብድር /ዱቤ/ ላይ የተመሰረተ ከሆነ ደግሞ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የታወቀ ጊዜ የተቆረጠለት የአርቦን ክፍያ እንደሆነ በመውሰድ የንግድ ህግ ቁጥር 666 (4) መሰረት በማድረግ ከአንድ ወር በኂላ ክፍያ መጠየቅ እንደማይቻል ደምድሞ የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጉ በሕጉ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ሌላ የክርክር ነጥብ እና በሥር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ያገኘው ውል የተቋረጠበት ጊዜ የተመለከተ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የክልሉ መንግስት በሰጠው ውሳኔ መሠረት የክልሉ መኪናዎች ከክልሉ እንሹራንስ ኩባንያ ጋር የመድን ውል እንዲገቡ ያዘዘ በመሆኑ የውል ማቋረጫ ደብዳቤ በቀን 12/11/2005

www.abyssinialaw.com

እና በ20/05/2006 ዓ/ም ለአመልካች ጽፈናል የሚል ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ከተጠሪ የተፃፉ ደብዳቤዎች ገቢ የሆኑት ጥር 22/2006 ዓ/ም መሆናቸውን አጥብቆ ተከራክሯል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀርቦ የተመለከታቸው ሁሉቱም ደብዳቤዎች ለአመልካች ጽ/ቤት ገቢ የሆኑት ጥር 22 ቀን 2006 ዓ/ም መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለአመልካች ተላኩ የተባሉ ደብዳቤዎች በ12/11/2005 እና በ20/5/2006 የተፃፉ ስለመሆናቸው ግልጽ ቢሆንም ለአመልካች በተፃፉበት ቀን ገቢ ስለመሆናቸው በተጠሪ በኩል የቀረበ ማረጋገጫ የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የአሁኑ ተጠሪ ውሉ እንዲቋረጥ በወቅቱ ጠይቀናል በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በአመልካች የተጠየቀው የአርቦን ክፍያ የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ የግራ ቀኙ ስምምነት የንግድ ሕጉ መሠረታዊ ይዘትና ዓለማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህታት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

ተጠሪ በዱቤ ሽፋን ለተሰጠው ተሽከርክሪ መክፈል ያለበት አርቦን መኖሩ ከተረጋገጠ ቀጥሎ መታየት ያለበት የአርቦን መጠኑ ነው፡፡ በግራ ቀኙ ስምምነት መሰረት በአመት መክፈል ያለበት የገንዘብ መጠን 38,431.80 መሆኑ አላከራከረም፡፡ ተጠሪ ውል ማቋረጡን ያሳወቀው የውል ዘመኑ ከመጀረ ከ11 ወር ከ11 ቀን በኃላ ስለመሆኑ አመልካች ካቀረበው የሰበር አቤቱታ ተረድተናል፡፡ ተጠሪ በሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው መልስ በአመልካች የተጠቀሰው ጊዜ ተገቢ አለመሆኑን በመካድ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ተጠሪ የተገለገለበት የ11 ወር ከ11 ቀናት የአርቦን ክፍያ መጠን 36,403.45/ ሰላሳ ስድስት ሺህ አራት መቶ ሶስት ከአርባ አምስት ሳንቲም /መሆኑን አመልካች በሰበር አቤቱታ አመልክቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በሰበር ችሎት በሰጠው መልስ ከላይ የተገለፀውን መጠን ገንዘብ አለመሆኑን በግልጽ ያቀረበው ክርክር የለም በተጠሪ በኩል በግልጽ ያልተካዳ ፍሬ ጉዳይ እንደታመነ የሚቆጠር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 83 እና 235 ያስገነዘቡናል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ ውሉን እስከ ተቋረጠበት ጊዜ ድረስ ለተገለገለበት የኢንሹራንስ ጊዜያት አርቦን ተሰልቶ የ11 ወር ከ11 ቀናት ብር 36,403.45 የመክፈል ኂላፊነት አለበት ብለናል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያቶች የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ በሰጠው የመድን ውል ሽፋን ተጠሪ ለተገለገለበት የኢንሹራንስ ጊዜያት በውሉ መሰረት ተገቢ የአርቦን ክፍያ መክፈል እያለበት ተጠያቂ ሊሆን አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሽረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 29030 በ19/06/2007 ዓ/ም የሰጠው ብይን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 205391 በ25/9/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል ፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ ለተገለገለበት የኢንሹራንስ ጊዜያት አርቦን የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡ ተጠሪ ለአመልካች ብር 36,403.45 (ሰላሳ ስድስት ሺ አራት መቶ ሶስት ከአርባ አምስት ሳንቲም) ይክፈል ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 104544

ግንቦት 25 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ፅጋብ ገብሩ
2. ቄስ ካህሳይ ገ/ማርያም
3. ወ/ሮ ገርገስ ገ/አናንያ
4. ወ/ሮ አማረች ወላይ

} የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ክርክሩ በተጀመረበት የሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሽሬ እንዳስላሴ ምድብ ችሎት ተከሳሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረበው በሰጠው የመድን ሽፋን መሰረት ለክሱ ኃላፊ መሆኑ በመረጋገጡ ከሳሾች ለነበሩት የአሁኖቹ ተጠሪዎች በድምሩ ብር 350,760.31 (ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ከሰላሳ አንድ ሳንቲም) ካሳ እንዲከፍል በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 16952 በ25/03/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 63314 በ26/09/2006 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪዎቹ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት ንብረትነቱ የ1ኛ ተጠሪ የሆነ የሰሌዳ ቁጥር ኢት-312179 ማርቸዲስ የጭነት መኪና የ4ኛ ተጠሪ ልጅ በሆነው አቶ ተከስተ ካህሳይ

www.abyssinialaw.com

ሲሽከረከር በደረሰበት የመገልበጥ አደጋ ሾፌሩ እና በጋቢናው ውስጥ ተሳፍሮ የነበረ አቶ ኃይለማርያም ካህሳይ የሚባል የ2ኛ እና የ3ኛ ተጠሪዎች ልጅ መሞታቸውን እና በተሽከርካሪው ላይም ከፍተኛ ጉዳት የደረሰ መሆኑን፣ተከሳሽ ድርጅት በተሽከርካሪው ላይ ለሚደርስ ጉዳትም ሆነ በተሳፋሪ እና በአሽከርካሪው ላይ ለሚደርስ የሞት አደጋ የመድን ሽፋን የሰጠ መሆኑን፣ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ከሟች ልጆቻቸው ያገኙት የነበረው ድጎማ የቀረባቸው መሆኑን እና ተከሳሽ ድርጅት ተሽከርካሪውን ከወደቀበት ያነሳ ቢሆንም ለማስጠገንም ሆነ የማስጠገኛ ወጪ ለመክፈል እንዲሁም ካሳ ለመክፈል ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን እና በዚህም ምክንያት 1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪውን በራሳቸው ወጪ ያስጠገኑ መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ፡-

1. 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ ለተሽከርካሪው ማስጠገኛ የወጣውን ብር 220,760.31 እና ተሽከርካሪው ለጥገና በቆመበት ጊዜ ለተቋረጠ ጥቅም ብር 120,000 በድምሩ ብር 340,760.31፣
2. 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን በተመለከተ በልጃቸው ሞት ምክንያት የተቋረጠውን ገቢ በመድን ሽፋኑ መጠን ብር 40,000፣
3. 4ኛ ተጠሪን በተመለከተ በአሽከርካሪው ሞት ምክንያት ለተቋረጠ ጥቅም በመድን ሽፋኑ መጠን ብር 90,000፣

በድምሩ ብር 470,760.31 ተከሳሽ ድርጅት ለከሳሾች እንዲከፍል ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ ከሌሎች የክርክር ነጥቦች በተጨማሪ ተሽከርከሪው ሕጋዊ መንጃ ፈቃድ በሌለው ሰው ሲሽከረከር ለሚደርስ ጉዳት መድን ሰጪው ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ በ1ኛ ተጠሪ እና በአመልካች መካከል በተደረገው የመድን ውል በአንቀጽ 3 የተመለከተ መሆኑን፣አቶ ተከስተ ካህሳይ ይዘውት የነበረው ቁጥሩ 04-465219 የሆነው መንጃ ፈቃድ የተሰጠው ለአቶ ተከስተ ካህሳይ ሳይሆን ለአቶ ቅዱስ ሙሉጌታ መሆኑን መንጃ ፈቃዱን የሰጠው አካል ያረጋገጠ በመሆኑ ሀሰተኛ መንጃ ፈቃድ በያዘ ሰው ሲሽከረከር ለደረሰው አደጋ አመልካች ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የ1ኛ ተጠሪን ምስክሮች ከሰማ በኋላ በመድን ውሉ አንቀጽ 3 አነጋገር አመልካች ድርጅት ኃላፊነት የማይኖርበት አደጋው በደረሰበት ጊዜ ተሽከርካሪው ሲሽከረከር የነበረው መንጃ ፈቃድ በሌለው ሰው በሆነ ጊዜ እንጂ ሕጋዊ መንጃ ፈቃድ በሌለው ሰው በሆነ ጊዜ ጭምር ተደርጎ መተርጎም የሚገባው አለመሆኑን፣1ኛ ተጠሪም አሽከርካሪውን የቀጠሩት ግለሰቡ የያዘውን መንጃ ፈቃድ አይተው ስለመሆኑ በምስክሮች ያስረዱ መሆኑን፣መንጃ ፈቃዱን ከማየት በቀር ሕጋዊነቱን ከሚመለከተው አካል የማረጋገጥ ግዴታ የመድን ውሉ የማይጥልባቸው መሆኑን፣ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎችም በሟቾቹ ይረዱ የነበረ ስለመሆኑ

www.abyssinialaw.com

እና ወራሽነታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ያቀረቡ መሆኑን፣1ኛ ተጠሪ ለተሸከርካሪው ማስጠገኛ ያወጡት ወጪ በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን እና የተሸከርካሪው የተቋረጠ ጥቅም ግን የመድን ሽፋን ያልተሰጠው መሆኑን ገልጾ አመልካቹን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ የተሸከርካሪውን የተቋረጠ ጥቅም አስመልክቶ ከተጠየቀው ገንዘብ ውጪ ያለውን በክሱ የተመለከተውን የካሳ መጠን አመልካች ለተጠሪዎቹ እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አደጋው በደረሰበት ጊዜ ተሸከርካሪውን ሲያሽከረክር የነበረው ግለሰብ ይዞት የነበረው መንጃ ፈቃድ ተገቢ ወይም ሕጋዊ ያልሆነ መንጃ ፈቃድ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የአመልካች ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች ታልፎ አመልካች በንግድ ሕጉ እና በመድን ውሉ መሰረት የመካስ ኃላፊነት አለበት ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው ነጥቦች፡-

1. ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን በቀጥታ በአመልካች ላይ ክስ ማቅረባቸው ስነ ስርዓታዊ ነው ወይስ አይደለም?
2. አመልካቹን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በክርክሩ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ከአንድ በላይ የሆኑ ከሳሾች የህብረት ክስ ሊያቀርቡ የሚችሉበትን ሁኔታ በተመለከተ ብዙ ሰዎች በአንድ ምክንያት ወይም ዓይነታቸው አንድ በሆኑ በብዙ ምክንያቶች የተመሰረተ ክስ ሲያቀርቡና ምክንያቱም እያንዳንዱን ከሳሽ የሚመለከት ሲሆን ከሳሾቹም ተነጣጥለው በየራሳቸው ስም ክስ ለማቅረብ የሚችሉ ሲሆኑ ለክሱ መነሻ የሆነው ሀብት ወይም መብት የጋራ ወይም የየራሳቸው ቢሆንም እንኳ በሚቀርበው ክስ ሊወሰን የሚችለው የሕግ እና የስረ ነገር ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ ከሳሾቹ በሕብረት ሆነው አንድ ክስ ብቻ ለማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 35 ይደነግጋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ የተሸከርካሪው ባለቤት ሲሆኑ ክሱን ያቀረቡትም ከአመልካች ጋር ያላቸውን የመድን ውል መነሻ በማድረግ የመድን ሽፋን የተሰጠውን እና የመገልበጥ አደጋ የደረሰበትን ተሸከርካሪ ጠግኖ ወደ ነበረበት ለመመለስ ተጠሪው ያወጡትን ወጪ ለማስተካት እና

www.abyssinialaw.com

የተቋረጠ ጥቅም ለማስከፈል በመሆኑ በተናጠልም ቢሆን በአመልካቹ ላይ ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም ያላቸው መሆኑ የሚያከራክር አይደለም:: ቀሪዎቹ ተጠሪዎቹ ክስ ያቀረቡት በተሽከርካሪው ተሳፍረው የነበሩት ሰው እና የተሽከርካሪው ሾፌር በመሞታቸው ከሟቾቹ ስናገኘው የነበረው ጥቅም ቀርቶብናል በሚል ተገቢውን ካሳ ለማስወሰን ነው:: በመሰረቱ ጉዳቱን አደረሰ የተባለው ተሽከርካሪ ባለንብረት 1ኛ ተጠሪ ናቸው:: ስለዚህ 2ኛ፣3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ተቋርጦብናል ለሚሉት ጉዳት የካሳ ክፍያ ክስ ሊያቀርቡ የሚችሉት አግባብነት ባላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት በተሽከርካሪው ባለቤት ላይ እንጂ በአመልካች ላይ ሊሆን አይችልም:: 2ኛ፣3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በተናጠል በአመልካቹ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚችሉበት አግባብ ከሌለ ደግሞ በጋራም በመሆን በአመልካቹ ላይ ክስ ሊያቀርቡ የሚችሉበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ አይኖርም::ተሽከርካሪው ለሚያደርሰው አደጋ እና ጉዳት ከአመልካች የተሰጠ የመድን ሽፋን መኖሩም ቢሆን 2ኛ፣3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎችን በቀጥታ በአመልካቹ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችላቸው አይሆንም:: 2ኛ፣3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ከአመልካቹ ጋር ሊከራከሩ የሚችሉት በ1ኛ ተጠሪ ላይ ክስ መስርተው በ1ኛ ተጠሪ ጠያቂነት አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 43 ድንጋጌ መሰረት ወደ ጉዳዩ እንዲገባ የተደረገ በሆነ ጊዜ ነው:: በመሆኑም ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን በቀጥታ በአመልካች ላይ ክስ ማቅረባቸው ስነ ስርዓታዊ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም:: ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ይህንኑ ተገንዝቦ በክሱ አቀራረብ ስነ ስርዓታዊነት ረገድ ተገቢውን ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ መስጠት ሲገባው ከስነ ስርዓት ውጪ በሆነ አግባብ የቀረበለትን ክስ መርቶ ውሳኔ መስጠቱ እና ውሳኔውም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተቀባይነት ማግኘቱ ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም::

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የመድን ውል በአንቀጽ 3 ስር የመድን ሽፋን የተሰጠው ተሽከርካሪ ለመንዳት ተገቢ የሆነውን መንጃ ፈቃድ ባልያዘ ወይም ይህን መንጃ ፈቃድ እንዳይዝ በተከለከለ ግለሰብ ሲነዳ ለደረሰ አደጋ መድን ሰጪው ኃላፊነት የማይኖርበት መሆኑን የሚደነግግ የማግለያ ድንጋጌ መኖሩ አላከራከረም:: የስር ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ በአመልካቹ የቀረበውን ክርክር ሳይቀበሉ የቀሩት የማግለያ ድንጋጌው ተገቢውን መንጃ ፈቃድ ባልያዘ ወይም እንዳይዝ በተከለከለ ግለሰብ የሚል እንጂ ሀሰተኛ መንጃ ፈቃድ በያዘ የሚል አነጋገር የሌለው መሆኑን፣እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ አሽከርካሪውን የቀጠሩት መንጃ ፈቃዱን በማየት በመሆኑ እና የመድን ውሉም በተሽከርካሪው ባለቤት ላይ የመንጃ ፈቃዱን እውነተኛነት የማረጋገጥ ግዴታ የማይጥል መሆኑን በመግለጽ ነው:: በመሰረቱ መንጃ ፈቃድ ማለት ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን ለመንዳት የሚያስችል አግባብነት ባለው አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሰረት የሚሰጥ የመንጃ ፈቃድ ስለመሆኑ በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 በአንቀጽ 2 (8) ስር ትርጉም የተሰጠው ሲሆን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ

www.abyssinialaw.com

ፈቃድ ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 600/2000 በአንቀጽ 2 (3) የተመለከተው የመንጃ ፈቃድ ትርጉምም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ነው።የ1ኛ ተጠሪ ሰራተኛ የነበሩት የተሽከርካሪው ሾፌር በተጠቀሱት አዋጆች ድንጋጌዎቸ መሰረት የተሰጠ መንጃ ፈቃድ ያልነበራቸው እና ይዘውት የነበረው መንጃ ፈቃድም የተሰጠው ለእርሳቸው ሳይሆን ለሌላ ግለሰብ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ግለሰቡ ይዘውት የነበረው መንጃ ፈቃድ ሀሰተኛ ነው ከሚባል በቀር ተገቢ መንጃ ፈቃድ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም።

የማግለያ ድንጋጌው መሰረታዊ ዓላማ ተሽከርካሪው ተገቢውን ትምህርት እና ስልጠና ባልወሰደ እና ስልጣን ካለው አካል አግባብነት ባለው ሕግ እና ደንብ መሰረት ተገቢው መንጃ ፈቃድ ባልተሰጠው ግለሰብ ሲነዳ ለሚደርሰው ጉዳት የመድን ሰጪውን ኃላፊነት ለማስወገድ እንደሆነ የሚታወቅ በመሆኑ የተሽከርካሪው የመገልበጥ አደጋ የደረሰው አሽከርካሪው አግባብነት ባለው ሕግና ደንብ መሰረት በባለስልጣኑ ያልተሰጠውን ሀሰተኛ መንጃ ፈቃድ ይዞ ሲያሽከረክር በነበረበት ጊዜ መሆኑ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ በማግለያ ድንጋጌ መሰረት መድን ሰጪው በኃላፊነት የሚጠየቅበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም። በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች ላይ የተጠቀሱት የንግድ ሕግ ቁጥር 654፣664 እና 668 ድንጋጌዎችም በመድን ውሉ አንቀጽ 3 ላይ የተቀመጠውን የማግለያ ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚያስቀሩ አይደሉም። በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ የማግለያ ድንጋጌው የመንጃ ፈቃዱን ሕጋዊነት የማረጋገጥ ግዴታ የሚጥልብኝ አይደለም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል አይደለም።

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. ሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሽሬ እንዳስላሴ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 16952 በ25/03/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 63314 በ26/09/2006 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል።
2. ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን በአመልካቹ ላይ በጋራ ክስ ሊያቀርቡ የሚችሉበት ሥነ - ስርዓታዊ አግባብ የለም በማለት ወስነናል።
3. ንብረትነቱ የ1ኛ ተጠሪ በሆነው ተሽከርካሪ ላይ የመገልበጥ አደጋ የደረሰው ተገቢውን መንጃ ፈቃድ ባልያዘ ወይም ሀሰተኛ መንጃ ፈቃድ በያዘ ግለሰብ ሲሽከረከር በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ላቀረቡት ክስ በመድን ውሉ አንቀጽ 3 በተመለከተው የማግለያ ድንጋጌ መሰረት አመልካች ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል።

www.abyssinialaw.com

4. ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች መብታቸውን መጠየቅ የሚችሉት የተሽከርካሪው ባለንብረት ከሆኑት 1ኛ ተጠሪ ነው በማለት ወስነናል።
5. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ።
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሃ/ወ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 115763

ቀን 09/02/2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ክፍለጽዮን ማሞ

ጳውሎስ ኦርሲሾ

አመልካች፡- ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንሽ ኩባንያ አ.ማ ጌታቸው ገዳሙ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ትዕግስት ገ/እግዚአብሔር ነገረ ፈጅ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው አመልካች የስር ከሳሽ በመሆን በአሁን ተጠሪ (1ኛ ተከሳሽ) እና በዛጌ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃላ/የተ/የግል ማህበር (2ኛ ተከሳሽ) ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ችሎት በቀን 19/02/2006 ዓ/ም በመሰረተው ክስ ነው፡፡

2ኛ ተከሳሽ ልዩ ልዩ ተሽከርካሪዎችን በዋስትና በማስያዝ ከ1ኛው ተከሳሽ ብድር የወሰደ ሲሆን አመልካች ለተሽከርካሪዎቹ የመድን ሽፋን ሰጥቷል ክሱንም ሊመሠርት የቻለው በሰጠሁት የመድን ሽፋን መሠረት ያልተከፈለኝ ቀሪ የኦርቦን ክፍያ ስላለ ሁለቱም (የስር) ተከሳሾች በአንድነትና በነጠላ ባለ ዕዳ ናቸው በሚል ነው፡፡

2ኛ ተከሳሽ የወሰደውን የባንክ ዕዳ እንደውሉ አጠናቆ ሊከፍል ባለመቻሉ 1ኛው ተከሳሽ በመያዣ ውሉ መሠረት ንብረቶቹን ካስቆጠረ በኋላ በሐራጅ በመሸጥ በብድር የሰጠውን ገንዘብ ሰብስቧል ቀጥሎ ለአመልካች በላከው ማስታወሻ የመድን ውሉ እንዲቋረጥ አሳስቧል፡፡

2ኛ ተከሳሽ በመክሰሩ ምክንያት ከ1ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) ጋር የነበረው ውል በመቋረጡና የመድን ፖሊሲውም እንዲሰረዝ በመደረጉ አመልካች ገቢ ያላደረገው ብር 42,037.15 እንዲከፈለው በሁለቱ ተከሳሾች ላይ ክስ መስርቷል የክሱ አመሠራረት ተጠሪን 1ኛ ተከሳሽ በማድረግ ሲሆን

www.abyssinialaw.com

ይዘቱም በመድን ፖሊሲው ላይ ተጠሪ እና የስር 2ኛ ተከሳሽ እንደጣምራ መድን ገቢዎች ሆነው የተጻፉ አርቦኑንም እንደ 2ኛ ተከሳሽ በመሆን 1ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) ሲከፍል የነበረ ፖሊሲው እንዲታይለም ተጠሪ ሲፈቅድም ሲስማማ የነበረ የመድን ሽፋን የነበራቸው ተሽከርካሪዎች በመሸጥ ተጠሪ እዳውን የሰበሰበና በዚህም ተጠቃሚ የሆነ በመሆኑ 2ኛ ተከሳሽ መክሰሩን ተከትሎ ተጠሪ የማሪውን አርቦን ልከፍል አይገባም ማለቱ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

አመልካች በበኩሉ በሰጠው መልስ ከአመልካች ጋር ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ግንኙነት አለመመስረቱን አመልካች የመድን ውሉን የፈረመው ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር እንጂ ከተጠሪ (1ኛ ተከሳሽ) ጋር አለመሆኑን ተጠሪ የመድን ግዴታ ውል ፈጽሞ አለመግባቱን እንዲሁም የመድን ውሉ እንዲታደስ መስማማቱ የውሉ ተጠቃሚ በመሆኑ እንጂ ባለእዳ ጌዴታ ያለበት መሆኑን አያመለክትም ብሏል፡፡

2ኛ ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ሳይቀርብ በመቅረቱ ፍ/ቤቱ የአመልካች (ከሳሽ) እና ተጠሪ (1ኛ ተከሳሽ) ክርክሮችንና ማስረጃዎችን ከመረመረ በኋላ ጉዳዩን መርመሯል እንደመረመረውም 1ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) አርቦኑን ሲከፍል እንደነበረ በመድን ውሉ ላይም ሁለቱም ተከሳሾች መድን ገቢዎች ለመሆናቸው "እና " በሚል ቃል የተጠቀሱ መሆኑ መድን ውሉ እንዳይቋረጥ ሲከታተል ና እንዲታደስ ሲፈቅድ የነበረው 1ኛ ተከሳሽ  (ተጠሪ) በመሆኑ የሰጠውን ብድር ከሰበሰቡ በኋላ የተጠራቀመውን አረቦን አልከፍልም የሚልበት አግባብ ባለመኖሩ 1ኛው ተከሳሽ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር በአንድነትና በነጠላ ሃላፊነት አለባቸው ሲል ስር ፍ/ቤት ወስኗል፡፡ ፤

ተጠሪ የስር ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቅሬታውን አቅርቧል ተጠሪ ቅሬታውን ሲያቀርብ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተመሰረቱ የውል ግንኙነት ሳይኖር በአመልካችና በ2ኛው ተከሳሽ መካከል የመድን ውሉ ከተመሠረተ በኋላ በተደረጉ በአመልካችና በተበዳሪው በ2ኛ ተከሳሽ መካከል ከነበሩ የብድር ውል ግዴታዎች አፈፃፀም ላይ ተመስርቶ አመልካችን እንደመድን ገቢ በመቁጠር የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊሻር ይገባዋል ብሏል፡፡ አመልካችም በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸውን የክርክር ነጥቦች አጠናክሮ አቅርቧል፡፡

ጉዳዩን የያዘው ከፍተኛ ፍ/ቤት በንግድ ህግ ቁ. 675 (1) ላይ በመመስረት መልስ ሰጭ የአሁን አመልካች ያቀረባቸውን መከራከሪያዎች ከመዘነ በኋላ በይግባኝ ባይ (ተጠሪ) እና በመልስ ሰጭ መካከል የመድን ሰጭና መድን ተቀባይ ውል አለ ለማለት የማያስችሉ በመሆኑ አረቦኑን መክፈል ያለበት የስር 2ኛ ተከሳሽ ብቻ ነው በማለት ወስኗል ፡፡

ፍ/ቤቱ በተጨማሪም የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ በአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መካከል በነበረው ክርክር በሰበር መዝገብ ቁ. 43886 በቀን 22

www.abyssinialaw.com

/4/2002 ዓ/ም የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ የይግባኝ ባይን (የአሁን ተጠሪን) ክርክር የሚደግፍ በመሆኑ የይግባኝ ባይ (አመልካች) ማመልከቻን አልተቀበልነውም ሲል ወስኗል፡፡

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበው በከፍተኛው ፍ/ቤት ተፈጸመ የተባለው የህግ ስህተት እንዲታረም ነው፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው ተጠሪ ተሽከርክሪዎችን ተረክቦ ከ5 ዓመት በላይ ካስተዳደረና ዋስትናው እንዲታደስ እየጠየቀ አርቦን በየአመቱ እየከፈለ ከቆየ በኃላ ንብረቶቹን ሽጦ ከብር 27 ሚሊዮን በላይ ከሰበሰበ በኂላ ውሉን በማቋረጥ አርቦንን አልከፍልም ያለበትን ክርክር ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቀብሎ መወሰኑ አግባብ አይደለም ይታረምልኝ ብሏል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የስር ክርክሩን በማጠናከር የከፍተኛው ፍ/ቤት አስገዳጅነት ያለውን የሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 43886 መሠረት ያደረገ ውሳኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው ሲል መልስ ሰጥቷል፡፡ እኛም መዝገቡን መርምረናል እንደመረመርነውም የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔውን መሠረት ያደረገው በውል ፖሊሲው ላይ ተጠሪና 2ኛ ተከሳሽ "እና" በሚል በመጣመራቸው ሲሆን ተጠሪ ከውል የመነጨ ግዴታ ያለበት ለመሆኑ ግን አግባብ ያለውን ህግ ወይም የሰበር ውሳኔ ጠቅሶ አላብራራም፡፡

በሌላ በኩል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከዚህ ቀደም ሰበር ችሎቱ በተመሳሳይ ጉዳይ በመዝገብ ቁ. 43886 የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ በመጥቀስ እና የንግድ ህግ ቁጥሮች 654 እና 657 -659 ን በአግባቡ በመተርጎም የሰጠው ውሳኔ ምንም ስህተት አልተገኘበትም፡፡ በዚህ መሠረት የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 147374 በታህሳስ 13 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠውን በጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 110005 በሚያዝያ 14 ቀን 2007 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348 (1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የስር 2ኛ ተከሳሽ ከተጠሪ ጋር በገባው የመድን ውል መሠረት ያልከፈለውን የአርቦን ክፍያና ወለድ ተጠሪ በአንድነትም ሆነ በነጠላ የመክፈል አላፊነት የለበትም ፡፡
3. የስር 2ኛ ተከሳሽ በገባው የመድን ውል መሰረት የተጠየቀውን አርቦን ክፍያና ወለድ ሙሉ በሙሉ የመክፈል አላፊነት አላበት
4. ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ይጻፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

# ወንጀል

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 88542

ሐምሌ 17 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ቢሆነኝ ደምሌ - ጉዳይ ተከታታይ መንበሩ ተስፋው - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የት/ብ/ክ/መንግስት ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ንግድ ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ሥራን በህገ ወጥ መንገድ ማከናወን ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው በት/ብ/ክ/መንግስት አላማጣ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ አመልካች ላይ ባቀረበው የወንጀል ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች ንግድ ፈቃድ ሳይኖረው በ17/11/2004 ዓ.ም ከጥዋቱ 3፡00 ሰዓት አካባቢ በአላማጣ ከተማ 02 ቀበሌ ልዩ ቦታው ወደ ዋጃ መውጫ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ አንድ ኩንታል ስኳር በመኪና ላይ ጭኖ ወደ ቆቦ ወረዳ ሲጓዝ ስለተያዘ አዋጅ ቁ 686/2002 አንቀፅ 60/1/ ተላልፎ በፈፀመው ሕጋዊ ያልሆነ ንግድ ሥራ በማካሄድ ተከሷል የሚል ሲሆን ተከሳሹም ቀርቦ ስኳሩን ወደ ቆቦ ከተማ ወስዶ ለመሸጥ በመኪና እየተጓዘ ሳለ መያዙን ጠቅሶ ንግድ ፈቃድ ሳይኖረው ይሄንን የንግድ ሥራ መፈፀሙ ጥፋት መሆኑን በማመን የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው ወረዳ ፍ/ቤትም ተከሳሹ የሰጠውን የእምነት ክህደት መነሻ በማድረግ ተከሳሹን በተከሰሰበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ካደረገ በኃላ በሁለት ዓመት ፅኑ እስራትና ብር 150,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) ገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወሙ ቅሬታውን ለዞኑ ከፍ/ፍ/ቤትና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃውን ጠብቆ ቢያቀርብም በሁለቱም ደረጃ ተቀባይነት አላገኘም አሁን የቀረበው የሰበር

www.abyssinialaw.com

አቤቱታም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም አንዱን ኩንታል ስኳር ገዝቼ ወደ ቆቦ ከተማ ስንጓዝ የነበረው ለንግድ ወይም ለሽያጭ ሳይሆን ወላጅ አባቴና ሴት አያቴ በሞት በመለየታቸው ምክንያት ለሃዘን ለሚመጡ ሰዎች ሻይና ቡና ማስተናገጃ ሆኖ ሳለ ጥፋተኛ መባሌ አላግባብ መሆኑን ለንግድ ነው ቢባል እንኳ የቀረበብኝን ክስ ሙሉ በሙሉ በማመን የእምነት ክህደት ቃልን መስጠቴ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኤን የወንጀል ሪከርድ የሌለብኝ መሆኔ የግል ሁኔታዬና የገቢ ምንጭ በወንጀል ህግ ቁ 88/2/፤ 90/2/ እና እንዲሁም በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በአግባቡ ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ ቅጣቱ መጣል ሲገባ ያላግባብ በሁለት ዓመት ፀኑ እስራትና 150,000 ብር የገንዘብ መቀጮ እንድቀጣ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው ተሻሽሎ የጥፋተኝነት ደረጃዬን ባገናዘበና የገንዘብ መቀጮውንም በተመለከተ የመክፈል አቅሜን ባገናዘበ መልኩ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

አቤቱታውም ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል መባሉ ተጠሪም ቀርቦ የበኩሉን መልስ የሰጠበት ሲሆን አመልካችም የመልስ መልሱን ሰጥቶበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር አቤቱታ በቀረበበት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል::

እንደመረመርነውም የጥፋተኝነት ውሳኔን በተመለከተ አመልካቹ የቀረበበትን የወንጀል ክስ መፈፀሙን በዝርዝርና ሙሉ በሙሉ በማመን የእምነት ክደት ቃሉን መስጠቱና ፍ/ቤቱም ይህንኑ የአመልካችን የእምነት ቃል መነሻ በማድረግ የጥፋተኝነት ውሣኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.134 /1/ ድንጋጌ አንፃር መስጠቱን መገንዘብ ተችሏል ሆኖም ግን አንድ ሰው በተሰጠበት የጥፋተኝነት የቅጣት ውሳኔ ላይ ደረጃውን ጠብቆ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ይግባኝ ለማለት የሚችል ቢሆንም የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠው በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ134/1/ ስር እንደተመለከተው የተከሳሹን የእምነት ቃል መነሻ በማድረግ ከሆነ በቅጣቱ ላይ ካልሆነ በጥፋተኝነቱ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ እንደማይቻል በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 185/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በአንድ በኩል አመልካች ወንጀሉን በህጉ አግባብ ሙሉ በሙሉ መፈፀሙን አምኖ የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቶና የጥፋተኝነት ውሳኔም ይህንኑ መነሻ በማድርግ ተሰጥቶ እያለ በሌላ በኩል ደግሞ በበታች ፍ/ቤት ከሰጠው እምነት ቃል በተቃራኒ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ እርስ በራሱ የሚጋጭ በመሆኑ ተቀባይት ያለው አይደለም ብለናል፡፡

የቅጣት ውሳኔን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የህጉ ድንጋጌ ከብር 150,000-300,000 የገንዘብ መቀጮና እንዲሁም ከ7-15 ዓመት ፅኑ እስራት እንደሚያስቀጣ የደነገገ ሲሆን

www.abyssinialaw.com

ከዚህ አኳያ የእስራት ቅጣቱን በተመለከተ የበታች ፍ/ቤቶች የወንጀሉን ክብደት የአመልካቹን የግል ሁኔታና ሌሎች የቅጣት ማቅለያዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በድንጋጌው ስር ከተመለከተው መነሻ የእስራት ቅጣት (7 ዓመት ፅኑ እስራት) በመውረድ አመልካቹ በሁለት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ የተወሰነበት ሲሆን ይህ ደግሞ ሊነቀፍ የሚችልበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታም አልተቀበልነውም፡፡

በሌላ በኩል የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተ በወ/ህ/ቁ 90/2/ ስር እንደተመለከተው ፍ/ቤቶች ይህንን የገንዘብ መቀጮ ሲወስኑ የወንጀሉ ክብደት የአጥፊውን አደገኛነት መጠን የሀብቱን ሁኔታ የገቢ ምንጩን ዕድሜውንና የጤንነቱን ሁኔታ ከቤተሰብ አስተዳዳሪነት አኳያ ያለንበትን ሸክም የሙያ ስራውንና ከስራው የሚያገኘውን ገቢ መጠን ከግምትና ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ ሁኔታ መቀጮው ሊጣል እንደሚገባ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ በተያዘው ጉዳይ በአመልካች ላይ የተጣለው የብር 150,000 የገንዘብ መቀጮ እነዚህ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የህጉን መስፈርቶች ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ አግባብ መሆን አለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ አያሳይም የመቀጮ ቅጣቱ እነዚህ መስፈርቶችን ባላገናዘበ ሁኔታ የሚጣል ሆኖ ከተገኘም የወንጀል ህጉ ካሰበው ዓላማ ውጭም በመውጣት አጥፊውንና ሌሎቹን ከማስተማር እና ከማስጠንቀቅ አልፎ አላስፈላጊ ጫናና ችግር በተከሳሹና በቤተሰቡ ላይ እንዳይፈጥር ጭምር ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል በተለይም አመልካቹ አርሶ አደርና የቤተሰብ አስተዳዳሪ ከመሆኑ አኳያ የሀብቱ ሁኔታ የገቢ ምንጩ አደገኛነቱና የወንጀሉ ክብደትም በተገቢ ሁኔታ ተመዝኖ መታየት ከነበረበት ባጠቃላይ በህጉ እስካልተከለከለ ድረስ በህጉ ከተመለከተው መነሻ መቀጮውም በመውረድ (አጠቃላይ የገንዘብ መቀጮው መነሻ እንደተጠበቀ ሆኖ) መቀጮው በወንጀል ህጉ አግባብና በተለይም በወ/ህ/ቁ88/2/ ፤ 90/2/ እና በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በወጣው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ 1/2002 አኳያ መጣል ሲገባ በደፈናው አመልካቹ በብር 150,000 እንዲቀጣ መወሰኑና ይኼውም በዞኑ ከፍ/ፍ/ቤት እና ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መታረም ሲገባ መፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፤

## ው ሳ ኔ

1. በአላማጣ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት መ.ቁ 03421 በ15/2/2005 ዓ.ም ተወስኖ በከፍተኛ ፍ/ቤቱና ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የፀናው የጥፋተኝነትና የእስራት ቅጣቱ ውሳኔ ክፍል በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ.195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፤
2. ሆኖም ግን አመልካች በብር 150,000 (መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) ገንዘብ መቀጮ ይቀጣ በማለት የተሰጠው የቅጣቱ ውሳኔ ክፍል ብቻ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 195/2/ /ለ/ /2/ መሰረት ተሽሯል፤

www.abyssinialaw.com

3. የአላማጣ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የራሱን መዝገብ በማንቀሳቀስና ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኂላ ከዚህ በላይ በፍርዱ ሐተታ ክፍል በተገለፀው አኳኂን የገንዘብ መቀጮውን ከወንጀል ህጉ ቁ 90/2/፤ 88 /2/ እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው ሌሎች ድንጋጌዎችና እንዲሁም በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በወጣው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ 1/2002 አኳያ የገንዘብ ቅጣቱን በማገናዘብ ከመረመረ በኃላ ተገቢውን አስልቶ እንዲወስን ዘንድ ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፤

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 116405

መጋቢት 2 ቀን 2008 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

**አመልካች**፡- የኦሮሚያ የስነ ምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ህግ - ጉዳኔ ፈቃዱ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ቴዎድሮስ አብርሃ ቀለቲ - ጠበቃ አማላዩ ፀጋዬ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የወንጀል ክስ ማሻሻልን የሚመለከት ነው፡፡ በስር 1ኛ ተከሳሽ ደርበው ሻንቆ እና 2ኛ ተከሳሽ በሆነው የአሁን ተጠሪ ላይ አመልካች የመሰረተውን ክስ ለማሻሻል ያቀረበው አቤቱታ ጉዳዩን ሲመለከት በነበረው የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 11311 በ23/4/2007 በዋለው ችሎት በትእዛዝ ውድቅ የተደረገ ሲሆን ትእዛዝ ላይ አመልካች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ/192830 በ3/6/2007 በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ትእዛዝ በመሻር ክሱ እንዲሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ ክስ እንዲሻሻል መፈቀዱን በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርበው ችሎቱ በመ/ቁ/ 203090 በ1/10/2007 የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የክስ ማሻሻል ጥያቄ የቀረበው መዝገቡ ለምርመራ ከተቀጠረ በኋላ በመሆኑ፣ በዚህ ሁኔታ ክሱ ይሻሻል ቢባል ክርክሩ እንደ አዲስ የሚጀምር በመሆኑ፣ይህ ደግሞ በኢ.ፌዴሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 20/1/ የተጠበቀውን አፋጣኝ ውሳኔ የማግኘት መብት የሚፃረር በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ሽሮ የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ትእዛዝ አጽንቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ አመልካች ምክንያቶችን በመዘርዘር በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ላሻሽል ጥያቄ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተቀባይነት ማግኘቱ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 20 /1/ የሚጥስ ነው ተብሎ ውድቅ የመደረጉን አግባብ ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከላይ ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ቅሬታ ያስነሳውን ውሳኔ እና የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር ችሎት ከተያዘው ጭብጥ እና ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች መስርቶት በነበረው ክስ የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ድርጅት የኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ኃላፊ የነበረው 1ኛ ተከሳሽ ከመንግስት የግዥ ወይም የጨረታ አወጣጥ ደንብና ከድርጅቱ መመሪያ ውጭ ስልጣኑን ያላግባብ በመገልገል ንብረትነቱ የመንግስት የሆነ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-07074 ገልባጭ መኪና ያለምንም ጨረታና የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ለአሁን ተጠሪ በጥገና ሰበብ በ21/07/2007 ዓ/ም እንዲሰጥ በማድረግ መንግስት ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ እንዲያጣ በማድረጋቸው ክስ ቀርቦባቸው የዓቃቤ ህግ ማስረጃዎች ተሰምተው እንዲከላከሉ ተፈቅዶላቸው መከላከያ ተሰምቶ መዝገቡ ለምርመራ ተቀጥሮ ነበር፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነው መኪና ለሌላ 3ኛ ወገን የተሸጠ መሆኑን፣ የገዛው ሰውም የህዝብ ማመላለሻ አውቶብስ የሰሌዳ ቁጥር በዚህ መኪና ላይ በመለጠፍ ከአዲስ አበባ መንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ሰራተኞች ጋር በመመሳጠር በህገ ወጥ መንገድ የሻንሲ፣ የሞተር ቁጥርና ሌሎች መረጃዎችን ከላዩ በመፋቅ የህዝብ ማመላለሻ አውቶብስ በማስመሰል ከትራንስፖርት ባለስልጣን እውቅና ሌሎች መረጃዎችን ከላዩ በመፋቅ የህዝብ ማመላለሻ አውቶብስ በማስመሰል ከትራንስፖርት ባለስልጣን እውቅና ደንብና መመሪያ ውጭ በላዩ ላይ እንዲመታ በማድረግ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ/ በመውሰድ በሽያጭ ለሌላ ግለሰብ አስተላልፎ መኪናው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በመስራት ላይ እንዳለ ከ6 ዓመታት ፍለጋ በኂላ ያላግባብ በተጠሪ ተወስዶ የተሰወረ መኪና እና በወንጀሉ ውስጥ ተካፋይ የሆኑ ሰዎች የተያዙና የስር ተከሳሾች የሙስና ወንጀል ድርጊት አፈፃጸምና የተገኘው ጥቅም በአግባቡ በግልጽ በመታወቁ፣ እንዲሁም በወንጀሉ ተካፋይ የሆኑ ሰዎች ላይ እንደተሳትፏቸው በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 118 እና 119/1/ መሰረት ክስ አሻሽለን ብናቀርብ ፍርድ ቤቱ ትክክለኛ እና ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት ይረዳዋል በማለት ክሱን አሻሽለው ለማቅረብ እንዲፈቀድ ጠይቀዋል፡፡

የተጠሪ ጠበቃ በበኩላቸው ጉዳዩ 1 አመት ከ6 ወር የቆየ መሆኑን፣ መዝገቡም ክርክሩ ተጠናቆ ለምርመራ መቀጠሩን ፣ ምንአልባት ዓቃቤ ህግ ሌሎች ሰዎች ላይ ክስ መመስረት ከፈለገ

www.abyssinialaw.com

የሚገድበው ነገር አለመኖሩንና የተጠቀሰው ምክንያት ክሱን አሻሽሎ ለማቅረብ የህግ ድጋፍ ያለው አለመሆኑን በማንሳት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በየደረጃው የተመለከቱት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ከፍ ሲል የተመለከቱትን ውሳኔዎች ሰጥተዋል፡፡ በተለይ የክልሉ ሰበር ችሎት ትክክለኛ እና ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት ሲባል ክሱ ሊሻሻል ይችላል በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ቢቀበለውም የክሱ መሻሻል አስቀድሞ በእስር ሆነው ጉዳዩን ሲከታተሉ የነበሩ ተከሳሾች አፋጣኝ ውሳኔ የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብት የሚያጣብብ በመሆኑ የክስ ላሻሽል ጥያቄው ተቀባይነት እንደሌለው ወስኗል፡፡

በመሰረቱ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ክሱ እንዲሻሻል ፍርድ ቤቱ ሊፈቅድ የሚችል ሲሆን በዚህ መልኩ ክሱ እንዲሻሻል ፈቃድ ሲሰጥ ወይም የክሱ መሻሻል ሲከለከል ፍርድ ቤቱ ተቀባይነት ያለው ህጋዊ ምክንያት እንዲሰጥ ይጠበቃል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የክልሉ ሰበር ችሎት ክሱ እንዲሻሻል በመፈቀዱ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው ጉዳዩ ለምርመራ ያደረ በመሆኑ እና ክሱ ተሻሽሎ እንደ አዲስ ቢጀመር አፋጣኝ ውሳኔ የማግኘት መብትን ይጋፋል በማለት ነው፡፡ ነገር ግን ከላይ እንደተገለጸው የክሱ መሻሻል ፍርድ ቤቱ ትክክለኛ እና ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለው መሆኑ ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ፤ ጉዳዩን የሚመለከተው ፍርድ ቤት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ክሱ እንዲሻሻል መፍቀድ እንደሚቻል በህጉ የተመለከተ በመሆኑ፤ እንዲሁም የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብት የሚረጋገጠው በህግ የተዘረጋን ስነ ስርዓት ተከትሎ ጉዳዩን ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ በመምራት እንጂ በህግ የተዘረጋን ስነ-ስርዓት ወደጎን በማለት ባለመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት የክሱ መሻሻል ለትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ ተገቢ መሆኑን ተቀብሎ ነገር ግን ክርክሩ የደረሰበትን ደረጃ ብቻ ግምት ውስጥ በማስገባትና አፋጣኝ ፍትህ የማግኘት መብትን ህጋዊ አፈፃጸም ባልተከተለ መልኩ ክሱ እንዲሻሻል ሊፈቀድ አይገባም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ እና ያሳለፈው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የተፋጠነ ፍትህ የሚገኘው ጉዳዩ የወንጀል ክርክር በሚመራበት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት ድንጋጌዎች አግባብ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ በመምራት በመሆኑ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 118 እና 119 እንዲሁም ተያያዥ ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት ባለው ምክንያት ክስ እንዲሻሻል መፈቀዱ የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብትን የሚያጣብብ ነው የሚባል አይሆንም ብለናል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ችሎት ክሱ እንዲሻሻል ሊፈቀድ አይገባም በማለት የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሩ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ተከታዩም ተወስኗል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ልዩ ዞን ፍንፍኔ ዙሪያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 11311 በ23/4/2007 በዋለው ችሎት ያሳለፈው ትእዛዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ሰበር ችሎት በመ/ቁ/ 203090 በ1/10/2007 የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ/ 195/2/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 192830 በ3/6/2007 ያሳለፈው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 11311 እየተካሄደ የነበረው ክርክር ታግዶ እንዲቆይ በዚህ ፍርድ ቤት ጥቅምት 15/2008 ዓ/ም የተሰጠው ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
4. አመልካች የተሻሻለውን ክስ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያቀርብ፤ የስር ፍርድ ቤትም የተሸሻለውን ክስ ተቀብሎ አከራክሮ እንዲወሰን ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.113143

መጋቢት 30 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- የሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትሕ ቢሮ ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ሕሊና ኃይሌ
2. አቶ ፋሲካ አፅምሮ } የቀረበ የለም
3. አቶ መላኩ ደምሴ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው የሐረሪ ክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሶስቱም ተጠሪዎች ላይ በወንጀል ሕግ ቁጥር 555 (ሐ) ስር በመዝገብ ቁጥር 40031 እንደቀደም ተከተሉ በ24/11/2006 ዓ.ም. እና በ29/11/2006 ዓ.ም. የሰጠባቸውን የጥፋተኛነት እና የእስራት ቅጣት ውሳኔ በከፊል ሽሮ እና በከፊል ደግሞ አሻሽሎ 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን በነጻ በማሰናበት እና 2ኛ ተጠሪን በተመለከተ ደግሞ ድንጋጌውን ወደ 557 (1) (ሐ) ለውጦ በብር 2,000 እንዲቀጡ በማለት የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12394 በ13/05/2007 ዓ.ም የሰጠው እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03061 በ24/08/2007 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

አመልካች በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪዎቹ ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡- ተከሳሾቹ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) (ሀ) እና 555 ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በሰው አካል ላይ ጉዳት ለማድረስ አስበው በ19/03/2006 ዓ.ም. ከቀኑ 11፡00 ሰዓት ላይ በሐረር ከተማ ቀበሌ 10 ክልል ልዩ ስሙ ሥላሴ ሐይቴክ ትምህርት ቤት አካባቢ ገ/መስቀል ገ/ሥላሴ የተባለውን የግል ተበዳይ ተባብረው ፊቱን እና አፍንጫውን በቦክስ በመምታት፣መላ ሰውነቱን በመደብደብ፣በአፍንጫው ላይ የአጥንት ስብራት ጉዳት፣በግራና በቀኝ ፊቱ ላይ የእብጠት፣በቀኝ አይኑ እና በቀኝ ጆሮው መካከል እብጠትና የመላላጥ ጉዳት እንዲደርስ በማድረጋቸው በሰው አካል ላይ ከባድ ጉዳት የማድረስ ወንጀል አድርገዋል የሚል ሲሆን ተጠሪዎቹ ያቀረቡት መቃወሚያ ውድቅ ተደርጎ የእምነት ክደት ቃል ሲጠየቁ ወንጀሉን አላደረግንም በማለታቸው አመልካች እንደክሱ ያስረዱልኛል በማለት ከቆጠራቸው ሰባት ምስክሮች መካከል የግል ተበዳይን ጨምሮ ስድስቱን አቅርቦ ያሰማ መሆኑን እና አንዱ ምስክር በአድራሻቸው አልተገኙም በመባሉ በምርመራ ጊዜ ለፖሊስ የሰጡት ምስክርነት ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ የተደረገ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ፍርድ ቤቱ የምስክሮቹን ቃል እና አመልካቹ በሰነድ ማስረጃነት ያቀረበውን የሀኪም ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በተጠሪዎቹ ላይ አመልካች በክሱ መሰረት ያስረዳባቸው መሆኑን ገልጾ መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎቹ ከቆጠሯቸው 11 የመከላከያ ምስክሮች መካከል እራሳቸውን ጨምሮ በድምሩ ሰባት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡

ከዚህ በኃላ ፍርድ ቤቱ በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪዎቹ ባሰሟቸው የመከላከያ ምስክሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰረተባቸውን ፍሬ ነገር ለማስተባበል አልቻሉም በማለት በሶስቱም ተጠሪዎች ላይ በክሱ በተጠቀሰባቸው ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ በማስተላለፍ ግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየታቸውን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት እንዲያቀርቡ አድርጓል፡፡ በመቀጠልም በአመልካቹ በኩል የቀረበ የማክበጃ ምክንያት አለመኖሩን፣በተጠሪዎቹ በኩል የቀረቡት የማቅለያ ምክንያቶች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን፣ወንጀሉ ደረጃ የወጣለትና የሚመደበውም በደረጃ አንድ መሆኑን እና በድንጋጌው ስር በደረጃ አንድ ለተመደበ ወንጀል በመመሪያው የተመለከተው ፍቅድ ስልጣን በአባሪ አንድ በእርከን 16 የተመለከተው መሆኑን ገልጾ በመመሪያው በእርከን 16 በተመለከተው ፍቅድ ስልጣን መሰረት 1ኛ ተጠሪ በሶስት ዓመት ከአራት ወር ጽኑ እስራት፣2ኛ ተጠሪ በሶስት ዓመት ከሁለት ወር ጽኑ እስራት፣ሶስተኛ ተጠሪ በሶስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ በመወሰን እና ተጠሪዎቹ ያቀረቡትን የቅጣት ገደብ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በከፊል ለመሻር እና በከፊል ደግሞ ለማሻሻል የሰጠው ምክንያት የግራ ቀኙ ማስረጃ በማገናዘብ ሲመረመር በግል

www.abyssinialaw.com

ተበዳይ ላይ ለደረሰው ጉዳት መንስኤ የሆነው እራሱ የግል ተበዳይ መሆኑን እና ጉዳቱም የደረሰበት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ተያይዘው በኮብልስቶን ድንጋይ ላይ በመውደቃቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔውን የሰጠው የግራ ቀኙን ማስረጃ በአግባቡ መዝኖ ነው ለማለት አልተቻለም የሚል መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያመለክታል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተመርመሮ የአመልካች የዓይን ምስክሮች ቃል በሁለቱ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውድቅ የተደረገበትን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመከለተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪዎቹ ተጠይቀው ወንጀሉን አላደረግንም በማለታቸው አመልካች አቅርቦ ካሰማቸው ስድስት ምስክሮች መካከል፡-

- የግል ተበዳይ የሆኑት 1ኛ ምስክር በክሱ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት በመንገድ ላይ በመሄድ ላይ እያለ 2ኛ ተጠሪ የግል ተበዳይን “ይህም የአጽብሃ ወንድም ነው” ብሎ አንቆ ከያዘው በኃላ ትፈለጋለህ በማለት በቦክስ ከፊቱ ላይ እንደመታው፣ 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በአካባቢው ከነበረ መኪና ውስጥ ወርደው ወደ ግል ተበዳይ በማምራት 1ኛ ተጠሪ በእጁ ይዞት በነበረው ጠፍጣፋ ነገር አፍንጫው ላይ ሲመታው 3ኛ ተጠሪ ደግሞ በጠረባ መቶት ከመሬት ላይ እንደጣለው እና በወደቀበትም ሶስቱም ተጠሪዎች እየረገጡ እንደደበደቡት፣በደረሰበት ድብደባ ምክንያትም የመስማት ችግር እንዳጋጠመው እና በአፍንጫው ስብራት እና ቁስል ምክንያት ማሽተት እንደሚቸግረው በመግለጽ  ምስክርነት መስጠቱን፤
- 3ኛ እና 4ኛ ምስክሮች በአካባቢው ከሚገኝ ግቢ ውስጥ የአናጺነት ስራ በመስራት ላይ እያሉ “ገደለው” የሚል ጩኸት ሰምተው ሲወጡ ተጠሪዎቹ የግል ተበዳይን አሸባሪ ነው እያሉ ሲናገሩ እንደሰሙ፣ተበዳይ ደምቶ እንደነበረ እና ተጠሪዎቹ ቀበቶውን አውልቀው ሲፈትሹት እንደነበረ እና ጠቡን ግን ከጅምሩ እንዳላዩ በመግለጽ ምስክርነት መስጠታቸውን፤
- 5ኛ ምስክር በቦታው በደረሰበት ሰዓት ተበዳይ አፍንጫው ላይ ደምቶ ማየቱን፣የግል ተበዳይ ሽጉጥ ጥሏል በማለት 1ኛ ተጠሪ ቆርቆሮ ስር ሲፈልግ እንደነበረ እና 3ኛ ተጠሪን ከቦታው እንዳላየው በመግለጽ ምስክርነት መስጠቱን፤
- 6ኛ ምስክር በቦታው በደረሰበት ሰዓት ተበዳይን 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እጁን ግራና ቀን ይዘው ማየቱን፣የተበዳይ ፊት ደም በደም ሆኖ እንደነበረ፣ምስክሩ ሲጠይቃቸው አሸባሪ ነው በማለት እንደመለሱለት፣ሽጉጥ ይዟል በማለት ሲፈትሹት እንደነበረ፣ምስክሩ የአካባቢው

www.abyssinialaw.com

ሰዎች ውሃ እንዲያመጡ አድርጎ ፊቱን ሲያጥቡለት 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ያዙኝ ልቀቁኝ ይል እንደነበረ በመግለጽ ምስክርነት መስጠቱን፤

- የግል ተበዳይ ወንድም መሆኑን የገለጸው 7ኛ ምስክር ከ1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር የቆየ ቂም እንደነበረው፣በዚሁ ዕለት ከምሽቱ 12፡30 ላይ ሁለት የፖሊስ አባላትን ይዘው በመምጣት ምስክሩን ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንደወሰዱት፣እዚያ እያለ የግል ተበዳይ አፉና አፍንጫው ደምቶ እንዳየውና ተጠሪዎቹ የደበደቡት መሆኑን እንደነገረው በመግለጽ ምስክርነት መስጠቱን፤በመግለጽ የመሰከሩ መሆኑን እና የሀኪም ማስረጃውም በግል ተበዳይ የግራ እና የቀኝ ፊት ላይ እብጠትና የሰንበር ምልክት መታየቱን፣በአፍንጫው ላይ እብጠት፣በቀኝ አይኑና በቀኝ ጆሮው መካከል እብጠትና የመላላጥ ምልክት መታየቱን እና በተደረገለት የራጅ ምርመራም የአፍንጫ አጥንት ስብራት መታየቱን የሚያረጋግጥ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ሶስቱን ተጠሪዎች ጨምሮ በተጠሪዎቹ በኩል የተሰሙት ሰባት የመከላከያ ምስክሮች አመሰካከር ተጠቃሎ ሲታይ በዕለቱ የግል ተበዳይ ሽጉጥ ይዞ ማንነቱ ከማይታወቅ ሰው ጋር በመሆን በ2ኛ ተጠሪ ላይ ጸብ ማንሳታቸውን፣በዚህ ጸብም የግል ተበዳይና 2ኛ ተጠሪ ተያይዘው ከኮብልስቶን ድንጋይ ላይ መውደቃቸውን፣በግል ተበዳይ ላይ ጉዳቱ የደረሰውም በኮብልስቶን ድንጋይ ላይ በመውደቁ መሆኑን፣1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በቦታው የነበሩ ቢሆንም በግል ተበዳይ ላይ የፈጸሙት ነገር አለመኖሩን የሚያመለክት ነው፡፡ተጠሪዎቹ በጠበቃቸው አማካይነት በሰጡት የሰበር መልስ ላይ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የግራ ቀኙን ማስረጃ የመመዘን ጉዳይን የሚመለከት እንጂ የመሰረታዊ የሕግ ስህተት ጥያቄን የሚያስነሳ ባለመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀት 10 ድንጋጌ አንጻር ሰበር ችሎቱ ጉዳዩን የመመርመር ስልጣን የለውም በማለት መከራከራቸውን ተገንዝበናል፡፡ እንደተባለው የዚህ ሰበር ችሎት ስልጣን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ መርምሮ በማረም የተገደበ በመሆኑ በሕግ ስልጣን የተሰጣቸው የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገርን በማጣራት እና ማስረጃን በመመዘን ረገድ የደረሱበትን ድምዳሜ አግባብነት የመመርመር እና የማቃናት ስልጣን የለውም፡፡ይህ ማለት ግን የማስረጃ ምዘናው በሕግ ተቀባይነት ያላቸውን መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆዎች በጣሰ መልኩ በተከናወነ ጊዜ ጭምር ጉዳዩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ጥያቄን አያስነሳም ወደሚል ድምዳሜ ለማምራት የሚያስችል አይደለም፡፡በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ እና በውሳኔው ላይ የቀረበው የሰበር አቤቱታ የማስረጃ ምዘና ጉዳይን የሚመለከት እንጂ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ጥያቄን የሚያስነሳ ስላልሆነ ሰበር ችሎቱ አቤቱታውን የማስተናገድ ስልጣን የለውም በማለት ተጠሪዎቹ ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

www.abyssinialaw.com

- በመሰረቱ የወንጀል ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከት ፍርድ ቤት ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ የማስረጃውን አጭር መግለጫ፣ማስረጃውን የተቀበለበትን እና ያልተቀበለበትን ምክንያቶች በፍርዱ ላይ ማስፈር እንደሚገባው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ በቁጥር 149 (1) ስር ተመልክቷል፡፡በሌላ በኩል የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ የማጽናት፣የማሻሻል ወይም የመሻር ስልጣን እንዳለው በዚሁ ሕግ ቁጥር 195 ስር የተደነገገ ቢሆንም በተለይ ውሳኔውን የሚሽረው ከሆነ እና የሚሽረውም በማስረጃ ምዘና ምክንያት ከሆነ በጉዳዩ ከቀረበው እያንዳንዱ ማስረጃ አንፃር በስር ፍርድ ቤት የተከናወነው የማስረጃ ምዘና ተቀባይነት የለውም የሚልበትን ምክንያት እና በስር ፍርድ ቤት የቀረበውን እያንዳንዱን ማስረጃ የተቀበለበትን  እና ያልተቀበለበትን ምክንያቶች በፍርዱ ላይ ማስፈር የሚጠበቅበት በመሆኑ የማስረጃ ምዘናን አስመልክቶ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 149 (1) ስር የተመለከተው መስፈርት ተፈጻሚነት የሚኖረው ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጭምር መሆኑን ከሁለቱ ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ አያዳግትም፡፡በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎቹ ጸብ በማንሳት የደበደቡት እና ጉዳት ያደረሱበት መሆኑን የግል ተበዳይ የሆነው ግለሰብ ቀርቦ ምስክርነቱን ሰጥቷል፡፡የግል ተበዳይ ሽጉጥ ይዞ እንደነበረ በተጠሪዎቹ መከላከያ የተነገረ ቢሆንም ይህ የተባለው ሽጉጥ አልተያዘም፡፡ድርጊቱ የተፈጸመው ቀን ላይ በመሆኑ የግል ተበዳይ ሽጉጥ ይዞ ነበር የሚሉ ከሆነ ተጠሪዎቹ የግል ተበዳይን ከደበደቡት በኃላ ወደ ፖሊስ ጽ/ቤት እንደወሰዱት ሁሉ የግል ተበዳይ ይዞት ነበር የተባለውን ሽጉጥ ወይም የግል ተበዳይ ሽጉጡን አቀብሎታል የተባለውን እና ማንነቱ አልታወቀም የተባለውን ግለሰብ ጭምር ይዘው ለፖሊስ ማድረስ ያልቻሉበት ምክንያት ስለመኖሩ በመከላከያ ምስክሮች የተገለጸ ነገር የለም፡፡ይህም የግል ተበዳይ ሽጉጥ ይዞ እንደነበረ እና ጠብ ቀስቃሽም እንደነበረ በማስመሰል ተጠሪዎቹ እንደዋነኛ የመከላከያ ጭብጥ አድርገው በመከላከያ ምስክሮቻቸው ያስነገሩት ፍሬ ነገር የሌለ እና በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን በግልጽ መገንዘብ የሚያስችል ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪዎቹ የአመልካችን ማስረጃ አስተባብለዋል ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰውም ይህንን በማስረጃ ያልተረጋገጠ ፍሬ ነገር እንደዋነኛ የመከላከያ ማስረጃ በመውሰድ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተከተለው የማስረጃ ምዘና መርህ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡በግል ተበዳይ ሰውነት ላይ መድረሱ በሕክምና ማስረጃ የተረጋገጠው የጉዳት ዓይነትም ቢሆን የሚያረጋግጠው እና የሚደግፈው በአመልካች ምስክሮች ከተመሰከረው ፍሬ ነገር ጋር እንጂ በተጠሪዎቹ የመከላከያ ምስክሮች ከተነገረው ፍሬ ነገር ጋር እንዳልሆነ ከግራ ቀኙ ምስክሮች ቃልና ከህክምና ማስረጃው ይዘት በግልጽ መገንዘብ የሚቻል ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በግል ተበዳይ ላይ በህክምና ማስረጃው ላይ የተመለከተው ጉዳት ሊደርስ የቻለው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ተያይዞ በወደቀበት ጊዜ በኮብልስቶን ድንጋይ ጠርዝ

www.abyssinialaw.com

በመመታቱ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ በግል ተበዳይ ላይ ስለደረሰው የጉዳት ዓይነት በህክምና ማስረጃው የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

- ሲጠቃለል ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በከፊል በመሻር እና በከፊል ደግሞ በማሻሻል የሰጠው እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ በሕግ ተቀባይነት ያለውን የማስረጃ ምዘና መርህን የጣሰ በመሆኑ ምክንያት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡በሌላ በኩል ተጠሪዎቹ በማቅለያ ምክንያትነት እንዲያዙላቸው የተለያዩ ምክንቶችን በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርበው ውድቅ የተደረጉባቸው ቢሆንም የቀደመ የወንጀል ሪከርድ ያለባቸው ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበ ክርክር ባለመኖሩ እና የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች ሳላለመሆናቸውም በአመልካች በኩል የቀረበ ተቃራኒ ክርክር እና ማስረጃ ባለመኖሩ የቀደመ የዘወትር ጸባያቸው መልካምነት እና የቤተሰብ አስተዳዳሪነታቸው በሁለት የማቅለያ ምክንያቶች ተይዘው የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለቅጣቱ መነሻ አድርጎ ከያዘው እርከን 16 በሁለት እርከኖች ዝቅ ተደርጎ በእርከን 14 በተመለከተው ፍቅድ ስልጣን መሰረት በቅጣቱ ረገድ ተገቢው መሻሻል ሊደረግበት የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የሐረሪ ብ/ክ/መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12394 በ13/05/2007 ዓ.ም. የሰጠው እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03061 በ24/08/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195 (2) (ሀ) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በተራ ቁጥር አንድ የተመለከተው ውሳኔ በሕግ ተቀባይነት ያለውን የማስረጃ ምዘና መርህ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስነናል፡፡
3. የሐረሪ ክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 40031 የሰጠው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
4. በተራ ቁጥር ሶስት ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ በሶስቱም ተጠሪዎች ላይ በወንጀል ሕግ ቁጥር 555 (ሐ) ስር በ24/11/2006 ዓ.ም. የተሰጠው የጥፋተኝነት የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
5. በተራ ቁጥር ሶስት ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ በሶስቱም ተጠሪዎች ላይ በ29/11/2006 ዓ.ም. የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሎ በዚህ ጉዳይ ከአሁን በፊት የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሆኖ 1ኛ ተጠሪ አቶ ሕሊና ኃይሌ በሁለት ዓመት ከዘጠኝ ወር ጽኑ እስራት፣2ኛ ተጠሪ አቶ ፋሲካ

www.abyssinialaw.com

አፅምሮ በሁለት ዓመት ከሰባት ወር ጽኑ እስራት፣3ኛ ተጠሪ አቶ መላኩ ደምሴ በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡

6. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ጋር በመሆን ተጠሪዎቹን ተከታትሎ በመያዝ ለክልሉ ማረሚያ ቤት እንዲያስረክባቸው እና ማረሚያ ቤቱም ተጠሪዎቹ ተይዘው ሲቀርቡለት ተረክቦ በቅጣት ውሳኔው መሰረት እንዲያስፈጽም ለሶስቱም አካላት ትዕዛዝ ይተላለፍ፡፡
7. በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት 2ኛ ተጠሪ የተወሰነባቸውን መቀጮ ብር 2,000 (ሁለት ሺ.ህ) ከፍለው ከሆነ በሚያቀርቡት ደረሰኝ መሰረት እንዲመለስላቸው ተጠሪው ለሚጠይቁት አካል ይጻፍ፡፡
8. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 119159

ሐምሌ 20 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡ ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ደጀኔ መኮንን ሀብተማርያም - ጠበቃ በሬሳ በየነ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን 2ኛ ተከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከሰሱት ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በመሆን በ1ኛ ክስ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 (1) (ሀ) እና 453 (1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ሀሰተኛ ምስክርነት የመስጠት ወንጀል አድርገዋል፤በ2ኛ ክስ ደግሞ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 (1) (ሀ) እና 375 (ሀ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ሀሰተኛ ሰነድ የመፍጠር ወንጀል አድርገዋል ተብለው ነው፡፡

የወንጀሎቹ አፈጻጸምም በ1ኛ ክስ ሟች አቶ ተፈሪ በቀለ ምንም ዓይነት ኑዛዜ ሳያደርጉ አመልካቹ በ16/04/1999 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀርበው ሟች ለስር 1ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ዕፀገነት ተፈራ ጥቅም በ27/11/1998 ዓ.ም. ኑዛዜ አድርገዋል፣ኑዛዜው ሟች እየተናገሩ በሌላ ሰው የተጻፈ ነው፣ለሟችም ሆነ ለምስክሮች ተነቧል፣ኑዛዜ ሲያደርጉ አንደበታቸውም ሆነ ሕሊናቸው ትክክል ነበር በማለት ሀሰተኛ ምስክርነት ሰጥተዋል የሚል ሲሆን በ2ኛ ክስ ደግሞ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ሳይኖር ያለ አስመስለው ሌሎች ተከሳሾች ባዘጋጁት የኑዛዜ ሰነድ ላይ በምስክርነት በመፈረማቸው ሀሰተኛ ሰነድ ፈጥረዋል የሚል መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካቹ ያቀረቡት መቃወሚያ በብይን ታልፎ የእምነት ክደት ቃል ሲጠየቁ ድርጊቶቹን መፈጸማቸውን፣ይሁን እንጂ የፈጸሙት ሀሰተኛ ምስክርነት ለመስጠት አስበው ሳይሆን የኑዛዜው ተጠቃሚ ናቸው ከተባሉት የስር 1ኛ ተከሳሽ ባለቤት ጋር በአንድ መስሪያ ቤት ስለሚሰሩ በእኒሁ የስራ ባልደረባቸው የተነገራቸውን ነገር እውነት እንደሆነ አድርገው በመቀበል ነው የሚል ቃል በማስመዝገባቸው ፍርድ ቤቱ አመልካቹ ክደው እንደተከራከሩ መዝገቦ የዐቃቤ ሕግን አንድ

www.abyssinialaw.com

ምስክር ከሰማ እና የሰነድ ማስረጃ ከተቀበለ በኃላ ተጠሪው በክሱ መሰረት ያስረዳባቸው መሆኑን ገልጾ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 142 (1) መሰረት መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ ብይን የሰጠ ቢሆንም የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ እንደማይችሉ በመግለጻቸው በስር 1ኛ ተከሳሽ በኩል የቀረበውን የሰው እና የሰነድ የመከላከያ ማስረጃ ከተቀበለ በኃላ በተከሳሾቹ ላይ በሁለቱም ክሶች በክሱ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች ስር በመዝገብ ቁጥር 113071 በ17/08/2006 ዓ.ም. የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ቀጥሎም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መዝግቦ ቅጣቱን በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት በማስላት የጥፋተኛነት ውሳኔው በተመሰረተባቸው ድንጋጌዎች ስር ከተመለከተው የቀላል እና የጽኑ እስራት ቅጣት አማራጭ መካከል ተገቢ ሆኖ የተገኘው የጽኑ እስራት ቅጣቱ መሆኑን፣የወንጀሎቹ ደረጃ በዝቅተኛ ደረጃ የተመደበ መሆኑን፣በ1ኛ ክስ ለተመለከተው ወንጀል መነሻ ተደርጎ የተያዘው አንድ ዓመት ከስድስት ወር መሆኑን፣በ2ኛ ክስ ለተመለከተው ወንጀል መነሻ ተደርጎ የተያዘው ሁለት ዓመት መሆኑን፣ይህ የቅጣት መጠን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 (1) (ለ) መሰረት ሲደመር ሶስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት ሆኖ በእርከን 16 ስር የሚወድቅ መሆኑን፣ወንጀሉ ተደራራቢ በመሆኑ በመመሪያው አንቀጽ 22 (1) (ሀ) መሰረት በአንድ ማክበጃ ወደ እርከን 17 ከፍ የሚል መሆኑን፣ወንጀሉ የተደረገው በግብረአበርነት በመሆኑ ቅጣቱ በአንቀጽ 84 (1) (መ) መሰረት እንዲከብድ ዐቃቤ ሕግ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣የአመልካቹ የዘወትር ፀባይ መልካምነት፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪነት እና በመንግስት እና በማህበራዊ ተቋማት የሰጡት ረዥም አገልግሎት እንደቀደም ተከተላቸው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 82 (1) (ሀ)፣82 (1) (ሠ) እና 86 ድንጋጌዎች መሰረት በሶስት የማቅለያ ምክንያትነት ሲያዙ እርከኑ ወደ 14 ዝቅ የሚል መሆኑን ገልጾ አመልካቹ በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሆኖ ነገር ግን የቤተሰብ ኃላፊ እና የልጆች አባት መሆናቸውን፣በርካታ አገልግሎት ፈጽመው በጡረታ ላይ የሚገኙ እና ዕድሜአቸውም ከ70 ዓመት በላይ መሆኑን በምክንያትነት በማስፈር የተወሰነባቸው የእስራት ቅጣት በአንቀጽ 192 ድንጋጌ መሰረት በሁለት ዓመት የፈተና ጊዜ ከመፈጸም ታግዶ እንዲቆይ በ15/09/2006 ዓ.ም የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በስር 1ኛ ተከሳሽ እና በአመልካች ላይ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ከክብደቱ እና ከአፈጻጸሙ አንጻር የወንጀሉ ደረጃ ሊመደብ የሚገባው በመካከለኛ ደረጃ ሆኖ ሳለ በስር ፍርድ ቤት በዝቅተኛ ደረጃ የተመደበው አላግባብ መሆኑን፣በ1ኛ ክስ ለተመለከተው ወንጀል መነሻ ተደርጎ የተያዘው ሁለት ዓመት ከሁለት ወር መሆኑን፣በ2ኛ ክስ ለተመለከተው ወንጀል መነሻ ተደርጎ የተያዘው አራት ዓመት መሆኑን፣ይህ የቅጣት መጠን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 (1) (ለ) መሰረት ሲደመር ስድስት ዓመት ከሁለት ወር ጽኑ እስራት ሆኖ በእርከን 22 ስር የሚወድቅ

www.abyssinialaw.com

መሆኑን፣ወንጀሉ ተደራራቢ ነው በሚል የስር ፍርድ ቤት የመመሪያውን አንቀጽ 22 (1) (ሀ) ጠቅሶ ቅጣቱን ማክበዱ ሕጋዊ መሰረት የሌለው መሆኑን፣የስር ፍርድ ቤት አንድ የማቅለያ ምክንያት የሚያስቀንሰው አንድ እርከን ብቻ እንደሆነ አድርጎ የወሰነ በመሆኑ ምክንያት አመልካች ለእያንዳንዱ የማቅለያ ምክንያት ሁለት እርከን እንዲቀነስላቸው በዐቃቤ ሕግ ይግባኝ ላይ ያቀረቡት ጥያቄ ስነ ስርዓታዊ አለመሆኑን፣በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ባገኙት ሶስት የማቅለያ ምክንያቶች ቅጣቱ ከእርከን 22 ወደ እርከን 19 ዝቅ የሚል መሆኑን እና የቅጣት ገደብን አስመልክቶ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 197 (1) ከተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች መካከል ለግል ተበዳይ ከፍለዋል የተባለ ካሳ ባለመኖሩ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው የገደብ ውሳኔ ሕጉን መሰረት ያደረገ አለመሆኑን ገልጾ ውሳኔውን በማሻሻል አመልካች በአራት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ እና ቅጣቱንም በማረሚያ ቤት ሆነው እንዲፈጽሙ በመዝገብ ቁጥር 111560 በ01/02/2008 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በሁለቱ ክሶች ጥፋተኛ የመባላቸውን አግባብነት ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 61 (3) ድንጋጌ አንጻር፣እንዲሁም ለቅጣቱ አወሳሰን መሰረት ተደርጎ መያዝ የሚገባው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ነው ወይስ ቁጥር 2/2006 ነው? የሚሉትን ነጥቦች ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

1. አመልካቹ በሁለቱም የወንጀል ክሶች ጥፋተኛ የተባሉት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም?
2. ቅጣቱ ሊሻሻል ይገባል ወይስ አይገባም?

የሚሉትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካቹ ወንጀሎቹን ማድረጋቸውን ያልካዱ ከመሆኑም በላይ ሟች አቶ ተፈሪ በቀለ ከመሞታቸው በፊት በነበረባቸው ሕመም ምክንያት መናገርም ሆነ መጻፍ የማይችሉ የነበረ መሆኑ፣ሟች ያደረጉት ነው በተባለው ኑዛዜ ላይ ከስማቸው ትይዩ የተመለከተው ፊርማም የእርሳቸው አለመሆኑ በፎረንሲክ ምርመራ የተረጋገጠ መሆኑ፣የስር 1ኛ ተከሳሽ ይህንኑ ኑዛዜ ለፍርድ ቤት አቅርበው በአመልካች ምስክርነት ጭምር በሀሰት ተናዛዡ አባታቸው እንደሆኑ በመግለጽ የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ ከወሰዱ በኋላ የሟች ንብረት የነበረውን ቤት የሸጡ መሆኑ፣የግል ተበዳይ ናቸው በተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክር አቤቱታ አቅራቢነት ኑዛዜውም ሆነ የኑዛዜ የወራሽነት ማስረጃው በፍርድ ቤት እንዲሰረዝ

www.abyssinialaw.com

የተደረገ መሆኑ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን እና ይህንኑ ማስረጃ ለማስተባበል አመልካቹ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ያልቻሉ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 61 (3) ድንጋጌ ተጠቅሶ የተያዘውን ጭብጥ በተመለከተ ድንጋጌው ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት መሆኑን የሚደነግግ ሆኖ የንዑስ ቁጥር (3) ድንጋጌም አድራጊው የተወሰነ ወንጀል ለማድረግ አሳብ አለው ተብሎ በሚገመትበት ጊዜ በተለይም የማይገባውን ብልጽግና ለማግኘት በንብረት ላይ ወንጀል አድርጎ እንደሆነ ወይም የሐሰት ገንዘብ ሰርቶ እንደሆነ ወይም ይህንኑ ገንዘብ እንዲዘዋወር አድርጎ እንደሆነ ወይም ሀሰተኛ ሰነድ ሰርቶ ተጠቅሞበት እንደሆነ የመጀመሪያውን የጥፋት ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ሲል መሰረታዊ ከሆነው ወንጀል በኃላ አከታትሎ ያደረገው ድርጊት ከቀድሞ ሃሳቡና ሊደርስበት ካቀደው ግቡ ጋር የተያያዘ ሆኖ በዋናው ወንጀል እንደሚጠቃለል የሚደነግግ ነው።የዚህ ንዑስ ቁጥር ድንጋጌ ዓላማ እና ይዘት የሀሰት ገንዘብ የሰራ አንድ ሰው ገንዘቡ እንዲዘዋወር ካላደረገ በቀር ወይም ሀሰተኛ ሰነድ የሰራ ሰው ካልተጠቀመበት በቀር በወንጀሉ ያቀደውን ዓላማ ከግቡ ሊያደርስ የማይችል በመሆኑ ምክንያት ተከታትለው የተፈጸሙት አድራጎቶች በአንድ የወንጀል ማድረግ ሀሳብ እንደተፈጸሙ ተቆጥረው በዋናው ወንጀል እንደሚጠቃለሉ እና አድራጊው የሚጠየቀው በአንድ ወንጀል መሆኑን የሚያመለክት ነው።በተያዘው ጉዳይ ሐሰተኛ ሰነድ የመፍጠሩ ወንጀል አስቀድሞ ከተጠናቀቀ እና ፍጻሜ ካገኘ በኃላ አመልካች በፍርድ ቤት ቀርበው ሟች ኑዛዜ ሲያደርጉ በምስክርነት ተገኝተው ማየታቸውን እና መስማታቸውን በማረጋገጥ የሀሰት ምስክርነት መስጠታቸው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 63 ድንጋጌ አነጋገር መሰረት በሁለቱ ወንጀሎች ተጠያቂነትን የሚያስከትል ከሚሆን በስተቀር በአንቀጽ 61 (3) ድንጋጌ አነጋገር መሰረት በአንድ ወንጀል የሚጠቃለል ነው ሊባል የሚችል ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም አመልካቹን በሁለቱም የወንጀል ክሶች ጥፋተኛ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም።

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ አመልካቹ ወንጀሎቹን ያደረጉት በ16/04/1999 ዓ.ም. ሲሆን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸው ደግሞ እንደቅደም ተከተሉ በ17/08/2006 ዓ.ም. እና በ15/09/2006 ዓ.ም. ነው።ይህንኑ ጊዜ መሰረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች ቅጣቱ የተሰላውም ከጥቅምት 1 ቀን 2006 ዓ.ም. ጀምሮ በስራ ላይ የዋለውን የተሻሻለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በማድረግ ነው።የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ በስራ ላይ ከነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ይልቅ ለተከሳሽ ወገን ቅጣቱን የሚያቀለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ከሆነ ለቅጣቱ አወሳሰን መሰረት ተደርጎ መያዝ የሚገባው ይኸው መመሪያ ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 95440 እና በሌሎችም መዝገቦች በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ለቅጣቱ አወሳሰን መሰረት ተደርጎ መያዝ የሚገባው የቀድሞው መመሪያ መሆኑን ተገንዝበናል።ይግባኙን የተመለከተው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡትን ክርክር

www.abyssinialaw.com

ሳይቀበል የቀረው አመልካቹ የዚህ ዓይነት ክርክር ዐቃቤ ሕግ ባስከፈተው መዝገብ ላይ ማቅረብ አይችሉም በማለት ነው፡፡ በመሰረቱ አመልካች በስር የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በተሰጠባቸው የጥፋተኝነት፣የቅጣት እና የገደብ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካልነበራቸው ይግባኝ የሚሉበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖራቸውም፡፡ ክርክሩ የወንጀል እንደመሆኑ መጠን ዐቃቤ ሕግ ባስከፈተው የይግባኝ መዝገብ ላይ ሕጉ የሚሰጣቸውን መብት መሰረት አድርገው የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 88 (3) የተመለከተው ድንጋጌም ሆነ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው በቅጣት አወሳሰን መመሪያ የተካተቱት ድንጋጌዎች ይህንኑ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ ባስከፈተው የይግባኝ መዝገብ ላይ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አስመልክቶ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ስነ ስርዓታዊ አይደለም በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተያዘው አቋም ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ለሁለቱ ወንጀሎች መነሻ ተደርጎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተያዘው ቅጣት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 (1) (ለ) መሰረት ሲደመር ስድስት ዓመት ከሁለት ወር ጽኑ እስራት ሆኖ በእርከን 22 ስር የሚወድቅ ሲሆን ይህ የቅጣት መጠን በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ባገኙት ሶስት የማቅለያ ምክንያቶች በቀድሞው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በእያንዳንዱ የማቅለያ ምክንያት በሁለት እርከን ዝቅ ሲደረግ ከእርከን 22 ወደ እርከን 16 ዝቅ የሚል በመሆኑ በአመልካቹ ላይ ለሚጣለው ቅጣት መነሻ ተደርጎ መያዝ የሚገባው በእርከን 16 ስር የተመለከተው የቅጣት ፍቅድ ስልጣን ነው፡፡

ሲጠቃለል በአመልካቹ ላይ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ያልተቻለ በመሆኑ እና ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በአመልካቹ ላይ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጥሎ የነበረው የቅጣት መጠን ግን ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአመልካቹ ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሁለቱም ክሶች በመዝገብ ቁጥር 113071 በ17/08/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 111560 በ01/02/2008 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በአመልካቹ ላይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 111560 በ01/02/2008 ዓ.ም. የተሰጠውን የአራት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት

www.abyssinialaw.com

በማሻሻል አመልካቹ በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ጊዜ ሁሉ ታስቦላቸው በሶስት ዓመት ከሶስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡

3. በተሻሻለው የጽኑ እስራት ቅጣት ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከመሸኛ ትዕዛዝ ጋር አመልካቹ ለሚገኙበት የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ይላክ፡፡ ለአመልካቹም በዚያው በኩል ይድረስ፡፡
4. እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይላክ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.118084

ሐምሌ 21 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡-አቶ ንጉሴ አሊ አስፋው -ጠበቃ አወል ሰይድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ -ሰላማዊት ወንድሙ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተከሰሱት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 676 (2) (ሀ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል አድርገዋል ተብለው ነው፡፡የወንጀሉ አፈጻጸምም አመልካቹ በን/ስ/ላ/ክፍለ ከተማ በቀበሌ 15 የላፍቶ ቁጥር 1 ኮንዶሚኒየም ባለቤቶች ኃላፊነቱ የተወሰነ የህብረት ስራ ማህበር ውስጥ በዋና ገንዘብ ያዥነት በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተመርጠው ሲሰሩ ከአባላቱ ከተሰበሰበው ገንዘብ ብር 823,617.00 ውስጥ ብር 749,997.00 ብቻ በማህበሩ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ገቢ አድርገው ልዩነቱን ብር 73,620.00 ገቢ ሳያደርጉ አጉድለው ተገኝተዋል ተብለው ሲሆን ያቀረቡት መቃወሚያ በብይን ታልፎ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ወንጀሉን አላደረኩም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ ሶስት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን ከሰማ እና የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ አመልካቹ መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 142 (1) በሰጠው ብይን መሰረት ሶስት የመከላከያ ምስክሮችን አሰምተዋል፡፡ የተለያዩ ሰነዶችን በማስረጃነት አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በተጠሪ ማስረጃ የተመሰከረባቸውን ፍሬ ነገር በመከላከያቸው አላስተባበሉም በማለት በተከሰሱበት ድንጋጌ ስር

www.abyssinialaw.com

በመዝገብ ቁጥር 71523 በ24/06/2007 ዓ.ም. የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ቀጥሎም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መዝግቦ ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት በማስላት የጥፋተኛነት ውሳኔው በተመሰረተበት ድንጋጌ ስር ከተመለከተው የቀላል እና የጽኑ እስራት ቅጣት አማራጭ መካከል ተገቢ ሆኖ የተገኘው የጽኑ እስራት ቅጣት መሆኑን፣ወንጀሉ በመካከለኛ ደረጃ የተመደበ መሆኑን፣መነሻ ተደርጎ የተያዘው አራት ዓመት ሆኖ ይህ የቅጣት መጠን የሚወድቀው በአባሪ አንድ በእርከን 19 ስር መሆኑን፣የአመልካቹ የቀድሞ የዘወትር ፀባይ መልካምነት፣የቤተሰብ አስተዳዳሪነት እና የጤና ችግር በሶስት የማቅለያ ምክንያትነት ሲያዙ ቅጣቱ በስድስት እርከን ዝቅ ብሎ በእርከን 13 ስር የሚሸፈን መሆኑን ገልጾ አመልካቹ በሁለት ዓመት ከሶስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ በ01/07/2007 ዓ.ም. ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቹ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን በመዝገብ ቁጥር 145422 በ16/10/2007 ዓ.ም. ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ዐቃቤ ሕግ ተፈጻሚነት ያለው አዋጅ የህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 ስለሆነ በወንጀል ሕጉ ክስ መቅረብ የለበትም፣ክሴን አንስቻለሁ እያለ ፍርድ ቤቱ በክርክሩ ቀጥሎ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፣ይህ ቢታለፍ የእምነት ማጉደል ወንጀል ስለማድረጌ አንድም ኦዲተር ቀርቦ አላረጋገጠም በማለት በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የስር ፍርድ ቤት አቤቱታ የቀረበበትን የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠው አመልካች ወንጀሉን አላደረኩም ቢሉም ከአባላት የሰበሰቡት እና ባንክ ያስገቡት የገንዘብ መጠን ሲቀናነስ መጠኑ በክሱ የተጠቀሰው ገንዘብ በጉድለት የተገኘባቸው መሆኑ በተጠሪው የሰው እና የሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ አመልካቹ ያቀረቡት መከላከያ የተጠሪውን ማስረጃ ለማስተባበል ያልቻለ መሆኑን በመግለጽ ሲሆን ፍሬ ነገርን በማጣራት እና ማስረጃን በመመዘን ረገድ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተደረሰበት ድምዳሜ ተመሳሳይ ስልጣን ባለው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡አመልካች በሰበር አቤቱታቸውም ቢሆን የህብረት ስራ ማህበራት የሂሳብ ምርመራ አዋጅ ቁጥር 147/1991 "ን" በሚያስፈጽመው አካል ካልሆነ በቀር በማህበሩ በራሱም ሆነ በሌላ አካል ኦዲት ሊደረግ አይችልም ከማለት በቀር የተገኘባቸው ጉድለት ስላለመኖሩ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡አዋጁ አመልካቹ የሚሉት ዓይነት ትርጉም ያለው ስለመሆኑ

www.abyssinialaw.com

አመልካች ጠቅሰው የሚከራከሩባቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች አያመለክቱም::በማህበሩ የውስጥ ኦዲተርም ሆነ ሂሳቡን እንደገና ባጣራው ገለልተኛ ኦዲተር የተገኘው ጉድለት ተመሳሳይ ስለመሆኑም የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል::

ተከሳሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ ንብረቱን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም የማዋል ሃሳብ እንዳለው የሚቆጠር ስለመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675 (3) የተመለከተው መርህ አመልካቹ ጥፋተኛ ለተባሉበት ድንጋጌም ተፈጻሚነት ያለው ነው::አመልካች በእጃቸው እንደገባ በተጠሪ ማስረጃ የተረጋገጠውን ገንዘብ በዚህ ድንጋጌ አነጋገር መሰረት ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋሉ መሆኑን ለማስረዳት እንዳልቻሉ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ በተከከሱበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ መባላቸው የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም::

በሌላ በኩል ተጠሪ ክሱን አንስቶ እያለ ፍርድ ቤቱ በራሱ ክርክሩን ቀጥሎ ውሳኔ ሰጥቶብኛል በማለት አመልካች በሰበር አቤቱታቸው የተከራከሩ ቢሆንም ይህ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም::ይልቁንም መዝገቡ የሚያረጋግጠው ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ የቅጣት ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ የክርክሩ አካል የነበረ መሆኑን ነው::በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ክሴን አንስቻለሁ በማለት የገለጸበት ጊዜ እንዳልነበረም ተጠሪው አሁን በሰበር መልሱ አረጋግጧል:: በመሆኑም ተጠሪው በስር ፍርድ ቤት ክሱ ቢነሳ አልቃወምም ብሏል በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም::አመልካች በጥፋተኝነት ውሳኔው ላይ ካልሆነ በቀር በቅጣት ውሳኔው ላይ ያቀረቡት የቅሬታ ነጥብ ካለመኖሩም በላይ የቅጣት ውሳኔውም የተሰላው አና የተወሰነው ሕጉን እና አግባብነት ያለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በማድረግ በመሆኑ የቅጣት ውሳኔው የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም::

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል::

www.abyssinialaw.com

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 71523 በ24/06/2007 ዓ.ም. እና በ01/07/2007 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 145422 በ16/10/2007 ዓ.ም. የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች እና አመልካቹ ለሚገኙበት አዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ይላክ፡፡ለአመልካቹም በዚያው በኩል ይድረስ፡፡
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 117877

ሐምሌ 22 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ማስረሻ ገሰሱ

ተጠሪ፡- የፌ/ዐ/ሕግ ወይን ገ/እግዚአብሔር

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ አመልካች ላይ በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘት በክስ 1. ተከሳሽ የወ/ህ/አ 543(3) የተመለከተውን በመተላለፍ ሲያሽከረክሩት የነበረው ሲኖትራክ ገልባጭ መኪና የመጫን አቅሙ 132 ኩንታል ሆኖ እያለ 200 ኩንታል ሲሚንቶ ጭኖበት ከአዲሱ ገበያ ወደ ሰሜን ሆቴል አቅጣጫ ያለጥንቃቄ በቂ ርቀት ሳይጠበቅ ሲያሽከረክር ከፊት ለፊቱ በተመሳሳይ አቅጣጫ ሲሽከረከር የነበረውን ኤፍ ኤስ አር መኪና በሃይል ከፊት ለፊት አካሉ በመግጨት ወደ ቀኝ ከመንገድ ውጪ እንዲወጣ ካደረገ በኋላ አልፎ በመሄድ ሚኒባስ መኪና ገጭቶ መንገድ ዳር ላይ ቆመው ከነበሩ ላዳዎች ጋር በማጋጨት ሟች ጥሩ ደምሴ፣ ገነት ጽጌን እና ቁስ በቀለ ደምሴ ሕይወታቸው እንዲያልፍ በማድረጉ በፈጸመው በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ተከሷል፡፡

በክስ 2. የወ/ሕ/ቁ. 559(2) የተመለከተውን በመተላለፍ በክስ 1. በተጠቀሰው አኳኋን ተከሳሽ መኪኖችን ገጭቶ በማገጫጨት በእግረኛ መንገድ ላይ የነበረችውን ወ/ሪት ሄለን አበባን በፊት ለፊት አካሉ በመግጨት ከላይኛው መንጋጋዋ ላይ 2 ጥርሶችንና ከታችኛው መንጋጋዋ አንድ ጥርስ እንዲወልቅ በማድረጉ፤

www.abyssinialaw.com

በክስ 3. የወ/ሕ/ቁ. 559(2) የተመለከተውን በመተላለፍ በክስ 1. በተጠቀሰው አኳኋን ተከሳሽ መኪኖችን ገጭቶ በመገጫጨት የሰ/ቁ. 3-12333 ኦሮ ሚኒባስ መኪና ውስጥ ተሳፋሪ የነበረችውን ወ/ሪት አስቴር ከፊት የዳሌ አጥንት ስብራት እንዲደርስባት ያደረገ በመሆኑ በፈጸመው በቸልተኝነት የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሷል፡፡

በክስ 4. የወ/ሕ/ቁ. 572(1) የተመለከተውን በመተላለፍ በክስ 1. በተጠቀሰው አኳኋን ኤፍ.ኤስ.አር መኪና ገጭቶ ከመንገድ ወጥቶ ከሌላ መኪና እና ሱቅ ጋር በማጋጨት ብር 45,000 የሚገመት ጉዳት እንዲደርስ ያደረገ በመሆኑ በፈጸመው የትራፊክ ደንብ በመጣስ በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡ ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) በአራቱም ክሶች ላይ የተመለከቱትን የወንጀል ድርጊቶችን መፈጸማቸውንና ጥፋተኛ መሆናቸውን በማመናቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 134(1) መሰረት ፍ/ቤቱ በተከሳሽ ላይ በአራቱም ክሶች የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መዝገብ በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 መሰረት በማስላት በየክሶቹ አራት የማቅለያ ምክንያቶችን ወስዶ በክስ 1. ተከሳሽ በ 3 አመት ከ 3 ወር እስራት እና በብር 2000 የገንዘብ ቅጣት በክስ 2 ተከሳሽ በ 2 ወር እስራት እና በብር 1000 የገንዘብ ቅጣት በክስ 3 ተከሳሽ በ 3 ወር እስራት እና በብር 1000 የገንዘብ ቅጣት በክስ 4 አፈጻጸሙን ዝቅተኛ በማድረግ በ 3 አመት ከ 10 ወር እስራት አና በብር 500 የገንዘብ መቀጮ በድምሩ በ 3 አመት ከ 10 ወር እስራት እና በብር 5000 የገንዘብ ቅጣት ተከሳሽ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ቅጣቱም በገደብ እንዲቆይ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ የቅጣት ውሳኔ ላይ ቅሬታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ግራቀኙን አከራክሮ የተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት አወሳሰንን በተመለከተ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 184(1)(ለ) ለእያንዳንዱ በተደራራቢነት ለተፈጸመ ወንጀል ተገቢ ቅጣት ተወስኖ እንደሚደመር ያስረዳል፡፡ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 አንቀጽ 22 (1(ሀ) እና 23(5) የተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት አወሳሰን የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 184(1)(ለ) የተከተለ ሆኖ ወደ ቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያዎች ከመግባቱ በፊት የእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት ተደምሮ ድምሩ የሚያርፍበት ዝቅተኛው የእስራት ቅጣት እርከን ተለይቶ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ የስር ፍ/ቤት በዚህ አግባብ ሳይሆን በእያንዳንዱ ወንጀል የእስራት ቅጣት እርከን ላይ የቅጣት ማቅለያዎችን በመጠቀም በተናጠል በየክሱ ቅጣቱን በማቅለል የወሰነው ከህጉ ውጭና መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ክስ 1. ደረጃ 2 እርከን 21 የገንዘብ መቀጮ ደግሞ እርከን 6 ይሆናል፡፡ መ/ሰጪ የ 3 ሰዎች ሕይወት እንዲጠፋ ስላደረገ መነሻ ቅጣት 6 ዓመት ጽኑ እስራት በክስ 2 በወንጀሉ ድርጊት የግል ተበዳይ 3 ጥርሶች የወለቁ በመሆኑ ወንጀሉ ደረጃ 3 እርከን 9 የገንዘብ መቀጫ እርከን 3 ይሆናል፡፡ 1 አመት ከ 6 ወር እስራት ወደ ጽኑ እስራት ሲለወጥ በ 9 ወር ጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት በክስ 3 መነሻ ቅጣት ደረጃ 1 እርከን 7 ላይ የእስራት ቅጣቱን

www.abyssinialaw.com

ወደ ጽኑ እስራት በመለወጥ በ 7 ወር ጽኑ እስራት በክስ 4 የእስራት ቅጣቱን ወደ ጽኑ እስራት በመለወጥ በ 3 ወር ጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት በመወሰን የአራቱንም ተደራራቢ ወንጀሎችን መነሻ ቅጣት በመደመር 7 አመት ከ 7 ወር ጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት ይዞ በአራት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች መነሻ ቅጣቱ ካረፈበት እርከን 24 ወደ እርከን 20 ዝቅ በማድረግ መ/ሰጪ (የስር ተከሳሽ) ለፈጸመው ወንጀል በ 5 አመት ከ 4 ወር ጽኑ እስራት እና በብር 7,000 የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጣ በመወሰን የስር ፍ/ቤትን የቅጣት ገደብ ውሳኔ በማንሳት መ/ሰጪ የጽኑ እስራት ቅጣቱን እንዲፈጽም የስር ፍ/ቤትን የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በዚህ ውሳኔ ላይ ተፈጸመ ያሉትን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ለማሳረም ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ የጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ገደብን አስመልክቶ ይግባኝ ባልተባለበት ቅጣት ማቅለያዎችን ከተቀበለ በኂላ የመጨረሻውን 5 አመት ከ 4 ወር በማሳደግ መወሰኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194(2)(ሐ) እና ከቅጣት አወሳሰን መርህ አንጻር ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ አቤቱታው እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ አመልካች ላይ በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት አራት የወንጀል ክሶችን ያቀረበ ሲሆን አመልካች የተከሰሱባቸውን አራቱም ክሶች ላይ የተመለከተውን ወንጀል መፈጸማቸውን በማመናቸው ፍ/ቤቱ በአራቱም ክሶች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠ በኂላ ቅጣት ሲወሰን በወ/ሕ/አንቀጽ 184(1(ለ) እና በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 አንቀጽ 21(1)(ሀ) መሰረት ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት በመወሰን እና መነሻ ቅጣቶቹን በመደመር ድምሩ የቅጣት መጠን የሚያርፍበትን ዝቅተኛ የቅጣት እርከን በመምረጥ ለይቶ በመቀጠል ወደ ቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶችን በማገናዘብ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት ተገቢ ነው የሚለው ቅጣት መወሰን ሲገባው አመልካች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠባቸው አራት ወንጀሎች በእያንዳንዱ ወንጀል በተናጠል አራት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመውሰድ ቅጣት ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ የስር ፍ/ቤት ቅጣት አወሳሰን ቅሬታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ የስር ከፍ/ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን የወንጀል ሕጉን እና የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን የተከተለ ባለመሆኑ በማረም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 መሰረት ለአራቱ ወንጀሎች በተናጠል መነሻ ቅጣት ወስኖ በመደመር ድምሩ የሚያርፍበትን ዝቅተኛ

www.abyssinialaw.com

እርከን ከለየ በኋላ ለአመልካች ለስር ፍ/ቤት የተያዘላቸውን 4 ማቅለያ ምክንያቶች ወስዶ በእርከን 20 ከተመለከተው የቅጣት ፍቅድ ስልጣን በ 5 አመት ከ 4 ወር ጽኑ እስራት እና በብር 7,000 የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጡ እና የተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ ከ 5 አመት በላይ ጽኑ እስራት በመሆኑ አመልካች የቅጣት ውሳኔውን በማ/ቤት ሆነው እንዲከታተሉ የሰጠው ውሳኔ የወ/ሕጉን አንቀጽ 184(1(ለ) ፣ 194(1)ለ) እና የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 አንቀጽ 21 (1(ሀ) እና 23(5) መሰረት ያደረገ ነው፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ተጠሪ ለስር ፍ/ቤት ባቀረበው ይግባኝ የስር ፍ/ቤት ቅጣት አሰላል ላይ የተፈጸመው ግድፈት ይታረምልኝ አለ እንጂ ቅጣቱ ከፍ ተደርጎ ይወሰንልኝ አላለም ያሉ ቢሆንም ተጠሪ ለስር ፍ/ቤት ባቀረበው አቤቱታ የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት 4 ማቅለያ ምክንያቶችን ከወንጀል ሕጉ እና ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው ውጭ በመደጋገም ለእያንዳንዱ ወንጀል በመጠቀም ቅጣት መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ በክስ 2 ደረጃ እና እርከን አለአግባብ ተይዟል በአራቱም ክሶች ላይ የተፈጸመው የቅጣት አሰላል ግድፈት ይስተካከልን በማለት ያቀረበውን ቅሬታ ተከትሎ ከፍ ሲል እንደተገለጸው በወንጀል ህጉ እና በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት የፌ/ከፍ/ፍ/ቤትን የቅጣት ውሳኔ በማረም መወሰኑ በይግባኝ ከተጠየቀው ዳኝነት ውጭ ወስኗል የሚያስብል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ አቤቱታ ግራቀኙን አከራክሮ የስር ፌ/ከፍ/ፍ/ቤትን የቅጣት አወሳሰን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184(1)(ለ) እና በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 አንቀጽ 21(1) (ሀ) እና 23(5) መሰረት በማረም መወሰኑ እና አመልካች ላይ የተወሰነው ቅጣት ከ 5 አመት ጽኑ እስራት በላይ በመሆኑ በወ/ሕጉ አንቀጽ 194(1)(ለ) መሰረት የስር ፍ/ቤትን የቅጣት ገደብ ውሳኔ በማንሳት አመልካች የተወሰነባቸውን 5 አመት ከ 4 ወር ጽኑ እስራት በማ/ቤት ሆነው እንዲፈጸሙ የሰጠው የቅጣት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 107679 በቀን 19/10/2007 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195(2)(መ) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 119500

ሐምሌ 22 ቀን 2008 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ፀሀይ ውብዬ } አልቀረቡም

**ተጠሪ**፡- የፌደራል/ዓ/ህግ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የመንግስት ማህተምን ያለአግባብ መገልገል ሙከራ ወንጀል የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች እና አብረዋቸው በተከሰሱ ተከሳሾች ላይ ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የአሁን አመልካች ላይ የቀረበው ክስ ይዘት ተከሳሽ ለመንግስት ስራ የሚውል ማህተምን ያላግባብ ለመገልገል አስባ በዐ/ህግ 3ኛ ምስክር አማካኝነት ለወ/ሮ ሜሮን ሚካኤል (1ኛ ተከሳሽ) 1000 ብር ከፍላ የኢት/ንግድ ባንክን ማህተም ከባንኩ ሰርቃ እንድታመጣላት ካደረገች በኋላ በምስክሯ ጥቆማ የተያዘች በመሆኑ የወ/ህ/አ 27(1) እና 363 (1)(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ የመንግስት ማህተም ያለአግባብ መገልገል ሙከራ ወንጀል ተከሰላች የሚል ነው፡፡

አመልካች (የስር ተከሳሽ) በክሱ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት በመካዳቸው ዐ/ህግ ማህተሙ የጠፋበት የኢት/ን/ባንክ ሱማሌ ተራ ቅርንጫፍ ሠራተኞችን ጨምሮ 3 ምስክሮችን አሰምቷል፡፡ ፍ/ቤቱ ከዐ/ህግ ምስክሮች 1ኛ ተከሳሽ የሆኑት ወ/ሮ ሜሮን ሚካኤል በተጨማሪ ምስክርነት ሰምቶ አመልካች ክሱ የቀረበበትን የወንጀል ድርጊት ለመፈፀማቸው የተመሰከረባቸው በመሆኑ እንዲከላከሉ ብይን የሰጠ ሲሆን አመልካች የሰው

www.abyssinialaw.com

መከላከያ ማስረጃ የለኝም በሚሮን ሚካኤል የግል ስልክ በወቅቱ ስለመደወሌ ከኢት/ቴሌኮም ዝርዝር ቀርቦ ይታይልኝ ብለዋል፡፡

ፍ/ቤቱ ከሰኔ ወር መጀመሪያ እስከ ሐምሌ ወር መጨረሻ 2006 ዓ/ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ወ/ሮ ሜሮን ሚካኤል በግል ስልካቸው የተደወለ የስልክ ቁጥር ዝርዝር እንዲቀርብ ባዘዘው መሠረት ከኢት/ቴሌኮም በቀረበው ዝርዝር ወ/ሮ ሜሮን ሚካኤል በሚጠቀሙበት ስልክ ቁጥር አመልካች በሚሰሩበት የመከላከያ ሚ/ር የቢሮ ስልክ ቁጥር ላይ ተደውሎ የነበረ መሆን አለመሆኑን ባያሳይም ወ/ሮ ሜሮን ሚካኤል ስልክ ላይ ተከሳሽ አልደወለችም ብሎ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያዳግት ነው በማለት አመልካች (ተከሰሽ) በተከሰሱበት የወንጀል ህግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ናቸው ብሎ በመወሰን የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በማገናዘብ በቅጣት አወሰሰን መመሪያው ቅጣቱን በማስላት በ3 ዓመት ከ3 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታቸውን ለፌ/ክልል ፍ/ቤት በይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር አመልካች ላይ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔን በማፅናት ወንጀሉ በሙከራ ደረጃ የቀረ እና በመንግስትና በህዝብ ላይ የደረሰ ጉዳት ባለመኖሩ ስር ፍ/ቤት የወንጀሉን ደረጃ በቀላል ደረጃ መመደብ ሲገባው መካከለኛ ደረጃ መመደቡ ተገቢ አይደለም ብሎ የወንጀሉን ደረጃ በቀላል ደረጃ በመመደብ መነሻ ቅጣት 3 ዓመት ወስኖ በ2 ማቅለያ ምክንያቶች ቅጣቱ ወደ 2 ዓመት ፅኑ እስራት በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተፈፀመ ያሉትን መሠረታዊ የህግ ስህተት በመጥቀስ እንዲታረምላቸው የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት የተወሰነባቸው በክሱ ላይ የተጠቀሰውን የህግ አንቀጽ የሚያቋቁም ድርጊት መፈፀማቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ መሆን አለመሆኑን እና በዚህ ጉዳይ በስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበሩትና ወ/ሮ ሜሮን ሚካኤልን በአመልካች ክስ በማጣሪያ ምስክርነት ጠርቶ የመስማቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ ምክንያት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ተከሰው ጥፋተኛ የተባሉት የወ/ህጉን አንቀጽ 27(1) እና 363 (1) “ለ” የተመለከተውን ተላልፈው ለመንግስት ስራ በተዘጋጀ ማህተም ያለ አግባብ መገልገል ሙከራ ወንጀል ሲሆን የድንጋጌው ይዘት ለመንግስት ስራ ጉዳይ ብቻ የሚታተምበትን የመንግስትን ወይም የመንግስታዊ አካላት የአንዱን ማህተም ያለአግባብ የተገለገለ እንደሆነ ከ3 ዓመት እስከ 10 ዓመት ሲደርስ

www.abyssinialaw.com

በሚችል ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል፡፡ አመልካች ለኢት/ንግድ ባንክ ሱማሌ ተራ ቅርንጫፍ መገልገያነት የተዘጋጀውን የመንግስት ማህተም በተጠሪ 3ኛ ምስክር እና በስር 1ኛ ተከሳሽ በሆኑት የባንኩ ተላላኪ ሠራተኛ አማካኝነት ማህተሙን ተቀብለው የባንኩ ተላላኪ ሠራተኛ ለሆኑት የስር 1ኛ ተከሳሽ ብር 1000 መላካቸው ስር ፍ/ቤት በቀረበው ማስረጃ በማረጋጥ አመልካች ላይ ያሳለፈው የጥፋተኛነት ውሳኔ በህጉ አግባብ በመሆኑ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም በሌላ በኩል አመልካች የተከሰሱት እና የጥፋተኛነት ውሳኔ የተላለፈባቸው በሙከራ ደረጃ በቀረ ወንጀል በመሆኑ በወ/ሕ/አንቀጽ 31 እንደተመለከተው ተከሳሹ ጥፋተኛ በተባለበት የሙከራ ወንጀል ድርጊት የደረሰ ጉዳት ከሌላ በወ/ህ/ቁ. 180 በተመለከተው መሠረት ቅጣቱን በመሰለው እንደሚያቀል የተደነገገ በመሆኑ እና በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ቀደም ሲል እንደነበረው የቅጣት አወሳሰን በሙከራ ደረጃ ለተፈጸመ ወንጀል ቅጣት እንደሚቀንስ በግልጽ ባይመለከትም በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 24 ስር በወንጀል ህጉ ቅጣትን በመሰለው እንዲያቀል በፈቀደ ጊዜ ፍ/ቤቱ በመመሪያው ሳይወሰን ቅጣትን በማቅለል እንደሚወሰን የተመለከተ በመሆኑ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በተመሳሳይ በሰ/መ/ቁ. 104937 አስገዳጅነት ያለው የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ ወንጀሉ በሙከራ ደረጃ የቀረ መሆኑን መሠረት በማድረግ የስር ፍ/ቤት ቅጣቱን በመሰለው ማቅለል ሲገባው ይህን በማለፍ በቀረቡለት 2 ማቅለያ ምክንያቶች ላይ ብቻ በመወሰን የሰጠው የቅጣት ውሳኔ ሊታረም የሚገባው በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 121682 በቀን 6/11/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 001102 በቀን 18/2/2008 ዓ/ም የሰጡት የጥፋተኛነት ውሳኔ እና ትዕዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 195(2) (ለ) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ያሳለፈው የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
3. አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት ወንጀል በሙከራ ደረጃ የቀረ እና በመንግስት ላይ የደረሰ ጉዳት ባለመኖሩ የወ/ህጉን አንቀጽ 27(1)፣31፣ 180፣ እና 363(1) (ለ) እንዲሁም የተሻሻለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 አንቀጽ 24 መሠረት በማድረግ ለአመልካች ስር ፍ/ቤት የተያዘላቸውን ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችንም ከግምት በማስገባት አመልካች ለፈፀሙት ጥፋት ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የታሰሩበት የሚታሰብላቸው ሆኖ በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ የስር ፍ/ቤትን የቅጣት ውሳኔ በመሻሻል ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

4. አመልካች ታስረው የሚገኙበት ማ/ቤት በዚህ በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ይፃፍ ብለናል መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.102982

መስከረም 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የትግራይ ብሔራዊ ክልል ዓ/ህግ -- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ቡሽራ ያህያ  አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይ/ሠ/ችሎት በመዝገብ ቁጥር 99191 ሰኔ 20 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልካች በቁጥር 1043/45/06 ሐምሌ 10 ቀን 2006 ዓ.ም የተጻፈ 03 ገጽ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ክርክሩ የወንጀል ጉዳይን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በጀመረበት በትግራይ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ለጉዳዩ መነሻ ምክንያት የሆነው አመልካች በቁጥር 18162/05 ህዳር 06 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የወንጀል ክስ በአሁኑ ተጠሪና በሌሎች ሁለት ግለሰቦች ላይ በማቅረባቸው ሲሆን በ1ኛ ክስ የተጠቀሰውና ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ክስ ይዘት በአጭሩ ሲታይ ተጠሪው የፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 652/2001 በአንቀጽ 8 ሥር የተደነገገውን በመተላለፍ ሐምሌ 16 ቀን 2004 ዓ.ም ከቀኑ 5፡00 ሰዓት ሲሆን ውቅሮ ከተማ በሚገኝ መኖሪያ ቤቱ ውስጥ ለሽብር ተግባር ለማዋል በማሰብ የኢህአዴግ መንግስት የአሜሪካንና የአይሁዶች መንግስታት ጥቅም ለማስጠበቅ

www.abyssinialaw.com

ፀረ እስላም እንቅስቃሴ የሚያደርግና የእስላም አንድነት ለማጥፋት የሚሠራ መንግስት መሆኑን የሚገልፁ፤ አህባሽ የሳውዲና የምዕራባዊን ተልዕኮ የሚያስፈፅም በእስልምና ሐይማኖት ላይም ክህደት የሚፈፅም ቡድን በመሆኑ ለመንግስትና ለመጅሊስ እውቅና መስጠት የለብንም የሚልና ሁሉም የእስልምና ሐይማኖት ተከታይ በኢህአዴግ መንግስት በፀሎት ተቃውሞውን ያቅርብ የሚል ይዘት ያላቸው ለሽብር ተግባር የሚያነሳሱ ሲዲዎችን ይዞ የተገኘ በመሆኑ ለሽብርተኝነት ድርጊት መፈፀሚያነት ንብረት መያዝ ወይም መጠቀም ወንጀል ፈፅሟል የሚል ነበር፡፡

ተጠሪም ፍርድ ቤት ቀርበው ክሱን ክደው የተከራከሩ ሲሆን አመልካች የሰው ምስክሮችንና ሌሎች ጠቃሚ ናቸው ያሏቸውን ማስረጃዎች አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የትግራይ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የአመልካችን ክስና ማስረጃ በመመርመር ተጠሪ እንዲከላከል ትዕዛዝ ሰጥቶ መከላከያ ምስክሮችን ሰምቷል፡፡ በመጨረሻም ተጠሪ በአመልካች ማስረጃ የፀረ ሽብርተኝነት አዋጁን አንቀፅ 8 ድንጋጌ በመተላለፍ ለሽብር ተግባር የሚያገለግሉ ንብረቶችን ይዞ የመገኘት ወንጀል ስለመፈፀሙ የተነገረባቸውን በመከላከያ ማስረጃቸው ማስተባበል አልቻሉም በማለት በተከሰሱበት ድንጋጌ የጥፋተኝነት ፍርድ ሰጥቶ ቅጣቱን በመመሪያው መሠረት በማስላት ተጠሪው በስድስት ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ፍርድ ቤቱ ቅሬታው መልስ ሰጭን ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን አከራክሮ ሲያበቃ ከተጠሪ ቤት ውስጥ የተገኙት ሲዲዎች የያዙት ንግግር በቴፕ ተደርጎ ሲደመጥ የኢህአዴግ መንግስት ሙስሊሞችን እንደሚጨቁን፤አልህባሽ የሚባለው የመንግስት ካድሬ እንዳልሆነ፤ነባሩ የእስልምና ሐይማኖት ፈርሶ በአዲስ እንዲተካ እንደሚጠይቅ፤ ውሃብያ ሐይማኖት እንዲስፋፋ እንደሚፈልግ፤መንግስት በሀይማኖት ጣልቃ እንደሚገባ እና የመጅሊስ ነባር አባላት የመንግስት ፈፃሚዎች ስለመሆናቸው የሚገልፅ መልዕክት የያዘ ለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ገልዖ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የሚያቋቁሙት ለሽብርተኝነት ድርጊት መፈጸሚያ እንዲውሉ ተጠሪው ንብረት መያዝን ሳይሆን በወንጀል ህጉ አንቀጽ 486(ለ) ስር የሚሸፈን የሐይማኖት ሁከት የመቀስቀስ ወንጀልን ነው በማለት በዚሁ አግባብ የጥፋተኛነት ፍርድ በመስጠት ቅጣቱን አስልቶ ተጠሪ በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ዳኝነት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይ/ሠ/ችሎት ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ሲሆን አቤቱታው በአጭሩ ተጠሪ የፈጸመው ድርጊት አመልካች ጠቅሶ ያቀረበውን የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 8 ሥር

www.abyssinialaw.com

የተመለከተውን ወንጀል የሚያቋቁም ሆኖ እያለ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያላግባብ ህጉንና ድንጋጌውን በመለወጥ ወስኗል የሚል ነው፡፡

ሰበር አጣሪው ችሎትም መዝገቡን መርምሮ ተጠሪው ጥፋተኛ መባል ያለበት በፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 8 ነው ወይስ በወንጀል ህግ አንቀጽ 486(ለ) ነው? የሚለውን ነጥብ ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ መልስ ያቀረቡ ሲሆን አመልካች የመልስ መልሳቸውን ሊያቀርቡ ባለመቻላቸው መብታቸው መታለፉን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ክርክሩ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ እኛም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ከተጠሪው ቤት የተገኙት ሲዲዎች ለሽብርተኝነት ድርጊት መፈፀሚያነት እንዲውሉ ታስበው የተያዙ ለመሆናቸው በፍሬ ነገር ደረጃ አመልካች አረጋግጧል ወይ? የሚለው ጭብጥ ምላሽ ማግኘት ያለበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ኢትዮጵያ በ2001 ዓ.ም ያወጀችው የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ለሽብር ድርጊት በቂ የህግ ማዕቀፍ ለመስጠት ታስቦ ከመደበኛው የወንጀል ህግ በተሻለ ሁኔታ ከሽብር ጋር የሚገናኙ ድርጊቶች ወንጀል በማድረግ የሽብር ወንጀልን መከላከልና መቆጣጠር ለማስቻል ታስቦ የወጣ አዋጅ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ለክርክራቸው መሠረት ያደረጉት የፀረ ሽብርተኝት አዋጅ አንቀጽ 8 ድንጋጌ ለሽብርተኝነት ድርጊት መፈፀሚያነት እንዲውል ንብረት መያዝ ወይም መጠቀምን ወንጀል አድርጎ ደንግጎታል፡፡ የድንጋጌውን ሙሉ ይዘት ስንመለከት ማንኛውም ሰው የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም ወይም እንዲፈፀም ለማመቻቸት እንደሚውል እያወቀ ወይም እንዲውል በማሰብ ማናቸውንም ንብረት የያዘ ወይም የተጠቀመ እንደሆነ የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአምስት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል በማለት ደንግጓል፡፡

አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ማስረጃ አቅርቦ ያረጋገጣቸው ፍሬ ነገሮች የተጠሪው ቤት ብርበራ ተደርጎ ሲዲዎች መገኘታቸው፤ እነዚህ ሲዲዎች የያዙት መልዕክትም ሲደመጥ የኢህአዴግ መንግስት ሙስሊሞችን እንደሚጨቁን፤አልሀባሽ የሚባለው የመንግስት ካድሬ እንደሆነ፣ ነባሩ የእስልምና ሐይማኖት ፈርሶ በአዲስ እንዲተካ እንደሚጠይቅ፤ ውሃብያ ሐይማኖት እንዲስፋፋ እንደሚፈልግ፤መንግስት በሀይማኖት ጣልቃ እንደሚገባ እና የመጅሊስ ነባር አባላት የመንግስት ተልዕኮ ፈፃሚዎች ስለመሆናቸው የሚገልፅ መልዕክት የያዙ ለመሆናቸው የሚያስረዱ ሲሆኑ ተጠሪው እነዚህን ሲዲዎች የያዟቸውን መልዕክቶችና ሲዲዎችን የሽብርተኝነት ተግባር እንዲፈፀም ለማመቻቸት አስቦ የያዘ ለመሆኑ የሚያረጋግጡ ፍሬ ነገሮች ለመኖራቸው አመልካች

www.abyssinialaw.com

ማስረጃ የመስማትና የማጣራት ሥልጣን ላላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ባቀረቡት ማስረጃ አላረጋገጡም፡፡

ወንጀልና አፈፃጸሙን በተመለከተ በሚደነግገው የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 23(2) ሥር እንደተደነገገው የሚያስቀጣ ወንጀል ተፈፅሟል ለማለት ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፤ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡ በልዩ ሁኔታ በህግ የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሽ ከዞረባቸው ጥቂት ወንጀሎች ውጭ በወንጀል የክርክር ሂደት በበቂና አሳማኝ ሁኔታ ፍሬ ነገርን የማስረዳት ሸክም በዐ/ህጉ ላይ የተጣለ ኃላፊነት ለመሆኑ ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 141 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ አንቀጽ 8 ሥር የሚገኙ ፍሬ ነገሮች የማስረዳት ሸክም በልዩ ሁኔታ ወደ ተከሳሹ የዞረ አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፤ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የማስረዳት ሸክሙን የመወጣት ግዴታ እንዳለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም አመልካች በተጠሪው እጅ ከላይ የተገለፀውን መልዕክት የያዙ ሲዲዎች መገኘታቸውንና በሲዲዎች ያለው መልዕክት ሲደመጥ ከላይ የተገለፀው መሆኑን በማስረዳቱ ብቻ አመልካች የያዛቸው ሲዲዎችም ሆኑ በውስጣቸው የነበሩት መልዕክቶች ለሽብረተኝነት ተግባር ለማመቻቸት የታሰቡ ነበሩ ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የትግራይ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪው ስለመፈጸሙ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች በፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 8 ሥር የሚሸፈን ወንጀልን ያቋቁማሉ በማለት መወሰኑ አመልካች የማስረዳት ሸክሙን ባልተወጣበት ሁኔታ የተወሰነ ስለነበር የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ተጠሪው የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም ወይም እንዲፈፀም ለማመቻቸት እንደሚውል እያወቀ ወይም እንዲውል በማሰብ ማናቸውንም ንብረት የያዘ ወይም የተጠቀመ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ በውጤት ደረጃ የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ይግባኝ በመዝገብ ቁጥር 99191 ሰኔ 20 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 195(2)(ለ)(2) በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 108550

መስከረም 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች - አልማው ወሌ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች - የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን - ዓቃቤ ህግ  አልቀረቡም

ተጠሪ - አቶ ልዑል አዳሙ ብዙነህ --ጠበቃ መአሪፍ ሰዒድ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪው የኮንትሮባንድ ዕቃ የጫነው መኪና ሾፌር እና ባለቤት ከመሆኑም በላይ ወንጀሉ በታወቀበት ጊዜም መኪናውን ያሽከረክር የነበረው እሱ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በነፃ ይሰናበት መባሉ እና፤ መኪናውም የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ ሲንቀሳቀስ የተገኘ ሆኖ እያለ ይለቀቅ መባሉ ከአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 እና 104 አንፃር ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

እንደመረመርነው የክሱ መነሻ ንብረትነቱ የስር 1ኛ ተከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) በሆነውና እራሱ በሚያሽከረክረው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-93060 አ/አ በሆነ FSR መኪና ላይ ሆን ብሎ ህገወጥ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ከ2ኛ ተከሳሽ አቶ ጉሌ እንዳለ (ረዳቱ) ጋር በመተባበር የ3ኛ ተከሳሽ አቶ ወገኔ ወርቅነህ ንብረት የሆኑትን 5 ካርቶን ጥፍር መቁረጫ፤ 3 ብርድ ልብስ እና ሁለት ጎማ ጭኖ መስከረም 4 ቀን 2007 ዓ.ም ከምሽቱ 6፡00 ሰዓት ከሃረር ወደ መሃል አገር ሲጓዝ አዋሽ ጉምሩክ ኬላ በፍተሻ ተይዟል በሚል በሶስቱም ተከሳሾች ላይ የወንጀል ህግ ቁጥር 32(1)(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ ተጠቅሶ ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡

ተጠሪ ድርጊቱ መፈፀሙን ገልፆ ነገር ግን እኔ አልፈፀምኩትም ጥፋተኛም አይደለሁም በማለት ክዶ የተከራከረ ሲሆን፤ 2ኛ ተከሳሽ (ረዳቱ) በበኩሉ ድርጊቱን ፈፅሜያለሁ እቃዉን ጭኛለሁ ኮንትሮባንድ መሆኑን አላወኩም አይቼ ባለመጫኔ ጥፋተኛ ነኝ 1ኛ ተከሳሽ አያውቅም ነበር ብሏል፡፡ 3ኛ ተከሳሽ በበኩሉ ድርጊቱን ፈፅሜያለሁ ንብረቱ የእኔ ነው ጥፍር መቁረጫ ኮንትሮባንድ መሆኑን ባለማወቅ ፈፅሜያለሁ ማወቅ ነበረብኝ ጥፋተኛ ነኝ በማለት አምኗል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የገቢ ረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾችን እንደ ክሱ ድርጊቱን ስለመፈፀማቸው አምነዋል በማለት ባመኑት መሰረት ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት

www.abyssinialaw.com

ወስኗል፡፡ 1ኛ ተከሳሽን በተመለከተ የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ የዓቃቤ ህግ ምስክሮች በወቅቱ ፍተሻ ሲደረግ ተጠሪ የሚያሽከረክረው መኪና ላይ ዕቃውን ማግኘታቸውን ከመመስከራቸው ውጭ እንደ ክሱ አቀራረብ ሆነ ብሎ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት ብሎ የፈፀመው ለመሆኑ አለማረጋገጣቸውን፤ ተከሳሹም ዕቃው መገኘቱን ሳይክድ በእኔ እውቅና አልተጫነም በማለት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ ማሰማቱን፤ የቀረቡት የመከላከያ ምስክሮች በእለቱ ከተከሳሽ ጋር የራሳቸውን መኪና ይዘው የሸንኩርት ጭነት ጭነው ሳይለያዩ ተከታትለው መጓዛቸውን አሰበ ተፈሪ ላይ ከምሽቱ 4:00 ሰዓት ሲሆን አንድ ላይ እራት ሲበሉ ረዳቱ (2ኛ ተከሳሽ) አለመኖሩን እና 3ኛ ተከሳሽ አሰበ ተፈሪ ከተማ ላይ የተሳፈረ መሆኑን፤ 1ኛ ተከሳሽ ዕቃው በፍተሻ ሲገኝበት ጉድ ሰራኝ አሰበ ላይ ተማሪ ነው ብሎ ያሳፈረው ሰው ብሎ ሲናገር እንደነበርና በማያውቀው ሁኔታ እራት በሚበሉበት ሰዓት 2ኛ ተከሳሽ አጋጣሚውን ተጠቅሞ ድርጊቱን መፈፀሙን ማስረዳታቸውን፤ እንዲሁም 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ዕቃውን የጫኑት 1ኛ ተከሳሽ ሳያውቅ እንደነበር የሰጡት የዕምነት ቃል የመከላከያ ማስረጃውን እንደሚያጠናክር፤ ተጭኖ ለነበረው ጎማ የዕጅ በዕጅ ሽያጭ ደረሰኝ መቅረቡን በመጥቀስ ተጠሪ ድርጊቱን ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ያልፈፀመው ስለመሆኑ፤ ይልቁንም ሊጠረጥር ወይም ሊገምት በማይችልበት ሁኔታ ከእውቅናው ውጭ የተፈፀመ መሆኑን ፍርድ ቤቱ አረጋግጧል በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 149(2) መሰረት በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በነፃ የተሰናበተ በመሆኑም የተያዘውን መኪና በተመለከተ በአዋሽ ጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ በአስተዳደር የገንዘብ ቅጣት ተቀጥቶ እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ እና ትዕዛዝ በመቃወም ለአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ በወንጀሉ ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው በመላ ሃሳቡ እና እውቀቱ ለፈፀመው ተግባር እንጂ ከእሱ እውቅና ውጭ ሌሎች ሰዎች በፈፀሙት ተግባር አብሮ ስለነበር ብቻ ኃላፊ እና ተጠያቂ የሚሆንበት ምክንያት የለም፤ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ስለተሰጠ ብቻ በድርጊቱ ምንም አይነት ተሳትፎ ያልነበረውን ባለንብረት በማያውቀውና ባልተመሰከረበት ነገር ጥፋተኛ ማድረግ ስለማይገባና የዓቃቤ ህግን ክስና ማስረጃ በሚገባ ስለተከላከለ ከክሱ በነፃ እንዲሰናበት መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የክልሉ ፍርድ ቤቶች ባሳለፉት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በማለት ለማሳረም ነው፡፡ አመልካች ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ ከፍ ሲል በመግቢያው የተጠቀሰው ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር መልስ የሰጡ ሲሆን አመልካቹም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

www.abyssinialaw.com

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት ውሳኔዎችና አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ተጠሪ ተከላክሏል ተብሎ በነፃ እንዲሰናበት በመወሰኑ፤ እንዲሁም ተሸከርካሪውን በተመለከተ ተጠሪ አስተዳደራዊ ቅጣት ተቀጥቶ እንዲለቀቅለት በተሰጠው ትዕዛዝ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በስር ፍርድ ቤት በማስረጃዎች ከተረጋገጡት ፍሬ ጉዳዮች እና አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

አመልካች በቅሬታቸው ክሱን አስረድተው እያለ እና ተጠሪም የቀረበበትን ክስ በአግባቡ ባልተከላከለበት ሁኔታ በነፃ መሰናበቱ እንዲሁም ተሸከርካሪው በተጠሪ ሲሽከረከር የነበረ ከመሆኑም ሌላ የስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጥፋተኛ መባላቸው በመኪናው የወንጀል ድርጊቱ መፈፀሙን ስለሚያረጋግጥ በአዋጁ አንቀፅ 104 መሰረት የውርስ ትዕዛዝ ለመስጠት ከበቂ በላይ ምክንያት እያለ ተሸከርካሪው እንዲለቀቅ ትዕዛዝ መስጠቱ የህግ ስህተት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው የመኪናው ሹፌር እና ባለቤት ብሆንም ተዋዉዬ በህጋዊ መንገድ የጫንኩት ሽንኩርት ብቻ መሆኑን አጣርቼ ከተጓዝኩ በኂላ የስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የእኔን አለመኖር ሽፋን በማድረግ ደብቀው እና እንዳይታይ በማድረግ የኮንትሮባንድ ዕቃውን መጫናቸውን የስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃዎች እና 2ኛና 3ኛ ተከሰሳሾ በዕምነት ከሰጡት  ቃል አረጋግጠው ያሳለፉት ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለ ውሳኔው ሊፀና ይገባል ብለዋል፡፡

በመሰረቱ የወንጀል ተጠያቂነት የሚኖረው በወንጀል ህጉ አንቀፅ 23(2) ሥር የተመለከቱት ህጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ሲሆን  በተያዘው ጉዳይም ሞራላዊ ፍሬ ነገሩ የተሟላ መሆን ያለመሆኑን በመመልከት ውሳኔ መስጠት የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 57 እንደተመለከተው ለድርጊቱ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት አንድ ወንጀል ካላደረገ በቀር በወንጀል ጥፋተኛ የማይሆን ሲሆን፤ የፈፀመው ድርጊት በህግ የሚያስቀጣ ቢሆንም ምንም ጥፋት ያላደረገ ሆኖ ሲገኝ ሊፈረድበት አይገባም፡፡ ከዚህም ሌላ በቸልተኝነት ወንጀል ማድረግን በተመለከተ ማንም ሰው በቸልተኝነት የወንጀል ተግባር አድርጓል የሚባለው ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም በሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን፤ ወይም ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ስለመሆኑ ከወ/ህጉ አንቀፅ 59(1) ግልፅ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከፍ ሲል እንደተገለፀው በአመልካች ምስክሮች የተረጋገጠው ተጠሪ በሚያሽከረክረው መኪና ላይ ዕቃው በፍተሻ መገኘቱ ብቻ ስለመሆኑ፤ ከዚህ ውጭ እንደ ክሱ አቀራረብ ሆነ ብሎ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት ብሎ የፈፀመው ለመሆኑ

አመልካች በማስረጃ አለማረጋገጡን፤ በአንጻሩ ተጠሪ በመከላከያዎቹ በእለቱ የሽንኩርት ጭነት ጭነው ከሌሎች አሽከርካሪዎች ጋር ሳይለያዩ ተከታትለው ይጓዙ እንደነበር፤ አሰበ ተፈሪ ላይ ከምሽቱ 4:00 ሰዓት ሲሆን አንድ ላይ እራት ሲበሉ ረዳቱ (2ኛ ተከሳሽ) ተጠሪ ያለመኖሩን አጋጣሚ ተጠቅሞ ተማሪ ነው በማለት 3ኛ ተከሳሽን ያሳፈረ መሆኑን፤ 1ኛ ተከሳሽ ዕቃው በፍተሻ ሲገኝበት ጉድ ሰራኝ አሰበ ተፈሪ ላይ ተማሪ ነው ብሎ ያሳፈረው ሰው ብሎ ሲናገር እንደነበር፤ በአጠቃላይ ዕቃው ተጠሪ በማያውቀው ሁኔታ በጉዞ መሃል ተደብቆ መጫኑን የስር ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡

ከዚህ የክርክር ሂደት መገንዘብ የሚቻለው ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በህጉ ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ድርጊቱን ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ያልፈፀመው ስለመሆኑ፤ በአንፃሩ ከነበረው ሁኔታ እና ከተጠሪ የሹፌርነት ኃላፊነት አንፃር ሊጠረጥር ወይም ሊገምት በማይችልበት ሁኔታ ከእውቅናው ውጭ የተፈፀመ መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ መስጠታቸውን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተጠሪ አስቦ ወይም በቸልተኝነት ሊባል በሚችል መልኩ ጥፋት መፈፀሙን የሚያሳይ አይደለም፡፡

በመሆኑም ተጠሪ አስቦ ወይም በቸልተኝነት የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት ማድረጉ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ጥፋተኛ ሊባል ይገባ ነበር በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር የወንጀል ህጉን አንቀጽ 23(2)፤ 57፤ 58 እና 59 ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

ሌላው የክርክር ነጥብ ተሽከርካሪውን በተመለከተ በተሰጠው ትዕዛዝ ተፈፀመ የተባለውን የህግ ስህተት የሚመለከት ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪ ከቀረበባቸው የኮንትሮባንድ ወንጀል ክስ በነፃ ተሰናብተዋል፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነውና በተጠሪ ሲሽከረከር የነበረው መኪና የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ መገኘቱ ተረጋግጦ 2ኛ ተከሳሽ (ረዳቱ) እና 3ኛ ተከሳሽ (ባለንብረቱ) ጥፋተኞች ተብለው የተቀጡ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104 መሠረት መኪናው መወረስ ነበረበት በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ ተከሳሽ በነፃ የተሰናበተ እንደሆነ ተሽከርካሪው ሊወረስ የሚቻልበት ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 104/3/ሀ/ ስር በተለየ ሁኔታነቱ (exceptional situation) ተመልክቷል፡፡ የተለየ ሁኔታነቱ መሰረታዊ ምክንያት ደግሞ የንብረት ውርስ ከወንጀል ቅጣቶች አንዱ መሆኑ እና ቅጣት የሚመጣው የወንጀል ጥፋተኝነትን ተከትሎ መሆኑ ነው፡፡ ለዚህም ነው ጥፋተኛ ባይባልም ንብረቱ የሚወረሰው 'ስለድርጊቱ አፈፃፀም ሁኔታ የሚያስረዳ አጥጋቢ ማስረጃ መቅረቡንና ፍ/ቤቱ አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው' የሚወሰን ስለመሆኑ በድንጋጌው ይዘት የተመለከተው አዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ያሻሻላቸው እና አዲስ ያካተታቸው ድንጋጌዎች ይዘትም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ በዚህ መሰረት የማጓጓዣ ባለቤቶች ጥፋት ሳይፈፅሙ በመጓጓዣው ወንጀል በመፈፀሙ ብቻ ተጥሎ የነበረው የገንዘብ ቅጣት ሁሉ እንዲቀር ተደርጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

ከዚህ አንፃር በዚህ መዝገብ የቀረበውን ክርክር ስንመለከት የስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጥፋተኛ ሆነው የተቀጡት በመኪናው የኮንተሮባንድ ዕቃ ጭነው በመገኘታቸው ሲሆን በስር ፍ/ቤት በቀረበው እና በተረጋገጠው ፍሬ ነገር ተጠሪ በወንጀሉ አፈፃፀም ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሃሳብ ወይም ቸልተኝነት ነበረው ሊያሰኝ የሚችል ሁኔታ እንዳልነበር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አንፃር በህጉ አነጋገር የተጠሪ ንብረት የሆነው መኪና እንዲወረስ ለማድረግ ፍ/ቤቱን ሊያሳምን የሚችል ማስረጃ በአመልካች በኩል ያልቀረበ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም የተጠሪ መኪና እንዲወረስ በአመልካች የቀረበው ጥያቄ በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ባለማግኘቱ በህጉ ረገድ መሠረታዊ የሆነ ስህተት ተፈፅሟል ማለት አልተቻለም፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአፋር ብ/ክ/መንግስት የገቢረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03484 በ16/03/2007ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ 3079 በ27/04/2007 ዓ.ም የተላለፈው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195(2) (ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ጥር 12 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.101003

ህዳር 02 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- መክብብ ሞገስ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነውን መሰረታዊ ጭብጥ አመልካች በልዩ ወንጀል ተካፋይነት በግብረአበርነት ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ከተወሰነ በኋላ ከሱ ጋር በግብረአበርነት ተከሰው ጥፋተኛ የተባሉ ተከሳሾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የተጣለባቸው ቅጣት ከተሻሻለ እና በግብረአበርነት ጥፋተኛ የተባለው አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ግን በአጣሪ ችሎት አያስቀርብም ተብሎ በመዘጋቱ ምክንያት ለግብረአበሮቹ የተደረገው የቅጣት ማሻሻያ አመልካችን ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆን ያለመሆኑን ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.196፣አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና አስገዳጅ የሰበር ውሳኔዎች አንፃር አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ጉዳዩ የወንጀል ክስ የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ አመልካችን ጨምሮ በሰባት ግልሰቦች ያቀረበው ክስ ነው ፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ 6ኛ ተከሳሽ ሲሆን በፈፀመው የወንጀል ድርጊትም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና(ለ) ፣33 እና 407(1)(ሐ) (2) ሥር በአንድ ክስ በልዩ ወንጀል መፈፀሙን ተካፋይነት በግብረአበርነት ሥልጣንን ያለአግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል መፈፀሙ ተረጋግጦ ከ2ኛ ፣3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ጋር ጥፋተኛ ነው ተብሏል፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ቅጣት ለመወሰን

www.abyssinialaw.com

ተፈፃሚነት ያለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሆኑን ግንዛቤ በመውሰድ ቅጣት ያሰላ ሲሆን አመልካች በአንድ የወንጀል ድርጊት (ክስ) ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ መነሻ ቅጣቱ 8 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራትና ብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ) በመያዝ የእስራት መነሻ ቅጣቱ በእርከን 27 መቀጮ ደግሞ በእርከን 9 ፍቅድ ሥልጣን የሚወድቅ ነው በማለት በአመልካች በኩል ከቀረቡ የቅጣት ማቅለያዎች አራቱ ተቀባይነት ያገኙ ስለመሆኑ ፤በዚህም በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ አንድ እርከን ዝቅ የሚል በመሆኑ በእርከን 23 የሚወድቅ መሆኑን በመግለጽ በፍቅድ ሥልጣኑ ከተቀመጠው 6 ዓመት እስከ 7 ዓመት ከ2 ወር ፣መቀጮውም የወ/ሕ/ቁ.90(2) መሰረት በማድረግ በስድስት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 25,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ተወስኗል።

አመልካች በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/መ/ቁ.97541 ያቀረበው ይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ውድቅ የተደረገ ሲሆን በመቀጠል ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.101003 ያቀረበው የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የለበትም ተብሎ ሰኔ 27 ቀን 2006 ዓ.ም መዝገቡ ለሰበር ችሎት አይቀርብም በማለት ትዕዛዝ ተሰጥቶበታል ። አመልካች ሰኔ 15 ቀን 2007 ዓ.ም ለዚህ ችሎት ባቀረበው አቤቱታ ከሱ ጋር በግብረ አበርነት ጥፋተኛ የተባሉ ግለሰቦች ጉዳያቸው በሰበር ሰሚ ችሎት ከታየ በኃላ በሰ/መ/ቁ.101225፣102826 እና 112435 በተሰጠው ውሳኔ ቅጣቱ መሰላት ያለበት በአዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ሳይሆን በቀድሞው መመሪያ ቁጥር 1/2002 ነው ተብሎ ቅጣት ተሻሽሎላቸው የተወሰነ በመሆኑ እሱም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.196(1) መሰረት ተጠቃሚ እንዲሆን አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የተዘጋው በራሱ ስሕተት ሳይሆን ከእርሱ ውጭ በሆነ ጉዳይ በመሆኑ በድጋሚ እንዲታይለት ጠይቋል ። ይህ ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ ከመረመረ በኃላ ጉዳዩን ለአጣሪ ችሎት ከሚያቀርብ በስተቀር በችሎቱ እንደማይስተናገድ ሰኔ 24 ቀን 2007 ዓ.ም ትዕዛዝ ተሰጥቷል። አመልካች አቤቱታውን ለአጣሪ ችሎት በድጋሚ በማቅረቡ ሐምሌ 09 ቀን 2007ዓ.ም ትዕዛዝ ተሰጥቷል አጣሪ ችሎትም አመልካች ከሌሎች ግብረአበሮቹ ጋር ተከሶ እንደነበር በመግለጽ "በአመልካችና በወንጀል ግብረ አበሮች ላይ የቀረበባቸው ክስ የተጠቀሰባቸው የሕግ አንቀጽና የተላለፈባቸው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ በሥር ፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ ሲጓዝ ቆይቶ በሰበር ደረጃ የግብረ አበሮቹ ጉዳይ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ተመርምሮ ቅጣቱ መሠላት የነበረበት ወንጀሉ በተፈጸመበትና ክስ በቀረበበት ወቅት ሥራ ላይ በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ እንጂ በአዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሆን አልነበረበትም ተብሎ ቅጣት ሲቀነስላቸው የአመልካች አቤቱታ ወደ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ ባለመደረጉ በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰነበትን ቅጣት እንዲፈጽም እየተደረገ ያለበት ሁኔታ አመልካቹ በሕገ መንግስቱ

www.abyssinialaw.com

የተቀመጠው በሕግ ፊት እኩል የመታየት መብቴ ተጥሷል በማለት ከጠቀሰው የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 25 እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.196 አንፃር ሊታይ ስለሚገባው እና በተመሳሳይ መንገድ በሰበር መ/ቁ 101056 ቀርቦ በመመርመር ላይ ካለው ጉዳይ ጋር እና ከዚህ ቀደም ቀርበው ተመርምረው በሰበር መዝገብ ቁጥር 101225 እና 102826 ላይ የተሰጠው ውሳኔ አመልካችን ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆን አለመሆኑን "ተጠሪን ያስቀርባል ተብሏል፡፡ ተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በ 05/12/2007 ዓ.ም መልስ ያቀረበ ሲሆን ዋናው ይዘቱ ፡- የአመልካች አቤቱታ አስቀድሞ በሰበር አጣሪ ችሎት ውድቅ እንደተደረገ ፣የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ.156 ለአመልካች ይጠቅማል የተባለው ውሳኔ ይግባኝ ያልጠየቀ ከሆነ እንጂ ይግባኝ የጠየቀ ከሆነ ተጠቃሚ እንደማይሆን ፣ውሳኔው ከእኩልነት መርህ ጋር እንደማይያያዝ ፣አጣሪ ችሎቱ የራሱን ብይን መልሶ መሻር እንደማይችል በሰ/መ/ቁ.101225 እና 102826 ላይ የተሰጡ ውሳኔዎች ለአመልካች ተፈፃሚ የሚሆንበት የሕግ አግባብ እንደሌለ በመግለጽ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ አመልክቷል፡፡ አመልካች አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ መስከረም 21 ቀን 2008 ዓ.ም አቅርበዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የሰ/መ/ቁ.101225 እና የሰ/መ/ቁ102826 በማስቀረብ የተመለከተ ሲሆን ፤በመጀመሪያው መዝገብ ከአመልካች ጋር ግብረአበር ሆኖ የተከሰሰው አቶ ገዛኸኝ አድገህ(የሥር 5ኛ ተከሳሽ ) ፤በሁለተኛው መዝገብ አቶ ያረጋል አይሸሹም (የሥር 1ኛ ተከሳሽ) ያቀረቡዋቸው የሰበር መዝገቦች ሲሆኑ ጉዳዩን የመረመረው ይህ ችሎትም ሁለቱም ተከሳሾች ያቀረቡት ጥፋተኛ አይደለንም የሚለውን ክርክር ውድቅ በማድረግ በቅጣት ረገድ ግን ተፈፃሚነት ያለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ወንጀሉ ሲፈጸም ወይም ክስ ሲቀርብ ሥራ ላይ የነበረው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2002 ስለመሆኑ፣የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22 እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 6 እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.95438 በሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት በማድረግ የቅጣት ማቅለያ ዋጋ አሰጣጥ ላይ ተመርኩዞ አቶ ገዛኸኝ አድገህ የስድስት አመት ጽኑ እስራት በማሻሻል በሦስት ዓመት ጽኑ እስራት ፣አቶ ያረጋል አይሸሹም የሰባት ዓመት ጽኑ እስራት በማሻሻል በሦስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የገንዘብ መቀጮ ግን ሳይነካ ማጽናቱን የውሳኔ ግልባጮቹ ያሳያሉ፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም አመልካች በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር እና ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ አመልካች እና ግብረአበሮቹ ጥፋተኛ ተብለው ለጉዳዩ ቅጣት ሲወሰን ተፈፃሚነት

www.abyssinialaw.com

የነበረው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አግባብነት እንዳለው ተጠቅሶ ቅጣት የተወሰነባቸው ስለመሆኑ የሚያከራክር ሆኖ አልተገኘም ፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች እና ሌሎች ግብረአበሮቹ ተገቢነው ያለውን ቅጣት ከወሰነ በኃላ በተናጠል ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ አቅርበው ተቀባይነት ባለማግኘቱ ቀጥሎ በተናጠል ለሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው በሥር ፍርድ ቤት 1ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች የነበሩት ለሰበር ችሎት የቀረበላቸው ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ግን አያስቀርብም ተብሎ መዘጋቱ በመዝገቡ የተያያዘው ትዕዛዝ አረጋጋጭ ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁ101225 እና 102826 የቀረቡለትን የሰበር አቤቱታዎች ከመረመረ በኃላ የጥፋተኝነት ውሳኔውን በማፅናት በቅጣት ረገድ ግን ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው የቀደሞ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ነው በማለት ቅጣቱን አሻሽሎ ወስኗል፡፡ የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ውድቅ በመደረጉ ምክንያት ግብረአበሮቹ ያገኙትን የቅጣት ማሻሻያ ማግኘትና መጠቀም አለመቻሉን መዝገቡ ያሳያል፡፡

በመሰረቱ ቅጣት ሲወሰን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 1፣4፣41፣88 እና የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረታዊ ድጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የተከተለ ሊሆን ይገባል፡፡ በአንድ የወንጀል ድርጊት በዋና ወንጀል አድራጊነት ወይም ግብረ አበርነት የተሳተፎ ተከሳሾች በግል ሁኔታዎች ማለትም የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ካለ ሊኖር የሚችለው ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ ለተመሳሳይ የወንጀል አፈፃፀምና የወንጀል ተሳትፎ ተመጣጣኝና ተመሳሳይ ቅጣት ሊወሰን እንደሚገባ ከኢፌዲሬ ህገ መንግስት አንቀጽ 25 የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 4 እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ 2/2006 አንቀፅ.3.2 ሥር ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው ፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች እና ሌሎች ግብረ አበሮቹ የተጠየቁበት የወንጀሉ ሕግ አንቀጽ ልዩነት የሌለው ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ከአመልካች ጋር በጋራ ተከሰው ጉዳያቸው በዚህ ችሎት ከታየ በኃላ በሰ/መ/ቁ101225 እና 102826 በተሰጠው ውሳኔ ተፈፃሚነት ያለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የቀድሞ መሆኑን በመለየት ቅጣት አሻሽሏል ፡፡ በአመልካች እና በሌሎች ግብረ አበሮቹ የተፈጠረ ልዩነት በወንጀል አፈፃፀም የተፈጠረ ሳይሆን በቅጣት ማቅለያዎች ብዛትና ዋጋ ብቻ ነው ፡፡ የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ውድቅ በመደረጉ በነባሩ /የቀድሞ/የቅጣት መመሪያ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም ፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ነባሩ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ለተከሳሹ የሚጠቅም ከሆነ የቀደም የቅጣት መመሪያ ሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ የተፈፀመ ወንጀል ወይም የቀረበ ክስ ከሆነ ቅጣቱ የሚወሰነው አዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ተፈፃሚ በሆነበት ጊዜ ቢሆንም የቀድሞ የቅጣት መመሪያ ለተከሳሹ በሚጠቅም አግባብ መተርጐም እንዳለበት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 6 ደንጋጌዎችን በመጥቀስ በሰ/መ/ቁ.95438 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ይህ ገዥ ውሳኔ በየትኛውም እርከን ባሉ

www.abyssinialaw.com

ፍርድ ቤቶች ተፈፃሚነት እንዳለው በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) ሥር ተደንግጓል ፡፡ አመልካች አራት ማቅለያዎች ያሉት በመሆኑ ቅጣቱ በነባሩ የቅጣት መመሪያ ቢሰላ ትርጉም ያለው የቅጣት ለውጥ እንደሚያመጣ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የአመልካች የሰበር አቤቱታ በአጣሪ ችሎቱ አያስቀርብም የተባለ በመሆኑ አመልካች በነባሩ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቅጣቱ ቢሰላ ሊያገኝ የሚችለው የእስራት ማሻሻያ ማግኘት አልቻለም፡፡

የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ በ 1954 የታወጀ ከመሆኑ አንፃር ጉዳዮች በይግባኝ ከታዩ በኃላ ለሰበር ቀርበው የሚታዩበት ሥርዓት ያልተዘረጋ ቢሆንም የሥነ ሥርዓት ሕጉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ(80(3)(ሀ) የተመለከተው የሰበር ሥርዓት መሠረታዊ ዓላማና ግብ በሚያሳካ መንገድ ሊተረጎም የሚገባው ነው፡፡ ከተያዘው ጉዳይ ተመሳሳይነት ያለው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.101056 ሐምሌ 30ቀን 2007ዓ/ም በሰጠው ገዥ ውሳኔ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.196 ድንጋጌ አሁን ላለው የሰበር ሥርዓት ለመጠቀም ካለው የሰበር ችሎት አደረጃጀትና አሰራር ጋር በሚጣጣምና የሰበርን መሰረታዊ ዓላማ ሊያሳካ በሚችል መንገድ መተርጎምና ስራ ላይ ማዋል እንደሚጠይቅ ገልጽ አድርጓል፡፡ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ196 ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት የተፈረደባቸው ብዙ ሰዎች ሆነው አንዱ ብቻ ይግባኝ ጠይቆ ቅጣቱ ቢሻሻልና የተሻሻለው ቅጣት ይግባኝ ላልጠየቁ ጥፋተኞችም የሚጠቅም ከሆነ ይግባኝ ላልጠየቁ ጥፋተኞችም ተፈፃሚነት እንዳለው የሚያመለክት ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በነባሩ የቅጣት መመሪያ መሰረት ቅጣት ሊቀነስለት እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም ከአመልካች ጋር በግብረአበርነት የተከሰሱ ግለሰቦች ለሰበር ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ ቅጣት ተቀንሶላቸዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.101056 በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ጉዳዩ በድጋሚ ታይቶ ቅጣቱን በቀደም የቅጣት መመሪያ ተሰልቶ ተጠቃሚ ሊሆን እንደሚገባ ተረድተናል፡፡

አመልካች በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ከተባለ በኃላ መነሻ ቅጣቱ 8 ዓመት ከ 6 ወር ጽኑ እስራት ሁኖ ተይዟል ፡፡ ይህ መነሻ ቅጣት በእርከን 27 የሚወድቅ ነው ፡፡ በአዲሱ የቅጣት መመሪያ እያንዳንዱ ማቅለያ 1 እርከን ብቻ እንደሚቀንስ በመመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 23/1 እና 4 ስር ተመልክቷል፡፡ቅጣቱ በቀድሞ መመሪያ ቁጥር 1/2002 ቢሰላ በእያንዳንዱ ማቅለያ 3 እርከን እንደሚቀነስ ከዚህ መመሪያ አንቀጽ 16(7) የምንገነዘበው ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ካቀረባቸው ማቅለያዎች አራቱ ተቀባይነት አገኝቷል፡፡ ቅጣቱ አመልካች ካቀረባቸው እና በሥር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ካገኙ ማቅለያዎች አንፃር ቅጣቱ ሲሰላ ከእርከን 27 ወደ እርከን 15 ዝቅ የሚል ሲሆን በዚህ እርከን ያለው የፍርድ ቤት ፍቅድ ሥልጣን ከ 2 ዓመት ከ 9 ወር እስከ 3 ዓመት ከ3 ወር ነው፡፡ ይህ ችሎትም አመልካችን ሊያርምና ሊያስተምር ይችላል ብሎ ያመነበት በዚህ ፍቃድ ስልጣን ከተቀመጠዉ ቅጣት በሶስት አመት ጽኑ እስራት ሊቀጣ ይገባል

www.abyssinialaw.com

ብለናል መቀጫ በተመለከተ የስር ፍ/ቤት የግራቀኙን አስተያየት መሰረት አድርጎ ተገቢ ነው ያለውን መወሰኑን ስለተገነዘብን የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አመልካች ከእሱ ጋር ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅጣት እንደ ተሻሻለላቸው ተከሳሾች ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22፣25፣የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 4 እና 6 እንዲሁም የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ይዘትና መንፈስ በአግባቡ ተፈፃሚ የሚያደርግ መሆኑን ስለ ተገነዘብን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 196(1) መሰረት በአመልካች ላይ የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አሻሽለን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 112435 በቀን 02/05/2006 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ይግባኝ ችሎት በወ/መ/ቁ.97541 በቀን 8/7/2006 የሰጠው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 196 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ተሻሽሏል ፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ ችሎት ሰኔ 27 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በዚህ ፍርድ ተለውጧል፡፡
3. አመልካች በዚህ ጉዳይ ተጠርጥሮ እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በሦስት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስነናል ፡፡ ገንዘብ መቀጮ አልተነካም ፡፡
4. የቅጣት ውሳኔ የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንደያስፈጽም ለክፍሉ ማረሚያ ቤትና ለአመልካች ይድረሳቸው ብለናል፡፡ ይፃፍ ፡፡ መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 131863

ህዳር 8 ቀን 2009 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጠታ

ክፍለጽዮን ማሞ

ጳውሎስ አርሺሶ

**አመልካች፡-** መሐመድ እንድሪስ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሀዋሳ ቅርንጫፍ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በዋስ ቢለቀቅ ቀነ ቀጠሮውን አክብሮ ሊቀርብ፣ስለማይችል በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ መብቱ ተነፍጎ በማረሚያ ቤት እንዲቆይ በማለት የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ብይን አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም /የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የጉዳዩ መነሻ ተጠሪ አመልካች አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168/2/ በመተላለፍ ንብረትነቱ የደርባን ትራስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በሆነ የሰሌዳ ቁጥር 430 Volvo መኪና የቀረጥና ታክስ መጠናቸው ብር 88,613.33 /ሰማንያ ስምንት ሺ ስድስት መቶ አስራ ሶስት ብር ከሰላሳ ሶስት ሳንቲም/ የሆኑ እቃዎቹን በመጫን ከዲላ ወደ ሀዋሳ መስመር ሰኔ 14 ቀን 2008 ዓ/ም ይዞ ሲጓዝ የተያዘ በመሆኑ የኮንትሮ ባንድ ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡
2. አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ እኔ ረመዳን ፆም ጾሜ እያፈጠርኩ እያለሁ፣ ረዳቱ ሳላየው የጫናቸው እቃዎች ስለሆነ ጥፋተኛ አይደለሁም፡፡ የዋስ መብቴ ይከበርልኝ በማለት

www.abyssinialaw.com

ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ የአመልካችን በዋስትና የመለቀቅ ጥያቄ እቃወማለሁ፡፡ ዋስትናውን የምቃወመው ተከሳሹ /አመልካች/ በመታወቂያው ላይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር 2654 እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን በመንጃ ፈቃድ ላይ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የቤት ቁጥር 352 እንደሆነ የተገለጸ በመሆኑ ተከሳሹ ሆነ ብሎ አድራሻውን የሚለዋውጥ በመሆኑ በቀጠሮ ቀን ላይ ሊቀርብ ይችላል ብለን ስለማናምን የዋስትና ጥያቄው ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዐቃቤ ህግን መቃወሚያ በመቀበል አመልካች የተለያየ አድራሻ ያለው በመሆኑ ላይቀርብ ይችላል በማለት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡

3. አመልካች ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን አጽንቶታል፡፡ አመልካች የመንጃ ፈቃድ ያወጣሁት በ1992 ዓ/ም ነው፡፡ በዚያ ጊዜ የምኖርበት የነበረው ቤት ለቅቄዋለሁ፡፡ ደርባን ትራንስፖርር ኃ/የተ/የግል ማህበር ስቀጠር የምኖርበት የነበረው አድራሻ ደግሞ ከስድስት አመት በፊት ስኖርበት የነበረው ነው፡፡ አሁን የምኖረው በሌላ ቦታ ሲሆን ይህንን አድራሻዬን ለመርማሪ ፖሊስ አስመዝግቢያለሁ፡፡ ስለዚህ በተለያየ ጊዜ ከተለያየ ቦታ መኖሬ በቀጠሮው ቀን ሊቀርብ አይችልም ከሚል መደምደሚያ ላይ የማያደርስ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን ሊሻርልኝ ይገባል በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ አመልካች ሶስት የተለያዩ አድራሻዎች ያሉት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካቹን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በወንጀል የተከሰሰው በዋስትና ወረቀት ተለቅቆ ጉዳዩን የመከታተል መብት ያለው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 16 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ የምንገነዘበው በወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው በዋስ መለቀቅ መሰረታዊ መብት ሲሆን ህግ አውጭም በልዩ ሁኔታ በህግ በደነገጋቸው ምክንያቶችና ፍርድ ቤቶች የሚቀርብላቸው ክርክር መረጃና ማስረጃ በሚሰጡት ብይን የተከሰሰ ሰው በዋስ የመለቀቅ መብቱ የሚነፈግበት ሁኔታ እንዳለ መገንዘብ ይቻላል፡፡

5. አመልካች የተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ በዋስ የመለቀቅ መብቱን የሚገድብ አይደለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በዋስ ለመለቀቅ ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 67/ሀ/ በመጥቀስ ነው፡፡ ድንጋጌው ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን በማክበር በቀነ ቀጠሮው ሊቀርብ የማይችል መሆኑን

www.abyssinialaw.com

ፍርድ ቤቱ ካመነ፣ የዋስትና ጥያቄውን ውድቅ ለማድረግ የሚችል መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚደርሰው በዘፈቀድ አይደለም፡፡ ዐቃቤ ህግ ተከሳሹ ቀጠሮውን አክብሮ ሊመጣና የዋስትናውን ግዴታ ሊያከብር አይችልም ከሚል መደምደሚያ ላይ ፍርድ ቤቱ ሊደርስባቸው የሚችሉ በቂ ምክንያትና መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

6. በያዝነው ጉዳይ አመልካች የመንጃ ፈቃድ ያወጣው 1992 ዓ/ም መሆኑን በዚያን ወቅት ይኖርበት የነበረውን አድራሻ የለቀቀ በመሆኑ አሁን ከሚሰራበት ድርጅት ሲቀጠር ይኖርበት የነበረው አድራሻ ከበፊቱ የተለየ መሆኑን፣ የአመልካችን መንጃ ፈቃድና የመስሪያ ቤት መታወቂያ ካርድ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በ2008 ዓ/ም በተሰጠው የቀበሌ ኗሪነት መታወቂያ ካርድ ላይ የተገለጸው አድራሻ ከስድስት አመት በፊት ደርባን ትራንስፖርት ሲቀጠር ይኖርበት ከነበረው አድራሻ የተለያየ መሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክር ተገንዝበናል፡፡ አመልካች የመንጃ ፈቃድ ሲያወጣ፣ ደርባን ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲቀጠርና አሁን የሚኖረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለያየ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳና የቤት ቁጥር መሆኑ አመልካች ቋሚ አድራሻ የለውም ከሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡

7. የመኖሪያ ቤት ከግለሰብ ተከራይተው የሚኖሩ ሰዎች፣ በአመታት ውስጥ ሳይሆን በወራት ወይም በቀናት ልዩነት የተከራዩትን ቤት በተለያየ ምክንያት ለቀው በሌላ ክፍለ ከተማ፣ ሌላ ወረዳ ሌላ ቤት ተከራይተው የሚኖሩ መሆኑንና በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የመኖሪያ ቤት እጥረት መኖሩ፣መንግስት በፖሊሲዎቹና ስትራቴጂዎች በግልፅ ያመነውና የአዲስ አበባ የቤቶች ኮንስትራክሽን ልማት ኤጀንሲ በአዋጅ በመቋቋም የጋራ መኖሪያ ቤቶች መምሪያ ቤቶች በመገንባት ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት እያደረገ መሆኑ በግልጽ የሚታወቅና ማስረጃ እንዲቀርብለት የማያስፈልግ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች መንጃ ፈቃድ ሲያወጣ የዛሬ አስራ አምስት አመት ይኖርበት የነበረውን አድራሻ አስመዝግቧል፡፡ ይህንን መኖሪያ አድራሻው ከስድስት አመት በፊት ደርባን ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲቀጠር፣ የለቀቀው መሆኑን በመግለጽና አዲሱን አድራሻውን ለመስሪያ ቤቱ አሳውቋል፡፡ ባሁኑ ወቅት የሚኖርበት አድራሻ በመ/ቤት ሲቀጠር ካስመዘገበው አድራሻ የተለየ መሆኑን የሚያረጋግጥ የቀበሌ መታወቂያ ማቅረቡ፣ አመልካች በአድራሻው ተፈልጎ እንዳይገኝ ሆነ ብሎ የፈጠረው ዘዴ ሳይሆን፣ አመልካች የራሱ የሆነ ቋሚ መኖሪያ ቤት ስለሌለው በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወሩና ቤት እየተከራየ የኖረ መሆኑን እውነታ /ፍሬ ነገር/ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

8. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በተለያየ ክፍለ ከተማዎች፣ ወረዳዎች በተለያዩ ጊዜ እየተዘዋወረ ቤት እየተከራዩ የሚኖሩ ሰዎች፣ በዋስ ቢለቀቁ ፣የዋስትና ጉዳያቸውን አክብረው በቀነ ቀጠሮው ቀን ሊቀርቡ አይችሉም የሚለውን መቃወሚያና መከራከሪያ ፣ሰዎች አዲስ አበባ ውስጥ የራሳቸው የሆነ የመኖሪያ ቤት ስለሌላቸው ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ ቤት እየተከራዩ የሚኖሩ በመሆናቸው ምክንያት ብቻ የዋስትና መብታቸው እንዳይፈቀድ የሚጠይቅ፣ የሰዎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በአዲስ አበባ ከተማ አንድ ቋሚ የሆነ አድራሻና መኖሪያ ቤት ስለሌላቸው ብቻ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 6 የተረጋገጠላቸው በዋስ የመለቀቅ መብት እንዲነፈግ የሚጠይቅ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 25 የተደነገገውን በሕግ ፊት እኩል የመሆንና እኩል የሕግ ጥበቃ የማግኘት መብትን የሚጥስ መቃወሚያና መከራከሪያ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው መቃወሚያ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች በተለያየ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለያዩ ክፍለ ከተማዎች፣ ወረዳዎችና ቤቶች ውስጥ የኖረ መሆኑን የሚያረጋግጡ ሰነዶች ማለትም የመንጃ ፈቃድ፣ የሚሰራበት መስሪያ ቤትና የመታወቂያ ካርድና የቀበሌ ኗሪዎች መታወቂያ ይዞ መገኘቱ አመልካች በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ በቀነ ቀጠሮው ሊቀርብ አይችልም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 69/ሀ/ ድንጋጌዎች ቋሚ የመኖሪያ ቤት ባለመኖሩ ምክንያት በተለያየ ጊዜ የተለያየ ቦታ እየተዘዋዋረ ቤት እየተከራየ መኖሩን መነሻ በማድረግ ብቻ ተከሳሹን የዋስትና መብቱን ለመንፈግ ታስቦ የተደነገገ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በዋስትና ለመለቀቅ የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 6 እና የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 69/ሀ/ ከተደነገገው ውጭ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነዉ በማለት ወስነናል፡፡

9. አመልካች የተከሰሰበት የሕግ ድንጋጌ በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ መብትን የማያስከለክል በመሆኑና ተጠሪ አመልካች በዋስትና እንዳይለቀቅ ያቀረበው መቃወሚያና መረጃ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 69/ሀ/ መሰረታዊ ይዘትና አላማ ውጭ በመሆኑ፣ አመልካች ለብር 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ የሚበቃ ዋስ አቅርቦ ወይም ገንዘብን አስይዞ በዋስ ተለቅቆ ሊከራከር ይገባል በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 75 መሰረት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 39554 ሰኔ 28 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

www.abyssinialaw.com

በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 68379 ሐምሌ 12 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

2. አመልካች ብር 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ በማስያዝ ወይም ለዚህ ገንዘብ የሚበቃ ዋስ በማቅረብ የተከሰሰበትን ወንጀል በዋስ እያቀረበ ይከራከር በማለት ወስነናል፡፡ ውሳኔው ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.118130

ህዳር 30 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡-ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ህፃን አድማሱ አገዘ--ከወልዲያ ማረሚያ ቤት ጉዳይ የምትከታተል እህቱ እየሩሳሌም አገዘ ቀርባለች

ተጠሪ፡-የአማራ ክልል ዓቃቤ ህግ አቶ ታራቀኝ አረጋ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በተከሰሰበት የግብረ ሥጋ ድፍረት ወንጀል በመፈጸም ጥፋተኛ ተደርጎ በ10 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍርድ ቤት የተወሰነበትን የሰሜን ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማጽናቱ እንዲሁም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በ5 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ቅጣቱን አሻሽሎ የወሰነበትን በመቃወም አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች እድሜው 11 (አስራ አንድ) ዓመት ሲሆን በጉባላፍቱ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 0200915 እድሜዋ 13 ዓመት ያልሞላትን የአራት ዓመት ህፃን ልጅ አፀደ ምስጌን አስገድዶ ክብረ ንጽህናዋን የደፈራት በመሆኑ በፈጸመው የህፃናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል ወንጀል ተከሷል በማለት በወንጀል ህግ ቁጥር 627(1) መሠረት ክስ ቀርቦበት በዚሁ ጥፋተኛ ተብሎ በ10 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት የተወሰነበትን በመቃወም ለሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ የወረዳ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በማጽናት ያሰናበተው በመሆኑ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ሰበር ሰሚ ችሎቱም ጥፋተኝነቱን በማጽናት አልፎ ቅጣቱ በምን መልክ ይፈጸም

www.abyssinialaw.com

የሚለውን በአብላጫ ድምፅ ወደ 5(አምስት) ዓመት ጽኑ እስራት ዝቅ በማድረግ አሻሽሎ እንዲቀጣ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

የአሁኑ አመልካች እድሜው የ11 (አስራ አንድ) አመት ህፃን መሆኑን ጠቅሶ ምንም ዓይነት ቀጥተኛ ማስረጃ እንዳልቀረበበት እና ጥፋተኛ ሊባል እንደማይገባው እንዲሁም ጥፋተኛ ቢባል እንኳን ቅጣቱን በማረሚያ ቤት ከሌሎች አዋቂ ታራሚዎች ጋር መታሠር እንደሌለበትና በቤተሰቦቹ ሥር ሆኖ ክትትል ሊደረግበት እንደሚገባ ገልጾ ቅሬታውን አቅርቧል፡፡

የሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካች እድሜ 11 ዓመት መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ቅጣቱ በወንጀል ሕግ ቁጥር 157 እስከ 168 ባሉት ድንጋጌዎች ለምን መፈጸም እንደሌለበት የሥር ፍርድ ቤቶች ሳይገልጹ በመደበኛ የቅጣት ድንጋጌዎች የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለት የክልሉ ዓቃቤ ህግ መልስ እንዲሰጥበት ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪም አመልካች ቅጣቱን ከአዋቂ ታራሚዎች ጋር ይፈጸም ቢባል በአመልካች ላይ ሊያስከትል ከሚችለው ጉዳት አንጻር ዕድሜውን መሠረት ያደረገ የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃ ተፈጻሚ ቢሆን እንደማይቃወም ገልጾ በቁጥር ወየሃ-424/08 በቀን 9/05/2008 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡

የክርክሩ ሂደት አጠር ባለመልኩ ከላይ እንደተመዘገበው ሲሆን ጉዳዩን ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ፣በዚህ ችሎት ከተደረገው ክርክር፣ አጣሪው ከያዘው ጭብጥ እንዲሁም አግባብነት ካለው ህግ አንጻር መርምረናል፡፡ አካለ መጠን ያላደረሱ ወጣቶች ወንጀል ፈጽመው በተገኙ ጊዜ የሚደረገው የክስ ሥነ ሥርዓት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 171 እና ተከታዩቹ ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ በነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት የምርመራውም ሆነ የክስ ሥነ ሥርዓት የሚመራው በፍርድ ቤት ክትትልና ቁጥጥር ነው፡፡ የቀረበው ክስ ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ በሆነ ጊዜ አቃቤ ህግ የክስ ማመልከቻውን አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ እንዲሚሰጥ በተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 172 (3) ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም አካለ መጠን ያልደረሰው ወጣት ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እስራት ወይም በሞት በሚያስቀጣ ወንጀል በተከሰሰ ጊዜ ፍርድ ቤቱ አካለ መጠን ያልደረሰውን ወጣት የሚረዳው ጠበቃ ያዝለታል በማለት በዚሁ የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 174 (ለ) ላይ ተደንግጓል፡፡ አካለ መጠን ያልደረሰ ወጣት የተከሰሰበትን የሚሰማው ችሎት በሌላ ነገር ተሰይሞ ከሚያነጋግረው አኳኋንና ሁኔታ የተለየ እንደሆነ የሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 176 (2) ደንግጓል፡፡እነዚህ ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡት አካለ መጠን ያልደረሰ ወጣት በተከሰሰ ጊዜ የወጣቱን እድሜ ባገናዘበ መልኩ ያለውን የአእምሮ ብስለት፣ስለ ጉዳዩ ያለውን አረዳድ፣የሞራል ሁኔታ፣ስለተከሰሰው ህፃን ደህንነት ህግ አውጪው ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ አሚጋች ፍርድ ቤት ስለ ጉዳዩ ልዩ ትኩረት በመስጠት ክርክሩን እንዲመራ ለማድረግ ታስቦ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ

www.abyssinialaw.com

ያደርሳል፡፡ ይህም ስለ ህፃናት መብት ከተደነገገው ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 36 (2) ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በህግ አውጪ አካላት የሕፃናት ደኅንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት በማለት ከተደነገገው ድንጋጌ ጋር የሚጣጣም እንደሆነ ለመመልከት ይቻላል፡፡ በህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 3(1) ላይ የሰፈረው ይህ መርህ የመንግስትም ሆነ የግል ተቋማት በሚወስዷቸው እርምጃዎች ለህጻናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት ያለባቸው መሆኑን ያሳስባል፡፡ የአፍሪካ የህፃናት መብቶች ደህንነት ቻርተር በአንቀጽ 4 (1) ላይ በተመሳሳይ መልኩ ደንግጓል፡፡ ወንጀል ፈጽሞ የተከሰሰ ህፃን ደህንነት የሚጠበቀው የህፃኑን ሥነ ልቦና በመጠበቅ፤በክርክር ሂደት የሚደርስበትን መሸማቀቅ በመከላከል፤ እንዳይጨናነቅ በማድረግ፣ አዋቂዎችን በሚያስችሉበት ችሎት አብሮ እንዳይሆን በማድረግ፤ የሚረዳው ጠበቃ እንዲኖር በማድረግ ነው፡፡

በዚህ መሠረት የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህጉም ሆነ የወንጀል ህጉ ለህፃናት ወንጀል ፈጻሚዎች ከአዋቂዎች የተለየ የምርመራ፣ የክስ፤ የፍርድ እና የቅጣት ሁኔታን ማስቀመጥ ያስፈለገው ህገ መንግሥቱ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች ላይ ከተደነገጉ የህፃናት መብቶች በእጅጉ ለማያያዝ ታስቦ ነው፡፡ የዚህም አስፈላጊነት መደበኛ የክርክር ሥርዓት ለመዘርጋት ያለመ ሳይሆን በህፃናት ላይ ለጥፋተኝነት የሚወሰን ቅጣት ማስተማርና ማረም እንጂ መበቀል እንዳይሆን ታሳቢ አድርጎ ህፃናት በአከባቢያቸው አብሮዋቸው የሚውለው፣ የሚያዩት፣የሚማሩበት በተለይም በምርመራ፣ ክስ፣ ፍርድ እና የቅጣት አፈጻጸም ላይ ጥንቃቄ ካልተደረገ እነርሱን ከመጉዳት አልፎ የመጡበትን ማኅበረሰብ፣አካባቢና ሀገር የሚጎዳ ማንነት እንዳይከሰት ነው፡፡በተጨማሪም ህፃናት እራሳቸውን የሚጠብቁና የሚቆጣጠሩ ባለመሆናቸው ያጠፉት ጥፋት ቢኖር እንኳ እኩል ከአዋቂዎች ዓይነት የቅጣት አፈጻጸም ከመከተል ይልቅ ስለወደፊት መልካም አስተዳደግ እና ደኅንነታቸው ቅድሚያ የሚሰጠው በመሆኑ ነው፡፡

ይህን ዓላማ ለማሳካትም ሲባል ከህገ መንግሥት አንቀጽ 36 (2) እና (3)፣ ከአህጉሩና ዓለም አቀፍ ስምምነት ሰነዶች በተጨማሪ በዝርዝር የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 157 እስከ 168 እና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ 171 እስከ 180 ላይ ዝርዝር የምርመራ፣ የክስ፣ የፍርድ እና የቅጣት አፈጻጸም ድንጋጌዎችም ሥራ ላይ እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ የተጣለው በፍርድ ቤት ላይ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በወንጀል ለተከሰሱ ህፃናት ምቹ የሆነ የክርክር መሰማት ሥርዓትን ማስጠበቅና ማስከበር በዓለም አቀፍ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን፣ በአፍሪካ የህፃናት መብቶች ቻርተር፣ በኢፌዴሪ ህግ መንግሥት፣በወንጀል ህግ እና በወንጀለኛ መቅጫ ህግ

www.abyssinialaw.com

ሥነ ሥርዓት በተደነገገው መሠረት የፍርድ ቤት ኃላፊነት ነው፡፡ የተያዘውን ጉዳይ የተመለከተው የጉባላፍቶ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንደሚያመለክተው ከላይ የተገለጹትን ሥነ ሥርዓታዊ ድንጋጌዎች ተከትሎ የተደረገ ክርክር አይደለም፡፡ ፍርድ ቤቱ በዚህ ረገድ የሥነ ሥርዓት ግድፈት እንደፈጸመ መገንዘብ ተችሏል፡፡

የጥፋተኝነት ውሳኔን በተመለከተ አመልካች የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት የፈጸመ መሆኑ በሥር ወረዳ ፍርድ ቤት በማስረጃ ተረጋገጦ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ቅጣትን በተመለከተ እድሜያቸው ከዘጠኝ እስከ አስራ አምስት ዓመት የሞላቸው ወንጀል ያደረጉ ወጣቶች የሚወሰንባቸው ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ከአንቀጽ 157 እስከ 168 የተደነገጉ ብቻ ናቸው፡፡ ለአዋቂ ጥፋተኞች የተደነገጉት መደበኛ ቅጣቶች ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፤ ከአዋቂዎችም ጋር አይታሰሩም በማለት የወንጀል ህግ አንቀጽ 53 (1) ይደነግጋል፡፡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 168 (2) ወጣቱ የፈጸመውን ወንጀል ከባድነትና ጥፋቱንም በፈጸመበት ጊዜ የነበረውን የዕድሜ ሁኔታ መሠረት በማድረግ ታስሮ የሚቆይበትን የጊዜ ልክ ፍርድ ቤቱ ይወስናል፡፡ ጊዜውም ከአንድ ዓመት ሳያንስ እስከ አስር ዓመት ሊደርስ ይችላል በማለት ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሚወሰነው ቅጣት ከአንድ ዓመት እስከ አስር ዓመት ሲሆን የሥር አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን የቅጣት ውሳኔን በማሻሻል አመልካች በአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ ቅጣቱንም የወልዳያ ማረሚያ ቤት እንዲያስፈጽም በአብላጫ ድምፅ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አነስተኛው ድምፅ የአመልካችን አቆያየት በተመለከተ የወንጀል ህግ ቁጥር 168 (1) ሀ) ላይ ከወንጀሉ ከባድነት አንጻር ወንጀለኛው ወደ ፀባይ ማረሚያ ተቋም ሊላክ እንደሚችል ቢገልጽም ይህ ዓይነት የማረሚያ ተቋም በአሁኑ ጊዜ የሌለ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የወንጀል ህግ ቁጥር 53 (1) ደግሞ በዚህ እድሜ ክልል የሚገኙ ወንጀለኞች ከአዋቂዎች ጋር አይታሠሩም በማለት ግልጽ የሆነ ክልከላ አስቀምጧል፡፡ ይህ ከመሆኑ አንጻር አመልካች ወደ ማኅበረሰቡ እንዲቀላቀል ተደርጎ ፀባዩ በፖሊስ ክትትል ሊደረግበት ሲገባ ግልጽ የሆነውን የህግ ክልከላ በመተላለፍ አብላጫው ደምፅ አመልካች ከአዋቂዎች ጋር እንዲታሠር መወሠኑ ተገቢነት የለውም በማለት ከአብላጫው ድምፅ ተለይቷል፡፡

የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አጣሪ አቤቱታውን ሲያስቀርብ የአመልካች እድሜ 11 ዓመት መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ቅጣቱ በወንጀል ሕግ ቁጥር 157 እስከ 168 ባሉት ድንጋጌዎች ለምን መፈጸም እንደሌለበት የሥር ፍርድ ቤቶች ሳይገልጹ በመደበኛ የቅጣት ድንጋጌዎች የመወሰኑን አግባብነት መመርመር ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለት ጭብጥ የያዘውም የአነስተኛውን ድምፅ

www.abyssinialaw.com

ልዩነት ሀሳብ ህጋዊ መሠረት ያለው መሆኑን ተመልክቶ ነው ወደ ሚል ድምዳሜ ያደርሰናል፡፡ እኛም የስር ፍርድ ቤት ሁለት ዳኞች በልዩነት ያነሱትን እንዲሁም አጣሪው የያዘውን ጭብጥ የምንስማማበት ነው፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ ይህ ችሎት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ህፃናት ፍትህ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ተገቢውን ባለሙያ በመመደብ ስለ አመልካቹ ህፃን ጠባይ፣ ስለአስተዳደጉ፣ ስለኑሮውና ስለህይወቱ እንዲሁም የአካልና የአእምሮ ሁኔታውን አስጠንቶ ውጤቱን እንዲያቀርብ ሚያዝያ 6 ቀን 2008 ዓ/ም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ መሠረት የህፃናት ፍትህ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያ በመመደብ በወልዲያ ማረሚያ ቤት ስለሚገኘው ህፃን አድማሱ አገዘ ሁኔታ ያጠናውን ጥናት በቁጥር ሂ/4-9-3/17920 ሐምሌ 19 ቀን 2008 ዓ/ም በተጻፈ መሸኛ ደብዳቤ ልኳል፡፡ ጥናቱም ከአመልካቹ፣ ከቤተሰቦቹ፣ ከጓደኛው፣ ከጎራቤቶቹ እና ከማረሚያ ቤቱ ሙያተኞች የተገኘ መረጃ እንደሆነ ሲገልጽ የሚከተሉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች ለመውሰድ የሚረዱ ሃሳቦች ለማግኘት እንዳስቻለ ያመለክታል፡፡ እነዚህም፡-

1. አመልካች ወንጀሉን መፈጸሙን ባያምንም ከዚህ በኃላ ፀባዩን ለማሻሻልና ትምህርቱ ላይ ብቻ ሙሉ ትኩረቱን ለማድረግ ማቀዱ፣
2. ህፃኑ ከቤተሰቡ እና ከጓደኞቹ ተለይቶ ማረሚያ ቤት መግባቱ ከባድ እንደሆነ በመረዳቱ እና ለወደፊት ከወንጀል ነክ ነገሮች ለመራቅ ማቀዱ፣
3. ህፃኑ ወደ ወላጅ እናቱ ጋር ለመኖር ከተመለሰባቸው ምክንያቶች አንዱ በሥራ ጫና ምክንያት ትምህርቱን ላለማቋረጥ ባደረገው ትግል ከወላጅ አባቱ እና ከእንጀራ እናቱ ጋር አለመስማማት ተፈጥሮ መሆኑ፣
4. ከማረሚያ ቤቱ ሙያተኞች ለመረዳት እንደተቻለው ህፃን አድማሱ/አመልካቹ/ ታዛዥ እና ምክርም የሚሰማ መሆኑ፤
5. ከቤተሰቦቹ፣ ከጓደኛው እና ከመኖሪያ አካባቢው የተገኘውም መረጃ አመልካች በባህሪይው ጨዋ እና ምስጉን እንደሆነ እና ከዚህ በፊት በወንጀል ድርጊት ተከሶም ሆነ ጥፋተኛ ተብሎ እንደማያውቅ የሚያሳይ በመሆኑ፣
6. የአመልካች ወላጅ እናትም ህጻኑ ወደ ወንጀል ድርጊት ሊገባ የቻለው በተለያየ ቦታ በማደጉ ከአስተዳደግ ክፍተት እና ከቤተሰብ ክትትል እና ቁጥጥር ማነስ ሊሆን እንደሚችል በማመን ወደፊት ኃላፊነታቸውን በሚገባ ለመወጣት እንዳቀዱ የገለጹ መሆኑ እና የተፈጠረውን ችግር ለመቅረፍ ቤተሰቡ ተበዳይን ለመካስ ጥረት ማድረጋቸው በጥናቱ የተካተቱ ነጥቦች ናቸው፡፡ እነዚህ የጥናት ውጤቶች በአመልካች ላይ ሊወሰድ የሚገባው ቅጣት ምን ሊሆን እንደሚገባ ግንዛቤ የሚሰጡ ሆነው

www.abyssinialaw.com

ተገኝተዋል፡፡የወንጀል ህግ ቁጥር 157 እስከ 168 ላይ የተመለከቱት የቅጣት እና የጥንቃቄ እርምጃዎች ተፈጻሚ ሲሆኑም የወጣቱን ፀባይ እና የቀድሞ ባህሪው ምን እንደሚመስል መገንዘብ እንደሚያስፈልግ የደነገገ ሲሆን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 177 (2) ድንጋጌም ይህንን ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ አንጻር አመልካች የፈጸመው የወንጀል ድርጊት ከእሱ ዕድሜ በታች ላይ የምትገኘው ህፃን ልጅ ላይ ግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸሙ ወንጀሉ ከባድ የሚባል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የቅጣት እርምጃ መወሰዱ ተገቢነት ቢኖረውም የቅጣት አፈጻጸም ሲታይ በምን መልኩ ተፈጻሚ መሆን አለበት የሚለው ጉዳይ ከአመልካቹ እድሜ እና ስለ ነበረው ባህሪ እና መልካም ፀባይ በመነሳት ከወንጀል ህግ ቁጥር 157 እስከ 168 አኳያ የተለያዩ እርምጃዎች ተፈጻሚ መሆን እንደሚገባቸው ህጉ ያስቀመጠ በመሆኑ የተወሰነበትን የእስራት ቅጣት ከአዋቂ የህግ ታራሚዎች ጋር ይፈጽም ቢባል ወደፊት በአመልካች ላይ ሊያስከትልበት ከሚችለው የሞራል እና የተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮች አኳያ ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የክስና የክርክር ሂደት የመሩበት አካሄድ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት፣ የወንጀል ህጉን መሠረታዊ ድንጋጌዎች እና በህገ መንግሥቱ ስለህፃናት የተቀመጡ መርሆችን የተከተለ ካለመሆኑም ባሻገር ፍርድ ቤቶቹ ቅጣቱን ሲወስኑ እንዲሁም ቅጣቱ ከአዋቂ ታራሚዎች ጋር እንዲፈጸም ትዕዛዝ መስጠታቸው ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 0200915 በቀን 04/06/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፣የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0205865 በቀን 10/06/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ፣የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቁጥር 03-10537 ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195/2/ለ/2/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የወንጀል ህግ ቁጥር 168/1/ሀ/ ከወንጀሉ ከባድነት አንጻር አካለ መጠን ያልደረሰ ወንጀል አድራጊ ወደ ፀባይ ማረሚያ ተቋም ሊላክ እንደሚችል ቢደነግግም ይህ ዓይነት ማረሚያ ተቋም በአሁኑ ጊዜ ያልተሟላ ሲሆን የወንጀል ህግ ቁጥር 53/1/ ደግሞ በዚህ እድሜ ክልል የሚገኙ ወንጀል አድራጊዎች ከአዋቂዎች ጋር አይታሰሩም በማለት ደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች አንጻር አመልካች ወደ ማኅበረሰቡ እንዲቀላቀል ተደርጎ በፖሊስ

www.abyssinialaw.com

ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡ በመሆኑም በሥር ፍርድ ቤቶች የተወሰነው የቅጣት ውሳኔ በወንጀል ህግ ቁጥር 171 እና 192 መሠረት ታግዶ እንዲቆይ ተወስኗል፡፡

3. ስለ አመልካቹ መልካም አስተዳደግና ባህርይ ክትትል እንዲያደርጉ ለአመልካቹ እናትና አባት እንዲገለጽ ታዟል፤ ይጻፍ፡፡
4. አመልካች ከማረሚያ ቤት ወጥቶ በማኅበረሰቡ ውስጥ በሚቆይበት ጊዜ ለፈተና በተሰጠው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚያሳየውን ባህርይ እንደከታተል ለሚገኝበት ወረዳ ፖሊስ በጽሁፍ እንዲገለጽ ታዟል፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለወልድያ ማረሚያ ቤት በመሸኛ እንዲደርሰውና አመልካቹንም እንዲፈታው የመፍቻ ዋራንት እንዲጻፍ ታዟል፡፡
6. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡
7. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.134228

የካቲት 08 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሃመድ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

አይሸሹም መለሰ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ስማቸው ከበደ

- ጠበቆች ታምሩ ወ/አገኝ፤ ሲሳይ ለምለም ፍስሃ አለማየሁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ - ያለምወርቅ አስታጥቄ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል ባለው የወንጀል ክስ ክርክር የቀረበን የዋስትና ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ክሱን እየተመለከተ ለሚገኘው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ከ2ኛው ክስ ነጻ ስለወጣሁና ተከላከል የተባልኩባቸው ክሶች ላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ዋስትና የማያስከለክሉ በመሆኑ የዋስትና መብት ይፈቀድልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ በሰጠው መልስ ተከሳሽ የተከሰሱበት ወንጀል ከአስር ዓመት በላይ የሚያስቀጣ መሆኑን፤ እንዲሁም ነፃ በወጡበት ጉዳይ ይግባኝ የጠየቁበት መሆኑን በማንሳት የዋስትና መብታቸው እንዲነፈግ ተከራክሯል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአመልካች እና 19ኛ ተከሳሽ በሆነው ድርጅታቸው ላይ የቀረቡት 37ኛ፤ 38ኛ፤ 40ኛ፤ 41ኛ፤ 42ኛ፤ 43ኛ፤ 44ኛ፤ እና 45ኛ ክሶች የግብር ዓዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 96 እና 97፤ እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49፤ 50፤ 102 እና 56 መሰረት ያደረጉ እና በእነዚህ 8 (ስምንት) ክሶች በድምሩ ብር 50,374,960.00 የሚጠጋ የመንግስት የገቢ ግብር እና ተጨማሪ እሴት ታክስ እዳ እንዳለባቸው የሚያሳዩ ግብር አሳውቆ አለመክፈልን እና አሳንሶ ማሳወቅን የሚመለከቱ የወንጀል ክሶች በመሆናቸው፤ በድርጅቱ ላይ የቀረቡትም ክሶች አመልካችን የሚመለከቱ እና በተደራቢነት የሚታዩ በመሆናቸው፤ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች በመርህ ደረጃ ዋስትና የሚከለክሉ ባይሆንም ተደራራቢ ቅጣትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ተደራራቢ ወንጀሎች በመሆናቸው አመልካች ሊከተል የሚችለውን ከፍተኛ ቅጣት በመሸሽ በዋስ ቢወጡ ሊቀርቡ ይችላሉ ተብሎ መገመት አለመቻሉን፤ የክሱ የገንዘብ መጠን ከፍተኛ መሆኑና በሃገር ኢኮኖሚ የሚያሳድረው ተፅእኖ ከፍተኛነት ሲታይ የድርጊቱ አፈፃፀም አደገኛነት እና የወንጀሉን ከባድነት ስለሚያስገነዝብ አመልካች በዋስትና ቢወጡ

www.abyssinialaw.com

ይቀርባሉ ተብሎ ለመገመት የማያስችል በመሆኑ፤ አመልካች ያላቸውን የኢኮኖሚ አቅም ተጠቅመው ከሃገር አይወጡም የሚለውን ግምት የሚያስተባብል አሳማኝ ምክንያት ያላቀረቡ በመሆኑ፤ በአጠቃላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች አመልካች የዋስትና መብት ቢፈቀድላቸው የዋስትና ግዴታን አክብረው ፍርድ ቤት በየቀጠሮው ይቀርባሉ የሚል ዕምነት ሊጣልበት የሚያስችል ሁኔታ የለም ብሎ ፍርድ ቤቱ ስላመነ የዋስትና ጥያቄውን አልተቀበልኩም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን ብይን በመቃወም ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ብይኑን ለመለወጥ የሚያስችል በቂ እና አሳማኝ ምክንያት አልተገኘም ተብሎ የይግባኝ ማመልከቻው ውድቅ ተደርጓል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡

አመልካች ህዳር 10 ቀን 2009 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የተከሰሱባቸው የወንጀል ክሶች በመርህ ደረጃ የአመልካችን የዋስትና መብት የሚያስነፍጉ ስላለመሆናቸው የሥር ፍርድ ቤት ተቀብሎ ነገር ግን ክርክሩ ከተጠናቀቀ በኋላ አመልካች ጥፋተኛ ቢባሉ ሊያስከትልባቸው ከሚችለው ቅጣት አንፃር አመልካች ከሃገር ሊሸሹ ይችላሉ የሚለውን ግምት መነሻ በማድረግ የዋስትና መብት የመከልከሉን አግባብነት፤ እንዲሁም ከሃገር ሊሸሹ ይችሉ ይሆናል የሚል ግምት ቢወሰድም እንኳ ከሀገር ለመሸሽ የማይችሉበትን ሥርዓት ማስፈፀም እየተቻለ መሰረታዊ የሆነውን የዋስትና መብት ለመንፈግ የተሰጠው ምክንያት እንደህጉ አነጋገር በቂ ምክንያትን የተመረኮዘ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ከዚህ ቀደም በሰበር መ/ቁ 31734 ከሰጠው ትርጉም አንፃር ማየት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ይቅረብ ተብሏል፡፡ በዚሁ መሰረት ግራ ቀኙ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር በፅሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት መርምረናል፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 19(6) በግልፅ እንደተመለከተው የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት ያላቸው ሲሆን ዋስትና ሊከለከል የሚችለው በህግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ነው፡፡ በህጉ ከተደነገጉት ልዩ ሁኔታዎች መካከል በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 67(ሀ) ሥር የተደነገገው ተጠቃሽ ነው፡፡ በድንጋጌው ሥር እንደተመለከተው ተከሣሹ የዋስትና ግዴታውን ሊፈጽም አይችልም ተብሎ ሲገመት ዋስትና መከልከል ይቻላል፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ በዋስ ቢለቀቁ ተመልሰው ሊቀርቡ አይችሉም የሚል ግምት ለመውሰድ እና ዋስትና ለመከልከል የሚያስችል ማስረጃም ሆነ ምክንያት ሳይኖር፤ ይልቁንም ከፍተኛ ባለሃብት በመሆናቸው በቢሊዮን የሚቆጠር ሃብት የሚያንቀሳቅሱ እና አንደኛ ደረጃ ግብር ከፋይ ተብለው መሸለማቸውን፤ እንዲሁም ከፍተኛ የሥራ ዕድል መፍጠራቸውን ሁሉ ለፍርድ ቤቱ ተገልፆ በገሃድ ቀርቦ እያለ ምንም ማፍረሻ ማስረጃ ሳይቀርብ በደፈናው አይቀርቡም የሚለውን ግምት ሊያስተባብሉ አልቻሉም በማለት መደምደሙ፤ እንዲሁም ጉልህ ግምት ቢኖር

www.abyssinialaw.com

ያንን እንዳፈርስ ወይም እንዳስረዳ እንኳ እድል ሳይሰጥ የተወሰነ ውሳኔ በመሆኑ በዚህ መልኩ የተሰጠው ብይን ተሽሮ ዋስትና ሊፈቀድ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ነገር ግን ተከሣሹ የዋስትና ግዴታውን ሊፈጽም አይችልም ለማለት የሚያስችል በበቂ ምክንያት የተደገፈ ግምት ካለ ይህ በመኖሩ ብቻ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67/ሀ/ መሠረት ዋስትና መከልከል የሚቻል ሲሆን በተያዘው ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት አመልካች የዋስትና መብት የተከለከሉት የዋስትና ግዴታን አክብረው ፍርድ ቤት በየቀጠሮው ይቀርባሉ የሚል ዕምነት ሊጣልበት የሚያስችል ሁኔታ አለመኖሩን ፍርድ ቤቱ በመቀበሉ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰው በአመልካች እና በድርጅታቸው ላይ የቀረቡትን ተደራራቢ ክሶች፤ ክሶቹ የያዙትን ከፍተኛ የገንዘብ መጠን እና ወንጀሉም ግብር አሳውቆ ካለመክፈል እና አሳንሶ ከማሳወቅ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች መሆናቸውን፤ እነዚህ ከፍተኛ ቅጣትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ተደራራቢ ወንጀሎች በመሆናቸው፤ የድርጊቱ አፈፃፀም አደገኛነት እና የወንጀሉ ከባድነት ሁሉ ሲታይ አመልካች በዋስትና ቢወጡ ይቀርባሉ ተብሎ ለመገመት የማያስችል መሆኑን፤ እንዲሁም አመልካች ያላቸውን የኢኮኖሚ አቅም ተጠቅመው ከሃገር አይወጡም የሚለውን ግምት የሚያስተባብል አሳማኝ ምክንያት ያላቀረቡ መሆኑን በማንሳት ነው፡፡

የወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 67(ሀ) በዋስትና ወረቀት የተመለከቱትን ግዴታዎች አመልካች የሚፈጽሙ የማይመስል እንደሆነ በዋስትና የመለቀቅ ማመልከቻውን መቀበል የማይቻል ስለመሆኑ ቢደነግግም ፍርድ ቤቱ ዋስትናውን ለመከልከል ግምቱን መነሻ የሚያደርግባቸው ሁኔታዎች በግልጽ አልተመለከቱም፡፡ በመሆኑም አንድ ተከሣሽ የዋስትና መብት ቢከበርለት ግዴታውን የሚፈጽም የማይመስል ነው ተብሎ ግምት የሚወሰደው በቂና ህጋዊ ሊባሉ በሚችሉ ምክንያቶች ሊሆን እንደሚገባ፤ እንዲሁም ምክንያቶቹ በቂና ህጋዊ ናቸው የሚለው ጉዳይ ከተለያዩ ከባባዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባህርይ አንፃር ፍርድ ቤቱ ሊገነዘበው የሚችለው ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚገባ ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 59304 እና ሌሎችም ተመሳሳይ መዛግብት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም በወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 67 መሰረት የዋስትና መብት የሚነፈግባቸው ምክንያቶች ፍርድ ቤቶች ከተለያዩ ሁኔታዎች አንፃር እየተመለከቱ ሊመዝኗቸው የሚገባቸው ናቸው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ያልተቀበለው የዋስትና መብት ቢፈቀድላቸው የዋስትና ግዴታውን አክብረው ፍርድ ቤት በቀነ ቀጠሮው ይቀርባሉ የሚል ዕምነት ሊጣልበት የሚያስችል ሁኔታ አለመኖሩን ነው፡፡ ለዚህ በምክንያትነት የተጠቀሰው ከፍ ሲል እንደገለፅነው የቀረቡት ክሶች ተደራራቢነት፤ ክሶቹ የያዙትን ከፍተኛ የገንዘብ መጠን፤ የወንጀሉ አይነት እና የድርጊቱ አፈፃፀም፤ ሊያስከትል የሚችለው ከፍተኛ ቅጣት፤ እንዲሁም አመልካች ያላቸውን የኢኮኖሚ አቅም ተጠቅመው ከሃገር አይወጡም የማያሰኝ ሁኔታ አለመኖሩን ነው፡፡ እነዚህ ምክንያቶች ለግምቱ መነሻ እንዳይደረጉ በህጉ ክልከላ ካለመኖሩም በላይ በምክንያትነት ተቀባይነት ሊኖራቸው አይገባም የሚባልበት ሁኔታ ባለመኖሩ የስር ፍርድ ቤት በተጠቀሰው

www.abyssinialaw.com

ምክንያት እና ግምት ላይ ተመስርቶ በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ማመልከቻውን ባለመቀበል በመወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ፈጽሟል ለማለት አልተቻለም፡፡

በሌላም በኩል ቅሬታው ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ከዚህ ቀደም በሰበር መ/ቁ 31734 ከሰጠው ትርጉም አንፃር ለማየትም እንዲቻል ተብሎ ቢሆንም በተጠቀሰው መዝገብ ተከሳሹ የብዙ ሃገር ፓስፖርትና ቪዛ በእጁ ስለሚገኝ ብቻ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም ለማለት የሚያስችል በቂ መንደርደሪያ ምክንያት ስላለመሆኑ፤ እንዲሁም የዋስትና ግዴታውን አክብሮ እንዲቀርብ የሚያደርግ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚቻል የተወሰነበት ከመሆኑ ውጭ በሁለቱ መዛግብት የቀረበው ክርክር እና ዋስትና ለመከልከል መንደርደሪያ የተደረጉት ምክንያቶች ተመሳሳይ ናቸው የሚባሉ ሆነው አላገኘናቸውም፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት በህጉ ተቀባይነት የላቸውም የማይባሉ ምክንያቶች ላይ በመመስረት አመልካች የዋስትና መብት ቢፈቀድላቸው የዋስትና ግዴታውን አክብረው ፍርድ ቤት በየቀጠሮው ይቀርባሉ የሚል ዕምነት ሊጣልበት የሚያስችል ሁኔታ የለም በማለት በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ማመልከቻውን በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 67/ሀ/ መሰረት ባለመቀበል በመወሰኑ፤ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የይግባኝ ማመልከቻውን ባለመቀበል በመወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወ/መ/ቁጥር 141352 ጥቅምት 1 ቀን 2009 ዓ.ም. የተሰጠው ብይን፤ እንዲሁም በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ 133103 ጥቅምት 15 ቀን 2009 ዓ.ም የተላለፈው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 75/2/ መሠረት በአብላጫ ድምፅ ፀንቷል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የልዩነት ሃሳብ

እኔ በተራ ቁጥር አንድ ስሜ የተገለፀው ዳኛ አብላጫው ድምፅ በደረሰበት ድምዳሜና ውሳኔ ያልተስማማሁ በመሆኑ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡ በሀሳብ የተለየሁባቸውን ምክንያቶች ግልፅ ለማድረግ በመጀመሪያ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረባቸውን የወንጀል ክሶች ይዘት፣ የስር ፍርድ ቤት የተጠሪን ማስረጃ ከተሰማ በኋላ አመልካች መከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በነፃ እንዲሰናበት የሰጠውን ብይንና ብይኑን በማስተካከል አመልካች በዋስ ልለቀቅ ይገባል በማለት ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የስር ፍርድ ቤት የሰጣቸውን ምክንያቶች በአጭሩና በዝርዝር መግለፁ አስፈላጊ ነው ብዬ ስለማስብ ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ አስፍሬለሁ፡፡

www.abyssinialaw.com

1. ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 141352 ባቀረበው የወንጀል ክስ

- አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 33፣ አንቀፅ 32 እና አንቀፅ 411 ንዑስ አንቀፅ 1/ሐ/ እና ንዑስ አንቀፅ 2 በመተላለፍ ከላይ ቁጥሩ በተገለፀው የወንጀል መዝገብ አንደኛና ሁለተኛ ተከሳሽ ሆነው ከተከሰሱት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስጣናት ጋር በመሆን የመንግስት ስራ በማያመች ሁኔታ የመምራት ከባድ የሙስና ወንጀል ፈፅሟል በማለት በሁለተኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ አመልካች በስር ፍርድ ቤት አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የሆነው ጂ ኤች ሴሚክስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስራ አስኪያጅ እንደሆነ ገልፆ፤
- አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 49 በመተላለፍ ከ1998 ዓ.ም እስከ 2004 የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 20,111,328.94 አሳውቆ ያለመክፈል ወንጀል ፈፅሟል በማለት በሰላሳ ሰባተኛው ወንጀል ክስ ላይ የገለፀ ሲሆን፣ አመልካች የ19ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 56 እና አንቀፅ 49 በመተላለፍ በሰላሳ ሰባተኛው ክስ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በማለት በሰላሳ ስምንተኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡
- አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ በመተላለፍ የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ አሳውቆ መክፈል ሲገባው 1998 ዓ.ም እስከ 2004 የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 20,111,328.94 የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ በመደበቅና የተጭበረበረ መረጃ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት የመስጠት ወንጀል ፈፅሟል በማለት በሰላሳ ዘጠነኛው የወንጀል ክስ ላይ የገለፀ ሲሆን፣ አመልካች የ19ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 56/1/ እና አንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ በመተላለፍ በሰላሳ ዘጠነኛው ክስ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በማለት በአርባኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡
- አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 96 የተመለከተውን በመተላለፍ ከ2001 ዓ.ም እስከ 2004 29, 433, 214.24 ያገኘውን ትክክለኛ ገቢ አሳውቆ መከፈል የሚገባውን ገቢ ግብር ያለመክፈል ወንጀል ፈፅሟል በማለት በአርባ አንደኛው ወንጀል ክስ ላይ የገለፀ ሲሆን፣ አመልካች 19ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 102/1/ እና አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ በመተላለፍ በአርባ አንደኛው ክስ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በማለት በአርባ ሁለተኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡

www.abyssinialaw.com

- አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ የተመለከተውን በመተላለፍ ከ2001 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም ብር 29,433,214.24 ያገኘውን ትክክለኛ ገቢ አሳውቆ መክፈል የሚገባው ገቢ ግብር በመደበቅና ያለመክፈል ወንጀል ፈፅሟል በማለት በአርባ ሶስተኛው ወንጀል ክስ ላይ የገለፀ ሲሆን፣ አመልካች 19ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 102/1/ እና አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ በመተላለፍ በአርባ ሶስተኛው ክስ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በማለት በአርባ አራተኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡
- አመልካች በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 98 የተመለከተውን በመተላለፍ ከቀረጥ ነፃ ያስገባቸውን የቀረጥ መጠናቸው 197556.61 የሆኑ መሳሪያዎች ከተፈቀደለት ተግባር ወጭ ተጠቅሟል በማለት በአርባ አምስተኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡

2. አመልካች በሁለተኛው የወንጀል ክስ የተከሰሰበትን ወንጀል ማለትም አመልካች ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 33 እና አንቀፅ 411 ንዑስ አንቀፅ 1/ሐ/ እና ንዑስ አንቀፅ 2 በመተላለፍ ፈፅሞታል የተባለው ከባድ የሙስና ወንጀል ከአስር አመት በላይ የሚያስቀጣ የሙስና ወንጀል በመሆኑ፣ በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀፅ 4/1/ መሰረት አመልካች በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ የሕጉ ድንጋጌ ስለማይፈቀድለት አመልካች በማረሚያ ቤት ሆኖ ሲከራከር ቆይቷል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሐምሌ 26 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች በሁለተኛው የወንጀል ክስ የተከሰሰበትን ከባድ የሙስና ወንጀል የፈፀመ ስለመሆኑ ተጠሪ በበቂ ሁኔታ ያላስረዳ በመሆኑ፣ ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በነፃ እንዲሰናበት በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 እና የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 በመተላለፍ በበኩላቸው የወንጀል ክሶች ከሳሽ /ተጠሪ/ በበቂ ሁኔታ ያስረዳ በመሆኑ ተከሳሽ /አመልካች/ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የስር ፍርድ ቤት ብይን ሰጥቷል፡፡
3. የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ከሰማ በኋላ አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ፣ በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀፅ 4/1/ መሰረት በዋስትና ወረቀት እንዳይለቀቅ ከማያስከለክለው ከባድ ሙስና የወንጀል ክስ ፍርድ ቤቱ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በነፃ እንዲሰናበት ብይን የተሰጠ መሆኑንና ተከላከል የተባለባቸው ሌሎች ወንጀሎች በዋስትና የመለቀቅ መብትን የሚያስከለክሉ መሆኑን ገልፆ፣ በዋስ የመለቀቅ መብቴ ይከበርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች ላቀረበው የዋስትና ጥያቄ ተጠሪ ነሐሴ 2 ቀን 2008 ዓ.ም

www.abyssinialaw.com

እና መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ.ም መልስ የሰጠ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ብይን ያሳያል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ በዋስትናው ጥያቄ ላይ ያደረጉትን ክርክር ከመረመረ በኋላ፤

- ተከሳሽ በተደራራቢ ወንጀል ማለትም በ37ኛ ፣ 38፣ 40፣ 41፣ 42፣43፣44፣ እና በ45ኛ በድምሩ በስምንት ክሶች ብር 50,374,960 ተጨማሪ እሴት ታክስና ገቢ ግብር አሳውቆ ያለመክፈል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሰና ክሶቹ ተደራራቢ የወንጀል ቅጣት የሚያስከትሉ በመሆናቸው፣
- ተከሳሽ የተከሰሰባቸው ተጨማሪ እሴት ታክስና ገቢ አሳውቆ ያለመክፈል ተደራራቢ ወንጀሎች ሳይከፍል ቀርቷል የተባለው ታክስና ግብር ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ያለው (ብር 50,374,960) በመሆኑና ወንጀሉ በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ከፍተኛነት ሲታይ የድርጊቱ አፈፃፀም አደገኝነትና የወንጀሉ ከባድነት ተከሳሹ በዋስትና ቢወጣ ይቀርባል ብሎ መገመት የማያስችል ምክንያት በመሆኑና፣
- ተከሳሹ ያለውን ኢኮኖሚ አቅም ተጠቅሞ ከአገር አይወጣም የሚለውን ግምት ሊያስተባብል የሚችል አሳማኝ ምክንያት በከሳሽ በኩል ስላልቀረበ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 67 (ሀ) እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 በሰጠው አስገዳጅ ትርጉም መሠረት ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም የሚል እምነት ያለን በመሆኑ ተከሳሹ በማረሚያ ቤት ሆኖ ይከራከር በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን ዋስትና መብት ለመገደብ የሰጡት ምክንያት የህገ መንግስቱንና የሌሎች ህግ ድንጋጌዎችን የተከተለ አይደለም በማለት ሲሆን ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

4. በእኔ በኩል የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ በብይኑ ላይ ያሰፈራቸው ምክንያቶች ህጋዊ ተቀባይነት ያላቸው ስለመሆናቸው የስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ ያለውን ከፍተኛ የኢኮኖሚ አቅም ተጠቅሞ ከአገር የማይወጣ ስለመሆኑ የማስረዳት ግዴታውን አልተወጣም በማለት የሰጠው ትርጉምና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በዋቢነት የጠቀሰበት ሁኔታ በሰበር ሊታረም የሚገባው መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

በመርህ ደረጃ የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀፅ 6 የመጀመሪያው ሐረግ “የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው” በማለት ቃል በቃል የተደነገገ ሲሆን በህግ በተደነገጉ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት የተከሳሹን በዋስትና የመለቀቅ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተከሳሹ በዋስትና የመለቀቅ መብት ተገድቦ ሊቆይ እንደሚችል በህግ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 ተከታዩ ሐረግ

www.abyssinialaw.com

ይደነግል፡፡ በአገራችን የተከሳሽን በዋስትና የመለቀቅ መብት ሕግ አውጭው በሕግ የገደበባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ ሕግ አውጭው የዋስትና መብትን አስገዳጅ በሆኑ የህግ ድንጋጌዎች በከለከለባቸው ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎችን ዳኞች በዋስ የመፍታት ፈቃደ ስልጣን የላቸውም፡፡ ሕግ አውጭው የተከሳሽን በዋስትና የመለቀቅ መብት አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ የገደበው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 63 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በተሻሻለው ልዩ የሙስና የስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ1 በተመለከቱ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎችን የሚመለከት ነው፡፡

5. ሕግ አውጭው የተከሳሽን በዋስትና የመለቀቅ መብት በህግ ከገደበባቸው ከላይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ በሆኑ ሌሎች ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎች በመርህ ደረጃ የቀረበባቸው የወንጀል ክስ ሊያስከትል የሚችለው ከፍተኛ የወንጀል ቅጣትና በተከሳሹ ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ ብዛት ግምት ውስጥ ሳይገባ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት በዋስ የመለቀቅ መብት አላቸው፡፡ በህግ በዋስትና የመለቀቅ መብታቸውን በማያስገድቡ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና የመለቀቅ መብት የሚገደበው መንግስትና ሕዝብን ወክሎ የሚከራከረው ዐቃቤ ህግ የተከሳሹን በዋስ መለቀቅ በመቃወም ክርክር ሲያነሳና ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙ በዋስትናው ላይ ያቀረቡትን ክርክር ማስረጃ መርምሮ የተከሳሹን በዋስ የመለቀቅ መብት የሚገድብ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ሲሰጥ ነው፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ዳኞች በህግ የተሰጣቸውን ፈቃደ ስልጣን በመጠቀም ተከሳሹ በዋስ እንዲለቀቅ ወይም የተከሳሽ በዋስ የመለቀቅ መብት ተገድቦ እንዲቆይ ትዕዛዝ የሚሰጡት ምን ምን ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ነው? የሚለው ነጥብ ሲሆን ይህም በዝርዝር ሲታይ፡-

- ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 የተረጋገጠው በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና የመለቀቅ መብት የሚገድብ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የሚሰጡት ምን አይነት ልዩ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ነው?
- ተከሳሹ በዋስ ለመልቀቅ የማያስችሉና የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብት በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በልዩ ሁኔታ ለመገደብ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ማን ነው?
- ተከሳሹን በዋስ ለመልቀቅ የማያስችሉና የተከሳሹን በዋስ የመለቀቅ መብት በፍርድ ቤት ውሳኔ (ትዕዛዝ በልዩ ሁኔታ ለመገደብ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ወገን፣ የማስረዳት ግዴታውን የሚወጣው በምን ደረጃ (standard of proof) እስከምን ድረስ ነው? የሚሉትን ነጥቦች በዝርዝር ማየት የሚጠይቅ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

6. ፍርድ ቤቶች በህገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 የተረጋገጠውን በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና የመለቀቅ መብት የሚገድብ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የሚሰጡባቸውን ጥቅል ሁኔታዎች ህግ አውጭው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 67 ለማመልከትና ለመደንገግ ሞክሯል፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 67 መሠረት አንድ ተከሳሽ በዋስትና የመለቀቅ መብቱን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የሚገደበው፡-

ሀ/ ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን የማይፈጽም የሚመስል የሆነ እንደሆነ

ለ/ ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ ሌላ ወንጀል ይፈጽም ይሆናል ተብሎ ሲገመት ወይም

ሐ/ ምስክሮችን በመግዛት (በማባበል) ወይም አስረጅ የሚሆኑበትን ያጠፋል ተብሎ የሚገመት ሲሆን እንደሆነ ቃል በቃል ተደንግጓል፡፡

ከላይ ዝርዝር ይዘታቸው የተገለጸው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 67 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ዓላማ ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ በተጀመረው የወንጀል ምርመራ ወይም በፍርድ ቤት በተጀመረው የወንጀል ፍርድ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ተግባሮችን ሊፈጽም ይችላል ብሎ ፍርድ ቤቱ የሚገምተውን ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በዋስትና የመለቀቅ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በማረሚያ ቤት ሆኖ ክርክሩን እንዲከታተል በማዘዝ፣ ወንጀል ምርመራው ወይም የፍርድ ሂደቱ ተከሳሹ በዋስ ተለቅቆ ሊፈጽማቸው ይችላል ተብለው ከሚገመቱ አሉታዊ ተግባራት ነፃ በሆነ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ለማስቻል መሆኑን የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 67 ድንጋጌዎች ባህሪ ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

7. ከላይ የተገለጸውን መሠረታዊ ዓላማ ለማሳካት የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና የመለቀቅ መብት እንዲገድብ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ በህገ መንግስት አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 ዕውቅናና ጥበቃ የተሰጠውን መብት የመገደብ ውጤት ያለው በመሆኑ፣ ፍርድ ቤቱ የተከሳሹን በዋስ የመለቀቅ መብት የገደበው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ክርክር የሚያስነሳ ነው፡፤ ከሁሉም በላይ ፍርድ ቤቱ የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብት ለመገደብ የጠቀሳቸው ምክንያቶችና ያስቀመጣቸው ሁኔታዎች ህገ መንግስታዊና ህጋዊ መሰረት ያላቸው ናቸው ወይስ አይደለም? የሚለውን ክርክር የሚያስነሱ ናቸው፡፡

8. ለዚህም መሠረት የሚሆነው የህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ይዘትና ትርጓሜ፣ ድንጋጌው በመንግስት ላይ የሚጥለው ግዴታና ኃላፊነት በወንጀል ፍርድ ሂደት ላይ የሚኖረው ተግባራዊ ተፈፃሚነትና የሚያስከትለው ህጋዊ ውጤት ነው፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 “የተከሰሱ ሰዎች በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ ሁሉ

www.abyssinialaw.com

በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠርና በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው" በማለት የሚደነግግ ሲሆን፣ የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዘኛ ቅጅ "During proceedings accused persons have the right to be presumed innocent until proved guilty according to the law and not to be compelled to testify against themselves" ተብሎ ተደንግጓል፡፡

9. ተከሳሹ ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ የመገመት ህገ መንግስታዊ መብት ያለው በመሆኑ፣ ተከሳሽ በዋስ ከተለቀቀ በኂላ ለወደፊት ይዘታቸው ከላይ የተገለጹት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 67 የተደነገጉ አሉታዊ ውጤት ከሚያስከትሉ ተግባራት አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ይፈጽማል ብሎ ፍርድ ቤቱ ከጅምሩ ግምት እዳይዘበት ዋስትናና ጥበቃ ይሰጠዋል፡፡ ይህም ማለት ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ከቀረበበት የወንጀል ክስ ውጭ የሆኑ በቂ ምክንያትና ማስረጃ ሳይቀርብበት ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 67 ከተዘረዘሩት የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብትን ሊያስገድቡ ከሚችሉ ተግባራት አንደኛውን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ሊፈጽም ይችላል ብሎ ግምት ለመያዝና የተከሳሽን ዋስትና ጥያቄ እንዲሰርዝ ከላይ ይዘቱን የገለጽነው ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ የሚፈቅድ አይደለም በዚህ ምክንያት ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ በወ/መ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 67 ከተዘረዘሩት በዋስ የመለቀቅ መብትን ሊያስገድቡ ከሚችሉ ተግባራት አንደኛውን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ሊፈጽም ይችላል ብሎ ፍርድ ቤቱ ምክንያታዊ ግምትና መደሚደሚያ ላይ ሊደርስ የሚችልባቸውን ፍሬ ነገሮች የማቅረብና የማስረዳት ግዴታ (burdon of proof) ያለበት ዐቃቤ ህግ ነው፡፡

10. በእርግጥ የዐቃቤ ህግ የማስረዳት ሸክም ደረጃና መጠን (standard of proof) ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 67 ከተዘረዘሩት በዋስ የመለቀቅ መብትን ሊያስገድቡ ከሚችሉ ተግባራት አንደኛውን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን በእርግጠኝነት የሚፈፅም መሆኑን በበቂ ሁኔታ የሚያረጋግጥ ማስረጃ በማቅረብ መሆን አይጠበቅበትም፡፡ የዐቃቤ ህግ የማስረዳት ሸክም ደረጃና መጠን (stanedard of proof) ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ፣ የዋስትና ግዴታውን ላይፈጽምና ቀጠሮውን አክብሮ ላይመጣ ይችላል፣ ወይም ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ ሌላ ወንጀል ይፈጽም ይሆናል ወይም ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ ምስክሮችን በመግዛት (በማባበል) ወይም አስረጅ የሚሆኑበትን ያጠፋል ብለው ዳኞች የህሊና ግምት ለመውሰድ የሚያስችሉ ህጋዊ ተቀባይነት ያላቸውና ታዓማኒነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች ከማቅረብ ያለፈ አይደለም፡፡ ይህም ዳኞች የተከሳሹን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ የሚያደርግ ትዕዛዝ የሚሰጡት በመጀመሪያ ዐቃቤ ህግ ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ ከተከሰሰበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ወደ ፊት የሚኖረው ባህሪ ሊፈጽም የሚችላቸው ተግባራትና ስነ ምግባሩ ጥሩ አይሆንም ከሚል

www.abyssinialaw.com

ምክንያታዊ ጥርጣሬና ግምት ላይ እንዲደርሱ የሚያስችል ማስረጃ ወይም ፍሬ ነገር ሲያቀርብና ሲያስረዳ መሆኑን ያሳያል፡፡

11. ከላይ የተገለጸውን መሠረታዊ ሀሳብ ይዤ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን በዋስ የመለቀቅ መብት ለመገደብ የሰጣቸውን ምክንያቶች አንድ በአንድ ተመልክቻለሁ፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን በዋስ የመለቀቅ መብት ለመገደብ የሰጠው የመጀመሪያው ምክንያት ተከሳሽ የተጨማሪ እሴት ታክስና የገቢ ግብር አሳውቆ ባለመክፈሉ ተደራራቢ የወንጀል ቅጣት የሚያስከትሉ ተደራራቢ የወንጀል ክሶች ቀርበውበታል፡፡ አመልካች በስምንት የወንጀል ክሶች መጠኑ ብር 50,374-960 ግብርና ታክስ ያለመክፈል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በተደራራቢ ወንጀሎች ተከሷል፡፡ ተከሳሽ የተከሰሰባቸው ተደራራቢ የወንጀል ክሶች ተደደራቢና ከባድ የወንጀል ቅጣት የሚያስከትሉ በመሆናቸው በወንጀሉ ያልተከፈለው የግብር የገንዘቡ መጠን ከፍተኛ በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረው አስተዋፅኦ የድርጊቱ አፈፃፀም አደገኛነት ያለው በመሆኑ አመልካች በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ አይቀርብም የሚል ነው፡፡

12. ከላይ እንደተገለጸው" የተከሰሱ ሰዎች በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ ሁሉ በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠርና በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው" በማለት የህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 መደንገጉ፣ የአመልካችን በዋስትና የመለቀቅ መብት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለማስገደብ ዐቃቤ ህግ በተከሳሽ ላይ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ይዘት፣ ብዛትና ወንጀሉ ሊያስቀጣ የሚችለው ቅጣት ክብደት መከራከሪያ አድርጎ ሊያቀርብ እንደማይችል እና ዐቃቤ ህግ መከራከሪያ አድርጎ ቢያቀርበው እንኳ ይህ ምክንያት የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብት ለመገደብ የሚያስችል ህጋዊ መሠረትና ተቀባይነት ያለው ምክንያት ተደርጎ በፍርድ ቤት መወሰድ የሌለበት መሆኑን ነው፡፡ በአንድ ሰው ላይ ዐቃቤ ህግ ብዙ የወንጀል ክሶች ማቅረቡ ብቻውን ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም ከሚለው ምክንያታዊ ጥርጣሬና ግምት ለማድረስ የሚያስችል ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ፍሬ ነገር (ማስረጃ) ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም አንድ ተከሳሽ የተከሰሰው በአንድ የወንጀል ክስ ወይም በብዙ የወንጀል ክሶች መሆኑ፣ተከሳሹ በተከሰሰባቸው ሁሉም የወንጀል ክሶች በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብቱን የሚያሳጣው አይደለም፡፡ የተከሳሽ ከፍርድ በፊት ንፁህ ነው ተብሎ የመገመት ህገ መንግስታዊ መብት በአንፃራዊነት መብቱን የማክበርና ማስከበር ግዴታ ባለበት መንግስት ላይ በጠቅላላውና አግባብነት ባላቸው የመንግስት አካላት ላይ በልዩ ሁኔታ የሚያስከትለው ኃላፊነት አለ፡፡

13. የተከሳሽ በተከሰሰበት (በተከሰሰባቸው) ወንጀሎች ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ የመገመት ህገ መንግስታዊ መብት በተከሳሹ ላይ የቀረበውን የወንጀል ክስ በሚያየው የዳኝነት አካል( ፍርድ ቤት) እንደ አንድ የመንግስት አካልና ጉዳዩን በሚያዩ ዳኞች ላይ የሚጥለው ግዴታና

www.abyssinialaw.com

ኃላፊነት አለ፡፡ ይኸውም ህገ መንግስታዊ ኃላፊነትና ግዴታ ተከሳሽ በተከሰሰበት (በተከሰሰባቸው) ወንጀሎች ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ የመገመት መብት የማክበርና የማስከበር ግዴታ እንደሆነ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 20 ንኡስ አንቀጽ 3 እና የህገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ይዘት ተግባራዊ ተፈፃሚነትና ህጋዊ ውጤት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ የዳኝነት አካሉ እንደተቋምና የወንጀል ጉዳዩን የሚያዩት ዳኞች የተከሳሽን በተከሰሰበት (በተከሰሰባቸው) ወንጀሎች ከፍርድ በፊት ንፁህ ነው ተብሎ የመገመት መብት የማክበር ኃላፊነታቸውን የሚወጡት የተከሳሹ ጉዳይ መታየት ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በሚሰጡት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ከህግ አግባብ ውጭ ሳይሸራረፉ ለተከሳሹ መብት ዕውቅናና ከበሬታ መስጠታቸውን በሚያረጋግጥ ሁኔታ ጉዳዩን አይተው እልባት ሲሰጡ መሆኑን የህገ መንግስቱን አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 እና የህገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡

14. ይህም ዐቃቤ ህግ የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብት ለማስገደብ የሚያቀርበው ምክንያት ፍሬ ጉዳይና ማስረጃ ተከሳሹ ከተከሰሰበት (ከተከሰሰባቸው) ወንጀሎች ይዘት ብዛትና ክብደት ውጭ የሆኑ ሌሎች ምክንያቶች መሆን ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡ የወንጀል ጉዳዩን የሚያዩት ዳኞች የተከሳሽን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የሚሰጡት በተከሳሽ ላይ የቀረበበትን የወንጀል ክስ ወይም ክሶች ይዘት ብዛትና ክብደት ተከሳሽ በዋስትና ወረቀት እንዳይለቀቅ ለመወሰን የሚያስችል በቂና ህጋዊ ምክንያት አድርገው በመቀበል መሆን አይገባም፡፡ ምክንያቱም የተከሰሱ ሰዎች በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ ሁሉ በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠርና በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው" በማለት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ድንጋጌ ዳኞች የፍርድ ሂደቱ ሳይጠናቀቅና በተከሳሽ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት ዐቃቤ ህግ በተከሳሽ ላይ ብዙ የወንጀል ክስ ስለቀረበበትና ተከሳሹ በቀረቡበት የወንጀል ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ ተደራራቢ የወንጀል ቅጣት ሊጣልበት ስለሚችል ተከሳሹ ወደ ፊት ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ የሚጣልበትን ተደራራቢ ቅጣት በመፍራት የዋስትና ግዴታውን አክብሮ በቀጠሮው ቀን ፍርድ ቤት ላይቀርብ ይችላል የሚል ግምትና መደምደሚያ እንዲይዙ የሚፈቅድ አይደለም፡፡ ዐቃቤ ህግ በተከሳሹ ላይ ያቀረባቸውን ወንጀል ክሶች ብዛትና ክብደት መነሻ በማድረግ የተከሳሽን ዋስትና መብት ለመገደብ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ከጅምሩ የተከሳሽን ከፍርድ በፊት ንፁህ ነው ተብሎ የመገመት መብት የሚጥስ ነው፡፡

15. በአንጻሩ ዐቃቤ ህግ በተከሳሽ ላይ ብዙ የወንጀል ክስ ስላቀረበበትና ተከሳሹ በቀረቡበት ወንጀል ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ ተደራራቢ የወንጀል ቅጣት ሊጣልበት ስለሚችል ተከሳሹ ወደፊት ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ የሚጣልበትን ተደራራቢ ቅጣት በመፍራት የዋስትና ግዴታውን

www.abyssinialaw.com

አክብሮ በቀጠሮው ቀን ፍርድ ቤት ላይቀርብ ይችላል የሚል ግምትና መደምደሚያ በመያዝ ዳኞች ተከሳሽ በእስር እንዲቆይ የሚሰጡት ትዕዛዝ በአንዱ ወይም በሌላ መልኩ የተከሳሹን ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ መገመት መብት ከህግ አግባብ ውጭ የተሸራረፈና ያልተከበረ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ በይዘቱም ሆነ በውጤቱ፣ ተከሳሽ በዐቃቤ ህግ ከቀረቡበት የወንጀል ክሶች በተወሰኑት የወንጀል ክሶች ወይም በሁሉም የወንጀል ክሶች ጥፋተኛ ሊባልና ሊቀጣ ስለሚችል፣ ተከሳሽ ወደ ፊት ጥፋተኛ ቢባል በፍርድ የሚወሰንበትን የወንጀል ቅጣት ለማምለጥ በዋስ ቢለቀቅ ከአገር ሊጠፋ ይችላል የሚል ዕምነትና ግምት ዳኞች ያላቸው መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይህም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በህገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት ዳኞች የተከሳሽን ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ መገመት መብት ባከበረና በሚያስከብር ሁኔታ ጉዳዩን አይተው እልባት የመስጠት ግዴታና ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጡ መሆናቸውን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ይሆናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የተከሳሽን ዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የተጠቀመበት ከላይ የተገለፀው ምክንያት ዳኞች አስቀድመው ተከሳሹ የተከሰሰባቸውን ወንጀሎች ፈጽሟቸዋል የሚል ግምትና አቋም ሳይዙ ገለልተኛ ሆነው ጉዳዩን አይተዋል ወይም አላዩም የሚል ክርክር የሚያስነሳ የህግ አተረጓጎም ነው፡፡

16. በእኔ እምነት ዐቃቤ ህግ የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብት በመቃወም ካቀረበው ክርክር አንፃር፣ ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 76 (ሀ) በተደነገገው መሠረት ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን የማይፈጽም ይመስላል ወይም አይመስልም? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን ፍርድ ቤቱ መመልከትና መመዘን ያለበት በተከሳሹ ላይ ዓቃቤ ህግ ያቀረበው ወንጀል ክስ ብዛትና ክብደት ሳይሆን የተከሳሽ ግላዊ ሁኔታ ባህሪውን፣ ስብዕናውን እና ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን በማክበር የፍርድ ሂደቱን እንዲከታተል ሊያደርጉት የሚያስችሉ ግላዊ፣ ቤተሰባዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችና ሌሎች ተጨባጭ ኩነቶች መኖራቸውን ወይም አለመኖራቸውን በመመዘን መሆን እንዳለበት የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6፣ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3፣ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የወንጀለኛ መቅጫ ስነ- ስርዓት ሕግ ቁጥር 67/ሀ/ ድንጋጌዎች የጣምራ ንባብ ይዘት፣ ዓላማና ተግባራዊ ተፈጻሚነት ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፍ/ቤቱ ጭብጡን መወሰን ያለበት ተከሳሹ በዋስ ከተለቀቀ በኂላ፣ ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን እንዲያከብር ለማድረግ የሚያስችሉና ተከሳሹን በእስር ከማቆየት የተሻሉ ሌሎች አማራጮች፣ ለምሳሌ ተከሳሽ በዋስ ከተለቀቀ በኂላ ከአገር እንዳይወጣ ወይም ከሚኖርበት ከተማ ውጭ እንዳይንቀሳቀስ በመገደብና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ትእዛዞች በመስጠት ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን እንዲያከብር ለማድረግ የሚቻል መሆኑን

ወይም አለመሆኑን በማገናዘብና በማጣራት መሆን ይገባዋል፡፡ በማጣራቱ ሂደት ፍ/ቤቱ ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን እንዲያከብር ለማድረግ የሚያስችሉና ተከሳሹን በእስር ከማቆየት የተሻሉ ሌሎች አማራጮች መኖራቸውን ከተረዳ ተከሳሽ በዋስ እንዲለቀቅ የሚሰጠውን ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን እንዲያከብር ለማድረግ ከሚያስችሉ ሁኔታዎች /የመብት ማዕቀቦች/ ጋር ተጣምረው እንዲፈጸሙ ትእዛዝ በመስጠት ፣ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6፣ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3፣ እና አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1፣ እና የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 67 /ሀ/ ድንጋጌዎች የጣምራ ንባብ ይዘትና ዓላማ ማሳካት ይገባዋል ብዬ አስባለሁ፡፡

17. በእኔ እምነት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 67/ሀ/ በተደነገገው መሰረት ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን የማይፈጽም ይመስላል ወይም አይመስልም? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን በተከሳሹ ላይ ዓቃቤ ሕግ ካቀረበው የወንጀል ክስ ክብደትና ብዛት በበለጠ፣

- ተከሳሽ በአገር ውስጥ ተለይቶ የሚታወቅ ቋሚ አድራሻ ያለው መሆኑ ወይም አለመሆኑ ፣
- ተከሳሹ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ ወይም አለመሆኑና ተከሳሽ ከቤተሰቦቹ ጋር በአገር ውስጥ የሚኖር መሆኑ ወይም አለመሆኑ፣
- ተከሳሹ በአገር ውስጥ የሚተዳደርበት ቋሚ ስራ፣ የገቢ ምንጭ ወይም ንግድ ወይም ኢንቨስትመንት ያለው መሆኑ ወይም አለመሆኑ፣
- ተከሳሹ በዋስ ከተለቀቀ በኂላ ያለበቂና አሳማኝ ምክንያት በቀጠሮው ቀን ፍርድ ቤት ባይቀርብ ፍ/ቤቱ በሕግ አግባብ በቀጣይ በሚሰጠው ትእዛዝ ሊያጣው የሚችለው መብትና ጥቅም ያለ መሆኑን ወይም አለመሆኑን፣
- ተከሳሽ በዋስ ከተለቀቀ በኂላ በነጻነቱ ላይ ሌሎች ገደቦችን በመጣል ለምሳሌ ከአገር እንዳይወጣ በመገደብ፣ እንደግለሰቡ ሁኔታ ተከሳሽ በሚኖርበት ከተማ ወይም ቀበሌ በየቀኑ ወይም በየሳምንቱ ለክፍሉ ፖሊስ በአካል እየሄደ ሪፖርት የሚያደርግበትንና ፖሊስም ተከሳሹ በፍርድ ቤት የታዘዘውን ገደብና ሁኔታ እያከበረ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርግና ፍ/ቤቱ ያስቀመጣቸውን ገደቦችና ሁኔታዎች ተከሳሹ ጥሶ ባገኘው ጊዜ፣ ተከሳሹን በቁጥጥር ስር አውሎ በዋስ እንዲለቀቅ ትእዛዝ ለሰጠው ፍ/ቤት የሚያቀርብበትን አሰራር በመከተል ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ እንዲቀርብ ለማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ ያለ መሆኑን ወይም አለመሆኑን፣
- በተከሳሹ ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ ሊወሰን የሚችል መሆኑን ወይም አለመሆኑን፣

www.abyssinialaw.com

- ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን ባለማክበሩ ጉዳዩ በሌለበት ቢታይና ተከሳሽ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ፣ ፍ/ቤቱ ሊወስን የሚችለውን የወንጀል ፍርድና ቅጣት፣ መንግስት ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠውን የወንጀል ፍርድና ቅጣት ተከትሎ በሕግ መሰረት በተከሳሽ ንብረት ላይ የሚሰጠው የመወረስ ውሳኔ ተከሳሹ ሊያጣ የሚችለው ገንዘብና ሃብት፣ ተከሳሹ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ የፍርድ ሂደቱን ጥሎ እንዲፈረጥጥ የሚገፋፉ ናቸው ወይስ ተከሳሽ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ የቀጠሮውን ቀን አክብሮ የፍርድ ሂደቱን እንዲከታተል የሚያስገድዱ ተጨባጭ ምክንያቶች የሚለውን በማነጻጸር፣ ከእያንዳንዱ ተከሳሽ ሁኔታ ጋር በማየትና በመመዘን ፍ/ቤቱ ምክንያታዊ ግምትና ሎጅካል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ ይገባዋል የሚል ሃሳብ አለኝ።

18. ከዚህ አንጻር የስር ፍ/ቤት ዓቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ ተደራራቢ የወንጀል ክስ ማቅረቡንና ተከሳሽ ሊጣልበት የሚችለውን ተደራራቢ ቅጣት ለመሸሽ በዋስ ቢለቀቅ ቀነ - ቀጠሮውን አክብሮ ፍ/ቤት ሊቀርብ አይችልም በማለት የሰጠው ምክንያት ከላይ በተራ ቁጥር 15 እና 16 የገለጽኳቸውን መሰረታዊ ሁኔታዎች ያላገናዘበና ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ ያላገኘሁት በመሆኑ አመልካች በዋስ ሊለቀቅ ይገባል በማለት በሃሳብ ተለይቻለሁ።

19. ከላይ በዝርዝር የገለጽኩት እንዳለ ሆኖ፣ የስር ፍ/ቤት አመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ አመልካች በስምንት ተደራራቢ የወንጀል ክሶች ማለትም ተጠሪ በወንጀል መዝገብ ቁጥር 141352 ባቀረባቸው በ 37ኛ ፣ 38ኛ፣ 40ኛ፣ 41ኛ፣ 42ኛ፣ 43ኛ፣ 44ኛ እና በ 45ኛ በድምሩ በስምንት ክሶች ብር 50,374,960 ግብርና ታክስ እንዳይከፈል በማድረግ ወንጀል እንደተከሰሰና መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ብይን እንደተሰጠበት አድርጎ በብይኑ ውስጥ ያሰፈረው ፍሬ ሃሳብ ሊታረምና ተገቢ የሕግ ትርጉም ሊሰጥበት የሚገባ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ለዚህም ምክንያቱ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የዋስትና መብት ለመገደብ ተደራራቢ ናቸው ብሎ የጠቀሳቸው ስምንት ክሶች፣ አመልካች ላይ የቀረቡትን የወንጀል ክሶች ብቻ የሚመለከቱ ሳይሆኑ አመልካቹ በስራ አስኪያጅነት ሲያስተዳድረው የነበረውና በስር ፍ/ቤት አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የሆነው ጂ ኤች ሴሚክስ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የተከሰሰባቸውን የወንጀል ክሶች ጨምሮ በመቁጠር የአመልካችን ዋስትና መብት መገደቢያ ምክንያት አድርጎ የስር ፍ/ቤት ብይን የሰጠ በመሆኑ ነው።

20. ከላይ ይዘታቸውን በተራ ቁጥር 1 የገለጽኳቸውና ተጠሪ በወንጀል መዝገብ ቁጥር 141352 በ 37ኛ፣ 41ኛ እና በ 43ኛ ያቀረባቸው ወንጀል ክሶች አመልካች በስራ አስኪያጅነት ሲያስተዳድረው የነበረው በስር ፍ/ቤት አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ ሆነው ጂ ኤች ሴሚክስ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የከሰሰባቸው የወንጀል ክሶች ናቸው። የንግድ ድርጅቱ የተከሰሰባቸው የወንጀል ክሶች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 34 ፣ በአዋጅ ቁጥር 285/94 እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 ልዩ ድንጋጌዎች መሰረት የንግድ ድርጅቱ ለተከሰሰበት ወንጀል

ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ፣ አመልካች ሳይሆን ራሱ የንግድ ድርጅቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የሚወሰንበት የእስራትና የጽኑ እስራት ቅጣት ወደ ገንዘብ ተለውጦ የሚቀጣባቸውና ቅጣቱን እንዲፈጽም የሚደረግባቸው የወንጀል ክሶች ናቸው፡፡ አስራ ዘጠነኛው ተከሳሽ ሕግ ወለድ ሰው በመሆኑ በፍርድ ሂደቱ በእስር ላይ አይገኝም፡፡ በዚህ ምክንያት አስራ ዘጠነኛው ተከሳሽ ያቀረበውና ሊያቀርበው የሚችለው የዋስትና መብት ጥያቄ የለም፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ፣ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረባቸውን የወንጀል ክሶች ብቻ ሳይሆን፣ በስር ፍ/ቤት አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የሆነው የንግድ ኩባንያ የከሰሰባቸውን የወንጀል ክሶች ጨምሮ በመቁጠር አመልካች ስምንት ተደራራቢ ወንጀል ክሶች እንደቀረቡበት አድርጎ ብይን መስጠቱ በሰበር ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡

21. የስር ፍ/ቤት የተከሳሹ የዋስትና መብት ጥያቄ ውድቅ ያደረገበት ሌላው ምክንያት ተከሳሹ ያለውን የኢኮኖሚ አቅም ተጠቅሞ ከአገር ሊወጣ ይችላል የሚለውን ግምት ሊያስተባብል የሚችል አሳማኝ ምክንያት በተከሳሽ በኩል አልቀረበም በማለት ነው፡፡ ሲጀመር ከፍተኛ የገንዘብ አቅም ያለው በወንጀል የተከሰሰ ባለሃብት ያለውን የገንዘብ አቅም ከቀረበበት የወንጀል ክስ ለማምለጥ ሊጠቀምበት ይችላል የሚል ግምትና መደምደሚያ ዳኞች ከፍርድ በፊት እንዲይዙ፣ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የተከሳሽ ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ መገመት መብት የሚፈቅድ አይደለም፡፡

22. በሁለተኛ ደረጃ ተከሳሽ በዋስ ቢፈታ ያለውን የገንዘብ አቅም ከቀረበበት የወንጀል ክስ ለማምለጥ ሊጠቀምበት ይችላል የሚለውን ፍሬ ጉዳይ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ዓቃቤ ሕግ እንጅ ተከሳሹ አይደለም፡፡ ዓቃቤ ሕግ በህግ የተጣለበትን የማስረዳት ግዴታ የሚወጣው ተከሳሹ ከፍተኛ የገንዘብ አቅም ያለው መሆኑን ለፍርድ ቤቱ በማሳየት ብቻ አይደለም፡፡ በአንጻሩ ተከሳሹ በአገሪቱ ውስጥ ያጠራቀመው ሃብት ወይም ተከሳሹ ኢንቨስት ያደረገበት የንግድ ዘርፍ በባህሪው፣ ተከሳሽ በዚህ አገር ያለውን እሴትና ገንዘብ በቀላል ሰብስቦ ወደ ሌላ አገር ለማሻገር ውጣ ውረድን የማያስከትል መሆኑን፣ ተከሳሹ በዚህ አገር የሚሳሳለትና ወደ ኋላ የሚቀር በቀላሉ ሊያንጉዘው የማይችል ቋሚ ሃብት የሌለው መሆኑን ተከሳሹ ከአገር ሊጠፉ ይችላል የሚልባቸውን፣ ሌሎች ተጨባጭ ምክንያቶች በማቅረብ መሆን አለበት፡፡

23. በያዝነው ጉዳይ ተከሳሽ በተከሰሰበት ወንጀል ሳይከፍለው የቀረ ነው ተብሎ በወንጀል ክሱ ከተጠቀሰው የግብርና ታክስ ገንዘብ ብር 50,374,960 በብዙ እጥፍ የሚበልጥ ካፒታል አውጥቶ በረዥም ጊዜ ኢንቨስትመንት ካፒታሉን በሚመልስ ሆቴል ግንባታ ስራ ያዋለ መሆኑን ተጠሪ አይክድም፡፡ ይህም ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ በዚህ አገር ኢንቨስት ያደረገውን ሃብትና ገንዘብ በቀላሉ ሊያንቀሳቅሰው በማይችለው የኢንቨስትመንት ዘርፍ ላይ ያፈሰሰው

www.abyssinialaw.com

መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ተከሳሹ በዚህ አገር የሚሳሳለትና ወደ ኋላ የሚቀር በቀላሉ ሊያንቀሳቅሰው የማይችል ቋሚ ሀብት ያለው መሆኑና ተከሳሹ ያለው ቋሚ ሃብት በወንጀል ስራው አግኝቶታል ከሚባለው የግብር ገንዘብ በብዙ እጥፍ የሚበልጥ መሆኑ ካላከራከረ፣ ይኸ ምክንያት ተከሳሹ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ የፍርድ ሂደቱን እስከመጨረሻው እንዲከታተል የሚያደርገው የንብረት መብትና ጥቅም ያለው መሆኑን ለመደምደምና ተከሳሽን በዋስ ለመልቀቅ የሚያስችል ምክንያት ከሚሆን በስተቀር ተከሳሽን የዋስትና መብት ለመንፈግ የሚያስችል አይሆንም፡፡

24. ተከሳሽ ከፍተኛ ኢኮኖሚ አቅም ያለው መሆኑን ፍ/ቤቶች የተከሳሽን የዋስትና መብት ለመገደብ በቂ ምክንያት አድርገው መቀበላቸው፣ ኢንቨስተሮችን ወደ አገራችን ለመሳብ በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል የዋስትና ሕግ ድንጋጌ አተረጓጎም ነው፡፡ መንግስት የተጀመረውን ፈጣን ልማትና ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማፋጠንና ለማስቀጠል ኢንቨስትመንት ይፈልጋል፡፡ መንግስት የአገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስተሮች መዋዕለ ነዋይ፣ ገንዘብና ካፒታል ፍሰት ለማሳደግና ለመሳብ ከሌሎች ኢንቨስትመንት ከሚቀበሉ አገሮች ጋር በሕግ ፣ በአስተዳደርና በፍትህ ዘርፍ ተወዳዳሪና ተመራጭ ሆኖ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡ መንግስት ኢንቨስተሮችን ለመሳብ የኢንዱስትሪ ፓርክ በመገንባት፣ ከሊዝ ነጻ መሬት በመስጠት፣ የታክስ፣ የግብርና ሌሎች ማበረታቻዎችን በሕግ ከመደንገግና ተፈጻሚ ከማድረግ አልፎ፣ ለውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስተሮች ዓለማቀፍ የመድን ዋስትና እየሰጠ መሆኑን በዚህ ዙሪያ የወጡ የሕግ ማእቀፎችን፣ የተደረጉ ዓለማቀፍ ስምምነቶችን ይዘትና ተግባራዊ አፈጻጸም በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

25. በአገር ደረጃ የተለያየ ማበረታቻ ተሰጥቷቸው፣ መዋዕለ ነዋያችንን በዚህ አገር ኢንቨስት ማድረግ ይሻለናል ብለው አገራችንን መርጠው የመጡ ከፍተኛ የገንዘብ አቅም ያላቸው ባለሃብቶች በወንጀል ተጠርጥረው ወይም ተከሰው በቁጥጥር ስር የሚውሉበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት በግልጽ በብይኑ ባሰፈረው መንገድ፣ ተጠርጣሪዎቹ ወይም ተከሳሾቹ ባለሃብቶችና ከፍተኛ የገንዘብ አቅም ስላላቸው ከአገር ሊጠፉ ይችላሉ የሚል ግምትና መደምደሚያ ፍ/ቤቶች እየያዙ የዋስ መብታቸውን የማያከብሩላቸው መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይህንን ግምትና የዋስትና ሕግ ድንጋጌ አተረጓጎም ይህ ሰበር ችሎት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ ፣ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 እና በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን ሳያርመው ማለፉ ተገቢ አይደለም ብዬ አስባለው፡፡ ይህ የሕግ አተረጓጎም አገሪቱን መርጠው ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለሃብቶች በወንጀል በተጠረጠሩ ወይም በተከሰሱ ጊዜ ይዘውት የመጡት ሃብት ከፍርድ በፊት እነርሱን አስሮ ለማቆየትና የዋስትና መብት ለመንፈግ የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል የሚያረጋግጥ፣ ለባለሃብቶቹ ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ

www.abyssinialaw.com

የመገመትና የነጻነት መብት ዋስትናና ጥበቃ የማይሰጥ አስፈሪና ባለሃብቶቹን በሩቁ እንዲሸሹ የሚያደርግ የሕግ አተረጓጎም ይሆናል፡፡

26. የሕግ አተረጓጎማችን የኢንቨስተሮች /ባለሃብቶች/ በወንጀል ተጠርጥረው በተያዙ ጊዜ ወይም በወንጀል በተከሰሱ ጊዜ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 የተረጋገጠላቸውን ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ የመገመት መብት፣ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 የተረጋገጠላቸውን በዋስ የመለቀቅ መብትና በአንቀጽ 25 የተረጋገጠውን እኩል የሕግ ጥበቃና የዋስትና ማግኘት መብት የሚጥስና በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ፣ ፈርጀ ብዙ የሆኑ ችግሮችን የሚያስከትል የሕግ አተረጓጎምና ውሳኔ ነው የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡ ከዚህ አንጻር የስር ፍ/ቤት አመልካች በዋስ ቢለቀቅ ያለውን ኢኮኖሚ አቅሙን ተጠቅሞ ከአገር የማይወጣ ስለመሆኑ ፍ/ቤቱን የሚያሳምን ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ የዋስትና ጥያቄውን አልተቀበልነውም በሚል መንገድ የተሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚል እምነት ስላለኝ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

27. የስር ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ከዚህ በፊት፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 በሰጠው አስገዳጅ ትርጉም የአመልካችን ዋስትና መብት ለመንፈግ በዋቢነት ሲጠቅስ በዚህ መዝገብ የተከሳሽ የዋስትና ጥያቄ ሲታይ የነበሩ ፍሬ ጉዳዮች፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ከተሰጠባቸው ፍሬ ጉዳዮች የሚለያዩበትና የተለየ የሕግ ትርጉም ለመስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን በአግባቡ አላገናዘበም፡፡ በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 የዋስትና ክርክሩ የተነሳው ተከሳሾች የወንጀል ክስ እንደቀረበባቸው ወዲያውኑ ክሱ በቀረበባቸው በሳምንታት ጊዜ ውስጥ ነው፤ በዚህ መዝገብ የአመልካች የዋስትና ጥያቄ አከራካሪ የሆነው አመልካች በቀረበበት የወንጀል ክስ ምክንያት ሶስት አመት ከስድስት ወር በላይ በእስር ከቆየ በኂላ ነው፡፡ አንድ ተከሳሽ ከፍርድ በፊት ታስሮ የቆየበት ጊዜ ተከሳሹ በዋስ እንዲለቀቅ ወይም በእስር እንዲቆይ በመወሰን ሂደት የራሱ የሆነ ትርጉምና ፋይዳ እንደዚሁም ህጋዊ ውጤት አለው፡፡ ረዥም ጊዜ በወሰደ የፍርድ ሂደት ምክንያት፣ አመልካች ከፍርድ በፊት ረዥም ጊዜ በእስር የቆየ መሆኑ በራሱ፣ ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም ከሚለው ሎጅካል መደምደሚያና ግምት ላይ ለመድረስ የማያስችልና አመልካቹን የዋስትና ጥያቄ ለመቀበልና በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በመውጣት የአመልካች የዋስትና ጥያቄ በልዩ ሁኔታ አይቶ ለመወሰን የሚያስችል ምክንያት ነው፡፡

28. ከዚህ በተጨማሪ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠውና የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ያደረገው አዋጅ ቁጥር 285/1994 እና የአዋጅ ቁጥር 286/1994 የወንጀል ድንጋጌዎች ይዘትና ቅጣት ላይ መሰረታዊ የሕግ ማሻሻያና ለውጥ በሕግ አውጭው ከመደረጉ በፊት ነው፡፡ አንድ ተከሳሽ

www.abyssinialaw.com

ተከሶበት የነበረው የወንጀል ድንጋጌ፣ የተከሳሹ ጉዳይ በመታየት ላይ እያለ፣ ተከሳሽ የተከሰሰበትን የሕግ ማዕቀፍ በሂደት በህግ አውጭው ተከሳሹን የሚጠቅም ይዘት ባለውና ቀላል ቅጣት በሚደነግግ ሌላ ሕግ የተሻሻለና የተለወጠ መሆኑ የተከሳሹን የዋስትና ጥያቄና ከተሻሻለው ህግ አንጻር አይቶ ለመወሰን የሚጠቅም መሆኑ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 67 ድንጋጌዎች ፣ ከሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 ፣የወንጀል አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 6 አስገዳጅ ድንጋጌ ጋር በማጣመር ለመተርጎምና ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካችን በተደራራቢ የወንጀል ክስ የተከሰሰባቸው የአዋጅ ቁጥር 285/1994 እና የአዋጅ ቁጥር 286/1994 ወንጀል ድንጋጌዎች፣ ሕግ አውጭው ባወጣው የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ተሻሽሏል፡፡ የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ድንጋጌዎች አመልካችን የሚጠቅም ይዘትና ቅጣት መጠን ያላቸው መሆኑን ድንጋጌዎቹን በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሲሰጥ በወቅቱ ባመለከቱት ተከሳሾች ላይ ተፈጻሚነት ነበራቸው የአዋጅ ቁጥር 285/1994 እና የአዋጅ ቁጥር 286/1994 ወንጀል ድንጋጌዎች፣ አመልካችን የሚጠቅም ይዘት ባለው አዋጅ ቁጥር 983/2008 ድንጋጌዎች የተለወጡና የተሻሻሉ መሆኑን ሳያገናዝብ የስር ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በአሁኑ ወቅት የተሻረ የሕግ ማዕቀፍ መሰረት በማድረግ በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አላግባብ በዋቢነት በመጥቀስ የአመልካችን ዋስትና ጥያቄ ውድቅ ያደረገ መሆኑን የሚያሳይና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

29. ከላይ በዝርዝር በገለጽኳቸው የሕግ አተረጓጎም ልዩነቶችና ዝርዝር ምክንያቶች የስር ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የሰጡት የሕግ ትርጉምና ውሳኔ ተሽሮ አመልካች በዋስ ሊለቀቅ ይገባል የሚል አቋም ስላለኝ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

# አፈፃፀም

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 117735

መጋቢት 28 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች-፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

ፊይሳ ወርቁ

አመልካች፡- ህጻን ሣራ ማርቆስ - ሞግዚት ብርነሽ ሁንዴ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ስዩም አሰፋ
2. አቶ ዮሐንስ አሰፋ
3. ወ/ት አብነት አሰፋ
4. አቶ ብሩክ ግርማ

(1–4) 3ኛ ተጠሪ የ4ቱም ተጠሪዎች ጠበቃ አቶ አያሌው አለማየሁ ቀረቡ

5. አቶ ማርቆስ አሰፋበሆኑት - መብታቸው ታልፏል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈጻጸምን የሚመለከት ክርክር ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 157255 በ17/07/2007 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 111970 በ15/10/2007 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የክርክሩን አመጣጥ በተመለከተ፡-በስረ ነገሩ ጉዳይ የህጻን ልጃቸውን ቀለብ የአሁኑ 5ኛ ተጠሪ በየወሩ ብር 5,000 (አምስት ሺህ) እንዲከፍሉ የአመልካች ሞግዚት ውሳኔ ማስጠታቸውን፣ በዚሁ ፍርድ መሰረት ለማስፈጸም እንዲቻል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቁጥሩ

www.abyssinialaw.com

213611 የሆነ የአፈጻጸም መዝገብ አስከፍተው የፍርድ ባለዕዳው በአገር ውስጥ የሌሉ መሆኑን ጠቅሰው ፍርዱ የፍርድ ባለዕዳው ከአሁኖቹ 1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር ከወላጆቻቸው በጋራ በውርስ ያገኙት በየካ ክፍለ ከተማ በወረዳ 5 የሚገኘው ቁጥሩ 327 የሆነው ቤት በሐራጅ ተሸጦ ከሽያጩ ገንዘብ የፍርድ ባለዕዳው ድርሻ በፍርዱ መጠን እንዲከፈላቸው ጥያቄ ማቅረባቸውን፣ፍርድ ቤቱም ይህንኑ ጥያቄ ተቀብሎ ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ ከሽያጩ ገንዘብ ከአንድ አራተኛው ውስጥ ውዝፍ ቀለቡ ታስቦ ለፍርድ ባለመብት እንዲከፈል፣ከውዝፍ ቀለቡ የተረፈው ደግሞ በህጻኗ ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተቀምጦ ዕድሜዋ 18 ዓመት እስኪሞላት ድረስ በየወሩ ብር 5,000 ወጪ እየተደረገ እንዲከፈላት በመዝገብ ቁጥር 213611 በ29/11/2006 ዓ.ም. ትዕዛዝ መስጠቱን፣አፈጻጸሙ በዚህ ሂደት ላይ እያለ የአሁኖቹ 1ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች ውርሱ ተጣርቶ የወራሾቹ ድርሻ ባልተለየበት ሁኔታ በውርስ ሀብቱ ላይ የሐራጅ ሽያጭ ትዕዛዝ የተሰጠው አላግባብ ነው በማለት በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 418 ድንጋጌ መሰረት መቃወሚያ ማቅረባቸውን፣የአፈጻጸም ችሎቱም የአመልካቿን ሞግዚት አስተያየት ከተቀበለ በኃላ የመቃወሚያ አቅራቢዎቹን ክርክር ተገቢ አድርጎ በመቀበል የሐራጅ ሽያጭ ትዕዛዙ እንዲቋረጥ በመዝገብ ቁጥር 213611 በ23/01/2007 ዓ.ም. ብይን መስጠቱን፣በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት የህጻኗ ሞግዚት ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የአሁኖቹ 1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የፍርድ ባለዕዳ ከሆኑት 5ኛ ተጠሪ ጋር የወላጆቻቸው ወራሾች መሆናቸውን በጋራ በማረጋገጥ የተሰጣቸውን የወራሽነት ማረጋገጫ ማስረጃ ጉዳዩ በሚመለከተው ክፍለ ከተማ አስተዳደር አቅርበው ከቤቱ ማህደር ጋር እንዲያያዝ ማድረጋቸው መረጋገጡን፣መቃወሚያ አቅራቢዎቹ ሌላ ወራሽ ወይም የውርሱ ዕዳ ወይም የሚቶቹ ኑዛዜ መኖር አለመኖሩ አልተረጋገጠም ከማለት በቀር ሌላ ወራሽ ወይም የውርሱ ዕዳ ወይም የሚቶቹ ኑዛዜ ስለመኖሩ ያቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ አለመኖሩን እና የወራሽነት ማስረጃ አቅርበው ከቤቱ ማህደር ጋር ካያያዙ ከሁለት ዓመት በኃላም ቢሆን መቃወሚያ አቅራቢዎቹ ውርሱ እንዲጣራ ያቀረቡት ጥያቄ አለመኖሩ ውርሱን የማጣራት ፍላጎት እንደሌላቸው የሚያመለክት መሆኑን ገልጾ ብይኑን በመሻር አፈጻጸሙ በስር ፍርድ ቤት በ29/11/2006 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት እንዲቀጥል በመዝገብ ቁጥር 157255 በ17/07/2007 ዓ.ም. ውሳኔ መስጠቱን፣በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁኖቹ 1ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች በተራቸው ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር ወራሾቹ በስምምነት ውርሱን የማያጣሩ ከሆነ ውርስ አጣሪ ሾሞ ውርሱ እንዲጣራ ካደረገ በኃላ በፍርድ ባለዕዳው ድርሻ ላይ ተገቢውን ትዕዛዝ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሰረት ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመመለስ በመዝገብ ቁጥር 111970 በ15/10/2007 ዓ.ም. ውሳኔ መስጠቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ውርሱ ስላልተጣራ በውርስ ሀብት ላይ ፍርዱን ማስፈጸም አይቻልም በሚል በተለይም የሀጻን የመብት ጥያቄ ወደ ጎን ተትቶ ውርሱ በቅድሚያ ይጣራ ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት በመዝገብ ቁጥር 34703 እና በመዝገብ ቁጥር 35710 ከተሰጠው ገዥ የሕግ ትርጉም አንጻር ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ በጋዜጣ ማስታወቂያ ተጠርተው መልስ ባለመስጠታቸው ምክንያት መብታቸው ከታለፈው 5ኛ ተጠሪ በስተቀር አመልካች እና ቀሪዎቹ ተጠሪዎች የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ከ1ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 418 ድንጋጌ መሰረት መቃወሚያ ያቀረቡት እና ከስር ጀምረው የሚከራከሩት የውርስ ማጣራት ሂደት ተከናውኖ ውጤቱ ባልታወቀበት ሁኔታ ፍርዱ ከውርስ ሀብቱ ውስጥ የ5ኛ ተጠሪ ነው በተባለው ድርሻ ላይ ሊፈጸም አይገባም በማለት መሆኑን የክርክራቸው ይዘት ያመለክታል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠው በዋናነት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 943 (3) ድንጋጌን አነጋገር መሰረት አድርጎ በመያዝ መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያመለክታል፡፡በመሰረቱ በውርስ ማጣራት ሂደት በአጣሪው የሚከናወኑት ተግባራት የውርስ ሀብቱ ምን እንደሆነ እና የውርሱ ተቀባዮች እነማን እንደሆኑ መወሰን፣ዕዳዎችን መክፈልና መቀበል፣ሚቹ ኑዛዜ ትቶ እንደሆነ መፈለግ፣የኑዛዜ ስጦታዎችን መክፈል፣የውርሱን ሀብት ማስተዳደር ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕጉ በቁጥር 944 እና 956 ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡በዳኞች ትዕዛዝ ጊዜው እንዲራዘም ካልተደረገ በቀር የውርሱ የሒሳብ ማጣራት ስራ ሚቹ ከሞተ ከአንድ ዓመት በኃላ የሚዘጋ ስለመሆኑ፣የውርሱ ሒሳብ ማጣራት በተዘጋ ጊዜ ከውርሱ ውስጥ ሆኖ የሚገኘው ንብረት ከወራሹ ሌላው ሀብት ጋር የሚቀላቀል ስለመሆኑ፣የጋራ ወራሾችም እንዳሉ የውርሱ ሆኖ የሚገኘው ንብረት የጋራ ወራሾች ንብረት እንደሚሆን፣የውርሱ አከፋፈል እስኪፈጸም ድረስ በወራሾቹ መካከል ውርሱ ሳይነጣጠል የሚቆይ ስለመሆኑ፣የጋራ ወራሾች የሆኑ ሰዎች ባልተከፋፈሉት የውርስ ንብረት ላይ ያላቸው መብት በፍትሐብሔር ሕጉ ስለጋራ ባለሀብትነት፣ስለሪምና ስለሌሎች ግዙፍ መብቶች በሚለው አንቀጽ በተነገሩት ድንጋጌዎች (ከቁጥር 1257 እስከ 1277) መሰረት የሚወሰን ስለመሆኑ እና ከእያንዳንዳቸው የጋራ ባለሀብቶች ላይ ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያላቸው ሰዎች የባለዕዳውን ድርሻ ለመያዝ የሚችሉ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 1052፣1053፣1060 እና 1260 ድንጋጌዎች ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች የአከራካሪው ንብረት የጋራ ወራሾች መሆናቸውን ገልጸው ጥያቄያቸውን ለፍርድ ቤት በማቅረብ የወራሽነት ማስረጃ በ2004 ዓ.ም.

www.abyssinialaw.com

የወሰዱ መሆኑ፣ይህንንም የወራሽነት የምስክር ወረቀት የቤቱ ማህደር በሚገኝበት ክፍለ ከተማ አስተዳደር በማቅረብ ከቤቱ ማህደር ጋር እንዲያያዝ ያደረጉ መሆኑ፣የውርስ ሀብቱ የሆነውን ቤትም በይዞታቸው ስር አድርገው እየተገለገሉበት መሆኑ በተጠሪዎቹ ያልተካዱ እና በስር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክርም የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡የውርስ ማጣራት ሂደት ተከናውኖ ውጤቱ ባልታወቀበት ሁኔታ ፍርዱ ከውርስ ሀብቱ ውስጥ የ5ኛ ተጠሪ ነው በተባለው ድርሻ ላይ ሊፈጸም አይገባም በማለት በደፈናው ከመከራከር በቀር በአከራካሪው ቤት ላይ መብት ያለው ሌላ የኑዛዜም ሆነ የሕግ ወራሽ ስለመኖሩ እነዚህ ተጠሪዎች በግልጽ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡እነዚህ ሁኔታዎች ተጠቃለው ሲታዩም 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች በሕጉ በተመለከተው የውርስ ማጣራት ሂደት ውስጥ ማለፍ ሳያስፈልጋቸው የውርስ ሀብት መሆኑ በተረጋገጠው ቤት ላይ እያንዳንዳቸው እኩል ድርሻ እንዳላቸው ተስማምተው እና ቤቱንም በቁጥጥራቸው ወይም በይዞታቸው ስር አድርገው በቤቱ ላይ በጋራ ባለሀብትነት መብት በማቋቋም እየተገለገሉበት መሆኑን መገንዘብ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠው በዋናነት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 943 (3) ድንጋጌን መሰረት በማድረግ ሲሆን ይህ ድንጋጌ ከወራሾቹ ከራሳቸው ገንዘብ ጠያቂ የሆኑ ሰዎች የውርሱ ሀብት በሚጣራበት ጊዜ በውርስ ሀብቱ ላይ አንዳችም መብት የሌላቸው መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ በመሰረቱ የውርስ ሀብት እና የጋራ ወራሾች ያልተከፋፈለ የውርስ ንብረት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን ከቁጥር 943 እና 1060 ድንጋጌዎች ይዘት በግልጽ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አንድ ሀብት የውርስ ሀብት ነው የሚባለው ውርሱ በመጣራት ሂደት ላይ ባለበት ጊዜ ስለመሆኑ የቁጥር 942 ድንጋጌ ያመለክታል፡፡በተያዘው ጉዳይ ግን ወራሾቹ በሕጉ በተመለከተው የውርስ ማጣራት ሂደት ውስጥ ማለፍ ሳያስፈልጋቸው ወራሽነታቸውን አረጋግጠው እና የውርስ ሀብቱንም በይዞታቸው ስር አድርገው እና ወደ ራሳቸው ንብረት ቀላቅለው የጋራ ባለሀብትነት መብት በማቋቋም እየተገለገሉበት በመሆኑ አከራካሪው ቤት በቁጥር 1060 ድንጋጌ አነጋገር መሰረት የጋራ ወራሾች ያልተከፋፈለ የጋራ ንብረት እንጂ በቁጥር 942 እና 943 ድንጋጌዎች አነጋገር መሰረት የውርስ ሀብት የሚባል ባለመሆኑ ቁጥር 943 (3) ድንጋጌ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ሊኖረው አይችልም፡፡ቤቱ የወራሾቹ የጋራ ሀብት መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ በቁጥር 1260 (2) ድንጋጌ መሰረት ከጋራ ባለሀብቶቹ መካከል ከአንደኛው ገንዘብ ጠያቂ የሆነ ሰው የዚህኑ የጋራ ባለሀብት ድርሻ የመያዝ መብት ይኖረዋል፡፡

ሲጠቃለል አከራካሪው ቤት የውርስ ሀብት በመሆኑ የውርስ ማጣራት ሂደት ተጠናቆ ውጤቱ ከመታወቁ በፊት ከወራሾቹ ላይ ገንዘብ ጠያቂ ለሆኑ ሰዎች የፍርድ ማስፈጸሚያ ሊውል አይችልም በማለት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ በክርክሩ

www.abyssinialaw.com

የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች እና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡በሌላ በኩል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከአከራካሪው ቤት ውስጥ የ5ኛ ተጠሪ ድርሻ ለአፈጻጸሙ ሊውል ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ቢሆንም 4ኛ ተጠሪ በዚህ ቤት ላይ የውርስ ድርሻ ያላቸው መሆን አለመሆኑ በክርክር ላይ እንደሚገኝ የታወቀ ሆኖ እያለ የክርክሩ ውጤት ባልታወቀበት ሁኔታ ከቤቱ የሽያጭ ገንዘብ ውስጥ ለአፈጻጸሙ ሊውል የሚገባው አንድ አራተኛው ነው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል መታረም ያለበት እና ለአፈጻጸሙ ሊውል የሚገባው ከተጠሪዎቹ ቁጥር አንጻር ከቤቱ የሽያጭ ገንዘብ ውስጥ አንድ አምስተኛ ሆኖ የ4ኛው ተጠሪ አንድ አምስተኛ ድርሻ ለጊዜው በሞዴል 85 ተይዞ እንዲቆይ ከተደረገ በኃላ የወራሽነት ክርክሩ የመጨረሻ ውጤት ከታወቀ በኃላ በዚህ በተቀማጨ ገንዘብ ላይ በአፈጻጸም ችሎቱ እንደአግባብነቱ ተገቢው ትዕዛዝ እንዲሰጥበት ሊደረግ የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ከወላጆቻቸው በጋራ በውርስ ያገኙት በየካ ክፍለ ከተማ በወረዳ 5 የሚገኘው ቁጥሩ 327 በሆነው ቤት የውርስ ሀብት በመሆኑ ውርሱ ተጣርቶ ውጤቱ እስካልታወቀ ድረስ ከወራሾቹ መካከል አንዱ ከሆኑት 5ኛ ተጠሪ ላይ ገንዘብ ጠያቂ በሆኑት አመልካች በአፈጻጸም ሊያዝ አይገባም በማለት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 111970 በ15/10/2007 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሸሯል፡፡
2. አከራካሪው ቤት የወራሾች የጋራ ሀብት እንጂ የውርስ ሀብት ባለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1060 (1) እና (2) እንዲሁም በዚሁ ሕግ በቁጥር 1260 (2) ድንጋጌ መሰረት ከወራሾቹ መካከል የአንደኛው ድርሻ ከዚሁ ወራሽ ላይ ገንዘብ ጠያቂ በሆኑ ሰዎች ሊያዝ ይችላል በማለት ወስነናል፡፡
3. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 157255 በ17/07/2007 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
4. በተራ ቁጥር 3 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ አከራካሪ ቤት በሐራጅ ተሸጦ የ5ኛ ተጠሪ ድርሻ ለአፈጻጸሙ ሊውል ይገባል በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
5. በተራ ቁጥር 3 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ የ4ኛ ተጠሪን ክርክር በዝምታ በማለፍ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
6. 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ከወላጆቻቸው በጋራ በውርስ ያገኙት በየካ ክፍለ ከተማ በወረዳ 5 የሚገኘው ቁጥሩ 327 የሆነው ቤት በሐራጅ ከተሸጠ በኃላ ከሽያጩ

www.abyssinialaw.com

ከሚገኘው ገንዘብ ውስጥ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 213611 በ29/11/2006 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ በገለጸው የአፈጻጸም ስርዓት መሰረት የፍርድ ባለዕዳው የ5ኛ ተጠሪ ድርሻ የሆነው አንድ አምስተኛው ለአፈጻጸሙ እንዲውል፣ሶስት አምስተኛው ለ1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው አንድ አምስተኛ ወጪ ተደርጎ እንዲከፈል፣ቀሪው አንድ አምስተኛ በሞዴል 85 ተይዞ እንዲቆይ ከተደረገ በኃላ የ4ኛ ተጠሪ የአቶ ብሩክ ግርማ የወራሽነት ክርክር የመጨረሻ ውጤት ከታወቀ በኃላ እንደአግባብነቱ ተገቢው ትዕዛዝ እንዲሰጥበት በማለት ወስነናል፡፡

7. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቁት ደግሞ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይላክ፡፡
8. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
9. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 104943

መጋቢት 30 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ይልማ ፈለቀ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጥበቡ ፈለቀ አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ግራ ቀኙን ያከራከረው የአፈፃፀም ጉዳይ ይፈፀም ከተባለው ፍርድ ይዘት ውጭ እንዲፈፀም የሚገልፅ ዳኝነት ተሰጥቷል ወይስ አልተሰጠም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በክርክር ሂደት ከተረጋገጠው የፍሬ ነገሮች ጉዳዮች እና አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበና ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል ነው፡፡

በዚህም መሰረት በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙ ከአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጀምሮ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ባለው ደረጃ በተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ አሁን ለዚህ ሰበር ጉዳይ መነሻ ሆኖ የተያዘውን እና ለአፈፃፀሙ ክስ ምክንያት የሆነውን ጥቅምት 08 ቀን 2005 ዓ.ም በሽማግሌ ዳኞች አማካኝነት ጉዳዩ በእርቅ እንዲያልቅ ከማድረጋቸው በፊት እርቅ ባደረጉበት ምክንያት ግራ ቀኙ ከነበራቸው የንግድ ሽርክና ውል የመነጨ የሀብት ድርሻ ክፍፍል ጥያቄ ምክንያት ጉዳያቸው በፍ/ቤት ቀርቦ በመ/ቁ 10208 በሆነው መዝገብ የአሁን ተጠሪ በስሙ ተመዝግበው የሚገኙትን ንብረቶች ለአሁን አመልካች እንዲያካፍል ፍርድ መስጠቱንና በዚህ ፍርድ መሰረት ለማስፈፀም የአፈፃፀም ክስ ቀርቦ በክርክር ላይ እያሉ በአፈፃፀም ደረጃ የደረሰውን ጉዳይ አስመልክቶ ግራ ቀኙ በሽማግሌዎች አማካኝነት በእርቅ እንዲያልቅ ተስማምተው፤ በሽማግሌዎችም ታይቶ አሁን ለዚህ ሰበር ጉዳይ ምክንያት በሆነው ጥቅምት 08 ቀን 2005 ዓ.ም በተደረገው የእርቅ ስምምነት

www.abyssinialaw.com

መሰረት የአፈፃፀሙ ክስ እንዲዘጋ መደረጉን ገልፆ ለክርክር የአሁን ተጠሪ ይህ በአዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10208 በሆነው መዝገብ ላይ አስቀድሞ ፍርድ ያገኘ ጉዳይ ነው በሚል የቀረበው ከስርዓት ውጭ የቀረበ ነው፤ ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ያለው ጥቅምት 8 ቀን 2005 ዓ.ም የተደረገው የእርቅ ስምምነት ብቻ ነው የሚል ክርክር ከማቅረባቸው በቀር በግልፅ የካዱት ጉዳይ አይደለም፡፡

ከስርዓት ውጭ የቀረበ ክርክር በመሆኑ ምክንያት አንድ ክርክር ውድቅ ሊደረግ የሚችለው ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መነሻና ዋነኛ ዓላማ የሆነውን የተከራካሪ ወገን የመደመጥ መብት ለማስከበር ሲባል ክርክርና ማስረጃ ስርዓቱን ጠብቆ በሚደረግበት ፍ/ቤት እና የክርክር ደረጃ እንዲቀርብ ለማድረግ ነው፡፡ ይህ አሁን በአሁን አመልካች በኩል የጉዳዩን አመጣጥና መነሻ ለማስረዳት ሲባል የቀረበው ክርክር ጉዳይ በፍ/ቤት ቀርቦና ታይቶ በመዝገብ ፍርድ የተቋጨበት ነው የሚል እስከሆነና ይህም አሁን ክርክር ከተነሳበት ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው እስከሆነ ድረስ ፍሬ ነገሩ እንደተባለው አይደለም፤ ሐሰት ነው የሚባል ከሆነ ይህንኑ በቀላል ለመግለፅ እና ለማስረዳት የሚቻል እንጅ ከሕግ ሐሳብ ውጭ በመራቅ የተሟላ የክርክር ሂደትን ጠብቆ በሙግት ደረጃ ነጥሮ እንደማይወጣ ጉዳይ ተቆጥሮ በደፈናው በስርዓት ውጭ ያቀረበ ነው ለማለት የሚያበቃ አይደለም፡፡ በዚህም የተነሳ እና ከክርክሩ መገንዘብ እንደሚቻለው ለአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነውና በሽማግሌዎች ፊት ጥቅምት 02 ቀን 2005 ዓ.ም ባደረጉት የእርቅ ስምምነት ላይ የካርታ ቁጥር 0442/2001 በሚል የተገለፀው የንግድ ቤት ለግራ ቀኙ የሽርክና ስራ ውል በመነጨ የአሁን ተጠሪ ግማሽ ድርሻ ለአሁን አመልካች ሊያካፍል ይገባል ተብሎ ፍርድ ያረፈበት ይህንኑም ፍርድ በማስፈፀም የአፈፃፀም ክስ ከቀረበ በኂላ አፈፃፀም ደረጃ የቀረበውን ክርክር በዚሁ የእርቅ ስምምነት አቋርጠው የእርቅ ስምምነት እንደተካው ተደርጎ በእርቅ ስምምነት መሰረት እንዲፈፀም የተደረገ ስለመሆኑ እስካልተካደ ድረስ የካርታ ቁጥር 0442/2001 በሚል የተጠቀሰው ስህተት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 2008 እንደተመለከተው በእርቁ አፃፃፍ ጊዜ የተፈፀመ የአፃፃፍ ስህተት ነው ከሚባል የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው አይደለም፡፡ የአሁን ተጠሪም ይኸው ንብረት ክፍፍል የሚደረግበት ከዚህ በፊት ፍርድ ያረፈበት በኂላም በሽምግልና የእርቁ ሰነዱ ላይ የተጠቀሰውና ክፍፍል የሚደረግበት ንብረት መሆኑን ተቀብሎ የንብረቱ ግምት በሽማግሌዎች የእርቅ ሰነድ ከተመለከተው ሊያንስ አይገባም፤ በተከታዩም ቀጠሮ ይህ ክፍፍል የተደረገበት ንብረት በባዶ መሬትነት የሚታወቅ እንጅ ቤት የሌለው መሆኑን የከተማው አስተዳደር አስቀድሞ የሰጠውን ማረጋገጫ ቀይሮ ማስረጃ ሰጥቶኛል ስለዚህ ባዶ መሬት የህዝብና የመንግስት ስለሆነ ላካፍል አይገባም በሚል መከራከራቸውን ከመረጋገጡ በቀር በካርታ ቁጥር 0442/2001 በሚል የተሰየመው ንብረት አከራካሪ ሆኖ ከተገኘው ንብረት የተለየ ነው በሚል ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ

www.abyssinialaw.com

እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባለው የክርክር ደረጃ ያቀረበው የማስተባበያ ክርክና ማስረጃ የለም፡፡ አልተገኘም

ስለሆነም ከዚህ በፊት አስቀድሞ በፍርድ ተቋጭቶ ያደረው የግራ ቀኙ ጉዳይ በአፈፃፀም የክስ ደረጃ ደርሶ እያለ በግራ ቀኙ ስምምነት የአፈፃፀሙ ጉዳይ ጥቅምት 08/2005 ዓ.ም በሽማግሌዎች አማካኝነት በተደረገው የእርቅ ስምምነት መሰረት እንዲፈፀም አድርገው መስማማታቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ለመሆኑና በዚህም የእርቅ ስምምነት መሰረት በእርቅ ሰነዱ ላይ የአሁኑ ተጠሪ ለአመልካች በድርሻነት ሊያካፍል ይገባል በማለት የተገለፀውን ገንዘብ ከእነ መጠኑ የአሁኑ ተጠሪ ስለመክፈሉ ተረጋግጦ ቀሪውን ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የንግድ ቤት በሽምግልና ዳኞች የእርቅ ስምምነት መሰረት ሽማግሌዎች አሽጠው ድርሻ ድርሻቸውን ለማከፋፈል ባደረጉት ጥረት ያጋጠመውን መጓተት በማሳየት ቀሪው ተግባር በፍርድ ቤት እገዛ እልባት እንዲያገኝ የተደረገበት አስቀድሞ በፍርድ የተቋጨው እና በአፈፃፀም ደረጃ ደርሶ የአፈፃፀሙ ጉዳይ በእርቅ ሰነዱ መሰረት እንዲመራ የተደረገበት የዚያው ተከታይ እና ቅጥያ ነው ከሚባል በቀር እራሱን እንደቻለ ፍርድም ሊቆጠር የሚችል አይደለም፡፡

በመሆኑም የካርታ ቁጥር 0442/2001 በሚል ጥቅምት 08 ቀን 2005 ዓ.ም ለተደረገው የእርቅ ሰነድ ላይ የተደረገው የካርታ ቁጥር አጠቃቀስ በአፃፃፍ ስራ ምክንያት የተከሰተ ግድፈት መሆኑን የስር የአዳማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተገንዝቦ ያው በፊትም ሆነ በኋላ ስለእርቁ ጉዳይ በተደረሰው ስምምነት ላይ የተጠቀሰው ንብረት እንጂ ሌላ የተለየ ንብረት አለመሆኑን በማረጋገጥ የአፃፃፍ ስህተቱ እንዲረታም አድርጓል ከሚባል በቀር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ እንዳሰፈረው ትችት ለአፈፃፀም መነሻ የሆነው የፍርድ ይዘት በአፈፃፀም የክርክር ጉዳይ ላይ እንዲለወጥ ተደርጓል የሚያሰኝ አይደለም፡፡

የአሁን ተጠሪ በበኩሉ አፈፃፀሙን ከዳር ለማድረስ ሲል ፍ/ቤቱ ባከናወነው የባለሙያ ግምት ስራ ውጤት አስቀድመን በስምምነታቸው ለተገለፀው የንብረቱ ግምት መጠን በታች ሊሆን አይገባም በሚል ያቀረቡትን የመከራከሪያ ነጥብ እንደተመለከትነው በእርግጥም በእርቅ ሰነዱ ላይ የተመለከተው የንብረቱ ግምት ብር 1,000,000.00 /አንድ ሚሊዮን ብር/ ግምት ሽማግሌዎች ሽጠው በሚል ተጠቅሶ እያለ ፍ/ቤቱ ይህንኑ በሽማግሌዎች አማካኝነት የተደረሰውን የንብረት ክፍፍል ስራ ከዳር ለማድረስ ሲል የመሸጫ ዋጋውን እንደገና ሲያስገምት ከዚሁ በሰነዱ ከተገለፀው በታች ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡

ይሁን እንጅ የዚህ አነስተኛ ሆኖ የተያዘው የንብረት ግምት ለሐራጅ ሽያጭ ሥራ ሲባል የተያዘ የመሸጫ መነሻ ዋጋ ነው የሚባል እንጂ ንብረቱ በዚሁ በባለሙያ ግምት መሰረት እንዲሸጥ የተደረገ መሆኑን አያመለክትም በዚሁ ግምት መሰረት ሊሸጥ የሚችል ነው የሐራጅ ውጤት

www.abyssinialaw.com

ከመታወቁ በፊት ለመደምደም የሚቻል አይደለም፡፡ ስለሆነም ውጤቱ እንደስጋታቸው ሆኖ ከተገኘ ከውጤቱ በኂላ ስርዓቱን ጠብቀው እንዲታረም ከማድረግ በቀር የተጀመረውን የአፈፃፀም ጉዳይ ግን ቀሪ ለማድረግ የሚያበቃ የክርክር ይዘት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት የፍርድ ሀተታዎች አንፃር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፋ/ቁ 175732 በቀን 19/12/2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተሉ በፍይል ቁጥር 16457 በቀን 26/02/2006 እና በፋይል ቁጥር 172185 በቀን 11/03/2006 ዓ.ም የሰጡት ዳኝነቶች ፀንተዋል፡፡
2. በስር የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጀመረው የአፈፃፀም ክርክር ጉዳይ ሊቀጥል ይገባል መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ለየራሳቸው ይቻሉ
4. የዚህ የክርክር ውጤት እስከሚታወቅ ድረስ በሚል በዚህ የሰበር መዝገብ ላይ ጥቅምት 05 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

# ልዩ ልዩ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 117907

ግንቦት 22 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካቾች -1ኛ- ወ/ሮ ዘውዴ ፍቅሬ -

2ኛ- አቶ ኃ/ሚካኤል ተስፋየ 1ኛ } አመልካች በራሳቸው እና ስለ 2ኛ አመልካች ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ አበራ ጌታነህ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጥብቅና አገልግሎት ክፍያን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካቾች ላይ በአማራ ክልል ደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘት ሶስት የተለያዩ ጉዳዮችን በመያዝ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ለመከራከር የጥብቅና አገልግሎት ውል አድርገን ተገቢውን አገልግሎት የሰጠሁ ሲሆን በውሉ መሰረት ሊከፍሉኝ የሚገባውን አበል ያልከፈሉኝ በመሆኑ ብር 39,850.00 (ሰላሳ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሃምሳ) ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መልስ በጥብቅና ውሉ መሰረት ተገቢውን አገልግሎት አልሰጠም፤ በክርክሩም ያስገኘልን ጥቅም የለም በመሆኑም የጠበቃ አበል ልንከፍል አይገባም፤ በአንፃሩ አገልግሎት ሳይሰጥ በመጀመሪያ ደረጃ ክፍያ የወሰደውን ብር 5,650.00 (አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ) እንዲመልስ እንዲወሰን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ከሳሽ በዉሉ መሰረት አገልግሎት ሰጥቻለሁ ይበል እንጂ የቀረቡት ማስረጃዎች በተደረገው የጥብቅና ውል መሰረት እስከመጨረሻው አገልግሎት መስጠቱን የሚያስረዱ ባለመሆኑ የዳኝነት ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ተከሳሾች የቅድሚያ ክፍያ ይመለስልን በማለት ያቀረቡት ጥያቄም ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ጉዳዩ በይግባኝ በየደረጃው እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ደርሶ የሰበር ችሎቱ በመጨረሻ ባሳለፈው ውሳኔ ተጠሪ ውል በተደረገባቸው በሶስቱም መዛግብቶች እስከ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ቅሬታ አቅርቦ የሰበር አቤቱታው አያስቀርብም ተብሎ የተዘጋ ስለመሆኑ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከፃፈው ደብዳቤ መረዳት

www.abyssinialaw.com

ይቻላል በማለት ተጠሪ ለሰጠው የጥብቅና አገልግሎት በቁርጥ ብር 20,000.00 (ሃያ ሺህ) አመልካቾች እንዲከፍሉት ወስኗል፡፡የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካቾች ነሀሴ 27/2007 ዓ.ም ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈለው የተወሰነበትን አግባብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ግራ ቀኙም የስር ሙግታቸውን በማጠናከር በፅሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡ከላይ ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የክልሉ ሰበር ችሎት የጥብቅና አገልግሎት እንዲከፈል ባሳለፈው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት ቢኖር በጭብጥነት ይዘን መርምረናል፡፡ በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል የጥብቅና አገልግሎት ውል ስለመደረጉና ስምምነቱም ተጠሪ ባለው የጥብቅና ሙያ ጉዳዩን እስከ መጨረሻ ድረስ ሊከራከርላቸውና በአንፃሩ ለአገልግሎቱ የተጠቀሰውን ዋጋ ሊከፍሉ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ አመልካቾች የተሟላ አገልግሎት ባልተሰጠበት ብር 20,000.00 እንዲከፈል የክልሉ ሰበር ችሎት መወሰኑ የህግ ስህተት ነው በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በሙያው ደንብና ልማድ መሰረት ህግንና ማስረጃን ተንተርሶ እስከመጨረሻ ጉዳዩን በመከታተል በአፈፃፀም እንዲያገኙ ያደረግሁ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት ማግኘት ከሚገባኝ ባነሰ ርትዕን መሰረት በማድረግ መወሰኑ የሚነቀፍ አይደለም ተብሎ ውሳኔው እንዲፀና ተከራክረዋል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ይዘዋቸው በነበሩ ሶስት የአመልካቾች ጉዳዮች እስከ ፌዴራሉ ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርበው የነበረ ስለመሆኑና ለሰበር አያስቀርብም በሚል የመ/ቁ 85890፣85891 እና 84464 የተዘጉ ስለመሆኑ ከፍርድ ቤቱ የተፃፈው ደብዳቤ ተጠቅሶ ከተሰጠው ውሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በገቡት ውል መሰረት እስከ መጨረሻ ድረስ ጉዳዩን ከተከታተሉ እና ከሙያቸው አንፃር እውቀትና ክህሎታቸውን ተጠቅመው አገልግሎት ከሰጡ የተፈለገው ውጤት ባለመምጣቱ ብቻ የተሟላ አገልግሎት አልሰጡም ሊሰኝ የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ምንም አይነት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር የውልም ሆነ የህግ መሰረት ስለሌለው የምንቀበለው አይሆንም፡፡ የነገሩ አጠቃላይ ሁኔታ ታይቶ ተጠሪ ለሰጠው የጥብቅና አገልግሎት በቁርጥ ብር 20,000.00 ይከፈል ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሚባል ህግ ስህተት ባለመኖሩም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 45107 ሰኔ 9 ቀን 2007 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 114888

ህዳር 20 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ አትሁነኝ አልማው ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአማራ ብሔራዊ ክልል ፍትህ ቢሮ ዐ/ህግ አባይነህ ከበደ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ በክልሉ የተሰጠ የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰረዝ የተሰጠን የዲሲፕሊን ውሳኔ ህጋዊነት የሚመለከት ነው፡፡ የድስፒሊን ክሱ የቀረበው አቶ ጓዙሁን አዘዘው የተባለ የድስፒሊን አቤቱታ አቅራቢ ነው፡፡ አቤቱታ አቅርበው በባህር ዳር ዙርያ ወረዳ ይነሳ 3ቱ ቀበሌ በሚች አቶ ወንዴ ተገኘ የገጠር መሬት ይዞታ ምክንያት ከአቶ በሪሁን ወንዴ ጋር እየተከራከሩኩ እገኛለሁ፡፡ አቶ በሪሁን ወንዴ የባህር ዳር ዙርያ ወረዳ የይነሳ 3ቱ ቀበሌም ሆነ በኢትዮጲያ ውስጥ ኗሪ አይደለም፡፡ አቶ በሪሁን ወንዴ ላለፉት ሰላሳ አንድ አመታት በእስራኤል አገር የሚኖር ሰው ነው፡፡ ሆኖም የዲስፒሊን ተከሳሹ ከቀበሌው ስራ አስኪያጅ ጋር በመመሳጠር በአገር ውስጥ ከሌለ ሰው በይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ በማስመሰል የሀሰት መታወቂያ በማውጣት ከጠበቆች ስነ ምግባር ውጭ ተገቢነት የሌለው ስራ በመምራትና ማስረጃ በማቅረብ ፍትህ የሚያጓድል ስራ እያሰራ ስለሆነ ፍትህ ቢሮ ክትትል አድርጎ የእርምት እርምጃ እንዲወስድበት በማለት በጽሁፍ አቤቱታ አቅርቧል፡፡
2. አመልካች የአቶ በሪሁን ወንዴ ጠበቃ ሆነው በተለያዩ ፍ/ቤቶች የተለያየ ክርክር እያቀረበ መሆኑን ገልፆ፣ የጥብቅና አገልግሎት በደንበኛዋ እየሰጠሁ ያለሁት በክልሉ ፍትህ ቢሮ የሰነዶችና ጠበቆች ማረጋገጫና ምዝገባዎች የስራ ሂደት ተገኝተው ደንበኛዬ ታህሳስ 22 ቀን 2005 ዓ/ም በህጋዊ መንገድ በሰጡኝ የውክልና ሰነድ መሰረት ነው፡፡ ለአቶ በሪሁን ወንዴ

www.abyssinialaw.com

የቀበሌ መታወቂያ አላወጣሁም የውክልና ሰነድም በህገ ወጥ መንገድ አላወጣሁም፡፡ ደንበኛዬ በእስራኤል አገር የሚኖር ቢሆንም ትውልዳቸው ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የይነሳ 3ቱ ቀበሌ ነው፡፡ ለዲስፒሊን ምክንያት የሆነው ጉዳይ በወረዳ ፍርድ ቤትና በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እየታየ ይገኛል፡፡ ፍትህ ቢሮ ህጋዊነቱን አረጋግጦ በሰጠኝ የውክልና ማስረጃ ምክንያት ልከሰስ አይገባኝም በማለት መልስ የሰጠ መሆኑን ተረድተናል፡፡

3. የክልሉ ፍትህ ቢሮ የጠበቆች ዲስፒሊን ጉባኤ በአመልካች ላይ የቀረበው የዲስፒሊን አቤቱታ እውነትነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚመለከታቸውን የባህር ዳር ወረዳ አስተዳደር አካላትና የይነሳ 3ቱ ቀበሌ አስተዳደር እንደዚሁም የኢሜግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ መምሪያ አግባብነት ያለው ማስረጃ እንዲሰጡት ጠይቋል፡፡ ከሚመለከታቸው የአስተዳደሩ አካላት ጋር በመሆን ተገቢውን ማጣሪያ ያደረገ መሆኑንና በማጣራቱ ሂደት በ2005 ዓ/ም አቶ በሪሁን ወንዴ ወደ አገር ውስጥ ስለመግባቱም ሆነ ከአገር ስለመውጣቱ መረጃ ያላገኘ መሆኑን የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ መምሪያ በጽሁፉ የገለጹለት መሆኑን አቶ በሪሁን ወንዴ የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የይነሳ 3ቱ ቀበሌ ነዋሪ አለመሆኑን የቀበሌው አስተዳደር በፅሁፍ የገለጸ መሆኑን፣ አቶ በሪሁን ወንዴ በአንድ ወቅት ከእስራኤል አገር በመጣበት ጌዜ የይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የቀበሌ መታወቂያ እንዲሰጠው ጠይቆ የነበረ መሆኑና የቀበሌው ነዋሪ መሆኑን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ማይሰጠው መሆኑን የባይነሳ ሶስቱ ቀበሌ አስተዳደር ተነገረው መሆኑ፣አቶ በሪሁን ወንዴ የባይነሳ ሶስቱ ቀበሌ ነዋሪ መሆኑን ሚያረጋግጥ መታወቂያ ያለው መሆኑን በመግለፅ ለባህርዳር ዙሪያ ወረዳ የመሬት አስተዳደርና የአካባቢው ጽ/ቤት መታወቂያ ይዞ የአቀረበው አመልካች መሆኑን እንዳረጋገጠ በመግለጽና አመልካች ከዚህ በፊት የጥብቅና ፈቃድ ለማውጣት የሀሰት ማስረጃ /የስራ ልምድ ተጠቅሟል የሚል ክስ ቀርቦበትና ይህም ተረጋግጦ በቢሮ ኃላፊ ውሳኔ ሳይቀጣ የታለፈ መሆኑን ገልፆ የአመልካች የሀሰት መታወቂያ በመጠቀም የተሚጋችነት ውክልና ማስረጃ የወሰደና አርሶ አደሮችን በመከላከል በከፍተኛ እንግልት በመዳረግ ከባድ የድስፒሊን ጥፋት ፈጽሟል በማለት የአመልካች የጥብቅና ፍቃድ እንዲሰረዙና ስሙ ከጠበቆች መዝገብ እንዲሰረዝ የሚል የውሳኔ ሀሳብ አቅርቦ የድስፒሊን ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ የቢሮ ኃላፊ ተቀብሎ አጽድቆታል፡፡ ውሳኔ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይገባኝ ሰሚ ችሎት ሰበር ችሎት ጸንቷል፡፡

4. አመልካች ሰኔ 18 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በ2005 ዓ/ም አቶ በሪሁን ወንዴ ወደ አገር ውስጥ መጥቶ የነበረ መሆኑን አቤቱታ አቅርበው ክዶ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ የኢምግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ መምሪያ አመልካች አቶ በሪሁን ወንዴ በ2005 አ/ም ወደ አገር ውስጥ የገባም ሆነ የወጣ ስለመሆኑ መረጃ አላገኘንም ከማለት ውጭ ወደ አገር ውስጥ ያልገባ ስለመሆኑ የሰጠው ማስረጃ የለም፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች በዲስፒሊን የተከሰሱበትን ጥፋት ስለመፈጸሜ በበቂ ሁኔታ ሳይረጋገጥብኝ በከባድ የድስፒሊን ጥፋት ጥፋተኛ መባሉ

www.abyssinialaw.com

መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የዲስፒሊን ጉባኤው አመልካች በድስፒሊን ባልተከሰስኩበትና ያልተከራከርኩበትን ጉዳይ ማለትም ከዚህ በፊት ከጥብቅና ፈቃድ አወጣጥ ላይ የሀሰት ማስረጃ ተጠቅሟል ተብዬ የተከሰሰኩበትንና በቢሮ ኃላፊው ውሳኔ ያለምንም ቅጣት በነፃ የተሰናበትኩበትን ጉዳይ በመጥቀስ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የሰጠብኝ በመሆኑ ውሳኔው የመከራከር መብቴን ያጣበበና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች የጥብቅና ፈቃዴን እንዲሰርዝ የተሰጠው ውሳኔ ከህግ አግባብ ውጭ የተሰጠና የድስፒሊን ጥፋት ስለመፈጸሜ በበቂ ሁኔታ ሳይረጋገጥብኝ የተሰጠ ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት  አመልክቷል፡፡

5. የክልል ፍትህ ቢሮ በሀምሌ 15 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ መልስ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚልበትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ ቢሮው በአማራጭ ባቀረበው ክርክር አመልካች የውጭ አገር ዷሪ ለሆነ ሰው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና  አጠቃቀም አዋጅና አዋጅን ለማስፈጸም የወጣው ደንብ ከሚደነገገው የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በማሰራት በውጭ አገር ዷሪ የሆነ ሰው የባህር ዳር ዙሪያ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ የዷሪነት መታወቂያ በማውጣትና  በ2005 ዓ/ም ደንበኛው አቶ በሪሁን ወንዴ ወደ ሀገር ውስጥ ሳይገባ የሀሰት የተሚጋችነት የውክልና ሰነድ በመውሰድ እየተከራከረ በአርሶ አደሮች ላይ ከፍተኛ እንግልት ያደረሰ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ደንበኛውን በ2005 ዓ/ም ወደ አገር ውስጥ የገባ መሆኑን የማያስረዳ ማስረጃ እንዲያቀርብ በጉባኤው ብቻ ሳይሆን በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እድል ተሰጥቶት አላቀረበም፡፡ አመልካች የጥብቅና ፈቃድ ሲያወጣ ፈጽሟል ተብሎ ተከሶበት የነበረው የድስፒሊን ጥፋትና ጉባኤው አጣርቶ የደረሰበት እውነት በጉባኤው ውሳኔ ከመገለጹ ውጭ ውሳኔው የጥፋተኝነትንም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ለመወሰን ጥቅም ላይ አልዋለም ስለሆነም አመልካች ከባድ የድስፒሊን ጥፋት መፈጸሙ ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

6. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸውን እኛም የክልሉ ፍትህ ቢሮ አመልካች የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰረዝ በማለት የሰጠው ውሳኔ በህግ አግባብ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

7. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የተሚጋችነት ውክልና ወስዶ የእርሻ መሬት ይዞታን በተመለከተ የተለያየ ክርክር የሚከራከርለትና አመልካች የጥብቅና አገልግሎት የሚሰጠው አቶ በሪሁን ወንዴ በባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ዷሪ እንዳልሆነ አቶ በሪሁን ወንዴ ከሰላሳ አንድ ዓመት በላይ በቋሚነት የሚኖረው በእስራኤል አገር እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ በእስራኤል አገር የሚኖረው አቶ በሪሁን ወንዴ መተዳደሪያው የእርሻ ስራ

www.abyssinialaw.com

ሳይሆንና የቀበሌው ኗሪ ባልሆነበት ሁኔታ አቤቱታ አቅራቢው ከሰላሳ አመት በላይ በይዞታው አድርጎ ሲጠቀምበት በኖረው የእርሻ መሬት ባለይዞታ የመሆኑን የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አቤቱታ አቅርባው ሳያውቅ ያወጣ መሆኑን ገልጾ በሀሰት ለአቶ በሪሁን ወንዴ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንዲሰረዝለት አቤቱታ አቅርበው ለባህር ዳር ዙሪያ የመሬት አስተዳደርና አካባቢ ጽ/ቤት ማመልከቱንና አቶ በሪሁን ወንዴ የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የባይነሳ ሶስቱ ቀበሌ ኗሪ መሆኑን የሚያረጋግጥ የቀበሌ መታወቂያ እንዲያቀርብ ሲጠይቅ አመልካች አቶ በሪሁን ወንዴ የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ መሆኑን የሚያሳይ መታወቂያ ለወረዳው መሬት አስተዳደርና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ይዞ በመቅረብ የሰጠ መሆኑ የወረዳው የመሬት አስተዳደርና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት በሰጠው ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን የድስፒሊን ጉባኤው ከሰጠው ውሳኔ ተረድተናል፡፡

8. ከላይ በዝርዝር የተገለጸው ፍሬ ጉዳይ አመልካች ደንበኛው አቶ በሪሁን ወንዴ በእስራኤል አገር የሚኖርና የባህር ዳር ዙሪያ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ እንዳልሆነ እያወቀ አቶ በሪሁን ወንዴ የባህር ዳር ዙሪያ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ እንደሆነ የሚገልጸውን ሀሰተኛ መታወቂያ ስለ እርሻ መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ለሚሰጠውና ውሳኔ ለሚሰጠው ክፍል ወስደው ያስረከቡ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አቤቱታ አቅርበው አመልካች ከቀበሌው ስራ አስኪያጅ ጋር በመመሳጠር ሀሰተኛ መታወቂያ በበሪሁን ወንዴ ስም በማውጣት ሀሰተኛ ማስረጃ በመጠቀም ከጠበቆች ስነ ምግባር ውጭ እየተከራከረው መሆኑን ገልፆ እውነታው እንዲጣራለት ስለጠየቀ ጉባኤው አመልካች ታህሳስ 22 ቀን 2005 ዓ/ም ከአቶ በሪሁን ወንዴ ተሰጥቶኛል የሚለው የተሚጋችነት የውክልና ሰነድ ትክክለኛነት የማጣራት ስራ የስራ መሆኑን ተረድተናል፡፡ በተደረገው የማጣራት ስራ በ2005 ዓ/ም አቶ በሪሁን ወንዴ አመልካች ወደ አገር ውስጥ የገባም ሆነ የወጣ ስለመሆኑ መረጃ ያልተገኘ መሆኑ የኢምግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ መምሪያ በጽሁፍ አረጋግጧል፡፡ አመልካች ይህ ማስረጃ ደንበኛው አቶ በሪሁን ወንዴ በ2005 ዓ/ም ወደ አገር ውስጥ ያልገባ መሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ አይደለም በማለት የሚከራከር መሆኑን አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ካቀረበው የሰበር ክርክርና የሰበር ማጣሪያ ችሎት ከያዘው ጭብጥ ተረድተናል፡፡

9. የአመልካች ደንበኛ አቶ በሪሁን ወንዴ ቋሚ የመኖሪያ ቦታው እስራኤል አገር መሆኑን አመልካች ክዶ ያልተከራከረ ከመሆኑም በላይ አቶ በሪሁን ወንዴ እስራኤል አገር ኗሪ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የዲስፒሊን አቤቱታ አቅርበው አቶ በሪሁ ወንዴ በ2005 ዓ/ም ወደ አገር ቤት የመጣ መሆኑን ክዶ አልተከራከረም የሚል መከራከሪያ ከማቅረቡ ውጭ ደንበኛው በ2005 ዓ/ም ወደ አገር ውስጥ የገባ ወይም ከአገር የወጣ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ለጉባኤውና ለይ/ባይ ሰሚ ችሎት ያላቀረበ መሆኑን የክልሉ ፍትህ ቢሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡትን ውሳኔ በማገናዘብ

www.abyssinialaw.com

ተረድተናል፡፡ በመሰረቱ አመልካች የዲስፒሊን አቤቱታ አቅራቢው አቶ ኀድይሁን አዘዘው የአመልካች ደንበኛ በ2005 ዓ/ም ወደ አገር ቤት የመጣ መሆኑን ባቀረበው አቤቱታ ላይ እንዳልካደ በመግለጽ ያቀረበው ክርክር አቤቱታ አቅርበው የካቲት 3 ቀን 2006 ዓ/ም ጽፎ ያቀረበውን ፍሬ ጉዳይና የገለጸውን እምነት የሚሳይ ክርክር ሆኖ አላገኘነውም፡፡

10. የዲስፒሊን አቤቱታ አቅራቢው አቶ በሪሁን ወንዴ ወደ አገር ቤት የመጣ ስለመሆኑ በአቤቱታው አልገለጸም፡፡ አቤቱታ አቅራቢው አቶ በሪሁን ወንዴ በእስራኤል አገር እንደሚኖርና አንድ ወቅት ወደ አገር ቤት መጥቶ እንደነበር ወደ አገር ቤት በመጣበትም ጊዜ ከህግ ውጭ እሱ በማያውቀው ሁኔታ ከሰላሳ አምስት ዓመት በላይ በእጅ አድርጎ የሚጠቀምበትን የእርሻ መሬት የአቶ በሪሁን ወንዴ መሆኑን የማያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያስመጣበት መሆኑን የይዞታ ደብተሩ እንዲሰረዝለት ለሚመለከተው አካል ሲያመለክት አመልካች በእስራኤል አገር የሚኖረው በሪሁን ወንዴ የባህር ዳር ዙሪያ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ መሆኑን የሚገለጽ ሀሰተኛ መታወቂያ በማስወጣትና ሀሰተኛ ማስረጃ በመጠቀም እየተከራከረው በመሆኑን በዲስፒሊን ጉዳይ እንዲታይ የሚገልጽ ነው፡፡ አቶ በሪሁን ወንዴ አመልካች ሀሰተኛ መታወቂያና ሀሰተኛ የተሚጋችነት ውክልና አምጥቷል ከተባለበት ጊዜ በፊት በአንድ ወቅት ወደ አገር ቤት መጥቶ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ነዋሪ መሆኑን የሚያሳይ መታወቂያ እንዲሰጠው የቀበሌውን አስተዳዳሪ ጠይቆ የነበረ መሆኑንና የቀበሌው አስተዳደርም መታወቂያው አይሰጥህም የሚል ምላሽ እንደሰጠው የዲስፒሊን ጉባኤው ከቀበሌው አስተዳደር ጋር ባደረገው ማጣራት እንዳረጋገጠ በውሣኔው በግልፅ አስፍሯል፡፡ አቤቱታ አቅራቢው አቶ በሪሁን ወንዴ በአንድ ወቅት ወደ አገር ቤት መጥቶ የነበረ መሆኑን ባቀረበው አቤቱታ መግለፁ አቶ በሪሁን ወንዴ በ2005 ዓ.ም ወደ አገር ቤት የመጣ መሆኑን በአቤቱታው ያመነና የገለፀ መሆኑን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አቤቱታ አቅራቢው አቶ በሪሁን ወንዴ ለዲስፒሊን ክስ መነሻ የሆኑት ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ወደ አገር ቤት መጥቶ የነበረ መሆኑ በአቤቱታው ላይ የገለፀው ፍሬ ጉዳይ ዕውነትነት ያለው መሆኑን በቀበሌው አስተዳደርም የተረጋገጠ መሆኑ ሲታይ አቤቱታ አቅራቢው በአቤቱታው ላይ ትክክለኛውን ፍሬ ጉዳይ ያሰፈረ መሆኑን ከሚያረጋግጥ ውጭ አቶ በሪሁን ወንዴ በ2005 ዓ.ም ወደ አገር ቤት የመጣ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ መከራከሪያና ሰነድ አይደለም፡፡

11. የዲስፒሊን አቤቱታ አቅራቢው የዲስፒሊን ክስ ዋና ይዘት አመልካች በባህር ዳር ዙሪያ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ነዋሪ ላልሆነው አቶ በሪሁን ወንዴ የቀበሌው ነዋሪ መሆኑን የሚያረግጥ መታወቂያ በማውጣት ሀሰተኛ የውክልና ሰነድ በመጠቀም እየተሟገተኝ ነው የሚል ነው፡፡ አመልካች ከአቶ በሪሁን ወንዴ የተሚጋችነት የውክልና ሥልጣን ተሰጥቶኛል የሚለው ታህሣሥ 22 ቀን 2005 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች የተሚጋችነት ውክልና ሰጥቶኛል

www.abyssinialaw.com

የሚለው በሪሁን ወንዴ በ2005 ዓ.ም ወደ አገር ውስጥ የገባ መሆኑን በጭብጥነት ይዞ ጉባኤው ማጣራቱ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አቶ በሪሁን ወንዴ በ2005 ዓ.ም ወደ አገር ውስጥ የገባና ከአገር የወጣ መሆኑ አከራካሪ ጭብጥ ከሆነ ስለ ጉዳዩ መረጃ የመያዝና መረጃ የመስጠት ሥልጣን ያለው አካል መጠየቁ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡

12. አንድ ሰው ወደ አገር ውስጥ ስለመግባቱና ከአገር ስለመውጣቱ ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርገውና ወደ አገር ውስጥ የሚገባም ሆነ ከአገር የሚወጣ ሰው ማሟላት የሚገባውን ሥርዓት ያሟላና የጉዞ ሰነዶችን የያዘ መሆኑን የማረጋገጥ ሥልጣን ያለው የደህንነት የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን መሆኑን በኢሚግሬሽን አዋጅ ቁጥር 354/95 ተደንግጓል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 354/95 አንቀፅ 16 ባለሥልጣኑ የኢሚግሬሽን ኦፊሰሮችን በመመደብ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡትንም ሆነ ከአገር የሚወጡ ሰዎች መንገደኞች የሚከታተልና መረጃ የሚይዝ ስለመሆኑ በውጭ አገር የሚኖር ሰው ወደ አገር ውስጥ ሲገባም ሆነ ሲወጣ አስፈላጊ የጉዞ ሰነዶች የያዘ መሆኑንና ከአገር ሲወጣ ሊይዘው የሚገባውን ማናቸውንም መረጃ እንደሚይዝ ከድንጋጌው ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከውጭ አገር ወደ አገር ቤት አንድ ሰው ተጓጉዞ ሲመጣና ሲወጣ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ወይም ከኢትዮጵያ የሚወጡ መንገደኞችን ያሣፈረ ማናቸውም ማጓጓዣ የመንገደኖችን ስም ዝርዝር የያዘ ሰነድ ለሚመለከተው የኢሚግሬሽን ኦፊሰር የመስጠት ግዴታ ያለበት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 354/95 አንቀጽ 17 ተደንግጓል፡፡

13. ከዚህ አንፃር ሲታይ የአመልካች ደንበኛ አቶ በሪሁን ወንዴ በ2005 ኢ.ም ወደ አገር ውስጥ ስለመግባቱም ሆነ ስለመውጣቱ የተገኘ መረጃ የሌለ መሆኑን ገልፆ የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ መምሪያ ለዲስፒሊን ጉባኤው የሰጠው መግለጫ በአዋጅ ቁጥር 354/95 በሚደነግገው መሠረት የአመልካች ደንበኛ በ2005 ዓ.ም ወደ አገር ውስጥ በህጋዊ መንገድ የገባ ስለመሆኑ ማስረጃ የሌለ መሆኑን የሚሳይ ነው፡፡ የአመልካች ደንበኛ በአዋጅ የተደነገጉትን መስፈርቶች በማሟላት በ2005 ዓ.ም ወደ አገር ውስጥ የገባና ከአገር የወጣ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አለመኖሩ በራሱ የአመልካች ደንበኛ ከአገር የወጣ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አለመኖሩ በራሱ የአመልካች ደንበኛ በ2005 ዓ.ም በህጋዊ መንገድ ወደ አገር ውስጥ አልገባም ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ማስረጃ ነው፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች ደንበኛው በ2005 ዓ.ም በህጋዊ መንገድ ወደ አገር ውስጥ የገባና ከአገር የወጣ መሆኑን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በማቅረብ ወይም አመልካች ደንበኛው ህጋዊ መስፈርቶችን ሣያሟላ በህገ ወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ የገባና ከአገር የወጣ መሆኑን የሚሳይ ማስረጃ በማቅረብ ያቀረበበትን ማስረጃ ካላስተባበለ አቶ በሪሁን ወንዴ በ2005 ዓ.ም አገር ውስጥ አልነበረም፡፡ አመልካች ታህሣሥ 22 ቀን 2005 ዓ.ም ከፍትህ ቢሮ የወሰደው የተሟጋችነት የውክልና ሰነድ አመልካች አቶ በሪሁን ወንዴ የባህርዳር ከተማ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ ስለመሆኑ የሚገልፀውን ሀሰተኛ

www.abyssinialaw.com

መታወቂያ በመጠቀምና ሌላውን ሰው በሪሁን ወንዴ አስመስሎ በማቅረብ የወሰደው ሀሰተኛ የውክልና ማስረጃ ነው በማለት የዲስፒሊን ጉባኤው የደረሰበትን የማስረጃና የፍሬ ጉዳይ መደምደሚያ ለመቃወም የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሠረት የሌለው መሆኑን የሚሳይ ነው፡፡

14. አመልካች ደንበኛው በ2005 ዓ.ም ህጋዊ መስፈርቶችን በማሟላት ወይም ከህግ አግባብ ውጭ ድንበር ጥሶ ወደ አገር ቤት መጥቶ የነበረ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ደንበኛው በ2005 ዓ.ም ወደ አገር የገባና ከአገር የወጣ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ካለው ማስረጃውን እንዲያቀርብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 345 መሠረት እድል ሰጥቶት አመልካች ማስረጃውን ሊያቀርብ ያልቻለ መሆኑን በውሣኔው በግልፅ አስፍሯል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የክልሉ ፍትህ ቢሮ አመልካች ደንበኛው በሪሁን ወንዴ በእስራኤል አገር ኗሪ መሆኑን እያወቀ በሪሁን ወንዴ የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ መሆኑን የሚገልፀውን የሀሰት መታወቂያ መጠቀሙንና የሀሰት የተሚጋችነት የውክልና ሰነድ በመያዝ ክርክር እያቀረበ መሆኑን ገልፆ አመልካች በክልሉ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ ምዝገባና የጠበቆችን ሥነ ምግባር ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 75/1994 የሚጥስ ከባድ የዲስፒሊን ጥፋት ፈፅሟል በማለት የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰበር ችሎት በማፅናታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

15. አመልካች የዲስፒሊን ጉባኤው ከዚህ በፊት ተከሳሽ በቢሮ ኃላፊው ውሣኔ በነፃ የተሰናበተበትን ጉዳይ በውሣኔ ውስጥ መግለፁን ምክንያት በማድረግ ባልተከሰሰኩበት ጉዳይ ጥፋተኛ ተብዬ ተቀጥቻለሁ የሚል የሰበር መከራከሪያ አቅርቧል፡፡ በእርግጥ ጉባኤው በአብላጫ ድምፅ በሰጠው ውሣኔ አመልካች የክልሉ 2ኛ ና 1ኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ ሲያወጣ አግባብነት የሌለው የሥራ ልምድ ተጠቅሟል የሚል የዲስፒሊን ክስ ቀርቦበትና ሁኔታው ተጣርቶ አመልካች የጥብቅና ፈቅድ የወሰደው አግባብነት የሌለው የሥራ ልምድ መሆኑን ተረጋግጦበት እንደነበርና የቢሮ ኃላፊው ቀደም ብለው በነበሩት የቢሮው አመራሮች ተምኖበት የተሰጠው መሆኑንና ፈቃዱ ቢሰርዝ ለአመልካች ላይ የሚደርሰው ማህበራዊ እና ቤተሠባዊ ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣት ሣይወሰንበት የቀረ መሆኑን በውሣኔው ገልፆል፡፡ የልዩነት ሀሳብ ይኸ ሀሳብ በዲስፒሊን ውሳኔ ላይ መፃፉ ተገቢ አይደለም በሚል ምክንያት የተፃፈ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

16. የዲስፒሊን ጉባኤው የአመልካች ማህደር ሲመረምር ከማህደሩ ጋር ተያይዞ ያገኘውን ፍሬ ጉዳይ በውሣኔው ውስጥ መግለፅ በክልሉ አዋጅ ቁጥር 75/1994 የተከለከለ ተግባር ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአንፃሩ የዲስፒሊን ጉባኤው አመልካች ማህበር ጋር ተያይዞ የሚገኘውን የሥነ ምግባር ሁኔታ መግለፁ በአዋጅ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 5 ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ

ሲገኝ በጠበቃው ላይ የሚጣለውን ቅጣት በመወሰን የወንጀል ሪከርድ የጠበቃውን የግል ማህደር ወይም ሌላ ተመሣሣይ ማስረጃ የማስቀረብ የማሰማትና የመመርመር ሥልጣን የተጠቀመ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጉባኤው በአመልካች ማህደር ተያይዞ ያገኘውን ፍሬ ጉዳይ በውሣኔው ከመግለፁ ውጭ ይህን ፍሬ ጉዳይ ቅጣቱን አቅልሎም ሆነ አክብዶ ለመወሰን ያልተጠቀመበት መሆኑን ከውሣኔው ተረድተናል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ጉባኤው ማህደሩን ሲመረምር ያገኘውን ግኝት በውሣኔው ውስጥ መግለፁ መሠረታዊ የህግ ስህተት እንደሆነ በመግለፅ ያቀረበው አቤቱታ የአዋጅ ቁጥር 75/94 አንቀጽ 21 ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

17. አመልካች በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4፣ የፌዴራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 456/97 በክልሉ መሬት አስተዳደር አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 እና በደንብ ቁጥር 51/99 መሠረት የገጠር የእርሻ መሬት ይዞታ በስጦታም ሆነ በውርስ የማግኘት መብት የሌለው በእስራኤል አገር ነዋሪ የሆነውን አቶ በሪሁን ወንዴ የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ነዋሪ እንደሆነ ተደርጎ በሀሰት ተዘጋጅቶ የተሰጠውን መታወቂያ እያወቀ ለባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የመሬት አስተዳደርና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ያቀረበና ይህንኑ መታወቂያ በመጠቀም አቶ በሪሁን ወንዴ ወደ አገር ውስጥ ባልገባበት በአገር ውስጥ በሌለበት ታህሣሥ 22 ቀን 2005 ዓ.ም የሀሰት የተሚጋችነት ውክልና በማውጣት አቤቱታ አቅራቢውንና ሌሎች አርሶ አደሮችን በመክሰስ ከፍተኛ እንግልት ያስከተለና ዕውነት እንዳይወጣና ፍትህ እንዲዛባ የሚደርግ ጥፋት የፈፀመ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የክልሉ ፍትህ ቢሮ የጠበቆች የዲስፒሊን ጉባኤና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተረጋግጧል፡፡

18. አመልካች የፈፀመው የዲስፒሊን ጥፋት እጅግ ከባድና በአዋጅ ቁጥር 75/1994 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2(መ) እና በሌሎች አግባብነት ያላቸውን የአዋጁን ድንጋጌዎች የጣሰ አመልካች ሕግን የማስከበር ፍትህን የማስገኘትና ለፍትህ አስተዳደሩ የማገዝ ኃላፊነቱን ወደ ጎን በመተው ተቃራኒ የሆነ ተግባር የፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ይኸም በመሆኑ አመልካች ላጠፋው ከባድ የዲስፒሊን ጥፋት የጥብቅና ፈቃዱ እንዲሰረዝ በማለት የክልሉ ፍትህ ቢሮ የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ማፅናታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሳ ኔ**

1. የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ የጠበቆች የዲስፒሊን ጉባኤና የቢሮ ኃላፊ የሰጠው ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 38431 የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 49403 የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 124618

ሕዳር 22 ቀን 2009 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አልማው ወሌ

2. ሙስጠፋ አህመድ

3. አብርሃ መሰለ

4. አብዬ ካሳሁን

5. እትመት አሰፋ

አመልካች፡-

1. ወ/ሮ ድባካ መሰለ - ቀረቡ
2. ሀብቱ ሞገስ - ሞግዚት ወ/ሮ ድባካ መሰለ - ቀረቡ
3. የሽወርቅ ሞገስ - ሞግዚት ወ/ሮ ድባካ መሰለ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሳጅን ኃይሉ ሞገስ - የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈጻጸምን የሚመለከት ክርክር ሲሆን አመልካቾቹ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡትም ለፍርድ አፈጻጸሙ ምክንያት የሆነው መኖሪያ ቤት ክፍፍል መፈጸም የሚገባው በሀራጅ ተሸጦ ነው በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍርድ በማጽናት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0311349 በ16/06/2008 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ፡- የ1ኛ አመልካች ባለቤት የነበሩት አቶ ሞገስ ጌታሁን በሞት መለየታቸውን ተከትሎ በተነሳው የውርስ እና የጋራ ንብረት ክፍያ ክርክር በዋግኽምራ ዞን በሰቆጣ ከተማ በቀበሌ 02 ክልል በሟች ስም ተመዝግቦ ይታወቅ ከነበረው ቤት ውስጥ ግማሹ የአሁኗ 1ኛ አመልካች ድርሻ ሆኖ ቀሪው ግማሽ ደግሞ ከሟች ለሚወለዱት ሰባት ልጆች እንዲከፋፈል ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፣ ይህንን የስረ ነገር ፍርድ ለማስፈጸም 1ኛ አመልካች በፍርድ ባለመብትነት ተሰይመው ባደረጉት እንቅስቃሴ በከተማው አስተዳደር በቀረበው የዋጋ ግምት መሰረት የቀሪዎቹን ወራሾች ድርሻ 1ኛ አመልካች ከፍለው እና ከወራሾቹ መካከል የአሁኑ

www.abyssinialaw.com

ተጠሪ ቤቱ በጨረታ መሸጥ ከሚገባው በቀር ግምቱን ለመቀበል አልስማማም በማለታቸው ድርሻቸው በሞዴል 85 እንዲያዝ ተደርጎ የቤቱ ስመሀብት አፈጻጸሙን በያዘው የሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወደ 1ኛ አመልካች የተዛወረ መሆኑን፣ 1ኛ ተጠሪ በዚህ ትዕዛዝ ባለመስማማት በየደረጃው ያቀረቡት ክርክር በመጨረሻ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ፍርድ ቤቶችን የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሽሮ ቤቱ ከተቻለ በዓይነት፣ ካልተቻለ ግራ ቀኙ እርስ በእርስ በሚያደርጉት ጨረታ፣ ይህም ካልተቻለ ለ3ኛ ወገን በጨረታ እንዲሸጥ በመዝገብ ቁጥር 03-08523 በ26/04/2007 ዓ.ም. ውሳኔ የሰጠ መሆኑን፣ የወረዳው ፍርድ ቤትም በዚሁ አግባብ ቤቱ በጨረታ እንዲሸጥ ለማስቻል የጨረታ ማስታወቂያ እንዲወጣ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን፣በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት 1ኛ አመልካች ያቀረቡት ይግባኝ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 010913 በ02/10/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የተዘጋ እና አቤቱታቸውም በክልሉ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0311349 በ16/06/2008 ዓ.ም. በተሰጠ በፍርድ ተቀባይነት ያጣ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካቾች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾቹ በአከራካሪው ቤት ላይ ያላቸው የጋራ ድርሻ በጣም ብዙ ሆኖ እያለ እና የተጠሪው ድርሻ ግን በድርሻቸው ብቻ የታጠረ ሆኖ እያለ፣ ይህንኑ ከግምት በማስገባትም 1ኛ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ በቀር ለቀሪው እያንዳንዱ ወራሽ ግምቱን ከፍለው ቤቱን በስማቸው አዛውረው እያለ የአሁኑ ተጠሪ ግምቱን ለመቀበል ባለመስማማታቸው ብቻ ቤቱ በሀራጅ እንዲሸጥ የመታዘዙን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. በስረ ነገሩ ፍርድ መሰረት ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ በቤቱ ላይ የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ እንዲወጣ በወረዳው ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?
2. አመልካቾቹ ከአከራካሪው ቤት ላይ አለን የሚሉትን አብላጫ ድርሻ መሰረት በማድረግ ቤቱን ማስቀረት የሚችሉበት የሕግ አግባብ አለ ወይስ የለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ 1ኛ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ከአከራካሪው ቤት በሚስትነታቸው ያላቸው ድርሻ ግማሽ ሆኖ እያለ እና የሰባት ወራሾች ድርሻ ከሆነው የቤቱ

www.abyssinialaw.com

አጋማሽ ውስጥ ደግሞ 1ኛ አመልካች ሞግዚት የሆኗቸው 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች እያንዳንዳቸው አንድ ሰባተኛ ድርሻ ያላቸው ሆኖ እያለ እንዲሁም ከተጠሪው ውጪ ላሉት ቀሪ ወራሾች 1ኛ አመልካች ድርሻቸውን ከፍለው እያለ ከቤቱ አጋማሽ ውስጥ አንድ ሰባተኛ ድርሻ ብቻ ላላቸው የአሁኑ ተጠሪ ጥቅም ብቻ ሲባል ወደ 1ኛ አመልካች ስም ተዛውሮ የነበረው ቤት በሀራጅ እንዲሸጥ የተሰጠው ትዕዛዝ ፍትሐዊ አይደለም የሚል መሆኑን የአቤቱታቸው ይዘት ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ የክልሉ ሰበር ችሎት የአፈጻጸም ሂደቱን አስመልክቶ ቀደም ሲል ቤቱ ከተቻለ በዓይነት፣ ካልተቻለ ግራ ቀኙ በመካከላቸው በሚያደርጉት ጨረታ፣ ይህም ካልተቻለ ደግሞ ለ3ኛ ወገን በጨረታ እንዲሸጥ በመዝገብ ቁጥር 03-08523 በ26/04/2007 ዓ.ም. ውሳኔ የሰጠው 1ኛ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ ውጪ ላሉት ሌሎች ወራሾች ድርሻቸውን ሰጥተው ቤቱን በስማቸው ካዛወሩ በኋላ በመሆኑ የተጠሪው ድርሻ ከቤቱ አጋማሽ ውስጥ አንድ ሰባተኛ ብቻ ሆኖ እያለ ቤቱ በሐራጅ ይሸጥ መባሉ ተገቢ አይደለም የሚሉ ከሆነ የሰበር አቤቱታቸውን በወቅቱ በስርዓቱ መሰረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው ተገቢውን ውሳኔ ማስጠት ይገባቸው የነበረ ከመሆኑ በቀር በክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረት ጉዳዩ ወደ ወረዳው ፍርድ ቤት ተመልሶ የአፈጻጸም ሂደቱ ከቀጠለ በኃላ ወደኋላ ተመልሰው ቤቱ በሀራጅ እንዲሸጥ የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ፍትሀዊ አይደለም በማለት አሁን እያቀረቡ ያሉት ክርክር ስነ ስርዓታዊ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም አፈጻጸሙን የያዘው የሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ቀደም ሲል በክልሉ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-08523 በ26/04/2007 ዓ.ም. የሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ በስረ ነገሩ ፍርድ መሰረት ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ በቤቱ ላይ የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ እንዲወጣ የሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ከአከራካሪው ቤት 1ኛ አመልካች ግማሽ ድርሻ፣2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ደግሞ ከቤቱ አጋማሽ ውስጥ እያንዳንዳቸው አንድ ሰባተኛ ድርሻ ያላቸው መሆኑ አላከራከረም፡፡ ይህም 1ኛ አመልካችም ሆኑ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ከቀሪዎቹ ወራሾች ጋር የአከራካሪው ቤት የጋራ ባለሀብቶች መሆናቸውን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ተይዞ የሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በሕብረት የያዙት እና ያልተከፋፈሉት በሆነ ጊዜ ከተካፋዮቹ አንዱ ንብረቱን ለመግዛት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኖ የቀረበ እንደሆነ የፍርድ ባለዕዳው እንደቀረበ ተቆጥሮ የተቀዳሚነት መብት የሚሰጠው ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 443 ይደነግጋል፡፡ ከስነ ስርዓት ሕጉ በተጨማሪም የጋራ ባለሀብቶች የሆኑ ሰዎች ያልተከፋፈለውን የጋራ ንብረት ከማንኛውም ሶስተኛ ወገን በፊት ቀዳሚ ሆነው በግዥ የማስቀረት ሕጋዊ መብት ያላቸው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1261 (1) የተደነገገ ሲሆን ይህ መብት ተግባራዊ የሚደረግበት ስርዓትም በዚሁ ሕግ

www.abyssinialaw.com

ከቁጥር 1386 እስከ 1409 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በመሆኑም አመልካቾቹ አከራካሪውን ቤት ለማስቀረት የሚችሉት በቤቱ ላይ በሚከናወነው ጨረታ መሰረት ከፍተኛ ዋጋ በማቅረብ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ጨረታውን ያሸነፈበትን ዋጋ መሰረት በማድረግ ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች በተጠበቀላቸው የቀዳሚነት መብት በመገልገል ነው፡፡ በቀጣይ የአፈጻጸሙ ሂደት አመልካቾቹ ከፍተኛ ዋጋ በማቅረብ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ጨረታውን ያሸነፈበትን ዋጋ መሰረት በማድረግ የቀዳሚነት መብታቸውን ተግባራዊ የሚያደርጉ ከሆነ በሰበር አቤቱታቸው እንደሚከራከሩት ከአሁኑ ተጠሪ ውጪ ላሉት ሌሎች ወራሾች ድርሻቸውን ከፍለው በቤቱ ላይ ያላቸውን ድርሻ ከፍ ያደረጉ መሆን አለመሆኑ፣ ጨረታውን ካሸነፉበት የዋጋ መጠን ውስጥ የራሳቸው ድርሻ ተቀንሶ ገቢ ማድረግ የሚገባቸው የገንዘብ መጠን ምን ያህል እንደሆነ እና መሰል የአፈጻጸም ጉዳዮች ፍርዱን በሚያስፈጽመው ፍርድ ቤት ተስተናግደው ተገቢው ትዕዛዝ የሚሰጥባቸው ይሆናል፡፡

ሲጠቃለል አመልካቾቹ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 443 እንዲሁም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1261 (1)፣ 1386 እስከ 1409 በተደነገገው የቀዳሚነት መብታቸው የመገልገል መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ አከራካሪው ቤት በሀራጅ እንዲሸጥ በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በዋግኽምራ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0101913 በ02/10/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍርድ በማጽናት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0311349 በ16/06/2008 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የስረ ነገሩ ፍርድ ያረፈበት ቤት በሀራጅ ይሸጥ መባሉ በአግባቡ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አከራካሪው ቤት በሀራጅ በሚሸጥበት ጊዜ አመልካቾቹ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 443፣ እንዲሁም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1261 (1)፣ 1386 እስከ 1409 በተደነገገው የቀዳሚነት መብት የመገልገል መብት አላቸው በማለት ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

4. እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት፣ ለዋግኽምራ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
5. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0311349 በ16/06/2008 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ06/07/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ